# የአማርኛ ሰዋስው

## የተሻሻለ ሁለተኛ እትም

ለዶ/ር ኡንሬት
ከመልካም ምኞት ጋር
ባዬ ይማም
መጋቢት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

ባየ ይማም

© የደራሲው መብት በህግ የተከበረ ነው

የመጀመሪያ እትም 1987
የተሻሻለ ሁለተኛ እትም 2000

ISBN 978 – 99944 – 999 – 8 - 4

ባዩ ይማም

መታሰቢያነቱ፣

ለይማም መኩንን አግደው

ካልቸር ኤንድ አርት ሶሳይቲ ኦፍ ኢትዮጵያ (ኬዝ) በባህልና ጥበብ ሙያዎች ውስጥ ባሉ ሰዎች የተመሰረተ መንግስታዊ ያልሆነ ማሕበር ነው።

የሶሳይቲው አላማ የኢትዮጵያን ሰፊ የባሕልና የልዩ ልዩ ጥበባት ሃብት፣ የሕዝቦቿን ነባር ልማዶች፣ ሀገር በቀል እውቀት፣ አመለካከት፣ ማህበራዊ አስተዳደር፣ የተፈጥሮ ሃብትና ይህን ሃብት በመልካም ሁኔታ ለመጠበቅና ለመንከባከብ ያሏቸውን ጥበብና ዘዴዎች፣ በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የኛ ናቸው የሚሏቸውን የእውቀት፣ የባሕልና የጥበብ ሃብት በመንከባከብ፣ በማልማትና ዘላቂነታቸው እንዳይደናቀፍ በማድረግ ረገድ ጠቃሚ የሆነ አስተዋፅኦ ለማበርከት ነው።

ይህን አላማ ለማሳካት ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አንዱ ሀገርኛ የሆኑ ባህሎችና ኪነጥበባዊ ክዋኔዎች እንዲበለፅጉና እንዲከበሩ የሚረዱ ስራዎችን ማገዝ ነው። ይህን የአማርኛ ስዋስው መጽሐፍ የማሳተሙን ስራ ለመደገፍ ሲወስንም የቋንቋው ተናጋሪ ህዝብ ባህል ህያው ሆኖ ለተከታይ ትውልድ እንዲሸጋገር ይረዳል በሚል እምነት ነው።

ዋና መስሪያ ቤቱ በዩናይትድ ስቴትስ ካሊፎርኒያ የሚገኘውና የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ነባር እውቀትና ባህላዊ ህይወት በመደገፍ ላይ የሚገኘው «ዘ ክሪስተንሰን ፈንድ» ድርጅት ኬዝ በልዩ ልዩ መስኮች ለሚያደርጋቸው ጥረቶች ያልተቋረጠ እገዛ በመስጠት ላይ ነው። የአገራችን ማህበረሰቦች የተፈጥሮአዊ አካባቢ ብዝሀ ህይወትን ዘለቄታዊ ጠቀሜታ እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ያሏቸውን ልማዳዊ የአስተዳደር ብልሃት ተንከባክቦ ለማቆየት መጠነ ሰፊ እርዳታም ያደርጋል። ድርጅቱ የዚህን መጽሐፍ የእርትኦትና የሕትመት ሙሉ ወጪ በመደገፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓልና በዚህ አጋጣሚ ምስጋናችንን ልናቀርብ እንወዳለን።

እንዲሁም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለበርካታ አመታት ምርምር በማካሄድ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባስተማሩባቸው አያሌ አመታት በመስኩ በርካታ ምሁራንን በማፍራት ለአገራቸውና ለአለም የላቀ አገልግሎት ላበረከቱትና ዛሬም ይህንን ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለውንና እጅጉን አድካሚ የሆነውን መጽሐፍ ላዘጋጁት ለፕሮፌሰር ባዬ ይማም፣ ከርሳቸው ጋርም ባህላዊና ስነልሳናዊ እውቀታቸውን በማካፈል ለመጽሐፉ ዝግጅት ትልቅ ድርሻ ለነበራቸው የቋንቋው ተናጋሪዎችና የባህል አዋቂዎች ሁሉ ካልቸር ኤንድ አርት ሶሳይቲ ኦፍ ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ምስጋና ያቀርባል።

ይህ የአማርኛ ሰዋስው መጽሐፍ በአማርኛ ቋንቋም ሆነ በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለሚያደረጉ ምርምሮችና ተከታታይ ጥናቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረውና ለሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችም አርአያ ሊሆን እንደሚችል ተስፋችን የላቀ ነው።

ካልቸር ኤንድ አርት ሶሳይቲ ኦፍ ኢትዮጵያ (ኬዝ)

ጥቅምት 2000፣አዲስ አበባ

# ማውጫ


ምህፃረ-ቃል viii
ምስጋና x
መቅድም xi
መግቢያ xvii

## ምዕራፍ አንድ 1

### ስነ-ድምፅ 1

መግቢያ 1
ተናባቢ 2
- እግድ 7
- ፍትግ 8
- ፍግድ 9
- ስርናዊ 10
- ጎናዊ 10
- ክፍናቢ 11

አናባቢ 13
ፎኒም 17

### አቀነጃጀት 20

ቀለም 23

### ድምፀ ልሳናዊ ሂደት 27

ምስለት 29
- ከናፍራዊነት 30
- ከፊል ላንቃዊነት 33
- ሙሉ ላንቃዊነት 35
- ትናጋዊነት 37
- ማንቁርታዊነት 38
- ክበት 39
- ድምፀት 40
- ኢድምፀት 42
- ግድፈት 44
- ጥብቀት 54
- ልለት 56

ኢምስለት 58
ስርገት 59
ቅየራ 65

ቅፅላዊ ሀረግ 273
ስማዊ ቅፅል 274
ግሳዊ ቅፅል 276
ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ 279
መስተዋድዳዊ ሀረግ 284
መስተዓምራዊ ሀረግ 292

አረፍተ ነገር 304
የአረፍተ ነገር አይነቶች 307

ተራ አረፍተ ነገር 312
ሀተታዊ አረፍተ ነገር 318
ሁነታዊ አረፍተ ነገር 319
ገቢር አረፍተ ነገር 323
ተገብሮአዊ አረፍተ ነገር 335
መጠይቃዊ አረፍተ ነገር 340
አሉታዊ አረፍተ ነገር 348
ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር 361

ውስብስብ አረፍተ ነገር 368
ውስብስብ ሀተታዊ አረፍተ ነገር 369
ውስብስብ ስማዊ ሀረግ 369
መሙሊያ አረፍተ ነገር 369
አዛማጅ አረፍተ ነገር 374
ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ 385
ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ 408
ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረግ 416
ውስብስብ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር 420

ሙዳየ ቃላት 448

ዋቢ መፃህፍት 458

# ምህፃረ ቃል


| | | |
|---|---|---|
| 273 | ሀ | ሀረግ |
| 274 | ሁዋ | ሁዋለኛ |
| 276 | ሳ | ሳየኛ |
| 279 | ል | ልከኛ |
| 284 | ታ | ታቸኛ |
| 292 | መ | መሀለኛ |
| 304 | መሙ | መሙሊያ |
| 307 | መስ | መስተዋድድ |
| | መስተ | መስተዓምር |
| | ማ | ማእከል |
| 312 | ማንቅ | ማንቁርት |
| 318 | ም | ምስሶ |
| 319 | ስ | ስርን |
| 323 | ስ | ስም |
| 335 | ስሀ | ስማዊ ሀረግ |
| 340 | ባ | ባሀሪ |
| 348 | ተ | ተናባቢ |
| 361 | ተግ | ተውሳከ ግስ |
| | ተግሀ | ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ . |
| 368 | ቅ | ቅፅል |
| 368 | ቅሀ | ቅፅላዊ ሀረግ |
| 369 | ቅጣ | ቅጣይ |
| 369 | ንሀ | ንኡስ ሀረግ |
| 374 | (ኢ)ነ | (ኢ)ነዛሪ |
| 385 | ከ | ከፉች |
| 408 | አ | አናባቢ |
| 416 | አነ | አረፍተ ነገር |
| 420 | አን | አንስታይ |
| | አኅ | አኅሳማሽ |
| 448 | ድ | ድድ |
| | ግ | ግስ |
| | ግሀ | ግሳዊ ሀረግ |
| 458 | ፊ | ፊተኛ |
| | ጨ | ጨራሽ |

# ልዩ ምልክቶችና ፊደሎች

| | |
|---|---|
| [ ] | በድምፅ ደረጃ ንበታዊ አፃፃፍን፣ በሀረግ ደረጃ መዋቅራዊ አንድነትን ያሳያል፡፡ |
| / / | ፎኒማዊ አፃፃፍን ያመለክታል፡፡ |
| * | በአረፍተ ነገር መነሻ ላይ ሲገኝ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያመለክታል። |
| ? | ተቀባይነቱ አጠራጣሪ የሆነ አባባልን ያመለክታል፡፡ |
| ብ [β] | አበባ ስንል የምንሰማውን ልል ወይም ፍትግ "ብ" ይወክላል፡፡ |
| ም [ɱ] | ከምፈር ስንል የምንሰማውን የከንፈርና የጥርስ የሆነ ውሁድ ድምፅን ይወክላል፡፡ |
| ን [ŋ] | አንገት ስንል የምንሰማውን የትናጋ "ን" ይወክላል፡፡ |

# መቅድም

ቋንቋዋ ሁለት የተያያዙ ዋና ዋና ተግባራት አሉት፡፡ አንደኛው ሀሳብን ማስተላለፍ ሲሆን፣ ሁለተኛውና የዚሁ ነፀብራቅ የሆነው ማንነትን ማመልከት ነው፡፡ የመጀመሪያውን ስነ-ልሳናዊ፣ ሁለተኛውን ማህበራዊ ተግባር ልንለው እንችላለን፡፡ ከዚህ አንፃር ማንኛውም ሰው ስለ አንድ ጉዳይ ሲናገር፣ የሚያስተላልፈው መልዕክት ሁለት ነው፡፡ አንደኛው፣ በቀጥታ ስለ ጉዳዩ የሚሰጠው አስተያየት ሲሆን፣ ሁለተኛውና ከዚህ የሚሰርፀው፣ ይህንን ሀሳብ በሚያስተላልፍበት ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ ባድማጩ ላይ ስለራሱ ማንነት የሚያሳድረው ግምት ነው፡፡ ስለዚህም ንግግሩ ብሉም ቋንቋዋው የሀሳቡ ብቻ ሳይሆን፣ የማንነቱም መግለጫ ነው፡፡

"ካነጋገር ይፈረዳል ካያያዝ ይቀደዳል" የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ከዚህ ላይ ሲጠቀስ ይችላል፡፡ አንድ በቴፕ የተቀረፀን ንግግር በመስማት፣ ከንግግሩ ፍሬ ሀሳብ፣ ካነጋገሩ ለዛ፣ ማለትም ከቃላት አመራረጡ፣ ከድምፅ አወራረዱ፣ ወዘተ፣ ስለ ተናጋሪው አንዳንድ ነገሮችን ከሞላ ጎደል በትክክል መናገር ይቻላል፡፡ ይኸውም ተናጋሪው ገጠሬ ወይም ከተሜ፣ ወጣት ወይም ሽማግሌ፣ ሴት ወይም ወንድ፣ ገበሬ ወይም ነጋዴ፣ ወዘተ፣ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በመለየት ነው፡፡ ከዚህም አልፈን፣ አንዳንድ ጊዜ "ይኸማ አገሬ አይደለም አንዴ!" እስከ ማለት ልንደርስ እንችላለን፡፡ ይህ አንግዲህ የአንድን ግለሰብ ንግግር ብሉም ማንነት በሚመለከት ነው፡፡

ከግለሰብ አልፈን፣ ባንድ አካባቢ የሚኖሩ የአንድ ቋንቋዋ ተናጋሪዎችንም በወንዝና በተራራ ተለይተው፣ ራቅ ባለ ሌላ አካባቢ ከሚኖሩ የዚያው ቋንቋዋ ተናጋሪዎች እንደዚሁ ባነጋገር ዘይቤያቸው ለይተን ልናውቃቸው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ አማርኛ ተናጋሪዎችን ብናይ፣ ዱዱብ የሚለውን ወሎየ፣ አልበልቶም ከሚለው ጎጃሜ፤ ባዔላ የሚለውን መንዜ፣ የግዳስ ጨቅሎቹን ከውናቸው[1] ከሚለው ጎንደሬ በቃል አመራረጡና አጠቃቀሙ መለየት ይቻላል፡፡ እያንዳንዱ አካባቢ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት ክልላዊ ዘይቤ አለው ማለት ነው[2]፡፡ ይሁን እንጅ፣ ይህ ዘይቤ የዚያው የአንድ አማርኛ የተለያየ ገፅታ ስለሆነ፣ ተናጋሪዎቹን በሀሳብ ከመግባባት አያግዳቸውም፡፡ እነሱም ቢሆኑ ቋንቋዋችሁ ምንድን ነው? ሲባሉ፣ በጥቅሉ "አማርኛ" ይላሉ

---

[1] ይልቅስ ህፃናቹን ሰብስባቸው ማለት ነው፡፡
[2] ይህን በተመለከተ ሀይሉ፣ ጌታቸውና ኮውሊ (1976)ን፣ ሀብተማርያም (1973)ን እንዲሁም ጌታሁን (1983)ን ይመልከቱ፡፡

እንጅ፣ በክልላዊ መልኩ መንዝኛ፣ ጎጃምኛ፣ ወዘተ፣ አይሉም[3]፡፡ ከሌሎች ህዝቦች ተለይተው <u>በተጨባጭ</u> የሚታወቁትም ከማንኛውም ሌላ መስፈርት ይልቅ፣ በዚሁ ቋንቋዋ ተናጋሪነታቸው ነው፡፡

ይህ ግን በአንድ ቋንቋዋ ተናጋሪዎች መካከል የሚታይ ሁኔታ ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባለ <u>*ልሳነ ብዙ*</u> ሀገር ደግሞ ዜጎች ካንድ ቋንቋዋ በላይ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ የሚናገሩዋቸው ቋንቋዋዎች የስርጭት ስፋትና የእድገት ደረጃም የተለያየ ነው፡፡ አንዳንዱ ቋንቋዋ ሰፋፊ ክልል የሚሸፍንና የዚያኑ ያህልም ብዙ ተናጋሪ ያለው ሲሆን፣ አንዳንዱ ደግሞ በጠባብ ክልልና በዚያው ውስጥ ብቻ በሚኖሩ ህብረተሰቦች የተወሰነ ነው፡፡ አንዳንዱ ለፅሁፍ የበቃና ሰፊ የስነ-ፅሁፍ ቅርስ ያለው ሲሆን፣ ሌላው ገና ለዚህ ያልደረሰና በንግግር ቋንቋዋነት ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ እንደዚህ ያሉ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን ቋንቋዋዎች በመናገር ዜጎች ብሄረሰባዊ ወይም ክልላዊ ማንነታቸውን ይገልፃሉ፡፡

ይሁን እንጅ፣ እንደዚህ ያሉ ልሳነ ብዙ ዜጎች ክልል-አለፍ በሆነ ደረጃ የሚግባቡበት እናም በጋራ የሚታወቁበት አንድ የጋራ ቋንቋዋ ያስፈልጋቸዋል፣ ይኖራቸዋልም፡፡ በሀገራችን በዚህ ደረጃ በማገልገል ላይ ያለው ቋንቋዋ አማርኛ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ቋንቋዋው ከሌሎቹ ቋንቋዋዎች የሰፋ ስርጭትና ከሁሉም የበዛ ተናጋሪ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ባንድ ክልል ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ ብሄራዊ ስርጭትና ይዘት ያለው ቋንቋዋ ነው፡፡ ወደ የትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ቢኬድ፣ አማርኛ ተናጋሪ ማግኘት አያስቸግርም፡፡ ርግጥ፣ የተናጋሪው ችሎታና ብዛት ከመሀል ሀገር እየራቁ በሄዱ ቁጥር፣ የዚያኑ ያህል እየቀነሰ ሊሄድ ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ ከማንኛውም ሌላ የሀገራችን ቋንቋዋ ይበልጥ ዜጎችን የማገናኘት እድሉ የተሻለ ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ቋንቋዋ የሀሳብ ብቻ ሳይሆን፣ የተናጋሪዎችን ማንነት መግለጫም ነው፡፡ ይህ ከሆነ፣ ብዙ ቋንቋዋ የሚናገሩ ሰዎች በልሳነ ብዙነታቸው አንድ ቋንቋዋ ብቻ ከሚናገሩት ተለይተው ይታወቃሉ ማለት ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ዜጎች እንደ ባለ ብዙ መታወቂያ ሰዎች ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ ርግጥ፣ የመታወቂያው አይነትና አገልግሎት የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በአንድ በኩል፣ በክልላቸው በሚናገሩት ቋንቋዋ ብሄረሰባዊ ወይም ክልላዊ ማንነታቸውን ሲያሳውቁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በብሄራዊ ደረጃ በጋራ በሚናገሩት ቋንቋዋ ብሄራዊ ዜግነታቸውን ያሳውቃሉ፡፡ በቀበሌ መታወቂያችን ጠባቡን ሰፈራችንን፣ በፓስፖርታችን ኢትዮጵያዊነታችንን እንደምናሳውቀው ማለት ነው፡፡

---

[3] በአንዳንድ የደቡብ ክፍል ህዝቦች፣ በተለይም በወላይታ፣ በጋሞ፣ በጎፋና በዳውሮ መካከል የዚህ አይነት አመለካከት አንዳለ በማስተማሪያ ቋንቋዋ ምርጫ ላይ በግልፅ ተከስቶአል፡፡ የወቅቱ ፖለቲካም አመለካከቱን የበለጠ አጠንክሮታል፡፡

# መቅድም

የቋንቋዋ ሞቱም ሆነ ልደቱ ባንድ ጀምበር የሚፈፀም አይደለም፡፡ ቀናትን ሳይሆን፣ ዘመናትን ይወስዳል፡፡ ምጡም ሆነ ጣዕሩ ረዥም ነው፡፡ ልደቱ የሚበሰረው በርካታ ተወላጅ ተናጋሪዎችን ሲያገኝና ጠንካራ ማህበራዊ መሰረት መያዝ ሲጀምር ሲሆን፣ መርዶው የሚነገረው ደግሞ ማህበራዊነቱ አክትሞ የመጨረሻ ግለሰብ ተናጋሪውን ሲያጣ ነው፡፡ የግዕዝ አሙዋሙዋትም ሆነ የአማርኛና የሌሎቹ ኢትዮሴማዊ ቋንቋዎች አፈጣጠር ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ የተለየ አይደለም፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ሰሜናዊያን የሴም ወገኖች ግዛታቸውን እያስፋፉ ወደ መሀል ሀገር የመጡት ልዩ ልዩ የኩሽ፣ የኦሞና የአባያዊ ቋንቋዎችን በሚናገር ዘማች ሰራዊትና ከግዕዝ ትንሽ ለየት የሚል የሴም ቋንቋዋ ይናገሩ በነበሩ አዝማቾች አማካኝነት እንደሆነ ይታመናል[5]፡፡ አዝማችና ዘማች ባቀኑት የአገው መሬት ላይ ከህዝቡ ጋር መኖር ይጀምራሉ፡፡ የተለያየ ቋንቋዋ ይናገር የነበረው ሰራዊትም፣ ቀስ በቀስ ያዝማቾቹን ሴማዊ ቋንቋዋ መልመድ ይጀምራል፡፡ አጀማመሩም ቋንቋዋውን እንዳለ በመማር ሳይሆን፣ ከራሱ ቋንቋዋ ጋር እያቀላቀለና እያዋሀደ በመናገር ነው፡፡ ዛሬ ታይፕ የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ወስደን፣ ተየበ፣ ታያቢ፣ ትየባ፣ ትይብ፣ ወዘተ፣ እያልን አማርኛ እያስመሰልን እንደምንጠቀምበት ሁሉ፣ ሴማዊያኑ የሚናገሩትን ቃላትም ሰራዊቱ በዚሁ አይነት ከራሱ ቋንቋዋ ጋር እያመሳሰለና እያዳቀለ ይናገር ነበር፡፡

ይህ በቃላት ደረጃ ሲሆን፣ በመዋቅር ደረጃ ደግሞ በግስ ይጀምር የነበረውን ያዝማቾቹን ቋንቋዋ የራሱን ቋንቋዋ በማስመሰል በግስ እንዲጨርስ ያደርገው ጀመር፡፡ በዚህም ምክንያት ዛሬ አማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ ሌሎቹም ኢትዮሴማዊ ቋንቋዋዎች፣ ከግዕዝ በስተቀር፣ እንደ ዐረብኛና እንደ ዕብራይስጥ ካሉ በግስ ከሚጀምሩ ሌሎች የሴም ቋንቋዋዎች ሊለዩ ችለዋል፡፡ የቃላቱ ቅርፅና የመዋቅሩ ስርዓት በዚህ አይነት ቀስ በቀስ እየተለወጠ የመጣው ያዝማቾቹ ቋንቋዋ፣ ከጊዜ ብዛት ሴማዊ ባህሪውን እየተወ፣ በዚያው ልክም የኩሽና የኦሞ ቋንቋዋዎችን (ኩሾኦሞአዊ) እየመሰለ መጣ፡፡ ወደ አራተኛው ክፍለ ዘመን አካባቢም ባብዛኛው መልኩ ከጥንቱ የሴም ቋንቋዋ የተለየ ይሆንና

---

[5] ቤንደር (1983)ን እንዲሁም ታደሰ ታምራት (1972)ን ይመልከቱ፡፡ የግዛት ማስፋፋቱ እንቅስቃሴና የህዝቦች የፍልሰት አቅጣጫ ከመሀል ወደ ዳር፣ ከኢትዮጵያ ወደ ባህር ማዶ ሊሆን እንደሚችል የሚጠቁሙ ስነ-ልሳናዊ መረጃዎች አሉ፡፡ ሆኖም ጉዳዩ አሁንም አከራካሪ ስለሆነ ከታሪክና ከቅድመ ታሪክ አንፃር በሰፋትና በጥልቀት ሊታይ ይገባዋል፡፡ ለጊዜው ግን ነባሩንና ውጭ - ተኮር የሆነውን የኡለንዶርፍ (1955)ን አመለካከት ለመነሻም ቢሆን መውሰድ ይቻላል፡፡ ወስጥ-ተኮር ስለሆነው ዘመናዊ አመለካከት ሀድሰን (1978)፣ ኤረት (1988)፣ እንዲሁም አየለ በከሪ (1997)ን ይመልከቱ፡፡

> Considering that this grammar could be *translated almost literally into Amharic,* it is not surprising that they talk it well. The constant intercourse between Semitic and Hamitic elements in Abyssinia is naturally reflected in the Amharic and Oromifa languages and a comparative study of the two would be most profitable, though it is beyond the scope of this book. At the same time knowledge of Amharic is of the greatest use in learning Oromo, and in enabling one to grasp the delicacy of its verbal formation and other idioms. (Hodson, A.A., and Walker, C.H. 1922:8)

አሁን በቅርቡም፣ በኢትዮጵያ የሴም ቋንቋዎች ላይ ከፍተኛ ምርምር የሚያካሂዱት ፕሮፌሰር ኦልጋ ካፔልዩክ፣ የቋንቋዎቹን ተመሳሳይነት አለመልከተው የሚከተለውን ፅፈዋል።

> Whereas the vocabulary and the phonological and morphological features of the modern languages vary considerably, their syntax is almost identical, and this is in addition to the similarity in word order. A text in Tigrinya can be translated correctly into Amharic or Gurage, and vice versa, by changing only the lexemes and maintaining the same constructions and idiomatic expressions. (Kapeliuk, 1989:6)

ይህ አባባል ምን ያህል ውነት እንደሆነ፣ ፍርዱን ይህን መፅሀፍ ከራባቸው ቋንቋዋ ጋር እያገናዘቡ ለሚያነቡ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ እተዋለሁ። በእኔ እምነት ግን ኢትዮጵያዊያንን ከሌሎች የቅርብም ሆነ የሩቅ ህዝቦች ለይቶ አንድ የሚያደርጋቸው ስነ-ልሳናዊ ብቻ ሳይሆን፣ ባህላዊና የእሱ ነፀብራቅ የሆነው <u>*ስነ-ልቦናዊ*</u> ባህሪም ጭምር ይመስለኛል። ተረቶቻችን፣ ምሳሌያዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮቻችን፣ እንቆቅልሹና እንካ-ስላንትያው ሁሉ የቅርፅ እንጅ የይዘት ልዩነት ያለው አይመስልም። የጠጣና የቀበሮ ብልጥነት፣ የጅብ ሆዳምነትና የአንበሳ አስፈሪነት ባንድ ብሄረሰብ ተረት ውስጥ ብቻ የሚታይ ክስተት ነው ለማለት የሚቻል አይመስልም። ርግጥ፣ ነገሩ ሰፋ ያለ ንፅፅራዊ የስነ-ቃልና የባህል ጥናት የሚሻ ጉዳይ ነው።

በዚህ ረገድ በመቅድሙ ላይ እንደተገለፀው፣ ቋንቋዋ ማህበራዊ አገልግሎትና መሰረት ያለውን ያህል፣ አዕምሮአዊ ተፈጥሮም እንዳለው ለመረዳት ይቻላል። ማህበራዊ አገልግሎቱን ከማህበራዊ ተራክቦና ከመደበኛ የክህሎት ትምህርት ማግኘት ይቻላል። ማንኛውም ወላጅ "ባሰኔ! እንደዚህ አይባልም፣ ነውር ነው!" እያለ ልጁን ሲቆጣና ስርዓት እንዲይዝ ሲያደርግ፣ የሚያስተምረው ማህበራዊነትን ብቻ ሳይሆን፣ የዚሁ መግለጫ የሆነውን የቋንቋዋውን መደበኛ አጠቃቀም ጭምር ነው። በትምህርት ቤት የሚሰጠውና መደበኛ የቋንቋዋ ትምህርት የሚባለውም በመሰረቱ የዚሁ ተከታይ ነው። ልዩነቱ የአደረጃጀት፣ የአቀራረብና የምዘና ነው።

በዚህ አይነት ባጠቃቀም፣ ማለትም በክህሎት ትምህርት አማካኝነት የቋንቋዋን አዕምሮአዊነት በውል ማሳየት አይቻልም። ይህን ማድረግ የሚቻለው፣ በትምህርትነት የሚሰጥን ቋንቋዋ ስርዓት ራሱን በቻለ መርሀ ግብር፣ በራሱ ዘዴና ዓላማ መሰረት በወጉ በሰለጠነ መምህር በማስተማር ነው። ይህ የስርዓት ትምህርት ለክህሎቱ ትምህርት አጋር ሊሆንም፣ ላይሆንም ይችላል። ይህን የሚወስነው ክህሎቱን የሚያስተምረው ባለሙያ ነው። ለዚያውም ከስ<u>ነ-ዘዴ</u> ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከስነ-አዕምሮና ከስነ-ልሳን ጋር ትውውቅ ያለው ከሆነ ነው።

ባጠቃላይ ግን የቋንቋዋን ትምህርት በሚመለከት አንድ ነገር ያለጥርጥር መናገር ይቻላል። ይኸውም የአንድን ቋንቋዋ አጠቃቀም ብቻ ካወቀ ተማሪ ይልቅ፣ አጠቃቀሙን፣ ማለትም ክህሎቱን ከነስርዓቱ የተገነዘበ ተማሪ የተሻለ ክህሎትና ስነ-ልሳናዊ ዕውቀት ያለው መሆኑ ነው። ይህ ዕውቀትም ከቋንቋዋው አልፎ፣ ከቋንቋዋው ጋር ተያያዥነት ካላቸው እንደ ሳይኮሎጂ፣ ሶሲዮሎጂና ፍልስፍና ካሉ የትምህርት ዘርፎች ጋር ተማሪው በቀላሉ እንዲተዋወቅ ይረዳዋል። ቋንቋዋ አዕምሮአዊ እንደሆነ ሁሉ ማህበራዊ ብሎም ባህላዊ ነውና። በዚህ መልኩ ቋንቋዋ ባህልም የባህል መግለጫም ነው።

የቋንቋዋውን አጠቃቀም ከነስርዓቱ የሚያውቅ ሰው መኪና አነዳድንና የመኪና አካላትን አሰራር እንደሚያውቅ መካኒክ ሾፌር የሚቆጠር ነው። እንዲህ አይነቱ ሾፌር ደግሞ የትራፊክን ህግ ጠብቆ እንዲያሽከረክር ከሰለጠነ ሾፌር የበለጠ የመኪና ስርዓትና ያነዳድ፣ ማለትም ያጠቃቀም ችሎታ ይኖረዋል። ስለዚህም ከተራ አሽከርካሪ ጋር አይመደብም። ሊመደብም አይገባም።

ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው፣ ማንኛውም የቋንቋዋ ተማሪ የተሟላ የቋንቋዋ ዕውቀት ሊያገኝ የሚችለው፣ ክህሎቱን ብቻ ሳይሆን ስርዓቱን፣ ማለትም የቋንቋዋውን ሳይንስ ጭምር ሲገነዘብ መሆኑን ነው። ክህሎቱን ብቻ ያገኘ ተማሪ ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ተራ አሽከርካሪ ብዙም አይለይም። ሁለቱም አጠቃቀሙን እንጅ ስርዓቱን መግለፅ አይችሉምና። ስርዓቱን ብቻ የተካነ ተማሪም ያጠቃቀም ድህ ከመሆን አያመልጥም። ሳይንሱን ከማነብነብ አልፎ፣

ጥሩ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ሁለቱን ትምህርቶች አጣጥሞ የያዘ ተማሪ ብቻ ነው፣ ከፍ ሲል እንደጠቀስነው ባለሙያ ሾፌር የሚቆጠረው፡፡ ስርዓቱን ከነአጠቃቀሙ ይዞአልና፡፡

የቋንቋዋ ትምህርት ሲባል ስርዓት ብቻ የሚመስላቸው እንዳሉ ሁሉ፣ ክህሎት ሲባልም ከማንበብ፣ ከመፃፍ፣ ከመናገርና ከመረዳት የማይዘል የሚመስላቸው አይጠፉም፡፡ ይህ ድንጋሬ የሚከሰተው ክህሎትን፣ ማለትም አጠቃቀምንና ስርዓትን ለያይቶ ከማየት ነው፡፡ ሁለቱ የተዛመዱ ግን ደግሞ የተለያየ ዓላማና ዘዴ ያላቸው የቋንቋዋ ዘርፎች ናቸው፡፡ ዝምድናቸው ሁለቱም በቋንቋዋ ላይ የተመሰረቱ መሆናቸው ሲሆን፣ ልዩነታቸው ደግሞ አንደኛው የስርዓት፣ ሌላው ያጠቃቀም ዘርፍ መሆኑ ነው፡፡ አጠቃቀሙ በአብዛኛው ማህበራዊና ባህላዊ ሲሆን፣ ስርዓቱ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ አዕምሮአዊና ማህበራዊ ነው፡፡

ይህን አንድነትና ልዩነት በመረዳት እንዳግባቡና እንዳስፈላጊነቱ ሁለቱንም ዘርፎች ባንድ ላይ አካቶና አጣጥሞ፣ እለያም ለያይቶ ማስተማር ይቻላል፡፡ በመሰረቱ ግን ስርዓት ስነ-ልሳናዊ ሲሆን፣ አጠቃቀም ግን ከፍ ሲል እንደተገለፀው ማህበራዊ ነው፡፡ የመጀመሪያው የቋንቋዋ ግንዛቤን፣ ሁለተኛው ያጠቃቀም ችሎታን የሚያዳብር ትምህርት ነው፡፡ የአጠቃቀሙ ችሎታ ግን የስርዓቱ ነፀብራቅ ነው፡፡ ስለዚህ የስርዓቱ ግንዛቤ ለአጠቃቀሙ ክህሎት ወሳኝ ነው ባይባልም፣ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሰረቱ የቋንቋዋ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ድርሰት ሲያርሙ ዋናው ትኩረታቸው በአረፍተ ነገሮቹ ትክክል መሆን ወይም አለመሆን ላይ ነው፡፡ የሀሳብ ጥንካሬ፣ ቅደም-ተከተላዊ አቀነጃጀት፣ የቃላት አመራረጥ፣ ግልፀት፣ ወዘተ፣ የአረፍተ ነገሩን ስርዓት ያህል አይተኮርባቸውም ለማለት ይቻላል፡፡ በአረፍተ ነገሩ ላይ የሚደረገው ትኩረትም ያልሰጡትን እንደመሻት የሚቆጠር ነው፡፡ ትክክለኛ የሀረግ አወቃቀር ስርዓትን ሳያስተምሩ፣ አረፍተ ነገርህ በትክክል አልተዋቀረም ብሎ አስተያየት መስጠትና ደብተርን ቀይ በቀይ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡ ሀሳቡን እስከገለፀ ድረስ የአረፍተ ነገሩ ትክክለኛ አለመሆን አያስጨንቀንም ማለትም፣ ተማሪውን ለስራ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዳይቀርብ የሚያደርግ አደገኛ አመለካከት ነው፡፡ በየጊዜው የሚሰማው የቀጣሪዎች እሮሮ የሚያመለክተው በየደረጃው እየተመረቁ የሚወጡት ተማሪዎች ተራ ዘገባ (ሪፖርት) ለማዘጋጀት የሚያስችል ብቃት እንደሌላቸው ነው፡፡ ባጭሩ ሀሳብን አስተካክሎ በተስተካከለ አረፍተ ነገር የመግለፅ ብቃት የላቸውም፡፡ ይህ እየታወቀ፣ ለዚህ የሚረዳውን ትምህርት ችላ ማለት ተገቢ አይመስለንም፡፡ ትክክልም አይደለም፡፡ ትክክል የሚሆነው ከስነ-ልሳኑና ከስነ-ዘዴው ሳይንስ ጋር አብሮ እየተራመዱም ባይሆን፣ ከስር ከስሩ እየተከተሉ የክህሎቱንም ሆነ የስርዓቱን ትምህርት ማጎልበት ነው፡፡

ስርዓቱንም ሆነ አጠቃቀሙን በወጉ ለማስተማር ደግሞ ከሞላ ጎደልም ቢሆን የተጠናቀረ የማስተማሪያና የማገናዘቢያ መፅሀፍ ያስፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አማርኛ በትምህርትነት መሰጠት የጀመረው ገና ዱሮ ነው፡፡ በዚያን ዘመን፣ ችግሩ የተሰማቸው እንደ ብላታ መርስዔ ሀዘን ወልደ ቂርቆስና እንደ ተክለማሪያም ፋንታዬ ያሉ ሊቃውንት ካዘጋጁዋቸው ሁለት መፃህፍት ሌላ፣ ዛሬ ምንም ነገር የለም ለማለት ይቻላል፡፡ እነዚህም ቢሆኑ በይዘታቸውም ሆነ ባመለካከታቸው ለዛሬው ዘመን ትምህርት በቂ አይደሉም፡፡ ብዙ ይጎድላቸዋል፡፡ ርግጥ፣ ይህ የአሁኑ መፅሀፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ከወጣ በሁዋላ፣ የዚህኑ ፈለግ የተከተሉ አንዳንድ የሰዋሰው መፃህፍት ወጥተዋል፡፡ በጣም ጥሩ ዕድገት ይመስለኛል፡፡ ለሊሎች ቋንቋዎችም መልካም አርአያ ስለሆነ ሊበረታታ ይገባዋል፡፡ በየትምህርት ቤቱ በትምህርትነት እየተሰጡ ያሉት የሀገራችን ቋንቋዎች በዚህ ረገድ ከፍተኛ ስራ ይጠይቃሉ፡፡ የየቋንቋዋው መምህራንም ከዚህ መፅሀፍ ብዙ ይጠቀማሉ የሚል እምነት አለኝ፡፡

የስርዓቱ ትምህርት ካንደኛና ከሁለተኛ ደረጃ አልፎ በየኮሌጁ መሰጠት ከጀመረ በርካታ አመታትን ቢያስቆጥርም፣ በዚሁ ቋንቋዋ ተዘጋጅቶ የቀረበ መደበኛ ማስተማሪያም ይሁን መመሪያ ወይም ማጣቀሻ መፅሀፍ አሁንም በብቃት የለም፡፡ ባለመኖሩም ትምህርቱ የሚሰጠው የተለያዩ የስነ-ልሳን ሰዎች በልዩ ልዩ የውጭ ቋንቋዋዎች ስለ ቋንቋዋው ከፃፉዋቸው የምርምር ስራዎች ላይ እየተቀነጨበ በሚወጣ ተበታኝ ወረቀት አማካኝነት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ፣ መምህራን በተቀያየሩ ቁጥር የትምህርቱ ይዘትና አቀራረብ እንደ መምህራኑ ዳራ እና እንደሚያጋጥማቸው የምርምር ስራ ሲቀያየር ኖሮአል፡፡ በዚህም ምክንያት የአንዱ ዘመን ተማሪ የተማረውን፣ የሌላው ዘመን ተማሪ አያገኘውም፡፡ ስለዚህም ተመጣጣኝ ችሎታና ግንዛቤ ያላቸውን ተማሪዎች ማፍራት ሲያስቸግር ቆይቶአል፡፡ ከዚህ ችግር ለመውጣት የሚቻለው፣ አንድ ወጥ የሆነ የማስተማሪያ መፅሀፍ በባዕድ ሳይሆን፣ በዚሁ ቋንቋዋ ሲዘጋጅና ሁሉም በዚሁ መነሻነት እያስተማረ ተፈላጊውን ግንዛቤና የአጠቃቀም ክህሎት ሲያዳብር ነው፡፡

እነሆ፣ በዚህ መፅሀፍ ለማድረግ የተሞከረውም ይኸው ነው፡፡ አንድ ወጥና አጠቃላይ የሆነ የአማርኛ ሰዋሰው ማዘጋጀት፡፡ በሶስተኛ ደረጃና ከዚያም ዝቅ ብሎ የሚሰጠውንና መሰጠትም የሚገባውን አጠቃላይ የአማርኛ ትምህርት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የቋንቋዋው ስርዓት በሶስት ምዕራፎች ተከፍሎ እንዲቀርብ ተደርጎአል፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የአማርኛን ድምፆች አይነትና ያሰካክ ባህሪ የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ ከድምፆቹ የሚመሰረቱትን ቃላት የርባታና የምስረታ ስርዓት የሚያካትት ሲሆን፣ ሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ የሀረግንና የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን ያወቃቀር ባህሪ የሚያሳይ ነው፡፡ ሶስቱም ምዕራፎች ለሶስተኛ ደረጃ ተማሪዎች ቢቻል በሶስት፣ አለያም በሁለት መንፈቅ ተጠቃለው ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ሶስቱም ምዕራፎች መፅሀፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲወጣ ከነበራቸው ይዘት በአጅጉ ተለውጠዋል፡፡ ተጨማሪ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ሂደቶችና ስነ-ምዕላዳዊ ስርዓቶች ተካተዋል፡፡ ከዋና ዋናዎቹ የቃላት ክፍሎች በተጨማሪ፣ መስተዓምር የሚል ራሱን የቻለ የቃል ክፍል ተካቶአል፡፡ በመዋቅሩ ክፍል አድራጊና አስደራጊ አረፍተ ነገሮችን የሚመለከት ክፍል ተጨምሮአል፡፡ በዚህም ምክንያት የመፅሀፉ ይዘት ሰፍቶአል፡፡ በመጀመሪያው ዕትም ተጠቅሰው የነበሩ አንዳንድ ምሳሌዎች ወጥተዋል ወይም በሌሎች ተተክተዋል፡፡ ይህም የተደረገው ፅንሰ-ሀሳቦችን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ሲባል ነው፡፡ በያንዳንዱ ንዑስ ክፍል መጨረሻ ላይ ለሙከራ የሚሆኑ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡

ዝግጅቱ ከመሰረተ ጉዳዮች ተነስቶ ቀስ በቀስ ጥልቅና ውስብስብ ወደሆኑ ነገሮች የሚሄድ ነው፡፡ ስለሆነም ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም ሆነ ከዚያ በታች ላሉት እንደ አስፈላጊነቱ ከያይነቱ እየተጨለፈና ቀጠንጠን እየተደረገ ሊቀርብ ይችላል፤ የሚል ግምት አለኝ፡፡ ከዚህም አልፎ፣ ከትምህርት ቤት ውጭ መፅሀፉን በግል በማንበብ ብቻ ስለ አማርኛ ቋንቋዋ ስርዓት፣ ብሎም ስለ አጠቃላይ የስነ-ልሳን ሳይንስ መሰረታዊ ግንዛቤ ለማግኘት ለሚፈልጉ ሁሉ፣ መፅሀፉ ጥሩ መነሻ ሊሆን የሚችል ይመስለኛል፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ደረጃ በግል ለሚያነቡ ሰዎች አንድ ማሳሰቢያ አለኝ፡፡ ይኸውም መፅሀፉ እንደ ተራ ልቦለድ ተዝናንቶ የሚነበብ ሳይሆን፣ ቀስ ተብሎ እየታሰበና እየተጠና የሚነበብ መሆኑን ነው፡፡ አንዳንድ ፅንሰ-ሀሳቦችን ለመረዳት አንዳንድ ጊዜ አረፍተ ነገሮቹን ደጋግሞ ማንበብ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ፅንሰ-ሀሳቦቹ አዕምሮአዊ የሆኑ ነገሮችንና ግንኙነቶችን የሚሸፍኑ ስለሆኑና እነዚህንም ለመግለፅ የተጠቀምኩባቸው ቃላት እንግዳ፣ አረፍተ ነገሮቹም ተራ ሳይሆኑ፣ ውስብስብ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው፡፡ የቃላቱን ችግር ለማቃለል፣ ይከብዳሉ ብዬ ለገመትኩዋቸው ቃላት፣ ሙዳየ ቃላት ተዘጋጅቶአል፡፡ በሙዳየ ቃላቱ ውስጥ የገቡት በግርጌያቸው ላይ የተሰመረባቸውና ትንጋደው የተፃፉት ብቻ ናቸው፡፡ ተጨማሪ ንባብና ምርምር ለማካሄድ ለሚፈልጉ ደግሞ እስካሁን ድረስ በቋንቋዋው ስርዓት ላይ የተፃፉትንና የታተሙትን የስነ-ልሳንና ሌሎችም ተዛማጅ መረጃዎች ከሞላ ጎደል የሚያሳይ መዘርዝር ቀርቦአል፡፡

መፅሀፉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታተም የህትመት ደረጃው የታቀደውን ያህል እንዳልነበረ ግልፅ ነው፡፡ ለዚህም ልዩ ልዩ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ይህም ከፍተኛ ቅሬታን ቢያሳድርብኝም ለበለጠ ስራ እንድነሳሳ ረድቶኛል፡፡ ይህ ያሁኑ ዕትም በአይነቱም ሆነ በይዘቱ ከመጀመሪያው የተሻለ እንደሆነ በየደረጃው ረቂቁን ያነበቡ ባልደረቦቼና ተማሪዎቼ ጠቁመውኛል፡፡ ያም ሆኖ በበኩሌ አሁንም “እንዲህ ቢሆኑስ” የምላቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ የምርምር ስራ ማለቂያ የለውምና ለጊዜው ባሉበት ትቻቸዋለሁ፡፡ ወደፊት ግን “እንዲያ” አደርጋቸው ይሆናል፡፡

መልካም ንባብ

# ምዕራፍ አንድ

## ስነ-ድምፅ

### መግቢያ

ማንኛውም ቋንቋ መሰረቱ ድምፅ ነው፡፡ ድምፅ ስንል በንግግር ጊዜ በአንደበት የሚፈጠረውን ማለታችን ነው፡፡ ድምፅ በአንደበት የሚፈጠረው በመደበኛ የስትንፋስ ሂደት ላይ ከሳንባ የሚነሳ ወይም ወደ ሳንባ የሚገባ አየር በተለያዩ የአንደበት አካላት፣ በተለያየ ቦታ ላይ እየታገደና እየተለቀቀ፣ ወይም ሳይታገድ እንደልቡ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ነው፡፡[1] አንድ ሰው በቋንቋ ሀሳቡን የሚያስተላልፈውም በመሰረቱ የተለያዩ ድምፆችን በቅደም-ተከተል በተለያዩ ያንደበት ክፍሎች በመፍጠር ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ልጅ፤

መፅሀፍ ማንበብ እፈልጋለሁ 1

በማለት፣ የመፅሀፍ ማንበብ ፍላጎቱን የሚገልፀው፣ የሚከተሉትን ድምፆች ተራ በተራ፣ በተለያየ ቦታና ሁኔታ በመፍጠር ነው፡፡

ም-ኧ-ፅ-እ-ሀ-እ-ፍ-ም-ኣ-ን-ብ-ኧ-ብ-እ-ፍ-ኧ-ልል-እ-ግ-ኣ-ልል-ኧ-ሀ-ኡ

እነዚህ ድምፆች ባብዛኛው የተለያዩ ናቸው፡፡ የልዩነታቸው ምክንያት የሚፈጠሩበት ቦታና ያፈጣጠራቸው ሁኔታ የተለያየ መሆኑ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ድምፆች ብንመለከት፣ [ም] ከንፈሮቻችንን በመዝጋት ከሳንባችን የሚወጣው አየር በሰርን በኩል አድርጎ በአፍንጫ እንዲወጣ ስናደርግ የሚፈጠር ሲሆን፣ [ኧ] ደግሞ ከንፈሮቻችንን አላቀን አፋችንን ስንከፍትና አየሩ በአፍ በኩል እንዲወጣ ስናደርግ የሚፈጠር ድምፅ ነው፡፡ በዚሁ ሁኔታ የሌሎቹንም ድምፆች የተለያየ የመፈጠሪያ ቦታንና የአፈጣጠር ሁኔታን መዘርዘር ይቻላል፡፡

ርግጥ፣ ከላይ የተጠቀሰው ልጅ የመፅሀፍ ማንበብ ፍላጎቱን የሚገልፀው ድምፆቹን በተደረደሩበት መልካቸው እያንዳንዳቸውን በተናጠል በመፍጠር ብቻ አይደለም፡፡ ቅደም-ተከተላቸውን ሳያፋልስ፣ በቡድን በቡድን በመከፈልና አንዱን ቡድን ከሌላው ጋር እንደሚከተለው እያደረገ በመለየት ነው፡፡

---

[1] ቀናው ከሳንባ የሚወጣው አየር ይሁን እንጅ በማንቁርትና በትናጋ ላይ በሚገኝ አየር አማካኝነትም ሊፈጠር ይችላል፡፡

መ - ፅ - ሀፍ - ማን - በብ - እ - ፈል - ል - ጋ - ለለ - ሁ (2)
በዚህ አይነት ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን 24 ድምፆች በ11 ሊመድባቸው ይችላል፡፡ ይህም ሆኖ፣ እንደዚህ እያደረገ በመከፈል ብቻ ሀሳቡን በሚገባ ላያስተላልፍ ይችላል፡፡ ይህን ለማድረግ የሚችለው እነዚህን 11 ቡድኖች እንደገና በአራት በማጠቃለል፣

መፅሀፍ - ማንበብ - እፈልግ - እለሁ (3)

ሲል፣ ወይም ደግሞ ከላይ በተራ ቁጥር (1) በቀረቡበት ስርዓተ ፅሀፈታዊ መልካቸው በሶስት ቡድኖች ብቻ አካቶ፣

መፅሀፍ - ማንበብ - እፈልጋለሁ (4)

ሲል ነው፡፡

በመሰረቱ ግን እነዚህ ከሁለት እስከ አራት የቀረቡት ቡድኖች ከላይ የተዘረዘሩት የ24ቱ ተናጠል ድምፆች ቅንጅት ናቸው፡፡ በሁለቱ፣ ማለትም በዝርዝሮቹና በቅንጅቶቹ (ቡድኖቹ) መካከል ያለው ልዩነት የቅንጅት ነው፡፡ 24ቱ ነጠላ ድምፆች ወደ 11፣ 11ዱ ደግሞ ወደ አራት፣ ከዚያም እልፎ፣ ወደ ሶስት እየተቀናጁ በተዋረድ ሊመጡ ችለዋል፡፡ ከዚህም ሁኔታ የምንረዳው አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ድምፆች _ተናጠላዊ_ እና ቅንጅታዊ ባህሪ ያላቸው መሆናቸው ነው፡፡ ተናጠላዊ ባህሪያቸው ካፈጣጠራቸው ጋር የተያያዘ ሲሆን፣ ቅንጅታዊ ባህሪያቸው ካገባባቸው የሚመጣ ነው፡፡ በድምፅ ደረጃ የሚደረግ የአንድ ቋንቋ ጥናትም በነዚህ ሁለት ባህሪያት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ እኛም በዚህ ክፍል የምናደርገው ይህንኑ ነው፡፡ የአማርኛን ድምፆች ተናጠላዊና ቅንጅታዊ ባህሪያት መመርመር፡፡

## ተናባቢ

ባህሪያቱን ለመመርመር መነሻችን ከላይ እንደተጠቀሰው ልጅ ያሉ እንደበተ ጤነኛ ሰዎች ንግግር ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የተጠቀሰው ልጅ "መፅሀፍ ማንበብ እፈልጋለሁ" ከማለት እልፎ፣ ስለ መፅሀፍ ንባብ ጠቃሚነት ረዘም ያለ ንግግር ቢያደርግና፣ ያን ንግግሩንም በቴፕ ቀርፀን፣ በውስጡ የሚገኙትን ድምፆች እየለየን በተናጠል ለማውጣት ብንሞክር፣ ከምናገኛቸው ዋና ዋና ድምፆች መካከል አብዛኞቹ የሚከተሉት እንደሆኑ እንረዳለን፡፡

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [ብ | ፍ | ጥ | ር | ጅ | ዥ | ኝ | ግ | (5) |
| ም | ድ | ስ | ን | ች | ሽ | ክ | ዕ | |
| ው | ት | ዝ | ል | ጭ | ይ | ቅ | ህ] | |

እነዚህ በሙሉ ተናባቢ ድምፆች ይባላሉ፡፡ ተናባቢ የሚባሉበት ምክንያት፣ ተንቀሳቃሽ በሚባሉት ያንደበት ክፍሎች ከሳንባ የሚወጣው አየር እየታገደና እየተለቀቀ ሲወጣ የሚፈጠሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ተንቀሳቃሽ የአንደበት ክፍሎች የሚባሉት ከናፍር፣ ምላስ፣ የትናጋ ጫፍ (ቬለም) እና ማንቁርት ውስጥ የሚገኙ ተርገብጋቢ አካላት ናቸው፡፡

ድምፆቹ በጥቅሉ ተናባቢ ይባሉ እንጅ፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ በመካከላቸው የሚታዩ ልዩነቶች አሉ፡፡ እነዚህም ልዩነቶች የሚመነጩት ከድምፆቹ <u>*መካነ ፍጥረት*</u> እና <u>*ባህርየ ፍጥረት*</u> ነው፡፡ መካነ ፍጥረት አንድ ድምፅ የሚፈጠርበት ቦታ ሲሆን፣ ባህረየ ፍጥረት ደግሞ፣ ድምፁ የሚፈጠርበት ሁኔታ ነው፡፡ መካነ ፍጥረት የሚባለው፣ በመሰረቱ ከከናፍር ጀምሮ እስከ ማንቁርት ድረስ ያለው የላይኛው ያፋችን ክፍል ነው፡፡ ይህም የላይኛውን ከንፈር፣ ጥርስን፣ ድድን፣ <u>*ድላንቃን*</u> (የድድና የላንቃ ድንበር) ላንቃን፣ ትናጋን፣ እንጥልን፣ ጉሮሮንና ማንቁርትን ያጠቃልላል፡፡

በመሰረቱ በነዚህ በያንዳንዳቸው ላይ በተንቀሳቃሾቹ ክፍሎች አማካኝነት አየር እየታገደ ሲለቀቅ፣ የተለያየ ድምፅ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከዚህ አኳዋያ ሲታይ፣ በየቋንቋዎው መካከል ሊኖር የሚችለው የድምፅ ልዩነት፣ እነዚህን ቦታዎች በከፊል ከመጠቀም ወይም ካለመጠቀም የሚመጣ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ አማርኛን ብንወስድ፣ እንጥልንና ጉሮሮን አይጠቀምም፡፡ ስለዚህም የእንጥልና የጉሮሮ ድምፆች የሉትም፡፡ በዚህ ምክንያት፣ የእንጥል ድምፅ ካሉዋቸው እንደ ሀምጣንጋ ካሉ የአገው ቋንቋዎችና የጉሮሮ ድምፅ ካላቸው እንደ ትግርኛ ካሉ የሴም ቋንቋዎች ይለያል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በቋንቋዎች መካከል ያለው የድምፅ አይነት ልዩነት፣ አንድም ከመካነ ፍጥረት ምርጫ እና/ወይም ከባህርየ ፍጥረት ልዩነት የሚመጣ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡

ባህርየ ፍጥረት ካየር ጋር የተገናዘበ ፅንሰ-ሀሳብን ያዘለ ስያሜ ነው፡፡ በመሰረቱ ድምፅ የሚፈጠረው አየር ሲኖር ነው፡፡ አየር ከሌለ ሰውም አይኖርም፡፡ ይኖራል እንኳዋ ቢባል፣ ድምፅ መፍጠር ስለማይችል፣ በንግግር ሀሳብን ማስተላለፍ አይችልም፡፡ ድምፅ የሚፈጠረው ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ባብዛኛው ከሳንባ በሚወጣ አየር ነው፡፡ ባብዛኛው የምንልበት ምክንያት ባንዳንድ ቋንቋዎች ወደ ሳንባ በሚገባ አየርም የሚፈጠሩ ድምፆች ስላሉ ነው፡፡ በሀገራችን ለምሳሌ እንደ ኦሮምኛ ያሉ የኩሽና እንደ ባስኬቶ ያሉ የኦሞ ቋንቋዎች በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩ ድምፆች አሉዋቸው፡፡ ከነዚህም አንዱ [ጵ] ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ድምፅ የሚፈጠረው ከሳንባ የሚነሳው አየር በማንቁርት አልፎ፣ በጉሮሮ አድርጎ፣ በአፍ ወይም ባፍንጫ በኩል ወደ ውጭ ይወጣል፡፡ በዚህ ጉዞው ላይ ከላይ በተዘረዘሩት ቦታዎች ማለትም፣ መካነ ፍጥረቶች ላይ እየታገደ ወይም ሳይታገድ እንደልቡ ሊወጣ ይችላል፡፡ የሚታገደውም ተንቀሳቃሽ ባልናቸው የአንደበት ክፍሎች ነው፡፡ እነዚህ ክፍሎች ከተጠቀሱት መካነ ፍጥረት ጋር በሚያደርጉት ንክኪ አማካኝነት፣ አየር እየታገደ ሲወጣ የሚፈጠሩት ድምፆች፣ ሳይታገድ ሲወጣ ከሚፈጠሩት ሌሎች ድምፆች የተለዩ ናቸው፡፡ ስለሆነም ሲታገድ የሚፈጠሩትን በጥቅሉ እግድ፣ ሳይታገድ የሚፈጠሩትን ልቅ ድምፆች

አንላቸዋለን። አግዶቹ በጥቅሉ ከፍ ሲል ተናባቢ ያልናቸው ሲሆኑ፣ ልቆቹ ደግሞ አናባቢ የሚባሉትና ወደፊት የምናያቸው ናቸው።

በአንድ መካነ ፍጥረት ላይ አየር የሚታገደው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሊሆን ይችላል። በዚህም መሰረት የሚፈጠሩትን ድምፆች እንደ እግዱ ደረጃ ሙሉ ወይም ከፊል እግድ በማለት በሁለት ብቻ እንከፍላቸዋለን። ሙሉ እግድ የሚባሉት፣ አየሩ ሙሉ በሙሉ ከታገደ በሁዋላ ባንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሲለቀቅ የሚፈጥሩት ሲሆኑ፣ ከፊል እግድ የሚባሉት ደግሞ ያየሩ መውጫ በተንቀሳቃሹ የአንደበት አካል በከፊል ሲዘጋ ወይም ሲጠብና ከዚህም የተነሳ አየሩ በጠበበው በር እየተሹለከለከና እየተፋተገ ሲወጣ የሚፈጠሩት ድምፆች ናቸው።

1-ሰርን
2-ከናፍር
3-ጥርስ
4-ድድ
5-ድላንቃ
6-ትናጋ
7-እንጥል
8-የምላስ ጫፍ
9-የምላስ መሀል
10-የምላስ ሁዋላ
11-አፍ
12-ጉሮሮ
13-የማንቁርት ክዳን
14-ማንቁርት
15-ርግብግቢት
16-አየር ማለፊያ
17-መዋዋጫ



የአንደበት አካላት

ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው፣ እንዳንድ ጊዜ ቁዋንቁዋንና ምላስን አንድ አድርገን የምንወስደው፡፡

እንግዲህ ከዚህ አጠቃላይ የድምፅ አፈጣጠር ሁኔታና ቦታ ተነስተን ቀደም ሲል የዘረዘርናቸውን ተናባቢ ድምፆች በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን፡፡

| | መካነ ፍጥረት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባህርየ ፍጥረት | ከናፍር | ስነፈር | ድድ | ድላንቃ | ላንቃ | ትናጋ | ማንቁርት |
| እግድ፡<br>ነ | ብ | | ድ | | | ግ<br>ግʷ | |
| ኢ | ፕ | | ት | | | ክ<br>ክʷ | ዕ |
| ፈ | ጵ | | ጥ | | | ቅ<br>ቅʷ | |
| ፍትግ፡<br>ነ | | | ዝ | ዥ | | | |
| ኢ | | ፍ | ስ | ሽ | | | ህ |
| ፈ | | | ፅ | | | | |
| ፍግድ፡<br>ነ | | | | ጅ | | | |
| ኢ | | | | ች | | | |
| ፈ | | | | ጭ | | | |
| ሰርናዊ፡ | ም | | ን | | ኝ | | |
| ጎናዊ፡ | | | ል<br>ር | | | | |
| ከፍናቢ፡ | ው | | | | ይ | | |

የፎኒም ሰጠረዥ[5]

በጥቅል አነጋገር፣ እነዚህ ድምፆች በሙሉ አግድ ናቸው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ እገዳው ከፊል ወይም ሙሉ ሊሆን ይችላል፡፡ ዝርዝር አፈጣጠራቸውን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

[5] ከዚህ ለተለየ የፎኒም ዝርዝር፣ ሙሉጌታ ስዩም ገቢየው፣ (2001)ን ይመልከቱ፡፡

የማንቁርት ፍትግ ድምፆች ይባላሉ። ፍትግ የሚባሉበት ምክንያት ከሳንባ የሚወጣው አየር በተጠቀሱት ቦታዎች አድርጎ ሲያልፍ፣ መንገዱ በከፊል ስለሚዘጋበትና ከዚህም የተነሳ ስለሚጣበብ፣ እንደልቡ ሳይሆን፣ እየተፋተገና እሽሽሽ... የሚል ድምፅ እያሰማ ስለሚወጣ ነው[7]። መንገዱን የሚዘጉበት ቀደም ሲል ተንቀሳቃሽ ያንደበት ክፍሎች ያልናቸው፣ ማለትም ከንፈር፣ ምላስና ማንቁርት ውስጥ የሚገኙት ከሮች ናቸው። ለምሳሌ የ[ፍ]ን አፈጣጠር ብንመለከት፣ ከሳንባ ተነስቶ በአፍ በኩል የሚወጣው አየር ጥርስ አካባቢ ሲደርስ፣ የታችኛው ከንፈራችን ወደ የላይኛው የፊት ጥርሳችን በመሄድ መውጫ መንገዱን ሲያጣብብበት፣ የግድ እየተፋተገና እየተሹለከለከ እንደሚወጣ እንረዳለን።

ከ[ዝ] እና ከ[ዥ] በስተቀር፣ ሌሎቹ ድምፆች በሙሉ ኢነዛሪ ናቸው። [ፅ] ግን ኢነዛሪ ብቻ ሳይሆን ፈንጅም ነው። ስለፈንጅ ድምፆች ቀደም ሲል የተሰጠውን መግለጫ ያስታውሱ።

## ፍግድ (ፍትግ-እግድ)

ፍግድ ድምፆች የሚባሉት የእግድና የፍትግ ድምፆች ያፈጣጠር ባህሪ ባንድ ላይ የሚታይባቸው ናቸው። እነሱም [ጅ፣ች] እና [ጭ] ናቸው። ካፈጣጠራቸው ባህሪ የተነሳ፣ ፍትግ-እግድ ድምፆች ሊባሉ ይችሉ ነበር። አጠራሩን ለማሳጠር፣ ብሎም ቀላል ለማድረግ ሲባል ፍግድ ተብለዋል[8]።

አየሩ የሚታገደው ድላንቃ ላይ ሲሆን፣ አጋጁም የምላስ የፊት ክፍል ነው። ይህ ክፍል ወደ ድላንቃ በመነሳት ከሳንባ የሚመጣውን አየር ሙሉ በሙሉ ያግደዋል። እስተጋገዱ ልክ እግድ ድምፆች ሲፈጠሩ እንደሚታየው አይነት ነው። አየሩ ከታገደ በሁዋላ፣ አየሩን ያገደው አካል ባንድ ጊዜና በፍጥነት ሳይሆን፣ በዝግታ ወደነበረበት ቦታ ሲመለስ፣ ታግዶ ለነበረው አየር መሹለኪያ በር ቀስበቀስ ይከፍትለታል። አየሩም በሚከፈትለት ጠባብ በር እየተፋተገና እየተሹለከለከ ቀስበቀስ ይወጣል። እንደ እግድ ድምፆች በአንድ ጊዜ ቡልቅ! ብሎ ሳይሆን፣ እንደ ፍትግ ድምፆች ሹልክልክ እያለ ይወጣል።

---

[7] ጌታሁን (1990) እነዚህን ድምፆች ሹልክልክ ይላቸዋል። በእኔ ግምት አይነተኛ ባህሪያቸው በጠበበው ቀዳዳ እየተፋተጉና ሽሽሽ.... የሚል ድምፅ እያሰሙ መፈጠራቸው ስለሆነ፣ ፍትግ የሚለው ቃል የበለጠ ይገልፃቸዋል። መሹለክለክ መፋተግን ላያስከትል ይችላል።

[8] ጌታሁን፣ዝኒ ከማሁ፣ እነዚህን ድምፆች ፍትግ ይላቸዋል። ይሁን እንጂ ባህሪያቸው የፍትግነት ብቻ ሳይሆን፣ የእግድነትም ጭምር ስለሆነ፣ ፍትግ ከሚለው ይልቅ፣ ፍግድ የሚለው ይበልጥ ይገልፃቸዋል። ስለዚህም ይህንን ስያሜ እንጠቀማለን። "ላሽ" የሚለው ስያሜ የጌታሁን መሆኑን እንገልፃለን።

ይለያያል:: [ሏ] ሰንሏ፣ ንከኪው ጠበቅ ያለና የሚወጣውም አየር ሞቅ (በዛ) ያለ እንደሆነ ይሰማናል:: ሁለቱም ነዛሪ ናቸው::

## *ከፍናቢ* (ከፊል እናባቢ)

በዚህ ውስጥ የሚመደቡት [ው] እና [ይ] ናቸው:: እነዚህ ድምፆች ከፊል እናባቢ በመባል ይታውቃሉ:: ስሙን ለማሳጠር ሲባል <u>*ከፍናቢ*</u> ተብለዋል:: ከፍናቢ የሚባሉበት ዋና ምክንያት የእናባቢነትንም ሆነ የተናባቢነትን ባህሪ ስለሚያሳዩ ነው:: ወደፊት እንደምናየው፣ እናባቢዎች የሚፈጠሩት ያለምንም አየር እገዳ ከናፍርንና ምላስን የተለያየ ቅርፅ በማስያዝ ብቻ ነው:: የከፍናቢዎችም አፈጣጠር እንደዚሁ ነው:: ለምሳሌ፣ [ኡ] የሚለው እናባቢ የሚፈጠረው ከንፈርን ሰብሰብ አድርጎ በማጥበብና ምላስን ወደ ሁዋላ ሽምቀቅ አድርጎ ወደ ትናጋ በማንሳት ነው:: የ[ው]ም አፈጣጠር ልክ እንደዚሁ ነው:: [ይ] ደግሞ ልክ [ኢ] እንደሚለው እናባቢ፣ ከንፈርን በመዘርጋትና የምላስን የፊት ክፍል ወደ የፊት ድድ አቅጣጫ በማንሳት የሚፈጠር ድምፅ ነው:: በከፍናቢዎቹና በእናባቢዎቹ መካከል ያለው ልዩነት የአፈጣጠር ነው:: ይኸውም የ[ኢ] እና [ኡ] አፈጣጠር ሙሉ በሙሉ የእናባቢ ሲሆን፣ የከፍናቢዎቹ ግን በተናባቢ ጀምሮ እጨራረሱ ላይ ወደ እናባቢ የሚያጋድል መሆኑ ነው:: ሁለቱም ከፍናቢዎች ነዛሪ ናቸው::

ይህ እንግዲህ የከፍናቢዎችን አፈጣጠር በተመለከተ ነው:: ስርጭታቸውን ስናይ ደግሞ ምድባቸው ከእናባቢዎች ጋር ሳይሆን፣ ከተናባቢዎች ጋር ሆኖ እናገኘዋለን:: ይኸውም እንደ ማንኛውም ተናባቢ፣ ከእናባቢ ጋር እንጅ ብቻቸውን በተናጠል ሊባሉ አለመቻላቸው ነው:: ይህም ማለት፣ ለምሳሌ እናባቢዎችን [አ፣ኡ፣ኢ፣ወዘተ፣] እያልን በተናጠል መጥራት እንደምንችል ሁሉ፣ ከፍናቢዎችን ግን በዚሁ አይነት መጥራት አንችልም ማለት ነው:: ርግጥ፣ [አ፣ኡ፣ኢ፣ ወዘተ፣] እንደምንል ሁሉ፣ [ዋ፣ዉ፣ዊ፣ ወዘተ ፣] ማለት እንችል የለም ወይ? የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል:: ይህ ትክክል ነው:: ነገር ግን [ዋ፣ዉ፣ዊ፣ ወዘተ፣] እያልን የምንጠራው እንደ [አ፣ኡ፣ኢ፣ ወዘተ፣] ያሉ ተራ ድምፆችን ሳይሆን፣ ቅንጅቶችን ነው:: [ዋ] የ[ው] እና የእናባቢው የ[አ] ፣ [ዉ]፣ የ[ው] እና የ[ኡ] እንደዚሁም [ዊ]፣ የ[ው] እና የ[ኢ] ቅንጅቶች ናቸው:: ባጭሩ እናባቢዎችን ከቅንጅት ውጭ በተናጠል ለማለት ሲቻል፣ ከፍናቢዎችን ግን ከቅንጅት ውጭ ለማለት ወይም ለመጥራት አይቻልም:: ከዚህ በመነሳት የሁለቱ፣ ማለትም የእናባቢዎችና የከፍናቢዎች፣ መሰረታዊ ልዩነት የአፈጣጠር ሳይሆን፣ የስርጭት ወይም የቅንጅት ነው፣ ለማለት ይቻላል:: ይኸውም ከፍናቢዎች አፈጣጠራቸው እንደ እናባቢ ሆኖ ሳለ፣ ስርጭታቸው እንደ ተናባቢ መሆኑ ነው:: ይኸውም ያለእናባቢ ሊነበቡ የማይችሉ በመሆናቸው ነው::

ቀደም ሲል በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ በሰባት መካነ ፍጥረት የተመለከቱት ተናባቢ ድምፆች፣ እንደ ተቀራራቢነታቸው፣ በአራት ክፍል ብቻ ሊጠቃለሉ ይችላሉ:: ይህም ከላይኛው ከንፈራችን ጀምሮ እስከ ማንቁርት ድረስ

ያለውን የላይኛውን የአፋችንን ክፍል የጫፍ፣ የፊት፣ የመሀልና የሁዋላ (ስር) ብሎ በአራት በመክፈልና በዚሁ መሰረትም ድምፆቹን እንደሚከተለው አድርጎ በመመደብ ነው፡፡

| ባህርየ ፍጥረት | ጫፍ | ፊት | መሀል | ሁዋላ |
|---|---|---|---|---|
| እግድ፡ ነ | ብ | ድ | ጅ | ግ ጕ |
| ኢ | ፕ | ት | ች | ክ ኵ ዕ |
| ፈ | ጵ | ጥ | ጭ | ቅ ቍ |
| ፍትግ፡ ነ | | ዝ | ዥ | |
| ኢ | ፍ | ስ | ሽ | ሀ |
| ፈ | | ፅ | | |
| ስርናዊ፡ | ም | ን | ኝ | |
| ጎናዊ፡ | | ል ር | | |
| ክፍናበ፡ | ው | | ይ | |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው፣ እግድና ፍግድ ድምፆች በአንድ ላይ ተጠቃለው በእግድ ስር ተመድበዋል፡፡ይህም ከባህርየ ፍጥረት መመሳሰል የተነሳ ነው፡፡ ፍግድ

ድምፆች የእግድነት ባህሪ ያሳያሉ፤ ክፍናቢ የሆነው [ው] የከናፍር ከሆኑት ጋር በአንድነት በጫፍ ስር ተመድቦአል፡፡ የድላንቃና የላንቃ ድምፆች በመሀለኛው፣ እንዲሁም የትናጋና የጉሮሮ ድምፆች በሁዋለኛው የአፋችን ክፍል ስር ተጠቃለዋል፡፡ እነዚህ አራት ክፍሎች፣ ወደፊት ከምናያቸው የምላስ የተለያዩ ክፍሎች ጋር ትይዩ ናቸው፡፡

ነው፡፡ ከእንቅስቃሴው አኳዋያም በሶስት ሊከፈል ይችላል፡፡ ክፍሎቹም ፊተኛ፣ መሀለኛና ሁዋለኛ ናቸው፡፡ ፊተኛ የሚባለው ከላይኛው የፊት ድድ ጋር ትይዩ የሆነውና ከድድ ጋር ንክኪ በመፍጠር ክፍ ሲል ፊተኛ ያልናቸውን ተናባቢዎች የሚፈጠረው ክፍል ነው፡፡ ሁዋለኛ የሚባለው ከትናጋ ጋር ትይዩ የሆነውና ሁዋለኛ ተናባቢ ያልናቸውን ድምፆች የሚፈጠረው ክፍል ነው፡፡ መሀለኛ የሚባለው ደግሞ በነዚህ በሁለቱ መካከል የሚገኘው ወይም የላንቃ ትይዩ የሆነው የምላስ ክፍል ሲሆን፣ እሱም መሀለኛ ያልናቸውን ተናባቢ ድምፆች የሚፈጥረው ነው፡፡ እያንዳንዱ ክፍል ራሱን ችሎ ለእሱ ተይዩ ወደሆነው ክፍል ሊንቀሳቀስ ይችላል፡፡ የሚንቀሳቀሰውም በእረፍት ላይ፣ ማለትም በማንነጋገርበት ጊዜ ከሚገኝበት ቦታና ሁኔታ ተነስቶ ወደ ፊት፣ ወደ መሀልና ወደ ሁዋላ በመነሳት ነው፡፡ እንደ ተንቀሳቃሹ የምላስ ክፍል አይነት፣ የሚፈጠረው ድምፅም እንደዚሁ የፊት፣ የመሀል ወይም የሁዋላ እናባቢ ወይም ተናባቢ ይባላል፡፡ በእንቅስቃሴው ምክንያት በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ አየር በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የሚታገድ ከሆነ፣ የሚፈጠሩት ድምፆች ተናባቢ ናቸው፡፡ እንቅስቃሴው አየር የማያግድ ከሆነ፣ የሚፈጠሩት ድምፆች እናባቢ ናቸው፡፡

ከዚህ እንፃር ያለምንም አየር እገዳ የሚፈጠሩትና ከላይ የተዘረዘሩት ሰባት እናባቢ ድምፆች እንደሚከተለው ሆነው በሶስት ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ይህም ቀደም ሲል በአፍ ውስጥ በምላስ አማካኝነት ይፈጠራሉ ካልናቸው ተናባቢ ድምፆች አመዳደብ ጋር አንድ ነው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፊተኛ | ኢ | ኤ | |
| መሀለኛ | እ | ኧ | ኣ |
| ሁዋለኛ | ኡ | ኦ | |

እንደዚሁም ተንቀሳቃሹ የምላስ ክፍል እንደሚገኝበት ከፍታ ወይም ዝቅታ መጠን፣ እነዚሁ እናባቢዎች ላየኛ፣ ልከኛ እና ታችኛ ተብለው እንደገና በሶስት እንደሚከተለው ይመደባሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ላየኛ | ኢ | እ | ኡ |
| ልከኛ | ኤ | ኧ | ኦ |
| ታችኛ | | ኣ | |

እነዚህን ሁለት አይነት አከፋፈሎች እንደሚከተለው አድርጎ በአንድ ማዕቀፍ አጠቃሎ ማሳየት ይቻላል፡፡

| ባህርየ ፍጥረት | ጫፍ | ፊት | መሀል | ሁዋላ |
|---|---|---|---|---|
| እግድ፣ ነ | ብ | ድ | ጅ | ግ ጕ |
| አ | ፕ | ት | ች | ክ ኵ ዕ |
| ፊ | ጵ | ጥ | ጭ | ቅ ቍ |
| ፍትግ፣ ነ | | ዝ | ዥ | |
| አ | ፍ | ስ | ሽ | ህ |
| ፊ | | ፅ | | |
| ሰርናዊ፣ | ም | ን | ኝ | |
| ጎናዊ፣ ሳሽ፣ | | ል ር | | |
| ከፍናቢ፣ | ው | | ይ | |




የአማርኛ ፎኒሞች

ለትርጉምም ሆነ ለሰርዓተ ፅሀፈት መሰረት ሊሆኑ የሚገባቸው ድምፆች እነዚህ ብቻ ናቸው:: ይሁን እንጅ ስርዓተ ፅሀፈታችን በነዚህ ድምፆች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በግዕዝ

ከዚህ አኩዋያ እስካሁን የተመለከትናቸው አናባቢም ሆኑ ተናባቢ ድምፆች ትርጉም-ለዪ ስለሆኑ፣ በሙሉ ፎኒሞች ናቸው፡፡ ትርጉም ለይነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ከላይ እንደተጠቀሱት ያሉና በአንድ ድምፅ ብቻ የሚለያዩ ጥንድ ጥንድ ቃላትን እየፈለጉ ትርጉማቸውን ማነፃፀር ያስፈልጋል፡፡ እዚህ ላይ በዚህ አይነት የሁሉንም ድምፆች ፎኒማዊነት ማሳየት ጊዜ-ፈጅ ስለሆነ፣ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ብቻ እናቀርባለን፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| [ከአርኣር] | ከራር | [ብኧልልኣ] | በላ | [እድድአር] | አድር | 2 |
| [ግአርኣር] | ግራር | [ብአልልኣ] | ባላ | [እድድአል] | አድል | |

እነዚህ ጥንድ ጥንድ ቃላት የሚለያዩት ባንዳንድ ትይዩ ድምፆች ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያው ጥንድ መነሻ ላይ ትይዩ ሆነው በገቡት በ[ግ] እና በ[ከ]፤ የሚቀጥለው ጥንድ፣ መካከል ላይ በሚገኙት በ[ኧ] እና በ[አ]፣ እንደዚሁም የመጨረሻው ጥንድ፣ መጨረሻ ላይ በሚገኙት በ[ል] እና በ[ር] ነው፡፡ በትይዩዎቹ ድምፆቹ ልዩነት ምክንያት፣ ቃላቱ የተለያየ ትርጉም ሊይዙ ችለዋል፡፡ ስለዚህም ለየጥንዱ ቃላት የትርጉም ልዩነት መንስዔ የሆኑት ድምፆች፣ ማለትም /ከ፣ግ፣ኧ፣አ፣ል፣እና ር/ፎኒሞች ናቸው፡፡ ከዚህ ላይ ግን ፎኒሞቹ የሚገኙበት ቦታ ትይዩ መሆኑን እንደገና ማጤን ያስፈልጋል፡፡ የሚገኙበት ቦታ ትይዩ ካልሆነ፣ ፎኒምነታቸውን በርግጠኝነት ለመናገር ያዳግታል፡፡

ፎኒሞች ረቂቅ ናቸው፡፡ ስለሆኑም አዕምሮአዊ እንጅ አካላዊ ገፅታ የላቸውም፡፡ አካላዊ ገፅታ የሚኖራቸው በእንደበት አካላት እየተፈጠሩ ሲወጡና በጆሮም ሲሰሙ ነው፡፡ እንደበታዊ አፈጣጠራቸው ደግሞ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ የተለያየ ነው፡፡ ስለዚህም አንድ ፎኒም የተለያየ አካላዊ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ብኣት/ | [ብኣት] | ባት | 3 |
| /ልኣብ/ | [ልኣብ] | ላብ | |

በነዚህ ቃላት ውስጥ የሚገኘው [ብ] የተለያየ *ንበት* አለው፡፡ ይኸውም ላብ ([ልኣብ]) በሚለው ቃል መድረሻ ላይ የሚገኘው፣ ልል [ብ] ሲሆን፣ ባት ([ብኣት]) በሚለው መነሻ ላይ የሚገኘው [ብ] ልል አለመሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፤ ባት በሚለው መነሻ ላይ ያለውን [ብ] አላልተን፣ ላብ በሚለው መጨረሻ ላይ የሚገኘውን ደግሞ አጥብቀን ብንጠራው፣ ቃሉ ትርጉሙን አይቀይርም፡፡ የሁለቱ ድምፆች መቀያየር የንበት እንጅ የትርጉም ለውጥ አያስከትልም ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ፣ ሁለቱ ድምፆች የአንድ አዕምሮአዊ ፎኒም የተለያዩ አካላዊ ገፅታዎች ወይም ክሳቾች እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ አዕምሮአዊ የሆነው አንድ ፎኒም አካላዊ ሆኖ ከአንደበት በሚወጣበት ጊዜ፣ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቅርፅ ሲያሳይ ይችላል፡፡ እነዚህ የተለያዩ አካላዊ ቅርፆች *ዘረ-ፎኒም*

## አቀነጃጀት

ቀደም ሲል በአይነት በአይነት ያስቀመጥናቸው ድምፆች፣ ካሁን በፊት እንደተገለፀው፣ ተናጠላዊና ቅንጅታዊ ባህሪ አላቸው፡፡ ባለፈው ንዑስ ክፍል ለማሳየት የሞከርነው ተናጠላዊ ባህሪያቸውን ነበር፡፡ ይኸውም እያንዳንዱ ድምፅ የትና እንዴት እንደሚፈጠር እናም አንዱ ከሌላው በምን እንደሚለይ በማሳየት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ የእያንዳንዱን ድምፅ ቅንጅታዊ ባህሪ ለማሳየት እንሞክራለን፡፡ ቅንጅታዊ ባህሪ ስንል፣ አንድ ድምፅ ከሌላ ድምፅ ወይም ድምፆች ጋር ሲሰለፍ፣ የሚይዘው ቦታና በዚያ ቦታ በመገኘቱም በራሱ ወይም በጎረቤቱ፣ ማለትም አብሮት በሚሰለፈው ድምፅ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ ማለታችን ነው፡፡ በለውጡ ምክንያት ፎኒሞች በተለያየ ቦታ፣ ማለትም አቀነጃጀት፣ የተለያየ ገፅታ ወይም መልክ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ የአንድ ፎኒም የተለያዩ ገፅታዎችም ዘረ ፎኒም እንደሚባሉ ከፍ ሲል ገልፀናል፡፡ ፎኒሞቹ በእዝባር (//) ውስጥ ሲፃፉ፣ ዘረ-ፎኒሞች በማዕዘን ቅንፍ ([ ]) ውስጥ እንደሚፃፉም አሳይተናል፡፡ ይህም አስማቀፋዊ የሆነ ስነ-ልሳናዊ የአፃፃፍ ስርዓት ነው፡፡

ከአሰላለፍ የሚመጣን ባህሪ በወጉ ለማየት፣ *መጀመሪያ ምን ፎኒም ከምን ሌላ ፎኒም ወይም ፎኒሞች ጋር ሊሰለፍ ይችላል?* የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይኖርብናል፡፡ ከዚህ አንፃር፣ ቀደም ሲል የተዘረዘሩት አናባቢና ተናባቢ ፎኒሞች እያንዳንዳቸው ከሌላ ፎኒም ጋር ሊሰለፉ፣ የሰልፉ *መጀመሪያ* (ከግራ ወደቀኝ) ወይም *መጨረሻ* የመሆን እድል አላቸው ብሎ፣ መነሳት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ተናባቢ ያልናቸውን ፎኒሞች ስርጭት ብንመለከት፣ ከአንዱ በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ በቃል መነሻ ላይ ሊገኙ፣ ማለትም የሰልፉ የመጀመሪያ ድምፅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ቦታ ላይ የማይገኘው /ኽ/ ብቻ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ፎኒም የሚጀምር የአማርኛ ቃል የለም፡፡ አስቲ ያስቡ፡፡

ከአናባቢዎች መካከል ደግሞ በመነሻ ሊገኙ የሚችሉት /እ፣ ኧ እና አ/ ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህም መሀለኛ አናባቢ ያልናቸው ናቸው፡፡ ሌሎቹ፣ ማለትም ዳረኞቹ፣ በቃል መነሻ ላይ አይገኙም፡፡ ስለዚህም በእነሱ የሚጀምር የአማርኛ ቃል ያለ አይመስልም፡፡ ርግጥ፣ እንደ <u>ኢየሱስ</u> ያሉ የውጭ ስሞች አሉ፡፡ ይሁን እንጅ ተወላጅ የአማርኛ ተናጋሪ እንደነዚህ ያሉትን ስሞች <u>እየሱስ</u> እንጅ፣ <u>ኢየሱስ</u> እያለ አይጠራም፡፡ ዳረኛውን /ኢ/ በመሀለኛው /እ/ ይተካዋል፡፡ የቋዋንቋዋው የአናባቢዎች የአገባብ ስርዓት አይፈቅድለትማ፡፡

እንግዲህ ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ከ/ኽ/ እና ከዳረኛ አናባቢዎች በስተቀር ማንኛውም ፎኒም በመነሻ ሊገኝ ከቻለ፣ ከዚያ ፎኒም ቀጥሎ ሊሰለፍ የሚችለው ፎኒም ምንድን ነው? የሚል ሌላ ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሰረቱ የመጀመሪያው ተሰላፊ ተናባቢ ከሆነ፣ ከእሱ ቀጥሎ የሚገባው አናባቢ ብቻ ነው፡፡ የመጀመሪያው ተሰላፊ አናባቢ ከሆነ ደግሞ፣ ከሱ ቀጥሎ ሊመጣ

የሚችለው አንድ ወይም ሁለት ተናባቢ ፎኒም ብቻ ነው፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

ተአ ምሳሌ፡

(ሀ) /ንእ/ ና 1

ተእ (ለ) /እፍ/ እፍ

በምሳሌ (ሀ) አካሄድ ብንቀጥል፣ ካናባቢው ቀጥለን አንድም የተለያዩ ሁለት ተናባቢዎችን ወይም አንድ ረዥም (ጥብቅ) ተናባቢን ብቻ ልናገኝ እንችላለን፡፡ ረዥም ተናባቢን ፊደሉን ደግመን በመፃፍ እናመለክታለን፡፡ ለላቀነጃጀቱ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

አተተ ምሳሌ፡
1 2

(ሀ) /እንድ/ 2

(ለ) /እምድ/

(መ) /እስም/

ከምሳሌ (2) እንደምንረዳው፣ ተከታትለው ከሚገቡት ሁለት ተናባቢዎች መካከል የመጀመሪያው *ቀጣይ* መሆን አለበት፡፡ ሁለተኛው ቀጣይ ወይም እግድ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ አገባብ ሊፋለስ አይችልም፡፡ ከተፋለለ፣ ማለትም እግዱ ቀድሞ ቀጣዩ ተናባቢ ከተከተለ፣ በመካከላቸው [እ] የሚለው አናባቢ ይገባል፡፡ ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) [ብእርቅ] 3

(ለ) [ፍእቅእር[

በቅንፍ ውስጥ ከሚታየው አፃፃፍ እንደምንረዳው፣ በምሳሌ 3(ሀ)፣ /ር/ እና /ቅ/ ሊከታተሉ እንደሚችሉ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ ግን /ቅ/ እና /ር/ ሊከታተሉ እንደማይችሉ እንመለከታለን፡፡ ይህም በመሆኑ፣ [እ] በመካከላቸው ሊገባ ችሉአል፡፡ አንድ ረዥም ተናባቢ የሚገኝባቸው ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

አተተ ምሳሌ፡
1 1

(ሀ) /እጥጥ/ እጥ 4

(ለ) /እክክ/ እክ

ተእተ ምሳሌ፡

(ሀ) /ልእት/ ላት 5

(ለ) /ብእት/ ባት

(መ) /ስእር/ ሳር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| (መ) | /ግአምምአ/ | ጋማ | (ሰ) | /ክአብብአ/ | ካባ |
| | /ግአምአ/ | ጋማ | | /ክአብአ/ | ካባ |

በየጥንዱ ውስጥ ያሉት ቃላት ትርጉም የሚለያየው በየመካከላቸው በሚገኘው ተናባቢ ድምፅ መርዘም ወይም አለመርዘም ምክንያት ነው። ይኸውም፣ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ የ[ን]፣ በምሳሌ (ለ) የ[ል]፣ በምሳሌ (መ) የ[ም]፣ እንዲሁም በምሳሌ (ሰ) የ[ብ] ድምፅ መርዘምና አለመርዘም ነው። ሁኔታው የሚያሳየው፣ ርዝመት ወይም ጥብቀት ትርጉም-ለዩ መሆኑን ነው። ሁለት ቃላት በሁለት ትይዩ ፎኒሞች መለያየት ብቻ የተለያየ ትርጉም ሊኖራቸው እንደሚችል ሁሉ፣ በአንድ ፎኒም ማጠርና መርዘም ምክንያትም እንደዚሁ የተለያየ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። ስርዓተ ፅሀፈታችን ከላይ በምሳሌዎቹ እንዳሳየነው የየድምፁን ፊደላዊ ምልክት ደግሞ በመፃፍ ርዝመትን ማሳየት ሲችል፣ ይህን ባለማድረጉ ጉዳዩ እንደ ችግር ሊቆጠር ኖሮአል[11]።

ወደተነሳንበት የቅንጅት ጉዳይ እንመለስ። በቃል መካከል ሊገኙ የሚችሉት ሁለት የተለያዩ ተናባቢዎች ወይም የአንድ ረዥም ተናባቢ ብቻ ነው። ሶስተኛ ተናባቢ ከተገኘ፣ ከሱ በፊት [እ] የሚለው አናባቢ ሰርጎ ይገባና ሶስተኛውን ተናባቢ ከቀዳሚዎቹ ተናባቢዎች ይለየዋል። ይህንን በሚቀጥለው ክፍል እናየዋለን።

## *ቀለም*

ከፍ ሲል በተመለከትነው ሁኔታ፣ ፎኒሞች ሲቀናጁ የሚፈጥሩት አካል ቀለም[12] ይባላል። ትርጉም ሊኖረው ወይም ላይኖረውም ይችላል። ቀለም የሚያስገኘው አንድ አናባቢ ብቻውን ወይም ከተናባቢ(ዎች) ጋር ሆኖ አንድ ቅንጅታዊ አካል መፍጠሩ ነው። ለምሳሌ፣ ሳሙና [ስኣምኡንኣ] የሚለውን ቃል እንመልከት።

[11] ምልክቱን እየደገሙ መፃፉ ራሱን የቻለ ጣጣ አለው። አንዱ እየደገመ የሚፅፈውን ሌላው እየነጠለ ሊፅፈው ይችላል። በላቲኑ አፃፃፍ የሚታየው ዋናው ችግር ይህ ነው። ርምጃው የፅሀፈት ትምህርትን ከባድ የሚያደርግ ነው። ዝርዝሩን በተመለከተ ባየ (1984)ን እና ባየ እና ቲም 89 (1989)ን ይመልከቱ።

[12] እዚህ ላይ ቀለም የምንለው በስርዓተ ፅሀፈታችን ውስጥ ቀለም ከምንለው የተለየ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ ልጅ ፊደል ቆጥሮ ሲጨርስ፣ ቀለም ለየ ይባላል። በዚህ አገባብ፣ ቃሉ የየፊደሉን ልዩ ምልክት ያመለክታል። እያንዳንዱ ምልክት ደግሞ የአንድ ተናባቢንና የአንድ አናባቢን ድምፅ ቅንጅት ባንድ ላይ ስለሚወክል፣ እኛ እዚህ ላይ <u>ቀለም</u> ከምንለው ጋር ይመሳሰላል። ይሁን እንጅ፣ እኛ ቀ<u>ለ</u>ም የምንለው፣ በውስጡ ከአንድ ተናባቢ በላይ ስለሚይዝና ትርጉምም ሊኖረው ስለሚችል፣ ከስርዓተ ፅሀፈቱ ቀ<u>ለ</u>ም ይለያል። ሁለቱን ቀለሞች ስርዓተ ፅሀፈታዊና ስርዓተ ድምፃዊ ብሎ መለየት ይቻላል። ሁለቱም <u>ምት</u> ስላላቸው፣ በስርዓተ ግጥም ለየስንኙ ቤት መምቻ እየሆኑ ያገለግላሉ። ለዝርዝሩ መንግስቱ (1963)ን፣ ደረጀ (1975)ን፣ ባየ እና ቲም (89) (1989)ን፣ ተሾመ (1997)ን፣ እንዲሁም ብርሀኑ (2000)ን ይምልከቱ።

ቃሉ [ሰእ - ምኡ - ንእ] የሚሉትን ሶስት ቀለሞች ይዞአል፡፡ የየቀለሙ አቀነጃጀት [ተእ-ተኡ-ተእ]፣ ማለትም ተናባቢ - አናባቢ - ተናባቢ - አናባቢ እያለ የሚሄድ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቀለም ትርጉም የለውም፡፡ ትርጉም ያለው የቀለሞቹ ቅንጅት የሆነው ሳሙና [ሰእምኡንእ] የሚለው ቅርፅ ነው፡፡ እንደዚህ ያለው ትርጉም-አዘል ቀለም *ምዕላድ* ይባላል፡፡ ዝርዝር ባህሪውን በምዕራፍ ሁለት ስለምንመለከተው፣ ከዚህ ላይ ከስሙ ጋር ብቻ እንተዋወቅ፡፡

ምዕላዶች በውስጣቸው ባለው የቀለም መጠን መሰረት ባለ አንድ፣ ባለ ሁለት፣ ባለ ሶስት፣ ወዘተ፣ ቀለም ምዕላድ እየተባሉ ይለያሉ፡፡ ለምሳሌ፡ እንደ ሳሙና ያሉት ባለ ሶስት፣ እንደ ሰባ [ሰእብእ] ያሉት ባለ ሁለት፣ እንደ ና [ንእ] ያሉት ደግሞ ባለ አንድ ቀለም ምዕላዶች ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት እንደ ና [ንእ] ያሉት ተራ፣ እንደ ሳሙና [ሰእምኡንእ] ያሉት ደግሞ ውስብስብ ቀለሞች ይባላሉ፡፡ የህፃናት የቋንቋዋ *ልምደት* የሚጀምረው በተራ፣ ማለትም በባለ አንድ ቀለም ምዕላዶች ነው፡፡ የንባብ ትምህርትም እንደዚሁ፡፡

በአንድ ቀለም ውስጥ የሚገኙ ድምፆች *በተናጠላዊ* ቅደም-ተከተል ብቻ የሚደረደሩ ሳይሆኑ፣ *በተዋረዳዊ* አቀማመጥም እየተዋቀሩ አንድ አካል የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ የመዋቅሩ ምሰሶ አናባቢው ድምፅ ነው፡፡ ያለሱ መዋቅሩ ሊቆም አይችልም፡፡ እሱ ግን ብቻውን አለያም ከአንድ ቀዳሚ ወይም ተከታይ ተናባቢ ጋር ሆኖ፣ የመዋቅሩን አንድ ክፍል ወይም ርከን ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይህ ክፍል ደግሞ እንደዚሁ ብቻውን ወይም ከአንድ ቀዳሚ ተናባቢ ድምፅ ጋር ሆኖ፣ አጠቃላዩን ቀለማዊ መዋቅር ይፈጥራል፡፡ ያወቃቀሩን ዝርዝር ስርዓት በ*ዕፀ-መዋቅር* እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡




ከታች ወደ ላይ ብንመለከት፣ የመዋቅሩ ምሰሶ የሆነው አናባቢ (እ) ብቻውን ቆሞ የመዋቅሩን *ማዕከል* (ማ)ን መስርቶአል፡፡ ይህ ማዕከል ደግሞ ከጨራሹ (ጨ) ተናባቢ ድመፅ ጋር ሆኖ፣ የቀለሙን *ምት* መስርቶአል፡፡ ምቱም በተራው ከከፋቹ (ከ) ተናባቢ ጋር ሆኖ፡ አጠቃላዩን ቀለም አዋቅሮአል፡፡ በሌላ አነጋገር [እ] ማዕከሉን፣ ማዕከሉና ጨራሹ ተናባቢ [ም] ምቱን፣ ምቱና ከፋቹ ተናባቢ (ል) ቀለሙን መስርተዋል፡፡ ከፋቹና ጨራሹ ተናባቢዎች ለመዋቅሩ የአናባቢውን

ያህል አስፈላጊ አይደሉም። ስለዚህም ሊቀሩ ይችላሉ። በዚህን ጊዜ ያለነሱ የሚዋቀረው ቀለም አናባቢውን ምሰሶ ብቻ ይዞ ይቆማል። ለምሳሌ፣ እሳ የሚለውን ምዕላድ ብንመለከት፣ በውስጡ ሁለት ቀለሞች እንዳሉት እንገነዘባለን። እነሱም [እ-] እና [- ስእ] ናቸው። የመጀመሪያው ቀለም ከአናባቢው ምሰሶ ላይ ብቻ የተመሰረተ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከምሰሶው እና ከጨራሹ ተናባቢ ብቻ የተዋቀረ ነው። የሁለቱን ቀለሞች አወቃቀር እንደሚከተለው በዕፀ መዋቅር እናሳያለን።

2




በግልፅ እንደሚታየው፣ የመጀመሪያው ቀለም ከምሰሶው፣ ማለትም ከአናባቢው ብቻ የተዋቀረ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከከፋችና ከአናባቢው ምሰሶ ጋር የተዋቀረ ነው። ሁለቱ ቀለሞች ርስበርስ ተዋቅረው ምዕላዱን መስርተዋል።

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም በባለብዙ ቀለም ምዕላድ ውስጥ የየቀለሙን ድንበር መለየት የሚቻለው እንዴት ነው? ለምሳሌ፣ ከላይ በተሰጠው ምዕላድ ውስጥ /ስ/ የተዋቀረው ከሁለተኛው ቀለም አናባቢ ጋር ነው። ከመጀመሪያው ቀለም አናባቢ ጋር አዋቅረን ቀለሞቹ /እስ-/ እና /-እ/ ናቸው፣ ለማለት አንችልም ወይ? የሚል ነው። ጥያቄው ተገቢ ነው። የትኛው ተናባቢ ከየትኛው አናባቢ ጋር እንደሚዋቀር የሚጠይቅ ነው። ስለዚህም በማንኛውም ቋንቋ፣ በባለ ብዙም ይሁን በባለ ተራ ቀለም ውስጥ ያለውን ያወቃቀር ስርዓት እንደሚከተለው እናቀርባለን።

(ሀ) መጀመሪያ ለቀለማዊ መዋቅር አይቀሬ የሆነው ክፍል አናባቢ ስለሆነ፣ እሱን ለይተን እናወጣለን፣

(ለ) ያወጣነውን አናባቢ፣ በግራው በኩል ከሚገኝ አንድ ተናባቢ ድምፅ ጋር እናቀናጀዋለን፤

(መ) በሶስተኛ ደረጃ ይህንኑ አናባቢ በቀኙ በኩል ከሚገኝ አንድ ሌላ ተናባቢ ጋር እናቀናጀዋለን፤

(ሰ) ይህንን አድርገን ስንጨርስ፡ ያልተቀናጀ (ተራፊ) ተናባቢ ካለ፣ ይህን ተናባቢ ከአናባቢው ቀኝ ጎን ከሚገኘው ጨራሽ ተናባቢ ጋር እናዳብለዋለን፡፡

በዚሁ ስርዓት መሰረት ለአብነት *ለላነጋገርናቸውም* የሚለውን ቃል እንውሰድና ቀለማዊ አወቃቀሩን እንመልከት፡፡

*መጀመሪያ ቃሉን በፎኒማዊ አፃፃፍ* እንደሚከተለው እንፅፈዋለን፡፡ ከዚያ በሁዋላ አናባቢዎቹን እየመረጥን፣ አናታቸው ላይ መስመር በማቆም እንደሚከተለው እንለያቸዋልን፡፡

(ሀ) አ ል አ ን ን ኧ ግ አ ግ ግ ኧ ር ን አ ች ች ኧ ው ም 3

ከዚህ ቀጥለን እነዚህን አናባቢዎች በየግራ ጎናቸው በኩል ካለው ተናባቢ ጋር እንደሚከተለው እናያይዛቸዋለን፡፡

(ለ) አ ል አ ን ን ኧ ግ አ ግ ግ ኧ ር ን አ ች ች ኧ ው ም 4

አሁን ደግሞ እነዚህኑ አናባቢዎች በየቀኝ ጎናቸው በኩል ካለው ተናባቢ ጋር እንደሚከተለው አናገናኛቸዋለን፡፡

(መ) 5

አ ል አ ን ን ኧ ግ አ ግ ግ ኧ ር ን አ ች ች ኧ ው ም

ይህን ካደረግን በሁዋላ የሚተርፍ ተናባቢ ቢኖር፣ በቀኝ ጎኑ በኩል ካለው ሌላ ተናባቢ ጋር እናገናኘዋለን፡፡ በዚህም መሰረት በቃሉ መጨረሻ ላይ የምትገኘው /ም/፣ ቀድሞአት ከሚገኘው ከ/ው/ ጋር ትያያዛለች፡፡ በዚህ አካሄድ የቃሉ ቀለሞች የሚከተሉትን ይመስላሉ ፡፡

6

(ሰ) 1 2 3 4 5 6 7

አ ል አ ን ን ኧ ግ አ ግ ግ ኧ ር ን አ ች ች ኧ ው ም

በመጨረሻ የቃሉ ቀለሞች /እ - ልእን -ንሽ - ግእግ -ግሽር -ንእች - ችኧውም/ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ቃሉ ባለ ሰባት ቀለም ስለሆነ፣ ውስብስብ ነው፡፡ የእወቃቀሩ ስርዓት የአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የማንኛውም ቋንቋዋ ነው፡. ስርዓቱን በትክክል ከተከተልን፡ የቱ ተናባቢ ከየቱ አናባቢ ጋር መዋቀር እንዳለበት በቀላሉ እንረዳለን፡፡ ሰባተኛው ቀለም ሁለት ጨራሺ ተናባቢዎች አሉት፡፡ ይሁን እንጅ ከነዚህ ተናባቢዎች ቀጥሎ አንድ አናባቢ ለምሳሌ፡ /እ/ ቢገባ፣ ከሁለቱ ጨራሺ ተናባቢዎች፡ የመጨረሻው፣ ማለትም /ም/፣ ከዚህ አናባቢ ጋር ይዋቀርና /ምእ/ የሚል ስምንተኛ ቀለም ይፈጥራል፡፡ ይህ ሲሆን፣ ሰባተኛው ቀለም አንድ ጨራሺ ተናባቢ ብቻ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አካሄድ፣ የአማርኛ መደበኛ ወይም አይነተኛ የቀለም እወቃቀር፣ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደሚታየው፣ /ተእተ/ የሚል ስርዓት እንደሚከተል ያሳያል፡፡

ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ የሚዋቀሩ ቀለሞች ዝግና ክፍት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ዝግ የሚባሉት ጨራሽ ተናባቢ ያላቸው ሲሆኑ፣ ክፍት የሚባሉት ጨራሽ የሌላቸው ናቸው፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር (6) ከተመለከቱት ሰባት ቀለሞች ውስጥ የመጀመሪያውና ስለተኛው ብቻ ክፍት ናቸው፡፡

ፎኒሞች ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ቀለምን ለመፍጠር ሲዋቀሩ ርስበርስ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በራሳቸው ላይ የተለያዩ ለውጦች ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ለውጡን የሚያስከትሉት ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶች ይባላሉ፡፡ የለውጡን ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## *ድምፀ ልሳናዊ ሂደት*

ከፍ ሲል ወደ ተነሳንበት የፎኒሞች ቅንጅት እንደገና እንመለስና በአቀነጃጀቱ ምክንያት ፎኒሞቹ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በተቃናጅ ፎኒሞች ላይ ስለሚደርሰው ለውጥ እንወያይ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ከሁለት ቃላት ጋር እንተዋወቅ፡፡ እነዚህም _ላዕላይ_ እና _ታህታይ_ የሚሉት ናቸው፡፡ በውይይታችን ላይ እየደጋገሙ ስለሚመጡ፣ ከወዲሁ ግልፅ ሊሆኑልን ይገባል፡፡ ላዕላይ ማለት እንደበታዊ፣ ማለትም ከአንደበት የሚወጣና በጆሮ የሚሰማ ማለት ነው፡፡ ታህታይ ደግሞ አዕምሮአዊ፣ ማለትም በአዕምሮአችን ብቻ የሚለማንና የምናውቀው፣ ግን በአንደበታችን የማናወጣው፣ ማለት ነው፡፡ አዕምሮአዊ የሆነ ነገር ረቂቅ ሲሆን፣ አንበደበታዊ የሆነ ደግሞ ግዘፍ ነው፤ እንደ ምላስ ባለ ግዘፍ የአንደበት አካል ስለሚፈጠርና በጆሮም ስለሚሰማ፡፡ ፎኒሞች አዕምሮአዊ ለለዚህም ረቂቅ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ አካላዊ፣ ማለትም አንደበታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም የሚሆነው በንግግር ጊዜ ከአዕምሮ ወጥተው በአንደበት አካላት አማካኝነት ሲፈጠሩ ወይም ሲገዝፉ ነው፡፡ እያንዳንዱ ፎኒም በአዕምሮ ውስጥ ረቂቅ የሆነ ገፅታ ሲኖረው፣ በአንደበት አማካኝነት በመካነ ፍጥረት ላይ በሚፈጠርበት ጊዜ አካላዊ የሆነ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ፎኒም ቢያንስ አንድ አካላዊ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ልዩነት በመነሳት፡

በመጨረሻ የቃሉ ቀለሞች /እ - ልእን -ንኽ - ግእግ -ግኽር -ንእች - ችኽውም/ መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ ቃሉ ባለ ለባት ቀለም ለለሆነ፣ ውስብስብ ነው፡፡ የአወቃቀሩ ስርዓት የአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የማንኛውም ቋዋንቋዋ ነው. ስርዓቱን በትክክል ከተከተልን፣ የቱ ተናባቢ ከየቱ አናባቢ ጋር መዋቀር እንዳለበት በቀላሉ እንረዳለን፡፡ ሰባተኛው ቀለም ሁለት ጨራሺ ተናባቢዎች አሉት፡፡ ይሁን እንጅ ከነዚህ ተናባቢዎች ቀጥሎ አንድ አናባቢ ለምሳሌ፣ /እ/ ቢገባ፣ ከሁለቱ ጨራሺ ተናባቢዎች፣ የመጨረሻው፣ ማለትም /ም/፣ ከዚህ አናባቢ ጋር ይዋቀርና /ምእ/ የሚል ስምንተኛ ቀለም ይፈጥራል፡፡ ይህ ሲሆን፣ ሰባተኛው ቀለም አንድ ጨራሺ ተናባቢ ብቻ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አካሄድ፣ የአማርኛ መደበኛ ወይም አይነተኛ የቀለም አወቃቀር፣ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደሚታየው፣ /ተእተ/ የሚል ስርዓት እንደሚከተል ያሳያል፡፡

ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ የሚዋቀሩ ቀለሞች ዝግና ክፍት ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ዝግ የሚባሉት ጨራሽ ተናባቢ ያላቸው ሲሆኑ፣ ክፍት የሚባሉት ጨራሽ የሌላቸው ናቸው፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር (6) ከተመለከቱት ሰባት ቀለሞች ውስጥ የመጀመሪያውና ስስተኛው ብቻ ክፍት ናቸው፡፡

ፎኒሞች ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ቀለምን ለመፍጠር ሲዋቀሩ ርስበርስ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በራሳቸው ላይ የተለያዩ ለውጦች ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ለውጡን የሚያስከትሉት ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶች ይባላሉ፡፡ የለውጡን ዝርዝር ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## *ድምፀ ልሳናዊ ሂደት*

ከፍ ሲል ወደ ተነሳንበት የፎኒሞች ቅንጅት እንደገና እንመለስና በአቀነጃጀቱ ምክንያት ፎኒሞቹ ከሚፈጥሩት ጉርብትና የተነሳ በተቃናጅ ፎኒሞች ላይ ስለሚደርሰው ለውጥ እንወያይ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ከሁለት ቃላት ጋር እንተዋወቅ፡፡ እነዚህም _ላዕላይ_ እና _ታህታይ_ የሚሉት ናቸው፡፡ በውይይታችን ላይ እየደጋገሙ ስለሚመጡ፣ ከወዲሁ ግልፅ ሊሆኑልን ይገባል፡፡ ላዕላይ ማለት እንደበታዊ፣ ማለትም ከአንደበት የሚወጣና በጆሮ የሚሰማ ማለት ነው፡፡ ታህታይ ደግሞ አዕምሮአዊ፣ ማለትም በአዕምሮአችን ብቻ የሚሰማንና የምናውቀው፣ ግን በአንደበታችን የማናወጣው፣ ማለት ነው፡፡ አዕምሮአዊ የሆነ ነገር ረቂቅ ሲሆን፣ አንበደበታዊ የሆነ ደግሞ ግዙፍ ነው፤ እንደ ምሳለ ባለ ግዙፍ የአንደበት አካል ስለሚፈጠርና በጆሮም ስለሚሰማ፡፡ ፎኒሞች አዕምሮአዊ ስለዚህም ረቂቅ ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ አካላዊ፣ ማለትም እንደበታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም የሚሆነው በንግግር ጊዜ ከአዕምሮ ወጥተው በአንደበት አካላት አማካኝነት ሊፈጠሩ ወይም ሲገዘፉ ነው፡፡ እያንዳንዱ ፎኒም በአዕምሮ ውስጥ ረቂቅ የሆነ ገፅታ ሲኖረው፣ በአንደበት አማካኝነት በመካነ ፍጥረት ላይ በሚፈጠርበት ጊዜ አካላዊ የሆነ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ፎኒም ቢያንስ አንድ አካላዊ ገፅታ ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ልዩነት በመነሳት፣

አዕምሮአዊ ገፅታውን ታህታይ፣ አካላዊ ገፅታውን ላዕላይ እያልን እንጠራዋለን፡፡ ይህ በፎኒም ብቻ ሳይሆን፣ ወደፊት እንደምናየው፤ በምዕላድ፣ በቃላት፣ በሀረጋትና በአረፍተ ነገር አወቃቀር ላይም የሚታይ አጠቃላይ የቋንቋዎ ባህሪ ነው[13]፡፡

ፎኒሞች ቀለማትን ለመመስረት ርስበርስ ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ቅርፅ ታህታይ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ማንኛውም ፎኒም አንድ ቅርፅ ብቻ አለው፡፡ ይህ ቅርፅ ከአንደበት በሚወጣበት፣ ማለትም በንግግር ጊዜ በአንደበት አካላት ሲፈጠር፣ መልኩ በከፊል ወይም በሙሉ ሲለወጥ ይችላል፡፡ ስለዚህም ከአንድ በላይ የሆኑ አንደበታዊ (ላዕላይ) ቅርፆች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም የተለያዩ ቅርፆች ዘረ ፎኒም እንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ የለውጡ መንስዔ አንዱ ፎኒም ከሚቀድመው ወይም ከሚከተለው ሌላ ፎኒም ጋር የሚፈጥረው ጉርብትና እና ይህም የሚያስከትለው ንክኪ ብሎም የባህሪ መወራረስ ሂደት ነው፡፡ ሁለቱን ቅርፆች ለመለየት ላዕላዩን በቅንፍ፣ ታህታዩን በዕዝባር ውስጥ እንፅፈዋለን፡፡ የታህታዊው አፃፃፍ ፎኒማዊ ሲባል፣ የላዕላዊው ዘረ ፎኒማዊ ወይም ንበታዊ ይባላል፡፡ ይህንም ቀደም ሲል በመጠኑም ቢሆን አይተነዋል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ሁኔታውን <u>በርቺ</u> የሚለውን ቃል አንውሰድና እንደገና በምሳሌ አንረዳው፡፡ የቃሉ ስርዓተ ፅህፈታዊ ቅርፅ ያው <u>በርቺ</u> ነው፡፡ ላዕላይ ዘረ ፎኒማዊ ቅርፁ [ብኧርችኢ] ነው፡፡ ታህታይ ቅርፁ ግን /ብኧርትኢ/ ነው፡፡ ይህ በአዕምሮአችን የሚለማን ቅርፅ ነው፡፡ በሁለቱ ቅርፆች መካከል ያለው ልዩነት፣ በታህታዩ ቅርፁ ውስጥ /ት/ የነበረችው ተናባቢ የድድ ድምፅ በላዕላዩ ቅርፅ ወስጥ ወደ ድላንቃ ተለውጣ [ች] መሆንዋ ነው፡፡

እዚህ ላይ [ች] በታህታዩ ቅርፅ ውስጥ /ት/ ለመሆንዋ ማስረጃው ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ድምፅዋ /ት/ ለመሆንዋ ማስረጃው፣ ለተባዕታይ ፆታ የምንጠቀምበት የቃሉ ቅርፅ ነው፡፡ እሱም በርታ [ብኧርትአ] ነው፡፡ ከ[ር] ቀጥሎ የምትታየው ድምፅ [ት] ነች፡፡ የቃሉ ታህታይ ቅርፅም /ብኧርትአ/ ነው፡፡ ከላዕላዩ ቅርፅ ጋር አንድ አይነት ነው፡፡ በ/ብኧርትአ/እና በ/ብኧርትኢ/ መካከል ያለው ልዩነት በመጨረሻዎቹ አናባቢዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ ይኸውም የ/ብኧርትኢ/ የመጨረሻ አናባቢ /ኢ/ ሲሆን፣ የ/ብኧርትአ/ የመጨረሻ አናባቢ /አ/ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በሁዋላ የሚነሳው ሌላው ጥያቄ /ብኧርትኢ/ በሚለው ታህታይ ቅርፅ ውስጥ /ት/ የነበረችው ፎኒም [ብኧርችኢ] በሚለው ላዕላይ ቅርፁ ውስጥ እንዴት ወደ [ች] ተለወጠች? ከተለወጠችስ <u>በርታ</u> በሚለው ላይ ለምን አልተለወጠችም የሚል ነው? ወደፊት ጉዳዩን በዝርዝር እስከምናየው ድረስ

---

[13] ባህሪነቱ ግን የቋንቋዎ ብቻ አይደለም፤ ማንኛውም ነገር ረቂቃዊና አካላዊ ባህሪ አለው፡፡ ለምሳሌ፣ የሰው ተፈጥሮ በከፊል አካላዊ (ስጋዊ) በከፊል ደግሞ መንፈሳዊ (ረቂቅ) ነው፡፡ ነፍስና ስጋ እያልን አንዱን ከሌላው እንለያለን፡፡ ስጋ ተሰዋዋጭ ነው፤ ይከሳል፣ ይጠቁራል፣ ያድጋል፣ ይጫጫል፣ ይሞታል፣ ይበሰብሳል፡፡ ነፍስ ግን አትሰዋወጥም፣ አትሞትም፤ ዘላለማዊት ናት ይባላል፡፡

/ብኸርትኢ/ በሚለው ውስጥ /ት/ ወደ [ች] የምትለወጠው /ኢ/ ከሚለው አናባቢ በፊት ገብታ ስትገኝ ብቻ ነው ብለን፣ አናልፈዋለን።

የሁለቱን ቃላት ቀለማዊ አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።




ከዕፀ-መዋቅሩ እንደምናየው፣ ምዕላዱ ባለሁለት ቀለም ሊሆን፣ የመጀመሪያው ቀለም ዝግ ነው። በተናባቢ ይጨርሳል። ሁለተኛው ጨራሽ ተናባቢ ስለሌለው ክፍት ነው። ለውጡም የሚካሄደው በሁለተኛው ቀለም ከፋች ተናባቢ በሆነችው በ/ት/ ላይ ነው። መንስኤውም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ከጎንዋ የሚገኘው /ኢ/ የሚለው አናባቢ ነው። አሁን ወደ ርዕስ ጉዳያችን እንመለስና ሌሎች ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶችን እንመልከት።

## ምስለት

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ በአንድ ቅንጅት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ፎኒሞች በትንጅቱ ውስጥ በሚፈጥሩት ጉርብትና ምክንያት፣ የአንዱ ባህሪ ወደ ሌላው ሊጋባ ይችላል። በዚህም ተጋቦት ምክንያት አንዱ ሌላውን ሊመስል ይችላል። የመመሳሰሉን ሂደት ምስስሉሽ፣ ውጤቱን ደግሞ ምስለት እንለዋለን። አንድ ድምፅ ከጎረቤቱ ጋር ይመሳሰላል የምንለው የጎረቤቱን ድምፅ ባህሪ በከፊል ወይም በሙሉ ሲወስድና እሱን ሲመስል ነው። በዚሁ መሰረት የምስለቱን ሂደት ከፊል ወይም ሙሉ ምስስሉሽ እንለዋለን። አንድ ድምፅ ከጎረቤቱ ጋር ሙሉ በሙሉ ተመሳሰለ እል የምንለው፣ ጎረቤቱ በሚፈጠርበት ቦታና ሁኔታ እሱም

ባህሪን እንጅ ከዚህ ወይም ከዚያ ድምፅ በፊት አያለ ስለማይዘረዝር በተራ ቁጥር (3) ከተጠቀሰው ቅምር የበለጠ እጠቃልይነት አለው፡፡ ይህን ከተገነዘብን፣ ወደ ሌላ የምስለት አይነት እንሂድ፡፡

## *ከፊል ላንቃዊነት*

ይህ የምስለት አይነት በተናጠላዊ ፍጥረታቸው ላንቃዊ ያልሆኑ ድምፆች በቅንጅታዊ ባህሪያቸው ምክንያት ከፊል ላንቃዊ የሚሆኑበት ሂደት ነው፡፡ የሚከተሉት ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ቃላት ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ክኢስ / | [ክʼኢስ] | ኪስ | I |
| /ብኤት/ | [ ብʼኤት] | ቤት | |
| /ጥኢስ/ | [ጥʼኢስ] | ጢስ | |
| /ምኧልትኢ/ | [ምኧልትʼኢ] | መልቲ | |
| /ክኧይስኢ/ | [ክኧይስʼኢ] | ክይሲ | |

የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ በእዝባር ውስጥ የተመለከተው ነው፡፡ ላዕላይ ቅርፃቸው በቅንፍ ውስጥ የሚታየው ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት በታህታዩ ውስጥ /ክ፣ብ፣ጥ፣ት፣ስ/ የነበሩት ፎኒሞች በላዕላዩ ውስጥ [ክʼ፣ብʼ ፣ጥʼ ፣ትʼ ፣ስʼ] ሆነው መከሰታቸው ነው፡፡ /ክ/ እና /ብ/ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ የትናጋና የከናፍር ድምፆች ናቸው፡፡ /ጥ፣ት/ እና /ስ/ ደግሞ የድድ ድምፆች ናቸው፡፡ [ክʼ፣ብʼ ፣ጥʼ ፣ትʼ እና ስʼ] እንደ ቅደም-ተከተላቸው የእነዚሁ ድምፆች ከፊል ላንቃዊ አቻዎች ናቸው፡፡ ባጭሩ ላንቃዊ ያልነበሩት ድምፆች ወደ ከፊል ላንቃዊነት ተለውጠዋል ማለት ነው፡፡

ለዚህ ለውጥ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድን ነው? ለምሳሌ ኪስንና [ክʼኢስ] እና ክይሲን [ክኧይስʼኢ] እያነፃፀርን እንመልከት፡፡ [ክʼኢስ] ውስጥ ያለችው [ክʼ] ከፊል ላንቃዊ ሆናለች፡፡ በመሆንዋም [ʼ] በሚል ምልክት ተጠቁማለች፡፡ [ክኧይስʼኢ] በሚለው ውስጥ ግን [ክ] ላይ የተጨመረ ምልክት የለም፡፡ ምልክት ያለው [ስʼ] ላይ ነው፡፡ [ክኧይስʼኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] ላንቃዊ አይደለችም ማለት ነው፡፡ [ክʼኢስ] ውስጥ ያለችው [ክʼ] ላንቃዊ ስትሆን፣ [ክኧይስʼኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] ለምን ላንቃዊ አልሆነችም? ለዚህ የምንሰጠው መልስ ከላይ ለጠየቅነውም ጥያቄ ምላሽ ይሆናል፡፡ መልሱ ከሁለቱ ድምፆች የአገባብ ልዩነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ [ክኧይስʼኢ] ውስጥ ያለችው [ክ] የገባችው [ኧ] ከሚለው የመሀል አናባቢ ቀድማ ነው፡፡ [ክʼኢስ] ውስጥ ያለችው [ክʼ] ግን የገባችው ከ[ኢ] በፊት ነው፡፡ ይህችም አናባቢ ላየኛና ፊተኛ ነች፡፡ ይህን ቀደም ሲል ከተሰጠው የአናባቢ ሰንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡ [ክ] ወደ [ክʼ]

ውስጥ እንደሚታየው [ጥ] ትሆናለች፡፡ የማንቁርታዊነቱን ባህሪ ያገኘችው ቀድሞአት ከገባው ክ/ጥ/ ነው፡፡ ባህሪው የሚሄደው ከግራ ወደ ቀኝ ስለሆነ፣ የምስስሎሹ አይነት ገስጋሽ ነው፡፡ ተመሳሳይ የምለስሎሽ ሂደት በአዲስ አበባ አማርኛም አለ፡፡ ሁኔታው ዝቅ ብለን ከምናየው ሌላ ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት ጋር የተያያዘ ስለሆነ እዚህ ላይ አናየውም፡፡ ስለዚህም ወደ ሌላ የምስስሎሽ ሂደት እንሽጋገራለን፡፡

## *ሙሉ ላንቃዊነት*

ሁለት አይነት የላንቃዊነት ደረጃ አለ፡፡ አንደኛው አይነት መለስተኛ ወይም ከፊል ያልነው ሲሆን፣ ሂደቱን በቦታው እንደ [ሰ^ኤት] እና [ከ^ኢስ] ያሉ ምሳሌዎችን እየጠቀስን ለማሳየት ሞክረናል፡፡ በታህታይ ቅርፃቸው /ስ/ እና /ክ/ የነበሩት ተናባቢ ድምፆች በላዕላይ ቅርፃቸው ወደ [ሰ^] እና [ከ^] ሊለወጡ ችለዋል፡፡ ለለውጡ ምክንያት የሆነችው ድምፅ /ኢ/ ወይም /ኤ/ ነች፡፡ ይህች ድምፅ በተፈጥሮዋ ላየኛ ስለሆነች፣ ከእሰዋ ቀድመው የሚገቡ ድምፆችን ወደ ላየኛነት የመለወጥ ባህሪ አላት፡፡ ይህም ሂደት ከፊል ላንቃዊነት እንደሚባል ተገልፆአል፡፡

ሁለተኛው አይነት ላንቃዊነት ከፍተኛ የሆነ የባህሪ ለውጥ የሚታይበት ሂደት ስለሆነ፣ ሙሉ ላንቃዊነት ይባላል፡፡ ከዚህ በታች በማዕዘን ቅንፍ ውስጥ የሚታዩት ምሳሌዎች የዚህ አይነት ለውጥ የሚካሄድባቸው ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ግኧድእል-ኢ/ | [ግኧድእይ] | ገዳይ | 1 |
| /ብኧርርእዝ-ኢ/ | [ብኧርርእዥ] | በራዥ | |
| /ክኧስእስ-ኢ/ | [ከኧስእሽ] | ከሳሽ | |
| /ዝኧምእት-ኢ/ | [ዝኧምእች] | ዘማች | |
| /ውኧልእድ-ኢ/ | [ውኧልእጅ] | ወላጅ | |
| /ዝኧንንእጥ-ኢ/ | [ዝኧንንእጭ] | ዘናጭ | |
| /ልኧምምእን-ኢ/ | [ልኧምምእኝ] | ለማኝ | |

እንደነዚህ ያሉ ቃላት አድራጊ ስሞች ይባላሉ፡፡ በሚቀጥለው ክፍል በስፋው እንደምናየው፣ አንድን ድርጊት የሚፈፅምን አካል ወይም ህይል ያመለክታሉ፡፡ በእዝባር ውስጥ የሚታየውን ታህታይ ቅንጅታቸውን ስንመረምር፣ ሁሉም በ/ኢ/ እንደሚጨርሱ እንረዳለን፡፡ ይህች ድምፅ ተራ አናባቢ ፎኒም አይደለችም፤ ምዕላዳዊ ፎኒም ነች፡፡ በመሆንመዋም ከፍ ሲል ስለ ከፊል ላንቃዊነት ስንወያይ ካየናት ፎኒማዊ /-ኢ/ ትለያለች፡፡ ንክኪውም የተፈጠረው በሁለቱ ምዕላዶች፣ ማለትም በእምዶቹና በዚች ምዕላዳዊ ፎኒም መካከል ነው፡፡ ከዚች ድምፅ በፊት የሚገኙት የየእምዱ ተናባቢ ድምፆች በሙሉ የድድ ድምፆች ናቸው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በየቅንፉ በሚታየው ላዕላይ ቅርፅ ውስጥ እንደሚታየው፣ የድድ የነበሩት

በቅንፉ ውስጥ የሚታየው የየቃሉ የመጀመሪያ ተናባቢ ድምፅ፣ በእዝባሩ ውስጥ ከሚታየው የየቃሉ የመጀመሪያ ድምፅ በመጠኑ የተለየ ነው። የሚለየውም የክብነት ባህሪ በመያዙ ነው። ይህን ባህሪ ያገኘው ከእሱ ቀጥሎ ከገባው ከ/ኡ/ ወይም ከ/ኦ/ ነው። እነዚህ እናባቢዎች ክብ ስለሆኑ፣ ይህኑ ባህሪያቸውን ቀድሞአቸው ለገባው ተናባቢም ሊያጋቡ ችለዋል። አሁንም ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ባህሪው የሚጋባው ከቀኝ ወደ ግራ ነው።

የለውጡን ሁኔታ እንደሚከተለው አድርጎ መቀመር ይቻላል።

$$\begin{bmatrix} +\ \text{ተ} \\ -\ \text{ክብ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} +\ \text{ተ} \\ +\ \text{ክብ} \end{bmatrix} \Big/ \ __ \begin{bmatrix} +\ \text{ተ} \\ +\ \text{ክብ} \end{bmatrix} \qquad 2$$

ተ = ተናባቢ

ቅምሩ ከ/ኦ/ ወይም ከ/ኡ/ በፊት የሚገኝ ተናባቢ ድምፅ ወደ ክብነት እንደሚለወጥ ያሳያል። የባህሪው ተጋቦት ከቀኝ ወደ ግራ መሆኑ ስለ መላሽ ምስስሎሽ የጠቀስነውን ያስታውሰናል።

## ድምፀት

አንድ በተፈጥሮው ኢነዛሪ የሆነ ድምፅ ነዛሪ በሆነ ድምፅ ጉርብትና ምክንያት ወደ ነዛሪነት ሊለወጥ ይችላል። የዚህ አይነት ሂደት <u>ድምፀት</u> ይባላል። ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን።

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ኣል-ት-ድኽፍርእም/ | [ኣድድኽፍርእም] | አደፍርም | 1 |
| /ኣል-ት-ዝኽርኣም/ | [ኣዝዝኽርኣም] | አዘራም | |
| /ኣስ-ዝኽርርኣህኡ/ | [ኣዝዝኽርኣህኡ$^{w}$] | አዘራሁ | |

በእዝባሩ ውስጥ በሚታዩት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ምሳሌዎች ውስጥ፣ በመነሻ ላይ የሚገኘው /ኣል-/ የአሉታ ምዕላድ ነው። ዝርዝሩን በሚቀጥለው ምዕራፍ እናየዋለን። ከእሱ ቀጥላ የምትገኘው /ት/ም ወደ ፊት እንደምናየው፣ የሁለተኛ መደብን የምታመለክት ምዕላድ ነች። ከእስዋ ቀጥሎ የሚገኘው የየግሱ እምድ ሲሆን፣ የሚጀምረውም በነዛሪ ድምፅ ነው። የአሉታው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ፣ ማለትም /ል/፣ የሁለተኛ መድብ አመልካችዋ /ት/፣ እንዲሁም የየግሱ እምድ የመጀመሪያ ድምፅ በመካነ ፍጥረታቸው አንድ ናቸው። ሁሉም ድዳዊ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ /ት/ ብቻ ኢነዛሪ እግድ የድድ ድምፅ ነች። በመሆንዋም ከእስዋ ቀጥሎ ያለውንና ነዛሪ የሆነውን የየግሱን እምድ የመጀመሪያ ድምፅ ባህሪ ትወርስና እስዋም እንደ እሱ ነዛሪ ትሆናለች።

አትታይም፡፡ ተገድፋለች ማለት ነው፡፡ በቀጥታ ከግሱ አምድ ላይ በምትገኝበት ጊዜ ግን በግሀድ ትታያለች፣ አትገደፍም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም አልቀረበም ([አልቅኧርርኧብኧም]) በሚሰው ውስጥ በግሀድ ስትታይ፣ አይቀርብም ([አይቅኧርብአም]) በሚለው ውሰጥ ግን አትታይም፡፡

አንድ መደብ አመልካች ቅጣይ ከግስ አምድ መነሻ ላይ የሚገኘው በካልዓይ አንቀፅ፣ በአምድ መድረሻ ላይ የሚገኘው ደግሞ በቀዳማይ አንቀፅ ግስ በሰሆን፣ የግድፈቱን አውድ ከዚሁ የአንቀፅ ልዩነት ጋር ማያያዝ ይቻላል፡፡ ከዚህም አአኩዋያ /ል/ የምትገደፈው በካልዓይ አንቀፅ ግስ ውስጥ ነው፣ ብሉ ማጠቃስል ይችላል፡፡ ይህም ቀደም ሲል የ/ው፣ይ፣ሀ፣ዕ/ን የግድፈት አአውድ ከተሰየ የቃል ክፍል፣ ማለትም ከግስነት፣ ጋር እንዳያያዝነው ሁሉ፣ አአሁንም የ/ል/ን ግድፈት ከተወበነ የግስ አአምድ አአይነት፣ ማሰትም ከካልዓይነት ጋር ማያያዛችን፣ የግድፈቱ ሂደት በሰነ-ድምፃዊ አአውድ ላይ ሳይሆን፣ በሰነ-ምዕ ላዳዊ ቅርፅ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ስለ ቀዳማይና ካልዓይ አአንቀፅ በሚቀጥለው ምዕራፍ በሰፊው እንወያያለን፡፡

## ኢድምፀት

ቀደም ሲል ድምፆች በተፈጥሮአቸው ነዛሪና ኢነዛሪ ተብሰው በሁሰት እንደሚከፈሉ ገልፀናል፡፡ በዚህ ልዩነት ምክንያት ነዛሪ ድምፆች [+ ድምፅ] ኢነዛሪዎቹ ደግሞ [ - ድምፅ] ተብለው ይመደባሉ፡፡ አንድ ነዛሪ የሆነ ድምፅ ነዛሪ ካልሆነ ሌላ ድምፅ ጋር ሲገባ፣ የባህሪ መወራረሰ ይከሰታል፡፡ ይኸውም ከፍ ሲል እንዳየነው፣ ኢነዛሪ የነበረው ነዛሪ ሊሆን፣ ወይም በተቃራኒው ነዛሪ የነበረው ኢነዛሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢነዛሪ የነበረን ድምፅ ነዛሪ የሚያደርግ ሂደት ድምፀት እንደሚባል ሁሉ፣ ነዛሪ የነበረን ድምፅ ኢነዛሪ የሚያደርገው ሂደት ኢድምፀት ይባሳል፡፡ የሚከተሉት የዚህ የሁለተኛው ሂደት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ፍኧልልኧግ-ክ/ | [ፍኧልልኧክክ] | ፈለክ | 1 |
| /ድኧንኧዝዝኧዝ-ክ/ | [ድኧንኧዝዝኧስክ] | ደነዘዝክ | |
| /አል-ት-ው-ጥአ/ | [አትትውጥአ] | አትውጣ | |

በአዝባሩ ውስጥ በሚታዩት የመጀመሪያ ምሳሌዎች፣ የየአምዱ የመጨረሻ ድምፅ፣ ማለትም /ግ/ እና /ዝ/፣ ነዛሪ፣ ሰለዚህም [+ ድምፅ] ናቸው፡፡ ከነዚህ ቀጥሳ የምትታየው /-ክ/ ግን ኢነዛሪ እናም [ - ድምፅ] ነች፡፡ በከትትሉሹ ምክንያት የ/-ክ/ ኢነዛሪያዊ ባህሪ ወደ ቀዳሚው ድምፅ ይጋባል፡፡ በዚህም ምክንያት /ግ/ እና /ዝ/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው ወደ [ክ] እና [ሰ] ሊለወጡ ችለዋል፡፡ በመጨረሻው ምሳሌም የአሉታዊው ምዕሳድ የመጨረሻ ድምፅ

የሆነችው /ል/ ከአሰዋ ቀጥላ በምትገኘውና ኢነዛሪ በሆነችው በ/ት/ ምክንያት፣ እሰዋም ወደ ኢነዛሪነት ተለውጣ፣ በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው [ት] ሆናለች፡፡

ከዚህ ላይ ቀደም ሲል የአሉታዊው ምዕላድ የመጨረሻ ድምፅ የሆነችው /ል/ መደብ አመልካች ከሆነችው ምዕላድ ከ/ት-/ቀድማ ስትገባ ትገደፋለች ብለን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ይህችው ድምፅ ማለትም /ል/ ወደ ኢነዛሪነት ትለወጣለች እያልን ነው፡፡ እነዚህ የሚጣረሱ ሀሳቦች ይመስላሉ፡፡ በአንድ በኩል ግድፈት፣ በሌላ በኩል ኢድምፀት ይካሄድበታል ማለታችን ነው፡፡ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ሂደቶች በአንድ ድምፅ ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ የግድፈቱንና የኢድምፀቱን አውድ መለየት ግን ያስፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ግድፈቱ የሚከሰተው በካልዓይ አንቀፅ ላይ ነው፡፡ ኢድምፀት ግን የሚከሰተው በትዕዛዝ አንቀፅ ላይ ነው፡፡

ተመሳሳይ የኢድምፀት ሂደት በአናባቢዎች ላይም ይከሰታል፡፡ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ጥኧግግኧብክ-ኡ/ | [ጥኧግግኧብክኡ$^{ሀ}$] | ጠገብኩ | 2 |
| /ውኧጥጥኣህ-ኡ/ | [ውኧጥጥኣህኡ$^{ሀ}$] | ወጣሁ | |

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የመጨረሻው አናባቢ ድምፅ /ኡ/ ነው፡፡ እንደማንኛውም አናባቢ ድምፅ በመሰረተ ባህሪው ነዛሪ ብሎም [+ ድምፅ] ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በማዕዘኑ ውስጥ እንደሚታየው፣ ወደ ኢነዛሪነት ተለውጦ [ኡ$^{ሀ}$] ሆኗል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ፣ ድምፁ ኢነዛሪ ከሆኑት ከ/ክ/ እና ከ/ህ/ ቀጥሎ መገኘቱና የእነሱ የኢነዛሪነት ባህሪ ወደሱ መጋባቱ ነው፡፡ የተጋቦቱ አቅጣጫ ግን ከፍ ሲል ከሚታየው የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም የላይኛው ሂደት መላሽ ያልነው አይነት ሲሆን፣ ይኸኛው ግን ቀደም ሲል የጠቀስነው የገስጋሽ ምስስሉሽ ምሳሌ ነው፡፡ ባህሪው የሚጋባው ወደፊት ማለትም ወደ ቀኝ ሂዶ ነውና፡፡

የሁሉንም ኢድምፀታዊ ሂደቶች ጠቅለል አድርጎ በአንድ ቅምር ማሳየት አስቸጋሪ ነው፡፡ አንደኛ ባህሪው ሚሄድበት የአቅጣጫ ልዩነት አለ፡፡ ሁለተኛም በቅምሩ ውስጥ ሲካተቱ የማይችሉ ምሳሌዎች ያጋጥሙናል፡፡ እነዚህም እንደ *ወደድክ* ([ውኧድድኧድክ]) እና *ወሰድክ* ([ውኧሰሰኧድክ]) ያሉት ቃላት ናቸው፡፡ ከፍ ሲል ባየነው አካሄድ መሰረት፣ በነዚህ ቃላት ውስጥ ከ/ክ/ በፊት የሚገኘው /ድ/ ወደ ኢነዛሪነት ተለውጦ [ት] መሆን ነበረበት፣ ግን ነዛሪነቱን እንደጠበቀ ይገኛል፡፡ በቅምሩ መሰረት ድምፁ ወደ ኢነዛሪነት ቢለወጥ ኖሮ፣ የቃላቱ ቅርፅ [ውኧድድኧትክ] እና [ውኧሰሰኧትክ] ይሆንና ተቀባይነትን ያጣ ነበር፡፡ በጥቅሉ ግን አንድ ነዛሪ የነበረ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ሌላ ድምፅ ቀድሞ ወይም ተከትሎ ሲገኝ፣ ወደ ኢነዛሪነት ይለወጣል የሚሉ ቅምሮችን እንደሚከተለው አድርጎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ተፈፃሚነቱን ሂደቱ በሚታይባቸው ቃላት ላይ ብቻ መወሰን ይቻላል፡፡

(ሀ) $\begin{bmatrix} + \text{ተ} \\ + \text{ድምፅ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} + \text{ተ} \\ - \text{ድምፅ} \end{bmatrix} / \text{—} \begin{bmatrix} + \text{ተ} \\ - \text{ድምፅ} \end{bmatrix}$ 3

(ለ) $\begin{bmatrix} + \text{ድምፅ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} - \text{ድምፅ} \end{bmatrix} / \begin{bmatrix} + \text{ተ} \\ - \text{ድምፅ} \end{bmatrix} \text{—}$

የመጀመሪያው ቅምር ነዛሪ የሆነ ተናባቢ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ተናባቢ ድምፅ በፊት ሲገኝ ወደ ኢነዛሪነት ሲለወጥ እንደሚችል፣ ሁለተኛው ግን ነዛሪ የሆነ ድምፅ ኢነዛሪ ከሆነ ተናባቢ በሁዋላ ሲገኝ ወደ ኢነዛሪነት ሲለወጥ እንደሚችል ያሳያል። ይህ ህግ እናባቢንም ያጠቃልላል።

## ግድፈት

በተጎራባች ድምፆች መካከል የባህሪ መወራረስ ብቻ ሳይሆን፣ አንዱ በሌላው ምክንያት ከቦታው የመጥፋት ሂደትም ሊደርስበት ይችላል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን እንደ <u>አዘነ</u>፣ <u>አየለ</u>፣ <u>አነፀ</u>፣ ወዘተ፣ ያሉት ግሶችና እንደ <u>ሀገር</u>፣ <u>ሀሞት</u>፣ ወዘተ ያሉ ስሞች ናቸው። የግሶቹ ታህታይ ቅርፅ፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣/ሀኧዝዝኧነኧ/፣ /ሀኧይይኧልኧ/፣ /ሀኧነነኧፅኧ/ ነው። ይህ ስለመሆኑ ማስረጃው፣ በየግሶቹ ስማዊ እቻ ላይ /ሀ/ የሚሰው የየቃሉ የመነሻ ድምፅ በግልፅ መታየቱ ነው። ለምሳሌ የ/ሀኧዝዝኧነኧ/ ስማዊ እቻ <u>ሀዘን</u> ([ሀኣዝኧን]) ሲሆን፣ የ/ሀኧይይኧልኧ/ ደግሞ <u>ሀይል</u> ([ሀኣይል]) ነው። ሌላው ማስረጃ የግሶቹ የመጀመሪያ ላዕላይ ድምፅ እናባቢ መሆኑ ነው። ይህ ከቁዋንቁዋው አጠቃላይ የግስ ባህሪ የሚያፈነግጥ ሁኔታ ነው። ከተወሰኑት በስተቀር፣ የአማርኛ ግሶች በተናባቢ እንጂ በእናባቢ አይጀምሩም። ለምሳሌ፣ እንደ <u>ገደለ</u>፣ <u>ሰበረ</u>፣ <u>ዘመረ</u>፣ ወዘተ ያሉ ግሶች በተናባቢ የሚጀምሩና፣ ከዚያ ተናባቢ ቀጥሎም /ኧ/ የሚለውን የመሀል እናባቢ የሚያስከትሉ ናቸው። ለምሳሌ፣ የ<u>ገደለ</u> ታህታይ ቅርፅ /ግኧድድኧልኧ/ ነው። በግልፅ እንደሚታየውም፣ የመጀመሪያው ድምፅ ተናባቢ ሲሆን ከእሱ ቀጥሎ የሚታየው እናባቢ ደግሞ ሌላ ሳይሆን፣ /ኧ/ ነው። ይህም መሀለኛ እናባቢ ነው። የቃሉ ላዕላይ ቅርፅም የሚጀምረው እንደዚሁ በተመሳሳይ ተናባቢ ድምፅ ነው።

/ሀኧዝዝኧነኧ/ በሚለው ቅርፅ መጀመሪያ ላይ የሚገኘው ተናባቢ፣ ማለትም /ሀ/፣ ከ/ኧ/ በፊት ሲገባ፣ ባህሪውን ለእናባቢው ድምፅ ሰጥቶ፣ እሱ ከቦታው ይጠፋል። የ/ሀ/ ባህሪ ታቸኛነት ነው። የታች ድምፅ ነው፣ ማለት ነው። የታች የሚባልበት ምክንያት፣ ድምፁ ማንቁርት ውስጥ ሲፈጠር ምላስ ወደታች ዝቅ ብሎ ስለሚገኝ ነው። ይህ ታቸኛ ድምፅ ከፍ ሲል ከተገለፀው መሀለኛ ከሆነው ከ/ኧ/ በፊት ሲገባ፣ የታቸኛነት ባህሪውን ለ/ኧ/ ሰጥቶ፣ እሱ ከዚያ ቦታ ይጠፋል።

የታቸኛነት ባህሪን የተላበሰው /ኸ/ም ከመሀለኛነት ወደ ታቸኛነት ይለወጥና [አ] ይሆናል፡፡ ዝርዝሩን በመተው አአጠቃላይ ለውጡን ብቻ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

(ሀ)

$$\begin{bmatrix} +\text{አ} \\ -\text{ታ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} +\text{አ} \\ +\text{ታ} \end{bmatrix} \Big/ \begin{bmatrix} -\text{አ} \\ +\text{ታ} \\ +\text{ሁዋ} \end{bmatrix} __ \qquad 1$$

(ለ)

$$\begin{bmatrix} -\text{አ} \\ +\text{ታ} \end{bmatrix} \longrightarrow \emptyset \Big/ __ \begin{bmatrix} +\text{አ} \\ +\text{ታ} \end{bmatrix}$$

አ = እናባቢ ታ = ታች

ህጎቹ ተከታታይና ተደጋጋፊ ናቸው፡፡ መጀመሪያ /ኸ/ በ/ሀ/ ምክንያት ወደ [አ] ይለወጣል፡፡ ከዚያ በሁዋላ፣ /ሀ/ በ[አ] ምክንያት ከቦታው ይጠፋል፡፡ ሂደቱ በከፊል የምስስሎሽ በከፊል ደግሞ የግድፈት ነው፡፡ ምስስሎሹ ለግድፈቱ መንስዔ ሆኖአል፡፡

በ/ሀ/ ምክንያት በ/ኸ/ ላይ የደረሰው ለውጥ ቀደም ሲል የጠቀስነው የገስጋሽ ምስስሎሽ ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው፡፡ /ሀ/ የታቸኛነት ባህሪዋን በቀኝዋ በኩል ለሚገኘው ለ/ኸ/ አጋብታ ጠፍታለች፡፡ የመሀለኛ እናባቢ የነበረችው /ኸ/ም በተጋቦቱ ምክንያት ታቸኛ ልትሆን ችላለች፡፡ ሌላም የዚህ አይነት ምሳሌ ስለ <u>ትናጋዊነት</u> ስንወያይ እንመለከታለን፡፡

/ሀ/ የምትገደፈው ከላይ እንደሚታየው በቃል መነሻ ላይ ብቻ አይደለም፡፡ በቃል መካከልና በቃል መድረሻም ጭምር ነው፡፡ በሁለቱም ቦታዎች የታቸኛነት ባህሪዋን ተከትሎአት ለሚገባው ድምፅ ሰጥታ እስዋ ከቦታዋ ትጠፋለች፡፡ የሚከተሉት ቃላት ለዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡

ማስ 2
ዓፌ

የእነዚህ ቃላት ታህታይ ቅርፅ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣

/ምኸሀኸልኸ/[18] 3
/ፅኸሀኸፍኸ/

---

[18] ቀደም ሲል እንደተገለፀው /ሀ/ ጠባቂ ድምፅ አይደለችም፡፡ ብትሆን ኖሮ፣ የግሱ ቅርፅ /ምኸሀሀኸልኸ/ ይሆን ነበር፤ ይህ ደግሞ ትክክለኛ አባባል አይደለም፡፡

በስማዊ አቻው ውስጥ /ዕ/ን በግሀድ ያሳያል፡፡ ይኸውም <u>ለዕል</u> በምንልበት ጊዜ ነው፡፡

/ዕ/ የተገደፈው በመጀመሪያው ግስ መሀልና በሁለተኛው ግስ መድረሻ ላይ ነው፡፡ በሁለተኛው ግስ ላይ ድምፁ የተገደፈው መድረሻ ላይ በመሆኑም የዚሁ ግስ አርዕስታዊ ቅርፅ፣ በተገደፈው ድምፅ ቦታ ላይ [ት]ን በምትክነት ያሳያል፡፡ ይኸውም <u>በላ</u> ብለን <u>መብላት</u> ስንል ነው፡፡ ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም /ዕ/ በመሀልና በመድረሻ እንደምትገደፍ ሁሉ፣ በመነሻስ ልትገደፍ ትችላለች ወይ? የሚል ነው፡፡ የዚሁ ተከታይ ሊሆን የሚችለው ሌላ ጥያቄ ደግሞ፣ /ዕ/ በግስ መነሻ ላይ የምትገደፍ ከሆነ፣ በአርዕስታዊ አቻው ላይ በ[ት] ትተካለች ወይ? የሚል ነው፡፡ በርግጥ /ዕ/ በአንዳንድ ግሶች መነሻ ላይ ትገደፋለች፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | |
|---|---|
| አወቀ | 9 |
| አበደ | |

የእነዚህ ግሶች መነሻ /አ/ የሚለው ታቸኛ አናባቢ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአማርኛ ግሶች ታህታይ ቅርፅ በተናባቢ እንጅ በአናባቢ አይጀምርም፡፡ በዚሁ መሰረት የነዚህ ግሶች ታህታይ ቅርፅም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣

| | |
|---|---|
| /ዕኧውውኧቅኧ/ | 10 |
| /ዕኧብብኧድኧ/ | |

መሆን ይኖርበታል፡፡ የሁለቱም መነሻ አግድ የማንቁርት ድምፅ የሆነው /ዕ/ ነው፡፡ ይህ ድምፅ እንደ /ህ/ የታቸኛነት ባህሪውን ከእሱ ቀጥሎ ለገባው መሀለኛ አናባቢ፣ ማለትም ለ/ኧ/ ይሰጥና ከቦታው ይጠፋል፡፡ የእሱን ባህሪ የወለደው /ኧ/ ከመሀለኛነት ወደ ታቸኛነት ተለውጦ [አ] ይሆናል፡፡ ይህ ቀደም ሲል ካየው ከ/ህ/ ሁኔታ ጋር አንድ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ /ዕ/ም ሆነ /ህ/ በመነሻ ላይ ሲገደፉ፣በሚገደፉበት አርዕስታዊ አቻ መድረሻ ላይ [ት]ን በምትክነት አያሳዩም፡፡ ለለዚህም የግሶቹ አርዕስታዊ አቻዎች <u>ማወቅ</u> እና <u>ማበድ</u> ናቸው፡፡ [ት]ን በመድረሻቸው ላይ ቢጨምሩ፣ <u>ማውቀት</u> እና <u>ማብደት</u> ይሆኑ ነበር፡፡ እነዚህ ደግሞ ተቀባይነት ያላቸው የአማርኛ ቃላት አይደሉም፡፡ ከዚህ የምንረዳው በአርዕስታዊ አቻቸው ላይ [ት]ን በምትክነት የሚያስገቡት እንደ <u>አየ</u> ያሉት የመነሻ ተናባቢ ድምፃቸውን ባህሪ ለሚቀጥለው አናባቢ ድምፅ ሳያጋቡ የሚገደፉት ብቻ መሆናቸውን ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተመለከትነው፣ የ<u>አየ</u> የመጀመሪያ ድምፅ /ር/ ነው፡፡ ይህ ድምፅ ከመነሻ ቦታው የጠፋው ያለምንም <u>ዱካ</u> ነው፡፡ ስለዚህም በግሉ መነሻ ላይ የተጎረደ ድምፅ እንዳለ ለማሳየት በአርዕ-ስቱ መድረሻ ላይ [ት]ን ያሳያል፡፡ ዝርዝሩን አሁንም ከባየ (1999) ላይ ይመልከቱ፡፡

የግድፈት ሂደት የሚታይባቸው ሌሎች ቃላትም አሉ፡፡ እነሱም እንደ ሸጠ እና መሸ ያሉት ግሶች ናቸው፡፡ በነዚህ ቃላት ላዕላይ ቅርፅ የሚገኙት አናባቢዎች [ኧ] እና [ኤ] ናቸው፡፡ በዚህም ቀደም ሲል ካየናቸው ገዳፊ ቃላት ይለያሉ፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል ባየናቸው ቃላት ላዕላይ ቅርፆች ውስጥ ያየናቸው አናባቢዎች [ኧ] እና [ኣ] ስለነበሩ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ በላ በሚለው ቃል ውስጥ መጀመሪያ [ኧ]ን ቀጥሎ ደግሞ [ኣ]ን ስናገኝ፣ ማለ በሚለው ቃል ውስጥ ደግሞ መጀመሪያ [ኣ]ን፣ ቀጥለን [ኧ]ን እናገኛለን፡፡ የአናባቢዎቹ መለያየትና የተናባቢዎቹ ሁለት ብቻ መሆንም፣ በየቃሉ ውስጥ አንድ ተናባቢ ድምፅ እንደ ተገደፈ ሊጠቁም ይችላል፡፡ የተናባቢዎቹ ሁለት ብቻ መሆን ግን ብቻውን የግድፈት ምልክት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከስረ-መሰረታቸው ባለሁለት ተናባቢ የሆኑ እንደ ተወ ያሉ ቃላት በቋንቋዋ ውስጥ ስለሚገኙ ነው[20]፡፡

ከዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ታዲያ እንደ ሸጠ እና መሸ ያሉት ቃላትስ ቢሆኑ አንድ ተናባቢ ለመግደፋቸው ማስረጃው ምንድን ነው? እነዚህስ ቢሆኑ ከስረ-መሰረታቸው እንደ ተወ ባለሁለት ተናባቢ ሊሆኑ አይችሉም ወይ? የሚል ነው፡፡ እንደ ሸጠ ያሉትን ባለሁለት ተናባቢ ናቸው እንዳንልማ፣ እንደ ተወ ካሉት ባለሁለት ተናባቢ የሚለዩበት አንድ ባህሪ አላቸው፡፡ ይኸውም በአርዕስታዊ ቅርፃቸው ላይ [ት] የምትለዋን ቤት ጠባቂ ድምፅ ማሳየታቸው ነው፡፡ ስለዚህም መሸ ብለን መምሸት እንደምንል ሁሉ፣ ተወ ብለን መተው እንጅ መተውት አንልም፡፡ ከዚህም በመነሳት እንደ መሸ ያሉት ግሶች በታህታይ ቅርፃቸው ባለሁለት ሳይሆኑ፣ ባለሶስት ተናባቢ ናቸው ለማለት እንችላለን፡፡ ከተናባቢዎቻቸውም መካከል የመጨረሻውን፣ ማለትም ሶስተኛውን፣ ተናባቢ ይገድፋሉ፡፡ ተገዳፊው እሱ ባይሆን ኖሮ፣ በአርዕስታዊ ቅርፃቸው ላይ [ት] አትታይም ነበር፡፡ ይህች ድምፅ ምትክነትዋ በቃል መጨረሻ፣ አንዳንድ ጊዜም በቃል መነሻ ላይ ለሚገደፍ ድምፅ ነው ብለናልና፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ሊነሳ የሚችለው ሌላ ጥያቄ የተገደፈው ድምፅ ምንድን ነው? የሚል ነው፡፡ ቀደም ሲል ያየነው /ህ/ ወይም /ዕ/ ሊሆን አኣይችልም፡፡ ቢሆን ኖሮ፣ ድምፁ ታቸኛ ስለሆነ፣ ይህን የታቸኛነት ባህሪውን ቀድሞት ለሚገባው አናባቢ፣ ማለትም ለ/ኧ/ ሰጥቶ ሲጠፋ፣ አናባቢው ወደ [ኣ] ተለውጦ፣ የየቃላቱ ላዕላይ ቅርፅ ሻጠ እና መሻ መሆን ነበረበት፡፡ ይህ አለመሆኑ፣ ተገዳፊው ድምፅ የታቸኛነት ባህሪ ያለው እንደ /ህ/ ወይም /ዕ/ ያለ ተናባቢ

---

[20]ይህን ጉዳይ አለመልከቶ ባየ (1999) ሁሉም የአማርኛ ግሶች በታህታይ ቅርፃቸው ባለሶስት ተናባቢ ብቻ እንደሆኑ ይገልፃል፡፡ በዚህ አመለካከት መሰረት፣ እንደ ተወ ያሉትም ባለሶስት ተናባቢ ናቸው፡፡ የመጨረሻው ተናባቢ ለመገደፉ ምልክቱ፣ በተወ አጠንካሪና አለሳላሽ ቅርፅ ላይ [ት] በምትክነት ብቅ ማለትዋ ነው፡፡ ምንም ድምፅ ባልጎረዱ እንደ ሰበረ ባሉ ግሶች አጠንካሪና አለሳላሽ ቅርፅ ምንም ምትክ ድምፅ አይገኝም፡፡ ስለዚህም ሰበረ ብለን ሰብር እንጅ ሰብርት አንልም፡፡ ተወ ብለን ትውት እንደምንለው ማለት ነው፡፡ ሸጠ ብለን መሸጥት ወይም ሸጥት አንልም፣ ምክንያቱም /ት/ በምትክነት የምትገባው በቃል መጨረሻ ላይ ለተጎረደ ድምፅ ነው፡፡ ሸጠ የጎረደው መካከለኛ ተናባቢውን ነው፡፡

እና ዞረ ያሉ ግሶች ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቃላት ላዕላይ ቅርፆች ሁለት ተናባቢ ብቻ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ከአናባቢያቸው መካከልም የመጀመሪያው /እ/ ነው፡፡ እንደ ሰበረ እና እንደ ደመረ ያሉ ግሶችን ስንመለከት ግን በየተናባቢያቸው መካከል ላይ የሚገኘው ድምፅ /ኧ/ የሚለው አናባቢ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ መደበኛው የግሶች ስርዓት ነው፡፡ የየግሉ አናባቢ ድምፅ ከ/ኧ/ የተለየ የሚሆነው፣ በግሱ ታህታይ ቅርፅ ውስጥ ከነበሩት ተናባቢዎች መካከል አንደኛው በላዕላይ ቅርፅ በማይታይበት ጊዜ ነው፡፡ ተናባቢዎቹ ድምፆች በሙሉ በላዕላይ ቅርፅ የሚታዩ ከሆነ፣ አናባቢው ድምፅ ምን ጊዜም /ኧ/ ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታዩ፣ እንደ ጦረ ያሉ ግሶች አንድ ተናባቢ ድምፅ ጎድሎአቸዋል ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው አናባቢያቸው /ኧ/ መሆን ሲገባው፣ /እ/ ሆኖአልና፡፡ የማንኛውም መደበኛ ግስ አናባቢ /ኧ/ ነው ካልን፣ የጦረ እና የዞረ ታህታይ ቅርፅም እንደሚከተለው መሆን አለበት፡፡

/ጥኧውውኧርኧ/ 12
/ዝኧውውኧርኧ/

በግልፅ እንደሚታየው፣ በሁለቱም ግሶች ውስጥ ቅድመ-መድረሻው ተናባቢ /ው/ ነው፡፡ አናባቢውም /ኧ/ ነው፡፡ በታህታይ ቅርፁ ውስጥ /ው/ የሚለው ተናባቢ ለመኖሩ ሶስት ማስረጃዎች አሉ፡፡ አንደኛው ከፍ ሲል እንደተጠቆመው የመጀመሪያው ተናባቢ ድምፅ ከመሀልኛነት ወደ ሁዋልኛነት፣ ማለትም ከ/ኧ/ ወደ /እ/ መለወጡ፣ ሁለተኛው ራሱ /ው/ የግሶቹ ሰማዊ አቻዎች በሆኑት፣

| | | |
|---|---|---|
| ጥውር | [ጥእውውእር] | 13 |
| ዘዋሪ | [ዝኧውእርኢ] | |
| መዘውር | [ምኧ-ዝኧውውእር] | |

በሚሉት ቃላት ውስጥ በግሀድ መከሰቱ ሲሆን፣ ሶስተኛው የየቃሉ መነሻ ተናባቢ ከዝርግነት ወደ ከብነት መለወጡ ናቸው፡፡ የግሶቹን የመነሻ ተናባቢ ድምፅ ለውጥ ከሚከተለው የየግሶቹ ላዕላይ ቅርፅ መመልከት ይቻላል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ጦረ | [ጥʷኦርኧ] | 14 |
| ዞረ | [ዝʷኦርኧ] | |

በግልፅ እንደሚታየው፣ በየታህታይ ቅርፁ ውስጥ /ጥ/ እና /ዝ/ የነበሩት ድምፆች በየላዕላይ አቻቸው ውስጥ ወደ [ጥʷ] እና [ዝʷ] ተለውጠዋል፡፡

የየግሶቹ ታህታይ ቅርፅ ከፍ ሲል እንደተመለከተው ከሆነ፣ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ /ው/ ባህሪውን ቀድሞት ለገባው አናባቢ ለ/ኧ/ ሰጥቶ ጠፍቶአል ማለት ነው፡፡ ታዲያ እዚህ ላይ ጥያቄው፣ /ው/ ለ/ኧ/ የሰጠው ባህሪ ምንድን

በእዝባር ውስጥ የሚታዩት ደግሞ ተደራጊ ስሞች ይባላሉ፡፡ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን፣ ማለትም የድርጊት ተጠቂ የሆነውን ነገር፣ ያመለክታሉ፡፡ በ(ለ) የመጀመሪያ ረድፍ ውስጥ የሚታዩት፣ የውጤት ስሞች ይባላሉ፡፡ አንድ ድርጊት ከተፈፀመ በሁዋላ የሚታየውን ውጤት ወይም ድራጊ ነገር ያመለክታሉ፡፡ ተደራጊዎቹና ድራጊዎቹ ቅደመ-መድረሻ ድምፃቸውን ያጠብቃሉ፡፡ በዚህም ምንም ድምፅ ከማያጠብቁት ከአድራጊ ስሞች ይለያሉ፡፡ ተደራጊና ድራጊ ስሞች የሚለያዩት /ተ/ን በማስቀደምና ባለማስቀደም ብቻ ነው፡፡ ተደራጊዎቹ ብቻ /ተ/ን ያስቀድማሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታም የዚሁ የቅድመ-መድረሻ ድምፅ መጥበቅና አለመጥበቅ በግሶች መካከልም ልዩነትን ይፈጥራል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| /ጥኧርርኧግኧ/ ጠረገ | /ይ-ጥኧርግአአል/ | ይጠርጋል | 4 |
| /ጥኧርርኧብኧ/ ጠረበ | /ይ-ጥኧርብአአል/ | ይጠርባል | |
| /ስኧብብኧርኧ/ ሰበረ | /ይ-ስኧብርአአል/ | ይሰብራል | |

በመጀመሪያው ዕዝባር ውስጥ የተመለከቱት ግሶች የቀዳማይ አአንቀፅ ግሶች ይባላሉ፡፡ ያለቀ ድርጊትን ያመለክታሉ፡፡ በዕፅተኛው ረድፍ የሚታዩት ደግሞ የካልዓይ አአንቀፅ ግሶች ይባላሉ፡፡ የሚያመለክቱት ያላለቀ ወይም ያልተጀመረ ድርጊትን ነው፡፡ የሁለቱን አአይነት ግሶች ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ ድምፅ ብንመለከት፣ በቀዳማዮቹ ውስጥ ድምፁ እንደጠበቀ፣ በካልዓዮቹ ውስጥ ደግሞ እንዳልጠበቀ እንረዳለን፡፡ የሁለቱ አአንቀፆች ልዩነት መሰረት የዚህ ድምፅ መጥበቅ ወይም አለመጥበቅ ነው፡፡ ከዚህ አአንፃር ሲታይ፣ ጥብቀት ስሞችንና ግሶችን በአአይነት በአአይነት የመለያየት ተግባር እንዳለው እንረዳለን፡፡ ቅድመ-መድረሻው ድምፅ የሚጠብቀው፣ ቀደም ሲል ግድፈትን አአስመልክተን እንደገለፅነው፣ ስነ-ድምፀ-ልሳናዊ በሆነ ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ምዕላዳዊ በሆነ አአገባብም ጭምር ነው፡፡

ከዚህ ላይ ጥብቀት በቃል መነሻ ካልሆነ በስተቀር፣ በሌላ በማንኛውም ቦታ ሊከሰት ይችላል፡፡ በቃል መካከል ላይ የሚከሰተው ከላይ በተራ ቁጥር (3) የሚታየውን ይመስላል፡፡ በቃል መድረሻ የሚከሰተውን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ስ-ብ-ረ-/ | [ስኧብኧርር-] | ሰበር- | 5 |
| /ፍ-ጥ-ን-/ | [ፍኧጥኧንን-] | ፈጠን- | |
| /ው-ስ-ድ-/ | [ውኧስኧድድ-] | ወሰድ- | |

በግልፅ እንደሚታየው፣ በእዝባሩ ውስጥ የተመለከቱት ቃላት የመድረሻ ተናባቢ ጥብቅ ነው፡፡ ቃላቱ በቀዳማይ አንቀፅ ቅርፅ ሲገኙ ይህን ተናባቢያቸውን እያጠብቁም፡፡ ስለዚህም [ስኧብብኧር-ኧ] እንጅ [ስኧብኧ<u>ርር</u>-ኧ] አንልም፡፡

## ልለት

<u>ልለት</u> የጥብቀት ተቃራኒ ነው፡፡ አንድ እግድ ድምፅ ወደ ፍግድነት ከዚያም አልፎ ወደ ፍትግነት ሊሰወጥ ይችላል፡፡ ይህ አይነቱን ለውጥ የሚያመጣው ሂደት ልለት ይባላል፡፡ የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| /ልኣብ/ | [ልኣብ] | 1 |
| /ክኣብ/ | [ክኣብ] | |
| /ሰ-ብ/ | [ሰእብ] | |
| /ዝ-ንኣብ/ | [ዝእንኣብ] | |
| /ጥ-ግኣብ/ | [ጥእግኣብ] | |

በዕዝባሩ ውስጥ የሚታዩት ቃላት የሚጨርሱት በ/ብ/ ነው፡፡ ይህ ድምፅ ደግሞ ቀደም ሲል እንዳየነው እግድ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ እነዚህን ቃላት በምናነብበት ጊዜ፣ ድምፁ የሚወጣው (የሚሰማን) እግድ ሆኖ አይደለም፤ ፍትግ ሆኖ ነው፡፡ በቃላት መካከልም እንደዚሁ ፍትግ ሆኖ የሚነበብበት ጊዜ አለ፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| /ፅኧብኧል/ | [ፅኧብኧል] | ፀበል | 2 |
| /ዝኧብኧንኣይ/ | [ዝኧብኧንኣይ] | ዘበናይ | |
| /ውኧብኧቅ/ | [ውኧብኧቅ] | ወበቅ | |

በቅንፉ ውስጥ በሚታዩት ምሳሌዎች ውስጥ የሚገኘው [ብ] ልል ነው፡፡ ድምፁ እግድ ሆኖ የሚነበበው እንደሚከተሉት ባሉ ቃላት ውስጥ፣ በመነሻ ላይ ሲገኝ ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| /ብኧግ/ | [ብኧግ] | 3 |
| /ብኧል/ | [ብኧል] | |
| /ብኧርር/ | [ብኧርር] | |
| /ብ-ል/ | [ብእል] | |

ሁኔታው ሁለት አይነት የ[ብ] ድምፅ እንዳለ ያስገነዝባል፡፡ አንደኛው እግድ፣ ሌላኛው ደግሞ ፍትግ [ብ] (β) ነው፡፡ ፍትጉ [ብ] በቃል መሀከልና በቃል

አናባቢዎችን *ቀለማይ*፣ ተናባቢዎችን (ከፍናቢዎችን ጭምር) <u>ኢቀለማይ</u> ብሎ መለየት ይቻላል። አንድ አናባቢ ወደ ከፍናቢነት ሲለወጥም፣ ሂደቱ ከቀለማይነት ወደ ኢቀለማይነት ነው። ከዚህ አኩዋያ ከላይ የሚታየውን ለውጥ እንደሚከተለው አያርጎ በቅምር ማስቀመጥ ይቻላል።

$$\begin{bmatrix} +\text{ቀለ} \\ +\text{ላይ} \\ +\text{ሁዋ} \end{bmatrix} \longrightarrow \begin{bmatrix} -\text{ቀለ} \\ +\text{ላይ} \\ +\text{ሁዋ} \end{bmatrix} \Big/ \begin{bmatrix} +\text{ቀለ} \end{bmatrix} __ \qquad (6)$$

ቀለ = ቀለማይ
ሁዋ = ሁዋላ

ይህ ቅምር እንድ፣ ሁዋለኛና ላየኛ የሆነ ድምፅ ከቀለማይ ድምፅ በሁዋላ ሲገባ፣ ወደ ኢቀለማይነት ይለወጣል የሚል ነው። በተራ እንጋገር፣ /ኡ/ ከሌላ አናባቢ በሁዋላ ሲገኝ፣ ወደ [ው]፣ /ኢ/ም እንደዚሁ ባለ አካባቢ ስትገኝ ወደ [ይ] ትለወጣለች የሚል ነው። ሌሎች የማይመሳሰሉ አናባቢዎች ተከታትለው ሲገቡ ከሁለቱ እንደኛው ይገደፋል እንጅ ወደ ከፍናቢነት አይለወጥም። ሁኔታውን ቀደም ሲል ስለ ግድፈት ስንወያይ አይተነዋል።

## *ኢምስለት*

እስካሁን ያየናቸው ሂደቶች አንድ ድምፅ ቀድሞት ወይም ተከትሎት ከገባ ሌላ ድምፅ ጋር ሲመሳሰል ነው። ስለዚህም ሂደቶቹ በሙሉ ምስለታዊ ነበሩ። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ አንድ ድምፅ ከጎኑ ካለ ሌላ ድምፅ ጋር በመሰረተ ፍጥረቱ ተመሳሳይ ከሆነ፣ ከዚያ ድምፅ የተለየ እንዲሆን የሚያደርግ ሂደትን እንመለከታለን። ለዚህ አይነቱ ሂደት የሚከተሉት ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| /አቅጥአጭጭአ/ | [አግጥአጭጭአ] | አቅጣጫ/አአግጣጫ[22] | 1 |
| /ግ-ድግ-ድድአ/ | [ግአርግአድድአ] | ግድግዳ/ግርግዳ | |
| /-ንብ-ድብ-ድ/ | [እንብእርብእድ] | እንብድብድ/ እንብርብድ | |
| /ግ<sup></sup>ኧድግ<sup></sup>አድድአ/ | [ግ<sup></sup>ኧርግ<sup></sup>አድድአ] | ጎድጉዋዳ/ጎርጓዳ | |

በዕዝባሩ ውስጥ /-ቅጥ-/፣ /-ድግ-/፣ /-ድብ-/ እና /-ድግ<sup></sup>-/ የነበሩት ድምፆች በማዕዘኑ ውስጥ[-ግጥ-]፣ [-ርግ-]፣ [-ርብ-] እና [-ርግ<sup></sup>-] ሆነዋል። በመጀመሪያው

[22] እዚህ ላይ በየዕዝባሩ የተመለከተው ታህታይ ቅርፅ ሁለት፤ ሁለት ላዕላይ ቅርፅ ሊኖረው እንደሚችል መረዳት ይቻላል። ምናልባትም አንዱ ቀርፅ በአንዱ አካባቢ፤ ሌላው ደግሞ በሌላ አካባቢ ሊነገር ይችላል። እንደዚህም ሆኖ፤ የቃላቱ ልዩነት መንስዔ በታህታይ ቅርፅ ላይ የሚታየው የድምፆቹ ተመሳሳይ ባህሪ ነው፤፤

ክትትሎሽ ሊከሰት ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ <u>ቀልድ</u> (ቅኸልድ) እና <u>ሰቅ</u> (ሰኸቅቅ) በሚሉት ባለ አአንድ ቀሰም ምዕላዶች መጨረሻ ላይ የሁለተኛ መደብ አመልካች የሆነውን /-ሀ/ን ብንጨምር፣ የምናገኘው <u>ቀልድህ</u> /ቅኸልድ-ህ/ እና <u>ሰቅህ</u> /ሰኸቅቅ-ህ/ የሚል ይሆናል፡፡ ይህም ከአናባቢው ቀጥሎ ሶስት ተናባቢዎች ተከታትለው እንደ ገቡ ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ ከቋንቋው የቀሰም አወቃቀር ሰርዓት ውጭ ነው፡፡ ምክንያቱም የአወቃቀሩ ሰርዓት ሶስት ጨራሽ ተናባቢዎችን አይፈቅድም፡፡ ሰርዓቱን እንዲከተል ከፈለግን፣ ከሁለተኛው ተናባቢ ቀጥሎ፣ አንድ አናባቢ ድምፅ ጣልቃ ማስገባትና የተከታተሉትን ተናባቢ ድምፆች መለያየት ያስፈልጋል፡፡ የምናስገባው አናባቢም፣ ማንኛውም ሳይሆን /እ/ ብቻ ነው፡፡

ይህ አናባቢ በተጠቀሱት ቦታዎች ሲገባ፣ የምናገኘው <u>ቀልድህ</u> [ቅኸልድእህ] እና <u>ሰቅህ</u> [ሰኸቅቅእህ] የሚል ይሆናል፡፡ ህጉ-ወጥ የነበረው የሶስት ተናባቢዎች ክትትሉሽ፣ በገባው አናባቢ ምክንያት ህገኛ ሊሆን ችሎአል፡፡ በዚህ አይነት የተናባቢዎችን ክትትሉሽ ለማስቀረት የሚገባ አናባቢ *<u>ሰርጎ-ገብ</u>* አናባቢ ሲባል፣ የማስገባቱ ሂደት ደግሞ *<u>ሰርገት</u>* ይባላል፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም ሰርጎ-ገብዋ አናባቢ በተናባቢዎቹ መካከል ስትገባ፣ በፊት የነበረው የቀለም አወቃቀር ይቀየራል ወይ? የሚል ነው፡፡ <u>ቀልድህ</u> [ቅኸልድእህ] የሚሰውን ቃል አንውሰድና ሁኔታውን አስቲ እንመልከተው፡፡ ቃሉ ሁለት ቀሰሞች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ቀለም በፊትም /ኸ/ በሚለው አናባቢ ምሰሶነት የተፈጠረውና ቀልድ [ቅኸልድ] የሚሰው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሰርጋ በገባችው አናባቢ አማካኝነት የተፈጠረው ሁለተኛው ቀሰም ነው፡፡ አፈጣጠሩም እንደሚከተለው ነው፡፡

(ሀ)  1

ቅኸልድእህ

በያናባቢው አናት ላይ የሚታዩት ቋሚ መስመሮች አናባቢዎቹ የቀለሙ ምሰሶ ወይም ቋሚ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ ቀደም ሲል ስለ ቀለም አወቃቀር ባየነው ሰርዓት መሰረት፣ አናባቢዎቹ መጀመሪያ በስተግራቸው ካለው አንድ ተናባቢ ጋር ይቀናጃሉ፡፡ ይህን ሲያደርጉ ቅንጅቱ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

2

(ለ) 

ቅኸልድእህ

ከዚህ በሁዋላ እያንዳንዱ አናባቢ በስተቀኙ ካለው ተናባቢ ጋር አንደገና ይዋቀራል፡፡ ይህ ሲሆን፣ በ(ለ) የተመለከተው መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

(መ) 3




በሰርጎ-ገብዋ እናባቢ ምክንያት ሁለት ቀለሞች ሊፈጠሩ ችለዋል፡፡

ሰርጎ-ገብዋ እናባቢ ከመግባትዋ በፊት የነበረው ቀለማዊ አወቃቀር የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

4




አሁን የዚህንና ከላይ በ(መ) የተመለከተውን የቀለም አወቃቀር እናነፃፅር፡፡ በዚህ ቀለም ውስጥ የጨራሹ ክፍል የሆነችው ተናባቢ ድምፅ፣ ማለትም [ድ]፣ በ(መ) ውስጥ ሰርጋ ከገባችው እናባቢ ጋር ተዋቅራ የሁለተኛው ቀለም ከፋች ተናባቢ ሆናለች፡፡ ያወቃቀር ለውጥ አድርጋለች ማለት ነው፡፡ ይህም ስለሆነ፣ የሁለቱ ቀለሞች ይዘት ከላይ እንደሚታየው [ቅኧል - ድእህ] የሚል ቅርፅ ሊይዝ ችሉአል፡፡ ሁለቱም ቀለሞች እኩል /ተአተ/ እና /ተአተ/ የሚል መዋቅር ሊይዙ ችለዋል፡፡ ባጭሩ /ተአተተ/ የነበረው መዋቅር፣ የመጨረሻ ተናባቢውን ለሁለተኛው ቀለም ሰጥቶ፣ /ተእተ/ ሆኖአል፡፡ ስለዚህም ከላይ ለተነሳው ጥያቄ መልሳችን፣ አወን የአወቃቀር ለውጥ ሲኖር ይችላል የሚል ነው፡፡ ለውጡም ሁለት ጨራሽ ተናባቢ ያለው ቀለም፣ የመጨረሻውን ጨራሽ ተናባቢ ለሚቀጥለው ቀለም ከፋች ተናባቢ እንዲሆን የሚያስገድድ ነው፡፡ ባጭሩ ብዙ ጨራሽ ተናባቢ ያለው፣ ምንም ከፋች ተናባቢ ለሌለው ቀለም እንደሚሰጥ ያሳያል፡፡

ከተሰጡት ምሳሌዎች እንደምንረዳው፣ እናባቢዋ ሰርጋ የምትገባው፣ በቀለሙ መድረሻ እና ቅድመ-መድረሻ ተናባቢዎች መካከል ነው፡፡ ሰርገቱ ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም፡፡ በቃል መነሻ ላይ በሚገኙ ተከታታይ ተናባቢ ድምፆች መካከልም ሊካሄድ ይችላል፡፡ ለዚህ የሚከተሉት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| /ል-ብ-ስ/ | [ልእብስ] | 5 |
| /ጥ-ብ-ቅ/ | [ጥእብቅ] | |
| /ው-ር-ስ/ | [ውእርስ] | |

ርግማን ([ርእግምእን] ) የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን፡፡ በሌላ በኩል፣ ይህችው አናባቢ ከመነሻው ተናባቢ፣ ማለትም ከ/ር/ ጋር ቦታ በመቀያየር በቃሉ መነሻ ላይ ስትገባ፣ [እርግምእን] የሚል ቅርፅ እናገኛለን፡፡ ይህ ቅርፅ ግን ከላይ ተጠቃሎ ከተቀመጠው ህግ ያፈነገጠ ነው፡፡ ምክንያቱም ከአአናባቢው ቀጥሎ ሶስት ተከታታይ ተናባቢዎች ስለሚገኙበት ነው፡፡ በቃል መካከል ቋንቋው የሚፈቅደው የሁለት ተናባቢዎችን ክትትሎሽ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የሶስቱን ተናባቢዎች ክትትሎሽ ለማስቀረት፣ ስርጎ-ገብዋን አአናባቢ ከሁለቱ ተከታታይ ተናባቢዎች ቀጥሎ እንደገና ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሲሆን፣ እርግማን ([እርግእምእን]) የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን፡፡ አአናባቢው ሁለት ሂደቶችን እእልፎአእል ማለት ነው፡፡ አአንደኛው ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች መግባት ሲሆን፣ ሁለተኛው ከመነሻው ተናባቢ ጋር ቦታ ተቀያይሮ የቃሉ የመነሻ ድምፅ መሆን ነው፡፡

ይህ ከመነሻው ተናባቢ ድምፅ ጋር ቦታ የመቀያየር ሂደት ግን ውሱን ነው፡፡ አናባቢው ቦታ የሚቀይረው የቃሉ የመነሻ ተናባቢ እንደ /ር፣ ን ፣ ል/ እና /ስ/ ያለ ቀጣይ ድምፅ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ <u>ቀጣይ</u> የሚባሉት ትንፋሽ ሳይቋረጥ የሚፈጠሩ ድምፆች ናቸው፡፡ እንደ /ክ፤ ድ፤ ግ፤ ወዘተ፤/ ካሉ ትንፋሽ ከሚቆርጡ ድምፆች ይለያሉ፡፡

በሌላ በኩል ግን ስርጎ-ገብዋ አናባቢ በሌሎች ተናባቢ ድምፆች በሚጀምሩ ቃላት መነሻ ላይም የምትገባ ትመስላለች፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | | |
|---|---|---|
| እደላ | [እድድኸልእ] | 10 |
| እገዳ | [እግግእድእ] | |
| እቅድ | [እቅቅእድ] | |
| እክት | [እክክእት] | |

እንደነዚህ ያሉ ቃላት ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው /ዕ/ በሚለው ተናባቢ የማንቁርት ድምፅ ነው፡፡ ለዚህ ምልክቱ ግሱ /አ/ በሚለው አናባቢ መጀመሩ ነው፡፡ ይኸውም አ<u>ደለ</u> /አድድኸለኸ/፣ አገደ /አግግእድኸ/፣ ወዘተ፣ ስንል ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአማርኛ ግስ ታህታይ ቅርፅ የሚጀምረው በጠቅላላው በተናባቢ ድምፅ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ስንነሳ፣ <u>አደለ</u> የሚለው ታህታይ ቅርፅም /ዕኸድድኸልኸ/ የሚል መሆን አለበት፡፡ ቀደም ሲል፤ ስለ ግድፈት ስንወያይ /ዕ፣ ው፣ ይ/ እና /ህ/ ባህሪያቸውን እጠገባቸው ለሚገኝ አናባቢ እያጋቡ እንደሚገደፉ ገልፀን ነበር፡፡ በዚሁ መሰረት /ዕ/ የታቾኛነት ባህሪዋን ከእስዋ ቀጥሎ ለሚገኘው ለ/ኸ/ አጋብታ ተገድፋለች፡፡ /ኸ/ም በዚሁ ተጋቦት ምክንያት ወደ /አ/ ተለውጣለች፡፡ ይህ እንግዲህ በግሱ ቅርፅ ላይ የሚካሄድ ለውጥ ነው፡፡

ከላይ የሚታዩት ቃላት ግን ስሞች ናቸው፡፡ አፈጣጠራቸውም ከግስ አፈጣጠር የተለየ ነው፡፡ ለምሳሌ <u>እደላ</u> የሚለውን ብንወስድ /ዕ-ድድ-ል/ ከሚለው

መስረት <u>ለበቅ</u> እና <u>በለቅ</u> የሚሉትን ቅርፆች አወጣጥ እንደሚከተለው አሳይተን ጉዳዩን እንቋጫለን፡፡

/ል$_1$ኧብ$_2$ኧቅ/ 7

[ል$_1$ኧብ$_2$ኧቅ] [ብ$_2$ኧል$_1$ኧቅ]

ታህታይ ቅርፁ በእዝባር የተመለከተው ነው፡፡ ከእሱ ላይ ሁለት ላዕላይ ቅርፆች ተመስርተዋል፡፡ የተመሰረቱትም የመጀመሪያዎቹን ሁለት ተናባቢዎች በቃ በመቀያየር ወይም ባለመቀያየር ነው፡፡ የሚቀያይረው [ብ$_2$ኧል$_1$ኧቅ] የሚለው የገጠሩ ቀበልኛ ቃል ነው፡፡

ይህን በዚህ እንተወውና በዚህ ክፍል እስካሁን በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃለው፡፡ በመሰረቱ ለማየት የሞከርነው ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮችን ነው፡፡ የመጀመሪያው በአማርኛ ውስጥ የሚገኙትን የንግግር ድምፆች መጠን፣ አይነትና አፈጣጠር መመርመር ሲሆን፣ ሁለተኛው የነዚህኑ ድምፆች አቀነጃጀትና ከዚህም ላይ የሚሰርፀውን የተለያየ ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት መመልከት ነው፡፡

የመጀመሪያውን በተመለከተ፣ ቋንቋው 30 ተናባቢዎችና ሰባት አናባቢዎች እንዳሉት አይተናል፡፡ ከተናባቢዎቹ መካከል 13ቱ አግድ፣ ሰባቱ ፍትግ፣ አራቱ ፍግድ፣ ሶስቱ ስርናዊ፣ ሁለቱ ከፍናቢ እና ሁለቱ ደግሞ ጎናዊ ናቸው፡፡ ይህ አከፋፈል ከባህርየ ፍጥረታቸው አኳያ ነው፡፡ ከመካነ ፍትረታቸው አንፃር ሲታዩ ደግሞ፣ ስድስቱ ከናፍራዊ፣(ለነፈራዊውን [ፍ]ን ጨምሮ)፣ ዘጠኙ ድዳዊ፣ ሰባቱ ዳላንቃዊ (ላንቃዊያኑን [ይ] እና [ኝ]ን ጨምሮ) ስድስቱ ትናጋዊ፣ ሁለቱ ደግሞ ማንቁርታዊ ናቸው፡፡

አናባቢዎቹ ደግሞ ሰባት ሲሆኑ፣ እነሱም ምላስ ወደ ፊትና ወደ ሁዋላ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አኳያ፣ የፊት፣ የመሀል እና የሁዋላ ተብለው፤ እንዲሁም ይኸው አካል ወደ ላይና ወደ ታች ከሚያደርገው እንቅስቃሴ አንፃር፣ ላየኛ፣ ልከኛና ታችኛ ተብለው በሶስት እንደሚከፈሉ አይተናል፡፡

ከ/ህ/ በስተቀር ተናባቢዎቹ በሙሉ ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡ ጥብቀቱም የትርጉም ልዩነትና የሰዋሰዋዊ ባህሪ ለውጥን ሊያስከትል ይችላል፡፡ እንደ <u>ገና</u> [ግኧንኣ] እና <u>ገና</u> [ግኧንንኣ] ያሉት የትርጉም ለውጥ የሚከሰትባቸው ቃላት ሲሆኑ፣ እንደ [ግእድድኣይ]፣ [ጥእርርኣጊ] ወዘተ፣ ያሉት የድራጊ፣ ማለትም የውጤት ስሞች፣ እና የተገብሮ ስሞች ናቸው፡፡ ተገብሮነትን ወደፊት እናየዋለን፡፡

የተናባቢዎቹን ስርጭ ስንመለከት፣ ከ/ኘ/ በስተቀር ማንኛውም ሌላ ተናባቢ ድምፅ በቃል መነሻ፣ መሀል ወይም መድረሻ ላይ ሊገባ ይችላል፡፡ /ኘ/

ብቻ በቃል መነሻ አይገኝም፡፡ ከአናባቢዎቹ መካከልም የመሀለኞቹ ብቻ በሁሉም ቦታ ሲገኙ፣ ዳረኞቹ በቃል መነሻ ብቻ አይገኙም፡፡

አቀነጃጀታቸውን ስንመለከት፣ ተናባቢ ድምፆች በቃል መነሻ ብቻ ተከታትለው አይመጡም፡፡ በሌላ ቦታም ቢሆን ከትትሎሹ ከሁለት ተናባቢዎች አይበልጥም፡፡ በልጦ ሲገኝ፣ ሶስተኛውን ተናባቢ ከሁለቱ ቀዳሚ ተናባቢዎች የሚለይ አናባቢ ድምፅ ሰርጎ ይገባል፡፡ ሁለተኛም ከሚከታተሉት ድምፆች የመጀመሪያው ልቅ መሆን አለበት፡፡ አናባቢ ድምፆች በላዕላይ ቅርፅ ተከታትለው አይገቡም፡፡ ከተከታተሉ አንድም ከሁለቱ አንደኛው ይገደፋል፣ ወይም ወደ ከፍናቢነት ይለወጣል፡፡ ወደ ከፍናቢነት የሚለወጡት የፊትና የሁዋላ አናባቢዎች ናቸው፡፡

በዚህ መሰረት አጠቃላዩ የቋንቋው ቀለም አወቃቀርም /ተ-አ-ተ/ የሚል ነው፡፡ በዚህ አይነት የሚዋቀሩ ቀለሞች እየተከታተሉ ሲገቡ፣ ከሚፈጠረው ንክኪ የተነሳ የአንዱ ድምፅ ባህሪ ወደ ሌላው ድምፅ የመጋባት ሂደት ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚታዩት የመካነ ፍጥረት ባህሪያት ከናፍራዊነት፣ ላንቃዊነትና ትናጋዊነት ናቸው፡፡ ከባህሪየ ፍጥረት አኳዋያ ደግሞ ድምፀት፣ ኢድምፀት፣ ጥብቀት፣ ልለት፣ ማንቁርታዊነት ዋና ዋናዎቹ ሂደቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የድምፅ ግድፈት፣ ሰርገት ወይም ቦታ ቅየራ ሊከሰት እንደሚችል አይተናል፡፡

ድምፀ-ልሳናዊ ሂደቶቹ በምዕላድ ውስጥ፣ በምዕላድ ድንበር ወይም በቃል ድንበር ላይ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ በዚህ ረገድ፣ ከፊል ላንቃዊነት በምዕላድ ውስጥ ሊከሰት፣ ሙሉ (ድ)ላንቃዊነትና ኢድምፀት በምዕላድ ድንበር ላይ እንደሚከሰቱ አይተናል፡፡ በዚህም ይህን ክፍል ተሰናብተን ወደሚቀጥለው እንሄዳለን፡፡

## መልመጃ

1. የምላስን ፊተኛ መሀለኛ እና ሁዋለኛ ክፍሎች መሰረት በማድረግ የአማርኛን ድምፆች በጠቅላላ በሶስት ክፍሎች ይመድቡ፡፡

2. ካላገኘንባቸውስ የሚለውን ቃል በፎኒማዊ ስርዓት ይፃፉና ፎኒሞቹን በባህርየ ፍጥረታቸው መሰረት ይከፋፍሉ፡፡

3. /ኸ/ እና /ኘ/ ፎኒም መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ጥንድ ጥንድ ቃላት ይፈልጉ፡፡

4. የሚከተሉተን ድምፆች መካነ-ፍጥረት ይግለፁ፡፡

   [ ም፣ ፍ፣ ጥ፣ ት፣ ስ ፣ ሽ፣ ጅ፣ ኽ፣ ቅ]

5.

| | | |
|---|---|---|
| ጥ | → | ጭ |
| ት | | ች |
| ድ | | ጅ |
| ዝ | | ዥ |
| ስ | | ሽ |
| ን | | ኝ |

(ሀ) ከቀስቱ በፊት (በስተግራ) የሚታዩት ድምፆች ከቀስቱ በስተቀኝ ወደሚታዩት አቻ ድምፆች የሚለወጡበትን ሂደት ይግለፁ።

(ለ) ለእያንዳንዱ ድምፅ ለውጥ ምሳሌ የሚሆን ቃል በፎኒማዊ አፃፃፍ ያሳዩ።

6. ጣለ፣ ማሰ፣ ሳለ፣ ወዘተ፣ የሚሉት ቃላት ስላ፣ ሰላ፣ ጠፋ፣ ወዘተ፣ ከሚሉት ቃላት ጋር እንዴት እንደሚመሳሰሉና እንዴት እንደሚለያዩ ያስረዱ።

7. በርታ፣ በረታ፣ አበረታታ፣ ካላበረታታህ የሚሉትን ቃላት የቀለም እወቃቀር ስርዓት ያሳዩ።

8. <u>ቀጤማ</u> እና <u>ቄጠማ</u> እንዲሁም <u>ሚስጥር</u> እና <u>ምስጢር</u> በትርጉም አንድ ናቸው። በቅርፅ ግን መጠነኛ ልዩነት ያሳያሉ። የልዩነታቸው ምክንያት ምን እንደሆነ ይግለፁ።

9. /ፍ/ ፤ /እ/ ፤ /ዝ/ ፤ /ከ/

(ሀ) እነዚህን ፎኒሞች በመጠቀም በአማርኛ የቀለም አወቃቀር ስርዓት መሰረት ሊፈጠሩ የሚችሉ ቀለሞችን አሳይ።

(ለ) ከቀለሞቹ መካከል በአንዱ ውስጥ /ዝ/ ወደ [ስ] ይለወጣል። የለውጡን ሂደትና አቅጣጫ ይግለፁ።

10. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት በፎኒማዊ ስርዓት ይፃፉ።

እንክብል፣ እበት፣ እንቁላል፣ ሙጫ፣ ቅቅል፣ መቸ

11. ጥበቀት የትርጉም ለውጥ እንዴት እንደሚያስከትል ጥንድ ጥንድ ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ።

# ምዕራፍ ሁለት

## ስነ-ቃላት

"መጀመሪያ ቃል ነበር" ዮሀንስ፣ምዕ. ፩፣ ቁ. ፩

### መግቢያ

ባለፈው ምዕራፍ ስለ አማርኛ ድምፆች አፈጣጠር፣ አይነት፣ አቀነጃጀትና ስለሚያደርጉት ስነ-ድምፀ-ልሳናዊ ለውጥ ተወያይተናል። ድምፆች ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ቀለሞችን ነው። ቀለሞች ትርጉም ሊኖራቸው ወይም ላይኖራቸው ይችላል። ትርጉም ያላቸው፣ ትርጉም ከሌላቸው ተለይተው ምዕላድ ይባላሉ። ምዕላዶች ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ቃልን ነው። ድምፆች የቀለም፣ የምዕላድ እንዲሁም የቃል መሰረት ናቸው ማለት ነው። ይህ ከሆነ፣ "መጀመሪያ ቃል ነበር" የሚለው ጥቅስ "መጀመሪያ ድምፅ ነበር፣ ድምፅም ቃል ሆነ" ማለት ነበረበት። ይህ ያልሆነበት ምክንያት አለው። ድምፆች በራሳቸው ትርጉም የላቸውም። ትርጉም ያላቸው የነሱ ቅንጅት የሆኑት ምዕላድና ቃላት ናቸው። የሰው ልጅም ሀሳቡን የሚያስተላልፈው ጎደለ ሲባል በቃላት፣ ሞላ ሲባል በአረፍተ ነገር ነው። ርግጥ፣ አንዳንድ ጊዜ ድምፅንና ቃልን አንድ አድርጎ የማየት ሁኔታ አለ። ድምፃችንን እናሰማ ስንል፣ እንናገር ማለታችን ነው። ከዚህ አንፃር ድምፅ እንደ ቃል ሊቆጠር ይችላል።

ከዚህም አልፎ ቃላት እንደ ዘር ሊታዩ ይችላሉ። ይበቅላሉ፣ ሀረግ ይሰዳሉ፣ ያብባሉ፣ በመጨረሻም ያፈራሉ። ፍሬአቸውም ያው ከፍ ሲል የጠቀስነው ትርጉማቸው ነው። በተራ ቃላትነት፣ ማለትም በዘርነታቸው፣ የሚሰጡት ትርጉም አንዱ ሲሆን፣ አድገው ሀረግ ሲሰዱና አረፍተ ነገር ሲመሰርቱ የሚሰጡት ትርጉም ሌላው አይነት ነው። ሁለቱን ትርጉሞች ቃላዊና አረፍተ ነገራዊ ብለን ልንለያቸው እንችላለን። የአረፍተ ነገር ትርጉም በከፊል አረፍተ ነገሩን የሚመሰርቱት ቃላት ትርጉም ድምር ውጤት ነው። በከፊል የተባለበት ምክንያት፣ አረፍተ ነገሩን የሚመሰርቱት ቃላት[1] አገባብም ለትርጉሙ አስተዋፅዖ ስለሚኖረው ነው። ለዚህ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች እንመልከት።

(ሀ) አንበሳ ነብር ነከሰ 1
(ለ) ነብር አንበሳ ነከሰ

[1] በርግጥ፣ እነዚህ ነገሮች በአረፍተ ነገር ደረጃ ሲታዩ፣ ቃላት አይደሉም፤ ሀረጎች ናቸው። እዚህ ላይ ውይይታችን ስለ ቃላት ስለሆነ፣ ለጊዜው ቃላት እያልን እንጠራቸዋለን። ለምን ሀረግ እንደሚባሉ በምዕራፍ ሶስት እንገልፃለን።

ሁለቱም አረፍተ ነገሮች የተመሰረቱት ከአንድ አይነት ቃላት ነው። ይሁን እንጂ፣ የአረፍተ ነገሮቹ ትርጉም ለየቅል ነው። የልዩነቱ መንስዔ አንበሳ እና ነብር የሚሉት ቃላት አገባብ የተለያየ መሆኑ ነው። በመጀመሪያው ምሳሌ፣ አንበሳ የሚለው ቃል የአረፍተ ነገሩ መነሻ ሆኖ ሲገባ፣ በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ የአረፍተ ነገሩ ቅድመ-መድረሻ ሆኖ ገብቶአል። በዚህም የአገባብ ልዩነት ምክንያት የትርጉም ለውጥ ሊከሰት ችሎአል። ይህም፣ አገባብ ለአረፍተ ነገራዊ ትርጉም ያለውን አስተዋፅዖ ያሳያል። በዚህ ምዕራፍ የምናየው ቃላዊውንም ሆነ አረፍተ ነገራዊውን ትርጉም አይደለም። ትኩረታችን በቃላት አይነትና ውስጣዊ የአቀነባበር ስርዓት ላይ ነው።

የእህል ዘር አይነት የተለያየ እንደሆነ ሁሉ፣ የቃላት ዘር አይነትም እንደዚሁ የተለያየ ነው። ልዩነቱ የቅርፅና የተግባር ነው። በአንድ በኩል ነገሮችንና የነገሮችን ባህሪ የሚገልፁ ቃላት አሉ። በሌላ በኩል የነገሮችን ተግባርና የአተገባበር ሁኔታ የሚገልፁ ሌሎች ቃላት አሉ። በዚህም መሰረት ቃላትን በጥቅሉ የነገርና የተግባር ወይም ድርጊት ብሎ በሁለት ብቻ መክፈል ይቻላል። የየክፍሉ ቃላት ቅርፅም በመጠኑም ቢሆን የተለያየ ነው። ልዩነቱን በዚህ መዕራፍ ዘርዘር አድርገን እናየዋለን።

አንድ ገበሬ በአንድ አካባቢ የሚገኙን የእህል ዘር በአይነት በአይነት እየለየ በተለያየ ዕቃ እንደሚያስቀምጥና በሁዋላም በተለያየ ወቅትና ማሳ ላይ ዘርቶ፣ ለተለያየ ዓላማ እንደሚያመርት ሁሉ፣ አንድ የስነ-ልሳን ባለሙያም በአንድ ቋንቋዋ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን እንደየቅርፅና ተግባራቸው በተለያየ መደብ እየመደበ ለተለያየ ተግባር የት፣ እንዴት እና መቼ እንደሚውሉ ማህበራዊ ህጋጋቱንና ስነ-ልሳናዊ ስርዓቱን ያስቀምጣል። በዚሁ መሰረት በአማርኛ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት እንደዚሁ በወገን በወገናቸው እየመደብን እናስቀምጣቸዋለን። የአንዱ ወገን ቃለት ተገባርም ከሌላው ወገን የተለየ እንደሆነ ለማሳየት እንሞክራለን። ወደ አመዳደቡ ከመግባታችን በፊት ግን በጥቅሉ ቃል የምንለው ነገር ምን ማለት እንደሆነ ትንሽ ዘርዘር አድርገን ማየት ይኖርብናል። ብዙ ጊዜ ለመግለፅ የሚያስቸግረን የምናውቀው የሚመስለን ነገር ስለሆነ፣ የዚህን ምዕራፍ ውይይት በቃል ትርጉም እንጀምራለን።

## ቃል

የቃልን ምንነት በወጉ ለመግለፅ፣ ከቃል አሰፍ ብለን በምዕላድ መጀመር አለብን። ባለፈው ምዕራፍ እንደገለፅነው፣ ምዕላድ የምንለው አንድን ትርጉም-አዘል የሆነንና አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን የማይችልን የመጨረሻ ንዑስ አሀድ ነው። ሰው የሚለውን አሀድ እንውሰድና ነገሩን በምሳሌ እንረዳው። ይህ አሀድ ትርጉም-አዘል ነው። ትርጉም አሰው ማለት ነው። ትርጉሙ አሀዱን በምንሰማበት ጊዜ በአዕምሮአችን የሚሰማንና በአይናችንም ልናየው የምንችለው ነገር ነው። አሀዱ ወደ አነስተኛ ትርጉም-አዘል ክፍሎች

ሊከፈል አይችልም፡፡ ቢከፈል የምናገኘው ፎኒሞችን ይሆናል፡፡ ፎኒሞች ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ትርጉም የላቸውም፡፡ ስለዚህም ሰው የሚለው አሀድ ምዕላድ ነው፡፡

ሰዎች የሚለውን አሀድ ደግሞ እንውሰድ፡፡ ይህም ትርጉም-አዘል ነው፡፡ በዚህም ሰው ከሚለው አሀድ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ሰዎች /ሰእው/ እና /-ኦችች/[2] ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል፡፡ ሁለቱ ክፋዮችም ትርጉም-አዘል ናቸው፡፡ የ/-ኦችች/ ትርጉም ከአንድ በላይ የሆነ፣ ጥቂት ወይም ብዙ ማለት ነው፡፡ /-ኦችች/ም ሰው እንደሚለው አሀድ አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል አሀዶች ሊከፈል አይችልም፡፡ ስለዚህም ምዕላድ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ /-ኦችች/ ሰው እንደሚለው ምዕላድ ራሱን ችሎ ሊቆም አይችልም፡፡ ስለዚህም እንደ ሰው ካለ ራሱን ችሎ ሊቆም ከሚችል ምዕላድ ጎን መጠጋት አለበት፡፡ ይህን ሊያደርግ የምናገኘው /ሰእው-ኦችች/ የሚለውን አሀድ ይሆናል፡፡ ይህ አሀድ ከሁለቱ ምዕላዶች የተመሰረተ ስለሆነ፣ ምዕላድ አይደለም፣ ከምዕላድ በላይ ነው፡፡ አንድ ከምዕላድ በላይ የሆነ አሀድ ቃል ይባላል፡፡ ስለዚህም /ሰእው/ እና /-ኦችች/ ምዕላድ ሲሆኑ፣ ከሁለቱ ቅንጅት የተገኘው ሰዎች የሚለው አሀድ ግን ምዕላድ ሳይሆን ቃል ነው፡፡

ነገሩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ሆዳም የሚለውን አሀድ ደግሞ እንመልከት፡፡ ይህ አሀድ ትርጉም አለው፡፡ አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡፡ ክፍሎቹም ሆድ እና /-እም/ የሚሉት አሀዶች ናቸው፡፡ ሁለቱም ትርጉም አላቸው፡፡ የሆድ ትርጉም ግልፅ ነው፡፡ የ/-እም/ ትርጉም ግን ትንሽ ገለፃ ያስፈልገዋል፡፡ /-እም/ አንድን ስም የሆ ቃል ወደ ቅፅል የመለወጥ ተግባር ያለው ቅጣይ ነው፡፡ በዚህም ተግባሩ ምክንያት ቅፅል መስራች ምዕላድ ልንለው እንችላለን፡፡ እንደ ሆድ ያለ ስም የሆነ አሀድ እንደ /-እም/ ያለ ቅጣይ ሲከተለው ቅፅል ይሆናል፡፡ ሁለቱም አሀዶች አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል አሀዶች ሊከፈሉ ስለማይችሉ ምዕላዶች ናቸው፡፡ ከሁለቱ ምዕላዶች የተመሰረተው ሆዳም የሚለው አሀድ ግን፣ የሁለቱ ምዕላዶች ቅንጅት የሆነ ቃል ነው፡፡ እንደ /-ኦችች/ ሁሉ፣ /-እም/ም ራሱን ችሎ የሚቆም ምዕላድ ሳይሆን፣ እንደ ሆድ ካለ ራስ-ቻይ ምዕላድ ጎን የሚጠጋ ነው፡፡

ከምሳሌዎቹ የምንረዳው፣ ምዕላድ ትርጉም-አዘልና አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊከፈል የማይችል ንዑስ አሀድ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ምዕላዶች ራሳቸውን ችለው ሊቆሙ እንደሚችሉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ይህን ማድረግ እንደማይችሉ ተገንዝበናል፡፡ እንደ ሰው እና ሆድ ያሉት ራሳቸውን ችለው ከሚቆሙት ወገን ሲሆኑ፣ እንደ /-ኦችች/ እና /-እም/ ያሉት ራሳቸውን ከማይችሉት ወገን የሚመደቡ ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ምዕላዶች ባጠቃላይ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙና የማይቆሙ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙት ነፃ፣ ራሳቸውን የማይችሉት ጥገኛ

---

[2] ቅጣይ ምዕላዶችን በአዝባር ውስጥ በፎኒማዊ አፃፃፍ እናመለክታለን፡፡ ይህም አፃፃፍ ከስርዓተ ፅህፈት የተለየ እንደሆነ እናስገነዝባለን፡፡

ምዕላድ ይባላሉ፡፡ ጉዳዩ እንደ ወላጅና እንደ ልጅ ግንኙነት መሆኑ ነው፡፡ ልጅ የወላጅ ጥገኛ ነው፡፡ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ 'የገሌ ልጅ' ይባላል እንጅ፣ 'እገሌ' እየተባለ በራሱ ስም ላይጠራ ይችላል፡፡ ልዩነቱ ልጅ ሲያድግ ነፃ ይሆናል፡፡ ጥገኛ ምዕላድ ግን ሁሌም ጥገኛ ነው፡ አልፎ አልፎ ነፃ የነበሩ ምዕለዶችም ጥገኛ የሚሆኑበት ጊዜ አለ፡፡ ይህም ደጋፊ እንደሚሹ አዛውንት ወላጆች መሆኑ ነው፡፡ ወደ ዋናው ጉዳይ እንመለስ፡፡

ጥገኛ ምዕላዶች ከነፃ ምዕላዶች ካልተጠጉ ትርጉም አይኖራቸውም፡፡ ለምሳሌ /-እችች/ የሚለው ምዕላድ ብቻውን ቢነገር፣ ምንም ትርጉም አይኖረውም፡፡ ብዛትን የሚያመለክተው ሊቆጠር የሚችል ነገርን ከሚገልፁ ስሞች ቀኝ ጎን ሲጠጋና የስሞቹ አካል ሲሆን ነው፡፡ ይህን ሲያደርግ ያ እሱ የተጠጋበት ቃል መጠናቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ነገሮችን እንደሚያመለክት ያሳያል፡፡ አንድ ምዕላድ ጥገኛ መሆኑን ለማመልከት ከጎኑ ላይ ጭረት(-) እናስቀምጣለን፡፡

ስለ ምዕላድ ይህን ያህል ከተገነዘብን፣ በምዕላድና በቃል መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ደግሞ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ መጀመሪያ ነገር፣ እንደ ምዕላድ ሁሉ፣ ቃልም ትርጉም-አዘል አሀድ ነው፡፡ ሁለተኛም፣ ቃል ራሱን ችሎ መቆም ስለሚችል ነፃ ነው፡፡ በዚህም ባህሪው ከነፃ ምዕላድ ጋር ሊመደብ ይችላል፡፡ ሶስተኛም፣ ቃል በውስጡ ብዙ ጥገኛ ምዕላዶችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ትርጉም-አዘል ወደሆኑ አነስተኛ ክፍሎች ሊሸነሸን ይችላል ማለት ነው፡፡ በዚህ ባህሪው ደግሞ (ከነፃ) ምዕላድ ይለያል፡፡ ምክንያቱም ምዕላድ የሆነ አሀድ ትርጉም-አዘል ወደሆኑ አነስተኛ ክፍሎች ሊሸነሸን አይችልም ብለናልና፡፡ አራተኛ፣ ቃል ከቃላት ክፍሎች ውስጥ ባንዱ ሊመደብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ሆዳም የሚለውን አሀድ ብንወስድ፣ ወደፊት በሰፊው እንደምናየው፣ ቅፅል በሚባለው የቃል ክፍል ውስጥ የሚመደብ አሀድ ነው፡፡ ምዕላድ ግን በዚህ አይነት ላይመደብ ይችላል፤ በተለይ ጥገኛ ከሆነ፡፡ ምናልባት እንደ /-እም/ ያለው ምዕላድ አንድን ስም የሆነ ቃል ወደ ቅፅል የሚለውጥ ስለሆነ፣ ራሱም በቅፅል ክፍል ሊመደብ ይችል ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ፣ እንደ /-እም/ ያለ አሀድ ንዑስ ወይም ቅጣይ ቅፅል ሊባል ይችላል፡፡ እንደዚህ እያደረጉ ቅጣዮችን በክፍል፣ በክፍል መመደብ ሁል ጊዜ ቀላል አይደለም፡፡ በየትኛውም የቃላት ክፍል ውስጥ ሊመደቡ የማይችሉ ምዕላዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ /-ስ/ የሚለው አሀድ ጥገኛ ምዕላድ ነው፡፡ <u>እኔ-ስ</u>፣ <u>አንተ-ስ</u>፣ ወዘተ፣ ሰንል በግልፅ እናየዋለን፡፡ ምድቡ ግን ወደፊት ከምናያቸው የቃላት ክፍሎች፣ ከየትኛውም ጋር አይገጥምም፡፡ ሌሎችም እንደዚህ ያሉ ምዕላዶች አሉ፡፡ ወደፊት እናያቸዋለን፡፡

እንግዲህ ከላይ ከአንድ እስከ አራት የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሙዋላ ማንኛውም አሀድ ቃል ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት <u>ሆድ</u> የሚለውን አሀድ እንደገና እንመርምረው፡፡ ትርጉም-አዘል ስለሆነ፣ ነፃ ስለሆነና ከቃላት ክፍሎች ውስጥም ባንዱ፣ ማለትም ስም በሚባለው ክፍል፣ ሊመደብ ስለሚችል ቃል ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ነፃ ምዕላድም ነው ሊባል ይችላል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አነስተኛ ወደሆኑ ትርጉም-አዘል ክፍሎች ሊሸነሸን ስለማይችል ነው፡፡

ወደ እነስተኛ ክፍሎች ብንከፋፍለው፣ የምናገኘው እሀዱ የተመሰረተባቸውን ፎኒሞች ብቻ ነው። ፎኒሞች ደግሞ ትርጉም ያላቸው እሀዶችን ይመሰርታሉ እንጅ፣ ራሳቸው ትርጉም እንደሌላቸው ቀደም ሲል ገልፀናል። ስለዚህም ሆድ የሚለው እሀድ የምዕላድንም ሆነ የቃልን ባሀሪ በከፊል ስለሚያሟላ ምድቡ ከቃል ወይም ከምዕላድ ሊሆን ይችላል። በሌላ አነጋገር፣ ነፃ ምዕላዶች ቃልም፣ ምዕላድም ናቸው።

ሆዳም የሚለውን እሀድ ብንወስድ ግን ሁኔታው ከዚህ የተለየ እንደሆነ እንረዳለን። ሆዳም የሚለው በውስጡ ሁለት ምዕላዶች ስላሉት፣ ማለትም ትርጉም-እዘል ወደሆኑ እሀዶች ሲከፈል ስለሚችል፣ ቃል እንጅ ምዕላድ አይሆንም። ከቃልም ባለሁለት ምዕላድ ቃል ስለሆነ፣ እንደ ሆድ ካለ ተራ ነፃ ምዕላድ የተለየ ነው። ይሁን እንጅ፣ ሆድ ከሚለው ጋርም አንድነት አለው። ይኸውም ሁለቱም ቃል መሆናቸው ሲሆን፣ ልዩነታቸው ሆድ የሚለው ብቻ ነፃ ምዕላድ መሆኑ ነው።

እንደነዚህ ያሉ ተራ ነፃ ምዕላዶች ተራ ፎኒማዊ ቃላት ሊባሉ ይችላሉ። ፎኒማዊ የሚያሰኛቸው መስረተ ነገራቸው ፎኒሞች መሆናቸው ነው። ቢከፋፈሉም ክፍልፋዮቹ ፎኒሞች ናቸው። ለምሳሌ ሆድ የሚለውን ምዕላድ ብንከፋፍለው፣ ውጤቱ /ሀ/፣ /እ/ እና /ድ/ የሚሉት ሶስት ፎኒሞች ናቸው። ስለዚህም እሀዱ ፎኒማዊ ምዕላድ ወይም ፎኒማዊ ቃል ነው።

እንደ ሆዳም ያሉት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ጥገኛ ምዕላዶችን በውስጣቸው የያዙ እሀዶች ምዕላዳዊ ቃላት ሊባሉ ይችላሉ። ምዕላዳዊ የሚስኙበት ምክንያት፣ የምዕላዶች ቅንጅት ውጤት መሆናቸው ነው። ስለዚህም የፎኒሞች ቅንጅት ከሆኑት ነፃ ፎኒማዊ ምዕላዶች ይለያሉ። በጥቅሉ ቃላትን የምዕላዶች፣ ምዕላዶችን ደግሞ የፎኒሞች ቅንጅት አድርጎ መውሰድና አንዱን ከሌላው በዚሁ መስረት መለየት ይቻላል። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ ማንኛውም ቋንቋ የነፃና የጥገኛ ምዕላዶች ክምችት ነው ሊባል ይችላል። ስለሆነም በዚህ ደረጃ የሚደረግ የአንድ ቋንቋ ጥናት በመሰረቱ ምዕላዶች እየተቀናጁ ቃላት እንዴት እንድሚመሰርቱ፣ እንዴትም በአይነት በአይነት እንደሚመደቡ፣ አንዱ አይነት ከሌላው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ የሚመረምር ነው። እኛም ከዚህ ቀጥለን ለማሳየት የምንሞክረው ይህንኑ ነው። የአማርኛ ቃላትን አቀነጃጀት፣ አከፋፈልና እያንዳንዱ ክፍልም ከሌላው ጋር ያለውን ተዛምዶ ማየት።

## የዋና ዋና ቃላት ክፍል

የምዕላድንና የቃልን አንድነትና ልዩነት ባለፈው ንዑስ ክፍል ለማየት ሞክረናል። ምዕላድ ከፎኒሞች የሚፈጠር ትርጉም-እዘል ንዑስ አሀድ እንደሆነ፣ ቃል ደግሞ የምዕላዶች ቅንጅት እንደሆነ ገልፀናል። አንድ ቋንቋም የእነዚህ ክምችት ነው ሊባል እንደሚችል ጠቁመናል። ይህ ክምችት ግን በዘፈቀደ በአንድ ቦታ የተከመረ ሳይሆን፣ ነፃውም ሆነ ጥገኛው ምዕላድ በየወገኑ እየተለየ

እንዲታይ በየሚያስችል ስርዓት የተቀመጠ ነው፡፡ ብቃል ደረጃ በተናጠል ሊታይ የሚችለውን ቃላት በፊደል ተራ እየመዘገቡ በቋንቋዋ ትምህርትነት ለአዲሱ ትውልድ ማቅረብ፣ አለያም በቅርስነት ለመጭው ትውልድ ማቆየት ይቻላል፡፡ የእንከሳቱ ብርሃን ተሰማ መዝገበ ቃላት ለዚህ የሚጠቀሱ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ አላማቸው ቃላትን በቅደም ተከተል ከነተለያየ ትርጉማቸው ማስቀመጥ ነው፡፡ ውስጣዊ የአቀነጃጀት ስርዓታቸውን ማሳየት አይደለም፡፡ ሊሆንም አይችልም ነበር፡፡ ምክንያቱም አሁን ያለው ጥበብ ያኔ እንዳሁኑ በአካባቢያችን አልደበረም፡፡

በአንድ ቋንቋዋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ እንደሚገኙ ግለሰቦች ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ ቋንቋዋውም እንደ ማህበረበብ ሊታይ ይችላል፡፡ በዚያ ውስጥ፣ ቃላት እንደ ግለሰብ ተወልደው ሊያድጉ፣ አድገውም ሊያረጁና ሊሞቱ ይችላሉ፡፡ ቋንቋዋው ግን ይቀጥላል፤ እንደ ህብረተሰቡ፡፡ ጥሩ ምሳሌ ባይሆኑም፣ የማዕረግ ስሞቻችን ለዚህ ሁኔታ በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ዛሬ አንደነ እጋፋሪ፣ ባልደራስ፣ ነጋድራስ፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ስሞች ከጥቅም ውጭ ናቸው፡፡ በአብዛኛው ንግግራችን ውስጥ የሚሰሙ አይደሉም፡፡ ሞተዋል ማለት ግን አይቻልም፤ በመዝገበ ቃላት ውስጥ ይገኛሉና፡፡ ሞተዋል ሊባሉ የሚችሉት ከአንደበት እንደጠፉ ሁሉ፣ ከመዝገብም ባይገኙ ነበር፡፡

አንደነ ነጋድራስ ያሉት ቃላት በመጥፋት ላይ ያሉትን ያህል፣ አንደነ ሙሰኛ ያሉ አዳዲስ ቃላትም እየተወለዱ ወይም በትውሰት ወደ ቋንቋዋው እየገቡ ነው፡፡ ነባሮቹን በቅርሰነት፣ አዲሶቹን በአንግድነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ የሚቻለው በአጠቃላይ በፅሁፍ፣ በተለይ ደግሞ በመዝገበ ቃላት አማካኝነት ነው፡፡

ቃላትን በቅደም-ተከተል በመዝገበ ቃላት ማስቀመጥ፣ በዚህ ደረጃ ለሚደረግ ጥናት አንዱ ክፍል ነው፡፡ ግን ውሱን ክፍል ነው፡፡ ውሱን የሚያደርገው አዘጋጁ በሚገኝበት ህብረተሰብ ማህበራዊ የቋንቋዋ ችሎታ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው፡፡ ችሎታው በቋንቋዋው ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን ቃል ሁሉ አይሸፍንም፡፡ ሊሸፍን የሚችለው የማህበረሰቡን ግንዛቤ የሚገልፁትንና በአዘጋጁም የግል ችሎታና ትውስታ ውስጥ ያሉትን ቃላት ብቻ ነው፡፡ የቋንቋዋው የቃላት ይዞታ ግን በአንድ የማህበረሰባዊ ግንዛቤ አይወሰንም፤ አልፎ ይሄዳል፡፡ ለምሳሌ፣ መዝገበ ቃላት አዘጋጁ ግርጣት የሚለውን ቃል ስለሚያውቅ፣ በሚያዘጋጀው መዝገበ ቃላት ውስጥ ተርታ አሲዞ ሊያሰፍረው ይችላል፡፡ ብርናት የሚለውን ቃል ግን ሊያሰፍረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ቃሉ ከእሱም ሆነ ከማህበረሰቡ ወቅታዊ የቋንቋዋ ችሎታ ውጭ ነው፡፡ ከቋንቋዋው ስርዓት ውጭ ግን አይደለም፡፡ ምክንያቱም ስርዓቱ በረታ ብሎ ብርታት፣ ገረጣ ብሎ ግርጣት የሚል የቃላት አካሄድ ስላለው፣ በዚሁ ሂሳብ በረታ በሚለው ግስ አኩዋያ፣ በረና የሚል ግስ እውጥቶ፣ ከእሱ ላይ ደግሞ ብርናት የሚል ስም መመስረት ይቻላል፡፡ ቋንቋዋው እንደነዚህ ያሉ ገና ማህበረሰባዊ ያልሆኑ *ፅንሰ-ቃላት* አሉት፡፡ የሚገኙትም በአዕምሮአችን ውስጥ ነው፡፡ ማንኛውም የአማረኛ ቋንቋዋ ተናጋሪ ገረጣ ብሎ ግርጣት ማለት እንደሚችል ሁሉ፣ በረና

ብሎ <u>ብርናት</u> ማለት አያቀተውም፡፡ ትረጉሙን ግን ላያውቅ ይችላል፡፡ ምክንያቱም ቃሉ አዕምሮአዊ ብቻ ነውና፡፡ አንድ ቃል፣ ከአዕምሮአዊነት ወደ ማህበራዊነት ሲመጣ ማህበራዊ ትርጉም ያገኛል፡፡ ይህም ትርጉም አያደር ግለሰባዊ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ያውቀዋል ማለት ነው፡፡

እንደነዚህ ያሉ ፅንሰ-ቃላት ሰጥነታቸው ለመዝገበ ቃላት አዘጋጆች ሳይሆን፣ ለ*ስነ-ቃላት* ተመራማሪ ነው፡፡ ተመራማሪው የቋዋንቋዋውን ስርዓት ስለሚያውቅ፣ በዚያው መሰረት እንደነዚህ ያሉ ፅንሰ-ቃላትን እየፈለፈለ በማውጣት ለልዩ ልዩ ግንዛቤ ሰያሜ ሊያውላቸው ይችላል፡፡ በዚህም ማህበራዊ ያደርጋቸዋል፡፡ ማህበራዊ ሲሆኑ፣ መዝገበ ቃላት አዘጋጁም ሰለሚያውቃቸው፣ ተርታ አሲዞ በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ ያስፍራቸዋል፡፡ ባጨሩ፣ የስነ-ለሳኑ ባለሙያ ቃላትን ከአዕምሮአዊነት ወደ ማህበራዊነት ያመጣቸዋል፤ የመዝገበ ቃላቱ ባለሙያ ደግሞ መዝግቦ ከነማህበራዊ ትርጉማቸው ለተጠቃሚ ያቀርባቸዋል፡፡ ለትውለድም ያቆያቸዋል፡፡

የተመራማሪው ተግባር ቃላትን ባጠቃላይ በቅደም-ተከተል ሳይሆን፣ በአይነት በአይነት መመደብና በየምድቡ ውስጥ የሚገኙትንና ሊገኙ የሚችሉትንም ፅንሰ-ቃላት ጭምር ውስጣዊ የአወቃቀር ስርዓት መመርመር ነው፡፡ በዚህም መሰረት፣ በቅደም-ተከተል የመመዝገቡን ክፍል *ምዝገባ ቃላት*፣ ውስጣዊ አወቃቀራቸውን የሚመለከተውን ክፍል *ስርዓተ-ቃላት* በማለት ሁለቱን ክፍሎች ልንለያቸው እንችላለን፡፡ *ስነ-ቃላት* እነዚህን ሁለት ክፍሎች የሚያጠቃልል አቢይ ዘርፍ ነው፡፡ በዚህ ክፍል የምናተኩረው ግን በሁለተኛው ክፍል፣ ማለትም በቃላት ክፍፍልና ውስጣዊ ስርዓት ላይ ነው፡፡

ቃላትን በወገን በወገን መከፋፈሉ፣ የእያንዳንዱን ክፍል ባህሪ ለመገንዘብና አንዱ ክፍል ከሌላው ጋር ያለውን ዝምድና በቀላሉ ለማየት ያስችላል፡፡ የቋዋንቋዋውን አጠቃላይ ባህሪ ለማወቅ፣ ቋዋንቋዋውን እንዳለ በጥቅሉ እያገላበጡ ከማየት ይልቅ፣ ከፋፍሎ እያንዳንዱን ንዑስ ክፍል በተናጠል፣ ከዚያም አንዱን ክፍል ከሌላው ጋር በጋራ ማየቱ ስለ ቋዋንቋዋው ባህሪ የተሻለ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ ይችላል፡፡ በቋዋንቋዋው ውስጥ ወደ ሀምሳ ሺ የሚጠጉ ቃላት አሉ ብንል፣ እያንዳንዱን ቃል ወይም ምዕላድ እያነሱና እየጣሉ በተናጠል መመርመሩ ምን ያህል አድካሚና ጊዜ-ፈጅ እንደሚሆን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ ከዚህ ይልቅ ቃላቱንም ሆነ ምዕላዱን እንደ ተቀራራቢነታቸው በክፍል በክፍል እየመደቡ፣ እያንዳንዱን ክፍል በተናጠልና በትኩረት፣ ከዚያም በጋራና በንፅፅር ማየቱ ቀና እና ፍሬያማ አሰራር ነው፡፡ በዚህ መሰረት የአማርኛን ቃላት እንዴትና በስንት ሊመደቡ እንደሚችሉ ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን፡፡ ይህንን ስናደርግም ቃላቱ የሚመደቡባቸውን ክፍሎች ለመለየት ቀደምት የስዋሰው ሊቃውንት ይጠቀሙባቸው የነበሩትን ሰያሜዎች እንደ አስፈላጊነታቸው እንጠቀምባቸዋለን፡፡

ሊቃውንቱ የአማርኛ ቃላት በሙሉ በስምንት ዋና ዋና ክፍሎች እንደሚመደቡና የክፍሎቹም ለሞች የሚከተሉት እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡

የቃላት ክፍል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስም | ግስ | መስተዋድድ | 2 |
| ተውላጠ ስም | ተውሳከ ግስ | መስተፃምር | |
| ቅፅል | | ቃለ-አጋኖ | |

እነዚህ እያንዳንዳቸው በንዑስ በንዑስ ክፍል ይመደባሉ። ለምሳሌ፣ ስም የሚለው ክፍል የወል፣ የተፀውዖ፣ የጥቅል፣ የረቂቅ፣ የቁሳቁስ ወዘተ፣ እየተባለ እንደገና ይለያል። በቁዋንቁዋው ውስጥ የሚገኙት ቃላት ግን በነዚህ በስምንቱም ሆነ በንዑስ ክፍሎቻቸው ብቻ የሚወሰኑ አይደሉም። በነዚህ በአንዱም ሊመደቡ የማይችሉ በርካታ ምዕላዶች አሉ። ያም ሆኖ የቃላቱ በዚህ አይነት መከፋፈል፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ እያንዳንዱን ቃል በስም እየጠቀሱ ባህሪውን ከመዘርዘር ይልቅ፣ በክፍል ስሙ፣ ስም፣ ግስ፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ እያሉ መለየቱ፣ ተናጠል ባህሪውን ከክፍሉ ባህሪ አንፃር ለማየት ስለሚረዳ ከአጠናንም ሆነ ከውጤት አኩዋያ የሚመረጥ አካሄድ ነው።

ቃላቱ እንዴት በስምንት ብቻ ሊከፈሉ ቻሉ? አንዱ ቃል የአንዱ ወይም የሌላው ክፍል አባል ለመሆኑ ወይም ላለመሆኑ መለኪያው ምንድን ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ከዚህ ላይ ሊነሱ ይችላሉ። የቃላቱ አከፋፈል የተመሰረተው በምስስልነት ላይ ነው። ምስስልነቱ አንዳንድ ጊዜ የቅርፅ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የትርጉም ነው። ለምሳሌ፣ ተክለማሪያም ፋንታዬ አንድን ቃል ስም ወይም የስም ክፍል ነው ሲሉ፣ መነሻቸው ትርጉም ነው። ይኸውም ቃሉ ለመጠሪያነት የሚያገለግል መሆኑ ነው። ስለዚህም ለመጠሪያ ተግባር የሚውሉ ቃላት በዚሁ የተግባር ተመሳሳይነታቸው ስም ተብለው፣ ለመጠሪያ ተግባር ከማይውሉት ሌሎች ቃላት ይለያሉ። ይሁን እንጅ፣ መጠሪያነትን እንደ መስፈርት ከወሰድነው መጠሪያ ያልሆነ ቃል በቁዋንቁዋው ውስጥ የለም ለማለት ይቻላል። ግስና ቅፅል በሚባሉት ክፍሎች ውስጥ የሚመደቡትን ቃላት ወስደን፣ በስም ክፍል ውስጥ ከመመደብ የሚያግደን ነገር የለም። ምክንያቱም በነዚህ ክፍሎች ውስጥ የሚመደቡ ቃላትም ቢሆኑ፣ የድርጊትና የባህሪ መጠሪያ ወይም ስያሜ ናቸው ብሎ መከራከር ስለሚቻል ነው። ለምሳሌ እንደ <u>ዘፈነ</u>፣ <u>ጨፈረ</u>፣ <u>ቆረጠ</u>፣ ወዘተ፣ ያሉትን ቃላት ብንወስድ፣ የሚያመለክቱት ወይም የሚሰይሙት የመዝፈንን፣ የመጨፈርንና የመቁረጥን ተግባር ነው። <u>ጨፈረ</u> ስንል፣ የምናመለክተው የጭፈራ ተግባርን ነው። እንደዚሁም እንደ <u>ረዥም</u>፣ <u>ብልህ</u>፣ <u>ጥቁር</u>፣ ወዘተ፣ ያሉትን ብናይ፣ መጠንን፣ ባህሪንና አይነትን የሚጠቁሙ ቃላት ሆነው እናገኛቸዋለን። እነዚህም በስም ውስጥ እንደሚመደቡት ቃላት ሁሉ ለመጠሪያነት ሲያገለግሉ ይችላሉ። ይህ ከሆነ ምድባቸው በስም ውስጥ ይሆናል።

ይህ አካሄድ ግን በቁዋንቁዋው ውስጥ የሚገኘውን ቃል ሁሉ ባንድ ክፍል ውስጥ የሚያጉር ነው። ምናልባት፣ አከፋፈሉን በመጠሪያነት ላይ ሳይሆን፣ በሚጠሩት ነገሮች ልዩነት ላይ ብንመሰርተው፣ የተለያዩ የመጠሪያ ክፍሎችን ልናገኝ እንችላለን። ይኸውም የነገሮች፣ የድርጊቶች፣ የሁነቶች፣ የባህሪያት፣ ወዘተ መጠሪያ እያልን በመለያየት ነው። እንደዚህም ሆኖ አከፋፈሉ የጠራ አይሆንም። ነገሮች የምንላቸው ምንድን ናቸው? ወደሚል የፍልስፍና

ጥያቄም ሊወሰደን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፤ ብልግና የሚለውን ቃል ብንወስድ፣ መጠሪያነቱ ለነገር፣ ለተግባር ወይስ ለባህሪ? መልሱ አስቸጋሪ ነው፡፡ በሌላ በኩል፤ እንደ ዛፍ ያለ ቃል መጠሪያነቱ ለነገር መሆኑ ብዙም የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ በተጨማሪም እንደ ዛፍ ያሉ ቃላት የድርጊት መጠሪያ ከሚባሉት የተለዩ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ልዩነታቸው የቅርፅ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ እንደ ዛፍ ያሉት፣ ነገሮችን የሚያመለክቱ ቃላት፤ የብዛት ምልክት የሆነውን /-ኦችች/ን ለማስከተል ሲችሉ፣ የድርጊት መጠሪያ የሆኑት ይህን ምልክት ሊያስከትሉ ከቶም አይችሉም፡፡ ስለዚህም ዛፍ ብሎ ዛፍ-ኦች ማለት ሲቻል፣ ጎደለ ብሎ ጎደለ-ኦች ማለት አይቻልም፡፡ /-ኦችች/ን ማስከተል መቻልና አለመቻል በነገሮችና በድርጊቶች መጠሪያዎች መካከል ያለ አንድ ልዩነት ነው፡፡ ስለሆነም ከዚሁ በመነሳት /-ኦችች/ን ሊያስከትሉ የሚችሉና የማይችሉ ብሎ፤ ቃላትን በቅርፃቸው ብቻ በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡ ይህ አይነቱ አከፋፈልም መጠሪያ የሆነ ወይም ያልሆነ በሚል ትርጉማዊ መስፈርት ላይ የተመሰረተ ሳይሆን፣ ቃላቱ በሚያሳዩት የቅርፅ ልዩነት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ሲበዙ /-ኦችች/ን ሊያስከትሉ የሚችሉና የማይችሉ ብሎ ቃላትን በሁለት መክፈል፣ የነገሮች፣ የድርጊቶች፣ የባህሪያት፣ ወዘተ፤ መጠሪያ የሆኑና ያልሆኑ ከሚለው አከፋፈል እጅግ የተሻለ ነው፡፡ ቢያንስ ነገሮች ምንድን ናቸው? ከድርጊቶችና ከባህሪያትስ እንዴት ይለያሉ ወደሚሉ ጥያቄዎች አይወስደንም፡፡

አንዳንድ ጊዜ ሊቃውንቱ መጠሪያ የሚለው ቃል ያዘለውን ፅንሰ-ሀሳብ ለማጥበብና ስም በሚለው ክፍል ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉትን ቃላት መጠን ለመወሰን ሲሉ፣ መጠሪያነትን ለሰው፣ ለቦታና ለነገሮች ብቻ ይወስኑታል፡፡ የሰውና የቦታ መጠሪያ ሊሆኑ የሚችሉትን ምናልባት በቀላሉ መለየት ይቻል ይሆናል፡፡ የነገሮች መጠሪያ የሚሆኑትን ቃላት መለየት ግን አሁንም አስቸጋሪ ነው፡፡ ሞት፣ ህይወት፣ ህልም፣ ዕውቀት፣ ወዘተ፤ ነገሮች ናቸው ወይስ አይደሉም? መለኪያው ምንድን ነው? ቤት፣ ዛፍ፣ ፈረስ፣ ወዘተ፣ ከሚሉት የነገሮች መጠሪያ በምን ይለያሉ? የማይለዩ ከሆነ፣ የሰው፣ የቦታና የነገሮች መጠሪያ ብሎ መደንገጉ ምን ያህል ያስኬዳል? የሚለዩ ከሆነ፣ እንደነዚህ ያሉ ቃላት ክፍላቸው ከምን ይሆናል? የሚሉ በርካታ ጥያቄዎች ሲነሱ ይችላሉ፡፡

በትርጉም ላይ የተመሰረተ የቃላት አከፋፈልም እንደነዚህ ካሉ ጥያቄዎች ሊያመልጥ አይችልም፡፡ ጥያቄዎቹም በቀላሉ የሚመለሱ አይደሉም፡፡ ለአንዱ የሚሰጠው መልስ ሌላ ጥያቄ ይጋብዛል፡፡ ከዚህ አይነቱ አከፋፈል ይልቅ ከፍ ሲል እንደተጠቆመው በቅርፅ ልዩነት ላይ የሚመሰረተው አከፋፈል ብዙ አያስቸግርም፡፡ የዚህ አይነት ቅርፅ ያላቸውና የሌላቸው እያለ ስለሚለይ፣ የበለጠ ተጨባጭና አስተማማኝ ነው፡፡ አያጨቃጭቅም፡፡ ስለዚህም ከአጠናን አንፃር ተመራጭ ነው፡፡

በቅርፅ ላይ የተመሰረተን አከፋፈል ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ቃላትን፣ ካገባባቸው አኳያም መለያየት ይቻላል፡፡ ቃላት በሀረግና በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ፣ አዘውትረው የሚገኙበትን ቦታ በመመልከት፣ በዚህ ቦታ ሊገቡ የሚችሉና የማይችሉ እያሉ መከፋፈል ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፤ እንደ ሰው

የቃላት ክፍል

ያሉ ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ፣ ቦታቸው በአረፍተ ነገሩ መነሻ ወይም መካከል ላይ ነው፡፡ በሌላ በኩል እንደ ገደብ ያሉ የድርጊት መጠሪያ የሚባሉት ቃላት በነዚህ ቦታዎች አይገቡም፡፡ እነሱ የሚገኙት በአረፍተ ነገሩ መነሻ ወይም መሀል ሳይሆን በመድረሻው ላይ ነው፡፡ ስለዚህም፣

(ሀ) ቀበሮ ፍየል በላ 3

ማለት ሲቻል፣

(ለ) በላ ቀበሮ ፍየል

ማለት ግን በተለየ ሁኔታ፣ ለምሳሌ በግጥም፣ ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት ያለው ጤነኛ አባባል አይደለም፡፡ የቀበሮ እና የበላ አገባብ ለየቅል ነው፣ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም አንዱ ሌላውን ተክቶ ሊገባ አይችልም፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ይህ አይነቱ የቃላት ክፍፍል የሚመሰረተው በቃላት ቅርፅ ላይ ሳይሆን፣ በአገባብ ላይ ነው፡፡ ከምሳሌዎቹ እንደሚታየው፣ እንደ በላ ያሉ የድርጊት መጠሪያ ቃላት በአርፍተ ነገር መድረሻ ላይ ሲገኙ፣ እንደ ሰው ያሉና የነገር መጠሪያ የሆኑት ግን በዚህ ቦታ አይገኙም፡፡ ከዚህም የሁለቱ የመጠሪያ ቃላት አገባብ የተለያየ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ ልዩነት በመነሳትም ቃላቱን በሁለት መከፈል ይቻላል፡፡ እንደ ቀበሮ እና ሰው ያሉትን የነገር መጠሪያዎች በአንድ በኩል፣ እንደ በላ ያሉትን የድርጊት መጠሪያዎች በሌላ በኩል፡፡

ይህ አይነቱ በአገባብ ላይ የሚመሰረት አከፋፈል በትርጉም ላይ ከሚመሰረት አከፋፈል የተሻለ ነው፡፡ ምክንያቱም የቃላቱ አገባብ እንደ ቅርፃቸው ሁሉ፣ በዐይን የሚታይ ግሀድ ነገር ስለሆነ ነው፡፡ ይህ አይነቱ አከፋፈል ለቋንቋዋ ትንተናም ሆነ ለቋንቋዋ ትምህርት አቀራረብ ቀና ነው፡፡ ብዙ ሰው በቀላሉ ሊያየውና ሊገነዘበው የሚችል ስለሆነ አያከራክርም፡፡ በትርጉም ላይ የሚመሰረት አከፋፈል ግን ለዐይን ሳይሆን፣ ለአዕምሮ ብቻ የሚታይና ለሚታዊ የሆነ ግንዛቤን ስለሚሰጥ፣ አከራካሪና ተቀባይነቱም እንደየግለሰቡ የግንዛቤ ደረጃና ስሜት የተለያየ ነው፡፡ አንድ ወጥ የሆነ መረጃ ሊያስገኝ አይችልም፡፡ ይህ ሲባል ግን ለቃላት አከፋፈል ትርጉም ፈፅሞ አያስፈልግም፣ ማለት አይደለም፡፡ የሚያስፈልግበት ጊዜ በርግጥ ይኖራል፣ ግን ለክፍፍሉ እንደ ዋና ሳይሆን፣ እንደ ረዳት መለኪያ ወይም መስፈርት ሆኖ መወሰድ ያለበት መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡

እንግዲህ ቃላትን ለመከፋፈል አይነተኛ መለኪያዎቹ ቅርፅና አገባብ ናቸው ካልን፣ በቅርፃቸው ወይም ባገባባቸው ወይም በሁለቱም የሚመሳሰሉትንና የሚለያዩትን ቃላት፣ በተለያየ ክፍል ማስቀመጡ በዚህ ደረጃ ለሚደረግ ጥናት የግድ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በአማርኛ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ከላይ የተዘረዘሩትን ስምንት ክፍሎች መነሻ በማድረግ፣ አንድባና እንገበኛቸዋለን፡፡

ይህን የምናደርግበት ምክንያት በትርጉም መስፈርትነት በስምንት የተከፈሉት ቃላት ከቅርፅና ከአገባብ አንፃር ብቻ ሲታዩ፣ በስንት ሊመደቡ እንደሚችሉ ለማወቅ ነው፡፡

## ስም

አንድ ቃል ስም ወይም የስም ክፍል ነው የሚባለው በቅርፁ /-ኦችች/ የሚሰውን የብዛት ምዕላድ ሊይዝ የሚችል ከሆነ፣ በአገባቡም በሚከተሉት ምሳሌዎች ውስጥ <u>ሰው</u> የሚለውን ቃል እየተካ ሊገባ የሚችል ከሆነ ነው፡፡

(ሀ) <u>ሰው</u> ቅዱስ ነው 1
(ለ) እኔ <u>ሰው</u> እፈራለሁ
(መ) ያ <u>ሰው</u>
(ሰ) ትልቅ <u>ሰው</u>
(ረ) ትናንት የመጣው <u>ሰው</u>

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ እንደ ልጅ፣ ውሻ፣ ፈረስ፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ቃላት <u>ሰው</u> የሚለውን ቃል እየተኩ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ሰው ቅዱስ ነው፤ እንዳልን ሁሉ፣

ልጅ ቅዱስ ነው 2

ለማለት እንችላለን፡፡ እንደነዚህ አይነት ቃላትም በዚሁ የአገባብ ተመሳሳይነት ምክንያት ስም ተብለው በአንድ ላይ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ረዥም፣ አጭር፣ ቀጭን፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላት <u>ሰው</u> የሚለውን ቃል ተክተው በዚሁ ቦታ ሊገቡ ስለማይችሉ፣ እሉ በተመደበበት ክፍል ስም ተብለው ሊመደቡ አይችሉም፡፡ በቅርፃቸውም ቢሆን እንደ ልጅ፣ ውሻ፣ ፈረስ፣ ወዘተ፣ ያሉት ቃላት /-ኦችች/ የሚለውን ምዕላድ ሊያስከትሉ ስለሚችሉ <u>ሰው</u> ከሚሰው ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ስለዚህም አንድ ላይ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

እንደነዚህ ያሉት ያገባብና የቅርፅ ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው፡፡ አንዳንድ ቃላት ግን በቅርፃቸው ሳይሆን፣ ባገባባቸው ብቻ ስም በሚለው ክፍል ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ ይመስላሉ፡፡ ለምሳሌ እኔ፣ አንተ፣ እሉ፣ ወዘተ፣ የሚሉትን ቃላት ብንመለከት፣ <u>ሰው</u> እንደሚለው ቃል /-ኦችች/ የሚለውን ምዕ ላድ አያስከትሉም፡፡ በዚህም ምክንያት እኔ-ኦች ወይም አንተ-ኦች ማለት አይቻልም፡፡ <u>ሰው</u> ከሚለው ቃል ጋር የቅርፅ ተመሳሳይነት የላቸውም ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ባገባባቸው <u>ሰው</u> የሚለው ቃል በገባበት ቦታ በከፊልም ቢሆን

ሊገቡ እንደሚችሉ በቀደምት ሊቃውንት ተደጋግሞ ይጠቀሳል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) እሱ ቅዱስ ነው 3
(ለ) እኔ እሱን እፈራዋለሁ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ <u>እሱ</u> የሚለው ቃል የገባው በተራ ቁጥር 3(ሀ) እና (ለ) በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ <u>ሰው</u> የሚለው ቃል በገባበት ቦታ ላይ ቃሉን (ሰውን) ተክቶ የገባ ይመስላል፡፡ በዚህም ምክንያት እንደነዚህ አይነት ቃላት ምድባቸው ስም በሚለው ክፍል ውስጥ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ከሌሎች በዚህ ክፍል ውስጥ ከሚገኙ ቃላት ጋር ባላቸው የቅርፅ ልዩነት ምክንያት በቀደምት የሰዋሰው ሊቃውንት ዘንድ ስም ሳይሆን፣ ተውላጠ ስም በሚል ልዩ ክፍል ውስጥ ለብቻቸው ሲመደቡ ችለዋል፡፡ ተውላጠ ስም ማለትም የስም ልዋጭ ወይም ምትክ ተብሎ ተገልፆአል፡፡ <u>ግላጼው</u> ቃላቱ ከስም ጋር ያላቸውን የአገባብ ተመሳሳይነት መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ተመሳሳይነቱ ግን ምሳሌዎቹ እንዲሁ ላይ ላዩን ሲታዩ፣ የሚከሰት ነገር ነው፡፡ ጠለቅ ብለን ስናየው፣ ተውላጠ ስም የሚባሉት በስም ቦታ ስምን ተክተው አይገቡም፡፡ በምሳሌ 3(ሀ) <u>እሱ</u> የሚለው ተውላጠ ስም የገባው ከዚህ በታች በምሳሌ (4) የሚታየውን <u>ልጅ</u> የሚለውን ስም ተክቶ አይደለም፡፡ ይልቁንስ የገባው በራሱ ቦታ ነው፡፡ ይህ ቦታ ደግሞ ልጅ ከሚለው ስም ቀድሞ ነው፡፡ ስለዚህም ምሳሌ 3(ሀ) በጥልቀት ሲታይ፣ <u>እሱ</u> የሚለው ተውላጠ ስም አገባብ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

<u>እሱ</u> ልጅ ቅዱስ ነው 4

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>እሱ</u> የሚለው ተውላጠ ስም ቦታ ልጅ ከሚለው ስም በፊት ነው፡፡ ልጅ የሚለው ስም ሲገደፍ፣ ተውላጠ ስሙ በስሙ ቦታ የገባ ይመስለናል፡፡ ከዚህም ምስስት የተነሳ፣ ቃሉ ተውላጠ ስም (የስም ልዋጭ) ለመባል በቅቶአል፡፡ በቅርፅም ቢሆን ተውላጠ ስሞች ከስሞች የተለዩ ናቸው፡፡ ስምሳሌ ስሞች ብዛትን ለማመልከት /-ኦችች/ የሚለውን ምዕላድ ያስከትላሉ፡፡ ተውላጠ ስሞች ግን /-ኦችች/ን አያስከትሉም፡፡ ስለዚህም <u>ልጅ</u> ብለን <u>ልጅ-ኦች</u> ማለት ስንችል፣ <u>እሱ</u> ብለን <u>እሱ-ኦች</u> ማለት አንችልም፡፡ ሁኔታው ተውላጠ ስም የሚባሉት በአገባብም ሆነ በቅርፅ ከስም የተሰዩ መሆናቸውን በግልፅ ያመለክታል፡፡ ስለዚህም ከስም ተለይተው ለብቻቸው መታየት አስባቸው፡፡ የሚታዩት ግን በተውላጠ ስምነት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ስምን <u>ተክተው</u> በስም በታ ስለማይገቡ ነው፡፡ ምሳሌ (4) የሚያሳየን ይህንን ሁኔታ ነው፡፡ ዝርዝሩን ወደሁዋላ እንመለስበታለን፡፡ በዚህ ከተስማማን ወደሚቀጥለው ንዑስ ክፍል እንሂድና ሌሎች ቃላትን እንመልከት፡፡

የቃላት ክፍል

## ግስ

ማንኛውም በአረፍተ ነገር መድረሻ ላይ ሊገባ የሚችልና እንደ /-ሁ/፣ /-ህ/፣ /-ሽ/፣ ወዘተ፣ ያሉ መደብ አመልካች ምዕላዶችን ሊያስከትል የሚችል ቃል ሁሉ ግስ ተብሎ በዚህ ክፍል ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) እኔ ዳቦ <u>በላ-ሁ</u> 1
(ለ) አንተ ወተት <u>ጠጣ-ህ</u>
(መ) አንቺ ዶሮ <u>ገዛ-ሽ</u>

በነዚህ ሶስት አረፍተ ነገሮች ውስጥ፣ የመድረሻዎቹ ቃላት <u>በላ-ሁ</u>፣ <u>ጠጣ-ህ</u> እና <u>ገዛ-ሽ</u> የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላት ለግስ የሰጠነውን የአገባብ መስፈርት ስለሚያሙዋሉ፣ ግስ ተብለው በዚሁ ክፍል ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በሚቀጥለው ክፍል በዝርዝር የምናያቸውን እንደ /-ሁ/፣ /-ህ/ እና /-ሽ/ ያሉትን መደብ አመልካች ምዕላዶችን ስላስከተሉ፣ በቅርፅ ረገድ የተሰጠውን መስፈርት ያሙዋላሉ፡፡ /-ኦችችን/ የሚለውን የብዛት ምዕላድ ከሚያስከትሉትና ስም በሚሰው ክፍል ውስጥ ከሚመደቡት ቃላትም በቅርፅ ብቻ ሳይሆን፣ በአገባብም እንደሚለዩ መረዳት ይቻላል፡፡ በስም ክፍል ውስጥ የሚመደቡት በአረፍተ ነገር መድረሻ ላይ አይገኙም፡፡ እንደ <u>በላ</u> ያሉ በግስ ክፍል ውስጥ የሚመደቡትም፣ በስም ውስጥ እንደሚመደቡት በአረፍተ ነገር መነሻ ላይ አይገኙም፡፡

እነዚህ ሁለት ክፍሎች በቋንቋዋው ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን አብዛኛውንና ለህሳብ መግለጫነትም እጅግ አስፈላጊ የሆነውን መደበኛ መድበለ ቃላት ይሸፍናሉ፡፡ በማንኛውም ቋንቋ ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ቃል የድርጊትና የነገር ስም ነው፡፡ አብዛኛው አረፍተ ነገርም የነገሮችና የድርጊቶች መግለጫ የሆኑት የስሞችና የግሶች ቅንጅት ነው፡፡ ሌሎች ቃላት የነዚህ የሁለቱ ክፍሎች አጃቢዎች ናቸው፡፡ ከነዚህም ከፊሎቹ ቅፅል የሚባሉትና ከዚህ ቀጥለን የምናያቸው ናቸው፡፡

## ቅፅል

በሚከተሉት ምሳሌዎች ውስጥ <u>ጎበዝ</u> የሚለውን ቃል እየተካ ሊገባ የሚችል ማንኛውም ቃል ቅፅል ተብሎ በዚህ ክፍል ሊመደብ ይችላል፡፡

(ሀ) <u>ጎበዝ</u> ተማሪ 1
(ለ) በጣም <u>ጎበዝ</u>

የቃላት ክፍል

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ ኀበዝ የሚለውን ቃል እንደ ብልህ፣ አስተዋይ፣ ረዥም፣ ሰነፍ፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላት ሊተኩት ይችላሉ፡፡ እንደ ገደለና እንደ ሰው ያሉት ግን ሊተኩት አይችሉም፡፡ ምክንያቱም፣

(ሀ) *ገደለ ተማሪ 2
(ለ) *በጣም ሰው

ማለት ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለምና፡፡ ከፍ ሲል እንደ ተመለከትነው፣ እንደ ገደለና ሰው ያሉት ቃላት ምድባቸው፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ በሰምና በግስ ክፍሎች ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህም በቅፅል ውስጥ እንደገና ሊመደቡ አይችሉም፡፡ አንድ ቃል ሊመደብ የሚችለው በመሰረቱ በአንድ ክፍል ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ርግጥ፣ አንዳንድ አጉራ-ዘለል አይጠፉም፤ እንደ ሰው፡፡

ከላይ በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ እንደሚታየው፣ ኀበዝ የሚለውን ቃል እንደ ሰውና እንደ ገደለ ያሉ ቃላት ሊተኩት አይቻሉ እንጅ፣ ሌሎች ቃላት ሊተኩት የሚችሉ ይመስላል፡፡ ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) ይህ ተማሪ 3
(ለ) በጣም ቸኮለ

በነዚህ ምሳሌዎች መሰረት፣ እንደ ይህና እንደ ቸኮለ ያሉ ቃላት በተራ ቁጥር (1) ውስጥ በሚገኙት ምሳሌዎች የሚገኘውን ቅፅል፣ ማለትም ኀበዝን፣ ተክተው ስለገቡ፣ ምድባቸው ቅፅል ውስጥ ነው፣ ሊባል ይችል ይሆናል፡፡ ይባል እንጅ፣ እንደ ይህ እና እንደ ቸኮለ ያሉ ቃላት ቅፅል አይደሉም፡፡ ምክንያቱም በ3(ሀ) ውስጥ ይህ የሚለው ቃል የገባው ኀበዝ የሚለውን ቅፅል ተክቶ አይደለም፡፡ ቃሉ የገባው በቅፅሉ ቦታ ሳይሆን፣ አሁንም በራሱ ቦታ ነው፡፡ ቅፅሉን ተክቶ የገባ የሚመስለው ቅፅሉ ሲገደፍ ብቻ ነው፡፡ ሁለቱም በየቦታቸው ሲገኙ፣ 3(ሀ) የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ይህ ኀበዝ ተማሪ 4

ይህ የሚለው ቃል፣ ኀበዝ የሚለውን ቅፅል ቀድሞ በራሱ ቦታ እንደገባ ግልፅ ነው፡፡ ኀበዝ የሚለው ቅፅል ከቦታው ሲገደፍ፣ ይህ በሚለው የተተካ ይመስላል፡፡ ዋናው ነገር ሁለቱ ቃላት የተለያየ ቦታ ያላቸው መሆኑ ነው፡፡

በነዚህ ቃላትና ቅፅል ባልናቸው መካከል ሌሎች የአገባብ ልዩነቶችም አሉ፡፡ ለምሳሌ በ3(ለ) ውስጥ እንደሚታየው፣ ቸኮለ የሚለው ቃል በጣም የሚለውን ቃል ተከትሎ ገብቶአል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ኀበዝ እንደሚለው ቅፅል፣ ተማሪ የሚለውንና ምድቡም ሰም ውስጥ የሆነውን ቃል ቀድሞ ሊገባ አይችልም፡፡ ስለዚህም፣

(ሀ) ጎበዝ ተማሪ 5

ማለት እንደሚቻል ሁሉ፣

(ለ) *ቸኮለ ተማሪ

ማለት አይቻልም፡፡ ይህ የሚለው ቃልም ቢሆን፡ ጎበዝ እንደሚለው ቅፅል በጣም የሚለውን ቃል ተከትሎ ሊገባ አይችልም፡፡ ስለዚህም፣

(ሀ) በጣም ጎበዝ 6

ማለት ሲቻል፣

(ለ) *በጣም ይህ

ማለት አይቻልም፡፡ ይህም የሚያሳየው፣ አንድ ቃል ቅፅል ለመባል ቀደም ሲል ስለ ቅፅል የተሰጡትን ሁለት መስፈርቶች ማሙዋላት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ከሁለቱ አንዱን ብቻ ማሙዋላቱ ቅፅል ሊያሰኘው አይችልም፡፡ ነገሩን ለማቃለል መስፈርቶቹን በአንድ ላይ አካቶ፣ እንደሚከተሰው ማቅረብ ይቻላል፡፡ በሚከተለው ምሳሌ ውስጥ ጎበዝ የሚሰውን ቃል የሚተካ ማንኛውም ቃል ቅፅል ሊባል ይቻላል፡፡

በጣም ጎበዝ ተማሪ 7

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ይህ የሚለውም ሆነ ቸኮለ የሚለው ቃል ጎበዝ የሚለውን ቃል ፈፅሞ ሊተካ አይችልም፡፡ ቃሉ ሊተካ የሚችለው፣ እንደ ሰነፍ፣ ብልህ፣ ንቁ፣ ወዘተ፣ ባለ ቅፅል ብቻ ነው፡፡ እንደዚህ ያለ ቃል ደግሞ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ምድቡ ቅፅል በሚለው ክፍል ውስጥ ነው፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም፣ በምሳሌ 5(ለ) እንደሚታየው፣ ቸኮለ ተማሪ ማለት አይቻል እንጅ፣ የቸኮለ ተማሪ ማለት በሚገባ ይቻላል፡፡ ይህ ከሆነ፣ የቸኮለ የሚለው ቃል ቅፅል አይሆንም ወይ?

ርግጥ ነው፣ የቸኮሰ የሚለው ቃል ጎበዝ የሚሰውን ቅፅል ሊተካ ይችላል፡፡ ስለዚህም ምሳሌ (7) እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፡፡

በጣም የቸኮለ ተማሪ 8

የቸኮለ የሚለው ግን ቸኮለ ከሚለው ይለያል፡፡ ምክንያቱም ቸኮለ የሚለው ሊጣ ግስ ሲሆን፣ የቸኮለ የሚለው ግን ከግስ በላይ ነው፡፡ የ የምትሰዋ ምዕላድና ቸኮለ የሚለው ግስ ቅንጅት ነው፡፡ ከቅንጅትም አረፍተ ነገራዊ ቅንጅት ነው፡፡ ስለዚህም በቃል ደረጃ የሚታይና በቃላት ክፍል የሚመደብ አሀድ አይደለም፡፡ ምድቡ ከአረፍተ ነገር ጋር ነው፡፡ ውስጣዊ ስርዓቱን ወደፊት እናየዋለን፡፡ በቃል ደረጃ ልናየው የምንችለው፣ ቸኮለ የሚለውን ሊጣ ግስ ብቻ ነው፡፡ እሱ ደግሞ በተራ ቁጥር 5(ለ) በግልፅ እንደሚታየው፣ ጎበዝ የሚለውን ቅፅል አይተካም፡፡

## የቃላት ክፍል

እስካሁን ያየነው የቅፅል አከፋፈል በአገባብ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ነው፡፡ እንደ ስምና ግስ ያሉት ቃላት አከፋፈል ግን ቅርፅንም መሰረት ያደረገ ነበር፡፡ ይህም ቅፅል ቅርፃዊ መለያ የለውም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊያሳስብ ይችላል፡፡ ርግጥ ነው፣ እንደ ረዥም ያሉ የቅፅል ክፍል ቃላት ከስሞችና ከግሶች የሚለያቸው ቅርፅ አላቸው፡፡ ይህም ብዛትን ወይም ስብስብን ከየሚያሳዩበት ስርዓት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የሚከትሉትን እንመልከት፡፡

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | 9 |
|---|---|---|
| ረዥም | ረዥ-አ-ዥም | |
| አጭር | አጭ-አ-ጭር | |
| ጥቁር | ጥቁ-አ-ቁር | |

በግልፅ እንደሚታየው፣ የነጠላ ቁጥሩ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ ድምፅ በብዙ ቁጥሩ ውስጥ ተደግሞአል፡፡ ሁለተኛም /አ/ የሚል አናባቢ ድምፅ በሁለቱ ተደጋጋሚ ድምፆች መካከል ገብቶአል፡፡ ይህ ስርዓት ቅፅሎችን ከስሞችና ከግሶች በመጠኑ ይለያቸዋል፡፡ በመጠኑ የምንልበት ምክንያት ስሞችና ግሶችም የዚሁ አይነት ባህሪ፣ ስየት ባለ መልክ፣ ስለሚያሳዩ ነው፡፡ ስሞች ስብስብን ለማመልከት ራሳቸውን የሚደግሙበት ስርዓት አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡ <u>ቅጠል</u> ብለን <u>ቅጠል-ኣ-ቅጠል</u> (ቅጠላቅጠል) እንላለን፡፡ ሁኔታው <u>ረዥም</u> ብለን <u>ረዥ-አ-ዥም</u> እንደምንለው ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ስሞች ሙሉ ቅርፃቸውን ሲደግሙ፣ ቅፅሎች ግን ቅድመ-መድረሻ ድምፃቸውን ብቻ ይደግማሉ፡፡ በሙ ሙሉ አካሉን ሲደግም፣ ቅፅሉ እንዱን ድምፁን ብቻ ይደግማል፡፡ ልዩነቱ የደረጃ ነው፡፡ ቢሆንም አንዱን ከሌላው ለመለየት ያስችላል፡፡ ወደሚቀጥለው እንሂድ፡፡

### ተውሳከ ግስ

ከዚህ በታች በተሰጠው አረፍተ ነገር ውስጥ <u>ትናንት</u> የሚለውን ቃል እየተካ ሊገባ የሚችል ማንኛውም ቃል ተውሳከ ግስ ሊባል ይችላል፡፡ የቃሉ ትርጉም የግስ ጭማሪ ማለት ነው፡፡ ከግስ ጋር እየገባ ግሱ ለሚገልፀው ድርጊት ተጨማሪ ሀሳብ ይሰጣል፡፡

አስቴር <u>ትናንት</u> ምሳ አልበላችም 1

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ትናንት</u> የሚለውን ቃል እንደ <u>ሰው</u>፣ እንደ <u>ቸኮለ</u> ወይም <u>ጎበዝ</u> ያሉ ቃላት ሊተኩት አይችሉም፡፡ ምክንያቱም እንደነዚህ ያሉ ቃላት ከፍላቸው ስም፣ ግስና ቅፅል ነው ብለናልና፡፡ ተውሳከ ግስ የሚባሉት ከነዚህ አይነት ቃላት በአገባባቸውም ሆነ በቅርፃቸው የተለዩ መሆን አለባቸው፡፡

በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ ትናንት የሚለው ቃል እንደ ቶሎ፣ ዛሬ፣ ገና፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላት ሊተኩት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣

(ሀ) እስቴር ቶሎ ምሳ አልበላችም 2
(ለ) እስቴር ገና ምሳ አልበላችም
(መ) እስቴር ዛሬ ምሳ አልበላችም

ማለት ይቻላል፡፡ በነዚህ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ቶሎ፣ ገና እና ዛሬ የገቡት በተራ ቁጥር (1) በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ ትናንት የሚለው ቃል በገባበት ቦታ ነው፡፡ ስለዚህም እንደነዚህ ያሉ ቃላት ክፍል ተውሳከ ግስ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ክፍሉ እንደ ስሞችና እንደ ግሶች በርካታ ቃላት የሉትም፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ምናልባት ልናገኝ የምንችለው የሚከተሉትን ነው፡፡

ግምኛ 3
ጅልኛ
ምንኛ
ክፉኛ
እንደገና

እነዚህ የተውሳከ ግሰ ክፍል ለመሆናቸው ማረጋገጫው፣ ከፍ ሲል በተራ ቁጥር (1) በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ፣ ትናንት የሚለው ቃል በገባበት ቦታ ሊገቡ መቻላቸው ነው፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እያነፃፀርን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ትናንት ታሞ ነበር 4
(ለ) ካሳ ክፉኛ ታሞ ነበር
(መ) ካሳ እንደገና ታሞ ነበር

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይኸውም በምሳሌ 2(ሀ) እና በምሳሌ (4) ውስጥ በተውሳከ ግስነት የገቡት ቃላት በምሳሌ (1) የሚታየውን ትናንት የሚለውን ቃል ተክተው ነው ወይ? የሚል ነው፡፡ ለምሳሌ፣

ካሳ ትናንት ክፉኛ ታሞ ነበር 5

ሰንል፣ ትናንት እና ክፉኛ ተከታትለው በየራሳቸው ቦታ እንደገቡ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ከሆነ፣ ሁለቱ ቃላት የተለያየ ክፍል ቃላት ናቸው፣ ለማለት አይቻልም ወይ? ርግጥ ነው፣ ቃላቱ ተከታትለው በየግል ቦታቸው ገብተዋል፡፡ ይህ ግን በተለያየ ክፍል ውስጥ እንዲመደቡ አያደርጋቸውም፡፡ ቃላት በክፍላቸው አንድ ሆነው፣ በግብራቸው ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ትናንት የሚለው ጊዜን የሚያመለክት

ቃል ሲሆን፣ ክፉኛ የሚለው ሁኔታን የሚያመለክት ነው፡፡ ሁለቱም ታሞ ነበር የሚለውን ግስ የሚገልፁ ተውሳከ ግሶች ናቸው፡፡ አንዱ የህመሙን ጊዜ፣ ሌላው የህመሙን መጠን ይገልፃል፡፡ ሁኔታው፣ የተለያየ ተውሳከ ግሳዊ ተግባርን የሚገልፁ የተለያዩ ተውሳከ ግሶች ተከታትለው ሊመጡ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡

በሌሎቹም ክፍሎች ቢሆን ተመሳሳይ ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ ቅፅሎችን ብንወስድ፣ እንደሚከተሉት ያሉ ምሳሌዎችን እናገኛለን፡፡

ካሳ ጥሩ ነጭ ላም አለችው 6

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ጥሩና ነጭ ተከታትለው ገብተዋል፣ ግን ክፍላቸው አንድ ነው፡. ተከታትለው የገቡት የተለያየ ቅፅላዊ ባህሪን ወይም አይነትን ለመግለፅ ነው፡፡ ጥሩ የሚለው ባህሪን ሲገልፅ፣ ነጭ የሚለው ቀለምን ይገልፃል፡፡ በዚህም መሰረት ሁለቱ ቃላት የባህሪና የአይነት ቅፅል ሊባሉ ይችላሉ፡፡

ተውሳከ ግስ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ቃላት በቋንቋዋ ውስጥ በብዛት የሉም፡፡ ይህ ግን ተውሳከ ግሳዊ የሆነ ተግባር የለም ማለት አይደለም፡፡ ብዙ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራት አሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ ሁኔታ፣ ወዘተ፣ መግለፅ ተውሳከ ግሳዊ ተግባር ነው፡፡ ይህ ተግባር የሚገለፀው ግን በአብዛኛው በተውሳከ ግስ ሳይሆን፣ በስማዊ ሀረጎች፣ በመስተዋድዳዊ ሀረጎች ወይም በጥገኛ አረፍተ ነገሮች ነው፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) የካሳ ልጅ [በፍጥነት ወደ ጎንደር ሄደ] 7
(ለ) አስቴር [የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር ሲሄድ አለቀሰች]

በ7(ሀ) ውስጥ በፍጥነት የሚለው ክፍል፣ የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር የሄደበትን ሁኔታ ያመለክታል፡፡ በ7(ለ) ውስጥ፣ የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር ሲሄድ የሚለው ክፍል አስቴር ያለቀሰችበትን ጊዜ ይገልፃል፡፡ በፍጥነት የሚለውም ሆነ *የካሳ ልጅ ወደ ጎንደር ሲሄድ* የሚለው ክፍል ተውሳከ ግስ አይደለም፡፡ ከቅርፅ አንፃር ሲታዩ፣ የመጀመሪያው ከመስተዋድድና ከስም የተቀናጀ መስታውድዳዊ ሀረግ ነው፡፡ መስተዋድዱ በ ሲሆን፣ ስሙ ደግሞ ፍጥነት የሚለው ነው፡፡ ሁለተኛው ከስማዊ ሀረግና ከግሳዊ ሀረግ የተመሰረተ ጥገኛ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ስማዊ ሀረጉ *የካሳ ልጅ* የሚለው ክፍል ሲሆን፣ ግሳዊ ሀረጉ ወደ *ጎንደር ሲሄድ* የሚለው ነው፡፡ መስተዋድዳዊ ሀረጉም ሆነ ጥገኛው አረፍተ ነገር ቅንጅታዊ መዋቅር እንጅ ተራ ተውሳከ ግሳዊ ቃላት አይደሉም፡፡ ተራ ተውሳከ ግሳዊ ቃላት የሚባሉት እንደ ክፉኛ ያሉ ተናጠል ቃላት ብቻ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የቦታ ተውሳከ ግስ ይባሉ የነበሩትን ብንመለከት፣ ክፍላቸው ከቃላት ሳይሆን፣ ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የሚከተሉት የነዚህ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

(ሀ) ካሳ ወደታች ወረደ 8
(ለ) አስቴር እዚህ ነበረች

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ ወደ ታችና እዚህ የሚሉት ክፍሎች፣ በተግባራቸው ተውሳከ ግስ ናቸው፡፡ የሚያመለክቱት ካሳ የወረደበትንና አስቴር የነበረችበትን ቦታ ነውና፡፡ በቅርፃቸው ግን መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ ወደታች የሚለው፣ ወደ ከሚለው መስተዋድድና ታች ከሚለው ስም የተመሰረተ ሀረግ ነው፡፡ እዚህ የሚለውም ከ የሚለው መስተዋድድና ይህ የሚለው ጠቋሚ ምዕላድ ቅንጅት ነው፡፡ ከዚህ ቦታ እንደ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው፡፡ ምናልባት ወደ ተራ ቃልነት የተለወጠ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው፤ ማለቱ ይቀል ይሆናል፡፡

ከነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳው፡ በአማርኛ የተውሳከ ግስ ተግባር የሚገለፀው በአብዛኛው በክፍላቸው ሳይሆን፣ በተግባራቸው ብቻ ተውሳከ ግሳዊ በሆኑ መስተዋድዳዊ ሀረጎችና ጥገኛ አረፍተ ነገሮች መሆኑን ነው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ተውሳከ ግስ የሚባለው ክፍል ሁሉንም ተውሳከ ግሳዊ ተግባራት የሚገልፅበት ተውሳከ ግሳዊ ሊባሉ የሚችሉ ቃላት ስለሌለው ነው፡፡ ክፍሉ እንደ ስም ወይም እንደ ግስ ስፊ የቃላት ክምችት ስለሌለው፣ እንደ ከፉኛ ባሉ መደበኛ ተውሳከ ግሶች ሊገለፅ የማይችለውን ተውሳከ ግሳዊ ተግባር፣ በሀረጎችና በጥገኛ አረፍተ ነገሮች ይገልፃል፡፡ ይህን በዚሁ እንተወውና ወደሚቀጥለው ክፍል እንሂድ፡፡

እስካሁን ያየነው ሁኔታ የአማርኛ ቃላት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ነው፡፡ ክፍሎቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ስም | ግስ | 9 |
| ቅፅል | ተውሳከ ግስ | |

እነዚህ በሙሉ የይዘት፣ ማለትም የትርጉም፣ ቃላት ናቸው፡፡ ዋና ዋና የተባሉበት ምክንያትም ለዚሁ ነው፡፡

በአራቱ ክፍሎች ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉትን ቃላት አገባባዊና ቅርፃዊ ባህሪያት ገልፀናል፡፡ በዚህ መሰረት፣ በቋንቋዋው ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ቃል በአገባቡ ወይም በቅርፁ ወይም በሁለቱም ከነዚህ ዋና ዋና ክፍሎች ውስጥ በአንዱ ወይም በሌላው ሊመደብ የሚችል ነው፡፡ በነዚህ ውስጥ ሊመደቡ የማይችሉ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ቃላት ግን አሉ፡፡ እነዚህም ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከታቸው ናቸው፡፡

# የንዑስ ቃላት ክፍል

ባሰፈው ክፍል ያየነው የዋና ዋና ቃላትን ክፍሎች ነው፡፡ ዋና ዋና ቃላት የሚባሉት በቃል ደረጃ ትርጉም፣ በመዋቅር ደረጃ ሰዋሰዋዊ ተግባር ያላቸው ናቸው፡፡ ከትርጉም አኳዋያ፣ ነገሮችንና ባህሪያቸውን እንዲሁም ድርጊቶችንና አደራረጋቸውን ይጠቁማሉ፡፡ ነገሮችን የሚጠቁሙት ስሞች ሲሆኑ፣ ባህሪያቸውን የሚጠቁሙት ቅፅሎች ናቸው፡፡ ድርጊቶችን የሚጠቁሙት ግሶች፣ አደራረግን የሚጠቁሙትም ተውሳከ ግሶች የሚባሉት ናቸው፡፡ በዚሁ መሰረት አራቱን የቃላት ክፍሎች የገላጭና የተገላጭ ወገን ብለን በሁለት ልንመድባቸው እንችላለን፡፡ ሰምና ግስ የተገላጭ ሲሆኑ፣ ቅፅልና ተውሳከ ግስ የገላጭ ወገን ናቸው፡፡ ህይወትም እንደዚሁ የገላጭና የተገላጭ ጥምረት ነው፣ በወጉ ካየነው፡፡

ከነዚህ ውጭ፣ ትርጉም ሳይሆን መዋቅራዊ ተግባራት ብቻ ያላቸው ቃላት አሉ፡፡ እነዚህም በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ተውላጠ ስም፣ መስተዋድድ፣ መስተፃምር፣ ቃሰ አጋኖ እንዲሁም በዘመናዊ ስነ-ልሳን መስተፃምር በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡ ሁሉንም በጥቅል ንዑስ ቃላት ብለናቸዋል፡፡ ንዑስ የሚሰኙባቸው የጋራ ባህሪያት አሉዋቸው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

(ሀ) የራሳቸው የሆነ ቃላዊ ትርጉም የላቸውም፤

(ለ) ለአዳዲስ ቃላት ምሰረታ ዘር ወይም እናት ቃል አየሆኑ ሊረቡ አይችሉም፤

(መ) የራሳቸው የሆነ የቁጥር፣ የፆታ፣ የጊዜ፣ ወዘተ፣ ቅጣይ ምዕላድ የላቸውም፤

(ሰ) ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ አይጨምርም፡፡ ሰለዚህም ትረጉም ያላቸው ቃላት መጠን ሲጨምር የእነሱ አይጨምረም፤ አይቀንስምም፤

(ረ) በ<u>*መጠነ-ወርዳቸው*</u> ንዑስ ናቸው

ወደፊት በሰፊው እንደምናየው፣ ዋና ዋና ክፍሎች የሚባሉት አዳዲስ ቃላትን ሰመፍጠር ግብዓት ወይም ዘር በመሆን ያገለግላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የየክፍሉ የቃላት መጠን በየጊዜው ይጭምራል፡፡ ከዚህ አፃርም የንዑስ ቃላት መጠን የመጨመርም ሆነ የመቀነስ አዝማሚያ አያሳይም፡፡ በወርደ-መጠናቸውም ድሁር ናቸው፡፡ ከትርጉም፣ ከቅርፅና ከመዋቅር አኳዋያ እንደነዚህ ያሉትንና ከአራቱ ዋና ዋና ክፍሎች ውጭ የሆኑትን ቃላት በሙሉ ንዑስ ቃላት ብለን ከዋና ዋና ቃላት ክፍሎች እንለያቸዋለን፡፡ ይሁን እንጅ፣ እንደመዋቅራዊ ባህሪያቸው በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ልንመድባቸው እንችላለን፡፡ እነዚህም መስተዋድድና መስተፃምር ናቸው፡፡ ዝርዝራቸውን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ከስም ጋር መግባቱ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ መስተዋድድ ያሰኘዋል፡፡ ስለ ገንዘብ የሚለውን የአረፍተ ነገሩን ክፍልም መስተዋድዳዊ ሀረግ ያደርገዋል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ይኸው ቃል በሊቃውንቱ ዘንድ የሚታወቀው መስተፃምር በመባል ነው፡፡ መስተፃምር የሚያሰኘው ምክንያት ደግሞ በሁለተኛው ምሳሌ እንደሚታየው ከግስ በፊት መግባቱ ብቻ ነው፡፡ ከፍ ሲል ስለ መስተዋድድ የተሰጡትን ሌሎች መስፈርቶች ሁሉ ስለሚያሙዋላ ቃሉ መስተዋድድ በሚለው ክፍል ውስጥ ሊገባ ይችል ነበር፡፡ አሁንም በዚሁ ክፍል ሊመደብ ስለሚችል መስተፃምር የሚል ከመስተዋድድ የተለየ ክፍል አያስፈልግም ብለን ልናልፈው እንችላለን፡፡ አገባቡን በተመለከተ ግን ትንሽ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

ከላይ እንደገለፅነው፣ መስተዋድድ የሚባሉት ከስም ጋር የሚገቡት ሲሆኑ፣ መስተፃምር የሚባሉት ከግስ ጋር የሚገቡት ናቸው፡፡ ከግስ ጋር የሚገቡትን እንደገና በሚከተሉት ምሳሌዎች እማካኝነት እንያቸው፡፡

(ሀ) ካሳ [ስለ ታመመ] አስቴር አዘነች 4
(ለ) ካሳ [እንደ መጣ] አስቴር ሄደች
(ሐ) ካሳ [ከለከረ] አስቴር ትናደዳለች
(ለ) ካሳ [ሲሄድ] (<ስ-ይ-ሄድ) አስቴር ትደሰታለች

ከምሳሌዎቹ እንደምንመለከተው፣ ስለ፣ እንደ፣ ከ- እና ሱ- እንደ ቅደም ተከተላቸው ታመመ፣ መጣ፣ ለከረ እና -ይሄድ ከሚሉት ግሶች በፊት ገብተዋል፡፡ ተግባራቸውም ግሶቹ የሚገኙበት አረፍተ ነገር፣ ራሱን የቻለ ሳይሆን፣ በሌላ አረፍተ ነገር ውስጥ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን ማመልከት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ብንመለከት፣

(ሀ) አስቴር አዘነች 5
(ለ) ካሳ ታመመ

ከሚሉ ሁለት አረፍተ ነገሮች የተዋቀረ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ አወቃቀሩም ካሳ ታመመ የሚለው፣ አስቴር አዘነች በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ እንደሚከተለው ሆኖ በመግባት ነው፡፡

[አስቴር [ካሳ ታመመ] አዘነች] 6

ካሳ ታመመ የሚለው አረፍተ ነገር አስቴር አዘነች በሚለው ውስጥ ጥገኛ ሆኖ ስለመግባቱ ምልክት ያስፈልገዋል፡፡ የጥገኝነት መታወቂያ ያስፈልገዋል ማለት ነው፡፡ መቼም ጥገኛ ምን ጊዜም ይኸው ነው! ለውነቱ ብቻ አይበቃውም፡፡

ለዚህ የጥገኝነት ምልክት የሚሆኑት ደግሞ እንደ ለስ ያሉ የትርጉም ሳይሆን፣ የግብር ቃላት ብቻ ናቸው፡፡ ጥገኝነትን የማመልከት ተግባር ስላላቸው በጥንት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተፃምር በመባል ይታወቃሉ፡፡

የቃላት ክፍል

ምልክትነታቸው ግን ጥገኛ ለሆነው አረፍተ ነገር ግስ ሳይሆን፣ በጠቅላላ ለጥገኛው አረፍተ ነገር ነው፡፡ ጥገኛ የሆነው ሙሉው አረፍተ ነገሩ እንጅ፣ ግሱ ብቻ አይደለምና፡፡ በመሆኑም ጥገኛ አረፍተ ነገር እንጅ ጥገኛ ግስ አንልም፡፡ በዚህም ምክንያት እንደ <u>ስለ</u> ያሉ ቃላት መዋቅራዊ ግንኙነት በመሰረቱ ጥገኛ ከሆነው፣ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው፡፡ ከአረፍተ ነገሩ ግሱ ጋር አይደለም፡፡ ርግጥ፣ በግህድ የሚታዩት የግሱ አካል ሆነው ነው፡፡ ይህ ግን ላይ ላዩን ስናይ ነው፡፡ መሰረታዊ ቦታቸውን በሌላ ክፍል እናየዋለን፡፡ የአንድ ሰው የጥገኝነት ምልክት በደረቱ ላይ ሊታይ ይችላል፡፡ ጥገኛው ግን ሙሉ አካሉ እንጅ ደረቱ ብቻ አይደለም፡፡

ሁኔታው መስተዋድድ የሚባሉት ቃላት በአገባብ ልዩነት መሰረት በሁለት ንዑስ ክፍሎች ሊመደቡ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል፣ ከስም ጋር ገብተው መስተዋድዳዊ ሀረግ የሚመሰርቱትን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከአርፍተ ነገር ጋር ገብተው ጥገኝነትን የሚያሳዩትን በመለየት ነው፡፡ ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩትን ብቻ ለይተን <u>ሞይ</u> በሚል ስያሜ እንጠራቸዋለን፡፡ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ያላቸውን የአወቃቀር ስርዓት በክፍል ሶስት በሰፊው እናየዋለን፡፡ እስከዚያው ግን፣ ከስም ጋር የሚዋቀሩት ተራ መስተዋድድ፣ ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት ሞይ መስተዋድድ ይባላሉ ብለን፣ እንስማማ፡፡ ስለ ሞይ መዋቅር ወደፊት በክፍል ሶስት እንወያያለን፡፡

ሌሎች ንዑስ ቃላት ሊባሉ የሚችሉት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ቃለ-አጋኖ በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙትም እንደ ጎሽ! ዘራፍ! እልል፣ ኡ! ኡ!፣ ዋ! ወዘተ፣ የመሳሰሉት ጨዋኂ ቃላት ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቃላት ድንጋጤን፣ ግራሜን (መገረምን)፣ ቁጣን፣ ወዘተ፣ አትልቶና ከበድ አድርጎ ለመግለፅ ሲፈልግ የሚገቡ የስሜት ቃላት ናቸው፡፡ የራሳቸው ትርጉም የላቸውም፡፡ የሌሎች ቃላትን ትርጉም የማጋነን ተግባር ግን አላቸው፡፡ ስለዚህም እንደ መስተዋድዶችና መስተፃምሮች የግብር ቃላት ናቸው፡፡ ቅርፃቸውን ስንመለከት፣ መስተዋድድ ካልናቸው ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው እንረዳለን፡፡ ይኸውም እንደ መስተዋድዶች ሁሉ ቃለ-አጋኖ የሚባሉትም ምንም አይነት ምዕላድ አያስከትሉም ወይም አያስቀድሙም፡፡ ስለዚህም ቅርፃቸውን አይለዋውጡም፡፡ ለአዳዲስ ቃላት ምስረታም መሰረት አይሆኑም፡፡ በነዚህ ቅርፃዊ ባህሪያታቸው ከመስተዋድዶች ጋር ስለሚመሳሰሉ በመስተዋድድ ክፍል ውስጥ ሊካተቱ ይችሉ ነበር፡፡

አገባባቸውን ስናይ ግን ቃለ-አጋኖዎች ከመስተዋድዶች ጋር ሊመደቡ የማይችሉበት ሁኔታ እንዳለ እንረዳለን፡፡ ቀደም ሲል፣ መስተዋድዶች ከስም ወይም ከአረፍተ ነገር ጋር እየገቡ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራትን እንደሚያሳዩ ገልፀናል፡፡ ቃለ-አጋኖዎች ከስምም ሆነ ከሌላ ቃል ጋር፣ ከዚያም አልፎ ከማንኛውም ቃል ጋር አይገቡም፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እናስተውል፡፡

(ሀ) <u>ጎሽ</u>! ካሳ መጣ 7
(ለ) <u>ዋ</u>! አንተ ልጅ ነግሬሀለሁ

ስሜት ከፍተኛነትና ዝቅተኛነት ድምፀታቸው ከፍና ዝቅ ይላል፡፡ ርግጥ ቃለ አጋኖ የሚለው ስያሜ መጋነንን ብቻ እንደሚገልፅ ተደርጎ ተወስዶአል፡፡

ይህ ስሜት ገላጭነታቸው ለዋለዋዊ፣ ማለትም መዋቅራዊ፣ ተግባራት ካላቸው እንደ ስምና ግስ ካሉ ቃላት ይለያቸዋል፡፡ ስሞች በአረፍተ ነገር ውስጥ የባለቤትነት ወይም የተሳቢነት፣ ግሶች ደግሞ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የአንቀፅነት ተግባር አላቸው፡፡ ወደፊት እንደምናየው፣ ባለቤትነት፣ ተሳቢነትና አንቀፅነት ለዋለዋዊ ተግባራት ናቸው፡፡ ሌሎቹም ቀደም ሲል በየክፍሉ ያየናቸው ቃላት እንደዚሁ ያሉ የተለያዩ ተግባራት አሉዋቸው፡፡ ቃለ-አጋኖዎች ግን ለዋለዋዊ ተግባር የላቸውም፡፡ የእነሱ ተግባር ከላይ እንደተጠቀሰው፣ በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቀሰን ሀሳብ ማጎልበት፣ ወይም ማኮሰስ ነው፡፡ ይህን ሲያደርጉም ስልፋቸው በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ከሚገኝ ከአንድ ወይም ከሌላ ቃል ጋር ሳይሆን፣ የሀሳቡ መግለጫ ከሆነው ከአጠቃላዩ አረፍተ ነገር ጋር ነው፡፡ ያም ሆኖ የተወሰነ ቦታ የላቸውም፡፡ እንደፈለጉ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ለመንሸራሸር ይችላሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ቃለ-አጋኖ የሚባል ክፍል በቃላት ክፍል ደረጃ መፍጠር አስፈላጊ አለመሆኑን ያጠናክራል፡፡

የቃለ-አጋኖዎች ባህሪ መታየት ያለበት በአረፍተ ነገር፣ ከዚያም አልፎ የአረፍተ ነገር ጥንቅር በሆነው በንግግር (ዲስኩር) ደረጃ ነው፡፡ እንደዚያም ሆኖ ጥናቱ በመዋቅራዊ ባህሪ ላይ ሳይሆን፣ መዋቅሩ በሚፈጥረው ስሜት ላይ ነው፡፡ ይህም ጥናቱን በከፊል ትርጉማዊ ያደርገዋል፡፡ ትርጉም ደግሞ አዕምሮአዊ ስለሆነ፣ ለመዋቅራዊ ስርዓት ብዙም አይገዛም፡፡ በጥቅሉ ቃለ-አጋኖ የመዋቅር ክፍል ቃላት ስላልሆኑ፣ በሰዋሰው ጥናት ውስጥ ሊታዩ አይገባም፡፡ ከታዩም በትርጉምና በአጠቃቀም ደረጃ ነው፡፡ አጠቃቀም ደግሞ መዋቅራዊ ብቻ ሳይሆን፣ ማህበራዊና ባህላዊ ስለሆነ፣ በመዋቅር ሀግጋት ውስጥ ወግ ባለው መልክ ሊካተት አይችልም፡፡ ርግጥ ነው፣ አንዳንድ የቋንቋ ሰዎች መዋቅርና የመዋቅር አጠቃቀም ተለያይቶ መታየት የለበትም ይላሉ፡፡ ወደ ዝርዘሩ አንሄድም፡፡

## መስተዓምር

መስተዓምር የሚባሉት ቃላት አንድ ነገር፣ ድርጊት፣ እና ባህሪ ከሌላ ነገር፣ ድርጊት፣ እና ባህሪ ተለይቶ የታወቀ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚያመለክቱ ንዑስ ቃላት ናቸው፡፡ መስተዓምር ማለትም የሚያሳውቅ፣ የሚለይ እንደ ማለት ነው[3]፡፡ ስያሜውን የሚያሳውቀውም በሶስት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው ነገሩን ከሌሎች ነገሮች ለይቶ፣ ከሚገኝበት ቦታ ወይም ጊዜ አንፃር በመጠቆም ነው፡፡ ሁለተኛው ነገሩ የማን እንደሆነ በማገናዘብ ሲሆን፣ ሶስተኛው ነገሩ በመጠን

[3] መስተዓምር የሚለውን ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቁት ባለቅኔው አለማየሁ ሞገስ ናቸው፡፡

የቃላት ክፍል

2




ጠቋሚው ለምሳሌ፣ <u>እኔ</u> ብሎ እራሱን ይጠቁምና፣ ከአጠገቡ የሚገኘውን ነገር ይህ፣ ይህች፣ ወዘተ፣ በማለት ያመለክታል፡፡ ተጠቋሚውን ሰው <u>አንተ</u> ብሎ ይጠራና፣ ከእሱ አጠገቡ ያለውን ነገር እሱ፣ እስዋ፣ ወዘተ፣ በማለት ያመለክታል፡፡ ከሁለቱም ርቆ የሚገኝን ነገር ያ፣ ያች፣ ወዘተ፣ ብሎ ያመለክታል፡፡

በ(ለ) ክፍል ውስጥ የሚገኙት ጠቋሚዎች ማንኛውንም ነገር ሳይሆን፣ በተለይ ሰውን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ስለዚህም *<u>ሰዋዊ</u>* ጠቋሚ ልንላቸው እንችላለን፡፡ ተናጋሪን፣ ተነጋሪንና ታዛቢን ያመለክታሉ፡፡ ተናጋሪው <u>እኔ</u> እያለ ራሱን፣ <u>አንተ</u> እያለ ተነጋሪውን እንዲሁም <u>እሱ</u> እያለ ታዛቢውን ይጠቁማል፡፡ ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) <u>እኔ ካሳ</u> ማንንም አልፈራም 3
(ለ) <u>አንተ ልጅ</u> ፖሊስ እንዳያስርህ
(መ) <u>እሱ ሰው</u> ጤና የለውም?

እሱ የሚለው ጠቋሚ ለሰው ብቻ የተወሰነ አይደለም፤ ማንኛውንም ነገር ሊጠቁም ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ <u>እሱ ሰው</u> እንዳልን ሁሉ፣ <u>እሱ መፅሀፍ</u> ማለት እንችላለን፡፡

እንደ እኔ፣ አንተና እሱ ያሉት ጠቋሚዎች ከሚጠቁሙት ስም በፊት እንደገቡ እንጅ ስሙን እየወከሉ በእሱ ፋንታ እንዳልገቡ እናስተውል፡፡ የተጠቋሚዎቹ ምንነት ከእውዱ በሚታወቅበት ጊዜ፣ ተጠቋሚዎቹን ነገሮች የሚገልፁት ስሞች በግልፅ ላይከሰቱ ይችላሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ለምሳሌ፣ 3(ሀ) እንደሚከተለው ሆኖ ሊከሰት ይችላል፡፡

እኔ ማንንም አልፈራም 4

ይህ ሲሆን፣ <u>ካሳ</u> የሚለው ስም <u>እኔ</u> በሚለው ጠቋሚ ምዕላድ የተተካ ሲመስለን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ጠቋሚዎቹ ተውላጠ ስም እንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚከሰተው፣ የቃላቱን አገባብ ጠለቅ አድርገን ሳናይ ስንቀር ነው፡፡ ጠለቅ አድርገን ካየነው፣ የጠቋሚዎቹና፣ የተጠቋሚዎቹ ስሞች አገባብ ለየቅል መሆኑን ከላይ በተራ ቁጥር (3) ከሚታየው ምሳሌ በግልፅ መረዳት ይቻላል፡፡

መስተዓምሮች እንደሚጠቁሙት ነገር ቅርበትና ርቀት፣ ቁጥርና ፆታ ቅርፃቸውን ይለዋውጣሉ፡፡ ለቁጥር /እንንኧ-/ የሚለውን ምዕላድ ሲያስቀድሙ፣ ለፆታ ደግሞ /-ኢ/ን ወይም /-አ/ን ያስከትላሉ፡፡ /-ኢ/ እንስታይ ተጠቋሚን፣ /-አ/ እንስታይ ታዛቢን ታመለክታለች፡፡ /እንንኧ-/ የሚለው ምዕላድ /-ኦችች/ የሚለው፣ የስሞች የቁጥር ምዕላድ እቻ ነው፡፡ ተግባሩም እንደ /-ኦችች/ ብዙነትን ሳይሆን፣ ጥቂትነትን ማመልከት ነው፡፡ በመሰረቱ መስተዓምሮች የሚጠቁሙት መጠነ-ጥቂትና ሊቆጠሩ የሚችሉ ነገሮችን ነው፡፡ መጠነ-ብዙ የሆነ ነገር <u>ይህ ሁሉ</u> ወይም <u>ያ ሁሉ</u> በግ፣ ሰው፣ ወዘተ፣ እየተባለ በጥቅሉ ይጠቆማል፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መስተዓምሮቹ የሚያስከትሉዋቸው ቅጣዮች የሚያመለክቱት የተጠቋሚውን ነገር ቁጥርና ፆታ ነው፡፡ ዝርዝሩን ወደፊት እናየዋለን፡፡

በምሳሌ 3(መ) እንደሚታየው፣ መስተዓምሮቹ የገቡበት ቦታ እንደ <u>ትልቅ</u> ያሉ የቅፅል ወገን የሆኑ ቃላት የሚገቡበት ነው፣ ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፣ <u>እሱ</u> በሚለው መስተዓምር ፋንታ፣ <u>ክፉ</u> የሚለውን ቅፅል በመተካት <u>ክፉ ሰው</u> ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ ያገባብ ተመሳሳይነት የተነሳ መስተዓምሮቹ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አመልካች ቅፅል በመባል ይታወቃሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተራ ቁጥር (1) እንደሚታየው፣ መስተዓምሮቹ ከመዋቅር ውጭ ብቻቸውን መቆም ይችላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት አመልካች ተውላጠ ስም ይባላሉ፡፡ አመልካች ቅፅል ወይም ተውላጠ ስም የሚያሰኛቸው፣ አብሮአቸው የሚዋቀረው ስም በቦታው በግህድ መታየት ወይም አለመታየት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

(ሀ) [ያቺ ልጅ] ሄደች 5
(ለ) [ያቺ — ] ሄደች

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>ያቺ</u> የሚለው፣ <u>ልጅ</u> ከሚለው ስም በፊት ስለገባ፣ በሊቃውንቱ አመለካከት አመልካች ቅፅል ነው፡፡ በምሳሌ (ለ)፣ <u>ልጅ</u> የሚለው ስም በቦታው ባለመገኘቱ፣ <u>ያቺ</u> የሚለው ጠቋሚ፣ <u>ልጅ</u> በሚለው ቦታ የገባ ይመስላል፡፡ እንደዚህ ሲመስል፣ ቃሉ አመልካች ተውላጠ ስም ነው፡፡ በሁለቱም ምሳሌዎች <u>ያቺ</u> የሚለው ቃል የገባው፣ <u>ልጅ</u> ከሚለው ስም ቀድሞ በራሱ ቦታ እንጅ፣ <u>ልጅ</u> በሚለው ስም ቦታ ስሙን ተክቶ አይደለም፡፡ ስለዚህም ተውላጠ ስም ሊሆን አይችልም፤ ሊባልም አይገባም፡፡ ስሙን ተክቶ አልገባምና፡፡ ስሙን

የቃላት ክፍል

የሚባሉት ትርጉም ያላቸው ሲሆኑ፣ የግብር የሚባሉት ትርጉም ሳይሆን፣ መዋቅራዊ ተግባር ያላቸው ናቸው፡፡

የይዘት ቃላት የሚባሉትን በቅርፅና በአገባብ ባህሪያቸው መሰረት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መድበናቸው፡፡ እነሱም ስም፣ ቅፅል፣ ግስና ተውሳከ ግስ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል ተውሳከ ግስ የሚባለው ክፍል በርካታ ቃላት እንደሌሉትና ተውሳከ ግሳዊ ተግባራትን ለመግለፅ ሀረጎችንና ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን እንደሚጠቀም አየን፡፡ ከነዚህ ከአራቱ ክፍሎች ውጭ የሚገኙትን ቃላት በሙሉ ንዑስ ቃላት ብለን ከዋናዎቹ ክፍሎች ለየናቸው፡፡ በዚህ ክፍል የሚካተቱት ቀደም ሲል የግብር ቃላት ብለን ከይዘት ቃላት የለየናቸው ናቸው፡፡

እነዚህንም በመዋቅራዊ ባህሪያቸው መሰረት መስተዋድድና መስተፃምር ብለን በሁለት ከፈልናቸው፡፡ መስተዋድድ የሚባለው ክፍል መስተፃምር ይባሉ የነበሩትን ሊያጠቃልል እንደሚችል አየን፡፡ መስተዋድድ የሚባሉት ከስማዊ ሀረጎች ጋር የሚዋቀሩት ሲሆኑ፣ መስተፃምር የሚባሉት ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት ናቸው፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ቃለ አጋኖ ይባሉ የነበሩት በቃል ሳይሆን በሀረግና በአረፍተ ነገር፣ ከዚያም አልፎ በአጠቃቀም ደረጃ መታየት ያለባቸው እንደሆኑ አሳየን፡፡ ተግባራቸው ሰዋሰዋዊ ተግባርን ሳይሆን ቅፅበታዊ ስሜትን እያጎሉ ወይም እያኮሰሱ መግለፅ እንደሆነም ገልፀናል፡፡ ስሜት ደግሞ ለአዕምሮአዊ ትርጉም እንጅ ለመዋቅራዊ ስርዓት ስለማይገዛ፣ በመዋቅር ደረጃ መታየት እንደሌለበት ገለፅን፡፡

መስተፃምር የሚባለው ክፍል በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ምድብ ተውላጠ ስም፣ አመልካች ቅፅልና አመልካች ተውላጠ ስም ይባሉ የነበሩትን ያጠቃልላል፡፡ መስተፃምር የሚባሉት ከአገባብ ባህሪያቸው አኳያ ጠቋሚ፣ አጣናዛቢና መጣኝ ተብለው በሶስት ሊከፈሉ እንደሚችሉ አየን፡፡ ጠቋሚዎቹ ተራ ጠቋሚና ለዪ ጠቋሚ ተብለው እንደገና ሊለዩ እንደሚችሉም ተረድተናል፡፡ በዚህም የአማርኛ ቃላት በአራት የይዘትና በሁለት የግብር ክፍሎች ብቻ እንደሚከፈሉ አይተናል፡፡

በአጠቃላይ በቋንቋዎች ውስጥ የሚገኙትን ቃላት የሰዋሰውና የአጠቃቀም ብሎ በሁለት ብቻ መክፈል ይቻላል፡፡ የሰዋሰው የሚባሉት እስካሁን ያየናቸው ናቸው፡፡ የአጠቃቀም የሚባሉት በማንኛውም የቃል ክፍል ሊመደቡ የማይችሉት ናቸው፡፡ እነዚህ የሚገኙት በንግግር (ዲስኩር) እና በድርሰት ውስጥ ነው፡፡ የሰዋሰው የሚባሉት በተራ ወይም በውስብስብ አረፍተ ነገር ደረጃ የሚገኙትና ከተለየ አውድ ጋር ቁርኝት የሌላቸው ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉትን የትርጉምና የግብር ብሎ በሁለት መለየት ይቻላል፡፡ የትረጉም የሚባሉት በአራቱ ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉት ናቸው፡፡ የግብር የሚባሉት በመስተዋድድና በመስተፃምር ውስጥ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ የትረጉም (ይዘት) የሚባሉት አራቱ ክፍሎች የገላጭና የተገላጭ ወገን ተብለው በሁለት ብቻ ሊጠቃለሉ እንደሚችሉ አይተናል፡፡ በዚህ መሰረት አጠቃላዩን የቋንቋዎችን ቃላት እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

የቃላት ክፍል




ከዘህ ላይ አንድ ነገር ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህም የግብር ቃላት ሲባል፣ ሁሉም የዚህ ክፍል ቃላት ይዘት የላቸውም ማለት አለመሆኑን ነው፡፡ እንደ ስሞችና ግሶች በቀጥታ የሚገልፁት ነገር ወይም ድርጊት የላቸውም ለማለት እንጅ፣ በጥቅሉ ትረጉም-አልባ ናቸው ለማለት አይደለም፡፡ በአረፍተ ነገር ውስጥ የይዘት ቃላትን ሲያገናኙ የሚሰጡት የተለያየ ትረጉም አለ፡፡ ይህን ወደፊት እንመለከተዋለን፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን መልመጃ በውይይታችን መሰረት እንዲሞክሩት እየጋበዝን፣ ወደሚቀጥለው ክፍል እንሄዳለን፡፡

## መልመጃ

1. በቃላትና በምዕላድ መካከል ያለውን ልዩነት ምሳሌ እየሰጡ ይግለፁ፡፡

2. ፎኒማዊ ቃላት ከስነ-ምዕላዳዊ ቃላት እንዴት እንደሚለዩ ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡

የቃላት ክፍል

3. /-ህ/ እና /-ሽ/ የሚሉትን መደብ አመልካች ቅጥዮች የሚያስከትል ቃል ሁሉ ግስ ነው ለማለት የማይቻለው ለምንድን ነው? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡

4. /-ኦችች/ የሚለውን የቁጥር ምዕላድ የሚያስከትል ቃል ሁሉ ስም ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ለምን?

5. <u>ሞት</u> ብለን <u>ሞቶች</u> እንልም፤ <u>ገደለ</u> ብለንም <u>ገደሎች</u> እንልም፡፡ ይህ ውነት ከሆነ፣ <u>ሞት</u>ና <u>ገደለ</u> የአንድ ክፍል ቃላት ናቸው ለማለት ይቻላል? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡

6. <u>በጣም</u> ከሚለው ምዕላድ ቀጥሎ የሚገባ ቃል ሁሉ ቅፅል ነው ለማለት የማንችለው ለምንድን ነው? ምሳሌ እየሰጡ ያስረዱ፡፡

7. <u>ገጠመኝ</u>፣ <u>አራዳ</u> ፣ <u>አይነ-ደረቅ</u> እና <u>እባክሽ</u> የሚሉትን ቃላት ክፍል ይግለፁ፡፡

8. የሚከተሉትን ምሳሌዎች ይመልከቱ፡፡
   (ሀ) <u>እንኳዋን</u> መጣህ
   (ለ) <u>እንኳዋን</u> አንተ ማንም ይሰራዋል
   (መ) <u>እንኳዋን</u> ለገንዘ ለሌላም አልጉዋጉዋ

<u>እንኩዋን</u> የሚለው ቃል ክፍል ምንድን ነው?

9. በስነ-ቃላት፣ በምዝገባ-ቃላትና በክፈለ-ቃላት መካከል የሚታየውን አንድነትና ልዩነት ምሳሌ እየሰጡ ይግለፁ፡፡

10. በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ የሚገባ ቃል ሁሉ ግስ ነው የሚለውን ድንጋጌ ከሚከተሉት ምሳሌዎች አንፃር ይገምግሙ፡፡

   (ሀ) ካሳ መጣ እንዴ?
   (ለ) ካሳ መጥቶአል እኮ!
   (መ) ካሳ መጣ፡፡

# ርባታ

ባለፈው ንዑስ ክፍል እንዳየነው የአማርኛ ቃላት በአራት ዋና ዋና እና በሁለት ንዑስ ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ይህ አከፋፈል በቃላቱ ቅርፅና አገባብ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፡፡ የቃላቱን ይዘት ግንዛቤ ውስጥ ብናስገባ፣ ምናልባት በሁለት ብቻ መከፈል ይቻል እንደነበር ገልፀናል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል ይዘት ያላቸው፣ በሌላ በኩል ይዘት የሌላቸው ቃላት በማለት ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በዚህ ክፍል ውስጥ ለምናያቸው ጉዳዮች ቀና መንገድ ይከፍትልናል፡፡ ወደ ክፍፍሉ ከመሄዳችን በፊት ግን ይዘት ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ ለመነሻ የሚሆን ሀሳብ እንስጥ፡፡

ይዘት የአንድ ቃል ትርጉም ወይም ፍች ነው፡፡ አንድን ቃል በተናጠል፣ ወይም ከሌሎች ቃላት ጋር በህብረት፣ በመዋቅር ውስጥ ሳገኘነው ጊዜ፣ በአዕምሮአችን ውስጥ የሚፈጥረው ስሜት ወይም ምስል የቃሉ ይዘት ወይም ፍች ነው፣ ለማለት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፣ <u>አንበሳ</u> የሚለውን ቃል ስንሰማ፣ በአዕምሮአችን ውስጥ አንድ የአራዊት ወገን የሆነ አስፈሪ ፍጡር ይታየናል፡፡ ያ አዕምሮአዊ ምስል የቃሉ ፍቺ ወይም ይዘት ነው፡፡ እንደ አንበሳ ያሉ ስሜት ወይም ምስል በአዕምሮአችን ውስጥ የሚፈጥሩ ቃላት፣ በምንሰማቸው ጊዜ ስሜት ወይም ምስል ከማይፈጥሩ ሌሎች ቃላት ተለይተው ሊጠኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ <u>እንደ</u> የሚለውን ቃል ብንወስድ፣ ቃሉን ስንሰማ፣ <u>አንበሳ</u> እንደሚለው ቃል በአዕምሮአችን ውስጥ የሚፈጥረው አንዳችም ምስል ወይም ስሜት የለም፡፡ በአጠቃላይ ግን ቃሉ እንደ <u>አንበሳ</u> ካሉ ባለይዘት ቃላት ጋር እየገባ በመዋቅር ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለሚያጋጥመን፣ ከዚያ ገጠመኝ የሚመነጭ፣ ግን ደግሞ ይህ ነው ለማለት የሚያስቸግር፣ ደብዛዛ የሆነ ስሜት ሊሰጠን ይችላል፡፡ ይህ ስሜት ግን ከቃሉ ከራሱ የመነጨ ሳይሆን፣ ይዘት ካላቸው ሌሎች ቃላት ጋር ገብቶ ከፈጠረው መዋቅራዊ ዝምድና የሚመጣ ነው፡፡ ለምሳሌ፣

እንደ አንበሳ 1

ብንል፣ <u>እንደ</u> የሚለው ቃል የንፅፅር ተግባርን የሚያሳይ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡

ካሳ <u>እንደ</u> አንበሳ ደፋር ነው 2

ብንል፣ የካሳንና የአንበሳን የድፍረት ተመሳሳይነት መግለፃችን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ግን <u>እንደ</u> የሚለው ቃል በራሱ በአዕምሮአችን ውስጥ የሚያሳየን ምስል ወይም የሚፈጥርልን ስሜት የለም፡፡ ስለዚህም የዚህ አይነት ቃላት ስሜት ከሚሰጡ ወይም ምስል ከሚፈጥሩ እንደ <u>አንበሳ</u> ካሉ ሌሎች ቃላት ይለያሉ፡፡ በዚህም መሰረት ከፍ ሲል እንደጠቀስነው፣ በቋንቋዋ ውስጥ ያሉትን ቃላት

ርባታ

ቁጥር ነጠላ፣ ጥቂትና ብዙ ወይም ጥቅል ተብሎ በሶስት የመከፈሉ ነገር የአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ የሌሎች የሴም ቁዋንቁዋችም ባህሪ ነው፡፡ ለምሳሌ ስልጢ በሚባለው የቤተ-ጉራጌ ቁዋንቁዋ የሚከተሉትን እናገኛለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ጫፍ | 'ቅጠል' | 11 |
| ቻፍ-ቻ | 'ጥቂት ቅጠሎች'[3] | |

የመጀመሪያው ምሳሌ ነጠላነትን ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ጥቂትነትን ያመለክታል፡፡ ብዙነት ወይም ጥቅልነት የሚገለፀው በምዕላድ ሳይሆን፣ እንደ አማርኛው በሀረግ ነው፡፡ ሁኔታው ምናልባትም በሌሎች የሴም ቁዋንቁዋዎች የሚታይ ሳይሆን አይቀርም፡፡

እንግዲህ እስካሁን እንዳየነው፣ የአማርኛ ስሞች የነጠላ፣ የጥቂትና የብዙ ወይም የጥቅል ተብለው በሶስት ይከፈላሉ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሲባል ግን ማንኛውም ስም በነዚህ ሶስት ክፍሎች ውስጥ ይካተታል ማለት አይደለም፡፡ ርግጥ፣ ማንኛውም ስም በነጠላነቱ በነጠላ ክፍል ውስጥ ሊመደብ ይችላል፡፡ ከዚህ ውስጥ በጥቂትነት ሊመደቡ የሚችሉት አንድ ሁለት ተብለው ሊቆጠሩ የሚችሉ ነገሮችን የሚያመለክቱ ስሞች ብቻ ናቸው፡፡ አንድ፣ ሁለት፣ ተብለው ሊቆጠሩ የማይችሉ ነገሮችን የሚያመለክቱ ስሞች ዝቅተኛ መጠንን ለማሳየት እንደ ጥቂት፣ ትንሽ፣ ወዘተ፣ ካሉ መጣኝ ምዕላዶች ጋር ይዋቀራሉ፡፡ ከፍተኛ መጠንን ለማሳየት ደግሞ እንደ ብዙ፣ መዓት፣ ጅንድ፣ (ከፍተኛ መጠን) ወዘተ፣ ካሉ ሌሎች መጣኝ ምዕላዶች ጋር ይቀናጃሉ፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| ነጠላ | ጥቂት | ብዙ | 12 |
|---|---|---|---|
| ስኩዋር | ጥቂት ስኩዋር | መዓት ስኩዋር | |
| ወተት | ትንሽ ወተት | ብዙ ወተት | |
| ላም | ላም-ኦች | መዓት ላም | |

ከቅርፅ አንፃር፣ ባጠቃላይ ስሞችን የሚቆጠሩና የማይቆጠሩ ብሎ በሁለት ብቻ መከፈል ይቻላል፡፡ የሚቆጠሩትን አንደገና የጥቂትና የብዙ ብሎ አሁንም በሁለት መመደብ ይቻላል፡፡ የጥቂት ስሞች ብቻ /-ኦችች/ን ያስከትላሉ፡፡ ሌሎቹ በሙሉ ከተለያዩ መጣኝ ምዕላዶች ጋር በመቀናጀት የተለያየ መጠንን ሊያመለክቱ ይችላሉ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

ይህ ግን ስሞችን በተመለከተ ነው፡፡ የመስተዓምሮች የቁጥር ስርዓት ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

---

[3] ስለዚህ ጉዳይ ሀሳብ የለገሱኝ ባልደረባዩ ዶ/ር ኧርነስት ጉት ናቸው፡፡ በክስታኔም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳለ ሌላው ባልደረባዩ በድሉ ዋቅጅራ አጫውቶኛል፡፡

መሰረታዊ ቃል እስ- ሲሆን፣ እሱም ራስ የሚለው ስም ጉራጅ ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ማስረጃው አፀፋ ተውላጠ ስም በሚባሉት ውስጥ ሙሉ ቃሉ በግልፅ መታየቱ ነው፡፡ አፀፋ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ነጠላ | ብዙ |
|---|---|
| ራስ-ኤ | ራስ-አች-ን |
| ራስ-ህ | ራስ-አች-ሁ |
| ራስ-ሽ | |
| ራስ-ኡ | ራስ-አች-ኧው |
| ራስ-ኡ-አ | |

ከዚህ ላይ መደቡ ቃል ራስ የሚለው ስም መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ከእሱ ቀጥለው የሚገኙት የመደብ፣ የፆታ ወይም የቁጥር ምዕላዶች ናቸው፡፡

እንተ በሚለው ተውላጠ ስም መድረሻ ላይ የምትታየው /-ት/ ሁለተኛ መደብ አመልካች ምዕላድ ነች፡፡ ከእሰዋ ቀጥላ የገባችው /-ኢ/ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ነች፡፡ በስነ-ድምፅ ክፍል እንዳየነው፣ በ/-ኢ/ ምክንያት /ት/ ወደ [ች] ትለወጣለች፡፡ ይህች በሚለው ጠቋሚ ቃል ውስጥ የሚታየው ሁኔታም እንደዚሁ ነው፡፡ ታህታይ ቅርፁ /ይህ-ት-ኢ/ ነው፡፡ /-ት/ የሶስተኛ መደብ ምዕላድ ስትሆን፣ /-ኢ/ አንስታይ ፆታ አመልካች ነች፡፡ ሁለቱ ሲከታተሉ /ት/ ወደ [ች] ትለወጣለች፡፡ ራስሽ በሚለው አፀፋ ተውላጠ ስም ውስጥ፣ የሁለተኛ መደብ የአፀፋ ምዕላድ የሆነው /-ህ/ እና የዚሁ መደብ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ የሆነችው /-ኢ/ ስለተከታተሉ፣ /-ህ/ ወደ [ሽ] ተለውጣለች፡፡ ባለፈው ምዕራፍ እንዳየነው፣ እነዚህ በምዕላድ ድንበር ላይ የሚታዩ የሙሉ (ድ)ላነቃዊነት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

እንግዲህ እስካሁን እንደ ተመለከትነው፣ እንስታይ ፆታን የሚያመለክተው ምዕላድ በስሞችና በቅፅሎች ላይ /-ኢት/፣ በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስሞችና ጠቋሚ ቃላት ላይ /-ኢ/፣ በሶስተኛ መደብ ላይ /-አ/ የሚል ቅርፅ አለው፡፡ እነዚህ የተለያዩ ቅርፆች ዘረ-ምዕላድ ይባላሉ፡፡ የአንድ ምዕላድ ዘሮች እንደማለት ነው፡፡ ከነዚህ ዘረ-ምዕላዶች አንዱን በራሱ ወይም አብሮት በሚዋቀር ግስ አማካኝነት የሚያሳይ ስም፣ ቅፅል ወይም መስተዓምር የአንስታይ ፆታ ስም፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ ሲባል፣ ይህንን የማያደርግ ደግሞ የተባዕታይ ፆታ ስም፣ ወዘተ፣ ይባላል፡፡ ማንኛውም ስም ከነዚህ ከሁለቱ በአንዱ ወይም በሌላው ውስጥ መመደብ አለበት፡፡

ይህን ሁኔታ ካለመገንዘብ፣ ቀደምት ሊቃውንት እንደ ፈረስ ላሉ ስሞች የወል ፆታ የሚባል ከአንስታይና ከተባዕታይ የተለየ ክፍል መድበው ነበር፡፡ መገለጫውም ወንዴ ወይም ሴቴ መሆኑን የማያመለክት ስም የሚመደብበት የፆታ አይነት የሚል ነው፡፡ በስሞች ቅርፅ ላይ ላይሆን፣ ስሞቹ በሚያመለክቱት ነገር የተፈጥሮ ፆታ ላይ የተመሰረተ ግላዌ ነው፡፡ በዚህም መሰረት እንደ ፈረስ በተፈጥሮአቸው ወንዴ ወይም ሴቴ የሆኑ እንስሳትን ሊያመለክቱ የሚችሉ

ስሞች፣ በዚህ ክፍል ውስጥ እንደሚመደቡ፡ ሊቃውንቱ ይገልፃሉ፡፡ እስካሁን በዚህ ክፍል ባየነው የፆታ ባህሪ መስረት ግን ማንኛውም የአንስታይ ፆታን ምዕላድ ያላስከተለ ስም፣ ምድቡ በተባዕታይ ፆታ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ መስረት እንደ ፈረስ ያሉ ስሞችም ምድባቸው በዚሁ ፆታ ስለሚሆን፣ የወል ፆታ የሚል ክፍል መመደብ አስፈላጊ አይደለም፡፡

የሊቃውንቱ ጥናት በአብዛኛው የተመሰረተው በስሞች ቅርፅ ላይ ሳይሆን፣ በትርጉም ላይ በመሆኑና፣ ትርጉምም ስሜታዊና ተለዋዋጭ ስለሆነ፣ በቅርፃቸው በአንድ ወይም በሁለት ክፍሎች ሊካተቱ ለሚችሉ ቃላት እንደ ትርጉማቸው ልዩነት፣ የተለያዩ ክፍሎች እንዲፈጠሩ አስገድደዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ከፍ ሲል እንዳየነው፣ ከቅርፅ አኳዋያ በሁለት ሊመደቡ ለሚችሉ ስሞች፣ ሶስት የፆታ ክፍሎች ሊፈጥሩ ችለዋል፡፡ ጉዳዩ ግን በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ እነዚህ ሶስት ክፍሎች ህይወት ያላቸውን ነገሮች ለሚያመለክቱ ስሞች ብቻ የተመደቡ ናቸው፡፡ ህይወት የሌላቸው ነገሮችን የሚያመለክቱ እንደ ድንጊያ፣ ዛፍ፣ ቤት፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞች በነዚህ ክፍሎች ሊካተቱ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ለእነዚህ አይነት ስሞች የተለየ ክፍል መፍጠር አስፈልጎአል፡፡ ለዚህም ግዑዝ ፆታ የሚባል አራተኛ የፆታ ክፍል ተመድቦአል፡፡

በእኔ አመለካከት እንደ <u>ድንጊያ</u> ያሉ ስሞች ህይወት የሌላቸው ነገሮችን ቢያመለክቱም፣ በቅርፃቸው ብቻ በተባዕታይ ፆታ ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ከቅርፃቸው አንፃር ሲመረመሩ፣ የግዑዝ ፆታ ምልክት የላቸውም፤ ሊኖራቸውም አይችልም፡፡ ምክንያቱም የወል ፆታ ምዕላድ በቋንቋዋ ውስጥ እንደሌለ ሁሉ፣ የግዑዝ ፆታ ምዕላድ የሚባልም የለም፡፡ በቋንቋዋ ውስጥ ያሚገኙት የፆታ ክፍሎች ቀደም ሲል የተጠቀሱት ተባዕታይ እና አንስታይ ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህም በተለየ ምዕላድ የሚገለፀው አንስታይ ፆታ ብቻ ነው፡፡ የዚህን ፆታ ምዕላድ ያስከተለ ማንኛውም ስም አንስታይ፣ ያላስከተለው ደግሞ ተባዕታይ ነው፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከነዚህ ከሁለቱ ውጭ የሚሆን ስም የለም፡፡ ስለዚህም የወልና የግዑዝ ፆታ ብሎ ተጨማሪ ክፍል መፍጠሩ አላስፈላጊ ብቻ ሳይሆን፣ አጨቃጫቂም ነው፡፡ ህይወት የሌላቸው ነገሮች ሲባል፣ ምን ማለት ነው? ወደሚል ጥያቄም ይወስዳል፡፡ ለምሳሌ፣ ግዑዝ የሚባለው ህይወት የሌለው ነው፣ ተብሎአል፡፡ በዚህ መስረት አንድ ህይወት የነበረው ነገር፣ ህይወቱን ሲያጣ ግዑዝ ሊሆን ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ፆታው ከምን ክፍል ሊመደብ ነው? ለምሳሌ፣ <u>ካስች</u> የሚለው የተፅውዖ ስም ፆታ አንስታይ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ [-ች] < /ት-እ/ የሚለውን የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ማስከተሉ ነው፡፡ በዚህ ስም የምትጠራዋ ሴት የተፈጥሮ ፆታ ሴቴ ነው፡፡ ይህች ሴት ህይወትዋን ብታጣ፣ ፆታዋ ግዑዝ ነው፣ ሊባል ነው? በእኔ አመለካከት ሲትዮዋ ህይወትዋን ብታጣም፣ የእስዋ መጠሪያ የሆነው <u>ካስች</u> የሚለው ስም፣ አሁንም ክፍሉ አንስታይ ነው፡፡ ምናልባት ሴትዮዋ ህይወትዋን ካጣች፤ በድን ወይም ግዑዝ ስለምትሆን፣ የዚያ ግዑዝ አካል የፆታ ክፍል ግዑዝ ነው፤ ይባል ይሆናል፡፡ በእኔ በኩል ግን ለዚያ

ባህሪውን፣ ወደፊት በቦታው እናየዋለን። አሁን ግን እነዚህን ተግባራት ሲፈፅሙ የሚያሳዩዋቸውን የተለያዩ የቅርፅ ለውጦች ብቻ እንገልፃለን።

ስሞች ከላይ ከተጠቀሱት ሙያዎች መካከል ለሁለቱ ብቻ ቅርፃቸውን በከፊል ይለውጣሉ። ሙያዎቹም ተሳቢና ዘርፍ ናቸው። ለዚህ የሚከተለውን እንመልከት።

| ስም | ባለቤት | ተሳቢ | ዘርፍ | 1 |
|---|---|---|---|---|
| ቤት | ቤት | ቤት-ን | ቤት-የ | ቤቴ |
| በግ | በግ | በግ-ን | በግ-የ | በጌ |
| ልጅ | ልጅ | ልጅ-ን | ልጅ-የ | ልጇ |
| ላም | ላም | ላም-ን | ላም-የ | ላሚ |

በግልፅ እንደሚታየው፣ ስሞቹ ለተሳቢነት /-ን/ን፣ ለዘርፍነት ደግሞ /-የ/ን ያስከትላሉ። ለባለቤትነት ምንም ምልክት የላቸውም። ምልክት አለማሳየታቸው ራሱ ምልክታቸው ነው፣ ለማለት ይቻላል። ስለዚህም በአረፍተ ነገር ውስጥ በባለቤት ቦታ የሚገኝ ማንኛውም ምልክት የሌለው ስም ሙያው ባለቤት ነው፣ ሲባል ይችላል።

ከላይ እንደተገለፀው ስሞች በባለቤትነትና በተሳቢነት በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ፣ የተለያየ ቦታ አላቸው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ አስቴር-ን መታት
(ለ) አስቴር ካሳ-ን መታችው
(ሐ) *አስቴር ካሳ መታችው

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ካሳ የሚለው ስም ባለቤት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለባለቤትነት የተለየ ምዕላዳዊ ምልክት የለም። ስለዚህም ስሙ የሚታየው ሌጣውን ነው። ይሁን እንጅ በአገባቡ የአረፍተ ነገሩ የመጀመሪያ ቃል ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ይኸው ስም መታችው ከሚለው ግስ ቀድሞ ገብቶአል። ይህ ቦታ የተሳቢ ስለሆነ፣ ስሙ የተሳቢ ምልክት የሆነውን /-ን/ን አስከትሎአል። ሶስተኛው ምሳሌ ተቀባይነት ያለው አርፍተ ነገር አይደለም። ምክንያቱም ካሳ የሚለው ስም በተሳቢ ቦታ ያለተሳቢ ምልክት መግባቱ ነው።

ዘርፍ ሙያ የሚገኘው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ስሞችን በያዘ ስማዊ ሀረግ ውስጥ ነው። የሚገልፀውም በሀረጉ ውስጥ የሚገኙትን ስሞች ዝምድና ነው። ዝምድናው የገንዘብና የባለገንዘብ ነው። ይህም የሚገለፀው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው ባለገንዘቡን ከሚጠቁመው ስም በፊት /የ-/ የሚል ምዕላድ በማስቀመጥ ሲሆን፣ ሁለተኛው ገንዘቡን ከሚጠቁመው ስም መድረሻ ላይ የተለያዩ ምዕላዶችን በመቀጠል ነው። ሁለቱንም መንገዶች እንደሚከተለው በየተራ እናሳያለን።

ርባታ

(ሀ) የ-ካሳ ቤት 3
(ለ) የ-እስቴር ቤት
(መ) የ-ልጆቹ ቤት

እነዚህ የስማዊ ሀረግ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በያንዳንዳቸው ውስጥ ሁለት፣ ሁለት ስሞች አሉ፡፡ ከሁለቱ ስሞች የመጀመሪያው፤ በሁለተኛው ስም የሚጠቀመው ነገር ባለገንዘብ ወይም ባለቤት ነው፡፡ ይህንንም የባለንብረትነት ሙያውን ለማሳየት /የ-/ን አስቀድሞአል፡፡ ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው ሀረግ ውስጥ ካሳ ባለገንዘብ፣ ቤት ደግሞ ገንዘብ ወይም ንብረት ነው፡፡ ስለሆነም ባለገንዘቡ ካሳ /የ-/ን አስቀድሞ ገብቶአል፡፡ ይህች ምዕላድ ገንዝብንና ባለገንዘብን ስለምታያይዝ *አገናዛቢ* ትባላለች፡፡

ሁለተኛው መንገድ ከላይ የሚታየው ተቃራኒ ነው፡፡ ይኸውም ባለገንዘቡን የሚያመለክተው ምዕላድ ከባለገንዘቡ ላይ ሳይሆን፣ ገንዘቡን ከሚጠቁመው ስም መድረሻ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ነው፡፡ የምዕላዱም ቅርፅ ከላይ እንደሚታየው እንደ /የ-/ አንድ አይነት ሳይሆን፣ እንደ ባለገንዘቡ መደብ፣ ቁጥርና ፆታ የተለያየ ነው፡፡ እንዴት እንደሚለያይ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

| መደብ | | ስም | ዘርፍ |
|---|---|---|---|
| 1ኛ | | ቤት | ቤት-የ |
| 2ኛ | ተ | | ቤት-ህ |
| | አ | | ቤት-ሽ </-ሀ-ኢ/[4] |
| 3ኛ | ተ | | ቤት-ኡ |
| | አ | | ቤት-ዋ </-ኡ-አ/ |
| | ብ | | ቤት-አችን /-እችች-ን/ |
| | | | ቤት-አችሁ </-አችች-ሀ-ኡ/ |
| | | | ቤት-አቸው </-አችች-ኸ-ኡ/ |

4

በዚህ አይነት ማንኛውም ስም የተለያዩ ቅጣዮችን በማስከተል ቅርፁን እየለዋወጠ ዘርፍ ሙያን ያሳያል፡፡ ምዕላዶቹ ባለገንዘብን ስለሚያመለክቱ፣ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አገናዛቢ አፀፋ በመባል ይታወቃሉ፡፡ አፀፋነታቸው ባለገንዘቡን ለሚያመለክተው ስም ነው፡፡ ይሁን እንጅ ምዕላዶቹ የሚያገናዝቡት ባለገንዘብና

[4] ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፤ /-ህ/ ሁለተኛ መደብ አመልካች ለሆን፣ /-ኢ/ አንስታይ ፆታን አመልካች ነች፡፡ [-ሽ] የሁለቱ ውህደት የፈጠራት ውሁድ ቅርፅ ነች፡፡ /ኢ-/ አንስታይ ፆታ አመልካችና ከመደብ አመልካቹ ከ/ሀ-/ የተለየች ለመሆንዋ ምልክቱ፣ በግሱ ትዕዛዛዊ ቅርፁ ውስጥ ብቻዋን መገኘትዋ ነው፡፡ ይህም ለምሳሌ፣ ኑር ብለን ኑር-ኢ ስንል ነው፡፡ እንደዚሁም /-ኡ-/ ሶስተኛ መደብ አመልካች ሊሆን፣ /-አ/ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ነች፡፡ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ዘረ-ምዕላዶች እንዳሉት ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ በብዙ ቁጥር ስር የሚታዩትም መደብንና ቁጥርን ያዋሀዱ ውሁድ ምዕላዶች ናቸው፡፡ ዝርዝሩን ከባየ (2004) ላይ ይመልከቱ፡፡

ገንዘብን ብቻ ሳይሆን፣ ባለድርጊትንና ድርጊትንም ሊሆን ይችላል። ባለድርጊት ስንል፣ ድርጊት ፈፃሚን የሚያመለክት ስም ማለታችን ነው። ስለ ሁኔታው የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

| መደብ | | ስም | ዘርፍ | | 5 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | | መሂድ | መሂድ-የ [5] | | |
| 2ኛ | ተ | | መሂድ-ሀ | | |
| | አ | | መሂድ-ሽ | </-ሀ-ኢ/ | |
| 3ኛ | ተ | | መሂድ-ኡ | | |
| | አ | | መሂድ-ዋ | </ኡ-አ/ | |
| | ብ | | መሂድ-አችን | </-አችች-ን/ | |
| | | | መሂድ-አችሁ | </-አችች-ሀ-ኡ/ | |
| | | | መሂድ-አቸው | < /-አችች-ኽ-ኡ/ | |

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የዘርፉ ምዕላዶች የሚያመለክቱት ባለገንዘብን ሳይሆን፣ ባለድርጊትን ነው። መሂድ የሚለው ቃል የድርጊት ስም ስለሆነ፣ ምዕላዶቹ የሚያመለክቱት የድርጊቱን ፈፃሚ፣ ማለትም አድራጊውን፣ ነው። ይህን ሙያውን አንድም፣ ከላይ እንደሚታየው፣ በተለያዩ ምዕላዶች፣ አለያም ቀደም ሲል እንደጠቀስነው፣ /የ-/ የሚለውን ምዕላድ በማስቀደም እንደሚከተለው ያሳያል።

| | | 6 |
|---|---|---|
| የ-እኔ | መሂድ | |
| የ-አንተ | መሂድ | |
| የ-አንቺ | መሂድ | |
| የ-እሱ | መሂድ | |
| የ-እስዋ | መሂድ | |
| የ-እኛ | መሂድ | |
| የ-እናንተ | መሂድ | |
| የ-እነሱ | መሂድ | |

አድራጊው ወይም ባለገንዘቡ ስም /የ-/ን አስቀድሞ ከገባ፣ ድርጊቱን ወይም ገንዘቡን የሚያመለክተው ስም፣ አድራጊውን ወይም ባለገንዘቡን የሚጠቁም ምንም አይነት ቅጣይ አያስከትልም። ስለዚህም፣

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| (ሀ) | *የእኔ | ቤት-የ | *የእኔ | መሂድ-የ | 7 |
| (ለ) | *የአንተ | ቤት-ሀ | *የአንተ | መሂድ-ሀ | |

ወዘተ፣

[5] የእነዚህን ምዕላዶች ባህሪ በተመለከተ ሀይሉ (1967)ን እንዲሁም ባየ (1990)ን ይመልከቱ።

ማለት ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለም፡፡ ባንፃሩ ግን፣

(ሀ) እኔ ቤት-የ እኔ መሄድ-የ 8
(ለ) አንተ ቤት-ሀ አንተ መሄድ-ሀ
ወዘተ፣

ማለት ይቻላል፡፡ ባጭሩ፣ ዘርፍ ሙ-ያ በቅጣይ የአፀፋ ምዕላዶች ወይም /የ/ በሚሰው ምዕላድ ይገለፃል፡፡ /የ/ የሚገባው ከባለገንዘቡ ወይም ከባለድርጊቱ፣ ወዘተ፣ ሰም በፊት ሲሆን፣ አፀፋው የሚገባው ከተገናዛቢው ሰም መድረሻ ላይ ነው፡፡

## *ዕምርነት*

ዕምርነት ሰንል ዕውቅ መሆን ማለታችን ነው፡፡ አንድ ሰም የሚገልፀው ነገር የታመረ (የታወቀ) ከሆነ፣ ሰሙ ላይ የዕምርነት ምልክት ይኖራል፡፡ ያልታመረ (ያልታወቀ) ነገርን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገልፅ ከሆነ፣ ኢዕምር ሰም ይባላል፡፡ ዕምር ያልሆነ ሰም ምንም ቅጣይ ምልክት የለውም፡፡ ዕምር የሆነ ሰም ግን ምልክት አለው፡፡ ምልክቱም /-ኡ/ ነው፡፡ ቀደም ሲል ከፆታ ጋር ያለውን ቁርኝት አሰመልከተን በመጠኑ አይተነዋል፡፡ የሚከተለውን ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

| ሰም | ኢዕምር | ዕምር | 1 |
|---|---|---|---|
| ቤት | ቤት | ቤት-ኡ | |
| በግ | በግ | በግ-ኡ | |
| ድመት | ድመት | ድመት-ኡ | |
| ዛፍ | ዛፍ | ዛፍ-ኡ | |
| አይጥ | አይጥ | አይጥ-ኡ | |

እነዚህ ሰሞች በሙሉ ተባዕታይ ናቸው፡፡ አንስታይ ሲሆኑ የዚሁ መግለጫ የሆነችውን /-ኢት/ን ከዕምሩ ምዕላድ በፊት ማስገባት፣ ወይም ሌላዋን ዘረ ምዕላድ፣ ማለትም /-ኣ/ን፣ ከዕምሩ ምዕላድ በሁዋላ ማስከተል አለባቸው፡፡ ይህ ሲሆን፣ ቤት የሚለው ሰም /ቤት-ኢት-ኡ/ ወይም /ቤት-ኡ-ኣ/ ይሆናል፡፡ /ቤት-ኡ-ኣ/ በሚለው ውስጥ የዕምሩ ምዕላድ /-ኡ/ እና የፆታው ምዕላድ /-ኣ/ እየተዋሀዱ /-ዋ/ የሚል ቅርፅ ይፈጥራሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ ይህ ውሁድ ቅርፅ እንደ ተራ ምዕላድ እየተቆጠረ የአንስታይ ፆታ ሰሞች የዕምርነት ምልክት እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ዕምርነትን ከቁጥር ጋር አገናዝበን ብንመለከተው፣ የፆታዋ ምዕላድ ከዕምርዋ ምዕላድ የተለየች እንደሆነች ለመረዳት ስለምንችል ነው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

ርባታ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንጥል ተባዕታይ፡ | /ሰኸው - እይይኽ - ኡ/ | ሰውየው | 2 |
| ንጥል አንስታይ፡ | /ሰኸው - እይይኽ - ኡ - ኣ/ | ሰውየዋ | |
| ብዙ፡ | /ሰኸው - - - ኦችች - ኡ -/ | ሰዎቹ | |
| | | *ሰውየዎቹ | |
| | | *ሰውየዎችኡኣ | |

በንጥሉ የተባዕታይ ስም፣ የንጥልነቱ ምዕላድ /-እይይኽ-/ እና የዕምርነቱ /-ኡ/ ተከታትለው እንደገቡ እናያለን፡፡ በንጥሉ የአንስታይ ስም ግን የንጥልነቱ /-እይይኽ-/፣ የዕምርነቱ /-ኡ/ እና የአንስታይነቱ /-ኣ/ በዚሁ ቅደም ተከተል ተከታትለው ገብተዋል፡፡ /-ኣ/ የምትለዋ ምዕላድ እንደ ሰውየው ባሉ ስሞች መድረሻ ላይ ስትገኝ፣ አንስታይነትን ሳይሆን፣ ንዑስነትን ታመለክታለች፡፡ ስለዚህም ሰውየዋ ስንል፣ በአዕምሮአችን የሚፈጠረው ምስል አጭር፣ ቀጭንና ምናልባትም ብልጣ-ብልጥ ሽማግሌ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህንኑ ሁኔታ /-ኢት/ በምትለዋ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ አማካኝንት መግልፅ ይቻላል፡፡ ስለዚህም ሰውየዋ (/ሰኸው-እይይኽ-ኡ-ኣ/) የሚለው ሰውየይቱ (/ሰኸው-እይይኽ-ኢት-ኡ/) ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ ቃል ውስጥ /-ኢት/ የምትለዋ ምዕላድ ከነጣዩ ምዕላድ ከ/-እይይኽ-/ ቀጥላ ገብታለች፡፡ በዚህም በቃል መድረሻ ከምትገኘው ከ/-ኣ/ በአገባብ ብቻ ትለያለች፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ /-ኢት/ እና /-ኣ/ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ የተለያዩ ቅርፆች ወይም ዘረ-ምዕላዶች ናቸው፡፡

በብዙ ቁጥር ላይ ደግሞ የንጥልነቱም ሆነ የአንስታይነቱ ምዕላድ አይታይም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ፣ በአንድ በኩል፣ አንድ ስም በአንድ ጊዜ ንጥልና ብዙ ሊሆን አለመቻሉ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ በአማርኛ የብዙ ቁጥር የሆነ ስም የአንስታይነትን ምዕላድ የማያሳይ መሆኑ ነው፡፡ ባጭሩ፣ አንድ ስም የብዙ ቁጥር ከሆነ፣ የንጥልነትንም ሆነ የአንስታይነትን ምዕላድ አያሳይም፡፡ አሳይቶ ቢገኝ፣ አባባሉ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ዋናው ቁም ነገር፣ በአማርኛ ዕምርነትና ፆታ፣ እንዲሁም አንስታይነትና ንዑስነት ቁርኝት ያላቸው መሆኑን መገንዘብ ነው፡፡

## ቅፅል

ቅፅሎች እንደ ስሞች ሁሉ ለቁጥር፣ ለፆታ፣ ለሙያና ለዕምርነት ቅርፃቸውን ይለዋውጣሉ፡፡ ሙያን፣ ዕምርነትንና ፆታን የሚያሳዩት ከፍ ሲል እንዳየናቸው እንደ ስሞች ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ እንደገና አንደግመውም፡፡ ቁጥርን በሚመለከት ግን ከስሞች ለየት የሚያደርጋቸው ትንሽ ሁኔታ ስላለ፣ በእሱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡

ቅፅሎች ብዛትን (ጥቂትነትን) የሚያሳዩት በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው፣ እንደ ስሞች /-ኦችች/ የሚለውን ምዕላድ በማስከተል ሲሆን፣ ሁለተኛው ከመጀመሪያው (ከግራ ወደ ቀኝ) ቀጥሎ የሚገኘውን ተናባቢ ድምፅ በመድገምና ከእሱ ቀጥሎ /-ኣ-/ የሚል አያያዥ ምዕላድ በማስገባት ነው፡፡

ርባታ

ይህን ሁለተኛውን ተናባቢ ድምፅ ይደጋግማል የሚለውን አመለካከት ግን በደንብ ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ቅፅሎቹ ሁለተኛውን ተናባቢ ድምፅ ይደጋግሙ ስንል፣ ምን ማለታችን ነው? በርግጥስ ድምፁ ነወይ የሚደጋገመው? የሚደጋገመው ቃሉ ራሱ ነው፣ ብንልስ? ለምሳሌ፣ <u>ቅጠል</u> የሚለው ቃል ራሱን ደግሞ <u>ቅጠል - ቅጠል</u> ይሆንና በተደጋጋሚዎቹ ቃላት መካከል /-አ-/ የሚለውን አያያዥ አናባቢ በማስገባት <u>ቅጠል-አ-ቅጠል</u> "ቅጠላቅጠል" የሚለውን የስብስብ ስም አገኘን እንበል፡፡ በዚሁ መሰረት ጥ<u>ቁዋቁር</u> የሚለውን ቅፅል እንየው፡፡ ጥቁር የሚለው ቃል ራሱን ደግሞ <u>ጥቁር-ጥቁር</u> ከሆነ በሁዋላ /-አ-/ የሚለውን አያያዥ ምዕላድ በሁለቱ ቃላት መካከል በማስገባት መጀመሪያ <u>ጥቁር-አ-ጥቁር</u> "ጥቁራጥቁር" ሆነ ለማለት እንችላለን፡፡ በመሰረቱ ይህን ቃል የሚሰማ አማርኛ ተናጋሪም የቃሉን ተርጉም ያጣዋል ለማለት አንችልም፡፡ አባባሉም ቢሆን፣ እንግዳ የሚሆንበት አይመስለንም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የዚህ አይነት ስርዓት የሚከተሉ እንደ <u>ሰው-አ-ሰው፣</u> <u>ልጅ-አ-ልጅ፣</u> ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን ስለሚያውቅ ነው፡፡ ይህ ከሆነ፣ እንደ <u>ጥቁር-አ-ጥቁር</u> ያሉ ቅፅሎች ከስሞቹ የሚለዩት የመጀመሪያውን ቃል የመጨረሻ ተናባቢና የሁለተኛውን ቃል የመጀመሪያ ተናባቢ በመግደፋቸው ብቻ ነው፡፡

እነዚህን የሚገደፉ ድምፆች ባለፈው ምዕራፍ ከተመለከትነው ከቀለም መዋቅር ጋር እያገናዘብን እናስባቸው፡፡ ማንኛውም ቀለም ከአንድ አናባቢና ከአንድ ወይም ከሁለት ተናባቢ ድምፆች እንደሚዋቀር አይተናል፡፡ ተናባቢዎቹ የየቀለሙ በር ከፋችና ዘጊ (ጨራሽ) እንደሆኑና አንዳንድ ጊዜም በግህድ እንደማይታዩ ገልፀን ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር በየቅፅሉ፣ በየስሙ፣ ወደፊት እንደምናየውም፣ በየግሱ ውስጥ ይደገማል የምንለውን ሁለተኛ ተናባቢ ድምፅ፣ የየቃሉ ሳይሆን፣ የየቀለሙ ከፋች እና ጨራሽ ተናባቢ ድምፅ ነው፣ ለማለት እንችላለን፡፡ <u>ጥቁር-አ-ጥቁር</u> የሚለውን ቅፅል እንመርምረው፡፡

1 2
/ጥ ቅ እ ር/ /ጥ ቅ ኡ ር/

የመጀመሪያው ቀለም ጨራሽ ተናባቢ ድምፅ /ር/ ነው፡፡ የሁለተኛው ቀለም ከፋች ተናባቢ ደግሞ /ጥ/ ነው፡፡ የሚጎረዱትም እነዚሁ ሁለት ድምፆች ናቸው፡፡ ሲጎረዱ የምናገኘው /ጥ ቅ ኡ/ - /ቅ እ ር/ የሚሉትን ጉርድ እህዶች ነው፡፡ ሁለቱን ጉራጆች አያይዞ አንድ ሙሉ ቃል ለመፍጠር /አ/ በመካከላቸው ይገባል፡፡ ከዚህ ሁኔታ የሚጎረዱት እንደ /ር/ እና /ጥ/ ያሉ ከፋችና ጨራሽ ተናባቢዎች ናቸው፤ ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡

ርግጥ፣ ይህን ድምፅን የመጉረድና ቃልን የማሳጠር ሂደት የማይፈቀዱ እንደሚከተሉት ያሉ ቃላት አሉ፡፡ እነሱን ለብቻ ማየት ይቻላል፡፡

ርባታ

| | | |
|---|---|---|
| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | 1 |
| ሰነፍ | ሰነፍ-ኦች | |
| ብልህ | ብልህ-ኦች | |
| ብልጥ | ብልጥ-ኦች | |
| የዋህ | የዋህ-ኦች | |
| ጎበዝ | ጎበዝ-ኦች | |

እንደነዚህ ያሉት <u>ሰነፍ - ሰነፍ፣ ብልህ - ብልህ</u> እያሉ የሚደግሙ ብቻ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡

ሰነፍ - ሰነፉ ስራ አይሰራም 2

ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ሆኖ ከላይ ባየነው መሰረት እነዚህንም ቢሆን፣ በ/አ/ አማካኝነት እያጣመሩ <u>ሰነፍ -አ- ሰነፍ</u> "ሰነፋሰነፍ" ማለት ይቻላል፡፡

ወደ ቁጥር ተግባር እንመለስ፡፡ /-ኦችች/ የሚለውን ምዕላድ ያሚያስከትሉ ቅፅሎች የአንድን ሰው ወይም እንስሳ ባህሪ፣ ማለትም ሰንፍናውን፣ ጉብዝናውን፣ ብልጠቱን፣ ወዘተ፣ መግለፅ ነው፡፡ ለለሆነም፣ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ የባህሪ ቅፅል በመባል ይታወቃሉ፡፡ ይሁን እንጅ፣ /-ኦችች/ የሚያመለከተው የባህሪውን መጠን ሳይሆን፣ የባህሪውን ባለቤቶች ቁጥር ነው፡፡ ባህሪ በአይነት እንጅ በአህዝ ሊቆጠር የሚችል ነገር አይደለምና፡፡ በአህዝ ሊቆጠር የሚችለው የባህሪው ባለቤት የሆነው ነገር ነው፡፡ ስለዚህም ሰነፎች ስንል፣ ሰነፍ የሆኑ ሰዎች ማለታችን ነው፡፡ /-ኦችች/ የሚለው ምዕላድ ሰው የሚለውን ስም እንጅ፣ ሰነፍ የሚለውን ቅፅል አያመለከትም፡፡

ከፍ ሲል በተገለፀው ሁኔታ ሙሉ አካላቸውን የሚደጋግሙትና ድምፅ የሚጎርዱት እንደሚከተሉት ያሉት ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | 3 |
| ረዥም | ረዥ-አ-ዥም | |
| ነጭ | ነጭ-አ-ጭ | |
| ቀይ | ቀይ-አ-ይ | |

እነዚህ የአንድን ነገር የቀለም አይነት ስለሚያመለክቱ፣ የአይነት ቅፅል ተብለው ከላይ ካየናቸው የባህሪ ቅፅሎች ሊለዩ ይችላሉ፡፡ ቅፅሎቹ የሚጠቁሙት የሰዎችን የቀለም አይነት ሲሆን፣ /-ኦችች/ የሚለውን ምዕላድ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ነጭ-ኦች፣ ጥቁር-ኦች፣ ወዘተ፣ በማለት የሰዎቹን ብዛት መግለፅ ይቻላል፡፡ እንደነዚህ አይነት ቅፅሎች በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ በቂ ቅፅል ይባላሉ፡፡ በቂ የሚባሉበት ምክንያት ያለምንም ስም ብቻቸውን ሊቆሙ መቻላቸው ነው፡፡ ለምሳሌ፣ *ጥቁር ህዝቦች* በማለት ፋንታ፣ *ጥቁሮች* ብሎ ህዝቦች የሚለውን ስም መግደፍ ይቻላል፡፡ <u>ህዝቦች</u> የሚለው ስም /-ኦችች/ የሚለውን

ርባታ

የቁጥር ምዕላድ ለቅፅሉ እየሰጠ ከቦታው ሊሰወር ይችላል፡፡ የሰሙን ባህሪ የያዘው ቅፅልም ስሙ ለሚፈፅመው ተግባር ብቁ እንደሆነ ተቆጥሮ፣ በቂ ቅፅል ሊባል ችሎአል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ተናባቢ ድምፃቸውን እየደጋገሙ የአንድን ነገር አካላዊ መጠን የሚገልፁ ቅፅሎችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | 4 |
|---|---|---|
| ትልቅ | ትል-ኣ-ልቅ | |
| ትንሽ | ትን-ኣ-ንሽ | |
| ረዥም | ረዥ-ኣ-ዥም | |
| ወፍራም | ወፍ-ኣ-ፍራም | |
| ቀጭን | ቀጭ-ኣ-ጭን | |

እንደነዚህ ያሉት ቅፅሎች፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀመው መጠንን ብቻ ሳይሆን፣ ወገንነትንም ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ <u>ትል-ኣ-ልቅ</u> የሚለውን ቃል ብንመለከት፣ የሚያመለክተው ከአንድ ስብስብ ውስጥ፣ የትልቅ ወገን የሆኑትን ነገሮች ነው፡፡ ትልቅ፣ ትልቅ የሆኑ ነገሮችን ብዛት ለማመልከት ሲፈለግ፣ ትል-ኣ-ልቅ በሚለው ላይ /-ኦችች/ን መጨመር ያስፈልጋል፡፡ ይህንን ስናደርግ ትላልቆች የሚለውን ቅርፅ እናገኛለን፡፡ ስለ ትርጉሙ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) ትላልቁን ዛፍ ቆረጠው 5
(ለ) *ትላልቁን ዛፎች ቆረጣቸው

ምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ያለው አባባል አይደለም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ትላልቅ የሚለው ቅፅልና ዛፎች የሚለው ስም በቁጥር ስምሙ አለመሆናቸው ነው፡፡ ዛፎች የሚለው ስም የብዙ ቁጥር (ጥቂት) ስለሆነ፣ እሱን የሚገልፀው ቅፅልም እንደዚሁ የብዙ ቁጥር መሆን አለበት፡፡ ትላልቅ የሚለው የብዙ ቁጥር ቢሆን ኖሮ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ያገኝ ነበር፡፡ የአረፍተ ነገሩ መዛባት ቅፅሉ ብዛትን ሳይሆን፣ ወገንን ብቻ እንደሚያመለክት ያስገነዝባል፡፡ ብዛትን እንዲገልፅ ከፈልግን፣ በቅፅሉ ላይ /-ኦችች/ን መጨመር ይኖርብናል፡፡ ይህን ስናደርግ፣ የሚከተለውን እናገኛለን፣

ትላልቆቹን ዛፎች ቆረጣቸው 6

ይህ ምሳሌ የሚያመለክተው የትልቅ ወገን የሆኑ ጥቂት ዛፎችን ነው፡፡

እንደ ትላልቅ ያሉ ቅፅሎች /-ኦችች/ የሚለውን ምዕላድ ሳያስከትሉ ብዛትን የሚገልፁበት ሁኔታም አለ፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ትልቅ ልጅ አለው 7
(ለ) ካሳ ትላልቅ ልጆች አሉት
(መ) ?ካሳ ትልቅ ልጆች አሉት

ርባታ

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ልጅ የሚለው ስም ነጠላ በመሆኑ፣ ትልቅ የሚለው ቅፅልም እንደዚሁ ነጠላ ሲሆን ችሎአል። በሁለተኛው ምሳሌም ልጆች የሚለው ስም የብዙ ቁጥር በመሆኑ፣ ቅፅሉም እንደዚሁ የብዙ ቁጥር ነው፣ ለማለት ይቻላል። ብዙነቱን የሚያመለክተው ግን /-ኦችች/ን በማስከተል ሳይሆን፣ ራሱን በመደጋገም ነው። ከዚህም የምንረዳው ድግግሞሽ አንዳንድ ጊዜ ወገንን፣ ሌላ ጊዜ ብዛትን የሚያመለክት መሆኑን ነው። ወገንን የሚያመለክተው ከቅፅሉ ጋር የሚዋቀረው ስም በምሳሌ 6(ሀ) እንደሚታየው የነጠላ ቁጥር ስም ሲሆን ነው። ብዛትን የሚያመለክተው ደግሞ ስሙ የብዙ ቁጥር ሲሆን ነው። ባጭሩ ድግግሞሽ ከነጠላ ስም ጋር ወገንን፣ ከብዙ ቁጥር ስም ጋር ብዛትን ያመለክታል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። የምሳሌ (መ) መዛባት የሚያሳየው ይህንኑ የስሞችንና የቅፅሎችን የቁጥር ስምሙነት ነው። ወደሚቀጥለው እንሂድ።

## ግስ

ግሶች ለመደብ፣ ለፆታ፣ ለቁጥር፣ ለአንቀፅ፣ ለስልት እንዲሁም ለጊዜ የተለያዩ ቅጣይ ምዕላዶችን፣ በማስቀደም ወይም በማስከተል፣ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን በማጥበቅ ወይም ባለማጥበቅ፣ እንዲሁም ከተለያዩ ረዳት ግሶች ጋር በመጣመር ቅርፃቸውን ሊለዋውጡ ይችላሉ። ዝርዝሩን በዚህ ንዑስ ክፍል እንመለከታለን። ከዚያ በፊት ግን አንድ ነገር ማንሳት አለብን። ይኸውም ግሶች የ(ሀ) እና የ(ለ) ክፍል ተብለው በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸውን ነው። የ(ሀ) ክፍል የሚባሉት ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን በቀዳማይ አንቀፅ ብቻ የሚያጠብቁ ሲሆኑ፣ የ(ለ) ክፍል የሚባሉት ይህንኑ ተናባቢ ድምፅ በማንኛውም አንቀፅ የሚያጠብቁ ናቸው። ለምሳሌ ሰረቀ ብለን ይሰርቃል ስንል፣ [ር] በመጀመሪያው ላይ ሲጠብቅ፣ በሁለተኛው ላይ አይጠብቅም። ፈለገ ብለን ይፈልጋል ስንል ግን [ል] በሁለቱም ላይ ይጠብቃል። ከዚህም የተነሳ እንደ ሰረቀ ያሉትን የ(ሀ)፣ እንደ ፈለገ ያሉትን ደግሞ የ(ለ) ክፍል ግሶች ብለን እንለያቸዋለን[6]። የተናባቢው መጥበቅ ወይም አለመጥበቅ የየግሱን የአንቀፅ አይነት ይወስናል። ይህን ወደ ሁዋላ እናየዋለን።

---

[6] ሶስተኛ የግስ ክፍል እንዳለ አንዳንድ ምሁራን ይገልፃሉ። ይህም የባረከ አይነት ግሶችን የሚይዝ ነው። መሰረቱም የተናባቢ ጥብቀት ሳይሆን፣ የአናባቢ አይነት ነው። ይኸውም የሌሎች ግሶች የመጀመሪያ አናባቢ /ኧ/ ሲሆን፣ የዚህ ክፍል ግሶች የመጀመሪያ አናባቢ /አ/ መሆኑና እንደ (ለ) ክፍል ግሶች፣ በካልዓይ አንቅፅ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን ማጥበቃቸው ነው። ይሁን እንጅ፣ ጥብቀቱ በሌሎቹ ቅርፆች የሚታይ ሳይሆን፣ በዚሁ አንቀፅ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

| | |
|---|---|
| /ፍኧልልኧገ-/ | /ብኣርርኧክ-/ |
| /ይ-ፍኧልል-ግ/ | /-ይ-ብኣርር-ክ/ |
| /ፍኧልል-ግ/ | /ብኣርክ/ |
| /ምኧ-ፍኧልልኧግ/ | /ምኧብኣርኧክ/ |

ርባታ

በሚለው ግስ አምድና <u>ሰብራት</u> በሚለው ስም አማካኝነት ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት::

| መደብ | ካልዓይ | ቀዳማይ | | ስም | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | እ-ሰብር | ሰበር-ኩ[7] | | ሰብራት-የ | |
| 2ኛ ተ | ት-ሰብር | ሰበር-ሀ | | ሰብራት-ሀ | |
| እ | ት-ሰብር-ኢ | ሰበር-ሽ | < /ሰበር-ሀ-ኢ/ | ሰብራት-ሽ | < /ሰብራት-ሀ-ኢ/ |
| 3ኛ ተ | ይ-ሰብር | ሰበር-ኧ | | ሰብራት-ኡ | |
| እ | ት-ሰብር | ሰበር-ኧች | </ሰበር-ኧት-ኢ/ | ሰብራት-ዋ | < /ሰብራት- ኡ-ኢ/ |
| ብ | እ-ን-ሰብር | ሰበር-ን | | ሰብራት-አች[8]-ን | |
| | ት-ሰብር-ኡ | ሰበር-አችሁ | | ሰብራት-አች-ሁ | </ሰብራት-አች-ሀ-ኡ/ |
| | ይ-ሰብር-ኡ | ሰበር-ኡ | | ሰብራት-አቸ-ው | /ሰብራት-አች-ኧ-ኡ/ |

4 የመደብ፣ የቁጥርና የፆታ ሰንጠረዥ

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው፣ በካልዓይ አንቀፅ /እ-/፣ /ት-/ እና /ይ-/ እንደ ቅደም-ተከተላቸው የአንደኛ፣ የሁለተኛና የሶስተኛ መደብ ምዕላዶች ናቸው:: /-ኢ/ የአንስታይ ፆታ ምዕላድ ስትሆን፣ አገባብዋም አምዱን ተከትላ ነው:: /-ን/ የአንደኛ መደብ፣ /-ኡ/ የሁለተኛና የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ምዕላዶች ናቸው:: መደብ፣ ቁጥርና ፆታ በተለያዩ ምዕላዶች እንደተገለፁ መረዳት ይቻላል:: በቀዳማይ አንቀፅ ደግሞ እነዚሁ የመደብ ምዕላዶች /-ኩ/፣ /-ሀ/ እና /-ኧ/ በሚሉ ቅርፆች በአምዱ መድረሻ ላይ ይታያሉ:: የፆታና የቁጥር ምዕላዶቹ በተናጠል ሳይሆን ከመደብ አመልካቾቹ ጋር እየተዋሀዱ ገብተዋል:: በስሙ ላይ ደግሞ የመደብ ምዕላዶቹ /-የ/፣ /-ሀ/ እና /-ኡ/ ሆነው ይታያሉ::

በግሶቹ ላይ የሚታዩት የመደብ፣ የቁጥርና የፆታ ምዕላዶች በአንድነት የባለቤት አፀፋ ይባላሉ:: በአረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት የሆነን ስም የሚያመለክቱ ወይም የሚተኩ ምዕላዶች ናቸው:: እነሱ በግሱ ላይ ስለሚታዩ፣ ስሙ በግሀድ ላይከሰት ይችላል::

አንድ ስም የአረፍተ ነገር ባለቤት መሆኑ የሚታወቀው በሁለት መንገድ ነው:: አንደኛው፣ በአረፍተ ነገር ውስጥ በሚገኝበት ቦታ ሲሆን፣ ሁለተኛው በግሱ ላይ በሚታየው የአፀፋ ምዕላድ አማካኝነት ነው:: በስሙ ላይ የሚታዩት አፀፋዎች የሚያመለክቱት፣ ስሙ የሚጠቁመው ነገር የማን መሆኑን ስለሆነ፣ በዚሁ መሰረት አገናዛቢ አፀፋ እንደሚባሉ ቀደም ሲል ገልፀናል::

---

[7] በቀዳማይ አንቀፅ የአንደኛ መደብ ምዕላድ ቅርፅ /-ሁ/፣ የሁለተኛ መደብ ደግሞ /-ህ/ ሆኖ ሊከሰት ይችላል:: ይህም የሚሆነው አምዱ በአናባቢ የሚጨርስ ሲሆን ነው::

[8] /-አችች-/ በአገናዛቢ ስሞች ላይ የሚገኘው የብዙ ቁጥር ምዕላድ ነው:: በግሶች ላይ የሚገኝበት ምክንያት፣ የቀዳማይ አንቀፅ ግሶች ከስም የመጡ ስለሆነና፣ የስሙ የብዙ ቁጥር ምዕላድም አብሮ በመምጣቱ ነው፣ የሚል ነው:: ዝርዝሩን ከሀድሰን (1981) ይመልከቱ::

ርባታ

ከላይ እንደሚታየው፣ መደቦች ነጠላ ወይም ብዙ ተብለው በቁጥር፣ እንዲሁም ተባዕታይ ወይም አንስታይ ተብለው በፆታ ይለያሉ፡፡ ይህን ቀደም ሲል በስሞች ርባታ ላይም አይተነዋል፡፡ አሁንም በግሶች ላይ እያየነው ነው፡፡ ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው፣ የአነስታይ ፆታ ምዕላድዋ /-ኢ/ ስትሆን፣ የሶስተኛ መደብ የአንስታይ ምዕላድ ደግሞ /-ት/ ነች፡፡ አሰዋም የምትገኘው በካልዓይ አንቀፅ አምድ መነሻ ላይ እና በቀዳማይ አንቀፅ አመድ መድረሻ ላይ ነው፡፡ በዚህ አምድ ከፆታ ምዕላድዋ ከ/-ኢ/ ቀድማ ትገኛለች፡፡ ሁለት የሶስተኛ መደብ ምዕላዶች አሉ ማለት ነው፡፡ አንደኛው /ይ-/ን እና /-ኧ-/ን ይዞአል፡፡ የመጀመሪያው በካልዓይ፣ ሁለተኛው በቀዳማይ አንቀፅ ይገኛል፡፡ ሁለተኛው /-ት-/ን ብቻ ይዞአል፡፡ እሰዋም በሁሉቱም አንቀፆች ትገባለች፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

| ካልዓይ | ቀዳማይ | | |
|---|---|---|---|
| /ይ-ስኧብር-/ | /ስኧብብኧር-ኧ/ | | 5 |
| /ት-ስኧብር-/ | /ስኧብብኧር-ኧ[9]-ት-ኢ/ | ሰበረች | |

በቀዳማይ አንቀፅ፣ የግሱን አምድ ተከትላ ለትመጣ፣ /-ት-/ በ/-ኢ/ ምክንያት ወደ ላንቃዊነት ትለወጥና [ች] ትሆናለች::

እነዚህ ባለፈው ክፍል ለለ ስሞች ርባታ ለንወያይ ያየናቸው የፆታ ምዕላዶች ናቸው፡፡ በዚያ ላይ፣ ማንኛውም ስም ተባዕታይ ወይም እንስታይ እንደሆነ ገልፀን፣ የወልና የግዑዝ ፆታ የሚባሉ ክፍሎች እንደሌሉ ጠቁመን ነበር፡፡ በዚህ በግሱ ርባታ ውስጥ የምናየው ሁኔታም ይህን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በግሱ ውስጥ የምትገኘው የአንስታይ ፆታ ምዕላድ /-ኢ/ ብቻ ነች[10]፡፡ የወልና የግዑዝ የሚባሉ የፆታ ክፍሎች ቢኖሩ ኖሮ፣ እንደ አንስታይ ፆታዋ ምዕላድ በተለያየ ቅርፅ በግሱ ርባታ ላይም መታየት ነበረባቸው፡፡

መደብ አመልካች ምዕላዶች ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የሚታዩት ብቻ አይደሉም፡፡ እነዚህ ባለቤት ወይም ባለገንዘብ የሆነን ስም መደብ የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከነዚህ ሌላ ተሳቢ የሆነን ስም መደብ የሚያመለክቱ ምዕላዶችም አሉ፡፡ እነዚህ ግን በሁሉም ግሶች ላይ ሳይሆን፣ ሳቢ በሚባሉት ላይ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡ ሳቢ ግሶች የሚባሉት ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ ጋር የሚቀናጁ ናቸው፡፡ አቀነጃጀቱን በሚቀጥለው ክፍል እናየዋለን፡፡ የአፀፋዎቹን አይነት ግን አሁንም ሰበረ በሚለው ሳቢ ግስ አማካኝነት እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

---

[9] ይህ አናባቢ /-ኧ-/ በስነ-ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት ምክንያት የገባ አናባቢ ድምፅ ነው፡፡
[10] ይህን የምንለው የሶስተኛ መደብ አንስታይ ፆታ ምዕላድ የሆነችውን /-አ/ ሳንዘነጋ ነው፡፡

ርባታ

| መደብ | ነጠላ | | ብዙ | |
|---|---|---|---|---|
| 1ኛ | ሰበር-ኧ-ኝ | | ሰበር-ኧ-ን | |
| 2ኛ ተ | ሰበር-ኧ-ሀ | | ሰበር-ኧ-ኣችሁ | </ሰበር-ኧ-ኣችች-ሁ-ኡ/ |
| አ | ሰበር-ኧ-ሽ | </ሰበር-ኧ-ሁ-ኢ/ | | |
| 3ኛ ተ | ሰበር-ኧ-ው | | ሰበር-ኧ-ኣችሁ | </ሰበር-ኧ-ኣችች-ኡ/ |
| አ | ሰበር-ኧ-ኣት | | | |

6. የተሳቢ ምዕላድ ሰንጠረዥ

ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው፣ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚታየው ምዕላድ /-ኧ/ ሲሆን፣ እሱም ከፍ ሲል ያየነው የሰስተኛ መደብ የባለቤት አፀፋ ነው፡፡ ከእሱ ቀጥሎ የሚገኙት የተሳቢ አፀፋዎች ናቸው፡፡ ከአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥርና ከሰስተኛ መደብ በስተቀር፣ የሌሎቹ አፀፋዎች ቅርፅ ከባለቤት አፀፋ ምዕላዶች ጋር አንድ አይነት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ የአንደኛ መደብ የባለቤት አፀፋ የብዙ ቁጥር /-ን/ ሲሆን፣ የተሳቢውም እንደዚሁ /-ን/ ነው፡፡

ከዚህ ላይ መረዳት ያለብን አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ይኸውም የምዕላዶቹን ቅደም-ተከተላዊ አገባብ የሚመለከት ነው፡፡ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚገኘው ሁል ጊዜም የባለቤት አፀፋ ሲሆን፣ ከእሱ ቀጥሎ የሚመጣው የተሳቢው አፀፋ ነው፡፡ የባለቤቱም ሆነ የተሳቢው አፀፋ የመደብና የቁጥር ወይም የፆታ ምዕላድ ውሁድ ነው፡፡ ምዕላዶቹ ከመዋሀዳቸው በፊት የሚገኙበት ቅደም-ተከተላዊ ስርዓትም መደብ አመልካቹ ቀድሞ፣ ቁጥር ወይም ፆታ አመልካቹ እሱን ተከትሎ የሚገኝበት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ /-ሽ/ የሚለው የሁለተኛ መደብ አንስታይ ፆታ ምዕላድ፣ የመደብ አመልካቹ /-ሀ/ እና የአንስታይ ፆታ አመልካችዋ /-ኢ/ ውሁድ እንደሆነ፣ ከፍ ሲል ተገልፆአል፡፡ የእነዚህ ምዕላዶች ቅደም-ተከተላዊ አቀማመጥም /-ሀ-ኢ/ ሲሆን፣ ወደ [-ሽ] የሚለወጡት በለነ-ድምፀ-ልሳናዊ ሂደት ነው፡፡ ሂደቱ ታሪካዊ አመጣጥ ያለው ሊሆን ይችላል፡፡ ግን ወቅታዊነትም አለው፡፡ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ ፆታ አመልካችዋ /-ኢ/ በየግሱ የትዕዛዝ እንቀፅ አምድ መድረሻ ላይ ብቻዋን ትገኛለች፡፡ ይህም ሰበሪ (/ሰ - ብኧር-ኢ/ ) ስንል ነው፡፡

እስካሁን ያየናቸው ስማዊ የተሳቢ አፀፋዎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ የሚያመለክቱት ተሳቢ የሆነ ስማዊ ሀረግን ነው፡፡ ከነዚህ ሌላ መስተዋድዳዊ አፀፋዎች የሚባሉ አሉ፡፡ እነዚህ የሚያመለክቱት የተለያየ ተውሳከ ግሳዊ ተግባር ያላቸውን መስተዋድዳዊ ሀረጎች ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ [በአዲሱ ብዕር] ደብዳቤ ፃፍ-ኧ-በት 7
(ለ) ካሳ [ገነትን] ገንዘብ ወስድ-ኧ-ባት </ብ-አት/

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ ከግሱ አምድ ቀጥሎ የሚገኘው /ኧ/፣ የባለቤቱ አፀፋ ነው፡፡ ከእሱ ቀጥሎ የሚገኘው /-በት/ የሚለው የመስተዋድድ ሀረግ አፀፋ

ርባታ

አፀፋ ብቻ የመያዝ ችሎታ እንዳለው ያሳያል:: የባለቤቱ አፀፋ ምን ጊዜም አይቀሬ ነው:: የተሳቢ አፀፋዎች ግን ሲቀሩ ይችላሉ:: በጥቅሉ የአማርኛ ግስ ቅርፅ የሚከተለው ይመስላል ብሎ መቁዋጨት ይቻላል::

(ሀ) አምድ-የባለቤት-{የተሳቢ፣ መስተዋድድ} አፀፋ 10

ምሳሌ፣ ሰበር-ኧ-ሽ < /ሀ-ኢ/

ሰበር-ኧ-ብኝ

(ለ) የባለቤት አፀፋ-አምድ-{የተሳቢ፣ መስተዋድድ} አፀፋ

ምሳሌ፣ ይ-ሰብር-ሽ- </ሀ-ኢ/

ይ-ሰብር-ብኝ-

የመጀመሪያው የቀዳማይ፣ ሁለተኛው የካልዓይ አንቀፅን የግስ ስርዓት ይከተላል:: በሁለቱም አንቀፆች መደብና ፆታ ወይም መደብና ቁጥር አመልካች ምዕላዶች አንድም ተለያይተው አለያም ተዋህደው ሊከሰቱ ይችላሉ:: ተዋህደው የሚከሰቱት አምዱን ተከትለው ሲመጡ ነው:: ይህም በቀዳማይና በጨራሽ አንቀፅ ነው:: ስለ አንቀፅ ከዚህ ቀጥለን እንወያያለን::

## *አንቀፅ*

አንቀፅ በአንድ ግስ የሚገለፅ ድርጊት ወይም <u>ሁነት</u> መታቀዱን፣ መጀመሩን፣ መቀጠሉን፣ በመጨረሻም ተፈፅሞ ያለቀ ወይም ያላለቀ መሆኑን የሚያሳይ ሰዋሰዋዊ ባህሪ ነው:: የተፈፀመ ድርጊትን የሚገልፅ ግስ የቀዳማይ አንቀፅ ግስ፣ ያላለቀ ድርጊትን የሚገልፅ የካልዓይ አንቀፅ ግስ ይባላል:: የሁለቱ አንቀፆች ቅርፅም የተለያየ ነው:: ልዩነቱን ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት::

| <u>ቀዳማይ</u> | | <u>ካልዓይ</u> | | |
|---|---|---|---|---|
| /ሰኧብብኧር-/ | ሰበር- | /-ሰኧብር-/ | -ሰብር- | 1 |
| /ግኧድድኧል-/ | ገደል- | /-ግኧድል-/ | -ገድል- | |
| /ፍኧልልኧግ-/ | ፈለግ- | /-ፍኧልልግ-/ | -ፈልግ- | |
| /ዝኧምምኧር-/ | ዘመር- | /-ዝኧምምር-/ | -ዘምር- | |

እነዚህ የመደብ፣ የቁጥር ወይም የፆታ ምዕላድ የቀራቸው አይነተኛ የአንቀፅ አምዶች ናቸው:: ቅርፃቸውም እንደሚከተለው ነው::

ቀዳማይ : / ተ$_1$ኧተ$_2$ተ$_2$ኧተ$_3$-/ 2

ካልዓይ : /-ተ$_1$ኧተ$_2$(ተ$_2$)ኧተ$_3$ -/

የቀዳማይ አንቀፅ አምድ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢውን ያጠብቃል:: ከመነሻው ተናባቢ በሁዋላና ከመድረሻው ተናባቢ በፊት /ኧ/ የሚለውን አናባቢ ያስገባል:: የካልዓይ አንቀፅ አምድ ደግሞ ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ ብቻ ይህንኑ አናባቢ

ያስገባል፡፡ ቅድመ-መድረሻ ተናባቢውን ሊያጠብቅ ወይም ላያጠብቅ ይችላል፡፡ ተናባቢው (ተ2) በቅንፍ ውስጥ የተቀመጠውም ይህንኑ ሁኔታ ለማሳየት ነው፡፡ እነዚህ ሁለት እንቀፆች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ከእነሱ ላይ የተለያዩ ቅጣዮችን በመጨመር ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተለያዩ የድርጊትና የሁነት አይነቶችን የሚገልፁ እንቀፆች መፍጥር ይቻላል፡፡ ከነዚህ መካከል አራቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

(ሀ) አቃጅ እንቀፅ 3
(ለ) ወጣኝ እንቀፅ
(ሐ) ቀጣይ እንቀፅ
(ለ) ጨራሽ እንቀፅ

## *አቃጅ እንቀፅ*

አቃጅ እንቀፅ የሚባለው አንድ ድርጊት ይፈፀም ዘንድ መታቀዱን የሚያመለክት ሲሆን፣ ልዩ ምለክቱ /ል-/ የሚል ምዕላድ ነው፡፡ የሚመሰረተው በካልዓይ እንቀፅ ላይ ነው፡፡ የሚከተለው የዚህ እንቀፅ ምሳሌ ነው፡፡

ካሳ እንጨት <u>ል-ይ-ፈልጥ</u> ነው = <u>ሊፈልጥ</u> 4

ምሳሌው፣ ካሳ እንጨት ለመፍለጥ ማቀዱን ያመለክታል፡፡ ይህን የምታመለክተው ምዕላድ የባለቤት አፀፋ የሆነችውን /-ይ/ ቀድማ በመነሻ ላይ ገብታለች፡፡

## *ወጣኝ እንቀፅ*

የታቀደ ነገር ሳይጀመር አይቀርም፣ ይዋል ይደር እንጅ፡፡ ሲጀመር፣ የድርጊቱ ገላጭ ከሆነው አምድ ቀጥሎ <u>ጀመር</u> የሚል ምዕላድ ይገባል፡፡ ይህም <u>ጀመረ</u> ከሚለው ግስ ጋር ተዛምዶ ይኑረው እንጅ፣ የተለየ ተግባር ያለው አሀድ ነው፡፡ ተግባሩ ለወጣኙ እንቀፅ ረዳት መሆን ነው፡፡ ዋናው አምድ የተመሰረተው ከአይነተኛው የካልዓይ እንቀፅ አምድ ላይ ነው፡፡ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡

ከሳ እንጨት <u>ይ-ፈልጥ ጀመር</u> 5

ምሳሌው ድርጊቱ መጀመሩን ብቻ ያመለክታል፡፡ ከዚያ በሁዋላ ስላለው ሁኔታ የሚነግረን ነገር የለም፡፡ የተጀመረው ድርጊት ሊቀጥል ወይም ሊቋረጥ ይችላል፡፡ የሚቀጥል ከሆነ የተለየ መግለጫ ይኖረዋል፡፡ ይህን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ቀጣይ አንቀፅ

ከስሙ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ቀጣይ አንቀፅ አንድ የተጀመረ ድርጊት ሳይቋረጥ መቀጠሉን ያመለክታል፡፡ ልዩ ምልክቱ /እይይኸ-/ የሚል ምዕላድ ነው፡፡ መሰረቱ ደግሞ የቀዳማይ አንቀፅ አምድ ነው፡፡ የሚከተለው የዚህ መሳሌ ነው፡፡

ካሳ እንጨት እየ-ፈለጠ ነው 6

አንቀፁ እየፈለጠ የሚለው ነው፡፡ እሱን ተከትሎ የገባው ነው የሚለው ረዳት ግስ ነው፡፡ ተግባሩን በሚቀጥለው ንዑስ ክፍል እናየዋለን፡፡

ድርጊቱ ተቋርጦ ወዲያውኑ ወይም ቆይቶ፣ እንደገና ሊጀምርና ሳይቋረጥ ለተወሰነ ጊዜ ሊቀጥል፣ እንደገናም ሊቋረጥና ደግሞ ሊቀጥል ይችላል፡፡ እንደዚህ ያለ ድርጊት ደጋጋሚ ይባላል፡፡ የሚደጋገመውም አንድም በድርጊቱ ፈፃሚ ሰው ባህሪ ምክንያት ወይም በድርጊቱ ልዩ ባህሪ ሊሆን የችላል፡፡ ለምሳሌ፣ አንዳንድ የመጠጥ ሱሰኞች በየምሽቱ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው ቤት የሚያደርጉት የመመላለስ ድርጊት የዚህ አይነት ነው፡፡ ድርጊቱ ደጋጋሚ መሆኑን ለመግለፅ የግሱ አምድ ራሱን ይደጋግማል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

ካሳ እዚህ ቤት ሁል ጊዜ ይ-መላለስ-ኣል 7

ድርጊቱ የአንድ ጊዜ ብቻ ሲሆን፣ አንቀፁ ይመለስ-ኣል የሚል የሆናል፡፡

አንዳንዱ ድርጊት በባህሪው ሳያቋርጥ ለተወሰነ ጊዜ የሚቀጥል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሙቀጫ ከከፍተኛ ቦታ ወደ ዝቅተኛ ቦታ የሚያደርገው የመንከባለል እንቅስቃሴ የዚህ አይነት ነው፡፡ ደልዳላ ቦታ ወይም ደጋፊ እስኪያገኝ ድረስ ይቀጥላል፡፡ ዳገት የመውጣት ተግባርም እንደዚሁ ጊዜ ፈጅ ነው፡፡ "ወጣ ወጣና እንደ ሸንበቆ፣ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ" እንደሚባለው አይነት ነው፡፡ ሁለቱም አምዶች ደጋጋሚ ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቀጣይ ድርጊቶችን እንደ ዱብ አለ፣ ከሚሉት ቅፅበተቀዊ ድርጊቶች ጋር በንፅፅር ማየቱ፣ ድርጊቶች አንድ ወጥ እንዳልሆኑ ለመረዳት ያስችላል፡፡ አንቀፅ የምንለውም በመሰረቱ ይህን የድርጊቶችንና የሁነቶችን ውስጣዊ ሁኔታ የሚመለከተውን የግስ ባህሪ ነው፡፡

## ጨራሽ አንቀፅ

ወጣኝ አንቀፅ ድርጊት መጀመሩን እንደሚያመለክት ሁሉ፣ ጨራሽ አንቀፅም አንድ ድርጊት ሙሉ በሙሉ ተፈፅሞ ማለቁን ያመለክታል፡፡ አትኩሮቱ ከፍፃሚው ላይ ነው፡፡ ይህን የሚገልፀው አንቀፅ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ በዝ አንቀፅ የሚባለው ነው፡፡ በዝ የሚባልበት ምክንያት ካልዓይ ወይም ቀዳማይ አንቀፅ ካልተከተለው በስተቀር በራሱ ብቻ ጊዜን ለመግለፅ ባለመቻሉ ነው፡፡ ይህን ከሚከተለው መሳሌ መረዳት የቻላል፡፡

ርባታ

ካሳ እንጨት ፈልጥ-ኦ ... 8

ይህን የሚሰማ ሰው፣ በርግጥ ፈለጣው ማለቁን ይረዳል፤ ግን ከዚያስ? የሚል ጥያቄ መጠየቁ አይቀርም። ጥያቄው እንዳይነሳ፣ <u>ሄደ</u> ወይም <u>ይሄዳል</u> የሚል የቀዳማይ ወይም የካልዓይ አንቀፅ ግስ እንዲከተለው ማድረግ ያስፈልጋል።

የጨራሽ አንቀፅ መሰረት ካልዓይ አንቀፅ ነው። በዚህም ከቀዳማይ አንቀፅ ላይ ከሚመሰረተው፣ ከቀጣይ አንቀፅ ይለያል። በተጨማሪም አምዱን ተከትሎ የሚገባው የባለቤት አፀፋ አገናዘቢ ነው። ስለዚህም ፈለጥ-<u>ኧ</u> ብሎ፣ ፈልጥ-<u>ኦ</u> ይላል።

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው አንቀፆች የተለያዩ የድርጊት ባህሪያትን ያመለክታሉ። ድርጊት መታቀዱን፣ መጀመሩን፣ መቀጠሉን፣ መቋዋጩቱንና ከዚያም መፈፀሙን ያመለክታሉ እንጅ መቸነቱን እያመለከቱም። ይህ የሚገለፀው <u>ጊዜ</u> በሚባለው ሌላ ሰዋስዋዊ የግስ ባህሪ ነው። እሱን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

## ጊዜ

ከፍ ሲል ድርጊቶች በጥቅሉ የተፈፀሙ ወይም ያልተፈፀሙ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ እንደሚችሉ ገልፀናል። ግን እያንዳንዱ ድርጊት የሚታቀድ፣ የሚወጠን፣ የሚቀጥል፣ እናም የሚቋዋጭ ሊሆን እንደሚችልና ይህም ሁኔታ የሚገለፀው በተለያየ የግስ አምድና በተለያዩ ቅጣዮች እንደሆነ ተጠቅሶአል። የተፈፀሙትም ሆኑ ያልተፈፀሙት ድርጊቶች በጊዜ ይወሰናሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ድርጊት የተፈፀመው የዛሬ አመት ወይም ከዚያ በፊት፤ ወይም ደግሞ የዚያን ያህል ሳይርቅ ከአንድ ደቂቃ በፊት ሊሆን ይችላል። ገና ያልተፈፀመ ድርጊትም ፍፃሜ የሚያገኘው ከቅርብ ወይም ከረዥም ጊዜ በሁዋላ ሊሆን ይችላል። በፊትና በሁዋላ የምንለው ስለ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ ተነስተን ነው። ያ ጊዜ <u>አሁን</u>፣ ከአሁን <u>በፊት</u> ወይም በ<u>ሁዋላ</u> ሊሆን ይችላል። ከዚያ ጊዜ በፊት የተፈፀመ ድርጊት የሀላፊ ጊዜ ሲባል፤ ከዚያ ጊዜ በሁዋላ የተፈፀመ፣ የትንቢት ጊዜ ድርጊት ይባላል። እነዚህ ሁለት የጊዜ አይነቶች የሚገለፁት ቀደም ሲል በተመለከትናቸው የተለያዩ የአንቀፅ አይነቶች መሰረትነትና በተለያዩ ረዳት ግሶች እንዲሁም የጊዜ ተውሳከ ግሶች ነው። አንቀፆቹ ድርጊቶቹን ሲገልፁ፣ ረዳት ግሶቹና ተውሳከ ግሶቹ ጊዜውን ያመለክታሉ። ሁኔታውን እያንዳንዱን የጊዜ አይነት እየጠቀስን እንደሚከተለው እናሳያለን[12]።

---

[12] በዚህ ጉዳይ ላይ ለፋ ያለ ትንታኔ ለማግኘት ጎልደንበርግ (1964)ን ይመልከቱ።

## የሀላፊ ጊዜ

ባለፈ ጊዜ የተፈፀመ ድርጊትን ይገልፃል። የቀሀ፣ የቅርብ፣ እንዲሁም የሩቅ ሀላፊ ተብሎ በሶስት ንዑስ ክፍሎች ይከፈላል። የመጀመሪያው በቀዳማይ አንቀፅ፣ ሌሎቹ በካልዓይ አንቀፅና በረዳት ግሶች አማካኝነት ይገለፃሉ።

## የቀሀ ሀላፊ

አንድ ድርጊት ባለፈ ጊዜ ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን ብቻ ያመለክታል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ አንበሳ ገደለ 1
(ለ) አሰቴር ስኒ ሰበረች

የምሳሌዎቹ ግሶች ቅርፅ የቀዳማይ አንቀፅ ነው። ግሶቹም የሚያመለክቱትም የድርጊቶቹን መፈፀም ብቻ ነው። ድርጊቶቹ የተፈፀሙበትን ጊዜ ለይተው አይጠቅሱም። ጊዜውን ለመወሰን እንደ ትናንት፣ ዛሬ፣ ወዘተ፣ ያሉ የጊዜ ተውሳከ ግሶችን መጠቀም ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን፣ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች የሚከተለውን ሊመስሉ ይችላሉ።

(ሀ) እኔ ትናንት አንበሳ ገደልኩ 2
(ለ) አሰቴር ዛሬ ስኒ ሰበረች
(መ) አሁን ስኒ ሰበረች

በዚህም ምክንያት በምሳሌ (1) እንደተጠቀሱት ያሉ አረፍተ ነገሮች አንቀፅ እንጅ በግሀድ የሚታይ የጊዜ ምዕላድ የላቸውም። <u>ገደልኩ</u> የሚለው አንቀፅ የሚገልፀው ድርጊትም በማንኛውም የሩቅም ሆነ የቅርብ ጊዜ የተፈፀመ ሊሆን ይችላል። የቀሀ የተባለበትም ምክንያት፣ ጊዜውን በውል ለማሳየት ባለመቻሉ ሊሆን ይችላል። አንቀፁ ባጠቃላይ ድርጊቱ ያለፈ መሆኑን እንጅ፣ መቼ እንደተፈፀመ ጊዜውን የሚያመለክት ረዳት ግስ የለውም።

## የቅርብ ሀላፊ

አንድ ድርጊት ሙሉ በሙሉ የተፈፀመ መሆኑንና፣ ከተፈፀመም ብዙ ጊዜ ያልቆየ፣ ስለዚህም ያልተረሳ መሆኑን ያመለክታል። ድርጊቱ የሚገለፀው በጨራሽ አንቀፅ አምድና /-አል/ በሚል ረዳት ግስ አማካኝነት ነው። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ካሳ አንበሳ ገድል-ኦ-አል (= ገድሎአል) 3

ርባታ

ሁሉም ያልተፈፀመ ድርጊትን ያመለክታሉ፡፡ ልዩነታቸው ድርጊቶቹ ወደፊት የሚፈፀሙበት ጊዜ፣ ንግግር ከምናደርግበት ጊዜ መራቅና መቅረብ ነው፡፡ ይህም የሚገለፀው በግሱ ቅርፅ ወይም በረዳት ግሱ ሳይሆን፣ በተውሳከ ግሶቹ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው በግሳዊ ቅርፁ ከትንቢት ጊዜ የተለየ፣ የአሁን የሚባል የጊዜ አይነት አለመኖሩን ነው፡፡

እስካሁን ያየነው በካልዓይ፣ በቀዳማይና በጨራሽ አንቀፆች የሚገለፁ ድርጊቶችንና /-አል/ እና ነበር በሚሉ ረዳት ግሶች አማካኝነት የሚገለፁ የጊዜ አይነቶችን ነው፡፡ አንቀፆቹ ያልተፈፀመ፣ የተፈፀመ እና የተጨረሰ ድርጊትን ሲያመለክቱ፣ ጊዜያቱ ድርጊቱ የተፈፀመበት ወይም ያልተፈፀመበት ወይም የተጨረሰበት ወቅት፣ ስለድርጊቱ ከምንነጋገርበት ጊዜ በፊት ወይም በሁዋላ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ከምንነጋገርበት ጊዜ በፊት ያለውን ሩቅ ጊዜ፣ ነበር በሚለው፣ ለምንነጋገርበት ጊዜ ቅርብ፣ ወይም ከእሱ ጋር አንድ የሆነውን ጊዜ፣ /-አል/ በሚለው ረዳት ግስ እንገልፃለን፡፡

የአንድ ድርጊት አፈፃፀም ግን ከዚህ ላይ እንደገለፅነው በሶስት ብቻ ሊወሰን የሚችል አይደለም፡፡ በመፈፀም ላይ ያለና ያላለቀ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህም የሚፈፀምበት ጊዜ እንደዚሁ ቀጣይ ሊሆን ይችላል፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጊዜው ብቻ ተለይቶ የማያቋርጥ ጊዜ ይባላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ቀጣዩ ጊዜው ብቻውን ሊሆን አይችልም፣ ቀጣዩ ድርጊቱ ነው፣ ሊባል ይችላል፡፡ ጊዜ ያለድርጊት ብቻውን አይታሰብም ማለት ይቻላል፡፡

አንድ ድርጊት ሳይቋረጥ በመፈፀም ላይ የሚገኘው አሁን ወይም ከአሁን በፊት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚሁ መሰረት የማያቋርጥ የአሁን ወይም የሀላፊ ጊዜ ድርጊት ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ የድርጊቱን ቀጣይነት ለማመልከት፣ /እይይኧ-/ የሚል ምዕላድ በአምዱ መነሻ ላይ ይገኛል፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

ካሳ እየ-እነበበ... 10

ይህ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ጊዜ የለውም፡፡ እየ-እነበበ የሚለው የቀጣይ አንቀፅ ግስ ነው፡፡ የሚያመለክተውም፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ አንቀፅን ብቻ ነው፡፡ ጊዜን አያሳይም፡፡ ይህን ለማሳየት ረዳት ግስ ያስፈልገዋል፡፡ የድርጊቱ ቀጣይነት ስለ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ በፊት ከሆነ፣ ነበር የሚል ረዳት ግስ ጋር ይገባል፡፡ ድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት ጊዜ ጋር አንድ ከሆነ፣ ነው ከሚለው ጋር ይገባል፡፡ የድርጊቱ ቀጣይነት ወደፊት የሚታይ ከሆነ፣ ከጊዜ ተውሳከ ግሰ ጋር ይገባል፡፡ ይህን ሲያደርግ፣ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር ግስ የሚከተሉትን ይመስላል፡፡

(ሀ) ካሳ መፅሀፍ እየ-እነበበ ነው (የአሁን) 11
(ለ) ካሳ መፅሀፍ እየ-እነበበ ነበር (የሀላፊ)
(መ) ካሳ [ነገ መፅሀፍ እየ-እነበበ] ይጠብቅሀል... (የትንቢት)

ምሳሌ (መ) ቀጣይ አንቀፅንና የትንቢት ጊዜን ያመለክታል፡፡

የሚለውን መዋቅር ብንመለከት፣ እንደ የሚለው መስተዋድድ የንጋት ኮከብ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣ ስማዊ ሀረጉ ከሌላ ካልተጠቀሰ ነገር ጋር የሚነፃፀር መሆኑን የሚገልፅ ቃል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለስማዊ ሀረጉ የሚያበረክተው የትርጉም አስተዋፅዖ የለውም፡፡ የሀረጉ ትርጉም የተመሰረተው ንጋት እና ኮከብ በሚሉት የይዘት ቃላት ላይ ብቻ ነው፡፡ እንደ የሚለው መስተዋድድ ንፅፅርን የማሳየት ተግባር ብቻ ያለው የግብር ቃል ነው፡፡ ስለዚህም ለአዳዲስ ቃላት መሰረት ወይም ዘር ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት በዚህ ክፍል የምናተኩረው እንደ ኮከብ እና ንጋት ባሉ የይዘት ቃላት ላይ ነው፡፡

ትኩረታችን በሁለት ወገን ነው፡፡ በአንድ በኩል የምናውቃቸውን፣ ማለትም የነባር ቃላትን፣ ውስጣዊ አቀነባበር ማየት ሲሆን፣ በሌላ በኩል የአቀነባበሩ ስርዓት የማናውቃቸውን አዳዲስ ቃላት እንዴት እንደሚፈጥር መረዳት ነው፡፡ ባለፈው ንዑስ ክፍል፣ ገና ጥቅም ላይ ያልዋሉ ፅንሰ-ቃላት በእያንዳንዱ ቋንቋዋ ተናጋሪ ልሳነ ተፈጥሮ ውስጥ እንዳሉ ገልፀን ነበር፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቃላትን ለእብነት ያህል በዚህ ክፍል በመጠኑም ቢሆን ለማየት እንሞክራለን፡፡ በስሞች እንጀምራለን፡፡

## ውልድ ስሞች

ሁለት አይነት ስሞች አሉ፡፡ አንደኛው እንደ ቤት፣ ሰው፣ ሴት፣ በግ፣ ልጅ፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን የያዘ ሲሆን፣ ሁለተኛው እንደ ሰውነት፣ ሴትነት፣ ልጅነት፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን የሚያካትት ነው፡፡ የመጀመሪያው አይነት ስሞች ከፎኒሞች የተመሰረቱ ነፃ ምዕላዶች ናቸው፡፡ ስለዚህም ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ምዕላዶች ይባላሉ፡፡ ለምሳሌ *ቤት* የሚለውን ቃል ብንመለከት፣ /ብ/፣ /ኤ/ እና /ት/ ከሚሉት ሁለት ተናባቢና ከአንድ አናባቢ ድምፅ የተፈጠረ ባለአንድ ቀለም ምዕላድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አፈጣጠሩ ባለፈው ክፍል ባየነው የቋንቋዋው የቀለም አወቃቀር ስርዓት መሰረት ሲሆን፣ ዝርዝሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

2



ሁለቱ ተናባቢ ድምፆች አናባቢውን ማዕከል አድርገው መዋቅሩን እንደፈጠሩ በግልፅ ይታያል፡፡ በስነ-ድምፅ ደረጃ መዋቅሩ ቀለማዊ ሲሆን፣ በስነ-ምዕላድ ደረጃ ምዕላዳዊ ነው፤ ትርጉም ስላለው፡፡

ይህ ምዕላድ ከሌላ ጥገኛ ከሆነ ምዕላድ ጋር በመዋቀር ቃል ሊፈጥር ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ /-ኧኘኘኣ/ የሚል ምዕላድ እንዲከተለው ብናደርግ፣ *ቤተኛ* የሚል ቃል ይሰጠናል፡፡ የሁለቱ አወቃቀርም እንደሚከተለው ነው፡፡



3

ሁለቱ ምዕላዶች ተዋቅረው *ቤተኛ* የሚል ቃል መስርተዋል፡፡ ይህ ቃል የሁለት ምዕላዶች ውጤት ስለሆነ፣ ስነ-ምዕላዳዊ ቃል ተብሎ፣ ከፍ ሲል ካየነው ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ምዕላድ ይለያል፡፡ በዚህም መሰረት ከፎኒሞች የሚዋቀሩትና፣ እንደ ቤት ያሉት ነባር፤ ከምዕላዶች የሚዋቀሩት እንደ ቤተኛ ያሉት ደግሞ ውልድ ስሞች ይባላሉ፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው ምዕላድ ከምዕላድ ወይም ከቃል ጋር እየተቀናጀ ቃላት የሚፈጥርበትን ስርዓት ነው፡፡ ወደ ዝርዝር የምስረታው ሂደት እንግባ፡፡

ውልድ ስሞች ከስም፣ ከቅፅል እና ከግስ ሊወለዱ ይችላሉ፡፡ ከነዚህ ክፍሎች እንዴት እንደሚወለዱ ከስም ከሚወለዱት በመጀመር ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን፡፡ ስሞች ለሌሎች ስሞች ወላጅ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹ ከፍ ሲል ነባር ስሞች ያልናቸው ናቸው፡፡ ከነሱ የሚወለዱ ስሞች የረቂቅ ስሞች ናቸው፡፡ በአይን የማይታይ ባህሪን ያመለክታሉ፡፡ ሁለት አይነት የረቂቅ ስሞች አሉ፡፡ የመጀመሪያው አይነት ከነባር ስሞች ላይ /-ነነኧት/[1] የሚል ምዕላድ ሲጨመር የሚወለዱ ስሞችን የያዘ ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን በሚከተለው ሰንጠረዥ እናሳያለን፡፡

---

[1] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሀይሉ (1967)ን ይመልከቱ፡፡ ለአቀራረብ እንዲቀል፣ በዚህ ክፍል የሚሰጡት ምሳሌዎች በሙሉ፣ ሁኔታ ካላስገደደ በስተቀር፣ በመደበኛው ስርዓተ ዕህፈት ይፃፋሉ፡፡ ቅጥይ ምዕላዶቹ ብቻ በፎኒማዊ አፃፃፍ በእዝባር ውስጥ ይፃፋሉ፡፡

| <u>ነባር ስም</u> | <u>ውልድ ስም</u> | | |
|---|---|---|---|
| ሰው | ሰው-ነት | ሰውነት | 4 |
| ልጅ | ልጅ-ነት | ልጅነት | |
| ሴት | ሴት-ነት | ሴትነት | |

የዚህ አይነት ስሞች ከስም ብቻ ሳይሆን፣ ከቅፅልም ሊወለዱ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ነው፡፡

| <u>ቅፅል</u> | <u>ስም</u> | | |
|---|---|---|---|
| ደግ | ደግ-ነት | ደግነት | 5 |
| ጥሩ | ጥሩ--ነት | ጥሩነት | |
| ብልህ | ብልህ-ነት | ብልህነት | |
| ቸር | ቸር-ነት | ቸርነት | |

የነዚህን ሁለት አይነት የረቂቅ ስሞች የአፈጣጠር ስርዓት እንደሚከተለው አጠቃሎ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ስርዓት 1፣

$$[\{ስም፣ቅፅል\}] + [–ነት] \longrightarrow [ስም]_{የረቂቅ}$$

ስርዓቱ፣ ከስም ወይም ከቅፅል ላይ /–ንንኧት/ የሚል ምዕላድ ሲጨምር፣ የረቂቅ ስም እንደሚፈጠር ያሳያል፡፡ ይህ አይነት ስም የሚመሰረተው በ/–ንንኧት/ አማካኝነት ስለሆነ፣ይህን ቅጣይ የረቂቅ ስም መስራች ምዕላድ እንለዋለን፡፡ ምዕላዱ በስሙ ወይም በቅፅሉ መድረሻ ላይ ተቀጥሎ ስለሚገባም ተከታይ ምዕላድ ይባላል፡፡ ይህን የአመሰራረት ስርዓት በመከተል ከማንኛውም ቅፅል ወይም ስም ላይ የረቂቅ ስም መመስረት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡ <u>ውብ</u> ከሚለው ቅፅል ላይ /-ንንኧት/ን ብንጨምር፡ <u>ውብነት</u> የሚል ስም እናገኛለን፡፡ ይህም <u>ውበት</u> ከሚለው በቅርፁ የተለየ ነው፡፡ ከውበት ጋር ተዛምዶ ላለው አዲስ ፅንሰ-ሀሳብ ስያሜ ሊሆን ይችላል፡፡ <u>የውብነትዋ</u> ደረጃ እስከምን ድረስ ነው ብንል? <u>የውበትዋ ደረጃ</u> እስከምን ድረስ ነው? ከሚለው ጋር አንድ አይመስልም፡፡

ሁለተኛው የረቂቅ ስሞች አይነት ከውልድ ስሞች፣ ከነፃ ወይም <u>*ዕስር*</u> ቅፅላዊ አምዶች ላይ / ̲ኧት/ የሚል ምዕላድ በመጨመር የሚፈጠሩ ስሞችን ያጠቃልላል፡፡ ወደ ዝርዝር ሁኔታው ከመግባታችን በፊት፣ ምናልባት <u>አምድ</u> የሚለውን ቃል ከዚህ ላይ መግለፅ ተገቢ ይሆናል፡፡ ቃሉን ቀደም ሲል በተደጋጋሚ የጠቀስነው ቢሆንም፣ ምንም አይነት ግላጼ አልሰጠነውም፡፡

ለመለየት አስቸጋሪ ነው፡፡ መለየት የማያስቸግረው እንደ ውፍረትና ግድፈት ያሉትን ውልድ ቃላት ክፍል ነው፡፡

ከላይ የሚታየው የተናባቢና የአናባቢ አቀነጃጀት እንደ ልብስ፣ ፍርድ፣ ምርት፣ ወዘተ፣ ያሉ ስሞችን አፈጣጠር የሚያካትት ስለሆነ፣ የስምና የቅፅል የጋራ ስርዓት ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ በዚህ አመለካከት መሰረት ከላይ በተራ ቁጥር (1) ያስቀመጥነውን ስርዓት እንደሚከተለው አድርገን ማሻሻል ይኖርብናል፡፡

ስርዓት 2፣

| | |
|---|---|
| [{ስም፣ ቅፅል}+[{–ነት፣–ኧት}] ⟶ | [ስም] የረቂቅ |

ስርዓቱ ከስም ወይም ከቅፅል ላይ /–ንነኧት/ ወይም /–ኧት/ የሚለውን ቅጣይ ምዕላድ በመጨመር አዳዲስ የረቂቅ ስሞችን መፍጠር ይቻላል፣ የሚል ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ይህን ህግ በመከተል እንደ ንድፈት፣ ንቅፈት፣ ንፍቀት፣ ፅንፈት፣ ንዋፈት፣ ግልፀት፣ ብግነት፣ ወዘተ፣ ያሉ አዳዲስ ስሞችን በመፍጠር ለአዳዲስ ስንፀ-ሀሳብ መግለጫ ማዋል ይቻላል፡፡ ስርዓቱ እንደ <u>ቅብጠት</u> ያለ ቃላትን ውስጣዊ አቀነጃጀት ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን፣ እንደ <u>ንፍቀት</u> ያሉና ገና በጥቅም ላይ ያልዋሉ ዕንስ-ቃላትንም አፈጣጠር ያሳያል፡፡

የረቂቅ ስሞች ረቂቅ ባህሪን ስለሚያመለክቱ የብዛት ምልክት የላቸውም፡፡ በዚህም አካላዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚያመለክቱት ተቆጣሪ ስሞች ይለያሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ልጅ ብሎ፣ ልጅ-ኦች ማለት ሲቻል፣ <u>ብልጠት</u> ብሎ <u>ብልጠት-ኦች</u> ማለት ግን አይቻልም፡፡ ብልጠት ሊቆጠር የሚችል የቁሳዊ ነገር ስም አይደለምና፡፡

ከረቂቅ ስሞች በተጨማሪ ሌሎች ስሞችንም ከነባር ስሞችና ቅፅሎች ላይ መመስረት ይቻላል፡፡ ስሞቹ የሚመሰረቱት ከአንዳንድ የወል ስሞችና የባህሪ ቅፅሎች ላይ /-ኦ/ የሚል ምዕላድ እንደሚከተለው በመጨመር ነው፡፡

| <u>ስም</u> | <u>ውልድ</u> | | 8 |
|---|---|---|---|
| ውሻ | ውሽ-ኦ | ውሾ | |
| ሌባ | ሌብ-ኦ | ሌቦ | |
| ንፍጥ | ንፍጥ-ኦ | ንፍጦ | |
| <u>ቅፅል</u> | <u>ስም</u> | | |
| ቂል | ቂል-ኦ | ቂሎ | |
| ሞኝ | ምኝ-ኦ | ሞኞ | |
| ብልጥ | ብልጥ-ኦ | ብልጦ | |

የአፈጣጠራቸው ስርዓት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

የተወሰኑ ቅፅሎችና ስሞች መሰረት፣ ተናባቢ ድምፆች ናቸው። የተናባቢዎቹ ቁጥር ከአንድ እስከ ስድስት እንደሚደርስ ሊቃውንት ይናገራሉ።

እያንዳንዱ ተናባቢ ድምፅ እግር ይባላል። ተናባቢዎቹ አንድ ላይ ሆነው የሚፈጥሩት ቅንጅት ስር ይባላል። ይህ ስር እንደ ተናባቢዎቹ ቁጥር ባለ ሁለት፣ ባለሶስት፣ ወዘተ፣ እግር እየተባለ ይለያል። ስሩ ብቻውን አጠቃላይ የሆነ ቅርፅና ትርጉም አለው። ስለዚህም ምዕላድ ነው። ለምሳሌ /ብ - ል- ጥ-/ የሚለውን ስር ብንወስድ፣ ከመብለጥ ጋር የተያያዘ አጠቃላይ የሆነ ትርጉም እንዳለው እንረዳለን። ቅርፁም እንደዚሁ ከተናባቢዎች ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ አሻሚ ነው። ምክንያቱም ከዚሁ ስር ላይ ቅፅልን፣ ግስን ወይም ስምን መፍጠር ስለሚቻል ነው። አሻሚነቱን ለማገድ፣ በስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ የተለያዩ አናባቢዎችን ማስገባት ያስፈልጋል። ይህን ስናደርግ፣ የሚፈጠረው ቅርፅ <u>አምድ</u> ይባላል። አምዱ የግስ፣ የቅፅል ወይም የስም ሊሆን ይችላል። በአቋዋሙም ነፃ ወይም ዕስር ሊሆን ይችላል። ከዚህ አምድ ላይ፣ ልዩ ልዩ ቅጣዮችን በመጨመር የተለያዩ ቃላትን መመስረት ይቻላል። የተመሰረቱትን ቃላት ክፍልም ማወቅ ይቻላል። የስሩን ክፍል ማወቅ ግን አይቻልም። የሁሉም እናት ስለሆነ ሁሉ-ገብ ነው። ይህ የአማርኛ ብቻ ሳይሆን የሴም ቋዋንቋዋዎች አጠቃላይ ባህሪ ነው።

ከላይ እንደተገለፀው፣ ውልድ ስሞች ከግስ ስር ወይም አምድ ላይ ሊፈጠሩ ይችላሉ። ከስሩ የሚፈጠሩት፣ በስሩ ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ አናባቢዎችን በመጨመር ሲሆን፣ ከአምዱ ላይ የሚፈጠሩት ቅጣዮችን፣ ማለትም መስራች ምዕላዶችን፣ በማስከተል፣ በማስቀደም ወይም የየስሩን ተናባቢ በመድገም ነው። ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።

ከግስ ስር የሚመሰረቱት የሚከተሉትን ይመስላሉ።

| <u>ስር</u> | <u>ስም</u> | 10 |
|---|---|---|
| /ል- ብ- ስ/ | [ልእብስ] | ልብስ |
| /ጥ- ቅ- ም/ | [ጥእቅእም] | ጥቅም |
| /ም- ር- ት/ | [ምእርት] | ምርት |
| /ው- ር- ስ/ | [ውእርስ] | ውርስ |

እነዚህ እይነት ስሞች በግሱ ስር ውስጥ ባሉት ክፍት ቦታዎች፣ ባንዱ ወይም በሁሉቱም ላይ /እ/ የሚለውን እናባቢ ድምፅ በመጨመር የሚፈጠሩ ናቸው። ሁኔታው /እ/ የሚለውን ድምፅ፣ ስም መስራች ምዕላድ ነው፣ ሊያስኝ የሚችል ይመስላል። በርግጥ ይህን ማለት ግን አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ይህ ድምፅ በስሩ ውስጥ የሚታዩትን ሶስቱን ተናባቢ ድምፆች ከተራ ድምፅነት ወደ ቀለምነት የመለወጥ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ የሆነ ተግባር ስላለው ነው። ይህን ተግባር በሚፈፅምበት ጊዜ የሚፈጠረው ቅርፅ እንዳጋጣሚ ስም ሊሆን ችሎአል። ሌላም ሊሆን ይችል ነበር፣ ለምሳሌ ቅፅል። ይህን ወደ ሁዋላ በቦታው

እናየዋለን፡፡ ከዚህ ላይ ግን ከግስ ስር ላይ [እ]ን በመጨመር የሚፈጠር ስም፣ አፈጣጠሩ ስነ- ምዕላዳዊ ነው ከማለት ይልቅ፣ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ነው፤ ማለቱ የሚበጅ ላይሆን አይቀርም፡፡ ምክንያቱም ከቁዋንቁዋው የቀስም አወቃቀር ስርዓት አንፃር ስናይ፣ ለቀስሙ መፈጠር የእናባቢው /እ/ መግባት የግድ ነው፡፡ እናባቢው /እ/ ባይሆን ኖሮ፤ ስርዓቱ ስነ-ምዕላዳዊ ይሆን ነበር፡፡ ለምሳሌ፤ ንጉስ [ንእግኡስ] የሚለውን ስም ብንመለከት፣ /ን-ግ-ስ/ ከሚል ስር ላይ /እ/ን እና /ኡ/ን በተናባቢዎቹ መካከል በማስገባት የተፈጠረ ቃል መሆኑን እንረዳለን፡፡ /እ/ የገባው በቀለማዊ ስርዓት መሰረት ነው፡፡ በስነ-ድምፁ ክፍል እንዳየነው፣ በቃል መነሻ ላይ ቁዋንቁዋው የተናባቢ ክትትሎሽን አይፈቅድም፡፡ ተናባቢዎች ተከታትለው በሚመጡበት ጊዜ፤ ክትትሎሹን ለመስበር [እ] በመካከላቸው ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ የሚገባው /እ/ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ነው፡፡ የተናባቢ ክትትሎሽ በሚፈቀድበት አውድ ላይ የሚገባ /እ/ ወይም ሌላ እናባቢ ግን ስነ-ምዕላዳዊ ነው፡፡ በዚህ መሰረት [ንእግኡስ] በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው [እ] ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ሲሆን፣ /-ኡ-/ የሚለው እናባቢ ግን ስነ-ምዕላዳዊ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር /-ኡ-/ ቅፅል መስራች ምዕላድ ነው፡፡ ምክንያቱም እገባቡ የተናባቢ ክትትሎሽን ለማገድ ላይሆን፤ በተናባቢ ብቻ ከተመሰረተው ስር ውስጥ ገብቶ ቃል ለመፍጠር ስለሆነ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ቁዋንቁዋው በቃል መሀል እና መጨረሻ ላይ የሁለት ተናባቢ ክትትሎሽን ይፈቅዳል፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም እንደ <u>ውርስ</u> ያሉ ስሞችን ከግሱ ስር ከመመስረት ይልቅ፣ ለምን ከራሱ ከግሱ መመስረት ለይቻልም? የሚል ነው፡፡ ይህም <u>ውርስ</u> የሚለውን ስም ለምን <u>ወረሰ</u> ከሚለው ግስ ላይ በቀጥታ መመስረት አይቻልም? እንደ ማለት ነው፡፡ ርግጥ፤ ይህን ማለት ይቻላል፡፡ ግን ሂደቱ ብዙና ውስብስብ ነው፡፡ እስቲ እንመልከተው፡፡

<u>ወረሰ</u> የሚለው ግስ ድምፃዊ ቅንጅት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

/ው - ኧ - ርር - ኧ - ስ -ኧ/ 11

በዚህ ቅንጅት ውስጥ ሶስት የ/ኧ/ ድምፆች አሉ፡፡ <u>ውርስ</u> በሚለው ስም ውስጥ ግን ከላይ እንዳየነው፣ አንድ የ/እ/ ድምፅ ብቻ ይታያል፡፡ እንግዲህ <u>ውርስ</u> የሚለው፤ <u>ወረሰ</u> ከሚለው ግስ ላይ ተመሰረተ ብንል፣ አንደኛ፣ <u>ወረሰ</u> ውስጥ ያሉት ሶስት የ/ኧ/ ድምፆች ወደ አንድ የ/እ/ ድምፅ ተለውጠዋል፤ ወይም ከናካቴው ጠፍተዋል ማለት ነው፡፡ ይህን ለውጥ መግለፁ ራሱ አንድ ስራ ነው፡፡ አስቸጋሪም ነው፡፡ ምክንያቱም ለለውጡ ጥሩ መንስዔ መስጠት የሚቻል አይመስልም፡፡ ሁለተኛ፣ <u>ወረሰ</u> የሚለው ግስ ስም የሚሆነው /ኧ/ የሚለው ድምፅ ወደ /እ/ ሲለወጥ ነው ካልን፣ /እ/ ስም መስራች ምዕላድ እንጅ፤ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ተናባቢዎቹን ድምፆች ወደ ቀስም የሚለውጥ ድምፅ አይደለም፤ ማለት ነው፡፡ በሌሎች ቃላት ውስጥ ያለው ሁኔታ ግን /እ/ ቀስም መስራች መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ብልህ /ብእልህ/ በሚለው ቅፅል ውስጥ /እ/

አለ፡፡ ይህ /እ/ ግን ቅፅል መስራች አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቅፅሉ የሚመሰረትበት "በለኸ" የሚል ግስ በቋንቋዋው ውስጥ የለም፡፡ ይህም አናባቢው /እ/ የገባው በቀለም መስራችነት መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ከሆነ፣ /ውእርስ/ በሚለው ስም ውስጥ ያለው /እ/ም እንደዚሁ ቀለም መስራች ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህን ካልን ደግሞ፣ ቃሉ ወረሰ ከሚለው ግስ /ኧ/ን በ/እ/ ለውጦ የመጣ ነው፣ የሚለው አመለካከት ትክክል አይሆንም፡፡ አቋዋራጩና ትክክለኛ የሚመስለው መንገድ፣ /ውእርስ/ የሚለው ስም /ው - ር - ስ/ ከሚለው ስር ላይ በቀጥታ ተመሰረተ የሚለው ነው፡፡ በዚህ ከተስማማን፣ እንደ ውርስ ያሉ ስሞች የሚፈጠሩበትን አጠቃላይ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ስርዓት እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ስርዓት 4፡

/ተ - ተ - ተ/ ⟶ [ተእተተ]

ከምሳሌው እንደሚታየው፣ ከዚህ ስርዓት እንደ ውርስ ያሉ ነፃ እምዶችን መፍጠር ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ስርዓት እንደ [ቅእልም-] ያሉ ዕስር እምዶችንም መፍጠር ይችላል፡፡ ከነሱም ላይ እንደ /-አኸ/ እና እንደ /-ንንእ/ ያሉ ቅጣይ ምዕላዶችን በመጨመር፣ -የሚከተሉትን አይነት ለሞች መፍጠር ይቻላል፡፡

| ስር | ስም | | 12 |
|---|---|---|---|
| ቅልም- | ቅልም-አኸ | ቅልሞኸ | |
| ስርቅ- | ስርቅ-አኸ | ስርቆኸ | |
| ግርድ- | ግርድ-አኸ | ግርዶኸ | |
| ጥብቅ | ጥብቅ-ንንእ | ጥብቅና | |
| ድርቅ | ድርቅ-ንንእ | ድርቅና | |
| ግብር- | ግብር-ንንእ | ግብርና | |
| ትህት- | ትህት-ንንእ | ትህትና | |

/-አኸ/ የሚለው ምዕላድ የሚጨመረው፣ እንደነዚህ ባሉ እስር እምዶች ላይ ብቻ አይደለም፡፡ በነፃ እምዶች ላይም ሊቀጠል ይችላል፡፡ ለምሳሌ ቅብብል ብሎ ቅብብል-አኸ፣ ድብብቅ ብሎ ድብብቅ-አኸ፣ ድግግም ብሎ ድግግም-አኸ፣ ወዘተ፣ ማለት ይቻላል፡፡ እንደነዚህ አይነት ስሞች አንዳንድ ጊዜ የአንድን ነገር ተደጋጋሚ ሂደት ሲያመለክቱ፣ ሌላ ጊዜ ውጤቱን ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ፣

(ሀ) ልጆቹ ቅብብሎሽ ይጫወታሉ 13

ብንል፣ ቅብብሎሽ የሚለው ስም የሚያመለክተው የአንድን ነገር የመቀባበል ረዥም ሂደት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣

(ለ) ካሳ ጥሎሽ ጥሎ (ሰጥቶ) ሚስት አገባ

ብንል፣ <u>ጥሎሽ</u> የሚለው ቃል የሚገልፀው፣ ለሙሽራ የሚሰጠውን ስጦታ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በዚህ ትርጉሙም ቢሆን፣ ለሙሽራ ስጦታ ሲሰጥ ጣል ጣል የማድረግን ተደጋጋሚ ድርጊት ሊያሳይ ይችላል፡፡

/-ንንእ/ በሚለው ምዕላድ አማካኝነት የሚፈጠሩት፣ እንደ <u>ግብርና</u> ያሉት፣ አንድ ሰው የሚሰራበትን ወይም የሚኖርበትን ሁኔታ ወይም ሙያ ስለሚያመለክቱ፣ የሙያ ወይም የሁኔታ ስሞች ሊባሉ ይችላሉ፡፡

ከላይ በተሰጠው ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞች ደግሞ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ እንደተዘረዘሩት ያሉ ናቸው፡፡

| <u>አምድ</u> | <u>ስም</u> | | 14 |
|---|---|---|---|
| ሰብር- | ሰብር-ኣት | ስብራት | |
| ሽልም- | ሽልም-ኣት | ሽልማት | |
| ሰቅል- | ሰቅል-ኣት | ሰቅላት | |
| ንቅስ- | ንቅስ-ኣት | ንቅሳት | |
| ዕርም- | ዕርም-ኣት | ዕርማት | |

ከሰንጠረዡ እንደሚታየው፣ ስሞቹ የተፈጠሩት ከዕለር ምዕላዶቹ ላይ /-ኣት/ የሚለውን መስራች ምዕላድ በመቀጠል ነው፡፡ በዚህ አይነት የሚፈጠሩ ስሞች አንድ ነገር ከተደረገ በሁዋላ የሚገኘውን ውጤት ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ፣ <u>ዕርማት</u> የሚለው ስም የሚያመለክተው አንድ ነገር ከታረመ በሁዋላ፣ የሚገኘውን ውጤት ነው፡፡ የማረሙን ሂደት የሚያመለክተው ቃል <u>ዕረማ</u> ሲሆን፣ የዚህ ሂደት ውጤት ደግሞ <u>ዕርማት</u> ይባላል[2]፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር (4) በተመለከተው ስርዓት መሰረት ([ተእተ(ተ)-]) በሚወጡ ሌሎች ዕለር አምዶች ላይ /-ኣት/ ወይም /-ኣትእ/ የሚል ሌላ ምዕላድ በመጨመር እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞችን መመስረት ይቻላል፡፡

---

[2] ይሁን እንጅ፣ እርማት የሚለው ራሱ እንደ ሂደት ስም ስለሚያገለግል <u>ዐረማ</u> የሚለውን ቃል አግዶታል፡፡ <u>ዐረማ</u> በሂደት ስምነት የሚታወቀው <u>ዐረም</u> ከማረም ጋር በተያያዘ ቅርፁ ነው፡፡ ርግጥ፣ ሁለቱም የማይፈለግ ነገርን ከሚፈለገው እየለዩ የማስወገድን ተግባር ያለመለክታሉ፡፡

በ(ሀ) ውስጥ የተዘረዘሩት ከመድረሻው ተናባቢ በፊት /እ/ን በማስገባት የሚፈጠሩ ስሞች ናቸው፡፡ ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /እ/ የተናባቢ ከትትሎሽ እንዳይፈጠር የገባ አናባቢ ነው፡፡ ተግባሩ ለነ-ድምፀ ልሳናዊ ስለሆነ፣ ስለሞቹ ምስረታ አስተዋፅዖ የሚያደርገው /እ/ ብቻ ነው፡፡

በ(ለ) ስር የሚታዩት፣ በ(ሀ) ስር እንዳሉት፣ /እ/ የሚለውን አናባቢ ከመድረሻው ተናባቢ በፊት በማስገባት፣ እምድ የሚፈጠሩና በየእምዱ መድረሻ ላይም /-ኤ/ የሚለውን ምዕላድ በመቀጠል የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ከመነሻው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /እ/ የተናባቢ ከትትሎሽ እንዳይኖር የገባ አናባቢ ነው፡፡

የስሞቹን የአመሰራረት ስርዓት እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ስርዓት 6፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| [[ተእተ(-ተ)እተ-] + [(-ኤ)]] | | ⟶ | [ተእተ-(ተ)እተ-(ኤ)] |
| እምድ | ቅጣይ | | የውጤት ስም |

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ለሞች የሚያመለክቱት የአንድን ተግባር ውጤት ነው፡፡ ለምሳሌ ውዳሴ የሚሰው ለም የሚገልፀው፣ ተግባርን ወይም ሂደትን ሳይሆን፣ የሂደትን ውጤት ነው፡፡ የሂደቱ ስም ው<u>ደሳ</u> ሲሆን፣ የተግባሩ ስም <u>ማወደስ</u> ወይም በግዕዝ መልኩ <u>መወድስ</u> ነው፡፡

ከላይ ከቀረቡት የተለየ የአመሰራረት ስርዓት ያላቸው የውጤት ስሞችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| <u>እምድ</u> | <u>ስም</u> | 17 |
|---|---|---|
| ውጥ- | ውጥ-ኤት | ውጤት |
| ስል- | ስል-ኤት | ስሌት |
| ስም- | ስም-ኤት | ስሜት |
| ምር- | ምር-ኤት | ምሬት |
| ስክ- | ስክ-ኤት | ስኬት |
| ቅል- | ቅል-ኤት | ቅሌት |

እምዶቹ ዕስር ናቸው፡፡ የንግግር ክፍላቸውን በትክክል መናገር ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከእነሱ ላይ /-ኤት/ የሚሰውን ቅጣይ በመጨመር ስሞቹን መመስረት ይቻላል፡፡ የአመሰራረት ስርዓታቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 7፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| [[ተእተተ-] + [-ኤት]] | | ⟶ | [ተእተተ-ኤት] |
| እምድ | ቅጣይ | | የውጤት ስም |

ከሌሎች ዕስር እምዶች ላይ ተከታይ ቅጣይ ምዕላዶችን በመጨመር የሚፈጠሩ ሌሎች ስሞች ደግሞ የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

| <u>እምድ</u> | <u>ስም</u> | | 18 |
|---|---|---|---|
| ድርግ- | ድርግ-ኢት | ድርጊት | |
| ቅንጅ- | ቅንጅ-ኢት | ቅንጅት | |
| ግፍ- | ግፍ-ኢት | ግፊት | |
| ዕልቅ- | ዕልቅ-ኢት | ዕልቂት | |
| ድርጅ- | ድርጅ-ኢት | ድርጅት | |
| ስርጭ- | ስርጭ-ኢት | ስርጭት | |
| ትንብ- | ትንብ-ኢት | ትንቢት | |

እነዚህ የውጤት ለሞች ይመስላሉ፡፡ ምናልባትም፣ እንደ <u>ስርጭት</u> ያሉት የሂደት ስሞች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሂደት ስሞች አንድ በመካሄድ ላይ ያለ ድርጊትን እንደሚገልፁ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ መዋቅራዊ ባህሪያቸው [በ - ላይ] በሚለው መስተዋድዳዊ አውድ ውስጥ ለመግባት መቻል ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) መድሀኒቱ በስርጭት ላይ ነው 19
(ለ) ወታደሮቹ በውጊያ ላይ ናቸው
(መ) *ወታደሮቹ በትንቢት ላይ ናቸው

<u>ስርጭት</u>ና <u>ዕልቂት</u> [በ - ላይ] በሚለው መስተዋድድ ውስጥ ገብተው ተቀባይነት ያለው አረፍተ ነገር ሊመሰርቱ ችለዋል፡፡ ት<u>ንቢት</u> የሚለው ስም ግን በዚሁ ቦታ ገብቶ የፈጠረው አረፍተ ነገር ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህም በመነሳት <u>ስርጭት</u> የሂደት፣ ዕ<u>ልቂት</u> የውጤት ስም ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ የሁለቱ ስሞች ስነ-ምዕላዳዊ ቅርፅ ተመሳሳይ ቢሆንም፣ አገባባዊ ባህሪያቸው ለየቅል መሆኑን ከምሳሌዎቹ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ አንዳንድ ጊዜ የሂደትና የውጤት ስሞችን በአገባባቸውም ቢሆን ለመለየት ያስቸግራል፡፡ ይህን ዝቅ ብለን እንመለከታለን፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ስሞች አመሰራረት ግን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 8፣

| | | | |
|---|---|---|---|
| [[ተእተ-(እ)ተ-ተ) ] - + [-ኢት]] | | ⟶ | [ተእተ-(እ)ተ-(ተ)-ኢት] |
| እምድ | ቅጣይ | | የውጤት ስም |

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ደግሞ እንመልከት፡፡

| አምድ | ስም | | 20 |
|---|---|---|---|
| ግፍ- | ግፍ-ኢይእ | ግፊያ | |
| ግብዝ- | [ግእብዝ--ኢይእ] | [ግእብዥእ] | ግብዥ |
| ዝርፍ- | ዝርፍ-ኢይእ | ዝርፊያ | |
| ሽም- | ሽም-ኢይእ | ሽሚያ | |
| ቅድም- | ቅድም-ኢይእ | ቅድሚያ | |
| ግጥም- | ግጥም-ኢይእ | ግጥሚያ | |
| ፍልም- | ፍልም--ኢይእ | ፍልሚያ | |
| ድርስ- | [ድእርስ-ኢይእ | [ድእርሽእ] | ድርሻ |

እነዚህ የተመሰረቱበት አምድ ከላይ በተራ ቁጥር(8) የሚታየው አይነት ሲሆን፣ መስራቹ ምዕላድ /-ኢይእ/ ነው፡፡ ስርዓቱም የሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 9፣

[[(ተእተ-ተ) - + [--ኢይእ]] ⟶ [ተእተ-ተ)-ኢይእ]
አምድ ቅጣይ የሂደት ስም

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ስሞች በአብዛኛው ሂደትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ውጤትንም ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ግብዣ የሚለውን ስም ብንወስድ፣ በአንድ ምክንያት የተዘጋጀ ድግስን፣ ማለትም ውጤትን፣ ወይም ድግሱን የመብላትን ሂደት ሊያመለክት ይችላል፡፡ ትርጉሙ አሻሚ ነው፡፡ በሌላ በኩል ድርሻ የሚለውን ቃል ብንመለከት፣ አንድ ሰው አንድ ነገር ከሌሎች ጋር ተከፍሎ ሲጨርስ፣ የሚደርሰውን መጠን ስለሚያመለክት የውጤት ስም ነው፡፡

ሌሎች የማያሻሙ የውጤት ስሞችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| አምድ | ስም | 21 |
|---|---|---|
| ሽፍት- | ሽፍት-እ | ሽፍታ |
| ቁምጥ- | ቁምጥ-እ | ቁምጣ |
| ጭፍን- | ጭፍን-እ | ጭፍና |
| ጭፍር- | ጭፍር-እ | ጭፍራ |
| ብስን- | ብስን-እ | ብስና |

የእነዚህ የአመሰራረት ስርዓት የሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 10፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ ተእተተ-] + [-እ] | ⟶ | [ተእተተ-እ] |
| አምድ ቅጣይ | | የውጤት ስም |

ስርዓቱ በየዕስር አምዱ ላይ /-እ/ የሚሰውን መሰራች ምዕላድ መቀጠል እንደሰብን ያሳያል፡፡

አሁን ደግሞ ወደ ሌሎች የውጤት ስሞች አመሰራረት እንሂድና የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመልከት፡፡

| ስር | ስም | 22 |
|---|---|---|
| /ስ - ር - ግ/ | [ሰኧርግ] | ሰርግ |
| /ም - ል - ስ/ | [ምኧልሰ] | መልስ |
| /ሽ - ፍ - ጥ/ | [ሽኧፍጥ] | ሸፍጥ |
| /ብ - ል - ግ/ | [ብኧልግ] | በልግ |
| /ስ - ል - ፍ / | [ስኧልፍ] | ሰልፍ |
| /ጥ - ር - ብ/ | [ጥኧርብ] | ጠርብ |

የነዚህና የመሳሰሉት ስርዓት የሚከተሰው ነው፡፡

ስርዓት 11፤

| | | |
|---|---|---|
| [ተ-ተ-ተ] | ⟶ | [ተኧተተ] |
| ስር | | የውጤት ስም |

ስርዓቱ ከየስሩ የመጀመሪያ ተናባቢ ቀጥሎ /ኧ/ የሚሰውን እናባቢ በማስገባት የውጤት ስሞችን መፍጠር እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ በዚህ ሰርዓት ከሚመሰረቱትም ብዙዎቹ ነፃ አምዶች ናቸው፡፡ በነሱ እና በጥቂት ሌሎች አምዶች ላይ /-ኧኛኛእ/ የሚል ምዕሳድ በመጨመር እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞችን መፍጠር ይቻላል፡፡

| ሰም | ስም | 23 |
|---|---|---|
| ግንብ | ግንብ-ኧኛኛእ | ግንበኛ |
| ሰልፍ | ሰልፍ-ኧኛኛእ | ሰልፈኛ |
| ፈረስ | ፈረሰ-ኧኛኛእ | ፈረሰኛ |
| ጥበብ | ጥበበ-ኧኛኛእ | ጥበበኛ |
| ሰፈር | ሰፈረ-ኧኛኛእ | ሰፈረኛ |

የስሞቹን አፈጣጠር እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

ስርዓት 15፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ ተ-ኸ-(ተ)ተ-አ-ተ-] [+ -ኢ] ] | ⟶ | [ ተ-ኸ-(ተ)ተ-ኣ-ተ-ኢ] |
| አምድ ቅጣይ | | የአድራጊ ስም |

ከዚህ ስርዓት ጋር ተቀራራቢ በሆነ መንገድ የሚከተሉትን አይነት ስሞች መፍጠር ይቻላል፡፡

| ስር | አምድ | ስም | 28 |
|---|---|---|---|
| /ጥ-ርር-ግ/ | [ጥእርርኣግ-] | [ጥእርርኣግ-ኢ] | ጥራጊ |
| /ው-ድድ-ቅ/ | [ውእድድኣቅ-] | [ውእድድኣቅ-ኢ] | ውዳቂ |
| /ል-ቅቅ-ም/ | [ልእቅቅኣም-] | [ልእቅቅኣም-ኢ] | ልቃሚ |
| /ፍ-ልል-ጥ/ | [ፍእልልኣጥ-] | [ፍእልልኣጥ-ኢ] | ፍላጭ |

እንደነዚህ ያሉት ስሞች፣ አንድ ድርጊት ሲፈፀም ተርፎ ወይም ወድቆ የሚቀርን ነገር የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ስለዚህም የቅሪት ስሞች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ጥራጊ የሚለው ስም ምርት ከተነሳ በሁዋላ አውድማ ተጠርጎ የሚገኘን ቀሪ ወይም ትርፍ እህል የሚገልፅ ቃል ነው፡፡ በእንዳንድ አካባቢ ግርድ ይባላል፡፡ "ምርትና ግርዱ ይለያል" የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

የዚህ አይነት ስሞች በትርጉማቸው ተደራጊ ናቸው፡፡ ይህን ለማመልከት ቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን ያጠብቃሉ፡፡ ለምሳሌ ጠራጊን (/ጥኸርኣግ-ኢ/) እና ጥራጊን ([ጥእርርኣግኢ]) ብናነፃፅር፣ ጥራጊ ውስጥ የሚገኘው /ር/ ጥብቅ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ሌሎች ተደራጊ ስሞች ተደራጊነትን የሚያሳዩት /ተ-/ የሚል ምዕላድ በአድራጊው ስም መነሻ ላይ በማስገባት ነው፡፡ ይህም ጠራጊ ብለን፣ ተ-ጠራጊ እንደምንለው ነው፡፡ ሁለቱን ተደራጊ ስሞች ለመለየት፣ እንደ ጥራጊ ያሉትን የድራጊ ስሞች ልንላቸው እንችላለን፡፡ ያፈጣጠር ስርዓታቸው እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 16፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ ተ-ተተአት][ +-ኢ]] | ⟶ | [ ተእተተአተ-ኢ] |
| አምድ ቅ | | የድራጊ ስም |

እስካሁን የየናቸው ስሞች እንድም ከግሱ ስር ወይም ከአምዱ መድረሻና መካከል ላይ የተለያዩ መስራች ምዕላዶችን በመቀጠል የሚፈጠሩ ሲሆን፣ ከዚህ ለየት ባለ ሁኔታ የሚፈጠሩት ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉ ሌሎች ስሞች ናቸው፡፡

| ስር | አምድ | ስም | 29 |
|---|---|---|---|
| /ስ-ድ-ብ/ | /-ስድኧብ/ | /ምኧ-ስድኧብ/ | መስደብ |
| /ስ-ብ-ር/ | /-ስብኧር/ | /ምኧ-ስብኧር/ | መስበር |
| /ፍ-ልል-ግ/ | /-ፍኧልልኧግ/ | /ምኧ-ፍኧልልኧግ/ | መፈለግ |
| /ጥ-ር-ግ/ | /-ጥርኧግ/ | /ምኧ-ጥርኧግ/ | መጥረግ |
| /ፍ-ል-ጥ/ | /-ፍልኧጥ/ | /ምኧ-ፍልኧጥ/ | መፍለጥ |

እንደነዚህ ያሉት ስሞች በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አርዕስት በመባል ይታወቃሉ፡፡ ተግባራቸው ድርጊትን ማመልከት ስለሆነ የድርጊት ስሞች ልንላቸው እንችላለን፡፡ የሚፈጠሩት /ምኧ-/ የሚለውን ቅጥያ በየአምዱ መነሻ ላይ እንደሚከተለው በመቀጠል ነው፡፡

ስርዓት 17፣

| | |
|---|---|
| [[ምኧ-] +[-ተ-ኧ-(ተ)ተኧተ]] ⟶ | [ምኧ-ተ-ኧ-(ተ)ተኧተ] |
| ቅጣይ   አምድ | የድርጊት ስም |

ከስርዓቱ እንደሚታየው፣ ከአምዱ የመጀመሪያ ተናባቢ ቀጥሎ ያለው አናባቢ /-ኧ-/ ሊገኝ ወይም ላይገኝ ይችላል፡፡ ይህን የሚወስነው የአምዱ ክፍል ነው፡፡ ቀደም ሲልም ሆነ፣ ባለፈው ንዑስ ክፍል እንደተጠቀሰው፣ የአማርኛ ግሶች የ(ሀ) እና የ(ለ) ተብለው በሁለት ክፍል ይመደባሉ፡፡ የ(ሀ) ክፍል የሚባሉት ቅድመ-መድረሻ እግራቸውን ሳያጠብቁ የሚመሰረቱና የሚረቡ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ በሚታየው የምስረታ ሂደት፣ አንድ አምድ የ(ለ) ክፍል ከሆነ፣ ከመነሻው ተናባቢ ድምፅ ቀጥሎ /-ኧ-/ን ያስገባል፡፡ <u>በመስበርና</u> <u>በመፈለግ</u> መካከል የሚታየው የአመሰራረት ልዩነት ከዚህ የመነጨ ነው፡፡ <u>ሰበረ</u> የ(ሀ) ክፍል ግስ ሲሆን፣ <u>ፈለገ</u> የ(ለ) ክፍል ግስ ነው፣ ስለዚህም ትድመ-መድረሻ እግሩን ያጠብቃል፡፡ ከመነሻ እግሩ ቀጥሎም /-ኧ-/ን ያስገባል፡፡

ከነዚህ አርዕስታዊ ስሞች ላይ /-ኢይእ/ የሚል ምዕላድ በመቀጠል ሌሎች ስሞችን መመስረት ይቻላል፡፡ ዝርዝሩን ከሚከተለው ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

| | አርእስት | ስም | 30 |
|---|---|---|---|
| መጥረግ | /ምኧጥርኧግ/ | /ምኧጥርኧግ-ኢይእ/ | መጥረጊያ |
| መስበር | /ምኧስብኧር/ | /ምኧስብኧር-ኢይእ/ | መስበሪያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መግለጥ | /ምኧግልኧጥ/ | /ምኧግልኧጥ-ኢይኣ/ | |
| | | [ምኧግልኧጭኣ] | መግለጫ |
| መፍለጥ | /ምኧፍልኧጥ/ | /ምኧፍልኧጥ-ኢይኣ/ | |
| | | [ምኧፍልኧጭኣ] | መፍለጫ |

የዚህ አይነት ስሞች አንድ ነገር የሚፈፀምበትን ጊዜ፣ ቦታ፣ መሳሪያ፣ ዘዴ፣ ወዘተ፤ ስለሚያመለክቱ፣ በጥቅሉ የማድረጊያ ስሞች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ መስረታቸውም ከፍ ሲል የተመለከትናቸው የድርጊት ስሞች ናቸው፡፡ የአፈጣጠራቸው ስርዓት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 18፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ መ-ተ-ተ-ኧ-ተ] +[ -ኢይኣ]] ⟶ | | [መ-ተ-ተ-ኧ-ተ-ኢይኣ] |
| አምድ | ቅጣይ | የማድረጊያ ስም |

እስካሁን ያየናቸው ውልድ ስሞች ከግስ ስሮች ላይ የተለያዩ አናባቢዎችን በመጨመር ወይም ከአምዶች ላይ የተለያዩ መስራች ቅጣዮችን በማስቀደም ወይም በማስከተል የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ከነዚህ ለየት ያለ የአፈጣጠር ስርዓት ያላቸውን ስሞች እንመረምራለን፡፡

| ስር | አምድ | ስም | 31 |
|---|---|---|---|
| /ሰ-ብ-ር/ | /-ሰሰኧብኣብኧር/ | /ኣ-ሰሰኧብኣብኧር/ | አሰባበር |
| /ን-ግ-ር/ | /-ንንኧግኣግኧር/ | /ኣ-ንንኧግኣግኧር/ | አነጋገር |
| /ል-ብ-ስ/ | /-ልልኧብኣብኧስ/ | /ኣ-ልልኧብኣብኧስ/ | አለባበስ |
| /ል-ቅ-ስ/ | /-ልልኧቅኣቅኧስ/ | /ኣ-ልልኧቅኣቅኧስ/ | አለቃቀስ |
| /ው-ል-ድ/ | /-ውውኧልኣልኧድ/ | /ኣ-ውውኧልኣልኧድ/ | አወላለድ |

የነዚህ ስሞች አፈጣጠር፣ በየአምዱ ላይ ቀዳሚ ቅጣይ የሚጨምር ብቻ ሳይሆን፣ የየአምዱን የመነሻ እግር የሚያጠብቅ፣ ቅድመ-መድረሻውን የሚደጋግምና በተደጋጋሚዎቹ እግሮች መካከል /-ኣ/ የሚለውን አናባቢ ድምፅ የሚያስገባ ነው፡፡ መጀመሪያ የአምዱን አፈጣጠር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 19፤

/1 - 2 - 3/ ⟶ /-11ኧ2ኣ2ኧ3/

ከቀስቱ በፊት የሚታዩት ቁጥሮች የስሩን ሶስት ተናባቢ ድምፆች ይወክላሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ በአንድ ቁጥር የተወከለው፣ ማለትም መነሻው፣ ተናባቢ ይጠብቃል፡፡ በሁለት ቁጥር የተወከለው፣ ቅድመ-መድረሻ ድምፅ ደግሞ ራሱን ይደግማል፡፡ ከዚያም በተደጋጋሚዎቹ ድምፆች መካከል /-ኣ-/ን፣ በሌሎቹ ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ን በማስገባት አምዱን ይመሰርታል፡፡ በተመሰረተው አምድ መነሻ ላይ /ኣ-/ የሚለውን ምዕላድ ያስገባል፡፡[4] ዝርዝር ስርዓቱ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ስርዓት 20፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ ኣ-]+ [11ኧ2ኣ2ኧ3 ]]<br>ቅጥይ አምድ | ⟶ | [ ኣ-11ኧ2ኣ2ኧ3]<br>የአደራረግ ስም |

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ ስሞች የሚያመለክቱት የአንድን ተግባር አፈፃፀም ማለትም አደራረግን ነው፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ሳቢ ዘር በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሳቢ ዘር የሚባሉበት ምክንያት ተናባቢ ድምፃቸውን በመሳሳብ፣ ማለትም በመደጋገም፣ ሰፋ ሰፋ ያለ አምድ ስለሚመሰርቱ ነው፡፡

አስካሁን ከስምና ከግስ ስር ወይም አምድ ላይ የተለያዩ ቅጥዮችን በመጨመር ወይም የተለያዩ አናባቢዎችን በግሱ ስር ውስጥ በማስገባት የተለያዩ ስሞችን እንዴት መመስረት እንደሚቻል አያየን መጥተናል፡፡ በየስርዓቱ የሚፈጠሩ ስሞችን ከትርጉማቸውና ከቅርፃቸው አኳዋያ ለመከፋፈል ሞክረናል፡፡ በዚሁ መሰረት ከግስ ስር የሚመሰረቱትን የአድራጊ፣ የድርጊት፣ የድራጊ፣ የማድረጊያ፣ የአደራረግ፣ የውጤት፣ የሂደት፣ ወዘተ፣ ስም በማለት የአንዱን

---

[4] ባየ (1987) ላይም ይህን ስም የሚመሰርተው ቅጥይ /አስ-/ እንደሆነ ተገልፆ ነበር፡፡ ከዚያ ወዲህ ጉዳዩን እንደገና በመመርመር ቅጥዩ ምናልባት /አስ-/ ሳይሆን፣ /ኣ-/ ብቻ ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ ተችሎአል፡፡ ቅጥዩ /አስ-/ የማይሆንበት ምክንያት ስነ-ድምፃዊ ነው፡፡ /አስ-/ ውስጥ የምትገኘው /ስ/ ከስሩ የመነሻ እግር ጋር ሙሉ በሙሉ ትመሳሰልና ድምፁን ጠባቂ ታስመስለዋለች፡፡ ከላይ በስርዓት (19) የሚታየውም ይኸው ነው፡፡ ችግሩም /ስ/ ከማንኛውም ድምፅ ጋር መመሳሰልዋ ነው፡፡ አንድ ተናባቢ ድምፅ ሊመሳሰል የሚችለው ከማንኛውም ሌላ ተናባቢ ጋር ሳይሆን፣ በቦታ ወይም በአፈጣጠር ባህሪ ከሚቀርበው ሌላ ድምፅ ጋር ነው፡፡ ሁለተኛም /አስ-/ የሚለው ምዕላድ አስደራጊነትን እንጅ አደራረግን የማያመለክት መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ስንነሳ ምናልባት አደራረግ የሚገለፀው /-11ኧ2ኣ2ኧ3/ በሚል ዕስር አምድ ነው፤ ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ አምዱ ዕስር ስለሆነ /ኣ-/ የሚለውን ምዕላድ በማስቀደም ወደ ሙሉ ግስነት ይለወጣል፡፡ /ኣ-/ በሌሎች ዕስር አምዶች መነሻ ላይ እየገባ ሙሉ ግሶችን የሚመሰርትበት ብዙ ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ /-ገኘ/ ከሚለው ዕስር አምድ መነሻ ላይ በመግባት /ኣ-ገኘ/ የሚለውን ግስ ይመሰርታል፡፡ ስለዝርዝር ሁኔታው ባየ (1999)ን በተጨማሪ ይመልከቱ፡፡

አይነት ከሌላው መለየት እንደሚቻል አሳይተናል፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የውልድ ቅፅሎችን አመሰራረት እንመረምራለን፡፡

## ውልድ ቅፅሎች

እንደ ስሞች ሁሉ ቅፅሎችም ነባርና ውልድ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ነባር የሚባሉት እንደ ብልህ፣ ትሁት፣ ደግ፣ የዋህ፣ ወዘተ፣ ያሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ላይ የተመሰረቱ አይደሉም፡፡ ስለዚህም ነባር ወይም ዘር ይባላሉ፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው፡፡ አብዛኞቹ ቅፅሎች ውልድ ናቸው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ የሚወለዱትም ከስሞችና ከግስ ስሮች ወይም አምዶች ላይ ነው፡፡ ያወላለዳቸውን ሁኔታ ከስም ከሚወለዱት በመጀመር ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን፡፡

| ስም | ቅፅል | | |
|---|---|---|---|
| ሀይል | ሀይል-ኧኛኛአ | ሀይለኛ | 1 |
| ቂም | ቂም-ኧኛኛአ | ቂመኛ | |
| ወረት | ወረት-ኧኛኛአ | ወረተኛ | |
| ጉልበት | ጉልበት-ኧኛኛአ | ጉልበተኛ | |
| ጀብድ | ጀብድ-ኧኛኛአ | ጀብደኛ | |

የእነዚህን አይነት ቅፅሎች የአመሰራረት ሂደት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 1፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ስም] + [-ኧኛኛአ]] | ———→ | [ስም-ኧኛኛአ] |
| ቅጣይ | | ቅፅል |

ስርዓቱ አንድ ስም /-ኧኛኛአ/ የሚል ምዕላድ ሲከተለው ቅፅል ይሆናል የሚል ነው፡፡ እንደ *ወረተኛ* ያሉ ቅፅሎች የአንድን ነገር ባህሪ ስለሚያመለክቱ፣ የባህሪ ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣

ካሳ ወረተኛ ሰው ነው 2

ብንል፣ <u>ወረተኛ</u> መሆን የካሳ ባህሪ ነው፣ ማለታችን ነው፡፡

ሌሎች ቅፅሎች ደግሞ ከስሞች ላይ /-አም/ ወይም /-አምምአ/ን በመጨመር እንደሚከተለው ይፈጠራሉ፡፡

ስርዓት 3፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ስም] + [-ሳውኢ ]]<br>ቅጣይ | ⟶ | [ስም-ሳውኢ ]<br>የወገን |

በዚህ አይነት የሚፈጠሩ ቅፅሎች ወገንን ወይም ክፍልን ያመለክታሉ። ስለዚህም በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ የወገን ቅፅል በመባል ይታውቃሉ። በአገባባቸው ከስሞች ጋር ስለሚመሳሰሉ በስም ክፍል ውስጥ ሊመደቡ ይችላሉ። ለምሳሌ፣

(ሀ) ሰዎቹ ጀግኖች ናቸው 5

ለንል፣ ሰዎቹ የሚለው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ ስም ነው። በእሱ ምትክ ኢትዮጵያዊያን የሚለውን ቃል ብናስገባ፣ አረፍተ ነገሩ፣

(ለ) ኢትዮጵያዊያን ጀግኖች ናቸው

የሚል ይሆናል። ኢትዮጵያዊያን የሚለው ቃል ሰዎቹ በሚለው ስም ቦታ ባለቤት ሆኖ ገብቶአል። በተጨማሪም እንደ ኢትዮጵያዊያን ያሉ ቃላት እንደ ማንኛውም ስም ቅፅልን እያስቀደሙ ሊገቡ ይችላሉ። ይህ ሲሆን፣ እንደ፣

ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን 6

ያሉ ስማዊ ሀረጎችን እናገኛለን። እነዚህ ሁኔታዎች እንደ ኢትዮጵያዊ ያሉ ቃላት ስሞች መሆናቸውን ይጠቁማሉ። ባለፈው ክፍል ስለ ቃላት ክፍሎች ስንወያይ፣ አንድ ቃል በርግጥ ቅፅል ለመባል እንደ፣

ያ በጣም---------- ተማሪ 7

ባለ ሀረግ ውስጥ በሚታየው ክፍት ቦታ ላይ መገኘት መቻል አለበት፣ ብለን ነበር። በዚህ መስፈርት መሰረት፣ እንደ ኢትዮጵያዊ ያለ ቃል በዚህ ቦታ ሊገባ ስለማይችል፣ ቅፅል ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፣

(ሀ) *ያ በጣም ኢትዮጵያዊ ተማሪ 8

ማለት፣ ተቀባይነት ያለው አባባል አለመሆኑ ነው። በአንፃሩ ግን፣

(ለ) ያ በጣም መንፈሳዊ ተማሪ

ማሰት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ያሰጥርጥር ቅፅል ናቸው፣ ሊባሉ የሚችሉ፣ እንደ መንፈሳዊ፣ ዘመናዊ፣ ፍትሀዊ፣ ወቅታዊ፣ ወዘተ፣ ያሉ ቃላትም በዚሁ በተራ ቁጥር (3) በተጠቀስው ስርዓት መስረት የሚፈጠሩ በመሆናቸው፣ ስርዓቱ ቅፅልን ብቻ ሳይሆን ስምንም እንደሚመሰርት መረዳት ይቻላል፡፡ ባጭሩ፣ እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያሉ ቃላት የወገን ስሞች ሲሆኑ፣ እንደ <u>መንፈሳዊ</u> ያሉት የወገን ቅፅሎች ናቸው፣ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ልዩነታቸውም የቅርፅ ሳይሆን፣ የአገባብ እንደሆነ ከተሰጡት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ <u>ኢትዮጵያዊ</u> ያሉ ስሞች፣ በወገን ስምነታቸው ሌሎች ስሞችን እየገለፁ ሲገቡ ይችላሉ፡፡ በዚህ አገባባቸው ገላጭ ከሆኑት ከቅፅሎች ጋር ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡

ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ጎበዞች ናቸው 9

ከዚህ በላይ ኢትዮጵያዊያን የሚለው ስም ተማሪዎች የሚለውን ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (7) እንደሚታየው፣ <u>በጣም</u> ከሚለው መጣኝ ምዕላድ ጋር ሊገባ አይችልም፡፡ ስለዚህም በተግባሩ ቅፅላዊ፣ በክፍሉ ስማዊ የሆነ ቃል ነው፣

ከዚህ በላይ የተመለከትነው ከስሞች የሚመሰረቱትን ቅፅሎች ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስማዊ ከሚመስሉ ዕስር አምዶች ላይ የሚመሰረቱትን እንመለከታለን፡፡

| | <u>አምድ</u> | <u>ቅፅል</u> | 10 |
|---|---|---|---|
| ጥ-ም-ም- | /ጥኧምኣም-/ | /ጥኧምኣም-ኣ/ | ጠማማ |
| ም-ል-ጥ- | /ምኧልኣጥ-/ | /ምኧልኣጥ-ኣ/ | መላጣ |
| ቅ-ር-ፍ-ፍ- | /ቅኧርፍኣፍፍ-/ | /ቅኧርፍኣፍፍ-ኣ/ | ቀርፋፋ |
| ቅ<sup>ʷ</sup>-ሽ-ሽ- | /ቅ<sup>ʷ</sup>ኧሽኣሽ-/ | /ቅ<sup>ʷ</sup>ኧሽኣሽ-ኣ/ | ቆሻሻ |
| ግ-ጥ-ብ- | /ግኧጥኣብ-/ | /ግኧጥኣብ-ኣ/ | ገጣባ |
| ስ-ብ-ር- | /ስኧብኣር-/ | /ስኧብኣር-ኣ/ | ሰባራ |
| ት-ል-ክ-ሽ- | /ትኧልክኣሽሽ- / | /ትኧልክኣሽሽ-ኣ/ | ተልካሻ |

የእነዚህ አይነት ቅፅሎች የአንድን ነገር ባህሪያዊ ወይም አካላዊ አይነት በሰሚጠቁሙ፣ የአይነት ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ አመሰራረታቸውን እንደሚከተለው አድርጎ ማሳየት ይቻላል፡፡

ስርዓት 4፣

[[ተኧተ(ተ)ኣ-ተ(ተ)-] + [-ኣ] ⟶ [ተኧተ(ተ)ኣተ(ት)-ኣ]]
የአይነት ቅፅል

ከዚህ ላይ /ተኸተ(ተ)እተ(ተ)-/ የሚለው ዕሰር እምድ፣ /ተ-ተ(ተ)-ተ(ተ)/ በሚለው ስር ውስጥ /ኸ/ን እና /እ/ን እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ በክፍቶቹ ቦታዎች በማስገባት የተፈጠረ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እምዱ በራሱ ትርጉምም ሆነ የቃል ክፍል የለውም፡፡ ሙሉ ቃል ሆኖ ትርጉምና የቃል ክፍል የሚያገኘው /-አ/ የሚለውን መስራች ምዕላድ ሲያስከትል ነው፡፡ ከዚህም ምዕላድ ገና ትርጉም ያላገ ባዶ ቅርፅ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡

እስካሁን የተመለከትነው ከስሞችና ከስም-መሰል ዕሰር እምዶች ላይ ቅጣዮችን በመጨመር የሚፈጠሩትን ቅፅሎች ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ከግስ ስር ወይም እምድ ላይ ሊመሰረቱ የሚችሉትን እንመለከታለን፡፡

| ስር | ቅፅል | 11 |
|---|---|---|
| /ሰ-ን-ፍ/ | /ሰኸንኸፍ/ | ሰነፍ |
| /ድ-ን-ዝ/ | /ድኸንኸዝ/ | ደነዝ |
| /ድ-ር-ቅ/ | /ድኸርኸቅ/ | ደረቅ |
| /ው-ድ-ል/ | /ውኸድኸል/ | ወደል |
| /ጥ-ብ-ድ-ል/ | /ጥኸብድኸል/ | ጠብደል |

የእንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች የአመሰራረት ስርዓት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 5፣

| | | |
|---|---|---|
| [[ተ-ተ(ተ)-ተ-] | ⟶ | [ተኸተ(ተ)ኸተ]<br>የባህሪ ቅፅል |

ስርዓቱ እንደሚያሳየው፣ ቅፅሎቹ የሚመሰረቱት በየስሮች ውስጥ በሚታዩት ክፍት ቦታዎች /-ኸ-/ የሚለውን እናባቢ በማስገባት ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቅፅሎች ባህሪን ወይም መጠንን ስለሚያመለክቱ፣ ቀደም ሲል ካየናቸው፣ እንደ ወረተኛ ካሉ ሌሎች የባህሪ ቅፅሎች ጋር ሊጠቃለሉ ይችሉ ነበር፡፡ የአመሰራረታቸው ስርዓትና የሚመሰረቱበት ክፍል የተለየ በመሆኑ ብቻ ለብቻቸው እንዲታዩ ተደርጓል፡፡ እንደ ዘፈን፣ ወረት፣ ከፈን፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉ ስሞችን በዚህ ስርዓት እንደሚፈጠሩ በስም ምስረታ ላይ አይተናል፡፡ ከዚህም ሁለቱ የቃላት ክፍሎች ተመሳሳይ የምስረታ ስርዓት እንደሚከተሉ መረዳት ይቻላል፡፡

ሌሎች ቅፅሎች ደግሞ ብግስ ስሮች ውስጥ በሚገኙት ክፍት ቦታዎች ላይ /ኸ/ እና /ኢ/ የሚሉትን እናባቢዎች በማስገባት በሚከተለው ሁኔታ ይመሰረታሉ፡፡

| ስር | ቅፅል | | 12 |
|---|---|---|---|
| /ር-ዝዝ-ም/ | /ርኧዝዝኢም/ | [ርኧዥዥኢም] | ረዥም |
| /ቅ-ጥጥ-ን/ | /ቅኧጥጥኢን/ | [ቅኧጭጭኢን] | ቀጭን |
| /ህ-ጥጥ-ር/ | /ህኧጥጥኢር/ | [ኣጭጭኢር] | አጭር |
| /ጥ-ይይ-ም/ | /ጥኧይይኢም/ | | ጠይም |
| /ፍ-ር - -/ | /ፍኧርኢ-/ | | ፈሪ |

እነዚህም ቀደም ሲል እንዳየናቸው የመጠንና የአይነት ቅፅሎች ናቸው፡፡ እንደ ረዥም ያሉት መጠንን ሲያሳዩ፣ እንደ ቀይ ያሉት ቀለማዊ አይነትን ያመለክታሉ፡፡ በጥቅሉ የአይነት ቅፅል ልንላቸው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡ "ሰውየው ምን አይነት ነው?" ብንባል፤ "ሰውየው አጭር፣ ረዥም፣ ቀይ፣ ወዘተ፡ ነው" ብለን፡ መመለስ እንችላለን፡፡ ርግጥ፡ "ሰውየው ክፉ ነው" ማለትም ይቻላል፡፡ ክፉ የሚለው ቅፅል ግን የሚያመለክተው የሰውየውን አይነት ሳይሆን፡ ግብሩን ነው፡፡ ክፉ የሚያስኘው ክፉ ምግባር ነውና፡፡ ስለዚህም የግብር ቅፅል ልንላቸው እንችላለን፡፡

እንደነዚህ ባሉ ቅፅሎች ውስጥ ቅደመ-መድረሻው ተናባቢ ወደ ላንቃዊነት ይለወጣል፡፡ የለውጡ ምክንያት /-ኢ-/ የምትለዋ አናባቢ ድምፅ ነች፡፡ በስሩ ውስጥ /ዝዝ/ የነበረው ድምፅ በ(ድ)ላንቃዊነቱ ምክንያት ወደ [ዥዥ]፡ እንደዚሁም /ጥጥ/ የነበረው ወደ [ጭጭ] ሊለወጥ ችሎአል፡፡ በመጨረሻዎቹ ሁለት ሰሮች ውስጥ የመጨረሻው ተናባቢ ዕግር ተጎርዶአል፡፡ እንደዚሁም /ህ-ጥጥ-ር/ በሚለው ሰር መነሻ ላይ የሚገኘው /ህ/ ሰለ ተጎረደ፡ ቅፅሉ በ/አ/ ሊጀምር ችሎአል፡፡ እነዚህ በስነ-ድምፁ ክፍል ባየነው የግድፈት ስርዓት መሰረት የመጡ ለውጦች ናቸው፡፡

የቅፅሎቹን የአፈጣጠር ስርዓት ብቻ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ሰርዓት 6፣

| | |
|---|---|
| [ተ-ተ(ተ)-ተ] ⟶ | [ተ-ኧ-ተ(ተ)-ኢ-ተ]<br>ቅፅል |

የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት፡፡

| ሰር | እምድ | ቅፅል | 13 |
|---|---|---|---|
| /ክ-ብ-ር/ | ክ-ብኡር | [ክእብኡር] | ክቡር |
| /ን-ፅ-ህ/ | ን-ፅኡህ | [ንእፅኡህ] | ንፁህ |
| /ጥ-ቅ-ር/ | ጥ-ቁኡር | [ጥእቅኡር] | ጥቁር |
| /ክ-ፍ - -/ | ክ-ፍኡ | [ክእፍኡ] | ክፉ |
| /ብ-ር-ት- -/ | ብ-ርትኡ | [ብእርትኡ] | ብርቱ |

እንደነዚህ ያሉት፣ አንድ ነገርን ብቻ አያመለክቱም፡፡ ባህሪን፣ አይነትን፣ ግብርን፣ ወዘተ፣ ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ የመጨረሻዎቹ ሁለት ስሮች፣ የመጨረሻ ተናባቢያቸውን ኀርደዋል፡፡ የቅፅሎቹ ስርዓተ-ፍጥረት እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 7፣

| | | |
|---|---|---|
| [ ተ-ተ-ተ-(ተ)] | ——→ | [ ተእ-(ተ)ተኡ-(ተ)]<br>ቅፅል |

ስርዓቱ ከመጨረሻው እግር በፊት ባለው ክፍት ቦታ ላይ /-ኡ/ የሚለውን አናባቢ ድምፅ በማስገባት፣ ቅፅሎችን መፍጠር እንደሚቻል ያመለክታል፡፡ ከመጀመሪያው ተናባቢ ቀጥሎ የሚታየው /እ/ ስነ-ምፅላዳዊ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የተናባቢ ክትትሎሽን ለመስበር የገባ ሰርጎ-ገብ አናባቢ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በየስሮቹ መካከል በሚገኙት ክፍት ቦታዎች /-ኧ-/ን እና /-አ-/ን በማስገባትና የቅድመ-መድረሻ ተናባቢያቸውን በማጥበቅ የሚመሰረቱ ሌሎች ቅፅሎች አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| ስር | ቅፅል | 14 |
|---|---|---|
| /ክ-ብብ-ድ/ | /ክኧብብአድ/ | ከባድ |
| /ቅ-ልል-ል/ | /ቅኧልልኣል/ | ቀላል |
| /ድ-ቅቅ-ቅ/ | /ድኧቅቅኣቅ/ | ደቃቅ |
| /ድ-ምም-ቅ/ | /ድኧምምአቅ/ | ደማቅ |
| /ው-ልል-ድ/ | /ውኧልልአድ/ | ወላድ |
| /ድ-ፍፍ-ር/ | /ድኧፍፍአር/ | ደፋር |

እንደነዚህ ያሉት ይዘትን ወይም ሁኔታን ስለሚያመለክቱ የይዘት ቅፅሎች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ አፈጣጠራቸው እንደሚከተሰው ነው፡፡

ስርዓት 8፣

| | | |
|---|---|---|
| [ተ-ተ-ተ-] | ——→ | [ተኧተተአተ]<br>የይዘት ቅፅል |

እስካሁን ያየናቸው ልዩ ልዩ ስርዓቶች በቋዋንቋዋው ውስጥ በጥቅም ላይ የሚገኙትን ስሞችና ቅፅሎች ውስጣዊ አቀነጃጀት እንድንመረምር ብቻ ሳይሆን፣ በጥቅም ላይ ያልዋሉ አዳዲስ ቃላትንም እንድንፈጥርና ለተለያዩ አዳዲስ ፅንሰ-

ሀሳብ ወይም ክስተት ስያሜ በማድረግ አንድንጠቀምባቸው የሚያስችሉ ናቸው። ስርዓቶቹ የተወሰኑ ቢሆኑም ሊፈጥሩት የሚችሉት የቃላት መጠን ወሰን የለውም። ከላይ በተሰጠው ስርዓት መሰረት እንደ ዘላል፣ ደባቅ፣ ቀዳድ፣ ወዘተ፣ ያሉ አዳዲስ ቅፅሎችን መፍጠርና ለአዳዲስ ቅፅላዊ ፅንሰ-ሀሳብ መግለጫ ማድረግ ይቻላል። ለምሳሌ፣ በየቦታው እየዞረ የሀሰት ወሬ የሚነዛን ሰው ቀዳድ ልንለው እንችላለን። ወሬ የሚቀድ ማለት ነው። ወደሚቀጥለው ክፍል እንሂድ።

## ውልድ ግሶች

ባለፉት ሁለት ንዑስ ክፍሎች ውስጥ ስሞች ከቅፅሎችና ከግስ ስሮች፣ ቅፅሎችም ከስሞችና ከስሮች እንዴት እንደሚመሰረቱ አይተናል። በጥቅሉ ሲታይ፣ የቃላቱ የአመሰራረት ስርዓቶች አንድን የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለውጡ ናቸው። ስምን ወደ ቅፅል፣ ቅፅልን ወደ ስም፣ እንዲሁም ግስን ወደ ስም ወይም ወደ ቅፅል የሚለውጡ ስለሆኑ፣ ክፍል ለዋጭ ስርዓቶች ልንላቸው እንችላለን። በዚህም ምክንያት ክፍል ከማይለውጡት የርባታ ስርዓቶች ይለያሉ።

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ግሶች እንዴት እንደሚመሰረቱ እንመለከታለን። የግሶች የአመሰራረት ስርዓት ከስሞችና ከቅፅሎች የአመሰራረት ስርዓት የተለየ ነው። ስሞችና ቅፅሎች ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ሲመሰረቱ፣ ግሶች ግን ከሌሎች የቃላት ክፍሎች ላይ ሳይሆን፣ በአብዛኛው ከስር ላይ በእናባቢዎች አማካኝነት ከሚመሰረቱ አሀዶች ላይ ነው። አሀዶቹ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ አዕማድ በመባል ይታወቃሉ። አዕማድ ቀደም ሲል አምድ አያልን ስንጠራው የነበረው ቃል የብዙ ቁጥር ነው። በሊቃውንቱ አመለካከት፣ ከየስሩ ላይ ሊመሰረቱ የሚችሉት የአዕማድ አይነቶች ሰባት ናቸው። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| አደራጊ | ተደራጊ | 1 |
| አስደራጊ | | |
| አዳራጊ | ተዳራጊ | |
| አደራራጊ | ተደራራጊ | |

በእኔ እምነት የአዕማዱ አይነት በነዚህ ብቻ የሚወሰን አይመስለኝም። ያልተጠቀሱ አዕማድ ያሉ ይመስለኛል። ከነዚህም አንዱ የአንድን ድርጊት መደጋገም ወይም መዘውተር የሚያመለክተው ዕስር አምድ ነው። ደጋጋሚ ወይም ደራራጊ አምድ ልንለው እንችላለን። ሌላው ድርጊትን የሚያመለክት ሊሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ መዳረግን የሚያሳይ ነው። ዳራጊ አምድ ሊባል ይችላል። በዚህ መሰረት የአዕማዱ ዝርዝር የሚከተለው መሆን አለበት።

| | | |
|---|---|---|
| ደራጊ<br>አድራጊ<br>አስደራጊ | ተደራጊ | 2 |
| ዳራጊ<br>አዳራጊ (ሀ)<br>አዳራጊ (ለ) | ተዳራጊ | |
| ደራራጊ<br>አደራራጊ (ሀ)<br>አደራራጊ (ለ) | ተደራራጊ | |

ከዝርዝሩ እንደሚታየው 12 የአዕማድ አይነቶች አሉ፡፡ ከዚህ ቀጥሰን የአያንዳንዳቸውን ዝርዝር የአመሰራረት ሁኔታ እንመልከታለን፡፡

## ደራጊ አዕማድ

ደራጊ አዕማድ የሚባሉት ያለምንም መሰራች ቅጣይ ምዕላድ በቀጥታ በየግሱ ሰር ውስጥ /-ኧ-/ የሚለውን እናባቢ በማስገባት የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ የሚገባው እናባቢ ቁጥር እንደ አዕማዱ አይነትና እንደ ተናባቢው ቁጥር ይለያያል፡፡ ለባለ ሶስት እግር ቀዳማይ አንቀፅ የሚያስፈልገው እናባቢ ሁለት ሲሆን፣ ለባለ አራት እግር የሚያስፈልገው ሶስት ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

| <u>ሰር</u> | <u>ቀዳማይ አዕማድ</u> | | 1 |
|---|---|---|---|
| /ሰ-ብ-ር/ | /ለኧብብኧር-/ | ሰበር- | |
| /ል-ም-ን/ | /ልኧምምኧን-/ | ለመን- | |
| /ፍ-ል-ግ/ | /ፍኧልልኧግ-/ | ፈለግ- | |
| /ድ-ም-ር/ | /ድኧምምኧር-/ | ደመር- | |
| /ጅ-ም-ር/ | /ጅኧምምኧር-/ | ጀመር- | |
| /ድ-ግ-ስ/ | /ድኧግግኧስ-/ | ደገሰ- | |

እንደነዚህ ያሉ ዕሰር የቀዳማይ አንቀፅ አዕማድ ናቸው፡፡ ነፃ የሚሆኑት መደብ አመልካች ቅጣዮችን ሲያስከትሉ ነው፡፡ ለምሳሌ ሰ<u>በር-</u> የሚለው አምድ አንደኛ መደብ አመልካች የሆነውን /-ከኡ/ን ሲያሰከትል፣ <u>ሰበር-ኩ</u> ይሆናል፡፡ ይህም ዕሰር ሳይሆን፣ ነፃ የቀዳማይ አንቀፅ ግስ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ የእነዚህ አይነት ግሶች ያለቀ ድርጊትን ስለሚገልፁ፣ ደራጊ አዕማድ ብለናቸዋል፡፡ ድርጊቱ ያለቀ መሆኑን የሚገልፁት በሰሩ መካከል በሚገባው እናባቢና በቅድመ-

መድረሻው ተናባቢ ድምፅ ጥብቀት ነው። ስርዓተ-ፍጥረታቸው እንደሚከተለው ነው።

ስርዓት 1፣

| | | |
|---|---|---|
| ስር | | ደራጊ አምድ |
| [1 - 22 - 3] | ⟶ | [1ኧ22ኧ3-] |
| /ድ - ግግ - ስ-/ | | [ድኧግግኧስ-] |

በመጀመሪያው ቅንፍ ውስጥ የሚታዩት ቁጥሮች የሰሩን ተናባቢ ድምፆች ይወክላሉ። ስሩ ከሶስት የተለያዩ ተናባቢዎች እንደተመሰረተ ያመለክታሉ። አምዱ ከመነሻውና ከቅድመ-መድረሻው ተናባቢ ቀጥሎ በሚገኘው ክፍት ቦታ ላይ /-ኧ-/ የሚለውን አናባቢ በመጨመርና ቅድመ-መድረሻውን ተናባቢ በማጥበቅ ይመሰረታል። ቅድመ-መድረሻው ተናባቢ ጥብቅ መሆኑን ለማመልከት ቁጥሩን ደግመን እንፅፈዋለን።

ደራጊ ግሶች ድርጊትን ስለሚያመለክቱ በጥቅሉ ገቢር ግሶች ሊባሉ ይችላሉ። እንደ መዋቅራዊ ባህሪያቸውም ሳቢ ወይም ኢሳቢ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ሳቢ የሚባሉት ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ጋር የሚዋቀሩት ሲሆኑ፣ ኢሳቢ የሚባሉት ይህን ማድረግ የማይችሉት ናቸው። ዝርዝር ልዩነታቸውን በክፍል ስስት እንመለከተዋለን፤ ለአብነት ግን የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) እስቴር [ልብስ ተኩሰች] 2
(ለ) እስቴር [---- ሳቀች]

በመጀመሪያው ምሳሌ ተኩሰች የሚለው ግስ ልብስ ከሚለው መሙሊያ ስም ጋር ተዋቅሮአል። ስሙ የግሱ ተሳቢ፣ ማለትም ተጎታች ነው። በሁለተኛው ምሳሌ ግን ሳቀች የሚለው ግስ ያለምንም ተሳቢ ብቻውን ይታያል። ሁለቱም ግሶች ገቢር ይሁኑ እንጅ፣ የመጀመሪያው ብቻ ሳቢ ነው። በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ተሻጋሪ ግስ በመባል ይታወቃል። ድርጊቱን ወደ ተሳቢው ስም የማሻገር ባህሪ አለው።

## አድራጊ አዕማድ

አድራጊ አዕማድ የሚባሉት አንድ ሰው አንድን ድርጊት እሱ ራሱ በሌላ ነገር ላይ መፈፀሙን የሚያመለክቱ ናቸው። አመሰራረታቸው ከደራጊ አዕማድ ላይ /አ-/ የሚል ምዕላድ በመጨመር ነው። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

| ደራጊ | አድራጊ | 3 |
|---|---|---|
| ቀመሰ- | አ-ቀመሰ-[6] | |
| በል- | አ-በል- | |
| ሰበሰ- | አ-ሰበሰ- | |
| ወረድ- | አ-ወረድ- | |
| ወጥ- | አ-ወጥ- | |

ስርዓቱ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ስርዓት 2፣

| ደራጊ | | አድራጊ |
|---|---|---|
| [1ኧ22ኧ3-] | ⟶ | [አ-1ኧ22ኧ3-] |
| /ቅኧምምኧሰ-/ | | [አቅኧምምኧሰ-] |

## አስደራጊ አዕማድ

አስደራጊ አዕማድ የሚባሉት አንድ ሰው አንድን ድርጊት በራሱ ሳይሆን፣ በሌላ ሰው አማካኝነት ማስፈፀሙን ያመለክታሉ፡፡ የሚመሰረቱት ከደራጊ ወይም ከአድራጊ አዕማድ ላይ /አስ-/ የሚል ምዕላድ በመጨመር ነው[7]፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| ደራጊ | አስደራጊ | 4 |
|---|---|---|
| ዘረፍ- | አስ-ዘረፍ- | [አዝዝኧርርኧፍ-] አዘረፍ- |
| ገረፍ- | አስ-ገረፍ- | |
| ፈተል- | አስ-ፈተል- | |
| ገዝ- | አስ-ገዝ- | |
| ቆረጥ- | አስ-ቆረጥ- | |
| ተከል- | አስ-ተከል- | |
| ጀመር- | አስ-ጀመር- | |
| ወጥ- | አስ-ወጥ- | |
| ሰከ- | አስ-ሰከ- | |
| ቀየር- | አስ-ቀየር- | |

ስርዓቱን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

---

[6] በዚህ ክፍል የምናያቸው ቃላት ቅባይ ብቻ የሚፈልጉ በመሆናቸው ቅርፃቸውን በስርዓተ ፅሀፈት እናመለከታለን፡፡
[7] ስዚህ ጉዳይ ላይ ለተለየ አመልካከት በዛ (1998)ን ይመልከቱ፡፡

ያስጥርጥር አስደራጊ ነው፡፡ መሰረቱ <u>አስቴር ስራ ያዘች</u> የሚል ደራጊ አረፍተ ነገር ነው፡፡

ከዚህም የምንረዳው ደራጊ፣ አድራጊ፣ አስደራጊና ተደራጊ አዕማድ በቁጥር የተለያዩ ስማዊ ሀረጎች ጋር የሚጥቀሩ መሆናቸውን ነው፡፡ በዚሁ መሰረት እያንዳንዱን ባስ አንድ፣ ባለ ሁለት እና ባለ ሶስት ስማዊ ሀረግ አምድ እያለን እንደ ባህሪው ልንለየው እንችላለን፡፡

## ተደራጊ አዕማድ

ተደራጊ አዕማድ የሚባሉት አንድ ድርጊት በአንድ ነገር ላይ መፈፀሙን የሚያመለክቱ ሲሆን፣ የሚመሰረቱት ከደራጊ አዕማድ መነሻ ላይ /ተ-/ የሚል የተደራጊነት ምዕላድ በማስገባት ነው፡፡ የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው፡፡

| <u>ደራጊ</u> | <u>ተደራጊ</u> | 7 |
|---|---|---|
| ገደል- | ተ-ገደል- | |
| በል- | ተ-በል- | |
| ጠጥ- | ተ-ጠጥ- | |
| ጀመር- | ተ-ጀመር- | |
| ፈረም- | ተ-ፈረም- | |
| ወቀስ- | ተወቀስ- | |

ስርዓቱን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

ስርዓት 4፣

| | | |
|---|---|---|
| ቅጣይ | ደራጊ | ተደራጊ |
| [ትኧ- + | [1ኧ22ኧ3-] | [ትኧ-1ኧ22ኧ3-] |
| | /ግኧድድኧል-/ | [ትኧግኧድድኧል-] |

የእነዚህ አይነት ግሶች መጥቅራዊ ባህሪ ከአንድ ተደራጊ ከሆነ ስማዊ ሀረግ ባለቤት ጋር ተጣቅር እንደሚከተሉት ያሉ አረፍተ ነገሮችን መመስረት ነው፡፡

(ሀ) ቡና ተፈላ 8

(ለ) እንቡሳው ተገደለ

የእነዚህ አይነት እዕማድ አረፍተ ነገር የሚመሰርቱት ከሶስት ሰማዊ ሀረግ ጋር እንደሚከተለው በመዋቀር ነው፡፡

(ሀ) ካሳ እስቴርን እንጨት አስባበራት 18
(ለ) እስቴር ገነትን ቤት አፈላሰገቻት

## ተደራራጊ እዕማድ

እነዚህ ከደራራጊ እዕማድ ላይ /ተ-/ የሚለውን የተደራራጊነት ምዕላድ በመቀጠል የሚመሰረቱ ናቸው፡፡ ተግባራቸው፣ ሰዎች ርስበርሳቸው አንድ ነገር የሚደራረጉ መሆናቸውን ማመልከት ነው፡፡ ድርጊቱ ተደጋጋሚ መሆኑን ለማመልከት፣ የየእምዱ ሁለተኛ (ከግራ ወደቀኝ) ተናባቢ ይደገማል፡፡ አንዱ የሌላው ድርጊት ተጠቂ መሆኑን ለማመልከት /ተ-/ በየእምዱ መነሻ ላይ ትገባለች፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| <u>ደራራጊ</u> | <u>ተደራራጊ</u> | 19 |
|---|---|---|
| ገዳደል- | ተ-ገዳደል- | |
| ፈራረም- | ተ-ፈራረም- | |
| ሰዳደብ- | ተ-ሰዳደብ- | |
| ፈላሰግ- | ተ-ፈላሰግ- | |

ስርዓታቸውን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

ስርዓት 11፣

| ቅጥይ | ደራራጊ | | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|
| [[ትኧ-] + | [1ኧ2አ22ኧ3-]] | → | [ትኧ-1ኧ2አ22ኧ3-] |
| | /ሰኧድአድድኧብ-/ | | [ትኧሰድአድድኧብ-] |

የተደራራጊ እዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ አንድ አፀፋዊ ተውላጥ ካለው የብዙ ቁጥር ሰማዊ ሀረግ ጋር አረፍተ ነገር መመስረት ነው፡፡ የሚከተሉትን እናስተውል፡፡

(ሀ) ልጆቹ ርስበርሳቸው ተሰዳደቡ 20
(ለ) ልጆቹ ርስበርሳቸው ተደባደቡ

ርስበርስ የሚለው አፀፋ መዋቅራዊ ዝምድና ከግሱ ጋር ሳይሆን፣ ከባለቤቱ ሰማዊ ሀረግ ማለትም ልጆቹ ከሚለው ስም ጋር ነው፡፡

**የእደራራጊ እዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ ክሰለት ስማዊ(...) [illegible] ያሉ እረፍተ ነገሮችን መመስረት ነው፡፡**

**እስካሁን የተመለከትናቸው [illegible] ናቸው፡፡ የድርጊት እዕማድ ልንላቸው እንችላለን፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ባህሪን የሚያመለክቱ እዕማዶችን [illegible] እንመለከታለን**

## የባህሪ እዕማድ

**ባህሪያዊ እዕማድ በቅርፃቸው ተዳራጊ እዕማድን ይመስላሉ፡፡ በትርጉማቸው ግን አንድ ሰው [illegible] ብሎ፣ አሰበ ወይም ልምድ ሆኖበት የሚፈፅመው መሆኑን [illegible] ባየናቸው በዳራጊ እዕማድ መሰረት ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡**

| ዳራጊ | ባህሪያው | |
|---|---|---|
| /-ሰእድድኧብ-/ | /ትኧ-ሰእድድኧብ-/ | 23 |
| [illegible] | /ትኧ-ንእግግኧር-/ | |
| /-ንእክክኧስ-/ | /ትኧ-ንእክክኧስ-/ | |

**ስርዓቱን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡**

**ስርዓት 13፣**

**ባህሪያዊ እዕማድ ሳቢ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡**

**ካሳ ሰው ተሳደበ** 24

**የዚህ [illegible] ተለቤት ካሳ ነው፡፡ [illegible] ድርጊቱን የፈፀመው [illegible] አሰበ ነው፡፡ ተሳዳቢው [illegible] አይታወቅም፡፡ ካሳ በድንገት ተሳድቦ ቢሆን ኖሮ፣ የግሱ ቅርፅ ደራጊ ይሆን ነበር፡፡ እንደማንኛውም**

እነዚህ የሁኔታ ተውሳከ ግሶች ናቸው፡፡ አንድ ድርጊት እንዴት እንደተፈፀመ ያመለክታሉ፡፡ መዋቅራዊ ባህሪያቸው ከግስ ጋር መግባት ነው፡፡ ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) ልጁ ክፉኛ ወደቀ[10] 3
(ለ) ምንኛ ጠግቦአል ጃል!

ከነዚህ በተጨማሪ ምናልባት ተውሳከ ግስ ልንላቸው የምንችለው እንደሚከተሉት ያሉትን ነው፡፡

የሁዋሊት 4
የምብርክክ
የጎድን
የጎሪጥ

እንደነዚህ ያሉት ከስሞች ላይ /የ-/ን በማስቀደም የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ቅርጻቸው የአገናዛቢ ስማዊ ሀረግን ቅርፅ ይመስላል፡፡ ተግባራቸው ግን ባለገንዘብን ሳይሆን፣ አደራረግን ማመልከት ነው፡፡ ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) ልጁ [[የሁዋሊት] ሄደ] 5
(ለ) ሰካራሙ ሰውየ [[የጎድን] ይሄዳል]
(መ) ልጁ [[የጎሪጥ] አየኝ]

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የሁዋሊት፣ የጎድን እና የጎሪጥ የሚሉት ተውሳከ ግሶች በግሶቹ የተጠቀሰው ተግባር እንዴት እንደተፈፀመ ያመለክታሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ

---

[10] ክፉኛ ከሚለው በስተቀር፡ ሌሎቹ ተውሳከ ግሶች ለአዲስ አበባው ሰው እንግዳ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ ይሁን እንጅ፣ በገጠር፣ በተለይም በጎንደርና በወሎ፣ እጅግ የተለመዱ ናቸው፡፡ በአዲስ አበባ ፣

ክፉኛ ታሞአል

ከማለት ይልቅ፣ በሀይል ወይም በጠና ታሞአል፣

ምንኛ ጠግቦአል

ይሆነኑ ሁኔታ በመስተዋድዳዊ ሀረግ መግለፅ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ <u>የሁዋሊት</u> በሚለው ፋንታ <u>ወደ ሁዋላ</u> የሚለውን መስተዋድዳዊ ሀረግ በመተካት፣

ልጁ [[ወደ ሁዋላ] ሄደ] 6

ማለት ይቻላል፡፡

በዚህና በ5(ሀ) በተጠቀሰው ምሳሌ መካከል የትርጉም ልዩነት ያለ አይመስልም፡፡ ይህ ከሆነ፣ በየተውሳከ ግሉ ውስጥ የምትገኘው /የ-/ በየመስተዋድዳዊ ሀረጉ ውስጥ የሚገኘው መስተዋድድ አቻ ነች፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህ ለመሆኑ ከሚከተሉት ምሳሌዎችም መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) የጎጃም መንገደኛ 7
(ለ) ወደ ጎጃም የሚሄድ መንገደኛ

(ሀ) የጎጃም አረቄ 8
(ለ) ከጎጃም የመጣ አረቄ

(ሀ) የጋን ጠላ 9
(ለ) በጋን የተጠመቀ ጠላ

በግልፅ እንደሚታየው በ(ሀ) ውስጥ /የ-/ የነበረው በ(ለ) ውስጥ *ወደ*፣ *ከ* እና *በ* ሆኖአል፡፡ ይህም እንደ የሁዋሊት ባሉት ተውሳከ ግሶች መነሻ ላይ የምትታየው /የ-/ የመስተዋድድ ምትክ ወይም አቻ ነች የሚለውን ሀሳብ የሚያጠናክር መረጃ ነው፡፡ ጉዳዩ ተጨማሪ ጥናት ይፈልጋል፡፡ ስጊዜው ግን እንደ <u>የሁዋሊትና</u> <u>የጎድን</u> ያሉት ከስም የሚመሰረቱ ተውሰከ ግሶች ናቸው፣ ለማለት የሚቻል ይመስላል፡፡ ያም ሆኖ፣ እንደ <u>ጎረጥ</u> እና <u>ሁዋሊት</u> የመሳሰሉ ቃላት ከፍል ስም መሆኑን በርግጠኝነት መናገር ያስቸግራል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ቃላት ስም ካልሆኑ፣ የ- የሚለው ምዕላድ የመስተዋድድ አቻ ነው ለማለትና እንደ <u>የሁዋሊት</u> ያሉ እሀዶችም መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው በሎ ስመደምደም ያስቸግራል፡፡

---

ከማለትም፣ <u>እንዴት ጠግበአል</u> ማለት የተለመደ ነው፡፡ በሀይል እና እንዴት የሚሉት ግን ተራ ተውሳከ ግስ ሳይሆኑ፣ ወደፊት በዝርዝር እንደምናየው፣ ሀረጎችና ጥምሮች ናቸው፡፡

እስካሁን በዚህ ንዑስ ክፍል በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልለዋለን፡፡ በመሰረቱ ለማየት የሞከርነው በአራቱ የቃላት ክፍሎች ውስጥ የሚገኙትን ቃላት የአመሰራረት ስርዓት ነው፡፡ ስርዓቱ ያንዱ ክፍል ቃላት ከሌላው ክፍል ቃላት ላይ እንዴት እንደሚመሰረቱ ያሳያል፡፡ እያንዳንዱ ስርዓት የሚፈጥረው የቃላት መጠንም ወሰን የለውም፡፡ ርግጥ፣ ውይይታችን በአብዛኛው ያተኮረው በምንጠቀምባቸው ቃላት ውስጣዊ አቀነጃጀት ላይ ነው፡፡ ያቀነጃጀቱ ስርዓት ጥቅም ላይ ያልዋሉ እጅግ ብዙ ቃላትንም ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይህን ስርዓት በወጉ ከተረዳን፣ ለአዳዲስ ፅንስ-ሀሳብ፣ ቁሳቁስ፣ ድርጊት፣ ወዘተ፣ መግለጫ የሚሆን ቃል ፍልጋ ወደ ሌላ ቋንቋ መሄድ አያስፈልገንም፡፡ በስርዓቱ መሰረት ከራሱ ከቋንቋው ማውጣት ይቻላል፡፡ ይህ ለአማርኛ ብቻ ሳይሆን፣ ማንኛውም የሀገራችን ቋንቋ የሚገጥመውን የሳይንስና የስነ ጥበብ ፅንስ-ሀሳብ መግለጫ የሚሆኑ ቃላት ለመፈልፈል የሚያስችል ስርዓት ነው፡፡

ቃላትን የምናወጣው በዚህ ንዑስ ክፍል እንዳየነው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው የቋንቋውን የድምፅ አሰካክ ስርዓት በመከተል ፎኒሞችን ከፎኒሞች ጋር በማቀናጀት ነው፡፡ ለምሳሌ፣

[ተእተተ] 10

በሚል የድምፅ አሰካክ ስርዓት እንደ፣

| | | |
|---|---|---|
| [ፍእርድ] | ፍርድ | 11 |
| [ጥእብስ] | ጥብስ | |
| [ልእብስ] | ልብስ | |
| [ውእርስ] | ውርስ | |

ያሉ ነባር ቃላትን አፈጣጠር አይተናል፡፡ በዚሁ መሰረት እንደ፣

| | | |
|---|---|---|
| [ውእርት] | ውርት | 12 |
| [ቅእርት] | ቅርት | |
| [ስእርት] | ስርት | |
| [ዝእልት] | ዝልት | |

ያሉ አዳዲስ ቃላትንም መፍጠር ይቻላል፡፡ እንደዚህ እያደረጉ በመፍጠር ለአዳዲስ ፅንሰ-ሀሳብና ክስተት ወይም ድርጊት ለያሜ ማግኘት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው መንገድ ምዕላድን ከምዕላድ ጋር ማገናኘት ነው፡፡ በዚህ መንገድ የሚፈጠሩ ቃላት ለነ-ምዕላዳዊ ናቸው፡፡ መስረታቸው ምዕላድ ነውና፡፡ በዚህም አካሄድ በርካታ ውልድ ስሞችን፣ ቅፅሎችንና ግሶችን እይተናል፡፡ ስሞቹ ከቅፅሎች፣ ከነባር ስሞችና፣ ከስሮች፤ ቅፅሎች ከስሞችና ከስሮች፤ ውልድ ግሶች ደግሞ ከስሮችና ከተለያዩ እዕማድ ላይ እንደሚመሰረቱ እይተናል፡፡ እነዚህ ዘረ-ብዙ ወይም ረቢ ያልናቸው የቃላት ክፍሎች ናቸው፡፡ ተውሳከ ግስ የሚባለው ክፍል እንደነዚህኞቹ በርካታ ቃላት እንደሌለው፣ ስለዚህም ተውሳክ ግሳዊ ተግባራት በሀረጎች፣ በጥገኛ አረፍተ ነገሮችና በአደራረግ ግሶች እንደሚገለፅ አይተናል፡፡

በዚህ መንገድ አዳዲስ ቃላት እንዴት መመስረት እንደሚቻልም ገልፀናል፡፡ ለአብነት እንደገና የሚከተለውን እንመልከት፡፡

| <u>ስር</u> | <u>እምድ</u> | <u>ቃል</u> | 13 |
|---|---|---|---|
| /ም-ር-ት/ | /ምኧርርኧት-/ | /ምኧርርኧት-ኧ/ | መረተ |
| | /አ-ምኧርርኧት-/ | /አ-ምኧርርኧት-ኧ/ | አመረተ |
| | /አ-ምርአት-/ | /አ-ምርአት-ኢ/ | አምራች |

እነዚህ የምናውቃቸው ቃላት ናቸው፡፡ በዚሁ መስረት የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት፡፡

| <u>ስር</u> | <u>እምድ</u> | <u>ቃል</u> | 14 |
|---|---|---|---|
| /ው-ር-ት/ | /ውኧርርኧት-/ | /ውኧርርኧት-ኧ/ | ወረተ |
| | /አ-ውኧርርኧት-/ | /አ-ውኧርርኧት-ኧ/ | አወረተ |
| | /አ-ውርአት-/ | /አ-ውርአት-ኢ/ | አውራች |
| | | /ውኧርኧት/ | ወረት |

ከነዚህ መካከል ወረት የሚለው ብቻ በጥቅም ላይ ይገኛል፡፡ ሌሎቹ በጥቅም ላይ ገና አልዋሉም፡፡ ስርዓቱን ተከትለን የፈጠርናቸው አዳዲስ ቃላት ናቸው፡፡ <u>አውራች</u> የሚለው ኢንቬስተር የሚለውን የውጭ ቃል ሊተካ የሚችል ጥሩ ስያሜ ነው፡፡ በዚሁ አካሄድ አስፈላጊውን ቃል እየፈጠሩ መጠቀም ስለሚቻል፣ ቃላት ፍለጋ ወደ ሌላ ቋንቋ መሄድ አያስፈልግም፡፡ የሰው እንጅ የቋንቋ ድሀ የለውም፡፡ አያንዳንዱ ቋንቋ የማያልቅ ማዕድን ነው፡፡ በዚህም ከዚህ ክፍል ጋር እንሰያያለን፡፡

# መልመጃ

1. የሚከተሉትን ስሞች ወደ ቅፅል ይለውጡ፡፡
   ጥፋት፣ ጥጋብ፣ ወረት፣ ሰበብ

2. ጥፋት ብሎ ጥፋተኛ ማለት ይቻላል፡፡ ከፋት ብሎ ከፋተኛ ማለት አይቻልም፡፡ ለምን?

3. /-እም/ በሚለው ምዕላድ የሚፈጠሩ ሶስት ቅፅሎችን ይጥቀሱ፡፡

4. ከነዚህ ቅፅሎች ላይ ምን አይነት ስሞች እንደሚፈጠሩ ምሳሌ እየሰጡ ያብራሩ፡፡

5. ስሞችን ወደ ቅፅል የሚለውጡ ምዕላዶች የቃል ክፍል ምን ይመስልዎታል? ለምን?

6. / ው - ር - ድ/ ከሚለው ስር ላይ

   (ሀ) አንድ የቀዳማይ፣ የካልዓይ፣ የቀጣይና የጨራሽ እምድ
   (ለ) አንድ ስም
   (መ) ሁለት የተላያዩ ቅፅሎችን ይመስርቱ፡፡

7. /ሰ-ብ-ር/ ከሚለው ስር ላይ፣

   የተለያዩ ስስር እምዶችን ይመስርቱና በነሱ ላይ የተለያዩ ቅጥዮችን በመጨመር ቅፅል፣ ስምና እና የቀዳማይ እንቀፅ ግስ ይመስርቱ፡፡

8. <u>መጥረጊያ</u> የሚለውን ስም የአመሰራረት ስርዓት ያሳዩ፡፡

9. በቀጥታ ከስም እምድ ላይ የተመሰረተ ግስ እንዲሁም ከግስ እምድ ላይ የተመሰረተ ስም ይስጡ፡፡

10. ደከመ፣ ደካማ እና ድካም የሚሉትን ቃላት ክፍል ይግለፁ፣ አመሰራረታቸውንም ያሳዩ፡፡

11. /ግ-ን-ፍ/ ከሚለው ስር ላይ አንድ ስም፣ ቅፅልና አንድ የቀዳማይ እንቀፅ ግስ ይመስርቱ፡፡ ለመሰረቱአቸው ቃላት ትርጉም ለመስጠት ይሞክሩ፡፡

12. የርባታ ምዕላዶች ከመሰራች ምዕላዶች እንዴት እንደሚለዩ ምሳሌ እየሰጡ ይግለፁ፡፡

# ጥመራ

ባለፈው ንዑስ ክፍል፥ ቃላት ከምዕላድና ከቃላት ላይ እንዴት እንደሚመሰረቱ ለማሳየ፡ት ሞክረናል፡፡ ከነባር ቃላት ላይ የተለያዩ መሰራች ምዕላዶችን በመቀጠል አዳዲስ ቃላትን መፍጠር እንደሚቻል ተመልክተናል፡፡ ስርዓቱን ቅጠላ ልንለው እንችላለን፡፡ ይህም አንዱና ምናልባትም ዋነኛው የቃላት ምስረታ ስርዓት ነው ልንል እንችላለን፡፡ ሌላው ስርዓት <u>ጥመራ</u> ነው፡፡ ይህ ስርዓት ከነባር ቃላት ላይ ዕስር ምዕላዶችን የሚቀጥል ብቻ ሳይሆን፣ ነባር ወይም ውልድ ቃላትን ከነባር ወይም ከውልድ ቃላት ጋር በማጣመር፣ ማስትም በማቀናጀት፣ ጥምር ቃላትን የሚፈጥር ነው፡፡ የአጠማመሩን ዝርዝር ሂደት በዚህ ንዑስ ክፍል እንመለከታለን፡፡ ካሁን በፊት እንዳደረግነው ሁሉ፣ አሁንም ከስም በመጀመር የእያንዳንዱን የቃላት ክፍል የጥመራ ስርዓት በየተራ እንመረምራለን፡፡

## *ጥምር ስሞች*

በጥመራ ስርዓት የሚፈጠሩ ስሞች ጥምር ስሞች ይባላሉ፡፡ አፈጣጠራቸውም ከስሞችና ከግሶች ነው፡፡ ከስሞች የሚፈጠሩት እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| <u>ስም</u> | <u>ስም</u> | <u>ጥምር ስም</u> | 1 |
|---|---|---|---|
| ቤት | ክርስቲያን | ቤት-ኧ-ክርስቲያን | ቤተ ክርስቲያን |
| ሊቅ | መንበር | ሊቅ-ኧ-መንበር | ሊቀ መንበር |
| በትር | መንግስት | በትር-ኧ-መንግስት | በትረ መንግስት |
| ሰብል | ወንጌል | ሰብል-ኧ-ወንጌል | ሰብለ ወንጌል |

ከመዘርዝሩ እንደሚታየው ሁለት ነባር ስሞች እየተጣመሩ አንድ ጥምር ስም ለመሆን ችለዋል፡፡ በየጥምሩ የመጀመሪያ ቃል መድረሻ ላይ /-ኧ-/ የሚል ቅጣይ አለ፡፡ ይህ ቅጣይ ሁለቱ ስሞች ተጣምረው አንድ አካል መሆናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህም አጣማሪ ምዕላድ ልንለው እንችላለን፡፡ በእሉ አማካኝነት የሚጣመሩትን ስሞች ተጣማሪ እንላቸዋለን፡፡ አጣማሪው ምዕላድ ከሌለ፣ ስሞቹ ጥምር መሆናቸው ይቀርና ዝምድና የሌላቸው ሁለት ተከታታይ ስሞች ብቻ ይሆናሉ፡፡ ጥምር ሲሆኑ የሚከተሉትን ስርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 1፣

$$[\text{ስም}]_{\text{ስም}} + [\text{ኧ}]_{\text{አጣማሪ}} + [\text{ስም}]_{\text{ስም}} \longrightarrow [\text{ስም-ኧ-ስም}]_{\text{ጥምር}}$$

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>ቤት ክርስቲያኑ</u> የሚለውን ጥምር <u>ቤቱ</u> የሚለው የጥምሩ የመጀመሪያ ቃል፣ ማለትም ተጣማሪ፣ ተክቶታል፡፡ ይህም ሲሆን የአረፍተ ነገሩ መሰረታዊ ትርጉም አልተለወጠም፡፡ በሁለቱም አረፍተ ነገሮች የተዘረፈው <u>ቤት</u> ነው፡፡ ነገር ግን ጥምሩን <u>ቤቱ</u> የሚለው ተጣማሪ ሳይሆን፣ <u>ክርስቲያኑ</u> የሚለው ተጣማሪ ቢተካው ኖሮ፣ ውጤቱ እንደሚከተለው ይሆን ነበር፡፡

ክርስቲያኑ ተዘረፈ 8

ይህ አረፍተ ነገር የተስተካከለ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በመሰረታዊ ትርጉሙ በተራ ቁጥር 7(ሀ) ከሚታየው ምሳሌ ትርጉም የተለየ ነው፡፡ ምክንያቱም በተራ ቁጥር 7(ሀ) ውስጥ የተዘረፈው <u>ቤተ</u> <u>ክርስቲያኑ</u> እንጅ <u>ክርስቲያኑ</u> አይደለም፡፡ በምሳሌ ተራ ቁጥር (8) ግን የተዘረፈው ቤቱ ሳይሆን፣ ክርስቲያኑ ነው፡፡ ክርስቲያን የሚለው ቃልሙሉ ጥምሩን ተክቶ ሲገባ፣ በአረፍተ ነገሩ ትርጉም ላይ ለውጥ አስከትሎአል ማለት ነው፡፡ ይህን የሚያደርግ ተጣማሪ፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ የጥምር መሪ ሊሆን አይችልም፡፡ መሪ ሊሆን የሚችለው፣ ያለምንም መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ ጥምሩን እየተካ ሊገባ የሚችለው ተጣማሪ ብቻ ነው፡፡ በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ፣ ይህን ሊያደርግ የሚችለው <u>ቤት</u> የሚለው ተጣማሪ ስለሆነ፣ እሱ የጥምሩ መሪ ነው፡፡ የዚህ የቃል ክፍልም ስም ስለሆነ፣ ከጥምሩ የቃል ክፍል ጋር አንድ ነው፡፡

<u>ክርስቲያን</u> የሚለው ተጣማሪ ቃል በጥምሩ ውስጥ ያለው ተግባር ምንድን ነው? የሚል ጥያቄም ማንሳት ይቻላል፡፡ የእሱ ተግባር መሪውን ተጣማሪ መግለፅ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በምሳሌው ውስጥ <u>ክርስቲያን</u> የሚለው ተጣማሪ ቤቱ የእስላም፣ የተማሪ፣ የመጠጥ፣ ወዘተ፣ ሳይሆን፣ የክርስቲያን ብቻ መሆኑን በመግለፅ ተግባሩን መወሰን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታዩ፣ ተጣማሪዎቹ ገላጭ እና ተገላጭ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ መሪው ተገላጩ ሲሆን፣ አጃቢው ወይም ተከታዩ ገላጩ ነው፡፡ ባጭሩ የተጣማሪዎች ዝምድና የመሪና የተመሪ፣ ብሎም የተገላጭና የገላጭ ነው፡፡

ይህ ዝምድና መሪውና አጃቢው (ገላጩ) በጥምሩ ውስጥ በሚገኙበት ቦታ ይወሰናል፡፡ ለምሳሌ፡ በጠቀስነው ጥምር ውስጥ የመሪው ቦታ ከአጃቢው በስተግራ (በፊት) እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ በተጠቀሱት ሌሎች ጥምሮች የሚታየው ቅደም-ተከተልም እንደዚሁ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እንደ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ያሉ ጥምሮች በሙሉ ግራ መሪ ጥምሮች ሲባሉ ይችላሉ፡፡ ግራ መሪ ለመሆናቸው ተጨማሪ ምልክት አለ፡፡ ይኸውም /-ኧ/ የሚለው አጣማሪ ምዕላድ ነው፡፡ ይህ ምዳድ የተቀጠለው በመሪው ተጣማሪ፣ ማለትም <u>በቤት</u>፣ ላይ ነው፡፡ ያንድን ጥምር መሪ ለማወቅ ይህ ምዕላድ የሚገኝበትን ተጣማሪ ማየቱ ጠቃሚ ሲሆን ይችላል፡፡ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> በሚለው ጥምር ውስጥ /-ኧ/ የሚገኘው <u>ቤት</u> በሚለው ተጣማሪ ላይ ስለሆነ፣ ይህ ቃል የጥምሩ መሪ ነው፡፡

ግራ መሪ ጥምሮች እንዳሉ ሁሉ፣ ቀኝ መሪ ጥምሮችም አሉ፡፡ እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

| <u>ስም</u> | <u>ስም</u> | <u>ጥምር</u> | 9 |
|---|---|---|---|
| ዳቦ | ቤት | ዳቦ ቤት | |
| አየር | መንገድ | አየር መንገድ | |
| ብረት | ድስት | ብረት ድስት | |

እንደነዚህ ያሉ ጥምሮች መሪ በቀኝ በኩል ያለው ተጣማሪ ነው። ለምሳሌ፣ <u>ዳቦ ቤት</u> የሚለውን ጥምር ብንወስድ፣ መሪው <u>ቤት</u> የሚለው ተጣማሪ ነው። <u>ዳቦ</u> የዚህ መሪ አጃቢ ብሎም ገላጭ ነው። የቤቱ ተግባር ምን እንደሆን ይገልፃል። ያጠማመሩን ስርዓት እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

ስርዓት 2፣

$$[\text{ለም}] + [\text{ስም}] \longrightarrow [\underset{\text{ጥምር}}{\text{ስም}}]$$

በዚህ ስርዓት መሰረት የሚፈጠሩ፣ እንደ <u>ዳቦ ቤት</u> ያሉ ቅንጅቶች ጥምር ቃል መሆናቸውን ቀደም ሲል በጠቀስናቸው መስፈርቶች ማረጋገጥ ይቻላል። ለምሳሌ፣

ዳቦ ቤት ገዛሁ 10

ብንል፣ <u>ዳቦ ቤት</u> የሚለውን ጥምር ያለ ምንም መሰረታዊ የትርጉም ለውጥ ሊተካው የሚችለው <u>ቤት</u> የሚለው ተጣማሪ ነው። ይኸውም፣

<u>ቤት</u> ገዛሁ 11

በማለት ነው። <u>ቤት</u> በሚለው ፋንታ <u>ዳቦ</u> የሚለው ተጣማሪ ቢገባ፣ የአረፍተ ነገሩ መሰረታዊ ትርጉም ይለወጣል። ከዚህም <u>ዳቦ</u> የሚለው ተጣማሪ የጥምሩ መሪ አለመሆኑን መረዳት ይቻላል።

እንደ <u>ዳቦ ቤት</u> ያሉትን ጥምር ቃላት መሪ ለማወቅ የሚቻለው ከተጣማሪዎቹ አገባብ እንጅ፣ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ከቅርፅ አኳዋያ አይደለም። ከቅርፅ ማወቅ የሚቻለው በአጣማሪ አማካኝነት የሚጣመሩ ቃላትን መሪ ብቻ ነው። ሁኔታው ጥምር ቃላትን አጣማሪ ያላቸውና የሌላቸው ብለን በሁለት እንድንከፍላቸው የሚያደርግ ነው። አጣማሪ ያላቸውን ጥምሮች መሪ፣ በቅርፅና በአገባብ መለየት ሲቻል፣ አጣማሪ የሌላቸውን ጥምሮች መሪ በአገባብ ብቻ ማወቅ ይቻላል።

ከፍ ሲል እንደ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> ያሉት ጥምሮች ግራ መሪ ሲሆኑ፣ እንደ <u>ዳቦ ቤት</u> ያሉት ቀኝ መሪ እንደሆኑ ገልፀናል። ይህ ደግሞ በቋንቋዋ ውስጥ ሁለት አይነት ጥምሮች እንዳሉ ያሳያል። ይህ ሊሆን ይችላል ወይ? በአንድ የቃላት ክፍል ውስጥ የሚገኙ ቃላት ሲቀናጁ የሚፈጠሩት ጥምሮች ግራ ወይም ቀኝ መሪ እንጅ፣ እንዴት ከፊሎቹ ግራ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ቀኝ መሪ ሊሆኑ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ ሲነሳ ይችላል። ጥያቄው ተገቢ ነው። በመሰረቱ

ስለሚሆኑ፣ የመሪና የተመሪ ጥያቄ አይኖርም፡፡ ከኖረ፡ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ መልሱ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ለዚህ አይነቱ ሁኔታ በአማርኛ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉት እንደ ደጃዝማች፣ ግራዝማች፣ ምስሌኔ፣ ወዘተ፣ ያሉት የማዕረግ ስሞችና እንደ በሶ ብላ፣(ዝቃቅቤ)፣ ባርማሽላ፣ ወዘተ፣ ያሉ የአዝርዕት ስሞች ናቸው፡፡ የማዕረግ ስሞቹ ቅርፅ በገጠሩ አካባቢ ወደ ደጃማይ፣ ግራማይ፣ ቀኛማይ፣ ወዘተ፣ እየተለወጠ መጥቶአል፡፡ ከጥምርነት ወደ አንድ ቃልነት ተሸጋግሯል፡፡ <u>ቤተ ክርስቲያን</u> የሚለውም ቢሆን ቅርፁን ለውጦ ቤተክሲያን የሚባልበት አካባቢ አለ፡፡ በዚያ አካባቢ ጥምሩ አንድ ቃል ሆኖአል፡፡ ስለሆነም የመሪና የተመሪ ወይም ገላጭ ጥያቄ አይነሳም፡፡

በስርዓት ስስት የተመለከትነው ከስሞችና ከግሳዊ አዕማድ የሚመሰረቱ ስሞችን ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ከግሳዊ አዕማድ ላይ የሚመሰረቱትን ጥምር ስሞች እንመለከታለን፡፡

17

| <u>ግሳዊ አምድ</u> | <u>ግሳዊ አምድ</u> | <u>ጥምር</u> |
|---|---|---|
| ስርት-አ | አደር- | ስርቶ አደር |
| ወልድ-አ | ገደል- | ወልዶ ገደል |
| ወር-አ | በላ | ወሮ በላ |
| ገምጥ-አ | ወጥ- | ገምጦ ወጥ |
| ወድ-አ | ገብ- | ወዶ ገብ (ገባ) |

እንደነዚህ ያሉ ጥምሮች የሚመሰረቱት ከሁለት ግሳዊ አዕማድ ነው፡፡ የመጀመሪያው (ግራ) ተጣማሪ አምድ በቀደምት ሊቃውንት ቦዝ አንቀፅ በመባል የሚታወቀውና ባለፈው ክፍል ጨራሽ አንቀፅ ያልነው ነው፡፡ መሰረቱ ካልዓይ አንቀፅ ነው፡፡ በርባታው ስርዓት እንዳየነው፣ ይህ አንቀፅ /1ኧ23-/ የሚል ቅርፅ አለው፡፡ ለምሳሌ፣ <u>ሰብር</u>- (/ ሰኧብር-/) የሚለውን አምድ ብንመለከት፣ /1ኧ23-/ የሚለውን ስርዓት ተከትሎ የተመሰረተ አንቀፅ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በዚህ አምድ ላይ /-አ/ የሚለውን ምዕላድ ስንጨምር፣ ሰብሮ (/ ሰኧብር-አ/ = 1ኧ23-አ) የሚለውን ቦዝ አንቀፅ እናገኛለን፡፡ አንቀፁ ብቻውን የአረፍተ ነገር መጨረሻ ሊሆን ስለማይችል፣ ቦዝ የሚል ስያሜ ሊሰጠው ችሎአል፡፡ ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል፡፡

ካሳ ሰራ ሰርቶ ... 18

ይህ ያለቀ ድርጊትን እንጂ ሙሉ አረፍተ ነገርን አይገልፅም፡፡ ስለዚህም፣ <u>ካሳ ሰራ ሰርቶ</u> ምን ሆነ? የሚል ጥያቄ የግድ ያስከትላል፡፡ የጎደለ ነገር አለ ማለት ነው፡፡

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ጥምሩ ባለቤት ሆኖ በአረፍት ነገሩ መነሻ ላይ ይገኛል። በሁለተኛው ምሳሌ፣ ተሳቢ ሆኖ ከግሱ በፊት ገብቶአል። የተሳቢ ምልክት የሆነውን /-ን/ የሚለውን ምዕላድም አስከትሎአል። በሶስተኛው ውስጥ ደግሞ ታታሪ ከሚለው ቅፅል በሁዋላ (በስተቀኝ) ይገኛል። እነዚህ አገባባዊ የሆኑ የስሞች ባህሪያት ናቸው። የጥምሩን ቅርፅ ስንመለከት ደግሞ /-ኦችች/ የሚለውን የስሞችን የቁጥር ምዕላድ እንዳስከተለ እንረዳለን። ያስከተለውም በቀኙ ተጣማሪ ነው። እነዚህ አይነተኛ የስም ባህሪያት ናቸው። ስለዚህም ጥምሩ ስም ነው።

ምናልባት ቅፅላዊ የሆነ አገባብ ስላለው፣ ጥምሩ ቅፅል ነው፣ ሊባል ይችል ይሆናል። ለዚህ የሚከተለውን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [[ጎበዝ] [ልጅ]] አለው 21
(ለ) ካሳ [[ወዝ አደር] [ልጅ]] አለው

በምሳሌ (ሀ) <u>ጎበዝ</u> የሚለው ቅፅል <u>ልጅ</u> ከሚለው ስም በፊት ገብቶ ይገኛል። በምሳሌ (ለ) ይኸው ቅፅል <u>ወዝ አደር</u> በሚለው ጥምር ተተክቶ ይታያል። ይሁን እንጅ፣ <u>ወዝ አደር</u> የሚለው ጥምር ዋነኛ የቅፅል መለያ ነው ያልነውን መስፈርት አያሟላም። ይህንም ከሚከተሉት ምሳሌዎች ንፅፅር መረዳት ይቻላል።

(ሀ) በጣም <u>ጎበዝ</u> 22
(ለ) * በጣም <u>ወዝ አደር</u>

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>ጎበዝ</u> የሚለው ቅፅል <u>በጣም</u> ከሚለው መጣኝ መስተዓምር ጋር ገብቶ ቅፅላዊ ሀረግ ለመመስረት ችሎአል። በሁለተኛው ምሳሌ፣ <u>ወዝ አደር</u> የሚለው ጥምር ከዚሁ መስተዓምር ጋር ገብቶአል። ይሁን እንጅ፣ ሀረጉ ተቀባይነት የለውም። ይህም <u>ወዝ አደር</u> የሚለው ጥምር ቅፅል አለመሆኑን ያረጋግጣል። ቅፅል ቢሆን ኖሮ፣ እንደ ማንኛውም ቅፅል <u>በጣም</u> ከሚለው መስተዓምር ጋር ሲዋቀር ተቀባይነት ያለው ቅፅላዊ ሀረግ መፍጠር ነበረበት። ሁኔታው በስርዓት (4) መስረት የሚፈጠሩ ጥምሮች፣ መስረታቸው ግስ ቢሆንም፣ ክፍላቸው ስም እንጅ ግስ ወይም ቅፅል እንዳልሆነ ያረጋግጣል። ይህ ከሆነ፣ የየጥምሩ ቀኝ ተጣማሪ፣ ማለትም መሪው፣ ስማዊ ባህሪ አለው ማለት ነው። ይህም ባህሪ ከተጣማሪው ቅርፅ ላይ ሳይሆን፣ ከትርጉሙ የሚሰርፅ ነው። ቅርፁ፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የቀዳማይ አንቀፅ ነው። ይህ ከሆነ፣ አንድ ቃል በቅርፅ ግሳዊ ሆኖ በትርጉም ስማዊ ሊሆን ይችላል፣ ማለት ነው። ለዚህ ሁኔታ ተጨማሪ ማስረጃ የሚሆኑን እንደ <u>ደረሰኝ</u> እና፣ ምናልባትም፣ እንደ <u>ገጠመኝ</u> ያሉ ቃላት ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ቃላት በቅርፃቸው ግሶች ሲሆኑ፣ በትርጉማቸው ግን ስሞች ናቸው። ይህን ከሚከተሉት መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ካሳ ደረሰኝ ተቀብሎአል 23
(ለ) አስቴር ብዙ ገጠመኝ አላት

ከምሳሌዎቹ መረዳት የሚቻለው፣ ቃላቱ በአገባባቸውም ሆነ በትርጉማቸው ስማዊ መሆናቸውን ነው፡፡ እንደ ስርቶ አደር ያሉ ጥምሮች ስማዊነትም ከዚሁ አንፃር ሊታይ ይችላል፡፡ በቅርፃቸው ግሳዊ፣ በአገባባቸውና በትርጉማቸው ስማዊ ናቸው፡፡

እንደ ስርቶ አደር ባሉ ጥምሮች ውስጥ ከመጀመሪያው ተጣማሪ ላይ ተቀጥሎ የሚገኘው /-ኦ/ አጣማሪ ምዕላድ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ አገባቡ ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን ባሉ ጥምሮች ውስጥ ከሚገኘው አጣማሪ፣ ማለትም ከ/-ኧ/፣ የተለየ ነው፡፡ የዚህ አጣማሪ አገባብ ከመሪው ጋር ሲሆን፣ የ/-ኦ/ ግን ከገላጩ ጋር ነው፡፡ ይህ አገባብ ቀደም ሲል እንደ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ጥምሮችን አስመልክተን፣ ስለ መሪ ባህሪ ከሰጠነው አስተያየት ጋር ይጋጫል፡፡ ምክንያቱም ያኔ የአንድ ጥምር መሪ፣ አጣማሪው ምዕላድ የሚገኝበት፣ ማለትም የሚያርፍበት ተጣማሪ ነው፣ ብለን ነበር፡፡ እሱን ከተከተልን፣ እንደ ስርቶ አደር ያሉ ጥምሮች መሪ ስርቶ የሚለው ተጣማሪ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም አጣማሪው ምዕላድ /-ኦ/ የሚገኘው ከእሱ ጋር ነውና፡፡ ይህ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ስርቶ ገላጭ እንጅ መሪ እንዳልሆነ ቀደም ሲል አይተናል፡፡ ሁኔታው አንድን መሪ በአጣማሪው አገባብ ብቻ፣ ሁል ጊዜ በትክክል መለየት እንደማይቻል ያመለክታል፡፡

ምናልባት፣ ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል፡፡ ይኸውም /-ኦ/ አጣማሪ ሳይሆን፣ መደብ አመልካች ምዕላድ ሊሆን አይችልም ወይ? የሚል ነው፡፡ ጥያቄው ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም በዝ በሚባሉት አምዶች ላይ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ አመልካች የሆነው ምዕላድ በርግጥም /-ኦ/ ነው፡፡ ስለሆነም፣ አጣማሪ ካልነው /-ኦ/ ጋር በቅርፁ አንድ ነው፡፡ በተግባሩ ግን የተለየ ነው፡፡ በጥምሮቹ ውስጥ የሚገኘው /-ኦ/ መደብ አመልካቹ ሳይሆን፣ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ አጣማሪው /-ኦ/ ነው፡፡ መደብ አመልካቹ ቢሆን ኖሮ፣ እንደየመደቦቹ የተለያየ ቅርፅ ይይዝ ነበር፡፡ ለምሳሌ፣ ለአንደኛ መደብ ሰርቼ /ሰኧርት-ይኤ/፣ ለሁለተኛ መደብ ሰርተህ /ሰኧርት-ኧህ/፣ ወዘተ፣ የሚል ይሆን ነበር፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቅርፁ የጥምር ሳይሆን፣ የሀረግ ይሆናል፡፡ ስምሳሌ፣ ስራ ሰርቼ፣ ስራ ሰርተህ፣ ወዘተ፣ የሚል አካሄድ ያለው ግሳዊ ሀረግ ይሆናል፡፡ ጥምር ከሆነ ግን እንደዚህ ያለ ልዩነት አያሳይም፡፡ ለዚህ ማስረጃ የሚሆኑን እንደሚከተሉት ያሉ ጥምር ስሞች ናቸው፡፡

| ግስ | ስም | ጥምር |
|---|---|---|
| ሰርቶ | አዳሪ | ሰርቶ አዳሪ |
| ወዶ | ዘማች | ወዶ ዘማች |
| ፈጥኖ | ደራሽ | ፈጥኖ ደራሽ |

24

ከጥምሩ ትርጉም አኳዋያ ስንመልከት ግን፣ ቢስ የሚለውን ተጣማሪ የጥምሩ መሪ ልናደርገው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም የጥምሩ ትርጉም ጎድ (ዕድል) የሌለው የሚል ነው፡፡ ልበ-ቢስ ስንልም፣ ልብ የሌለው ማለታችን ነው፡፡ ትርጉሙ ከእጦት ጋር የተያያዘ ስለሆነ፣ ይህን ሀሳብ የሚገልፀውን ተጣማሪ የጥምሩ መሪ አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህ ተጣማሪም፣ እስካሁን እንዳየናቸው ሌሎች ጥምሮች መሪ፣ የጥምሩ የቀኝ አካል ነው፡፡

ከቃሉ ቅርፅ መሪነቱን ለማወቅ የማይቻልበት ምክንያት ቃሉ የርባታም ፀነ የምለረታ ምዕላድ የማያስከትልና ብቻውንም ለመቆም የማይችል በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም የቃላት ክፍሉን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ትርጉሙ አሉታዊ ስለሆነ፣ ከዚሁ በመነሳት፣ ቢስ የአሉታ ምዕላድ ነው፣ ለማለት እንችላለን፡፡ አሉታዊነት ደግሞ ከቃል ክፍል ጋር ሳይሆን፣ ከሀረግና ከአረፍተ ነገር ተግባር ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ነው፡፡ ወደፊት እናየዋለን፡፡

ቀደም ሲል እንዳየናቸው ጥምሮች ሁሉ፣ በእነዚህም ውስጥ አጣማሪው /-ኧ/ የሚገኘው ከጎላጩ ተጣማሪ ጋር ነው፡፡ ይህም ቀደም ሲል፣ ይህን አጣማሪ ምዕላድ ያስከተለ ተጣማሪ ሁሉ፣ መሪ እንዳልሆነ ያስገነዘብነውን ያጠናክራል፡፡ ምናልባትም፣ /-ኧ/ የሚገኝበት ተጣማሪ መሪ የሚሆነው እንደ ቤተ ክርስቲያን ባሉ ግዕዛዊ ጥምሮች ብቻ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ባጭሩ በአማርኛው ስርዓት /-ኧ/ የሚያርፍበት ተጣማሪ ገላጭ ሲሆን፣ በግዕዙ ግን ይህ ምዕላድ የሚገኝበት ተጣማሪ፣ መሪ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

## ጥምር ግሶች

እንደ ስሞችና ቅፅሎች ሁሉ ግሶችም በጥመራ ይፈጠራሉ፡፡ ይሁን እንጂ አፈጣጠራቸው ውሱን ነው፡፡ ይህም በሁለት በኩል ነው፡፡ በአንድ በኩል፣ ከተጣማሪዎቹ አንዱ ቀደም ሲል በአዕማዱ ክፍል እንዳየናቸው እንደ ስብር- [ስአብብእCC-] ያሉ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙ አዕማድ በመሆናቸው ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከእነዚህ ጋር የሚጣመሩት ግሶች አለ እና አደረገ የሚሉት ብቻ መሆናቸው ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| አምድ | ግስ | ጥምር ግስ | |
|---|---|---|---|
| ውጥት- | አለ | ውጥት አለ | 1 |
| ፍርጥ- | አለ | ፍርጥ አለ | |
| ብድግ- | አለ | ብድግ አለ | |
| ስብር- | አለ | ስብር አለ | |
| እልም- | አለ | እልም አለ | |
| ብልጭ- | አለ | ብልጭ አለ | |

ስርዓት-ፍጥረታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 1፣

[1-22-33-] + አል-      [1እ22እ33 አል-]
አምድ                        አምድ      አጠንካሪ

እምዱ ሙሉ ቃል ስላልሆነ የጥምሩ ክፍል በውል የሚታወቅ አይመስልም። ከግስ ጋር ተጣምሮ ግስ እንደሚመሰርት ሁሉ፣ ከቅጣይ ምዕላድ ጋርም ስምን ሊመሰርት ይችላል። እንደ ብልጭ-ታ፣ ስርቅ-ታ፣ እሽ-ታ፣ ወዘተ፣ በዚህ አይነት የሚመሰረቱ ስሞች ናቸው።

የጥምሩ መሪ <u>አለ</u> የሚለው ግስ ነው። እንደ <u>ብልጭ</u> [ብእልልእጭጭ-] ያሉ ቃላት እንደ ግስ ወይም እንደ ስም ወይም ቅፅል ራሳቸውን ችለው አይገኙም። የርባታ ስርዓትም የላቸውም። ስምሳሌ፡ <u>ብልጭ</u> የሚለውን ብንወስድ፣ እንደ መደበኛ ግስ፣ ስምሳሌ፡ እንደ ሰበረ፣ መደብን፣ ቁጥርን ወይም ፆታን አያሳይም። ስለዚህም <u>ይሰበር</u>፣ <u>ሰብሮ</u>፣ <u>ስበር</u>፣ ወዘተ፡ እንደምንል ሁሉ፣ <u>ይብለጭ</u>፣ <u>ብልጮ</u>፣ ወዘተ፣ ማለት አይቻልም። በዚህም ምክንያት እንደ <u>ብልጭ</u> ያሉትን <u>አይረቤ</u> ቃላት እንደ <u>ሰበረ</u> ካሉት ረቢ ቃላት መለየት ያስፈልጋል። እንደ <u>ሰበረ</u> ያሉትን ለርባታ የደረሱ በመሆናቸው አቢይ ቃላት ልንላቸው እንችላለን። እንደ <u>ብልጭ-</u> ያሉትን ደግሞ ለርባታ ያልደረሱ በመሆናቸው ንዑስ ቃላት ልንላቸው እንችላለን። ንዑስም በመሆናቸው ራሳቸውን ችለው አይቆሙም።

ንዑስ ቃላት ራሳቸውን ችለው ስለማይቆሙና ስለማይረቡም፣ ራሳቸውን ችለው ከሚቆሙና ከሚረቡ አቢይ ቃላት ጋር እየተጣመሩ አቢይ ውልድ ቃላትን ሊመሰርቱ ይችላሉ። በዚህ መሰረት <u>ፀጥ</u> የሚለው ንዑስ ቃል <u>አለ</u> ከሚለው አቢይ ግስ ጋር በመጣመሩ <u>ፀጥ አለ</u>፣ የሚል ጥምር ግስ ሊፈጠር ችሎአል። ይህ ግስ እንደ ማንኛውም አቢይ ግስ <u>ፀጥ ይላል</u>፣ <u>ፀጥ ይበል</u>፣ <u>ፀጥ ብሉ</u>፣ <u>ፀጥ በል</u>፣ ወዘተ፣ እያለ ይረባል። የርባታ ምዕላዶቹ የሚታዩት ግን በመሪው ላይ ነው። ስምሳሌ፣ <u>ፀጥ ይበል</u> በሚለው ጥምር፣ የሶስተኛ መደብ ምዕላዱ /ይ-/ የሚገኘው በግሱ፣ ማለትም በመሪው፣ ላይ ነው። ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል በጥምር ቅፅሎችና ስሞች ላይም ታይቶአል። አሁንም በግሶች ላይ መታየቱ፣ ቅጣይ ምዕላዶችን መያዝ አጠቃላይ የመሪ ባህሪ መሆኑን ሊያመለክት ይችላል።

<u>አለ</u> በሚለው ግስ አማካኝነት የሚፈጠሩ ግሶች ምድብ ከኢሳቢዎች ጋር ነው። ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ኢሳቢ ግሶች ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አይፈልጉም። ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ <u>ፀጥ አለ</u> 2
(ለ) *ካሳ አንበሳ ፀጥ አለ

ሁለተኛው ምሳሌ ተቀባይነት የለውም። ስለዚህም ምክንያቱ ግሱ ከስም ጋር መግባቱ ነው። ከስም ጋር ሊገቡ የሚችሉት <u>አደረገ</u> ከሚለው ግስ ጋር የሚፈጠሩ ጥምር ግሶች ናቸው። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

ደጋጋሚው አምድ የየስሩን ቅድመ-መድረሻ ተናባቢ በማጥበቅና አምዱን ሙሉ በሙሉ በመድገም ይመሰረታል፡፡ ከዚያም አስ/አደረገ ከሚለው ግስ ጋር ይቀናጅና ጥምር ይሆናል፡፡

አጠንካሪ አዕማድ የሚባሉት የየስሩን የመጨረሻ ሁለት ሁለት አግሮች ይደጋግሙና የመጨረሻውን ብቻ ያጠብቃሉ፡፡ ሁለቱን ተናባቢዎች የተፈለገውን ያህል በመድገም ሰብርብርብርብርብር...... እያሉ መቀጠል ይቻላል፡፡ የድግግሞሹ መጠን ለመግለፅ የተፈለገውን ሀሳብ የጥንካሬ ደረጃ ሊያመለክት ይችላል፡፡ ስለዚህም ለምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድ አደረገው 6
(ለ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድድድ አደረገው
(መ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድድድድድድድድድድ አደረገው

ብንል፣ የአቀዳደዱ የጥንካሬ፣ ምናልባትም ፍጥነትና የሰውየው የልህ መጠን የተለያየ መሆኑን እንረዳለን፡፡ የሚከተሉትን አዕማድ ደግሞ እንመለከት፡፡

| ስር | ድርብ ስር | አጠንካሪ | 7 |
|---|---|---|---|
| /ሰ-ብ-ር-/ | /ሰ-ብ-ር-ብ-ር-ብ-ር-ብ-ርር.../ | [ሰእብእርብእርብእርር...] | |
| /ግ-ል-ብ-ጥ-/ | /ግ-ል-ብ-ጥ-ብ-ጥ-ብ-ጥጥ..../ | [ግእልብእጥብእጥብእጥጥ....] | |
| /ው-ል-ቅ-/ | /ው-ል-ቅ-ል-ቅ-ል-ቀ-ል-ቅቅ.../ | [ውእልእቅልእቅልእቅልእቅቅ...] | |

ስርዓቱ እንደሚከተለው ነው፡፡

ስርዓት 3፣

| ስር | አምድ | አጠንካሪ |
|---|---|---|
| /1-2-3-/ | /1-2-3-2-3-2-33.../ | [1እ2እ3ልእ2እ32እ33...] |
| /ሰ-ብ-ር/ | /ሰ-ብ-ር-ብ-ር-ብ-ርር../ | ሰእብእርብእርብእርር...} |

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ እንደነዚህ ያሉ አዕማድ የሚፈጠሩት የግሱን መድረሻና ቅድመ መድረሻ ተናባቢዎች በመደጋገም ስለሆነ፣ ድግግሞሹ ክፍል ነው፡፡ በነዚህና ከፍ ሲል በተመለከትናቸው ደጋጋሚ አምዶች መካከል ያለው ልዩነትም በድርጊቱ የድግግሞሽ መጠን ላይ ነው፡፡ ከፍ ሲል ያየናቸው፣ ድርጊቱ እየተቋዋረጠና እንደገና እየተጀመረ መቀጠሉን ያመለክታሉ፡፡ በነዚህኞቹ የሚገለፀውን የድግግሞሽ መጠን በቁጥር ለመግለፅና በአህዝ ለመወሰን ያስቸግራል፡፡ ተናጋሪው ስለ ድርጊቱ ያለው ስሜት እስኪበርድ ድረስ የሚቀጥል ስለሆነ፣ መጠኑን መወሰን የሚቻል አይመስልም፡፡ ለምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድድ አደረገው 8
(ለ) ካሳ ወረቀቱን ቅድድ ቅድድ አደረገው

ብንል፣ ከመጀመሪያው ይልቅ በሁለተኛው አረፍተ ነገር የተገለፀውን ተግባር የድግግሞሽ መጠን መወሰን የሚቻል ይመስላል፡፡ ሂደቱ ቀጣይ ሳይሆን፣ እየተበጠሰና እየተቀጠለ የተፈፀመ ስለሆነ፣ ይህን ያህል ጊዜ ተፈፀመ ለማለት ይቻላል፡፡

እንደ <u>ስብር</u> <u>ስብር</u> ያሉ አፅማድ <u>አለ</u> ወይም <u>አደረገ</u> ከሚለው ግስ ጋር ሲቀናጁ የሚፈጥሩት ጥምር ተራ ሳይሆን ውስብስብ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ <u>ስብር</u> <u>ስብር</u> የሚለው ደጋጋሚ ቅርፅ ራሱ እንደ አንድ ጥምር ስለሚቆጠርና <u>አለ</u> ወይም <u>አደረገ</u> ከሚለው ግስ ጋር ሲቀናጅ የጥምረቱ ደረጃ ከፍ ስለሚል ነው፡፡ አጠማመሩን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

ስርዓት 4፣

(ሀ) [ስብር] ⟶ [ስብር ስብር]
አምድ ሙሉ ደጋጋሚ

(ለ) [ ስብር ስብር] + [ አለ] ⟶ [ስብር ስብር አለ]
ደጋጋሚ አምድ ግስ ውስብስብ ደጋጋሚ ጥምር

እንደ [ስብር ስብር አለ] ያሉ ግሶች የአንድን ድርጊት ተደጋጋሚነት ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ የተለየ ድርጊትን የሚያመለክቱ ጥምሮችም አሉ፡፡ እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

ያዝ ለቀቅ 9
ከፍ ዝቅ
ሳብ ረገብ
ብቅ ጥልቅ
ወጣ ገባ
ፈራ ተባ

እንደነዚህ ያሉ ጥምር አፅማድ ናቸው፡፡ ተጣማሪዎቹ ተቃራኒ ድርጊትን ወይም ይዘትን ያመለክታሉ፡፡ የተጣማሪዎቹ የቃል ክፍል ስለማይታወቅ፣ የጥምሩ ክፍልም ሆነ መሪው በትክክል አይታወቅም፡፡ ርግጥ፣ እስካሁን ያየናቸው ተጣማሪዎች በአብዛኛው ቀኝ መሪ ስለሆኑ፣ የነዚህም መሪ በስተቀኝ በኩል ያለው ተጣማሪ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ እነዚህን ጥምር አፅማድ ከፍ ሲል

በተመለከትነው ሁኔታ አለ ወይም አደረገ ከሚለው ግስ ጋር እያጣመሩ ውስብስብ ጥምር ግሶችን እንደሚከተለው መመስረት ይቻላል፡፡

ስርዓት 5፣

(ሀ) [[[ተኧተአ] + [ተኧተአ]] +አለ] ⟶ [አምድ-አምድ አለ]
　　አምድ 1 　 አምድ 1/2 　　　　　 ውስብስብ ጥምር

(ለ) [[[ተእተተ] + [ተእተተ / ተእተተ]] +አለ] ⟶ [አምድ-አምድ አለ]
　　አምድ 1 　 አምድ 1/2 　　　　　 ውስብስብ ጥምር

(መ) [[[ተእተተ] + [ተኧተኧተተ]] +አደረገ] ⟶ [አምድ-አምድ አደረገ]
　　አምድ 1 　 አምድ 1/2 　　　　　 ውስብስብ ጥምር

የተጣማሪዎቹ አዕማድ ውስጣዊ አቀነጃጀት አንድ ወጥ አይደለም፡፡ በ(ሀ) ውስጥ እንደ ፈራ ተባ፣ በ(ለ) ውስጥ እንደ ብቅ ጥልቅ እንዲሁም በ(መ) ውስጥ እንደ ሳብ ረገብ ያሉት ይገኛሉ፡፡ ሁሉም ተቃራኒ ወይም ደጋጋሚ ድርጊትን ወይም ይዘትን ያመለክታሉ፡፡ ጥምሮቹም እንደዚሁ አንድ ድርጊት በሙሉ ልብና በቁርጠኝነት ወይም በወላዋይነት መፈፀሙን ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ፣

ካሳ ፈራ ተባ እያለ ወደ ቤት ገባ 10

ስንል፣ ካሳ በልበ - ሙሉነት ሳይሆን በወላዋይነት ቤት ውስጥ እንደገባ እንገነዘባለን፡፡ በሙሉ ልብ የሚፈፀም ድርጊትን ለማመልከት ጥምሩ በደጋጋሚ አዕማድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ አካሄድ፣

(ሀ) ካሳ ወደ ቤት ገባ ገባ አለ 11
(ለ) ካሳ ወደ ደጅ ወጣ ወጣ አለ

ማለት ይቻላል፡፡

አስካሁን ሁለት አይነት ጥምር ግሶችን አይተናል፡፡ እነሱም ከተራና ከጥምር አዕማድ የሚፈጠሩ ናቸው፡፡ ተግባራቸው የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ማመልከት ነው፡፡ አፈፃፀሙ፣ ደጋጋሚ፣ አጠንካሪ፣ አለሳላሽ (ወላዋይ) ወይም ቁርጠኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ድርጊትን ብቻ ሳይሆን፣ አፈፃፀምንም ጨምረው ስለሚገልፁ በክፍላቸው ግሳዊ፣ በተግባራቸው ተውሳከ ግሳዊ ናቸው፡፡ ስለዚህም ተውሳከ ግሳዊ ጥምር ግሶች ሊባሉ ይችላሉ[2]፡፡

[2] ይህን ጉዳይ በተመለከተ መንግስቱ እንበርብር (1998)ን፣ ባየ (1999)ን ይመልከቱ፡፡

## ጥምር ተውሳከ ግሶች

ተውሳከ ግስ የሚባለው ክፍል በርካታ ተራ ቃላት እንደሌሉት ቀደም ባለው ክፍል ደጋግመን ገልፀናል፡፡ ተራ ቃላት ከሌሉት ጥምር ቃላት ይኖሩታል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጅ በድግግሞሽ የሚፈጠሩ ጥቂት ተውሳከ ግላዊ ቃላት ስላሉ፣ እነሱን ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ የሚከተሉት ለዚህ አብነት ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡

ጥቂት ጥቂት 1
ትንሽ ትንሽ

ትንሽና ጥቂት የሚሉት ቃላት በመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው፡፡ በቅፅልነታቸው እንደ ማንኛውም ቅፅል በገላጭነት ከስም በፊት እንደሚከተለው እየሆኑ ይገባሉ፡፡

(ሀ) በጣም ጥቂት እህል 2
(ለ) በጣም ትንሽ ልጅ

እነዚሁ ቃላት ከፍ ሲል ባስቀመጥነው ድግግሞሽ መልክ ሲመጡ ደግሞ፣ እንደ ተውሳከ ግስ ይገባሉ፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) ትንሽ ትንሽ [እንጀራ ይበላል] 3
(ለ) ጥቂት ጥቂት [ውሀ ይጠጣል]

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ <u>ትንሽ ትንሽ</u> እና <u>ጥቂት ጥቂት</u> በየግሶቹ የተገለፀውን ተግባር አነስተኛነት ስለሚያመለክቱ፣ የመጠን ተውሳከ ግስ ሊባሉ ይችላሉ፡፡ የሚያመለክቱት የተበላውን ወይም የተጠጣውን ነገር መጠን ላይሆን፣ የአበላሉን ወይም የአጠጣጡን ደካማነት ነው፡፡ ገላጭነታቸውም ለዚሁ ተግባር መሆኑን ከሚከተለው ምሳሌ ይበልጥ መረዳት ይቻላል፡፡

ትንሽ ትንሽ [ለሀገራችን እንሙት] 4

በዚህ ምሳሌ <u>ትንሽ ትንሽ</u> የሚለው ደጋጋሚ ቃል የሚገልፀው ሌላ ነገርን ላይሆን፣ ለሀገር የመሞትን፣ ማለትም መስዋዕት የመክፈልን ተግባር ነው፡፡ ገላጭነታቸው በቅንፍ ውስጥ ለተመለከተው ግላዊ ሀረግ ነው፡፡

እንደ ቅፅሎች ሁሉ <u>ቶሎ</u> የሚለው ተራ ተውሳከ ግስም በድግግሞሽ መልክ ሲገባ፣ የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ወይም መጠን ሲያመለክት ይችላል፡፡ የሚከተሉትን እናነፃፅር፡፡

(ሀ) ካሳ ቶሎ መጣ 5
(ለ) ካሳ ቶሎ ቶሎ ዘመዶቹን ይጠይቃል

በመጀመሪያው ምሳሌ ቶሎ የሚለው ተውሳከ ግስ፣ መጣ በሚለው ግስ የተገለፀው ድርጊት የሚወስደው ጊዜ አነስተኛ መሆኑን ሲያመለክት፣ በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ፣ ቶሎ ቶሎ የሚለው ደጋጋሚ ጥምር፣ ካሳ ዘመዶቹን ለመጠየቅ የሚያደርገውን ምልልስ ያሳያል፡፡ የመጀመሪያው የጊዜ ተውሳከ ግስ ሲሆን፣ ሁለተኛው የመጠን ተውሳከ ግስ ነው፡፡ ድርጊቱ ምን ያህል ተደጋጋሚ እንደሆነ ይገልፃልና፡፡ ሁኔታው ቀደም ሲል ካየናቸው ደጋጋሚ እዕማድ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ለማመልከት መስተዋድዳዊ ሀረጎችን እንደምንጠቀም፣ ስለ ቃላት ክፍሎች ስንወያይ ገልፀን ነበር፡፡ ይሁን እንጅ፣ ይህንኑ ሁኔታ ተውሳከ ግስ ሊባሉ በሚችሉ ጥምር መሰል ቃላትም መግለፅ ይቻላል፡፡ ቃላቱም እንደ፣

ቀስበቀስ 6
ጥቂት በጥቂት
ትንሽ በትንሽ

ያሉ ሲሆኑ፣ አገባባቸውም እንደሚከተለው ነው፡፡

ሰዎቹ ቀስበቀስ ከቤት ወጡ 7

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ቀስበቀስ የሚለው እሀድ የሰዎቹን የአወጣጥ ሁኔታ ስለሚያመለክት፣ የሁኔታ ተውሳከ ግስ ነው፡፡ ውስጣዊ ቅርፁን ስንመለከት የቀስ እና ቀስ ጥምር ይመስላል፡፡ በጥምሩ መካከል የሚገኘው /-በ-/ ሁለቱን ንዑስ ቃላት የሚያጣምር ምዕሳድ ይመስላል፡፡ አጣማሪ መስተዋድድ ልንለው እንችላለን፡፡

ከዚህ ሁኔታ ቀስበቀስ የሚለው ጥምር በቀስታ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ተውሳከ ግሳዊ አቻ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ አባባላችን ማስረጃ የሚሆኑ ተጨማሪ አቻ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣

(ሀ) በመኪና ተጉዋዘ 8
(ለ) ወደ ጎንደር ተጉዋዘ

በሚሉት ግሳዊ ሀረጎች ውስጥ፣ በመኪና እና ወደ ጎንደር የሚሉት መስተዋድዳዊ ሀረጎች ተጉዋዘ የሚለውን ግስ ይገልፃሉ፡፡ የነዚህ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ስማዊ

አቻዎች ደግሞ <u>የመኪና</u> እና <u>የጎንደር</u> የሚሉት ሲሆኑ፣ አገባባቸውም ስምን በመግለፅ፣

(ሀ) የመኪና ጉዞ 9
(ለ) የጎንደር ጉዞ

የሚል ይሆናል፡፡ ከዚህ አካሄድ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ መስተዋድዳዊ ሀረጎች በስማዊ ሀረግ ውስጥ ስማዊ አቻ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ በመስተዋድዳዊ ሀረጉ ውስጥ /በ/ የነበረው መስተዋድድም በስማዊ ሀረጉ ውስጥ /የ/ እየሆነ እንደሚገባ ቀደም ባለው ክፍልም ገልፀናል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ <u>ቀስበቀስ</u> የሚለው <u>በቀስታ</u> <u>በቀስታ</u> የሚለው ድርብ መስተዋድዳዊ ሀረግ ጥምር ተውሳከ ግሳዊ አቻ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ስማዊ አቻው <u>የቀስታ</u> <u>የቀስታ</u> ነው፡፡ የሶስቱን ክፍሎች የአቻነት ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| መስተዋድዳዊ ሀረግ | ፡ | በቀስታ በቀስታ |
| ስማዊ ሀረግ | ፡ | የቀስታ የቀስታ |
| ተውሳከ ግሳዊ ጥምር | ፡ | ቀስበቀስ |

በሌላ በኩል /በ-/ መስተዋድድ ስለሆነ፣ <u>ቀስበቀስ</u> የሚለው ጥምር ቃል ሳይሆን፣ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው ለማለት ይቻል ይሆናል፡፡ ይህ አመለካከት ግን ትንሽ ችግር አለበት፡፡ ምክንያቱም መስተዋድዳዊ ሀረግ የሚመሰረተው፣ ወደፊት በስፋው እንደምናየው፣ ከመስተዋድድና ከስማዊ ሀረግ ስለሆነ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ቀስ የሚለው ቃል ስም ነው ለማለት እንቸገራለን፡፡ ቃሉ ቀደም ሲል እንደጠቀስናቸው አንደ ዝም፣ ፀጥ፣ ብቅ፣ ወዘተ፣ ያለ ንዑስ ቃል ነው፡፡ ስለሆነም የቃል ክፍሉ በውል አይታወቅም፡. ይሁን እንጅ፣ እንደ ሌሎች ንዑስ ቃላት <u>አለ</u> ከሚለው ግስ ጋር እየተቀናጀ ጥምር ግስን ይፈጥራል፡፡ ቅንጅቱ ጥምር ለመሆኑም ተጨማሪ ማስረጃ አለ፡፡ ይኸውም እንደማንኛውም ጥምር ቃል ባዕድ ምዕላድ በመካከሉ ለማስገባት አለመቻሉ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እናነፃፅር፣

(ሀ) በጣም ቀስበቀስ 10
(ለ) *ቀስ በጣም በቀስ

የመጀመሪያው ምሳሌ ተቀባይነት ሲኖረው፣ ሁለተኛው የለውም፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው የቅርፅ ልዩነት <u>በጣም</u> የሚለው መጣኝ መስተዓምር በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ መገኘቱ ነው፡፡ አንድ ቅንጅት ጥምር ቃል ከሆነ፣ በዚህ ንዑስ ክፍል መጀመሪያ ላይ እንደተገለፀው፣ በመካከሉ ምንም ነገር

ማስገባት አይችልም፡፡ የሁለተኛው ምሳሌ ተቀባይነት ማጣት ከመስተዓምሩ ጣልቃ ገብነት የተነሳ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡

እንደ <u>ትንሽ በትንሽ</u> ያሉ ቃላት አመሰራረትም እንደዚሁ ተውሳከ ግሳዊ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው እንደ <u>ትንሽ</u> እና <u>ጥቂት</u> ያሉ ቃላት አገባብ ተውሳከ ግሳዊ ነው፡፡ ራሳቸውን ሲደጋግሙም ሆነ በአጣማሪ አማካኝነት ጥምር ቃል ሲሆኑ የሚገልፁት ተውሳከ ግሳዊ ባህሪን ነው፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ትንሽ ትንሽ ይበላል 11
(ለ) ትንሽ በትንሽ ስራውን ጨረሰ

በተግባር ሁለቱም የሚያመለክቱት የአንድን ድርጊት አፈፃፀም ነው፡፡ በቅርፅ ግን የመጀመሪያው በድግግሞሽ ሁለተኛው በጥመራ የተፈጠሩ ስለሆኑ ይለያያሉ፡፡ ሁለቱም ተውሳከ ግሳዊ ናቸው፡፡

እስካሁን በዚህ ንዑስ ክፍል ያየናቸውን ዝርዝር ጉዳዮች እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ጉዳዮቹ ጥምር ስሞችን፣ ግሶችን፣ ቅፅሎችንና ተውሳከ ግሶችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ጥምር ስሞች ከስም እና ከስም፣ እንዲሁም ከስምና ከግስ ሲፈጠሩ ይችላሉ፡፡ አፈጣጠራቸው በሁለት መንገድ ነው፡፡ አንደኛው የግዕዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው የአማርኛ ነው፡፡ በግዕዙ መንገድ የሚፈጠሩት ግራ መሪ ሲሆኑ፣ በአማርኛው መንገድ የሚፈጠሩት ቀኝ መሪ ናቸው፡፡ ጥምሮቹም ልል፣ ጥብቅ እና ውሁድ ተብለው በሶስት ደረጃ ሲሰዩ ይችላሉ፡፡ ልል የሚባሉት አጣማሪ ምዕላድ የላቸውም፡፡ ጥብቅ የሚባሉት /ኧ/ ወይም /-እ/ የሚል አጣማሪ ምዕላድ አላቸው፡፡ በ/ኧ/ የሚጣመሩት ስማዊ መሰረት ያላቸው ሲሆኑ፣ በ/እ/ የሚጣመሩት ግሳዊ መሰረት ያላቸው ናቸው፡፡ ውሁድ የሚባሉት ከጥምርነት ወደ አንድ ቃልነት የተሸጋገሩ ናቸው፡፡ ስለዚህም አጣማሪ የላቸውም፡፡

ጥምር ግሶች ከዕሰር አዕማድና <u>አለ</u> ወይም <u>አደረገ</u> ከሚሉት ግሶች ይመሰረታሉ፡፡ በ<u>አለ</u> አማካኝነት የሚፈጠሩት ኢሳቢ ሲሆኑ፣ በ<u>አደረገ</u> አማካኝነት የሚፈጠሩት ሳቢ ናቸው፡፡ ጥምሮቹ ተራ ወይም ድርብ ሲሆኑ ይችላሉ፡፡ ድርብ ጥምሮች ተቃራኒ ወይም ደጋጋሚ ድርጊቶችን ያመለክታሉ፡፡ ጥምር ግሶች በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው፡፡

ጥምር ቅፅሎች ከስምና ከቅፅል ይመሰረታሉ፡፡ እንደ ጥምር ስሞች ሁሉ፣ ጥምር ቅፅሎችም ቀኝ መሪ ናቸው፡፡ አንዳንድ ቅፅሎች በድግግሞሽ ይፈጠራሉ፡፡ ተደጋጋሚዎቹ ቃላት /-አ-/ በሚል ምዕላድ ይያያዛሉ፡፡ ይህም ከአንዳንድ ጥምር ስሞች የአጠማመር ስርዓት ጋር ይመሳሰላል፡፡

ተውሳከ ግሶች በድግግሞሽና በጥመራ ይመሰረታሉ፡፡ አጣማሪው <u>በ</u> ወይም <u>ለ</u> ሲሆን ተጣማሪዎቹ የመጠን ቅፅል የሚባሉትና ባለፈው ክፍል በመጣኝ መስተዓምር ስር የመደብናቸው ናቸው፡፡ የጥምሩን መሪ መለየት ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጅ ከሌሎች ጥምሮች አካሄድ በመነሳት ተውሳከ ግሶችም ቀኝ መሪ

ናቸው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ በዚሁ ይህን ንዑስ ክፍል እንሰናበታለን፡፡

## መልመጃ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ጥምርነት ያረጋግጡ፤ ትርጉማቸውን ይስጡ፣ ክፍላቸውንም ይናገሩ፡፡

(ሀ) እሳተ ክላ
(ለ) በገ ፈጅ
(ሐ) ሀገረ ሰብ
(ሰ) ሰበር ሰካ

2. የትኛው የቃል ክፍል ከየትኛው የቃል ክፍል ጋር ሊጣመር እንደሚችል በሰንጠረዡ ውስጥ ምሳሌ እየሰጡ ያሳዩ፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌ ተሰጥቶአል፡፡

| | ስም | ግስ | ቅፅል | ተውሳከ ግስ |
|---|---|---|---|---|
| ስም | ግብረ ሀይል | -------- | መልከ ጥፉ | ------- |
| ግስ | | | | |
| ቅፅል | | | | |
| ተውሳከ ግስ | | | | |

3. ገጠመኛችን የሚለውን ቃል በዕፀ-መዋቅር ተንትነው ያሳዩ፡፡ ዘመናችን ከሚለው ጋርም ያነፃፅሩና የአወቃቀር ልዩነታቸውን ይግለፁ፡፡

4. ቀሰበቀስ የሚለው ጥምር ተውሳከ ግስ እንደሆነ ተገልፆአል፡፡ በዚሁ መሰረት እጅለጅ የሚለውም ጥምር ተውሳከ ግስ ነው ለማለት የሚያስችል ምክንያት ይጥቀሱ፡፡

5. አጣማሪ ምዕላድ ያረፈበት ተጣማሪ ሁሉ የጥምር መሪ ነው፡፡ ይህን አባባል የሚደግፍ ምሳሌ በአንድ በኩል፣ የሚቃረን ምሳሌ በሌላ በኩል ይስጡ፡፡

6. ባለቤት የሚለውን ቃል ውስጣዊ ስርዓት ያመልክቱ፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## ስነ-መዋቅር

*መግቢያ*

ባለፈው ምዕራፍ ስለ አማርኛ ቃላት አከፋፈልና በየክፍሉ ስለሚገኙት ቃላት የርባታና የምስረታ ስርዓት ተወያይተናል። ትኩረታችን በቃላቱ ውስጣዊ ስርዓት ላይ ነበር። ስርዓቱ በየክፍሉ ውስጥ የሚገኙት ቃላት ከምንና እንዴት እንደሚመሰረቱ የሚያሳይ ነበር። ለምሳሌ፣ እንደ <u>ደግነት</u> ያሉ ቃለተ <u>ደግ</u> ከሚለው ቅፅላዊ ነፃ ምዕላድና /-ንንኧት/ ከሚለው ዕስር መሰራች ምዕላድ ላይ የተፈጠሩ የስም ክፍል ቃላት እንደሆኑ ተመልክተናል። የአቀነጃጀታቸው ስርዓትም ከነፃው ቅፅላዊ ምዕላድ ቀኝ ጉን ላይ /-ንንኧት/ የሚለውን ዕስር ምዕላድ መቀጠል ነው።

በዚህ ሁኔታ የሚፈጠሩ ለሞች ለመደብ፣ ለቁጥር፣ ለፆታ፣ ለሙያ፣ ወዘተ፣ ይረባሉ። ይህን ሲያደርጉም ቅርፃቸውን በከፊል እንደሚለዋውጡ አይተናል። ሁኔታውን ይበልጥ ለመረዳት <u>ደግነት</u> የሚለውን ስም ርባታ ከዚህ ቀጥለን እናሳያለን።

| መደብ | | | 1 |
|---|---|---|---|
| 1ኛ | | ደግነት-ኤ | |
| 2ኛ | ተ | ደግነት-ህ | |
| | አ | ደግነት-ህ-ኢ > ሽ | |
| 3ኛ | ተ | ደግነት-ኡ | |
| | አ | ደግነት-ኡ-አ | |
| | ብ | ደግነት-እች-ን | |
| | | ደግነት-እች-ህ-ኡ | |
| | | ደግነት-እች-ኧ-ኡ | |

የርባታውን ስርዓት ስናይ እንደ /-ኤ/፥ /-ህ/፥ ወዘተ፥ ያሉ ቅጣይ የርባታ ምዕላዶች ቀደም ሲል <u>ደግ</u> ከሚለው ቅፅል ላይ /-ንንኧት/ በሚለው መስራች ምዕላድ አማካኝነት ከተመሰረተው፥ <u>ደግነት</u> ከሚለው ስም ቀኝ ጉን ላይ እንደሚቀጠሉ

እንረዳለን። ስዚሀ ሁኔታ የሚፈጠሩትና የሚረቡትን ቃላት ውስጣዊ ስርዓት በጥቅሉ እንደሚከተለው እናሳያለን።

2




እንግዲህ ባለፈው ክፍል የተመለከትነው እንደዚሀ ያሉ ቃላትን ያወቃቀር ስርዓት ሲሆን፥ በዚሀ ክፍል ደግሞ ቃላት ብቻቸውን እየቆሙ፣ ወይም ከሀረግ ጋር እየተቀናጁ ሰፋ ሰፋ ያሉ መዋቅሮችን እንዴት እንደሚመሰርቱ እንመለከታለን። ከላይ በሚታየው ሁኔታ፣ ምዕላድ ከምላድ ጋር ሲቀናጅ ቃል እንደሚፈጥር ሁሉ፣ ቃልም ከሀረግ ጋር ሲቀናጅ ከቃል ከፍ ያለ መዋቅርን ይፈጥራል። ምዕላድ ከምዕላድ ጋር እየተቀናጁ ቃል የሚፈጥሩበት ስርዓት ስነ-ቃላት እንደሚባል ሁሉ፣ ቃላት ከሀረግ ጋር እየተቀናጁ ሰፋፊ መዋቅርን የሚፈጥሩበት ስርዓትም ስነ-መዋቅር ይባላል። ባለፈው ክፍል በስነ-ቃላቱ ላይ እንዳተኮርን ሁሉ፣ በዚሀ ክፍል በስነ-መዋቅሩ ላይ እናተኩራለን።

ባለፈው ክፍል እንዳደረግነው፥ በዚሀ ክፍልም እያንዳንዱን የቃላት ክፍል በየተራ እየወሰድን በውስጡ የሚገኙ ቃላት ከክፍላቸው ወይም ከሌላ ክፍል ሀረጎች ጋር እንዴት እንደሚቀናጁ፣ ማለትም እንደሚዋቀሩ ለማየት እንሞክራለን።

## *ሀረግ*

ሀረግ የምንለው እንድን ከቃል የሰፋ፥ ከአረፍተ ነገር ያነሰን መዋቅር ነው። ከዚሀ ላይ አንድ ነገር ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይኸውም በመዋቅርና በሀረግ መካከል ያለውን ልዩነት የሚመለከት ነው። መዋቅር አጠቃላይ ቃል ነው ፣ ማንኛውንም ቅንጅት ያካትታል። ለምሳሌ፥ በስነ-ድምፅ ደረጃ የቀለምን፣ በስነ-ቃላት ደረጃ የቃላትን፣ እንደዚሁም በስነ-መዋቅር ደረጃ የሀረግንና የአረፍተ ነገርን ውስጣዊ ቅንጅት

ይመለከታል። ሀረግ ግን ውሱን ነው። ውሱንነቱም በሁለት ወገን ነው። በአንድ ወገን በአይነቱ ወይም በክፍሉ ሲሆን፣ በሌላ ወገን በይዘቱ፣ ማለትም በመጠኑ ነው። በክፍሉ ሲታይ፣ አንድ ሀረግ ስማዊ፣ ግሳዊና ቅፅላዊ፣ ወዘተ፣ ሲሆን ይችላል። ስለዚህም ስማዊ ሀረግ፣ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ወዘተ፣ እያልን አንዱን የሀረግ አይነት ከሌላው እንለያለን።

የሀረጉ አይነት የሚወሰነው በቋንቋዋ ውስጥ በሚገኙት የቃላት ክፍሎች መጠን ነው። አንድ ቋንቋ አምስት የቃላት ክፍሎች አሉት ብንል፣ የሀረጉ አይነትም እንደዚሁ አምስት ይሆናል። ባለፈው ክፍል የአማርኛ ቃላት በስድስት እንደሚከፈሉ አይተናል። ስለዚህም ቋንቋዋው ስድስት የሀረግ አይነቶች ይኖሩታል። እያንዳንዱ የቃላት ክፍል በውስጡ ከሚገኘው ቃል ላይ ሀረግ የመመስረት ዕድል አለውና። ባለፈው ንዑስ ክፍል፣ ቃላት በቅለው ሀረግ ሊሰዱ ይችላሉ ብለን ነበር። ለምሳሌ፣ አንድ ስም የሆነ ቃል፣ አድጎ ሀረግ ሲሰድ፣ ስማዊ ሀረግ ይሆናል። ይህ እንግዲህ ከአይነት አንፃር ሲታይ ነው።

ከመጠን አኳያ ሲታይ ደግሞ፣ አንድ ሀረግ ንዑስ ወይም አቢይ ሲሆን ይችላል። ይህ የሚወሰነው በሀረጉ ውስጣዊ ይዘት ነው። ትንሽ ነገሮችን የያዘ ንዑስ ሲባል፣ በርካታ ነገሮችን የያዘ አቢይ ሀረግ ይባላል። ይህን ወደ ዝርዝሩ በንገባ እናየዋለን። ከዚህ ላይ ለመግለፅ የምንፈልገው ንዑስም ይሁን አቢይ ሀረግ በቃል ላይ የተመሰረተ የመዋቅር አይነት መሆኑን ነው።

## ስማዊ ሀረግ

ስማዊ ሀረግ የምንለው ከአንድ ስምና ከሌሎች ሀረጎች የሚፈጠርን መዋቅር ነው። የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

የሳር ቤት 1

ይህ የስማዊ ሀረግ መዋቅር ነው። የተዋቀረውም ቤት ከሚለው ስምና የሳር ከሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ስሙ ከሀረጉ ጋር ተቀናጅቶ አንድ ከቃል በላይ ያለ አሀድ ፈጥሮአል። ይህም አሀድ የሳር ቤት የሚለው መዋቅር ሲሆን፣ በአይነቱ ስማዊ፣ በመጠኑ ደግሞ ሀረጋዊ ነው። ከቃል ይሰፋል ማለት ነው፡፡

ከዚህ ላይ እሁንም ሁለት ነገሮችን ከወዲሁ ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የመጀመሪያው ማንኛውም ሀረግ ከመሪ ቃልና ከሀረግ የሚፈጠር መሆኑ ነው። ቃሉ ለሚፈጠረው ወይም ለሚመዘዘው ሀረግ ዘር ሲሆን፣ ሀረጉ ደግሞ አሳዳጊው ነው። የሚያሳድገውም ልዩ ልዩ መግለጫ ስለዘሩ በመስጠት ነው። ሁለተኛው ጉዳይ ከስሙና ከሀረጉ የሚፈጠረው መዋቅር አንድ አሀድ ለመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? ከሚል ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነው። ጥያቄው መሰረታዊ ነው። ወደፊት በየደረጃው አንድ አሀዳዊ መዋቅር ነው፣ እያልን የምንለየውንና የምንተነትነውን መዋቅር ሁሉ የሚመስከት ስለሆነ፣ ከወዲሁ ውል ያለው ምላሽ ማግኘት አለበት።

የሚለው ቃል [የሳር ቤት] በሚለው ቅንጅት ውስጥ ጣልቃ መግባቱ ነው። የዚህ ቃል ጣልቃ መግባት አረፍተ ነገሩን ሊያዛባውና ተቀባይነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ችሎአል። ቃሉ በቅንጅቱ መካከል ሳይሆን፣ በመነሻው ላይ ቢገባ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት ይኖረዋል። ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው።

ካሳ [ትንሽ [የሳር ቤት]] አለው 6

የምሳሌ 5(ለ) ተቀባይነት አጠያያቂ መሆን፣ በአንፃሩ ደግሞ የምሳሌ (6) ትክክል መሆን የሚያመለክተው፣ [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት፣ በውስጡ ሌላ ቃል ሊያስገባ አለመቻሉን ነው። ይህም ቅንጅቱ እንደ አሀዳዊ መዋቅር እንደሆነ ያመለክታል።

የመጨረሻው መስፈርት አንድ ቅንጅት አሀዳዊ መዋቅር ከሆነ፣ እንደ እና ወይም ባሉ አያያዥ ምዕላዶች ሊቀናጅ የሚችለው ከእቻ መዋቅር ጋር ብቻ እንደሆነ ይገልፃል። በዚህ መሰረት የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት ሊያያዝ የሚችለው እንደ የቆርቆሮ ቤት ካለ እቻ ቅንጅት ጋር ነው። ይህም እንደሚከተለው ነው።

(ሀ) [የሳር ቤት] እና [የቆርቆሮ ዳስ] 7
(ለ) ?[የሳር ቤት] እና [ዳስ]

የምሳሌ 7(ለ) ተቀባይነት አጠራጣሪ ነው። ምክንያቱም የሳር ቤት የሚለው ቅንጅት የተያያዘው ዳስ ከሚል ተራ ስም ጋር በመሆኑ ነው። ዳስ የሚለው ተራ ስም ሊያያዝ የሚችለው እንደሱ ተራ ከሆነ ስም ጋር እንጅ፣ እንደ የሳር ቤት ካለ ስፊ ቅንጅት ጋር አይደለም። እንደ ቤት ካለ ተራ ስም ጋር ሲያያዝ፣ የሚከተለውን ይመስላል።

ቤት እና ዳስ 8

ይህ ተቀባይነት ያለው መዋቅር ነው። ሁኔታው "ያላቻ ጋብቻ... " ጥሩ አይሆንም የሚለውን ተረትና ምሳሌ ሊያስታውሰን ይችላል፡፡

እንግዲህ [የሳር ቤት] የሚለው ቅንጅት ከፍ ሲል ከ(ሀ) እስከ (ረ) ድረስ የተዘረዘሩትን የመዋቅር መስፈርቶች ስለሚያሙዋላ እንደ አንድ አሀዳዊ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል። ማንኛውም እነዚህን መስፈርቶች የሚያሙዋላ ቅንጅት ሁሉ፣ እንደዚሁ እንደ አንድ መዋቅር ሊቆጠር ይችላል። ወደፊት መዋቅር እያልን የምን ጠቅሳቸው ቅንጅቶች ሁሉ፣ ከነዚሁ መስፈርቶች አኩዋያ የሚታዩ መሆናቸውን ከወዲሁ እንገልፃለን። አሁን ከፍ ሲል ወደጀመርነው የመዋቅር ጉዳይ እንመለስ።

ከላይ ስመጠቆም እንደሞከርነው፣ በማንኛውም መዋቅር ውስጥ የሚገኝ ክፍል ተዋቃሪ ይባላል። ማንኛውም መዋቅርም የተዋቃሪዎች ቅንጅት ነው። አንድ ተዋቃሪ በመዋቅር ውስጥ የሚገኝበት የተለየ ቦታና ተግባር አለው። ተግባሩ የመዋቅሩ መሪ ወይም ተመሪ መሆን ነው። ለምሳሌ በ5(ሀ) ውስጥ [የሳር ቤት] የሚለው መዋቅር ተዋቃሪዎች ቤት የሚለው ስምና የሳር የሚለው ህረግ ናቸው። አቀማመጣቸው የሳር የሚለው ቀድሞ፣ ቤት የሚለው እሱን ተከትሎ በመምጣት ነው። በዚህ አቀማመጥ፣

ቤት የሚለው ተዋቃሪ ተግባር አጠቃላይ መዋቅሩን መምራት ነው። የመዋቅሩ ምሰሶ ነው፣ ለማለት ይቻላል። ያለሱ መዋቅሩ ብቻውን አይቆምም። ስለዚህም የመዋቅሩ *አይቀሬ* አካል ወይም ተዋቃሪ ነው። የሳር የሚለው ተዋቃሪ ተግባር መሪውን፣ ማለትም ቤት የሚለውን ስም ማጀብ ነው። አጅቦም [የሳር ቤት] የሚለውን ስማዊ ሀረግ ይመሰርታል። ያለመሪው ብቻውን ይህን ሊያደርግ አይችልም። መሪው ስም ግን ያላጃቢው ብቻውን እንደ ምሰሶ ሊቆምና ሀረግ ሊሆን ይችላል። ስሬ መዋቅር ግን ሊሆን አይችልም፣ አጃቢ የለውምና። በዚሁ መሰረት ወደፊት እንደ ምሰሶ ብቻቸውን እየቆሙ የምናገኛቸውን አሀዶች ሀረግ እያልን እንጠራቸዋለን። ስራዊቱ እንደከዳው የጦር መሪ ሊቆጠሩ ይችላሉ።።

መሪው ከአጃቢ ጋር ሲዋቀር፣ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ አጃቢውን በስተግራ አስከትሎ እሱ በስተቀኝ ቀድሞ በመገኘት ነው። መሪው ከአጃቢው ቀድሞ በስተቀኝ ስለሚገኝ ሀረጉ ቀኝ መሪ ሀረግ ይባላል። ይህም ባለፈው ክፍል ስለ ተምር ቃላት ስንወያይ እንዳየነው የተጣማሪዎች አሰላለፍ መሆኑ ነው። በአጃቢው መነሻ ላይ የምትገኘው "የ" ባለፈው ክፍል ያየነውን በርፍ ሙያን አመልካች ምዕላድ ነች። እስዋ የምትገኝበት ስም ሙያው ባለቤት ወይም ተሳቢ ሳይሆን ዘርፍ ነው[1]። ይህን ወደፊት በስፋት እናየዋለን። ለጊዜው ግን ተግባርዋ አጃቢው ስም፥ ማለትም ሳር፥ የመሪው አካል ሆኖ ሀረጉን መመስረቱን ማመልከት ነው፣ ብለን፣ ከፍ ሲል ወደ አነሳነው የመሪና የተመሪ (አጃቢ) ተግባር እንመለስ።

አንድ መሪ የሀረግን አይነት ብቻ ሳይሆን፣ ክፍሉንም ይወስናል። መሪው ስም ከሆነ፥ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ይሆናል። መሪው ግስ ከሆነ፣ መዋቅሩም እንደዚሁ ግሳዊ ሀረግ ይሆናል። ከዚህ አንፃር ከላይ የተጠቀሰው ምሳሌ መሪ ቤት የሚለው ስም ስለሆነ፣ ሀረጉ ስማዊ ነው።

የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።

ትልቅ ቤት 9

ይህ መዋቅር ትልቅ የሚለው ቅፅልና ቤት የሚለው ስም ቅንጅት ነው። የመዋቅሩ መሪ አሁንም ቤት የሚለው ስም ሲሆን፣ አጃቢው ትልቅ የሚለው ቅፅል ነው። መሪው ስም ስለሆነ፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው፣ የአንድ መዋቅር መሪ ስም እስከሆነ ድረስ፣ አጃቢው ምንም ይሁን ምን፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ እንጅ ሌላ ሊሆን እስመቻሉን ነው ።

በምሳሌ (1) እና (7) ውስጥ መሪው የተዋቀረው ከአንድ አጃቢ ጋር ብቻ ነው። ይህ ሁኔታ ግን አንድ መሪ ከአንድ በላይ አጃቢ አይኖረውም ወደሚል

[1] የ "የ"ን የተለያየ ተግባር በተመለከተ አሁንም ሀይሉ (1967)ን ይመልከቱ።

ድምዳሜ አይወስድም፣ ብዙ አጃቢ ሊኖረው ይችላል፤ እንደ ትልቅ መሬ። ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት።

ትልቅ የሳር ቤት (10)

ይህ አንድ መዋቅር ነው። መሪው አሁንም <u>ቤት</u> የሚሰው ስም ስለሆነ፣ መዋቅሩ ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው ሁለት አጃቢዎች አሉት። እነሱም <u>የሳር</u> የሚለው ስማዊ ሀረግና <u>ትልቅ</u> የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ናቸው። በምሳሌ (1) ውስጥ <u>የሳር ቤት</u> የሚለው ቅንጅት ራሱን የቻለ ስማዊ ሀረግ እንደሆነ ከፍ ሲል አይተናል። በዚህ ምሳሌ ውስጥ ደግሞ ያው ሀረግ <u>ትልቅ</u> ከሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። ይህን በማድረጉ የተለየ ሀረግ አልፈጠረም። አሁንም የፈጠረው ስማዊ ሀረግ ነው። ርግጥ፣ የአሁኑ ሀረግ ከፊተኛው ሰፋ ይላል። ስለዚህም በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የይዘት ነው። በተራ ቁጥር (1) የሚታየው መዋቅር አንድ ስማዊ ሀረግ ከሆነ፣ ከእሱ ይሰፋል ያልነውና በተራ ቁጥር (10) የሚታየው መዋቅር ምን ሊባል ነው? ሀረግ ወይስ ከሀረግ በላይ የሆነ መዋቅር?

ቀደም ሲል፣ አንድ ሀረግ በመጠኑ ንዑስ ወይም አቢይ ሊሆን እንደሚችልና ይህንንም የሚወስነው በውስጡ የሚገኘው የተዋቃሪ ብዛትና ተግባር እንደሆነ ገልፀን ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በተራ ቁጥር (1) የሚታየው መዋቅር አንድ አጃቢ ብቻ ስላለው፣ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ ከሚገኘውና ሁለት አጃቢ ካለው መዋቅር በይዘቱ ያነሰ ነው። ስለዚህም ይህን መዋቅር ንዑስ ስማዊ ሀረግ ልንለው እንችላለን። ከእሱ የሚበልጠውንና በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚገኘውን መዋቅር ደረጃ ለመወሰን፣ ተጨማሪ ምሳሌዎች ያስፈልጉናል። እስቲ የሚከተለውን እንመልከት።

የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት (11)

ይህ መዋቅር በተራ ቁጥር (1)ም ሆነ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ ከሚገኘው መዋቅር የሰፋ ነው። የሰፋበት ምክንያት መሪው ሶስት አጃቢዎች ስላሉት ነው። በዚህም ምክንያት መዋቅሩን አቢይ ስማዊ ሀረግ ልንለው እንችላለን። ይህን ስንል ግን፣ መዋቅሩ ከዚህ የበለጠ ሊሰፋ አይችልም ማለታችን አይደለም። ከዚህ የበለጠ ሊሰፋ ይችላል፤ ደረጃው ግን አሁንም ከአቢይ ሀረግ አያልፍም። እንዴት እንደሚሰፋ ከማየታችን በፊት በተራ ቁጥር (1፥ 10፥ እና 11) ውስጥ የሚታየውን የአጃቢዎችና የመሪ ቅንጅት ከሁለቱ የአቢይና የንዑስ ሀረግ ደረጃዎች አንፃር እንደገና እናጢነው።

በተራ ቁጥር (1) ውስጥ የሚገኘው መዋቅር ንዑስ ስማዊ ሀረግ ነው ካልን፣ በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚገኘው መዋቅር ከዚህ ንዑስ ሀረግና <u>ትልቅ</u> ከሚለው ቅፅላዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው፤ ለማለት ይቻላል። ይህም ማለት፣ ምሳሌ (10) <u>ቤት</u> ከሚለው መሪና <u>የሳር</u> እና <u>ትልቅ</u> ከሚሉት አጃቢዎች በአንድ ጊዜና በአንድ ደረጃ

የተዋቀረ ሳይሆን፣ መጀመሪያ ቤት የሚለው መሪና የሳር የሚለው አጃቢ ተዋቅረው በተራ ቁጥር (1) የሚታየውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ ከፈጠሩ በሁዋላ፣ በሁለተኛ ደረጃ ወይም ርከን ላይ ትልቅ የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ ከዚሁ ንዑስ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በተራ ቁጥር (10) የሚታየውን ሰፋ ያለ መዋቅር ፈጥሮአል ማለት ነው። ከዚህ በሁዋላ ደግሞ ይኸው በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የሚታየው ሀረግ፣ የትናንቱ ከሚለው ጊዜን አመልካች ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በተራ ቁጥር (11) የሚታየውን በጣም ሰፊ የሆነ አቢይ ሀረግ ፈጥሮአል። በሌላ አነጋገር፣ አቢይ ሀረጉ በውስጡ ሁለት ሀረጎችን ይዞአል። እነሱም የሳር ቤት የሚለው ንዑስ ሀረግና የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት የሚለው አቢይ ሀረግ ናቸው። የንዑሱ ሀረግ መሪ ቤት የሚለው ስም እንደሆነ ሁሉ፣ የአቢይ ሀረጉ መሪ የሳር ቤት የሚለው ንዑስ ሀረግ ነው። ይህን የሁለቱን ሀረጎች የደረጃ ልዩነት እንደሚከተለው አድርጎ በዕፀ መዋቅር ማሳየት ይቻላል።




12

ከዕፀ-መዋቅሩ እንደምናየው፣ በመጀመሪያው ርከን ላይ የሳር እና ቤት ተዋቅረው [የሳር ቤት ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) ፈጥረዋል። [የሳር ቤት] የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ የሆነበት ምክንያትም መሪው አንድ አጃቢ ብቻ ስላለው ነው። በሁለተኛው ርከን ላይ፣ ይህ ሀረግ ትልቅ ከሚለው አጃቢዎች ጋር ተዋቅሮ፣ [ ትልቅ የሳር ቤት ] የሚለውን ሰፊ ስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ፈጥሮአል። ይህ አቢይ ስማዊ ሀረግ ነው። አቢይ የሚያሰኘው ከንዑሱ ስማዊ ሀረግ የበለጠ ሰፊ ያዘት ያለው መሆኑ

[2] የሀረጎችን ውስጣዊ አቀነጃጀት ከዚህ ላይ እንደሚታየው፣ በቅንፍ ወይም በዕፀ-መዋቅር ማመልከት ይቻላል። ዕፀ-መዋቅር የአቀነጃጀቱን ስርዓት በቀላሉ ስማየት ስለሚያስችል፣ ብዙ ጊዜ እሱን እንጠቀማለን፤ ምንም እንኳ ቦታ-ፈጅ ቢሆንም።

ነው። ንዑሱ ስማዊ ሀረግ የዚህ አቢይ ሀረግ አካልና መሪም ነው። ሀረጉ <u>የትናንቱ</u> ከሚለው የጊዜ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በርከን (3) ላይ እንደሚታየው ከሁሉም የሰፋ ሀረግ ሊሆን ችሎአል፡፡

ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፥ ጠቅላላ ሀረጉ ሶስት ርከኖች አሉት። እነሱም በቁጥሮቹ የተመለከቱት የንዑሱ ሀረግ (ስሀ1) የአቢዩ ሀረግ (ስሀ2) እና ስሀ(3) <u>አንጉዋዎች</u> ናቸው። በነዚህ ርከኖች ላይ የሚገኙት አጃቢዎችም የተለያዩ ናቸው። ልዩነታቸውም መሪውን ከሚገልፁበት ተግባር አኩዋያ ነው። በንዑስ ሀረጉ ርከን ውስጥ የሚገኘው <u>የሳር</u> የሚለው አጃቢ፣ የሀረጉ መሪ የሆነው፣ <u>ቤት</u> የሚለው ቃል የሚጠቁመው ነገር ከምን እንደ ተሰራ ያመለክታል። <u>የሳር ቤት</u> ስንል፣ ቤቱ ከሳር የተሰራ መሆኑን መግለፃችን ነው።

በሁለተኛው ርከን ላይ የሚገኘው <u>ትልቅ</u> የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ <u>የሳሩ ቤት</u> መጠን ምን ያህል እንደሆነ ይገልፃል። የመጀመሪያው አጃቢ ቤቱ የተሰራበትን ነገር ሲገልፅ፣ ሁለተኛው አጃቢ የቤቱን መጠን፣ ማለትም ትልቅነቱን፣ ይገልፃል። በሶስተኛው ርከን ላይ የሚገኘው <u>የትናንቱ</u> የሚለው ተጨማሪ አጃቢ ቤቱ የተሰራበትን ወይም የተገኘበትን ጊዜ ያመለክታል። ሶስቱም አጃቢዎች መሪውን ሰም ከተለያየ አንፃር ይገልፁታል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ሁሉም ገላጭ አጃቢዎች ናቸው።

መሪውን ከተለያየ አንፃር የሚገልፁ እንደመሆናቸው መጠን፣ አገባባቸውም እንደዚሁ በተለያየ ርከን ላይ ነው። መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር ከምን እንደተሰራ የሚገልፀው አጃቢ በመጀመሪያው ርከን፣ በንዑስ ሀረጉ ውስጥ፣ በቀጥታ ከመሪው ስም በስተግራ በኩል ተጠግቶ ሲገባ፣ መሪው የሚጠቁመውን ነገር መጠን የሚገልፀው ቅፅል በሁለተኛው ርከን ላይ፣ ጊዜውን የሚያመለክተው <u>የትናንቱ</u> የሚለው አጃቢም በሶስተኛው ርከን ላይ <u>የሳር ቤት</u> የሚለውን ንዑስ ሀረግ እየቀደመ ገብተዋል። በዚህ ደረጃ <u>የትናንቱ ትልቅ የሳር ቤት</u> የሚለው አቢይ ሀረግ መሪ <u>ትልቅ የሳር ቤት</u> የሚለው ሀረግ ነው። የዚህ ሀረግ መሪም <u>የሳር ቤት</u> የሚለው ንዑስ ሀረግ ነው። የአቢይ ሀረጉ መሪ ንዑስ ሀረግ ሲሆን፥ የንዑስ ሀረጉ መሪ ግን ሀረግ ሳይሆን ተራ ቃል ነው። ቃሉ ሌሎች ነገሮችን በየርከኑ እየጨመረ በማደግ መጀመሪያ ንዑስ፣ ከዚያ በየደረጃው እየሰፋ አቢይ ሀረግ ይሆናል። ከዚህ ሳይ ባለፈው ንዑስ ክፍል ቃላት ሀረግ ይመዛሉ ያልነውን ያስታውሱ፡፡

ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፥ ሀረጉ በተራ ቁጥር (11) ከሚታየው የበለጠ ሊሰፋ ይችላል። የሚሰፋውም የተለያዩ አጃቢዎችን በመጨመር ነው። ተጨማሪዎቹ አጃቢዎች የሚገቡት በተለያየ ርከን ላይ ነው። በመጀመሪያው ላይ የሚገባ ተጨማሪ አጃቢ የለም። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ሊገባ የሚችለው አጃቢ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚያመለክት አጃቢ ብቻ ነው። እንደዚህ ያለ አጃቢ ደግሞ ከአንድ በላይ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ምንም እንኩዋ አንዳንድ ነገሮች ከብዙ ነገር ሊሰሩ የሚችሉ ቢሆኑም፣ የሚጠቀሱት ከተሰሩባቸው ነገሮች በአንዱ ብቻ ስለሆነ ነው። ለምሳሌ፣ <u>የሳር ቤት</u> ስንል፣ ቤቱ ከሳር የተሰራ መሆኑን መግለፃችን ነው። ይሁን እንጅ፣ ቤቱ ከሳር ብቻ ሳይሆን፣ ከሌሎች ነገሮች ጭምር የተሰራ ሊሆን ይችላል። ቢሆንም፣ ከሁሉም ጎልቶ የሚታየው የቤቱ ጣሪያና ግድግዳ ስለሆነ፥ በዚሁ መሰረት ጣሪያው ወይም ግድግዳው የተሰራበትን ነገር በመጥቀስ፣ ጠቅላላ ቤቱን እንገልፃለን። የሳር ወይም የቆርቆሮ በማለት ክዳኑን፣ የእንጨት፣ የሸክላ፣ ወዘተ፣ በማለት ግድግዳውን እንጠቁማለን። ስለዚህም አንድን ቤት ስንገልፅ አትኩሮታችን ከነዚህ ከሁለቱ አያልፍም። በንዑስ ሀረግ ደረጃ ሊገባ የሚችለው አጃቢ አንድ ብቻ የሚሆነውም ከነዚህ

ከሁለቱ በአንዱ ብቻ ስለሚጠቀስ ነው። ሌሎች ነገሮችንም የምንገልፀው እንደዚሁ በእንዱ ባህሪያቸው ወይም አካላቸው ላይ በማተኮር ነው።

ሁለተኛው፣ በስስተኛው፣ ወሰተ ርከን ላይ ግን ከላይ በተራ ቁጥር (11) እንደሚታየው፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ገላጭ አጃቢዎች ሊገቡ ይችላሉ። ተግባራቸውም ንዑስ ሀረጉ የሚጠቀመው ነገር የሚገኝበትን ሁኔታ ወይም የተሰራበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ ምክንያት፣ ዓላማ፣ መሳሪያ፣ ወሰተ፣ መግለፅ ነው። የሚከተለውን ተጨማሪ ምሳሌ እንመልከት።

የመርከቶው ትልቅ የላር ቤት 13

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ <u>የመርከቶው</u> የሚለው ገላጭ አጃቢ፣ <u>ትልቅ</u> ከሚለው ቅፅል ቀድሞ ገብቶአል። ተግባሩም <u>የሳር ቤት</u> የሚለውን ንዑስ ሀረግ ከቦታ አንፃር መግለፅ ነው። <u>የትናንቱ</u> የሚለው የጊዜ ሀረግ በዚህ ምሳሌ ውስጥ ሊገባና ሀረጉን የበለጠ ሊያሰፋው ይችላል። አገባቡም ከዚህ ቀጥሰን እንደምናየው በሀረጉ መነሻ ላይ ነው።

(ሀ) <u>የትናንቱ</u> የመርከቶው ትልቅ የሳር ቤት 14
(ለ) ?የመርከቶው <u>የትናንቱ</u> ትልቅ የሳር ቤት
(መ) * የመርከቶው ትልቅ <u>የትናንቱ</u> የሳር ቤት

የእነዚህ ምሳሌዎች የተቀባይነት ደረጃ ከ(ሀ) ወደ (ለ) ከዚያም ወደ (መ) እሽቆልቁሎአል። ለዚሀም ምክንያት የሆነው <u>የትናንቱ</u> የሚለው ገላጭ ሀረግ በ(ሀ) ውስጥ የሚገኝበትን ቦታ ትቶ፣ መጀመሪያ በ(ለ) ውስጥ <u>ትልቅ</u> ከሚለው ቅፅል በፊት፣ እንደገናም በ(መ) ውስጥ <u>የሳር</u> ከሚለው ስም በፊት መግባቱ ነው። ከዚህ የምንረዳው በእቢይ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ ገላጮች ቅደም-ተከተልና ተዋረዳዊ ስርዓት የሚከተሉ መሆናቸውን ነው። ይኸውም የጊዜው ገላጭ ከቦታው፣ የቦታው ገላጭ ደግሞ ከቅፅሉ እየቀደመና ከፍ እያለ የሚገባ መሆኑ ነው። ይህ ቅደም-ተከተልና ተዋረዳዊ ስልፍ ሲፋለስ አረፍተ ነገሩ ይዛባል።

በዚሁ አይነት ሌሎች ገላጭ አጃቢዎችን እየጨመሩ ሀረጉን ማስፋትና በዚያም ውስጥ ቅደም-ተከተላዊ አገባባቸውን ማየት ይቻላል። ለተጨማሪ ማስረጃ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) <u>የበርሜሉ</u> ደረቅ የማር ጠጅ 15
(ለ) ? ደረቅ <u>የበርሜሉ</u> የማር ጠጅ
(መ) * ደረቅ የማር <u>የበርሜሉ</u> ጠጅ

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>የበርሜሉ</u> የሚለው ስማዊ ገላጭ በመነሻ ላይ ይገኛል። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ደግሞ በቅፅሉና <u>የማር</u> በሚለው ገላጭ መካከል ይገኛል። ስዚህም ምክንያት የሀረጉ ተቀባይነት አጠያያቂ ሆኖአል። በምሳሌ (መ) ውስጥ ደግሞ ጠ<u>ጅ</u> ከሚለው መሪ ስም ቀድሞ በመግባቱ አረፍተ ነገሩ ተዛብቶአል።

በነዚህና በተራ ቁጥር (12) ውስጥ በአቢዩ ሀረግ ርከን ላይ የሚገኙ ስማዊ ገላጮች ቦታቸውን እየለቀቁ ወደ ንዑሱ ሀረግ በተጠጉ ቁጥር፣ የሀረጎቹ ተቀባይነት እየቀነሰ እንደሚሄድ አይተናል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በንዑስ ሀረግ ርከን ላይ መገኘት ያለበት ገላጭ ቦታውን ለቆ ወደ እቢይ ሀረጉ ርከን ሲጠጋ፣ የአረፍተ ነገር መዛባትን ሊያስከትል ይችላል። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት።

አየሰጠ የሚያጅብና የሚያሰፋ እናም የሚያጎላምሰ መዋቅር ነው። ርከኑም በሶስት ብቻ ሳይወሰን ይችላል፡፡ የኮከብ ምልክትዋ (*) የምታመለክተውም ይህን ሁኔታ ነው፡፡

በተራ ቁጥር (12) ከሚታየው ዕፀ-መዋቅር ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ ተዋቃሪዎቹ በሙሉ ተራ ቃላት ይመስላሉ። ይህ ግን ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም መሪው ስም ብቻ ነው፣ ተራ ቃል ሊሆን የሚችለውና የየሀረጉ ዘር በመሆንም አይነቱን የሚወስነው። መሪው ቃል ስም ከሆነ፣ ሀረጉ ስማዊ ይሆናል። መሪው ቃል ቅፅል ከሆነም፣ ሀረጉም እንደዚሁ ቅፅላዊ ይሆናል፣ ወዘተ። የሀረጉ አይነት በመሪው ቃል ክፍል እንደሚወሰን ሁሉ፣ ሀረጋዊ ስፋቱ፣ ይዘቱ ብሎም ርከኑ በተዋቃሪዎቹ ሀረጎች ይወሰናል። ስለዚህም ከመሪው ጋር የሚዋቀሩት ክፍሎች በሙሉ ሀረጎች ናቸው። ባጭሩ አንድ ሀረግ አይነቱን ከመሪው፣ ሀረጋዊ ደረጃውን ከተዋቃሪ መሙሊያዎችና አጎላማሽ ሀረጎች ያገኛል ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

እስካሁን የተመለከትነው አንድ ስም ከአንድ መሙሊያና ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ አጎላማሾች ጋር በተዋረድ እየተዋቀረ ንዑስና አቢይ ስማዊ ሀረግን ሊመሰርት ነው። ከስሙ ጋር የሚዋቀሩት ሀረጎች በነዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም። ከአቢይ ሀረጉ ጋር እየተዋቀሩ ይህንኑ ሀረግ ወደ ከፍተኛ አቢይ ሀረግ ሊያሳድጉ የሚችሉ ሌሎች መዋቅሮች አሉ። እነዚህም ባለፈው ክፍል ያየናቸውና መስተዓምር ያልናቸው ክፍሎች ናቸው። አገባባቸው በየሀረጉ መነሻና አንዳንድ ጊዜም በመድረሻው ላይ ነው። ዝርዘሩን ቆየት ብለን እናየዋለን፡፡ ለጊዘየው የሚከተሉትን ለእብነት እንመልከት።

(ሀ) ያ ጎበዝ የሰዋሰው መምህር 18
(ለ) አንድ የጎጃም የቅኔ መምህር
(መ) የእኛ የእንግሊዝኛ መፅሀፍ
(ሰ) የእንግሊዝኛ-ው መፅሀፍ

የመስተዓምሮች ተግባር አቢይ ስማዊ ሀረጎች የሚገልፁዋቸውን ነገሮች መወሰን ነው። እወሳሰኑም ነገሮቹ ከሚገኙበት ቦታ፣ ከመጠናቸውና ከንዛቢያቸው (ባለቤታቸው) እና ከዚህ በፊት የተጠቀሱና ስለዚህም የታወቁ ከመሆናቸው ወይም ካለመሆናቸው አኳዋያ ነው። በዚሁ መሰረት ጠቋዋሚ፣ መጣኝ፣ አገናዛቢ እና ዕምር (የታወቁ) መስተዓምሮች እንደሚባሉ ባለፈው ክፍል ተገልፆአል። ከነዚህ መካከል የዕምርነቱ ምዕላድ በመሪው ቃል ወይም በአጎላማሹ መድረሻ ላይ ይገኛል፡፡ የሀረጎቹ ወርዳዊ (ቅደም-ተከተላዊ) አቀማመጥ በምሳሌ (ሀ) እንደሚታየው ሲሆን፣ ተዋረዳዊ አቀማመጣቸው ደግሞ ከዚህ በታች እንደተመለከተው ነው።




19

ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፣ መስተዓምሩ ያ የተዋቀረው ከስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ጋር ነው። ተግባሩም ይህ ስማዊ ሀረግ፣ ማለትም ጎበዝ የሰዋሰው መምህር የሚለው ክፍል፣ የሚጠቁመውን ነገር የትነት መወሰን ነው። እንደዚያ እያደረገ ሀረጉን ወደ ከፍተኛ አቢይ ሀረግ (ስሀ3) ያሳድገዋል።

ሶስቱ የመስተዓምር አይነቶች ተከታትለው ሲመጡና ስማዊ ሀረጉን (ስሀ2)ን ሊወስኑ ይችላሉ። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

(ሀ) እነዚያ የእኔ ሁለት [የሰዋሰው መፃህፍት] 20
(ለ) ? የእኔ እነዚያ ሁለት [የሰዋሰው መፃህፍት]
(መ) ? ሁለት የእኔ እነዚያ [የሰዋበው መፃህፍት]

መስተዓምሮቹ የሚወስኑት በቅንፉ ውስጥ የሚታየውን አቢይ ስማዊ ሀረግ ነው። መሰረታዊ ቅደም-ተከተላዊ ብሎም ተዋረዳዊ አገባባቸውም በምሳሌ (ሀ) እንደሚታየው፣ ጠቋሚው ቀድሞ፣ አገናዛቢው እሱን ተከትሎ፣ መጠኑ ደግሞ ሶስተኛ ሆኖ በመሰለፍ ነው። ይህ አገባብ ቢፋለስ፣ ውጤቱ በምሳሌ (ለ) እና (መ) እንደሚታየው ያለ መዛባት ይከሰታል። ይህን ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት እንደሚከተለው እናሳያለን።

[3] መስተዓምሮችም የራሳቸውን ሀረግ ይመሰርታሉ። እንዴት እንደሚመሰርቱ ቆይተን እንመለከታለን።

አሉ እንዴ? የሚል ጥያቄን ያስነሳል። ርግጥ ነው፣ የዚህ አይነት ስሞች አሉ። ስለዚህም ስሞችን መሙሊያ ያላቸውና የሌላቸው ብሎ በሁለት መመደብ ይቻላል። ሁኔታው ግን በስሞች ብቻ የሚወሰን አይደለም፤ ሌሎች የቃላት ክፍሎችንም ያጠቃልላል። ዝርዝሩን ወደፊት እናየዋለን። አሁን መሙሊያ ወደሌላቸው ሀረጎች እንሂድና ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት።

(ሀ) ያች የምስራቅ ኮከብ 23
(ለ) ያች የንጋት ጨረቃ
(ሐ) የገና ጀንበር
(መ) የጥቅምት ውርጭ

የእነዚህ ሀረጎች መሪ ስሞች <u>ኮከብ፣</u> <u>ጨረቃ፣</u> <u>ጀንበር</u> እና <u>ውርጭ</u> የሚሉት ስሞች ናቸው። ከእነዚህ ጋር የተዋቀሩት ጊዜንና ቦታን የሚያመለክቱ ተውሳክ ስማዊ ገላጮችና መስተዓምሮች ናቸው። ተግባራቸውም እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ አንድን ንዑስ ሀረግ ማጎላመስና መወሰን ነው። የየምሳሌዎቹ ንዑስ ሀረግ የተመሰረተው በመሪው ስም ብቻ ነው። ለዚህ ምክንያቱ መሪው ስም የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚገልፅ ሀረግ አለመኖሩና ሊኖርም አለመቻሉ ነው። <u>ቤት</u> ከምን እንደሚሰራ የሚታወቀውን ያህል፣ ኮከብ ከምን እንደሚፈጠር ቢያንስ ለተራው የቋንቋዋ ተጠቃሚ ዕውቅ አይደለም። ስለዚህም እንደ <u>ኮከብ</u> ያሉ ስሞች ገላጭ እንጅ መሙሊያ ሀረግ የላቸውም። በዚህ መሰረት የምሳሌ 23(ሀ) መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል።

24




<u>ኮከብ</u> የሚለው መሪ ስም መሙሊያ ስለሌለው፥ ንዑሱን ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) የመሰረተው ብቻውን ነው። አቢዩን ስማዊ ሀረግ (ስሀ2) ግን <u>የምስራቅ</u> ከሚለው ገላጭ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ መስርቶአል። ይህ ደግሞ በተራው <u>ያች</u> ከሚለው ጠቋሚ መስተዓምራዊ ሀረግ ጋር በመቀናጀት ዋናውን ሀረግ ሊመሰርት ችሉአል።

እንደ ኮከብና ጠጅ ባሉ ስሞች መካከል ያለው መዋቅራዊ ልዩነት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ይኸውም እንደ ጠጅ ያሉት፣ ከፍ ሲል እንዳየነው፣ መሙሊያ ሲኖራቸው፣ እንደ ኮከብ ያሉት የሌላቸው መሆኑ ነው። ከዚያ ውጭ ሁሉም ከገላጮችና ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ አቢይ ሀረጋቸውን ስለሚመሰርቱ በመካከላቸው ልዩነት የለም።

እስካሁን ያየነው የነባር ስሞችን ሀረግ አወቃቀር ነው። ከዚህ ቀጥለን የውልድ ስሞችን ባህሪ እንመለከታለን። በክፍል ሁለት እንዳየነው፣ ውልድ ስሞች የሚባሉት ከነባር ስሞች፣ ቅፅሎችና ከስሮች ላይ በመስራች ምዕላድ እማካኝነት የሚፈጠሩ ናቸው። የነዚህ አይነት ስሞች የሀረግ አወቃቀር ባህሪ ከሚወለዱበት ቃል ያወቃቀር ባህሪ ጋር ተመሳሳይ ነው። ምንጩ ቃል መሙሊያ የሚይዝ ከሆነ፣ ውልዱ ቃልም እንደዚሁ መሙሊያ ይይዛል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ዜማ ደረሰ 25
(ለ) ያ የዜማ ደራሲ
(መ) ያ የዜማ ድርሰት

የነዚህ ሀረጎች መሪዎች የተሰመረባቸው ቃላት ናቸው። ሁሉም ውልድ ሲሆኑ፣ እወላለዳቸው /ድ-ር-ስ/ የሚለውን ስር መሰረት ያደረገ ነው። ይህ ስር ደግሞ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋል። የእሱ ውልድ የሆኑት ደረሰ፣ ደራሲ እና ድርሰትም እንደዚሁ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። በግሱና በስሞቹ መካከል ያለው ልዩነት፣ ግሱ መሙሊያዎቹን የግድ ሲፈልግ፣ ስሞቹ ግን የግድ የማይፈልጉ መሆናቸው ነው። በሌላ አነጋገር፣ ስሞቹ ያለመሙሊያቸው ሀረጉን እንደሚከተለው ሊመሰርቱ ይችላሉ።

(ሀ) ያ [ ] ደራሲ 26
(ለ) ያ [ ] ድርሰት
(መ) ? ካሳ [ ] ደረሰ

ቅንፎቹ ዜማ የሚለውን መሙሊያ ቦታ ያመለክታሉ። መሙሊያው በምሳሌ (ሀ) እና (ለ) ቢገደፍም፣ የምሳሌዎቹ ተቀባይነት አልቀነሰም። የምሳሌ (መ) ተቀባይነት ግን ጥያቄ ውስጥ ገብቶአል። ለዚህ ምክንያቱ የመሙሊያው መገደፍ ነው። ይህም እንደ ደረሰ ያሉ ግሶች ያለመሙሊያቸው ሊቆሙ እንደማይችሉ ያሳያል። ዋናው ቁም ነገር፣ ከአንድ ዘር የሚፈጠሩ ቃላት የሀረግ አወቃቀር ባህሪ ሊወራረሱ የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ነው።

ስለ ስማዊ ሀረግ እስካሁን በዝርዝር ያየነውን እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል። ማንኛውም ስማዊ ሀረግ ከመሪ ስም፣ ከመሙሊያ፣ ከተለያዩ ገላጮች እና ከመስተዓምሮች ይመሰረታል። መሪው ስም ከመሙሊያው ጋር ተቀናጅቶ ንዑሱን ሀረግ ይመሰርታል። ይህ ሀረግ ደግሞ ከቅፅላዊና ከተውሳከ ስማዊ ሀረጎች ጋር በተዋረድ እየተዋቀረ አቢዩን ስማዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይህም አቢይ ሀረግ ከመስተዓምሮች ጋር በመቀናጀት ዋናውን ስማዊ ሀረግ ይፈጥራል። መሪው ስም

ሊዋቀር የሚችለው ከአንድ መሙሊያ ሀረግ ጋር ብቻ ነው። ይህም መሙሊያ መሪው ቃል የሚጠቁመው ነገር የተሰራበትን ነገር የሚያመለክት ነው። ከአቢዩ ሀረግ ጋር የሚዋቀሩት መስተዓምሮች ሶስት አይነት ናቸው። እነሱም ጠቋሚ፣ አገናዛቢና መጣኝ ይባላሉ። ጠቋሚው የትነቱን፣ አገናዛቢው የማንነቱን፣ መጣኙ ደግሞ መጠኑን ይወስናል። የንዑሱ ሀረግ መሪ ስም ተራ ቃል ነው። ሀረግ ሊሆን የሚችለው በየርከኑ ከመሙሊያና ከገላጭ ሀረግ ጋር በሚዋቀር ነው። ከየተዋቃሪው ሀረግ ሀረጋዊነትን፣ ከመሪው ስም በማዊነትን ያገኛል። ስሞች መሙሊያ በመያዝና ባለመያዝ በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። መሙሊያ የማይዙት ንዑስ ሀረጋቸውን በመሪው ስም አማካኝነት ብቻ ይመሰርታሉ። በሌላ በኩል ደግሞ መሪ ስሞች ነባርና ውልድ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ውልድ የሆኑት የተወሰዱበትን ቃል መዋቅራዊ ባህሪ ይወስዳሉ። ቃሉ መሙሊያ የሚወስድ ከሆነ፣ እነሱም መሙሊያ ይወስዳሉ። በዚህም ይህን ንዑስ ክፍል ለጊዜው እንቋጫለን። ለጊዜው የምንልበት ምክንያት ወደፊት በሌላ ክፍል ስለምንመለስበት ነው።

## ግሳዊ ሀረግ

ባለፈው ንዑስ ክፍል በሞች ከበማዊ መሙሊያ ሀረግ፣ ከተውሳከ ሰማዊና ቅፅላዊ አንላማሽ ሀረጎች እንዲሁም ከሶስት አይነት መስተዓምሮች ጋር በየደረጃው እየተዋቀሩ ንዑስና አቢይ በማዊ ሀረጎችን ሊመሰርቱ ተመልክተናል። በዚህ ንዑስ ክፍል፣ ግሶች ልክ እንደ በሞች ከመሙሊያዎች፣ ከአንላማሾችና ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ ንዑስና አቢይ ሀረጋቸውን እንዴት እንደሚመሰርቱ እናያለን።

ይህን ለማድረግ ቀና ይሆን ዘንድ፣ ግሶችን በአይነት በአይነታቸው እንከፋፍላቸዋለን። ከትርጉም አንፃር ሲታዩ፣ ግሶች የሁነትና የድርጊት ተብለው በሁለት ብቻ ሊከፈሉ ይችላሉ። የድርጊት የሚባሉት አንድ ሰው የሚፈፅመውን ተግባር የሚገልፁ ናቸው። መጀመሪያ የሚከተሉትን የድርጊት ግሶች እንይ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጠጣ | መጣ | ሄደ | 1 |
| ጠረገ | ሰበረ | ቀደደ | |

የድርጊት ግሶች ባለቤት አድራጊ፣ ማለትም የድርጊቱ ፈፃሚ ነው። ለምሳሌ፣

ካሳ ብርጭቆ ሰበረ 2

ብንል፣ ካሳ የሚለው ስም የድርጊቱ ፈፃሚ ባለቤት መሆኑን መግለፃችን ነው። ድርጊቱ የተፈፀመው በብርጭቆ ላይ ነው። በለዚህም ብርጭቆ ተደራጊ ወይም ድርጊት ተቀባይ ስም ነው።

የሁነት ግሶች የሚባሉት፣ እንደ ሰው የሚፈፅመውን ድርጊት ሳይሆን፣ እሱ ራሱ የሚሆነውን ነገር ወይም የሚገኝበትን ሁኔታ እንዲሁም፣ የሚያሳየውን ባህሪ የሚገልፁ ናቸው። የሚከተሉት የእነዚህ ምሳሌዎች ናቸው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሆነ | ወፈረ | አዘነ | 3 |
| ከሳ | ቀጠነ | ፈዘዘ | |

የእነዚህ አይነት ግሶች ባለቤት ሁዋኝ ስም ነው። አድራጊ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፣

ካሳ አለተማሪ ሆነ 4

ስንል፣ የምንገልፀው የካሳን አስተማሪ የመሆን ነገር ነው። በዚህም ካሳ አስተማሪ ካለመሆን አስተማሪ ወደ መሆን መለወጡን እንረዳለን። ካሳ ወፈረ ስንልም፣ ካለመወፈር ወደ መወፈር መለወጡን እንገነዘባለን። ግሶቹ የሚገልፁት ድርጊትን ሳይሆን፣ ለውጥን ነው። ባለቤታቸውም የለውጡ ተቀባይ ወይም ተለዋጭ ነው።

ከመዋቅራዊ ባህሪ አኳያ ሲታዩ፣ የድርጊትና የሁነት ግሶች የተለያዩ ናቸው። የድርጊት ግሶች ከሚገልፁት ድርጊት ጋር የሚዛመድ መሙሊያ አላቸው። የሁነት ግሶች ግን አንድም መሙሊያ የላቸውም፣ ካላቸውም ከሁኔታው ጋር ሳይሆን፣ ከሁዋኙ ባለቤት ጋር የተገናዘበ ነው። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) ካሳ ብርቱካን በላ 5
(ለ) ካሳ ገበሬ ሆነ

በላ የሚለው የድርጊት ግስ መሙሊያ ብርቱካን የሚለው ስም ነው። ይህ ስም የድርጊቱ ተጠቂ (ተደራጊ) ነው። ከካሳ ጋር ያለው ግንኙነት የአድራጊና የተደራጊነት ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥ ገበሬ የሚለው ስም ሆነ የሚለው ግስ መሙሊያ ነው። ከካሳ ጋር ያለው ግንኙነትም የእኩነት ነው። ሁለቱም የሚጠቁሙት አንድን ነገር ነው። ገበሬው ካሳ ነው፤ ካሳም ገበሬው ነው። በሁለቱ መካከል ልዩነት የለም፡፡

በድርጊትና በሁነት ግሶች መካከል ያለው ሌላው መዋቅራዊ ልዩነት የሚወስዱት የመሙሊያ መጠን ነው። የድርጊት ግሶች አንድ ወይም ሁለት መሙሊያ ሊኖራቸው ይችላል። የሁነት ግሶች መሙሊያ አንድ ብቻ ነው፡፡ እሱም ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ራሱ ሁዋኙ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ [ለአስቴር ገንዘብ ሰጣት] 6
(ለ) ካሳ [ምሳውን በላ]
(መ) ካሳ [ወታደር መሰለ]
(ሰ) ካሳ [ከሳ]

ሰጣት የሚለው የድርጊት ግስ ነው። ሁለት መሙሊያዎች አሉት። እነዚህም የተሰመረባቸው ስሞች ናቸው። በላ የሚለውም እንደዚሁ የድርጊት ግስ ነው። ይሁን እንጅ መሙሊያው አንድ ስም ብቻ ነው። እሱም ምሳውን የሚለው ስም ነው፡፡ መሰለ የሚለው ደግሞ የሁነት ግስ ሲሆን፣ እሱም በላ እንደሚለው ግስ ባለአንድ መሙሊያ ነው። መሙሊያውም ወታደር የሚለው ስም ነው፡፡ በመጨረሻም ከሳ የሚለው ግስ አለ። ይህም እንደ መሰለ የሁነት ግስ ነው። ይሁን እንጅ፣ መሙሊያ የለውም[6]። በጥቅሉ ግሶችን እንደ መሙሊያቸው አይነትና መጠን መከፋፈል ይቻላል። ከዚህ ቀጥለን የምናሳየው የሀረግ አወቃቀር ይህንን ልዩነት መሰረት ያደረገ ነው።

---

[6] ከዚህ ላይም ካሳ ራሱ መሙሊያ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ነገር ላለማከበድ ወደ ዝርዝሩ አንገባም፡፡

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>በድንገት</u> የሚለው ቅንጅት መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ ተግባሩ <u>ወደ ጎንደር ሄደ</u> የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መግለፅ ነው። አገላለፁም የአካሄዱን ሁኔታ በመወሰን ነው። በምሳሌ (ለ) ውስጥም <u>በሀይል</u> የሚለው እንደዚሁ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፥ ተግባሩ የድንጋጤውን ደረጃ መግለፅ ነው። ሁለቱ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ገላጭ አጎላማሾች ሲሆኑ፣ ሁለቱ ንዑስ ሀረጎች ደግሞ ተገላጭ መሪዎች ናቸው። ከላይ በቅንፍ የሚታየውን የገላጭና የመሪ አቀማመጥ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ምሳሌ (ሀ)ን ብቻ በዐፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።




4

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>ወደ ጎንደር</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የግሱ መሙሊያ ሆኖ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)ን መሰርቶአል። <u>በድንገት</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግም የንዑሱ ሀረግ ገላጭ ሆኖ በመግባት አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) አዋቅሮአል። ይህ አቢይ ሀረግ ተጨማሪ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ [ትናንት] [በድንገት] [በመኪና] [ወደ ጎንደር ሄደ]] 5
(ለ) [ [በድንገት] [ትናንት] [በመኪና] [ወደ ጎንደር ሄደ]]
(መ) [ [በመኪና] [ትናንት] [በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ]]

ትናንት፣ <u>በድንገትና</u> <u>በመኪና</u> የሚሉት ሀረጎች <u>ወደ ጎንደር ሄደ</u> የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከጊዜ፣ ከሁኔታና ከማድረጊያ አኳዋያ ይገልፁታል። ቅደም-ተከተላቸውም ሊቀያየር ይችላል። ይህም ሀረጎቹ በተመሳሳይ ርከንና ተግባር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን ያመለክታል። ርከናቸው አቢዩ ሀረግ ሊሆን፣ ተግባራቸው ገላጭነት ነው። ገላጭነታቸውም ለንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ነው። ይህም በስማዊ ሀረጎች ላይ ያየነውን ሁኔታ ሊያስታውሰን ይገባል።

እንደ ምሳሌ 5(ሀ) ያሉ አቢይ ግሳዊ ሀረጎች ከመጣኝ መስተዓምር ጋር በመዋቀር ዋናውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ እንደሚከተለው ይመሰርታሉ።

[ [እንዴ][ [በድንገት] [ወደ ጎንደር ሄደ] ] ] 6

(ሀ) 11




(ለ)




በ11(ሀ) ውስጥ፣ በርግጥ የሚለው ሀረግ በዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ስር ተዋቅሮአል። ገላጭነቱም ለአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ነው። በ11(ለ) ውስጥ ግን ይኸው ሀረግ በአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ስር ተዋቅሮ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1)ን ይገልፃል። ይህን ሊያደርግ የቻለውም ከዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ወርዶ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ጋር በመዳበል ነው። በ11(ለ) ውስጥ፥ ከዋናው አቢይ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ) ስር የሚታየው ነጠብጣብ፣ ሀረጉ ከመውረዱ በፊት የነበረበትን መሰረታዊ ቦታ ያመለክታል።

አረፍተ ነገራዊ ገላጮች ከመሰረታዊ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ሌላ ቦታ የመንቀሳቀስ ዕድላቸው ከሌሎች ገላጭ ሀረጎች የበለጠ ነው። ሌሎች ገላጮች የሚንቀሳቀሱት በአብዛኛው ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ ነው። አረፍተ ነገራዊ ገላጮች

አዛማጅ አረፍተ ነገር ሲሆን፣ መሪው መኪና የሚለው ስም ነው። በምሳሌ 15(ሀ) ውስጥ፣ በርግጥ የሚለው አረፍተ ነገራዊ ገላጭ ግን፣ በ15(ለ) ውስጥ እንደሚታየው ወደ ስማዊ ሀረግነት ሊለወጥ አልቻለም። ይህም በአረፍተ ነገራዊ ገላጮችና በግሳዊ ሀረግ ገላጮች መካከል ላለው ልዩነት ተጨማሪ ማስረጃ ነው። የግሳዊ ሀረግ ገላጮች ብቻ ወደ ስማዊ ሀረግነት የመለወጥ ችሎታ አላቸው።

እንደ ምናልባት ያሉ አረፍተ ነገራዊ ገላጮች፣ እንደ በመኪና ካሉ ከግሳዊ ሀረግ ገላጮች የሚለዩበት ሌላም ሰዋስዋዊ ባህሪ አለ። ይህም አፅንዖት ነው። የግሳዊ ሀረጎች የተለየ ባህሪ ይመለሳል። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) [ካሳ ምናልባት በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ ይሆናል] 16
(ለ) በመኪና ነው [ካሳ ምናልባት ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ የሚሆነው]
(መ) ? ምናልባት ነው [ካሳ በመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄዶ የሚሆነው]

ምሳሌ (ሀ) በለሆሳስ (ያለአፅንዖት) የተነገረ አረፍተ ነገር ነው። ምሳሌ (ለ)፣ በመኪና የሚለው የግሳዊ ሀረግ ገላጭ በአፅንዖት የተነገረበት አረፍተ ነገር ነው። ሀረጉ አፅንዖት ያገኘው፣ ነው ከሚለው ግስ ጋር ተዋቅሮ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ በመገኘቱ ነው። በዚህም ምክንያት ይህ ሀረግ ያዘለው ሀሳብ ከሌሎቹ የበለጠ አፅንዖት ሊያገኝ ችሎአል። በምሳሌ (መ)፣ በተመሳሳይ ሁኔታና ቦታ፣ ምናልባት የሚለው አረፍተ ነገራዊ ገላጭ፣ ነው ከሚለው ግስ ጋር ተዋቅሮ ገብቶአል። ይሁን እንጅ፣ የአረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አጠያያቂ ሆናአል። ከዚህም አረፍተ ነገራዊ ገላጮች አፅንዖታዊ መዋቅር እንደሌላቸው፣ ማለትም በአፅንዖት ሊነገሩ እንደማይችሉ መገንዘብ ይቻላል።

ከዚህ በላይ በዝርዝር ያየናቸው ሁኔታዎች የሚያመለክቱት፣ እንደ ምናልባት ያሉ ሀረጎች እንደ በመኪና ካሉት በአገባብ የተለዩ መሆናቸውን ነው። ልዩነታቸው ያገባብ ብቻ ሳይሆን፣ የተግባርም ነው። እንደ ምናልባት ያሉት ሀረጎች የሚገልፁት፣ አንድ ድርጊት የተፈፀመበትን ሁኔታ ሳይሆን፣ የድርጊቱን ውነትነት ወይም አጠራጣሪነት ነው። ይህ ደግሞ እንደየግለሰቡ ሊለያይ የሚችል የዕምነት ወይም የስሜት ጉዳይ ነው። በዚህም ምክንያት አንዱ ውነት የሚለውን፣ ሌላው ሀሰት ሊለው ይችላል። ስለዚህም እንደዚህ ያሉትን ከግል ስሜት ጋር የሚያያዙ ነገሮችን የሚገልፁ ሀረጎችን ከሌሎች ሀረጎች ለይቶ ማየት ያስፈልጋል። ከፍ ሲል ያየነው ያወቃቀር ልዩነትም ይህን የሚያጠናክር ነው። እንደ ምናልባት ያሉ ሀረጎች መሰረታዊ መዋቅራዊ ዝምድና ከአረፍተ ነገሩ ጋር ሲሆን፣ እንደ በመኪና ያሉት ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ነው። ስለዚህም በመካከላቸው የርከን ልዩነት አለ።

በዚህ ንዑስ ክፍል እስካሁን የተመለከትነው የኢሳቢ ግሳዊ ሀረግን ውስጣዊ ያወቃቀር ስርዓት ነው። ኢሳቢ ግሶች መሙሊያ ሀረግ ሊኖራቸው እንደሚችልና ከዚህም ሀረግ ጋር ንዑስ ግሳዊ ሀረጋቸውን እንዴት እንደሚመሰርቱ አይተናል። መሙሊያው ሀረግ ድርጊት ተቀባይ ወይም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ እንደማይሆንም ተመልክተናል። ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ወይም ስማዊ



8

ይህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው፡፡ የሚገልፀውም ገንዘብ ለተማሪዋ የመስጠትን ድርጊት ብቻ ነው። የሰጭውን ማንነት፣ የአሰጣጡን ሁኔታ፣ ጊዜ፣ ቦታ፣ ምክንያት፣ ወዘተ፣ አይገልፅም። እንደዚህ ያሉትን ተጨማሪ መረጃዎች መስጠት ሲያስፈልግ፣ ልዩ ልዩ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ወይም ወደፊት እንደምናየው ጥገኛ አረፍተ ነገሮችን ከንዑሱ ሀረግ በፊት እንደሚከተለው ማስገባት ያስፈልጋል።

[በፖስታ [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት]] 10

<u>በፖስታ</u> የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት[ የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። ይህ መሰረታዊው ቦታው ነው። በዚህ ቦታ ሆኖ ገንዘቡ የተሰጠበትን ዘዴ ወይም መንገድ ይገልፃል።

እንዳንድ ጊዜ ተሳቢዎቹ ሀረጎች እየቀደሙት ሊገቡ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ የሀረጎቹ ቅደም- ተከተል እንደሚከተለው ይሆናል።

(ሀ) ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ [በፖስታ[– – ሰጣት]] 11
(ለ) ብዙ ገንዘብ ለተማሪዋ [በፖስታ[– – ሰጣት]]

በግልፅ እንደሚታየው፣ ተሳቢዎቹ ሀረጎች በነጠብጣብ የተመለከተውን መሰረታዊ ቦታቸውን ለቀው፣ <u>በፖስታ</u> የሚለውን ገላጭ ሀረግ በመቅደም፣ ከሀረጉ ውጭ ሆነዋል። ይህ አገባብ በአጠቃቀም ጊዜ ለሀረጎቹ አፅንዖት ለመስጠት ሲፈለግ የሚታይ ነው። በተራ ቁጥር (10) የሚታየውን የሀረጎቹን መሰረታዊ አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።




12

ይህ መሰረታዊው የመሙሊያዎቹ (የተሳቢዎቹ) እና የአንላማጅ ሀረግ አቀማመጥ ነው[10]። መሙሊያዎቹ ይህን መሰረታዊ ቦታቸውን እየለቀቁ በተራ ቁጥር (11) እንደሚታየው፣ ከሀረጉ ውጭ ሊሆኑ ይችላሉ። በመሰረታዊው አወቃቀር ደረጃ፣ ይህ አቢይ ሀረግ መጣኝ መስተጻምር ያስፈልገዋል። መስተጻምሩ የሚዋቀረው ከአብዩ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) ጋር ነው። ይህ ሲሆን፣ በተራ ቁጥር (10) የሚታየው ሀረግ የሚከተለውን ይመስላል።

[ሁለት ጊዜ [በፖስታ ስተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጣት]] 13

ይህ ያወቃቀር ስርዓት ባለፈው ንዑስ ክፍል ካየነው ከአሳቢ ግሶች ያወቃቀር ስርዓት ጋር ተመሳሳይ ነው። ልዩነት ቢኖር፣ መሙሊያ በመያዝና ባለመያዝ፣ እንዲሁም በመሙሊያው አይነትና ተግባር ላይ ነው። ሳቢ ግሶች መሙሊያ ሀረግ የግድ ያስፈልጋቸዋል፣ መሙሊያ ሀረጉም ስማዊና መስተዋድዳዊ ሲሆን፣ ተግባሩ ተሳቢነት ነው። በተራ ቁጥር (13) የተመለከተው አቢይ ሀረግ በዐውመቅር ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።

[10] መሰረታዊው አገባብ ርባዑ ተሳቢ ቀድሞ፣ ኢርባዑ እሱን ተከትሎ የሚገኝበት ነው፤ ለማለት ይቻላል፡፡ ተዋረዳዊ አቀማመጣቸውም ከዐፀ መዋቅር (9) እንደሚታየው ሶስትዮሽ ሳይሆን ሁለትዮሽ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ ይህም ከትውረት አንፃር ነው፡፡ ለጊዜው ወደ ዝርዘሩ አንገባም፡፡




14

ይህ የተሟላ ሀሳብ ያዘለ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ላይ ሊጨመር የሚችለው ገንዘብ የመስጠቱን ተግባር የሚፈፅመውን ሰው የሚጠቁም ስማዊ ሀረግ ነው። ይህ ሀረግ ከዚህ አቢይ ግሳዊ ሀረግ ጋር ሲዋቀር የምናገኘው እንደሚከተለው ያለ አረፍተ ነገርን ነው።

[ያ ልጅ [ሁለት ጊዜ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]] 15

በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ የሚታየው፣ አቢዩ ግሳዊ ሀረግ ነው። በውጪኛው ቅንፍ ውስጥ የሚታየው የድርጊቱን ፈፃሚ የሚያመለክተው ስማዊ ሀረግ ነው። ይህ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። አረፍተ ነገሩ የተሟላ ሀሳብ ይሰጣል። ይህን ሀሳብ የሚያጠራጥር ወይም የሚያረጋግጥ ሀረግ መጨመር ይቻላል። ሀረጉም የሚዋቀረው ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ከአጠቃለዩ አረፍተ ነገር ጋር ነው። ይህም ሲሆን፣ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር የሚከተለውን ይመስላል።

[በርግጥ [ያ ልጅ ሁለት ጊዜ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]] 16

<u>በርግጥ</u> የሚለው አረጋጋጭ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ ውጭ ነው። ከዚህ ቦታ ላይ ሆኖ፣ መሉ አረፍተ ነገሩን ያጎላምሳል። ስለዚህም ነው ቀደም ሲል፣ አረፍተ ነገራዊ አጎላማሽ ነው ያልነው። ከአረፍተ ነገሩ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ዝምድና እንደሚከተለው እናሳያለን።



17

አረፍተ ነገራዊ አጎላማሾች ከግሳዊ ሀረግ አጎላማሾች የሚለዩባቸው ሁለት ባህሪያት እንዳሉዋቸው ቀደም ሲል ገልፀናል። እነዚህም ወደ ስማዊ ሀረግ ሊለወጡ አለመቻላቸውና በአረፍተ ነገሩ ውስጥ እንደ ልብ ሲንቀሳቀሱ መቻላቸው ናቸው። ይህ ሁኔታ በሚከተሉት ምሳሌዎችም ይታያል፡

(ሀ) ያ ልጅ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>የሰጠበት ፖስታ</u> 18
(ለ) *ያ ልጅ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>የሰጠበት ርግጥ</u>

<u>በፖስታ</u> የሚለው የግሳዊ ሀረግ አጎላማሽ ገንዘብ <u>የሰጠበት ፖስታ</u> ወደሚል ስማዊ ሀረግ መለወጥ ሲችል፣ <u>በርግጥ</u> የሚለው አረፍተ ነገራዊ አጎላማሽ ግን ይህን ማድረግ እንዳልቻለ፣ የምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ማጣት ምልክት ነው።

የአረፍተ ነገራዊ አጎላማሾችን የእንደልብ እንቅስቃሴ ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ያ ልጅ <u>በርግጥ</u> [በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል] 19
(ለ) ያ ልጅ በፖስታ <u>በርግጥ</u> [ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]
(መ) ያ ልጅ በፖስታ ለተማሪዋ <u>በርግጥ</u> [ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]
(ለ) ያ ልጅ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ <u>በርግጥ</u> [ሰጥቶአታል]
(ረ) [ያ ልጅ በፖስታ ለተማሪዋ ብዙ ገንዘብ ሰጥቶአታል]፣ <u>በርግጥ</u>

<u>በርግጥ</u> የሚለው ሀረግ በተራ ቁጥር (16) ከሚታይበት መሰረታዊ ቦታው በመነሳት፣ ሁሉንም ሀረግ እያቋዋረጠ እስከ አረፍተ ነገሩ መጨረሻ ድረስ እንደሄደ ማየት ይቻላል። በተራ ቁጥር (16) ሙሉውን አረፍተ ነገር ያጎላምሳል። በተራ ቁጥር (19) ግን ከሚገኝበት ቦታ ቀጥሎ ያለውን ሀረግ ብቻ ያጎላምሳል። በ19(ረ) ውስጥ፣ በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ ቢገኝም፣ የሚያጎላምሰው ሙሉውን አረፍተ ነገር ነው። ርግጥ፣ አጎለማመሱ በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ላይ ሆኖ እንደሚፈፀመው አይደለም፤ ጥንካሬ ይጎለዋል። ማንኛውም በመጨረሻ የሚነገር፣ አንድም መጀመሪያ ተረስቶ ድንገት ትውስ ያለ፣ አለያም አፅንዖት ሊሰጠው ያልተፈለገ ነገር ነው።

ወደ መግቢያው አካባቢ፣ ግሶችን የድርጊትና የሁነት ብለን በሁለት ከፍለን ነበር። እስካሁን ያየነው የድርጊት ግቦችን መዋቅራዊ ባህሪ ብቻ ነው። እነሱንም ኢሳቢና ሳቢ ብለን በሁለት ንዑስ ክፍሎች በመለየት ከንዑስ እለከ አቢይ ሀረግ ድረስ ያለውን ያወቃቀር ስርዓታቸውን ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የሁነት ግሶችን ባህሪ እንመረምራለን።

## *የመሆን ግስ ሀረግ*

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የመሆን ግስ የሚባሉት ድርጊትን ሳይሆን፣ ሁነትን ወይም በአንድ ቦታ መገኘትን ያመለክታሉ። ባለቤታቸው ሁዋኝ ወይም ነዋሪ ስማዊ ሀረግ ነው። ሁነትን የሚያመለክቱት ባለቤቱን ለማዊ ሀረግ በአቻነት የሚገልፅ መሙሊያ ይፈልጋሉ። ኑረትን (መኖርን) የሚያመለክቱት ነዋሪው ባለቤት የሚገኝበትን ቦታ የሚያመለክት መስተዋድዳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

(ሀ) ካሳ አስተማሪ ሆነ (1)
(ለ) ካሳ ጎበዝ ሆነ
(መ) ካሳ አስተማሪ ነው
(ስ) ካሳ ጎበዝ ነው
(ረ) ካሳ አስተማሪ ይመስላል
(ሸ) ካሳ ጎበዝ ይመስላል
(ቀ) ካሳ ቤት ውስጥ አለ

<u>ሆነ</u>፣ <u>ይመስላል</u> እና <u>ነው</u> አንድ ነገር መሆንን ስለሚያመለክቱ፣ የመሆን ግስ ናቸው። <u>አለ</u> የሚለው በአንድ ቦታ መገኘትን ስለሚያመለክት፣ የመኖር ግስ ነው። መኖርና መሆን ተቀራራቢ ናቸው። ለምሳሌ፣ አንድን ሰው " ኖእዚ ሀ ሁን " ስንል፣ እዚህ ቦታ ተቀመጥ ወይም ተገኝ ማለታችን ነው። እዚያ ቦታ ሲቀመጥ ወይም ሲገኝ ደግሞ፣ <u>እዚህ አለ</u> እንላለን። በዚህ ምክንያት ሁለቱንም አይነት ግሶች በአንድ ስም የመሆን ግሶች እንላቸዋለን።

መዋቅራዊ ልዩነት ግን አላቸው፤ ይኸውም፣ የመኖር ግሶች ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ለመመስረት መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲፈልጉ፣ የመሆን ግሶች ቅፅላዊ ወይም ስማዊ ሀረግ የሚፈልጉ መሆናቸው ነው። የሀረጎቹ ተግባርም እንደዚሁ ይለያያል። የመሆን

የሚወሰዱትን ግሳዊ ቅፅል በማለት ልንለያቸው እንችላለን። ስማዊ የሚባሉት እንደ ሆዳም፣ አመለኛ፣ እልኸኛ፣ ወዘተ፣ ያሉት ሲሆኑ፣ ግሳዊ የሚባሉት ደግሞ እንደ ጎበዝ፣ ጥቁር፣ ቀይ፣ ወዘተ፣ ያሉት ናቸው። የሁለቱንም ክፍሎች መዋቅራዊ ስርዓት ከዚህ ቀጥለን በየተራ እንመለከታለን።

## ስማዊ ቅፅል

ስማዊ ቅፅሎች ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ ከስም የሚመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። መዋቅራዊ ባህሪያቸው እንደተመሰረቱበት ስም ባህሪ ይለያያል። ስሙ መሙሊያ የሚፈልግ ከሆነ፣ ቅፅሉም እንደዚሁ መሙሊያ ይፈልጋል። ስሙ መሙሊያ የማይፈልግ ከሆነ፣ ቅፅሉም አይፈልግም። ባጭሩ ውልድ ቅፅሎች የናታቸውን መዋቅራዊ ባህሪ ይወርሳሉ። ጉዳዩ የቅፅሎች ብቻ አይደለም፣ ስሞችም የተመሰረቱበትን ግስ መዋቅራዊ ባህሪ ይወርሳሉ። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) ሁለት መፅሀፍ <u>ሸጠ</u> 2
(ለ) የሁለት መፅሀፍ <u>ሻያጭ</u>

ምሳሌ 2(ሀ) ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>ሸጠ</u> የሚለው ሳቢ ግስ ሲሆን፣ የተዋቀረው <u>ሁለት መፅሀፍ</u> ከሚለው መሙሊያ ለማዊ ሀረግ ጋር ነው። 2(ለ) ስማዊ ሀረግ ነው። መሪው <u>ሻያጭ</u> የሚለው ውልድ ስም ነው። የተወለደው <u>ሸጠ</u> የሚለው ሳቢ ግስ ከተወለደበት ስር ነው። ስለሆነም እሱም እንደ ግሱ ከመሙሊያ ጋር ተዋቅሮአል። የሁለቱ ሀረጎች ልዩነት የአይነት እንጅ ያወቃቀር አይደለም። ስማዊና ግሳዊ ከመሆናቸው በስተቀር መዋቅራዊ ይዘታቸውም ሆነ አያያዛቸው ተመሳሳይ ነው።

በዚሁ አይነት የስማዊ ቅፅሎችን መዋቅራዊ ባህሪ እንመለከታለን። ከላይ እንደተገለፀው፣ ስማዊ ቅፅል የሚባሉት ከስም ላይ የሚመሰረቱ ናቸው። እንደዚህ ያሉ ቅፅሎች መሙሊያ የላቸውም። ስለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት በመሪው ቅፅል አማካኝነት ብቻ ነው። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) [እልኸኛ] 3
(ለ) [አመለኛ]

የመጀመሪያው <u>እልህ</u>፣ ሁለተኛው <u>አመል</u> ከሚለው ስም ላይ የተመሰረቱ ቅፅሎች ናቸው። ለሞቹ መሙሊያ እንደማይፈልጉ ሁሉ፣ ቅፅሎቹም እንደዚሁ አይፈልጉም። የመጀመሪያውን ምሳሌ ንዑስ ሀረግ እንደሚከተለው እናሳያለን።

ከአረፍተ ነገሩ ትርጉም ለመረዳት እንደሚቻለው፣ ካሳ እና አሰቴር እኩል [ሽማግሌ አታላይ] ናቸው። እንደ የሚለው መሰተዋድድም አነፃፃሪ ነው።

[እንደ ካሳ ሽማግሌ አታላይ] የሚለው አንድ አሀዳዊ ሀረግ መሆኑን ከሚከተለው ምሳሌ ማረጋገጥ ይቻላል።

(ሀ) [እንደ ካሳ ሽማግሌ አታላይ] [አሰቴር [ --- ] ነች] 5
(ለ) አስቴር [እንደ ካሳ [ሽማግሌ አታላይ]] ነች፣ አልማዝስ?
(መ) እሱዋ እንኳዋ [ —— ] አይደለችም

በምሳሌ (4) [እንደ ካሳ ሽማግሌ አታላይ] የሚለው ሀረግ ነች ከሚለው ግስ በፊት ገብቶአል። ይሀ መስረታዊ ቦታው ነው። በምሳሌ 5(ሀ) ውስጥ፣ ይኸው ሀረግ አስቴር የሚለውን የአረፍተ ነገሩን ባለቤት ቀድሞ ገብቶአል። ይህን ያደረገው በተራ ቁጥር (4) የነበረበትን መሰረታዊ ቦታውን በመልቀቅ ነው። የለቀቀውም ያለ ምንም ቀሪ እንደ አንድ አካል ሆኖ ከቦታው በመንቀሳቀስ ነው። ይህም ቅንጅቱ አንድ መዋቅር ለመሆኑ ማስረጃ ነው። በተጨማሪም፣ በምሳሌ (መ) ውስጥ ይኸው ሀረግ ከቦታው ተገድፎአል። የተገደፈውም አሁንም ያለ ምንም ቀሪ ነው። ቅንጅቱ አንድ አሀዳዊ መዋቅር ባይሆን ኖሮ፣ የዚህ ምሳሌ ተቀባይነት አጠራጣሪ ይሆን ነበር።

የሀረጉን ውስጣዊ አቀነጃጀት እንደሚከተለው በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን።

6




እንደ በሚለው መስተዋድድ አማካኝነት የሚመሰረቱ እንደ ካሳ ያሉ ንፅፅራዊ የመስተዋድድ ሀረጎች አስቴርና ካሳ እኩል አታላይ መሆናቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ይህን እቻነት የሚያሳየው እንደ የሚለው መስተዋድዳዊ መሪ ነው። ከዚህም የተነሳ ይህን መሪ አደላዳይ መስተዋድድ ልንለው እንችላለን። አደላዳይ ማለትም እኩል አድራጊ ማለት ነው። የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።

አስቴር [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር]] ነች 7

ደፋር የሚለው ደፈረ የሚለው ሳቢ ግስ ከተመሰረተበት ስር ላይ የተመሰረተ ቅፅል ነው። ስለዚህም እሱም እንደ ግሱ ሳቢ ነው። በመሆኑም መሙሊያ ይፈልጋል። ስለዚህም ጨለማ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [ጨለማ ደፋር] የሚለውን ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህ ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ደግሞ [እንደ ካሳ] ከሚለው አነፃፃሪ የንፅፅር መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር]] የሚለውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ መስርቶአል።

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ በጣም ከሚለው መጣኝ መስተዓምር ጋር ተዋቅሮ ዋናውን አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ እደሚከተለው ይመሰርታል።

[በጣም [እንደ ካሳ [ጨለማ ደፋር]]] 8

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ፣ በዕፀ-መዋቅር ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል።




9

ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ዋናው ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ) ከመጣኝ መስተዓምርና ከአቢዩ ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ2) የተዋቀረ ነው። ቅፅላዊው ሀረግ የዋናው ሀረግ መሪ ነው። ይህ መሪ ሀረግ (ቅሀ2) ከአነፃፃሪ መስተዋድዳዊ ሀረግና ከንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ (ቅሀ1) ጋር ተዋቅሮአል። ንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ የአቢዩ ሀረግ መሪ ነው። በመጨረሻም

ንዑሱ ቅፅላዊ ሀረግ <u>ጨለማ</u> ከሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግና <u>ደፋር</u> ከሚለው ቅፅል ጋር እንደተዋቀረ እናያለን። ቅፅሉ የንዑሱ ሀረግ መሪ ነው።

እስካሁን ያየነው የአወቃቀር ስርዓት ከግሳዊ ሀረግና ከስማዊ ሀረግ ስርዓት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። በሁሉም ውስጥ መስተዓምር፣ አንላማሽና መሙሊያ አለ። የእያንዳንዳቸው ወርዳዊና ተዋረዳዊ አገባብም አንድ አይነት ነው። በሁሉም ሀረጎች መስተዓምሩ ያቀድማል፤ ገላጩ ይከተላል፤ መሙሊያው ይቀጥልና መሪው መጨረሻ ላይ ይመጣል። በሶስቱ የሀረግ አይነቶች መካከል ያለው ልዩነት በመሙሊያው ላይ ነው። ይኸውም የስማዊና የቅፅላዊ ሀረግ መሙሊያ በቦታው ሊገኝ ወይም ላይገኝ ይችላል። የግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ግን የግድ በቦታው መገኘት አለበት። መስተዓምሮቹና አንላማሾች በሶስቱም የሀረግ አይነቶች ውስጥ በቦታቸው ላይገኙ ይችላሉ። ከዚህ ስንነሳ በሶስቱም ሀረጎች ውስጥ ከቦታው መጥፋት የሌለበት የግስ መሙሊያ ብቻ ነው። ይህም ግስን ከስምና ከቅፅል የምንለይበት ዋና መዋቅራዊ ባህሪ ነው። ቅፅልንም ከስም የምንለይበት መዋቅራዊ ባህሪ አለ። እሱም የአንላማሹ አይነትና ተግባር ነው። እስተውስን ከሆነ፣ የቅፅል አንላማሽ ሁል ጊዜ ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው።

## ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

ባለፉት ንዑስ ክፍሎች የስማዊ፣ የግሳዊና የቅፅላዊ ሀረጎችን የአወቃቀር ስርዓት ለማየት ሞክረናል። ሁሉም ንዑስ ሀረጋቸውን ከመሙሊያ ሀረጎችና ከመሪዎች፣ አቢይ ሀረጋቸውን ከተለያዩ አንላማሽ ሀረጎችና ከንዑስ ሀረግ እንደሚመሰርቱ ተረድተናል። አቢይ ሀረጎቹ ደግሞ በተራቸው ከመስተዓምሮች ጋር እየተዋቀሩ ዋናውን አቢይ ሀረግ ሲመሰርቱ አይተናል። በሁሉም ሀረጎች ውስጥ የመሪው ቦታ በስተቀኝ ነው። ይህ ያወቃቀር ስርዓት ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎችንም ሊያጠቃልል ይችል እንደሆነ፣ ከዚህ ቀጥለን እንመረምራለን።

ዶጋግመን እንደጠቀስነው፣ ተውሳከ ግስ የሚባለው ክፍል እንደሌሎቹ ክፍሎች በርካታ ቃላት የሉትም። ባንፃሩ ግን የተለያዩ ተውሳከ ግሳዊ የሚባሉ በርካታ ተግባራት አሉ። እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው።

የሁኔታ 1
የጊዜ
የምክንያት
የማድረጊያ
የቦታ
የንፅፅር
ወዘተ

እነዚህ ተውሳከ ግሳዊ ተግባራት የሚገለፁት በአብዛኛው በስማዊ ሀረግ፣ በመስተዋድዳዊ ሀረግና በጥገኛ አረፍተ ነገሮች አማካኝነት ነው። በዚህም ምክንያት፣ እንደነዚህ ያሉ ሀረጎችን ብዙ ጊዜ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች እንላቸዋለን።

በቋዋንቋዋው ውስጥ የሚገኙት ጥቂት መደበኛ ተውሳከ ግሶች የሚከተሉት ናቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| (ሀ) | ቶሎ | (ለ) | ክፉኛ | 2 |
| | ገና | | ግምኛ | |
| | እንደገና | | ድልኛ | |
| | መቸ | | ምንኛ | |

በ(ሀ) ስር ያሉት ነባር ተውሳከ ግሶች ሲሆኑ፣ በ(ለ) ስር ያሉት ግን /-ኛኛእ/ በሚለው መስራች ምዕላድ አማካኝነት ከቅፅሎች ላይ እንደሚመሰረቱ በምስረታው ክፍል ተመልክተናል።

ተውሳከ ግሶች መሙሊያ የላቸውም። ስለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት በመሪው ቃል ብቻ ነው። በዚህ መዋቅራዊ ባህሪያቸው ከሌሎቹ የቃላት ክፍሎች ይለያሉ። ቀደም ሲል በተከታታይ እንዳየነው፣ ሌሎቹ ክፍሎች በከፊልም ቢሆን፣ መሙሊያ አላቸው። በግስ ክፍል ውስጥ፣ ሳቢ ግሶች ያለመሙሊያ አይቆሙም። ስሞችና ቅፅሎችም ከመሙሊያ ጋር ሲዋቀሩ ይችላሉ። ርግጥ፣ መሙሊያዎቹ ቀሪ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ረገድ ተውሳከ ግሶች ልዩ ናቸው። ከሌሎቹ ጋር የሚመሳሰሉት በአቢይ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው። ምክንያቱም በዚህ ደረጃ እንደ ማንኛውም የሀረግ ክፍል ከመስተዋድዳዊ ሀረግና ከመጣኝ መስተዓምር ጋር ሊዋቀሩ ይችላሉ። መስተዋድዳዊ ሀረጉ ግን የተወሰነ ነው። የሚከተሉትን እንመልከት።

(ሀ) እስቴር [እንደ ካሳ [ክፉኛ]] ወደቀች 3

(ለ) እስቴር [እንደ ካሳ [ቶሎ]] ተነሳች

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ሲሆን፣ ቅንጅቱም በውስጠኛው ቅንፍ ውስጥ ከሚታዩት [ክፉኛ] እና [ቶሎ] ከሚሉት ተውሳከ ግሶች ጋር ነው። ተግባሩም የእስቴርን የአወዳደቅ ሁኔታ ከካሳ የአወዳደቅ ሁኔታ ጋር ማነፃፀር ነው። ስለዚህም ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መዋቅራዊ ስርዓቱን በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።

4




[እንደ ካሳ] የሚለው ንፅፅራዊ ሀረግ ተግባር፣ የአወዳደቁን ወይም የአመጣጡን ሁኔታ፣ ማለትም መጥፎነቱን ወይም ፍጥነቱን፣ መግለፅ ነው። መጥፎነቱም ሆነ ፍጥነቱ የሚገለፀው ደግሞ [ከፉኛ] እና [ቶሎ] በሚሉት ተውሳከ ግሶች ስለሆነ፣ የመስተዋድዳዊ ሀረጉ መዋቅራዊ ግንኙነትም ከነዚሁ ተውሳከ ግሶች ጋር ነው። ተውሳከ ግሶቹ በሀረጉ በስተቀኝ ስለሚገኙ፣ ሀረጉ ቀኝ መሪ ነው።

ከዚህ ላይ የተውሳከ ግስንና የቅፅልን መዋቅራዊ ባህሪ ተመሳሳይነት ልብ ልንል ይገባል። የሁለቱም ገላጭ ሀረግ ንፅፅራዊ መስተዋድድ ነው። ሁለቱም ከፍሉች ገላጭ ስለሆኑ፣ የተግባር አንድነት አሳቸው። ይህ የተግባር አንድነት መዋቅራዊ ተመሳሳይነትን ሊያስከትል ችሉአል። በመካከላቸው ያለው ልዩነት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ነው። ቅፅሎች መሙሊያ ሲኖራቸው፣ ተውሳከ ግሶች የላቸውም።

ቀደም ሲል ስለ ቅፅላዊ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ግንኙነት ከተውሳከ ግሱ ጋር ሳይሆን፣ ከእሱ ጋር ከተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው፤ ሊባል ይችላል። ይህም ማለት፣ ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው እረፍተ ነገር ውስጥ፣ [እንደ ካሳ] የሚለው ሀረግ ግንኙነት [ከፉኛ] ከሚለው ተውሳከ ግስ ጋር ሳይሆን፣ [ከፉኛ ወደቀ] ከሚለው ግሳዊ ሀረግ ጋር ሊሆን ይችላል። ይህም ሲሆን፣ ንፅፅራዊ ገላጭነቱ በተውሳከ ግሱ ለተገለፀው ሁኔታ ሳይሆን፣ በግሱ ለተገለፀው ድርጊት ሊሆን ይችላል። የመስተዋድዳዊው ሀረግ አገባብ እሻሚ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ንፅፅራዊ ሀረጉ ግሳዊንም ሆነ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግን ሊገልፅ የሚችል መሆኑ ነው። ከተውሳከ ግሱ ጋር ያለው አቀነጃጀት ከፍ ሲል እንደተመለከተው ሲሆን፣ ከግላዊ ሀረጉ ጋር የሚኖረው ግንኙነት ደግሞ ከዚህ በታች እንደሚታየው ነው።

5




መስተዋድዳዊ ሀረጉ የተውሳከ ግሱ ወይም የግሳዊ ሀረጉ አጎላማሽ ሊሆን እንደሚችል ዕፀ-መዋቅሮቹ ያመለክታሉ። እንደዚህ አይነቱ መዋቅራዊ አሻሚነት፣ በመዋቅር ደረጃ፣ በዚህ አይነት ሊፈታ ይችላል። ከመዋቅር ባሻገር ግን፣ ለምሳሌ፣ በንግግር ጊዜ፣ አሻሚነቱ ሊፈታ የሚችለው፣ በንግግሩ አውድ ብቻ ነው።

ክፍ፡ ሲል እንደገለፅነው፣ ተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች [በጣም] ከሚሰው መጣኝ መስተዓምር ጋር ሊዋቀሩ ይችላሉ። የመስተዓምሩ ቦታም እንደ ማንኛውም መስተ-ዓምር በሀረጉ መነሻ ላይ ሲሆን፣ ተግባሩም በሀረጉ የተገለፀውን ሁኔታ ከመጠን አንፃር መወሰን ነው። ለምሳሌ፣ [ክፉኛ] ወይም [ቶሎ] ስንል፣ የፍጥነቱን ወይም የክፋቱን ደረጃ አናውቅም። ይህ የሚታወቀው [በጣም] የሚለውን መስተዓምር በመጠቀም [በጣም ቶሎ] ወይም [በጣም ክፉኛ] ስንል ነው። አቢይ ሀረጉ ውስጥ [በጣም] የሚገኘው በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር የሚከተለውን እንመልከት፡




6

ዕፀ-መዋቅሩ [በጣም] የሚለው መስተዓምር ከአቢዩ ሀረግ _እንጉዎ_ ላይ እንደሚወርድና በሀረጉ መነሻ ላይ እንደሚገኝ ያሳያል። ይህ ግን በታህታይ መዋቅር ውስጥ የሚታይ ቅደም-ተከተል ነው። በላዕላይ መዋቅሩ ውስጥ፣ መስተዋድዳዊ ሀረጉ ከቦታው እየተነሳ ወደ አቢይ ሀረጉ መነሻ ስለሚሄድ፣ መስተዓምሩ ከመሪው፣ ማለትም ከ[ቆሎ] ቀድሞ የገባ ሊመስል ይችላል። ይህ ሲሆን ሀረጉ እንደሚከተለው ይሆናል።

[እንደ ካሳ [በጣም [—] ቆሎ ]] 7

በግልፅ እንደሚታየው፣ [እንደ ካሳ] የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በነጠብጣብ የተመለከተውን መሰረታዊ ቦታውን ለቆ፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ገብቶአል። ይህ ሁኔታ በቅፅላዊ ሀረግም ይታያል። የሚከተለውን እንመልከት።

[እንደ ካሳ [በጣም [—] ረዥም]] 8

ይህ አቢይ ቅፅላዊ ሀረግ ነው። መሪው [ረዥም] የሚለው ቅፅል ነው። የሀረጉ ታህታይ እወቃቀር እንደሚከተለው ነው።

[በጣም[ እንደ ካሳ [ረዥም]]] 9

ይህ መዋቅር ከላይ በተራ ቁጥር (7) ከሚታየው ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው። በሁለቱ ሀረጎች መካከል ያለው ልዩነት የአወቃቀር ሳይሆን፣ የአይነት ብቻ ነው። ይኸውም አንዱ ተውሳከ ግሳዊ ሲሆን፣ ሌላው ቅፅላዊ መሆኑ ነው። የሁለቱ መዋቅር ይህን ያህል ተመሳሳይ የሆነው ያለምክንያት አይደለም። ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ ሁለቱም ገላጮች ናቸው። ተውሳከ ግሶቹ ግስን፣ ቅፅሎቹ ስምን ይገልፃሉ። ስምና ግስ ተገላጭ፣ ቅፅልና ተውሳከ ግስ ገላጭ እንደሆኑ፣ በምዕራፍ ሁለት ስለ ቃላት ክፍል ስንወያይ ገልፀናል፡፡

ወደ መስተዓምሩ እንመለስና አንድ ጥያቄ እናንሳ። ይኸውም [በጣም] የሚለው መጣኝ መስተዓምር ታህታይ ቦታ በሀረጉ መነሻ ላይ ስመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? የሚል ነው። ቀደም ሲል ሌሎቹን አስመልክተን እንደ ገለፅነው ሁሉ፣ አንድ መሪ ቃል ንዑስ ሀረጉን የሚመሰርተው ከመሙሊያ ጋር በመዋቀር ወይም ያለ መሙሊያ ብቻውን በመቆም ነው። ምርጫው መሙሊያ በመፈለግና ባለመፈለግ ነው። በማንኛውም መንገድ የተዋቀረ ንዑስ ሀረግ የተለያዩ ገላጮች ያስፈልጉታል። ገላጮቹ ሀረጉን ከጊዜ፣ ከምክንያት፣ ከዓላማ፣ ከማድረጊያ፣ ወዘተ፣ አኩዋያ ተጨማሪ መረጃ በመስጠት በቅርፅም ሆነ በይዘት ያጎላምሉታል። በዚህ ሁኔታ ያደገ ሀረግ መጠኑን የሚገለፅበት መጣኝ ሀረግ ያስፈልገዋል።

መጣኞቹ እንደ [በጣም] ያሉ የመጠን መስተዓምሮች ናቸው። ቦታቸውም ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በሀረጉ ውስጥ ያሉ ሌሎች ቦታዎች በሙሉ ሀረጉን እየሞሉና እያጎላመሉ በሚገቡት መሙሊያዎችና ገላጮች ስለሚያዙ ነው። አንድ መሪ ሀረጉን መዞና አሳድጎ የሚጨርሰው በመሙሊያዎችና በገላጭ አጎላማሾች ነው። በእነዚህ እየታጀበ ካደገ በሁዋላ መጠኑን የሚያሳይበት መጣኞች፣ የትነቱን የሚያሳይበት ጠቋሚዎች፣ እንዲሁም የማንነቱን የሚያሳውቅበት አገናዛቢዎች ያስፈልጉታል። እነዚህም ሊገቡ የሚችሉት በመነሻው ላይ ነው። የሀረጉን ይዘት ሊወስኑ የሚችሉት ሙሉ ሀረጉን እየቀደሙ በመነሻ ላይ ሊገቡ ነውና፡፡ ከሀረጉ መሀል ቢገኙ፣ ሊወስኑ የሚችሉት ሙሉውን ሀረግ ሳይሆን፣ ከሚገኙበት ቦታ ጀምሮ ያለውን የሀረጉን ከፊል አካል ብቻ ይሆናል። በሌሎቹ ሀረጎች ያየነው ሁኔታም እንደዚሁ ነበር። መስተዓምሮቹ የየሀረጉ መነሻ ናቸው። በዚህም የተውሳከ ግስን ብቻ ሳይሆን የዋና ዋናዎቹን የቃላት ክፍሎች የሀረግ አወቃቀር ስርዓት እናጠቃልላለን።

## መስተዋድዳዊ ሀረግ

እስካሁን ያየነው የዋና ዋና ቃላት ክፍሎችን የሀረግ አወቃቀር ስርዓት ነው። ዋና ዋና የቃላት ክፍሎች የሚባሉት፣ ትርጉም ወይም ይዘት ያላቸው ክፍሎች ናቸው። እነዚህም የስም፣ የግስ፣ የቅፅልና የተውሳከ ግስ ክፍል ቃላት ናቸው። ሌሎቹ የቃላት ክፍሎች መስተዋድድና መስተዓምር ናቸው። እነዚህ የይዘት ሳይሆን፣ የግብር ቃላት ክፍሎች ናቸው። ከዚህ ቀጥለን የነዚህን ሁለት ክፍሎች ስርዓተ-መዋቅር እንመለከታለን። መጀመሪያ የመስተዋድዶችን እንመልከት።

እንደ ሌሎች የቃላት ክፍሎች ሁሉ፣ መስተዋድዶችም ንዑስና አቢይ ሀረጎችን ይመሰርታሉ። ንዑስ ሀረጎችን የሚመሰርቱት ከመሙሊያዎች ጋር በመዋቀር ነው። መሙሊያዎቹም ስማዊ ሀረጎች፣ መስተዋድዳዊ ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች ናቸው።

(ሀ) [ወደ [ትልቁ ትምህርት ቤት]] 3
(ለ) [[እስከ [ትልቁ ትምህርት ቤት]] ድረስ]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ <u>ወደ</u> የሚለው መስተዋድድ [ትልቁ ትምህርት ቤት] ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። ስማዊ ሀረጉ መሙሊያ ነው። መሪው መስተዋድድ ከዚሁ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። አገባቡም ትልቅ የሚለው ተለጣፊ በመሆን ነው። ተለጣፊነቱ በተለይ <u>ወደቤት</u> ለንልና ለንፅፍ የጎላ ነው።

በምሳሌ (ለ) ውስጥ፣ <u>ድረስ</u> የሚለው መስተዋድድ [እስከ ትልቁ ትምህርት ቤት] ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮአል። አገባቡ መሙሊያውን ተከትሎ ነው። የሁለተኛውን ሀረግ ያወቃቀር ስርዓት በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።

4




በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>ድረስ</u> የሚለው መሪ መስተዋድድ ነው፡፡ [እስከ ትልቁ ትምህርት ቤት] የሚለውን መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግ ተከትሎ በስተቀኝ በኩል ገብቶአል። <u>እስከ</u> የሚለው የመሙሊያው መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪ ነው፡፡ እሱም [ትልቁ ትምህርት ቤት] የሚለውን መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ቀድሞ ገብቶአል። ሁኔታው የሁለቱ የመነሻና የመድረሻ መስተዋድዶች አገባብ ለየቅል መሆኑን ያስረዳል። ይህም ልዩነት ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ምናልባት ከመሪዎቹ መስተዋድዶች ራስን ችሎ ከመቆምና ካለመቆም የሚመጣ ሊሆን ይችላል። ራሳቸውን ችለው የሚቆሙት መሪዎች መሙሊያውን ተከትለው ሲገቡ፣ ራሳቸውን ችለው የማይቆሙት፣ መሙሊያውን እየቀደሙ ይገባሉ። አገባባቸውም በተለጣፊነት ነው። ይህ ልዩነት ግን መሰረታዊ ሳይሆን፣ በመዋቅሩ ላዕላይ ገፅታ ላይ የሚከሰት የመሪና የመሙሊያ ዝምድና ነው፣ ለማለት ይቻላል። በመሰረታዊ (ታህታይ) አወቃቀር ደረጃ ላይ፣ የማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪ ቦታ ከመሙሊያው

በስተቀኝ በኩል ነው፣ ብሎ ማሰብ ይቻላል። በዚህም መሰረት፣ በተራ ቁጥር (4) የሚታየው መዋቅር ታህታይ አወቃቀር እንደሚከተለው ይሆናል።




5

ይህ መዋቅር መስተዋድዳዊ መሪዎቹ ከመሙሊያዎቹ በስተቀኝ እንደገቡ ያሳያል። ይህም የማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ ስርዓት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ መሪው ከመሙሊያው እየቀደመ የሚገባው በላዕላይ መዋቅር ነው። በተራ ቁጠር (4) የሚታየውም ይኸው ነው።

የመሪው ቦታ ከመሙሊያው በስተቀኝ ለመሆኑ ማስረጃው ሌሎቹ ቀደም ሲል ያየናቸው ሀረጎች መሪ በስተቀኝ መሆኑ ነው። ለምሳሌ ትልቁ ትምህርት ቤት የሚለው ስማዊ ሀረግ መሪ ትምህርት ቤት የሚለው ጥምር ስም ሲሆን፣ ቦታውም በስተቀኝ ነው። እንደ ካሳ ሽማግሌ ደፋር የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ መሪም ደፋር የሚለው ቅፅል ሲሆን፣ የእሱም አገባብ እንደዚሁ በቀኝ በኩል ነው። ባለፈው ንዑስ ክፍል ያየነው የግሳዊ ሀረግ ስርዓትም እንደዚሁ ነው። ከዚህ አጠቃላይ የአገባብ ሁኔታ ስንነሳ፣ ሀረጎች በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው ብሎ መደምደም ይቻላል።

ከላይ የሚታዩት የንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ምሳሌ ናቸው። ከዚህ ቀጥለን የአቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን መዋቅር እንመለከታለን።

(ሀ) [ከወገብ [በታች]] 6
(ለ) [እንደ አሳ [በባህር]]

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ በታች የሚለው ከፍል ንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። መሪው በ የሚለው መስተዋድድ ሲሆን፣ መሙሊያው ታች የሚለው ስም ነው[12]። በምሳሌ (ለ) ውስጥ፣ ደግሞ ይኸው መስተዋድድ ባህር ከሚለው ስም ጋር ተዋቅሮአል። እነዚህ ንዑስ ሀረጎች ከወገብ እና እንደ አሳ ከሚሉት ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ተዋቅረው አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረግ መስርተዋል። ከወገብ የሚለው ገላጭ

---

[12] ስም ነው ከማለት ይልቅ መስተንምር ነው ማለቱ ይቀላል፤ ሁኔታውን ወደሁዋላ እናየዋለን፡፤

በባህር ይኖራሉ 9

የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ እናገኛለን። ይህም ንዑስ ግሳዊ ሀረግ እንደ አሳ ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀርና፣

እንደ አሳ በባህር ይኖራሉ 10

የሚል አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርት ይችላል። በዚህም ምክንያት እንደ አሳ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የግሳዊው ሀረግ አጎላማሽ አካል ይሆናል። አሻሚ የአወቃቀር ስርዓት አለው ማለት ነው። በአንድ በኩል፣ በ6(ለ) እንደሚታየው፣ በባህር ከሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር፣ በሌላ በኩል፣ በባህር ይኖራሉ ከሚለው ግሳዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀር ይችላል። ይህን አሻሚነት በዐፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።

11




በግልፅ እንደሚታየው፣ በ11(ሀ) ውስጥ እንደ አሳ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ገላጭ ሆኖ ገብቶአል። መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በ11(ለ) ውስጥ፣ ይኸው ሀረግ በባህር የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ገላጭ ሆኖ ገብቶአል። መዋቅራዊ ግንኙነቱም ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ነው።

የዚህ አይነት መዋቅራዊ አሻሚነት የገላጭ ሀረጎች ባህሪ ነው። አንድ መዋቅር ከሌላ መዋቅር ጋር ሲቀናጅ፣ የአንደኛው መዋቅር ገላጭ ሀረግ፣ የሌላውም ገላጭ ሆኖ ሊታይ ይችላል። ገላጭነቱ ለአንዱ ወይም ለሌላው መሆኑን ከላይ በሚታየው ሁኔታ በዐፀ-መዋቅር እየለዩ ማሳየት ይቻላል።

ወደ መስተዋድዳዊ ሀረጎቹ ውስጣዊ አወቃቀር እንመለስ። አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከመጣኝ መስተዓምር ጋር እየተዋቀሩ ዋናውን አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረግ

ይመሰርታሉ። ይህን ሲያደረጉም በገላጮች ላይ ያየነው መዋቅራዊ አሻሚነት ይከሰታል። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

(ሀ) [[አንድ ጊዜ ] [እንደ አሳ በባህር ]] ዋኙ 12
(ለ) [ [ሁለት ጊዜ ] [እንደ ወፍ በሰማይ]] በረሩ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ [አንድ ጊዜ] እና [ሁለት ጊዜ] የሚሉት መጣኝ መስተዓምሮች ናቸው። መዋቅራዊ ግንኙነታቸው [እንደ አሳ በባህር] እና [እንደ ወፍ በሰማይ] ከሚሉት መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ነው። የሚያሳዩትም የባህሩን እና የሰማዩን ነገር ነው። ለምሳሌ <u>ሁለት ጊዜ ወደ ላይ፣</u> <u>አንድ ጊዜ ወደ ታች</u> ለንል፣ መጣኝ ሀረጎቹ የሚገልፁት የላይነቱንና የታችነቱን መጠን ነው። ርግጥ ነው፣ መጣኞቹ ሀረጎች የመዋኘቱንና የመብረሩን መጠንም ሊገልፁ ይችላሉ። ይህን ሲያደረጉም መዋቅራዊ ግንኙነታቸው ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ይሆናል። ይህን አሻሚነት እንደሚከተለው እናሳያለን።

(ሀ) 13



(ለ)




በምሳሌ (ሀ) <u>አንድ ጊዜ</u> የሚለው መጣኝ ሀረግ ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ተዋቅሮአል። የሚገልፀውም የመዋኘቱን ተግባር መጠን ነው። በምሳሌ (ለ) ደግሞ ይኸው ሀረግ፣ ከመስተዋድዳዊ ሀረጉ ጋር ተዋቅሮአል። የሚገልፀውም <u>እንደ አሳ</u> በባሀር የመሆኑን መጠን ነው። በምሳሌ (11) እና (13) የምናየው ገላጮችና መስተ-ዓምሮች አሻሚ የሆነ መዋቅራዊ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ነው። መስተ-ዓምርነታቸው ለግሳዊ ሀረግ ወይም በግሳዊ ሀረግ ውስጥ ለሚገኝ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊሆን ይችላል። ገላጮችም እንደዚሁ።

እስካሁን በዚህ ንዑስ ክፍል ስለ መስተዋድዳዊ ሀረግ በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን። መስተዋድድ በሚባለው ክፍል ውስጥ የሚገኙ ቃላት አገባብ በመስተዋድዳዊ ሀረግ፣ ከስማዊ ሀረግና ከአረፍተ ነገር ጋር እንደሆነ አይተናል። ከአረፍተ ነገር ጋር የሚዋቀሩት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተፃምር ይባሉ የነበሩት ናቸው። ተግባራቸው አንድ አረፍተ ነገር በሌላ አረፍተ ነገር ውስጥ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን ማመልከት ነው። መስተዋድዶች ከስማዊ ሀረግና ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር በመቀናጀት ንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። ንዑስ ሀረጎቹ ደግሞ ከገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር እየተቀናጁ አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን ይመሰርታሉ። በንዑስ ሀረጉ ውስጥ የሚገቡት

መሙሊያዎቹ ሊሆኑ፣ በአቢይ ሀረጉ ውስጥ የሚገቡት አጎላማሾች ናቸው። አጎላማሾቹ እንደ ንፅፅራዊ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ያሉ ናቸው። አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከመጣኝ ስማዊ ሀረጎች ጋር እየተዋቀሩ ዋናውን አቢይ መስተዋድዳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ። ይሀ የመጣኙ ሀረግ አወቃቀር በርግጥ ከመስተዋድዳዊው ሀረግ ጋር መሆኑ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም፡፡ ምናልባትም የመጣኙ ሀረግ ግንኙነት ከግሳዊ ሀረጉ ጋር ነው የሚለው አመለካከት የበለጠ አስተማማኝ ሊሆን ይችላል፡፡ ጉዳዩን ለጊዜው በዚሁ እንተወዋለን፡፡

በሳፅሳይ መዋቅር፣ የመስተዋድዳዊ ሀረጎች መሪ በቀኝ ወይም በግራ ሊገኝ ይችላል። ይህም የሚሆነው በንዑስ ሀረግ ደረጃ ነው። በአቢይ ሀረግ ደረጃ፣ መሪው ምን ጊዜም በቀኝ በኩል ነው። በግራ በኩል የሚታዩት መስተዋድዳዊ መሪዎች ራሳቸውን ችለው ለመቆም የማይችሉት ናቸው። አጠቃላዩ የቁዋንቁዋው የሀረግ አመሰራረት ስርዓት መሪውን በቀኝ በኩል የሚያሳይ ስለሆነ፣ በዚሁ መሰረት በታሀታይ ደረጃ መስተዋድዳዊ ሀረጎችም በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው ብለን አጠቃለናል።

መስተዋድዳዊ ሀረጎች ለግሳዊ ሀረግ ወይም ለመስተዋድዳዊ ሀረግ ገላጭ እየሆኑ ስለሚገቡ፣ መዋቅራዊ ግንኙነታቸው አሻሚ ሊሆን ይችላል። ገላጩ ሀረግ ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ወይም ከግሳዊ ሀረግ ጋር መሆኑን ለይቶ በመዋቅር ማሳየት ይቻላል። መስተዓምሮችም እንደ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከግሳዊ ሀረግ ወይም ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ስለሚዋቀሩ፣ አሻሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ አይተናል። ከየትኛው ሀረግ ጋር እንደተዋቀሩ መዋቅራዊ በሆነ መንገድ ማሳየት ይቻላል።

## *መስተዓምራዊ ሀረግ*

ስለ ቃላት ክፍሎች ስንወያይ እንደገለፅነው፣ መስተዓምር የሚባለው ሶስት አይነት የግብር ቃላትን የያዘ ክፍል ነው። ክፍሎቹም ጠቋሚ፣ አገናዛቢና መጣኝ መስተ-ዓምሮች ናቸው። ጠቋሚና አገናዛቢ መስተዓምር የሚባሉት ተውላጠ ስሞችን በሙሉ ያጠቃልላሉ። መጣኝ የሚባሉት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ የመጠንና የአህዝ ቅፅል የሚባሉትን ይይዛሉ።

እስካሁን ድረስ በዚህ ክፍል ያየነው፣ እያንዳንዱ የቃላት ክፍል ከሌሎች ክፍሎች ጋር እየተቀናጀ ሀረግ ሲመሰርት ነው። የስም ክፍል ስማዊ ሀረግ፣ የቅፅል ክፍል ቅፅላዊ ሀረግ፣ የግስ ክፍል ግሳዊ ሀረግ፣ ወዘተ፣ ሊሆን አይተናል። ከንዑስ የቃሳት ክፍልም መስተዋድድ የሚባሉት፣ መስተዋደዳዊ ሀረግን ሲመሰርቱ አይተናል። በዚሁ አካሄድ፣ መስተዓምር የሚል ንዑስ የቃላት ክፍል ካለ፣ መስተ-ዓምራዊ ሀረግ የሚል መዋቅር መመስረቱ አይቀሬ ነው። እያንዳንዱ ክፍል ሀረግ የመመስረት ችሎታ አለው ብለናልና። ሀረጉም የሚመሰረተው፣ በመስተዓምሩና ለመሙሊያዎች አማካኝነት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት።

[ያ [ትልቅ ]የቅኔ ተማሪ]]]

ቀደም ሲል ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ እንደተገነዘብነው ከሆነ፣ ይህ የስማዊ ሀረግ መዋቅር ነው። መሪው ተ<u>ማሪ</u> የሚለው ስም ሲሆን፣ <u>የቅኔ</u> የሚለው የዚህ መሪ ስም መሙሊያ ነው። መሪውና መሙሊያው [የቅኔ ተማሪ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ መስርተዋል። <u>ትልቅ</u> የሚለው ቅፅል የዚህ ንዑስ ስማዊ ሀረግ ገላጭ እጎላማሽ ነው። <u>ያ</u> የሚለው ደግሞ [ትልቅ [የቅኔ ተማሪ]] የሚለውን አቢይ ስማዊ ሀረግ የሚጠቁም መስተዓምር ነው። ይህ እንግዲህ መዋቅሩ እንደ አንድ ስማዊ ሀረግ ሲተነተን ነው።

ከላይ ባነሳነው የነገር አካሄድ መሰረት ደግሞ፣ ይህ መዋቅር እንደ ስማዊ ሳይሆን፣ እንደ መስተዓምራዊ ሀረግ ሲተነተን ይችላል። አተናተኑም፣ <u>ያ</u> የሚለውን መስተዓምር እንደ መሪ፣ [ትልቅ [የቅኔ ተማሪ]] የሚለውን አቢይ ስማዊ ሀረግ የዚሁ መሪ መሙሊያ አድርጎ በመቁጠር ነው። እንደ ማንኛውም መሪ፣ መስተዓምሩ ከመሙሊያው ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ንዑሱን መስተዓምራዊ ሀረግ ይመሰርታል። አወቃቀሩን በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።

2




ይህ መስተዓምራዊ ሀረግ ነው። መሪው መስተዓምሩ ሲሆን፣ አገባቡም በሀረጉ መነሻ ላይ ነው። ሁኔታው ቀደም ሲል እንዳየናቸው እንደ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ነው። በንዑስ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ውስጥ መሪው መስተዋድድ መሙሊያውን እየቀደመ ሲገባ አይተናል። ከዚህም ሁለቱ ንዑስ የቃላት ክፍሎች የአወቃቀር ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሁለቱም ስማዊ ሀረግ መሙሊያ አላቸው። በሁለቱም መሪው በሀረጉ መነሻ ላይ ይገኛል። ይህ ግን በላዕላይ መዋቅር ደረጃ ነው።

መስተዓምራዊው መሪ ከሌላ መስተዓምራዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀርና ንዑስ መስተዓምራዊ ሀረግ ሊመሰርት ይችላል። ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል።

ያ ትልቅ-ኦ የቅኔ ተማሪ 3

በዚህ ምሳሌ ውስጥ ሁለት መስተዓምሮች አሉ። እነሱም ያ እና /-ኦ/ ናቸው። /-ኦ/ ቅጣይ መስተዓምር ነች። ይህም ቀደም ሲል እንዳየናቸው ቅጣይ መስተዋድዶች አይነት መሆኑ ነው። የተቀጠለው ከቅፅሉ ላይ ነው። ይሁን እንጅ መስተዓምርነቱ ለቅፅሉ ሳይሆን፣ ለአጠቃላዩ ስማዊ ሀረግ ነው። ይህ ውነት ከሆነ፣ መዋቅራዊ ዝምድናው ከስማዊ ሀረጉ ጋር መሆን አለበት። ታህታይ አገባቡም ስማዊ ሀረጉን ተከትሎ ነው። ይህ ለመሆኑ ማስረጃው ስማዊ ሀረጉ ገላጭ በሌለው ጊዜ፣ መስተ-ዓምሩ የሚቀጠለው ከመሪው ስም ላይ መሆኑ ነው። ይህም እንደሚከተለው ነው።

ተማሪ-ው 4

መስተዓምሩ /-ኦ/ ከስሙ ላይ እንደተቀጠለ ማየት ይቻላል። ይህን መሰረት በማድረግ፣ በተራ ቁጥር (3) ውስጥም የዚሁ መስተዓምር ታህታይ አገባብ ከስማዊ ሀረጉ ቀጥሎ ነው፣ ለማለት ይቻላል። አወቃቀሩንም በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው ማሳየት ያቻላል።

5



በግልፅ እንደሚታየው፣ የሁለቱ መስተዓምሮች አገባብ የተለያየ ነው። ያ በመነሻ ሲገባ፣ /-እ/ የሚለው ቅጣይ መስተዓምር ግን በመድረሻ ገብቶአል። ይህም ከፍ ሲል የጠቀስነውን የመስተዋድዶችን አገባብ የሚያስታውሰን ይመስላል። እንደ /ለ/ ያሉ ቅጣይ መስተዋድዶች በመነሻ ሲገቡ፣ እንደ ድረስ ያሉ ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ መስተዋድዶች፣ በመድረሻ ላይ እንደሚገቡ አይተናል። ይሁን እንጅ፣ ከዚህ ላይ የምናየው የቅጣይ መስተዓምሩ አገባብ ከቅጣይ መስተዋድዶች አገባብ የተለየ ነው። ምክንያቱም መስተዓምሩ የሚገባው በመድረሻ ላይ በመሆኑ ነው። ቀደም ሲል፣ የስማዊ፣ የግሳዊ፣ የቅፅላዊ እና የተውሳከ ግሳዊ ሀረጎች መሪ በቀኝ በኩል ስለሆነ፣ ከዚሁ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት፣ የመስተዋድዳዊ ሀረጎች መሪ ታህታይ በታም እንደ ሌሎቹ ሁሉ በሀረጉ መድረሻ ነው ፣ ብለን ደምድመን ነበር። በዚያው ድምዳሜ መሰረት፣ የመስተዓምራዊ ሀረጎች መሪም ታህታይ አገባብ በሀረጉ መድረሻ ነው ፣ ለማለት ይቻል ይሆናል። ጉዳዩ ሰፋ ያለ ጥናት ያስፈልገዋል፡፡ ከዚያ በመለስ ግን ከላይ በተራ ቁጥር (2) እና (5) የተመለከቱትን መስተዓምራዊ ሀረጎች እንደሚከተለው በአንድ ላይ አካቶ ማበቀመጥ ይቻላል።

6




ከዚህ ላይ ትልቅ የቅኔ ተማሪ የሚለው ስማዊ ሀረግ /-እ/ ከሚለው መስተዓምር ጋር በመሙሊያነት ሊዋቀር ችሎአል። የመዋቅሩ ውጤት ስማዊ ሳይሆን፣ መስተዓምራዊ ሀረግ ነው። ምክንያቱም መሪው መስተዓምር ስለሆነ ነው።

ስማዊ ሀረግ ገብቶአል። ይህም መስተዓምር መሙሊያ እንጅ አንሳማሽና መስተዓምር እንደሌለው ያሳያል።

ከላይ ከሚታየው መዋቅር አሁንም አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ይኸውም ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ፣ አንድ ስማዊ ሀረግ መስተዓምር እንደሚኖረውና ቦታውም ከእቢዩ ስማዊ ሀረግ ስር እደሆነ ገልፀን ነበር። አሁን ደግሞ መስተዓምሩ ከስማዊ ሀረጉ ውጭ ራሱን ችሎና ስማዊ ሀረጉን መሙሊያ አድርጎ እንደሚዋቀር እያየን ነው። እነዚህ ሁለት አመለካከቶች አይጣረሱም ወይ? የሚል ነው። መልሳችን አይጣረሱም ነው። መስተዓምሮቹን ጠቋዋሚ፣ መጣኝ እና አገናዛቢ ብለን በሶስት ከፍለናቸው ነበር። ከነዚህ መካከል ጠቋዋሚውና መጣኙ ከፍ ሲል በተገለፀው መሰረት ከስማዊ ሀረግ ጋር እየተቀናጁ የራሳቸውን ሀረግ ይመሰርታሉ። በዚህ አካሄድ የጠቋዋሚው መስተዓምራዊ ሀረግ አወቃቀር በተራ ቁጥር (5) እንደተመለከተው ሲሆን፣ የመጣኝ መስተዓምራዊ ሀረግ አወቃቀር ግን እንደሚከተለው ነው።

8




አንድ የሚለው መጣኝ መስተዓምር ትልቅ የቅኔ ተማሪ ከሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ ንዑሱን መጣኝ መስተዓምራዊ ሀረግ አዋቅሮአል።

ከመጣኙና ከጠቋዋሚው መስተዓምር የሚለየው አገናዛቢው መስተዓምር ነው። ይህ መስተዓምር እንደሌሎቹ መስተዓምሮች ከስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ መስተዓምራዊ ሀረግ ይመሰርታል። ይህም መስተዓምራዊ ሀረግ እንደገና የሌላ ስማዊ ሀረግ መስተዓምር ሆኖ ይገባል። የሚከተሰውን ምሳሌ እንመልከት።

የልጆቹ የስዕል አስተማሪ 9

በዚህ ምሳሌ፣ የልጆቹ የሚለው መስተዓምራዊ ሀረግ ነው። መስተዓምሩም /-ኡ / ሲሆን መሙሊያው የልጆች የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። በዚህ ሀረግ መነሻ ላይ የምትታየው የ አገናዛቢ ምዕላድ ነች። ልጆች የሚለው ስም ባለገንዘብ መሆኑን ታመለክታለች። ከዚህ ግንዘቤ በመነሳት፣ በተራ ቁጥር (9) የተመለከተውን ስማዊ ሀረግ አወቃቀር እንደሚከተለው እናባያለን።

10




ልጆቹ የሚለው ስማዊ ሀረግ አስተማሪ ለሚለው ስም ባለገንዘብ ነው። አስተማሪው የልጆቹ ነውና። ከፍ ቢል እንደተገለፀው፣ የ የሁለቱ ስሞች ዝምድና የገንዘብና የባለገንዘብ መሆኑን ታመለክታለች። አገናዛቢ የተባለችውም ለዚህ ነው።

መስተዓምሩ አገናዛቢ ተውላጠ ስም ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን ከላይ የሚታየው ምሳሌ የሚከተለውን ሊመስል የችላል።

የእሱ የስዕል አስተማሪ 11

<u>የእሱ</u> የሚለው መስተዓምር ነው። ከእሱ ጋር የሚዋቀረው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ተገድፎአል። ስለዚህም መስተዓምሩ ብቻውን ሊቆም ችሎአል። ስማዊ ሀረጉ በማይገደፍበት ጊዜ፣ አጠቃላይ መዋቅሩ የሚከተለውን ይመስላል።

<u>የእሱ ልጆች</u> የስዕል አስተማሪ 12

በዕፀ መዋቅር ሲሰፍር የሚከተለውን ይመስላል።

13




<u>ልጆች</u> የሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ በሚገደፍበት ጊዜ፣ አገናዛቢው መስተዓምር ብቻውን ይቆማል። መሙሊያው ስማዊ ሀረግ የሚገደፈው ከመስተዓምሩ ጋር በቁጥር፣ በፆታና በመደብ አንድ ሲሆን፣ ወይም የሚጠቁመውን ነገር ምንነት ከ<u>ሰውደ ነገሩ</u> ለማወቅ የሚቻል ሲሆን ነው። ለምሳሌ፣ <u>የእሱ ሰው የስዕል አስተማሪ</u> ብንል፣

እሱ የሚለው መስተዓምርና ሰው የሚለው መሙሊያ ተመሳሳይ ነገርን ስለሚያመለክቱ፣ መሙሊያው ሊገደፍ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ መስተዓምሩም ሊገደፍ ይችላል። በዚህን ጊዜ መሙሊያው ስም የ የሚለውን የእገናዛቢ ምዕላድ በማስቀደም የልጆች የሚል ይሆናል። እጠቃላይ ሀረጉም የልጆች የሰዕል አስተማሪ የሚል ይሆናል።

ከዚህ ቀጥለን ጠቋሚዎችና እገናዛቢ መስተዓምሮች በአንድ መዋቅር ውስጥ ሲገኙ፣ ቅደም-ተከተላቸው ምን እንደሚመስል በሚከተለው ምሳሌ እማካኝነት እናሳያለን።

ያ የእሱ እንድ ብርሌ የገብስ ጠላ 14

የገብስ ጠላ የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ከፍ ሲል እንደገለፅነው የአንድ ስማዊ ሀረግ መስተዓምር እገናዛቢ የሆነ ስማዊ ሀረግ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ መሰረት የእሱ ከሚለው እገናዛቢ መስተዓምር ጋር የተዋቀረ መሪ - አልባ ስማዊ ሀረግ አለ፣ ለማለት እንችላለን፡፡ ይህ እገናዛቢ መሪ - አልባ ሀረግ የገብስ ጠላ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር እንደሚከተለው ሆኖ ይዋቀራል።

15



ይህ አቢይ ስማዊ ሀረግ መጀመሪያ አንድ ብርሌ ከሚለው መጣኝ መስተ-ዓምራዊ ሀረግ ጋር ይዋቀራል፡፡ በሁዋላም የእሱ ከሚለው አገናዛቢ መስተዓምር ጋር ይቀናጃል፡፡ ከዚያም ያ ከሚለው ጠቋሚ መስተዓምር ጋር ይዋቀርና ዋናውን መስተዓምራዊ ሀረግ እንደሚከተለው ይመሰርታል።

16




በአጠቃቀም ጊዜ አንድ ብርሌ የሚለው መጣኝ መስተዓምራዊ ሀረግ የእሱ የገብስ ጠላ የሚለውን አገናዛቢ መስተዓምራዊ ሀረግ ቀድሞ ሊገባ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን የአጠቃላዩ ሀረግ ቅደም-ተከተል የሚከተለውን ሊመስል ይችላል፡፡

## መልመጃ

1. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መዋቅሮች አይነትና የአወቃቀር ስርዓት ይግለፁ፡፡

   (ሀ) በጣም ጎበዝ ወዝ አደር
   (ለ) በጣም ተስቃየ
   (መ) በጣም በችግር ኖሩ

2. ከላይ የተሰጡትን መዋቅሮች መሪ ይጥቀሱና መሪ ለመሆናቸው ማስረጃ ይስጡ፡፡

3. በተራ ቁጥር (1) በተሰጡት ምሳሌዎች ውስጥ <u>በጣም</u> የሚለውን መጣኝ መስተዓምር መዋቅራዊ ዝምድና ይግለፁ፡፡

4. <u>ተማሪ</u> ከሚለው ቃል ጋር ሊዋቀር የሚችል፣

   (ሀ) መሙሊያ
   (ለ) ገላጭ
   (መ) መስተዓምር

   ምሳሌ ይስጡ፡፡

5. [.የ የአስቴር የሰዋስው መፅሀፍ] የሚለውን ሀረግ በዕፀ-መዋቅር ተንትነው ያሳዩ፡፡

6 በተራ ቁጥር (5) የተመለከተው ሀረግ አሻሚ ነው፡፡ አሻሚነቱ አስቴር የሚለው ስም ሙያ ላይ ነው፡፡ ስሙ የሚገልፀው የመፅሀፉን ደራሲ ወይም ያዥ (ባለደራ) ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሀረጉን በተለያየ ዕፀ-መዋቅር ተንትነው አሻሚነቱን ያሳዩ፡፡

7. (ሀ) አንዳንድ ጊዜ በጠብ እንለያያለን፡፡
   (ለ) አንዳንድ ጊዜ እንለያያለን፡፡

7(ለ) ከ7(ሀ) ላይ የተመሰረተ ነው ብንል፣ <u>አንዳንድ ጊዜ</u> ስለሚለው መጣኝ ሀረግ አገባብ ምን ድምዳሜ መስጠት እንደሚቻል ያስረዱ፡፡

# አረፍተ ነገር

ሰዋሰው ጨዋታ አማርኛ ቅኔ
አጫውትሻለሁ እያፋታሁ እኔ፡፡

የማን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ባገር ቤት (በገጠር) የተለመደ የዘፈን ግጥም ነው፡፡ ምናልባት *ትውፊታዊ* ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከዚህ ላይ ልንጥቅሰው የፈለግነው ያለምክንያት አይደለም፡፡ የቅኔንና የሰዋሰውን ግንኙነት የሚገልፅ ህዝባዊ ይትበሀል ሆኖ ለላገኘነው ነው፡፡ ቅኔ፣ በተለይም ሰምና ወርቅ የሚባለው ዘርፍ መሰረቱ ብሎም ትንታኔው አንዳንድ ጊዜ ቃላዊ፣ አንዳንድ ጊዜ ሰዋስዋዊ ነው፡፡ ቃላዊ የሚሆነው፣ ከአንድ በላይ ትርጉም ከሚሰጥ ቃል ላይ ሊመሰረት ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ቅኔ ውስጥ እያፋታሁ የሚለው ቃል የዚህ ምሳሌ ነው፡፡ ቅኔ እየተረጎምኩ ወይም ባል እያፋታሁ ተብሎ፡ በሁለት መንገድ ሊተነተን ይችላል፡፡ ዘፋኙ ቅኔ እየተረጎምኩ አጫውትሻለሁ የሚል መስሎ፣ ከባልሽ ጋር እያፋታሁ እኔ አጫውትሻለሁ ይላታል፡፡ በአንድ ቅርፅ ሁለት መልዕክት አስተላልፎአል ማለት ነው፡፡

ሰዋሰዋዊ የሚሆነው ቅኔው ከአንድ በላይ ያወቃቀር ስርዓት ሊኖረው ከሚችል መዋቅር ላይ ሊመሰረት ነው፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡

ሞጣ ቀራንዮ ምነው አይታረስ
በሬሳላይ መጣሁ ከዚያ እስከዚህ ድረስ[1]፡፡

በሁለተኛው ስንኝ ውስጥ የሚታየው በሬሳላይ የሚለው መዋቅር ንበት አሻሚ ነው፡፡ እንደ ግሳዊ ወይም እንደ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊነበብ ይችላል፡፡ በግሳዊ ሀረግ ቅርፁ በሬ ሳላይ ተብሎ ይነበባል፡፡ በዚህ መልኩ ሰውዬው ብዙ አገር አቋርጦ ሲመጣ፣ በሬ እንዳላየ ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው መዋቅር በሬሳ ላይ ተብሎ እንደ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊነበብ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ከመጀመሪያው ሀረግ የተለየ ትርጉም ይሰጣል፡፡ ይኸውም ከሞጣ ጀምሮ ያለው ህዝብ ስላለቀ፣ መንገዱ ሁሉ ሬሳ ብቻ ነው፤ የሚል ነው፡፡ እንግዲህ አንዱ ላዕላይ መዋቅር አንድ ጊዜ እንደ ግሳዊ፣ ሌላ ጊዜ እንደ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሆኖ ሊነበብ እና ሊተነተንም በመቻሉ የተለያየ ትርጉም ሊሰጥ ችሎአል፡፡ ቅኔውም የተመሰረተው ከዚህ አሻሚ ንበት ላይ ነው፡፡ ሁኔታው ባለፈው ክፍል ስለ ሀረግ ስንወያይ ያየነውን አሻሚነት ሊያስታውሰን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

[የጎጃም ነጭ ጤፍ እንጀራ]



[1] ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወ.መ. (1959፡72)

ይህ ስማዊ ሀርግ ነው፡፡ የሀረጉ መሪ እንጀራ የሚለው ስም ሲሆን፣ ነጭ ጤፍ የሚለው መሙሊያው፣ የጎጃም የሚለው ደግሞ አጎላማሹ ነው፡፡ በዕፀ-መዋቅር ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

2




በዚህ መልኩ፣ ሀረጉ ከጎጃም ስለ መጣ ነጭ ጤፍ እንጀራ ይገልፃል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የጎጃም ነጭ ጤፍ የሚለው፣ እንጀራ ለሚለው ስም መሙሊያ ሆኖ ሊገባ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን አወቃቀሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

3



በዚህ መልክ ሲታይ፣ መዋቅሩ ጤፉ የጎጃም መሆኑን ይገልፃል፡፡ እንጀራው የተጋገረው አዲስ አበባ ሊሆን ይችላል፤ ጤፉ ግን የጎጃም ነው፡፡ በተራ ቁጥር (2) በሚታየው ውስጥ እንጀራው የጎጃም ነው፤ ጤፉ የጎንደር ሊሆን ይችላል፡፡

ዋናው ቁም ነገር የቃላቱም ሆነ የመዋቅሩ አሻሚነት አይደለም፡፡ ይህ የታወቀ የቋዋንቋዋ ባህሪ ነው፡፡ በሰነ-ፅሁፍ እንደውበት ይቆጠራል፡፡ ትልቁ ነገር ምንም ትምህርት የሌላቸው የቋዋንቋዋው ተናጋሪዎች፣ ይህን አሻሚነት ለመገንዘብና ጥልቅ በሆነ ቅኔያዊ ንግግር ለመጠቀም መቻላቸው ነው፡፡ ይህ ችሎታ ባይኖራቸው ኖሮ፣ ለአባባሉ የተለያየ ትርጉም እየሰጡ ሰዛ ባሰው ሚስጥራዊ አማርኛ አይነጋገሩም ነበር፡፡ ችሎታው ራሱ ምንድን ነው? ከምንስ ይመጣል? እንዴትስ ይገለፃል? እነዚህ የስነ-ልሳንን ብቻ ሳይሆን፣ የሰነ-አዕምሮ ሰዎችንም ሲያነጋግሩ የኖሩ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው፣ በተለያየ ጊዜም የተለያየ መልስ ተሰጥቶአቸዋል፡፡ ወደ መልሶቹ አንሄድም፡፡ የእኛ ፍላጎት የችሎታውን ምንጭ ማወቅ ሳይሆን፣ ችሎታውን ራሱን በተቻለ መጠን ለመግለፅ መሞከር ነው፡፡

ችሎታው ባለፉት ክፍሎች በተከታታይ ለማሳየት እንደሞከርነው፣ ድምፅን ከድምፅ፣ ምዕላድን ከምዕላድ፣ ቃላትን ከቃላት፣ ሀረግንም ከሀረግ ጋር በወርድና በተዋረድ እያቀናጁ የተለያዩ መዋቅሮችን የመፍጠርና ለየመዋቅሮቹም የተለያየ ቃላዊና ሀረጋዊ ትርጉም የመስጠት ነው፡፡ ሀሳብን በሚገባ ለመግለፅ የሚቻለው ድምፅንም ሆነ ቃላትን በተናጠል በመደርደር ሳይሆን፣ በወርድና በተዋረድ እያቀናጁ ሰፋፊ መዋቅሮችን በመፍጠርና የተለያየ ትርጉም በማላበስ ወይም በመስጠት ነው፡፡ የአንድ ቋዋንቋዋ ተናጋሪዎች የተፈጥሮ ልሳናዊ ችሎታም በመሰረቱ ይኸው ነው፤ መዋቅር፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው በከፊልም ቢሆን፣ የዚህ አይነት ያወቃቀር ባህሪ ያላቸውን መዋቅሮች ነው፡፡ በከፊል ያልንበት ምክንያት ጉዳዩን በተለያየ ደረጃ ባለፉት ክፍሎችም እያየነው ስለመጣን ነው፡፡

ባለፈው ክፍል ያየነው የተለያዩ ሀረጎችን ያወቃቀር ስርዓት ነው፡፡ እያንዳንዱ የአቢይና የንዑስ ቃላት ክፍል ከሌላ የቃላት ክፍል ጋር እየተዋቀረ ንዑስና አቢይ ሀረግ ሲመሰርት አይተናል፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ከሀረግ ሰፋ ያለ ይዘት ያላቸውን መዋቅሮች ስርዓት እናያለን፡፡ እነዚህም የአረፍተ ነገር መዋቅሮች ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ የሚደረገው ጥናት በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ሰዋሰው በመባል ይታወቃል፡፡ ስዚህ ነው፣ አኛም ይህን ክፍል "ሰዋስው ጨዋታ..." በሚል ስንኝ የጀመርነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ሰዋስው የሚለው ቃል ዛሬ የሚሸፍነው ፅንሰ-ሀሳብ ከጥንቱ የሰፋ ነው፡፡ ዛሬ፣ በጠባቡ ሲታይ፣ ቃሉ መዋቅርን ብቻ ይመለከታል፡፡ በሰፊው ሲታይ፣ አጠቃላይ የቋዋንቋዋ ትንተናን ወይም ጥናትን ያካትታል፡፡ ስለዚህም አሻሚ ነው፡፡ አሻሚነቱን ለማስወገድ፣ ቃሉን፣ ሰፊውን የቋዋንቋዋ ትንተናን ብቻ ለማመልከት እንጠቀምበታለን፡፡ ጠባቡን የመዋቅርን ክፍል ለማመልከት ስነ-መዋቅር የሚለውን ቃል

እንጠቀማለን። በዚያውም ስነ-መዋቅር የሰዋሰው፣ ማለትም የስፌው የቋዋንቋዋ ጥናት አንድ ንዑስ ክፍል መሆኑን እናስገነዝባለን።

## የአረፍተ ነገር አይነቶች

ባለፉት ሁለት ክፍሎች የቃላት ክፍሎችንና የሀረግ አይነቶችን ተመልክተናል። የሀረግ አይነቶች በቃላት ክፍሎች እንደሚመሰረቱና በነሱም እንደሚወሰኑ ተገንዝበናል። ለምሳሌ ስማዊ ሀረግ በስም ክፍል ወስጥ በሚመደቡ ቃላት ይወሰናል። ከዚህ አኳዋያ የአረፍተ ነገር አይነት በምን ላይ ይመሰረት ይሆን?

ወደ አረፍተ ነገር አይነቶች ከመግባታችን በፊት ስለ አረፍተ ነገር ምንነት ትንሽ እንወያይ። አረፍተ ነገር በቁሙ የነገር መቋዋጫ ወይም ማረፊያ ማለት ነው። አንድ ሀሳብ ተሙዋልቶ ከተገለፀ በሁዋላ፣ ሌላ ሀሳብ እስኪመጣ ድረስ የሚደረግ ረፍት እንደማለት ነው። በቅርፁ አረፍተ ነገር የተለያዩ ሀረጎች በወርድና በተዋረድ ተቀናጅተው የሚመሰርቱት ስፌ መዋቅራዊ አሀድ ነው። ለስነ-ልሳናዊ ትንተናም አቢዩም ሆነ ንዑሱ አሀድ እሱ ነው። አንድ መዋቅር ከአረፍተ ነገር ከበለጠ፣ ድርሳን፣ ከአረፍተ ነገር ካነሰ፣ ሀረግ ይሆናል። ሁለቱም ለስነ-ልሳናዊ ትንታኔ አይሆኑም፤ ካልቸገረ በስተቀር። ድርሳኑ ይበዛል፤ ሀረጉም የዚያኑ ያህል ሊያንስ ይችላል። ድርሳኑ በአረፍተ ነገር ደረጃ ሊታዩ የማይችሉ ባህሪያትን ያጣቅሳል። ስለዚህም ድርሳኑን በድርሰት፣ አረፍተ ነገሩን በመዋቅር እየለዩ ለየብቻ ማጥናት ያስፈልጋል። ርግጥ ይህ ሲባል፣ አረፍተ ነገሩ ድርሰታዊ ዳራ አይኖረውም ማለት አይደለም። የጥናቱ ትኩረት በዳራው ላይ ሳይሆን በአረፍተ ነገሩ አወቃቀር ላይ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ከአጠቃቀም አንፃር፣ አረፍተ ነገር የተለያዩ ተግባራት አሉት። ከነዚህም አንዱ ሙሉ ሀሳብን መግለፅ ነው። ሙሉ ሀሳብ ለንል ምን ማለታችን እንደሆነ፣ በሚከተሉት ምሳሌዎች እናስረዳለን።

(ሀ) አንድ ትልቅ ልጅ 1
(ለ) በሁለት ብር
(መ) አራት እንቁላል ገዛ

እነዚህ ሰስት የተለያዩ ሀረጎች ናቸው። የመጀመሪያው ስማዊ፣ ሁለተኛው መስተዋድዳዊ፣ መጨረሻው ደግሞ ግሳዊ ሀረጎች ናቸው። በተናጠል ሲነገሩ፣ ሀረጋዊ ሀሳብ ይገልፃሉ። ሀረጋዊ ሀሳብ ግን ሙሉ አይደለም። ስለዚህም ጥያቄ ያስከትላል። ለምሳሌ የመጀመሪያውን ሀረግ ወስደን፣

አንድ ትልቅ ልጅ 2

ብንል፣ የሚሰማን ሰው፣

አንድ ትልቅ ልጅ ምን ሆነ ወይም ምን አደረገ? 3

ብሎ መጠየቁ አይቀርም፡፡ ጥያቄውን አይቀሬ የሚያደርገው፣ <u>አንድ ትልቅ ልጅ</u> ከማለት በስተቀር፣ ስለ ልጁ የተናገርነው ሌላ ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ባለመኖሩም የሀሳብ ጉድለት ሊከሰት ችሎአል፡፡ እንደዚሁም፣

በሁለት ብር 4

ብለን ብናቆም፣ አሁንም በሁለት ብር ምን ተደረገ? የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ ጥያቄው መነሳቱ አሁንም የጎደለ ሀሳብ ለመኖሩ ምልክት ነው፡፡

አራት አንቁላል ገዛ 5

የሚለውም እንደዚሁ በተናጠል ቢነገር፣ ማነው የገዛው? ያሰኛል፡፡ ሶስቱም ሀረጎች በተናጠል ሲነገሩ፣ *<u>አይቀሬ</u>* ጥያቄ ያስከትላሉ ማለት ነው፡፡ ጥያቄ የሚነሳው የሀሳብ ጉድለት ወይም ግድፈት ሲከሰት ስለሆነ፣ ሀረጎቹ ሀሳበ-ጎደሎ ናቸው፣ ለማለት ይቻላል፡፡

ሀረጎቹን በተናጠል ሳይሆን፣ በአንድ ላይ ብናቀናጃቸው፣

አንድ ትልቅ ልጅ በሁለት ብር አራት እንቁላል ገዛ 6

የሚል ሰፊ መዋቅር ይሰጡናል፡፡ ይህ መዋቅር ከፍ ሲል እንደተነሱት ያሉ አይቀሬ ጥያቄዎችን አይጋብዝም፡፡ ጥያቄ አለማስነሳቱ የሚጠቁመው የጎደለ ሀሳብ አለመኖሩን ነው፡፡ ስለዚህም ሙሉ <u>ሀረጋዊ</u> መዋቅር ነው፡፡ ርግጥ ለሚያችን መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ ከማን ጋር ገዛ? እያለ ሊመረምረን ይችላል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎች ግን ከፍ ሲል እንደ ተነሱት አይቀሬ አይደሉም፡፡ ላይነሱ ይችላሉና፡፡ የማይነሱበት ምክንያት መዋቅሩ መያዝ ያለበትን አይቀሬ ሀሳብ አሙዋልቶ መግለፁ ነው፡፡ እንግዲህ ከዚህ አኩዋያ ሲታይ፣ አረፍተ ነገር አይቀሬ ሀሳብን አሙዋልቶ የያዘ ሰፊ ሀረግ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህ ከተግባሩ አንፃር ሲታይ ነው፡፡

ከመዋቅራዊ ቅርፁ አንፃር ሲታይ ደግሞ ለየት ያለ ብያኔ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ከላይ የተሰጠውን አረፍተ ነገር ቅርፅ ብንመለከት፣

በመጀመሪያ ደረጃ የሁለት አቢይ ሀረጎች ቅንጅት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሀረጎቹም አንድ ትልቅ ልጅ እና በሁለት ብር አራት እንቁላል ገዛ የሚሉት ናቸው፡፡ ባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው፣ እነዚህ ሀርጎች ስማዊና ግሳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ የስማዊ ሀርጉ መሪ ልጅ የሚለው ስም ሲሆን፣ የግሳዊ ሀረጉ መሪ ገዛ የሚለው ግስ ነው፡፡ እነዚህ መሪዎች ከመሙሊያ፣ ከገላጭ እጎላማሽ እንደዚሁም ከመስተዓምር ጋር ደረጃ በደረጃ ተዋቅረው አቢይ ሀረግ ሆነዋል፡፡ አረፍተ ነገሩን ሲመሰርቱ የሚቀናጁበት ስርዓት እንደሚከተለው ነው[2]፡፡

[ስሀ + ግሀ] 7

ይህም ማለት ስማዊ ሀረጉ ቀድሞ፣ ግሳዊ ሀረጉ እሱን ተከትሎ ይገባል ማለት ነው፡፡ ሁለቱ ሀረጎች በዚህ ሁኔታ ተከታትለው ሲመጡ የሚፈጠረው መዋቅር አረፍተ ነገር ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ ከሁለቱ ሀረጎች ጋር ያለውን መዋቅራዊ ተዛምዶ እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡




8

መዋቅሩ፣ አረፍተ ነገር በውስጡ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎችን እቅፎ እንደሚይዝ ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ውስጣዊ ይዘቱ በዚህ ብቻ አይወሰንም፡፡ በስማዊ ሀረጉም ሆነ በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ ሌሎች ሀረጎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ትልቅ ልጅ በሚለው ስማዊ ሀረግ ውስጥ ትልቅ ልጅ የሚል ሌላ ሀረግ አለ፡፡ ይህ ሀረግ ትልቅ የሚለው ቅፅልና ልጅ የሚለው ስም ቅንጅት የፈጠረው ንዑስ መዋቅር ነው፡፡ ሀሳባዊ ይዘቱም የልጁ ትልቅነት ነው፡፡ መዋቅሩ ከአንድ ስምና ከአንድ ቅፅል ብቻ የተዋቀረ በመሆኑ ስፋቱ አንድ ትልቅ ልጅ ከሚለው አቢይ ስማዊ ሀረግ ያነሰ ነው፡፡ አቢዩ ስማዊ ሀረግ የዚህ ንዑስ መዋቅርና አንድ የሚለው መጣኝ መስተዓምር ቅንጅት ነው፡፡ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ፣ የአጠቃላዩን ስማዊ ሀረግ ወርዳዊና ተዋረዳዊ አወቃቀር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

[2] የሀረጎቹን ታህታይ አሰላለፍ በተመለከተ ባህ (1970)ን እንዲሁም ሀድሰን (1972)ን ይመልከቱ፡፡

9




ከዚህ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገሩን የሚመሰርተው ግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ መዋቅር ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

10




[3] ባለፈው ክፍል ስለ መስተዓምራዊ ሀረግ ስንወያይ፣ በዚህ ቦታ የሚገኘው አገናዛቢ መስተዓምር እንደሆነና ጠቋሚና መጣኝ መስተዓምራዊ ሀረጎች ስማዊ ሀረጉን መሙሊያ እያደረጉ የራሳቸውን ሀረግ እንደሚመሰርቱ ገልፀን ነበር፡፡ ከዚህ ላይ ግን ለቀላል አቀራረብ ሲባል እንደተለመደው፤ ሁሉንም መስተዓምራዊ ሀረጎች በስማዊ ሀረጉ ውስጥ እናሳያለን፡፡

በግልፅ እንደሚታየው፣ ግሳዊ ሀረጉ በውስጡ አንድ መስተዋድዳዊ ሀረግና አንድ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ አቅፎአል፡፡ ንዑሱ ግሳዊ ሀረግም እንደዚሁ አንድ ስማዊ ሀረግና ግስ ይዞአል፡፡ ግሱ የንዑሱ ሀረግ መሪ ሲሆን፣ ስማዊ ሀረጉ የዚሁ መሪ ግስ መሙሊያ ነው፡፡ መስተዋድዳዊ ሀረጉ የንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ገላጭ አጎላማሽ ነው፡፡ የሚያጎላምሰውም በግሱ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀሚያ (ማድረጊያ) በመግለፅ ነው፡፡

ይህ ግሳዊ ሀረግ ከላይ በተራ ቁጥር (9) ከተመለከተው ስማዊ ሀረግ ጋር በተራ ቁጥር (8) በተገለፀው የአወቃቀር ስርዓት ወይም ቅደም-ተከተል መሰረት ሲቀናጅ የሚፈጠረው አረፍተ ነገር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

11




ይህ እንግዲህ ሙሉ ሀሳብን የሚገልፅ ሙሉ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ነው፡፡ በውስጡ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎችን አቅፎአል፡፡ እነዚህ ሁለት ሀረጎች ደግሞ በውስጣቸው ሌሎች ሀረጎችን አቅፈዋል፡፡ ሀረጎቹ የመሪ፣ የመሙሊያ፣

የአጎላማሽና የመስተዓምር ቅንጅቶች ናቸው። አቀነጃጀቱም ወርዳዊና ተዋረዳዊ ነው። ወደፊት የምናያቸው የተለያዩ አረፍተ ነገራዊ መዋቅሮች ሁሉ በዚሀ መሰረት ከሀረጋት የሚዋቀሩ ናቸው። አንዱ ከሌላው የሚለየው በሚፈፅመው ተግባርና በውስጡ በሚያቅፈው የሀረግ መጠንና አይነት ነው።

ከዚሀ ላይ ታዲያ አንድ ቁልፍ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ይኸውም አረፍተ ነገር ከአቢይ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎች የሚፈጠር ስፌ መዋቅር ነው ካልን፣ የዚህ ስፌ መዋቅር መሪ ከሁለቱ ተዋቃሪ ሀረጎች አንደኛው መሆን አለበት። ባለፈው ክፍል ስለሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ የአንድ ሀረግ አይነት በመሪው ቃል እንደሚወሰን አይተናል። የስማዊ ሀረግ መሪ ስም ነው፤ የግሳዊ ሀረግም ግስ ነው። አረፍተ ነገር ከፍ ሲል እንደተገለፀው ስፌ ሀረጋዊ መዋቅር ከሆነ፣ የዚህ ሀረጋዊ መዋቅር መሪ ግስ ነው? ወይስ ስም? ጥያቄው መሰረታዊ ነው። መልሱ ወደ ከፍተኛ ትውረት ይወስደናል። ባጭሩ ግን የማንኛውም አረፍተ ነገር መሪ ግስ ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። ከዚህ ሀረግ ጋር የሚዋቀረውና ባለቤት የምንለው ስማዊ ሀረግም የግሳዊ ሀረጉ አድራጊ መስተዓምር ነው። በዚህ አመለካከት መሰረት፣ ከላይ በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው መዋቅር <u>እኔ</u> ሳይሆን፣ <u>ግሀ</u> መሆን አለበት። ይሀ አመለካከት ባለፈው ክፍል ስለሀረግ ስንወያይ ከጠቀስነው አጠቃላይ የሀረግ አወቃቀር መርሀ ጋር ይጣጣማል። መርሁ ማንኛውም ሀረግ ስር ከመሰረተበት ዘር-ቃል የተለየ ሊሆን አይችልም የሚል ነበር። ለሩ ስም ከሆነ፣ ሀረጉ ስማዊ መሆን አለበት። በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ግን ይህን ይፃረራል። ምክንያቱም <u>እኔ</u> የሚለው ከስማዊ ሀረጉም ሆነ ከግሳዊ ሀረጉ ላይ የተመሰረተና ያደገ አይደለም። በሁለቱ ሀረጎች እናት ላይ ጉብ ያለ ባዕድ ነገር ነው። መርሁን የሚከተለው አንድም የስማዊው አለያም የግሳዊው ሀረግ <u>እዳጊ</u> ሲሆን ነው። ከሁለቱ የየትኛው እንደሆነ ለመረዳት ትርጉሙን ማየት ያስፈልጋል። አጠቃላይ መዋቅሩ ስለ እንቁላል መግዛት ስለሆነና ይሀን የሚገልፀው መሪ ቃልም ግሱ ስለሆነ፣ የሀረጉ ክፍል ግሳዊ መሆን አለበት። ለጊዜው በዚሁ እንተወው። የጥያቄው መልስ ግን በዚሀ ብቻ አያበቃም። ግሳዊ ሀረጉ ራሱ የሌላ መሪ መሙሊያ ነው። ወደ ዝርዝሩ አንገባም፤ ለተነሳንበት አጠቃላይ ዓላማም ብዙ አስፈላጊ አይደለም። ስለዚሀ ወደጀመርነው የአረፍተ ነገር አይነት እንመለስና የተለያዩ አረፍተ ነገሮችን ተግባርና የአወቃቀር ስርዓት በተለመደው አካሄድ እንመልከት።

## ተራ አረፍተ ነገር

ከመዋቅራዊ ይዘት አኳያ አረፍተ ነገር ተራና ውስብስብ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። ተራ አረፍተ ነገር የሚባለው በውስጡ አንድ ግሳዊ ሀረግ ብቻ የያዘ መዋቅር ነው። የሀረጉ መሪ የሆነው ግስ ሳቢ ከሆነ፣ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ይኖረዋል። ስማዊ ሀረጉ የግሱ ተሳቢ ይባላል። ከግሱ ጋር ተዋቅሮ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል። በዚሀ ሁኔታ የተመሰረተው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎችና ከመጣኝ መስተዓምራዊ ሀረጎች ጋር

ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታል፡፡ በዚህ አይነት ደረጃ በደረጃ የተመሰረተው አቢይ ግሳዊ ሀረግ በግሱ የተገለፀውን ተግባር የሚፈፅመውን አካል ከሚገልፅ ስማዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ የአረፍተ ነገሩን መዋቅር ይፈጥራል፡፡ ይህ ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ይባላል፡፡

ከዚህ አኳዋያ ሊታይ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው መዋቅር ተራ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ግሳዊ ሀረግ ስላለው ነው፡፡ የዚህ ግሳዊ ሀረግ መሪ ገዛ የሚለው ሳቢ ግስ ነው፡፡ ሳቢ በመሆኑ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ያስፈልገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት አራት እንቁላል የሚለው ስማዊ ሀረግ በመሙሊያነት፣ ብሎም በተሳቢነት፣ ከዚሁ ግስ ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ በሁለት ብር የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የዚህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ገላጭ አጎላማሽ ነው፡፡ ተግባሩ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ የተገለፀውን ድርጊት መፈፀሚያ (ማድረጊያ) በመግለፅ፣ ስለ ንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ተጨማሪ መረጃ መስጠት ነው፡፡ መረጃው መሰረታዊ ሳይሆን፣ ተጨማሪ በመሆኑ ይህን መረጃ የሚገልፀው አጎላማሽ ሀረግ ሊገደፍ ይችላል፡፡ መሙሊያው ስማዊ ሀረግ ግን ሊገደፍ አይችልም፡፡ ምክንያቱም ያለሱ ንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ስለ መሪው ግስ ሙሉ ሀሳብ ስለማይሰጥ ነው፡፡ ሙሉ ሀሳብ ካልሰጠ ደግሞ ቀደም ሊል እንዳየነው አይቀሬ ጥያቄ ያስነሳል፡፡ በይዘቱም ሆነ በመዋቅራዊ ቅርፁ የተሙዋላ አይሆንምና፡፡

ከላይ እንደተገለፀው፣ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር የሚዋቀረው ስማዊ ሀረግ ባለቤት ይባላል፡፡ ባለቤትነቱ ለአረፍተ ነገሩ ነው፡፡ አገባቡ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ሲሆን፣ መዋቅራዊ አወራረዱም በተራ ቁጥር (11) ላይ እንዳየነው በቀጥታ ከአረፍተ ነገሩ እንጉዋ ላይ በመውረድ ነው፡፡ በዚህም ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ እንጉዋ ላይ ከሚወርዱት ገላጭ ሀረጎች፣ እንዲሁም ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ስር ከሚወርደው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ይለያል፡፡ ሁለተኛም ባለቤት ስማዊ ሀረግ እንደ መሙሊያ ሰማዊ ሀረግ አይቀሬ ነው፡፡ ሁለቱ ስማዊ ሀረጎች ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ከሚወርዱት ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች በአይቀሬነታቸው ይለያሉ፡፡ በዚህ አይነት በታሀታይ መዋቅር ውስጥ ከሚወርዱበት እንጉዋ እንፃር ሀረጎችን ባለቤት፣ አጎላማሽ እና መሙሊያ፣ እንዲሁም እንደሚሰጡት መረጃ አይነት፣ ቀሪና አይቀሬ እያሉ በቦታቸውና በተግባራቸው መሰረት መለየት ይቻላል፡፡ ይህ መዋቅራዊ (አገባባዊ) መሌያቸው ነው፡፡

ሌላው መለያቸው ምዕላዳዊ ነው፡፡ ባለቤትም ሆነ ተሳቢ እንዲሁም አጎላማሽ ሀረግ በቅጣይ ምዕላዶች ይጠቆማል፡፡ ምዕላዶቹ የሚገኙት በአረፍተ ነገሩ ግስ አምድ መነሻ ወይም መድረሻ ላይ ነው፡፡ በመነሻ የሚገኙት አምዱ ካልዓይ እንቀፅ ሲሆን ነው፡፡ በመድረሻ የሚገኙት፣ የቀዳማይ ወይም የጨራሽ እንቀፅ አምድ ሲሆን ነው፡፡ ምዕላዶቹ አፀፋ ተውላጠ ስም በመባል ይታወቃሉ፡፡ የሀረጎቹ አጣፌ ወይም ነፀብራቅ ናቸው፡፡ ዝርዝራቸውን በርባታው ክፍል አሳይተናል፡፡ ቢሆንም ለማስታወስ ያህል፣ ብዙ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ የቀዳማይ እንቅፅ አፀፋዎችን ብቻ እንደገና እናሳያለን፡፡

| ባለቤት | | | ተሳቢ | | አጎላማሽ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| መደብ | ነጠላ | ብዙ | ነጠላ | ብዙ | ነጠላ | ብዙ |
| 1 | -ሁ | -ን | -ኝ | -ን | -ብ-ኝ | -ብ-ን |
| 2 | -ህ | -አችሁ | -ህ | -አችሁ | -ብ-ህ | -ብ-አችሁ |
| አን | -ሽ | -አችሁ | -ሽ | -አችሁ | -ብ-ሽ | -ብ-አችሁ |
| 3 | -ኧ | -ኡ | -ው | -አቸው | -ብ-ኧት | -ብ-አቸው |
| አን | -ኧች | -ኡ | -አት | -አቸው | -ብ-አቸው | -ብ-አቸው |

1 የቀዳማይ አንቀፅ የባለቤትና የተሳቢ አፀፋ

እነዚህ የባለቤት፣ የተሳቢና የመስተዋድዳዊ ሀረግ አፀፋ ናቸው። ማንኛውም ባለቤት ስማዊ ሀረግ በባለቤት አፀፋ ይጠቀሳል። ማንኛውም ዕምር የሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግም በተሳቢ አፀፋ ይጠቀሳል። ማንኛውም ገላጭ (አጎላማሽ) መስተዋድዳዊ ሀረግ በመስተዋድድ አፀፋ ይጠቀሳል። አፀፋዎቹ በተለያየ ርከን ላይ የሚገኙ ሀረጎቹን ስለሚጠቅሱ፣ በተግባራቸው መዋቅራዊ ናቸው። በቅርፃቸው ግን ምዕላዳዊ ናቸው። ስለሆኑም ከላይ እንደሚታየው፣ የሚገኙት ከየግሱ እምድ ላይ ነው። አንድ አምድ ሊይዝ የሚችለው ሁለት አፀፋዎችን ብቻ ነው። የባለቤት አፀፋ ምን ጊዜም አይቀሬ ነው። ከእሱ ቀጥሎ የተሳቢ ወይም የመስተዋድድ አፀፋ ሊመጣ ይችላል። የመስተዋድዳዊ አፀፋ /ብ-/ የሚለው መስተዋድድና የተሳቢ አፀፋ ቅንጅት ነው። ለምሳሌ /ብ-ኝ/ የሚለውን ብንመለከት፣ የመስተዋድዱ /ብ-/ እና /-ኝ/ የሚለው የአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተሳቢ አፀፋ ቅንጅት እንደሆነ እንረዳለን። ከዚህ አንፃር በሚከተሉት ምሳሌዎች ውስጥ ያለውን የአፀፋ ሁኔታ እንመልከት።

(ሀ) አስቴር ልጁን ሰደበችው (ሰደብ-ኧች-ኡ) 2
(ለ) አስቴር በርሳሱ ለዕሉን ሳለችበት (ሳል-ኧች-ብ-ኧት)
(መ) *አስቴር በርሳሱ ለዕሉን ሳለችውበት (ሳል-ኧች-ኡ-ብ-ኧት)

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ አስቴር የሚለው የአንስታይ ፆታ ስም ባለቤት ስለሆነ፣ /-ኧች/ በሚለው የባለቤት አፀፋ ተጠቅሶአል። ልጁን የሚለው ዕምር ስማዊ ሀረግ ተሳቢ ስለሆነ /-ኡ/ በሚለው የተሳቢ አፀፋ ተጠቅሶአል። የሁለቱ አፀፋዎች ቅደም-ተከተል የባለቤቱ አፀፋ ቀድሞ፣ የተሳቢው ደግሞ እሱን ተከትሎ እንደሚገባ ያሳያል። ይህም ቅደም-ተከተል በመዋቅር ውስጥ ባለቤትና ተሳቢ ሀረጎች የሚከተሉትን ስርዓት ያንፀበርቃል። በመዋቅር ውስጥ ባለቤቱ ሀረግ ተሳቢውን እየቀደመ እንደሚገባ ሁሉ፣ በግሱ አምድ ላይም የባለቤቱ አፀፋ የተሳቢውን አፀፋ እየቀደመ ይገኛል።

በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ አስቴር ከሚለው ባለቤት በተጨማሪ በርሳሱ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ እና ለዕሉን የሚለው ዕምር ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይገኛሉ። በአፀፋ የተጠቀሱት የባለቤቱና የመስተዋድዳዊው ሀረግ ብቻ ናቸው። ደብዳቤውን የሚለው ዕምር ተሳቢ ሀረግ ሊጠቀስ አልቻለም። ምክንያቱም የግሱ አምድ ሊያስከትል የሚችለው ሁለት አፀፋዎችን ብቻ ነው። ሶስቱም ሀረጎች

በአፀፋ ከተጠቀሱ፣ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምሳሌ (መ) የሚያመለክተው ይህንኑ ሁኔታ ነው፡፡

እንግዲህ ማንኛውም ስማዊ ሀረግ በባለቤትነት ወይም በተሳቢነት፣ እንዲሁም ማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ በገላጭነት (አጎላማሽነት) መግባቱን ለማወቅ፣ መጀመሪያ ከፍ ሲል በተራ ቁጥር (11) እንደተመለከተው፣ መዋቅራዊ አቀማመጡን፣ ከዚያም ምዕላዳዊ አፀፋውን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ሁለቱን መለያዎች መዋቅራዊና ምዕላዳዊ ልንላቸው እንችላለን፡፡ ከሁለቱ መለያዎች፣ ይበልጥ የሚያስተማምነው ምዕላዳዊው መስፈርት ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ባለቤት ስማዊ ሀረግ በግሀድ ላይታይ ይችላል፡፡ ሁለተኛም በግሀድ በሚታይበት ጊዜም ቢሆን፣ የሚታይበት ቦታ ሁል ጊዜ የአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይሆን ይችላል፡፡ ባጭሩ በአረፍተ ነገር መነሻ ላይ የሚታይ ስማዊ ሀረግ ሁሉ፣ ባለቤት ላይሆን ይችላል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) እስቴር ፈተናዋን ጨረሰች (ጨረስ-ኧች) መሰለኝ (መሰል-ኧ-ኝ) 3
(ለ) እስቴር ልጆች አሉአት (አል-ኡ-አት)

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ፣ ሁለት ግሶች አሉ፤ ጨረሰችና መሰለኝ፡፡ ሁለት ግሶች አሉ ማለት ደግሞ፣ ሁለት ግሳዊ ሀረጎች ብሎም ሁለት አረፍተ ነገሮች አሉ፣ ማለት ነው፡፡ ጨረሰች የሚለው ግስ /-ኧች/ የሚል የባለቤት አፀፋ አለው፡፡ ይህም አፀፋ የሚጠቅሰው እስቴር የሚለውን ስም ነው፡፡ ስለዚህ እስቴር የሚለው ስም የዚህ ፈተናዋን ጨረሰች የሚለው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው፡፡ መሰለኝ የሚለው ግስ ደግሞ /-ኝ/ የሚል የባለቤት አፀፋ አለው፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ አፀፋ የሚጠተበና ስስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነ ባለቤት ስማዊ ሀረግ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በግሀድ አይታይም፡፡ በግሀድ የሚታየው ባለቤት እስቴር የሚለው ስም ነው፡፡ እሱ ደግሞ የዚህ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም መሰል-ኧ-ኝ በሚለው ግስ ውስጥ /-ኧ-/ የሚለው አፀፋ የሚያመለክተው ተባዕታይ ፆታ የሆነን ስም ነው፡፡ ስለዚህ የእንስታይ ፆታ ስም የሆነው፣ እስቴር የሚለው ስም፣ የዚህ ግስ ባለቤት ሊሆን አይችልም፡፡

በምሳሌ (ለ) ውስጥ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ የሚታየው ስም እስቴር ነው፡፡ ከግሱ አምድ ተጥሎ የሚታየው አፀፋ /-ኡ/ ነው፡፡ ሶስተኛ መደብና የብዙ ቁጥር የሆነን ባለቤት ስማዊ ሀረግ ያመለክታል፡፡ በዚህ አፀፋ ሊጠቀስ የሚችለው ስም ልጆቹ የሚለው ነው፡፡ ስለዚህም ይህ ስም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው፡፡ አገባቡ ግን በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ አይመስልም፡፡ በአንፃሩ እስቴር የሚለው ስም በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ይግባ እንጅ፣ ባለቤት አይደለም፤ ተሳቢ ነው፡፡ በተሳቢነቱም /-አት/ በሚለው የተሳቢ አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ከፍ ሲል በተራ ቁጥር (11) በተመለከተው ዕፀ-መዋቅር፣ ተሳቢ (መሙሊያ) ስማዊ ሀረግ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ እንጉዋ፣ ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግም ከአረፍተ ነገሩ እንጉዋ እንደሚወርድ ገልፀናል፡፡ እስቴር የሚለው ስም ተሳቢ ሆኖ ሳለ፣ ከግሱ አካባቢ ርቆ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ መታየቱ፣ ከዚህ ህግ ውጭ ያደርገዋል፡፡ ይህ ግን ምሳሌዎቹን ከላይ በቀረቡበት መልካቸው ስናያቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ላዕላይ አቀማመጣቸው ነው፡፡ በተራ ቁጥር (11) የተመለከተው አወራረድና ድንጋጌ በሀረጎቹ ታህታይ

አቀማመጥ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በታህታይ አወቃቀር፣ ከአረፍተ ነገር አንጉዋ ላይ የሚወርድ ስማዊ ሀረግ ባለቤት፣ ከንዑስ ግሳዊ ሀረግ አንጉዋ ላይ የሚወርድ ስማዊ ሀረግ ተሳቢ፣ እንዲሁም ከአቢይ ግሳዊ ሀረግ አንጉዋ ላይ የሚወርድ ማንኛውም ሀረግ ገላጭ ነው፡፡

ይህ የአወራረድ ስርዓት ምን ጊዜም አይቀየርም፡፡ በስርዓቱ መሰረት በየቦታቸው መውረድ ያለባቸው ሀረጎችም ይወርዳሉ፡፡ ከወረዱ በሁዋላ ግን ቦታ ሊቀይሩ ይችላሉ፡፡ ቦታ ቀይረው የሚታዩበት መዋቅር ላዕላይ ይባላል፡፡ ከታህታዩ የወጣና በእሱም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ምሳሌ 3(ለ) ከሚከተለው ታህታይ መዋቅር ላይ የተመሰረተ ላዕላይ መዋቅር ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡

4




ይህ በተራ ቁጥር 3(ለ) የሚታየው ምሳሌ ታህታይ መዋቅር ነው፡፡ በግልፅ እንደሚታየው <u>እስቴር</u> የሚለው ስም /ለ-/ የሚለው መስተዋድድ መሙሲያና ተሳቢ ነው፡፡ አወራረዱም ከግሳዊ ሀረጉ አንጉዋ ላይ ነው፡፡ <u>ልጆች</u> የሚለው ስም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው፡፡ አወራረዱም ከአረፍተ ነገሩ አንጉዋ ላይ ነው፡፡ እስቴር የሚለው የመስተዋድዱ ተሳቢ ስም ቦታውን ለቆ፣ የአረፍተ ነገሩን ባለቤት ቀድሞ ሲገባና መስተዋድዱ /ለ-/ ከቦታው ሲጠፋ፣ አረፍተ ነገሩ

በ3(ለ) የሚታየውን ላዕላይ ቅርፅ ይይዛል[4]፡፡ ከዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን የማንኛውንም ሀረግ መሰረታዊ አገባብ ለመወሰን ላዕላይ አቀማመጡን ሳይሆን፣ ታህታይ አወራረዱን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ካሁን በፊት እንደገለፅነው፣ ታህታይ መዋቅር ረቂቅና አዕምሮአዊ ነው፡፡ ላዕላይ መዋቅር ግህድና አንደበታዊ ነው፡፡ የመጀመሪያው በአዕምሮ የሚታሰብ ሲሆን፣ ሁለተኛው በአንደበት የሚነገር ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ሁል ጊዜ ልዩነት አለ፡፡ ይህ የማንኛውም መዋቅር ባህሪ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ በስነ-ድምፅ፣ ከዚያም በሁዋላ በስነ-ምዕላዱ፣ አሁን ደግሞ በስነ- መዋቅሩ እየታየ ነው፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይህም አስቴር የሚለው ተሳቢ ስም ታህታይ ቦታውን ለቆ የሚሄደው ለምድን ነው? የሚል ነው፡፡ አስቴር የሚለውና ልጆቹ የሚለው ስም ግንኙነት የገንዛቢና የተገንዛቢ ነው፡፡ አስቴር ገንዛቢ (ባለገንዘብ) ስትሆን፣ ልጆቹ የሚለው ተገንዛቢ ነው፡፡ የዚህ አይነት ግኙነት ያላቸው ስሞች የላዕላይ አገባብ ስርዓት ገንዛቢውን ቀዳሚ፣ ተገንዛቢውን ተከታይ የሚያደርግ ነው፡፡ ባለገንዘብ ቀዳሚ፣ ገንዘብ ተቀዳሚ (ተከታይ) መሆኑ ከሰው ልጅ ልዕልና ጋር የተያያዘ መዋቅራዊ ባህሪ ነው፡፡ ገንዘብ ለሰው ተፈጠረ እንጂ፣ ሰው ለገንዘብ አልተፈጠረም፡፡ ርግጥ፣ ለገንዘብ ብቻ የተፈጠሩ የሚመሳሰሉ ይኖራሉ፡፡

ወደ ጉዳያችን እንመለስ፡፡ ገንዛቢ ቀድሞ፣ ተገንዛቢ ተከትሎ የመግባቱ ነገር በማንኛውም ቋዋንቋዋ የሚታይ መዋቅራዊ ባህሪ ነው፡፡ በዚህ መሰረት፣ በታህታይ መዋቅር ውስጥ ቀዳሚ ሆኖ የገባው ባለቤት ስም፣ በላዕላይ መዋቅር፣ አስቴር በሚለው ገንዛቢ ስም ሊቀደም ችሎአል፡፡ ሌሎችም ይህን ስርዓት የሚከተሉ መዋቅሮች አሉ፡፡

(ሀ) አስቴርን ውሻ ነከሳት 5
(ለ) ካሳን አሾህ ወጋው

የእነዚህ አረፍተ ነገሮች ታህታይ መዋቅር አስቴርንና ካሳን ተሳቢ የሚያደርግ ነው፡፡ ግሶቹ ሳቢ ናቸውና፡፡ ውሻና አሾህ ደግሞ ነካሽና ወጊ ባለቤት ናቸው፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅር ውስጥ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ይገባሉ፡፡ ይህ ሲሆን፣ መዋቅሮቹ የሚከተውን ይመስላሉ፡፡

(ሀ) ውሻ አስቴርን ነከሳት 6
(ለ) አሾህ ካሳን ወጋው

በዚህ አይነት በተመሰረተው ታህታይ መዋቅር ውስጥ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (5) እንደሚታየው፣ ተሳቢዎቹ ስሞች ታህታይ ቦታቸውን በመልቀቅ፣ ባለቤቶቹን ስሞች እየቀደሙ ላዕላይ ቦታቸውን ይይዛሉ፡፡ ተሳቢዎቹ ባለቤቶቹን የሚቀድሙበት

---

[4] ይህን ጉዳይ በተመለከተ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ለማግኘት ባየ (1994፣ 1997)ን ይመልከቱ፡፡

መስረት በሆነው በተግባራቸው ላይ ያተኮረ ይሆናል። ማንኛውም አረፍተ ነገር የሚነገርበት ምክንያት ወይም ዓላማ አለው። የዓላማው አይነት የቅርፁን አይነት ሊወስን ይችላል። ከዚህም በመነሳት አንዱን አረፍተ ነገር ከሌላው መለየት ይቻላል። ከዚህ ቀጥለን የምንመለከተው ይህንኑ ነው።

## ሀተታዊ አረፍተ ነገር

ሀተታዊ አረፍተ ነገር አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ፣ ግህዳዊ ወይም ምናባዊ ለሆኑ ነገሮች፣ ሁነቶችና ስሜቶች ያለንን ግንዛቤ ከስሜታችን ጋር አዋህደን የምናትትበት የመዋቅር አይነት ነው። ዓላማው ማተት ነው። ሀተታውም ስለ አንድ የተወሰነ ወይም አጠቃላይ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ፣ አንድ የራበው መንገደኛ ስለ ምግብ አያስበ ሲጉዋዝ፣ ሰዎች ስንጋ ጥለው ብልት ሲያወራርዱና ጮማ ሲቆርጡ ቢያጋጥመው፣ ከሚለማው ርሀብና ካጋጠመው ትዕይንት ተነስቶ፣ ለራሱም ቢሆን፣ በአንደበቱ ወይም በልቡ የሚከተለውን ማለቱ አይቀርም።

አቦ! እንዴት ያለ ጮማ ነው! 1

ይህን በማለት ሰውየው ስለ ስጋው ጮማ መሆን ተናግሮአል ወይም አትቶአል። አነጋገሩም ስሜትን የተላበሰ ነው። <u>አቦ!</u> እና <u>እንዴት ያለ</u> የሚሉት አባባሎች የሚያመለክቱት በለውየው አመለካከት፣ ስጋው ተራ ሳይሆን፣ ከከ የመሰለ ጮማ መሆኑን ነው። አቦ! የሚለው ቃለ-አጋኖ ነው። የሰውየውን ስሜት ይገልፃል። ከዚያ ያለፈ ትርጉም የለውም። ይህን ስሜታዊ የሆነውን ክፍል ትተን፣ ተጨባጩን ነገር ብቻ ለመግለፅ ብንፈልግ፣ ከላይ የተመለከተውን አባባል እንደሚከተለው ማለት ይቻላል።

ስጋው ጮማ ነው 2

ከመዋቅር አኳዋያ ይህ ተራ አረፍተ ነገር ነው። ግሱም <u>ነው</u> የሚለው ተራ የመሆን ግስ ነው። <u>ጮማ</u> የሚለው ቅፅል የዚህ ግስ መሙሊያ ነው። <u>ስጋው</u> የሚለው ስም ደግሞ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። ግሱና መሙሊያው ተቀናጅተው ግሳዊ ሀረግ በመሆን፣ ስለ ስሙ ያትታሉ። ስሙን እንደ ርዕስ፣ ግሳዊ ሀረጉን እንደ ሀተታ-ርዕስ፣ አረፍተ ነገሩን እንደ ድርሰት አድርገን ልንመለከተው እንችላለን። መሙሊያው ከግሱ ጋር ተዋቅሮ የሚያትተው ስለ ርዕሱ፣ ማለትም ስለ <u>ስጋው</u> ነው። ግሱ ከመሙሊያው ቀፅል ጋር የሚፈጥረውን ግሳዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሀረጉም በተራው ከባለቤቱ ስማዊ ሀረግ፣ ማለትም ከርዕሱ ጋር ተዋቅሮ፣ የሚፈጥረውን ቅንጅት በጀመርነው አይነት በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን።

---

[5] ይህን ጉዳይ በሚመለከት ባየ (1994)ን ይመልከቱ።




3

ይህ እንግዲህ የአንድ ተራ ሀተታዊ አረፍተ ነገር መዋቅር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተለያዩ ሀተታዊ አረፍተ ነገሮችን እንመለከታለን፡፡

## ሁነታዊ አረፍተ ነገር

ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው፣ ሁነታዊ አረፍተ ነገር የአንድን ነገር፣ አንድ ነገር መሆን ያትታል፡፡ ከፍ ሲል በተሰጠው ምሳሌ፣ ግሱና ቅፅላዊ መሙሊያው የሚፈጥሩት ሀረግ የሚያትተው ስለ ስጋው ጮማ መሆን ነው፡፡ መሆንን ስለሚገልፅ ግሱ የመሆን ግስ በመባል ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጅ፣ የዚህ አይነት ሀታታዊ አረፍተ ነገር ግስ፣ መሆንን ብቻ ሳይሆን፣ ከአንድ ነገር ወደ ሌላ ነገር መለወጥንም ሊያሳይ ወይም ሊያትት ይችላል፡፡ ለዚህ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡

አስቴር አስተማሪ ሆነች 4

ይህ አረፍተ ነገር ስለ አስቴር ያትታል፡፡ የሚያትተውም አስተማሪ ካለመሆን፣ አስተማሪ ወደ መሆን ያደረገችውን ለውጥ ነው፡፡ ለውጡን የሚያመለክተው ሆነች የሚለው ግስ ነው፡፡ ከፍ ሲል ከጠቀስነው፣ ነው ከሚለው ግስ፣ የተለየ ነው፡፡ ነው የሚለው ግስ የሚገልፀው *ነኝነትን* ነው፡፡ ሆነች የሚለው ግን ልውጠትን ነው የሚያሳየው፤ ስለዚህም *የልውጠት* ግስ ነው፡፡ አረፍተ ነገሩም የዚሁ ልውጠት ሀተታ ነው፡፡ የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት፡፡

ልጆቹ ክፍል ውስጥ አሉ 5

ይህ አረፍተ ነገር የሚያትተው ልጆቹ ስለሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ሀተታውም ቤት ውስጥ ስለ መኖራቸው ነው፡፡ ስለ ሁነት ወይም ለውጠት አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ግሱን የኑረት ግስ ልንለው እንችላለን፡፡ ልጆቹ የሚለው ስም ነዋሪ ባለቤት ነው፡ ሁዋኝ ወይም ለውጥ ባለቤት አይደለም፡፡

እስካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች ሁነትን፣ ለውጠትንና ኑረትን የሚያትቱ ናቸው፡፡ የሁሉም ሀተታ ስለ አረፍተ ነገሮቹ ባለቤት ነው፡፡ ከነዚህ ጋር የሚመሳሰሉ እናም በዚሁ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ሌሎች አረፍተ ነገሮችም አሉ፡፡ የሚከተለው የነዚህ ምሳሌ ነው፡፡

ካሳ አባቱን ይመስላል 6

ይህ አረፍተ ነገር የሚያትተው ምስለትን ነው፡፡ ግሱ መስተዋድዳዊ ሀረግ መሙሊያ አለው፡፡ የሀረጉ መሪ የሆነው መስተዋድድ /-ን/ ነው፡፡ ይህ /-ን/ ተሳቢ ስማዊ ሀረግን የሚያመለክተው /-ን/ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይመስላል የሚለው ግስ ሳቢ አይደለም፡፡ ስላልሆነም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አይፈልግም፡፡ መሙሊያ ግን ይፈልጋል፡፡ መሙሊያውም ሊሆን የሚችለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው፡፡ ግሳዊ ሀረጉ የሚያትተው ካሳ በሚለው ባለቤት ስምና አባቱ በሚለው መሙሊያ ስም መካከል ያለውን ምስለት ነው፡፡ ከትርጉም አኳያ መምሰልና መሆን ለየቅል ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይቀራረባሉ፡፡ እንዲያውም ከመዋቅር አንፃር ሲታዩ አንድ ናቸው፡፡ ሁሉም መሙሊያ ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን እያነፃፀርን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ አስተማሪ ይሆናል 7
(ለ) ካሳ አስተማሪ ነው
(ሐ) ካሳ አስተማሪ ይመስላል
(ረ) ካሳ ረዥም ነው
(ሰ) ካሳ ረዥም ሆነ
(ቀ) ካሳ ረዥም ይመስላል

እነዚህ ምሳሌዎቹ ነው፣ ይመስላል እና ይሆናል የሚሉት ግሶች ቅፅሳዊ ወይም መስተዋድዳዊ ወይም ስማዊ ሀረግን መሙሊያ እያደረጉ ግሳዊ ሀረግ እንደሚመሰርቱ ያሳያሉ፡፡ ይህን ያገባብና መጠነኛም ቢሆን፣ የትርጉም ተመሳሳይነት መሰረት በማድረግ ግሶቹን በሁነት ግስ ስር ልናጠቃልላቸው እንችላለን፡፡ የአረፍተ ነገሮቹ መሰረታዊ አወቃቀርም አንድ አይነት ነው፡፡ ግሶቹ ከመሙሊያ ሀረግ ጋር ይዋቀራሉ፡፡ መሙሊያዎቹም ተሳቢ አይደሉም፣ ምክንያቱም ግሶቹ ሳቢ አይደሉምና፡፡

እስካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች በሙሉ የባለቤትና የመሙሊያ ቁርኝት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ መሙሊያዎቹ ስለ ባለቤቶቹ ምንነት፣ የትነት (ኑረት) ሁነት የሚያወሱ ናቸው፡፡ ግሶቹም የሚያሳዩት ይህንን የሁለቱን ቁርኝት ነው፡፡ ለምሳሌ ከላይ በተሰጡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ፣ (እንደ ቅደም-ተከተላቸው)፣ ካሳ እና ረዥም፣ እንዲሁም ካሳ እና አስተማሪ፣ ተቆራኝተዋል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያው ምሳሌ፣ ረዥም የሆነው ወይም የሚመስለው ካሳ ሲሆን፣ በሁለተኛው ምሳሌ ድግሞ አሰተማሪ የሆነው ወይም የሚመስለው አሁንም ያው ካሳ ነው፡፡ በጥቅሉ አረፍተ ነገሮቹ የባለቤትን አንድ ነገር መሆን ወይም በአንድ ቦታ መገኘት ያመለክታሉ፡፡ የግሶቹም ተግባር ይህንኑ የሁለቱን ቁርኝት ማመልከት ስለሆነ፣ በጥቅሉ *አቆራኝ* ግሶች ልንላቸው እንችላለን፡፡ ባለቤትና መሙሊያን ያቆራኛሉ፤ ያያይዛሉ ማለት ነው፡፡ አረፍተ ነገሩም የሚያትተው ይህንኑ ነው፡፡ መዋቅራዊ ሁኔታቸውን እንደሚከተለው አድርገን በአንድ ዕፀ-መዋቅር አጠቃለን እናሳያለን፡፡

8




በዚህ መዋቅር ከተጠቃለሉት ሁነታዊ አረፍተ ነገሮች ጋር በመጠኑ የሚመሳሰሉ ሌሎች አረፍተ ነገሮችም አሉ፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

9

(ሀ) ልጆቹ ባለጉ
(ለ) ሌቶቹ ሰከሩ
(መ) አለቴር ወፈረች

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ስለ ባለቤታቸው ባህሪ የሚያትቱ ናቸው፡፡ ግሶቹም ባህሪን የሚያመለክቱ ቅፅላዊ አቻ አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡ ባለጌ ለሚለው ባለጌ፣ ሰከረ ለሚለው ሰካራም፣ እንደዚሁም ወፈረች ለሚለው ወፍራም የሚል አቻ ቅፅል አለው፡፡ ስለዚህም ልጆቹ ባለጉ በሚለው ፋንታ፣

ልጆቹ ባለጌ ሆኑ 10

የሚል ሁነታዊ አረፍተ ነገር መመስረት ይቻላል፡፡ የሌሎቹ ምሳሌዎች ባህሪም እንደዚሁ ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉትን ስለ ባለቤት የሚያትቱ አረፍተ ነገሮችን ባህሪያዊ አረፍተ ነገሮች፣ ግሶቹን ደግሞ የባህሪ ግሶች ልንላቸው እንችላለን፡፡ ከነዚህ ጋር በአወቃቀር የሚመሳሰሉ ሌሎች አረፍተ ነገሮች ደግሞ እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

(ሀ) ካሳ ተደሰተ 11
(ለ) አስቴር ተጨነቀች
(መ) ልጆቹ ተበሳጩ

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች የሚያትቱት ባለቤቱ የሚገኝበትን ሁኔታ ነው፡፡ ይኸውም በደስታ፣ በብስጭት፣ በጭንቀት፣ ወዘተ፣ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡ ባለቤቱ የሁኔታው ገፈት ቀማሽ ነው፡፡ ግሶቹም ከሌሎች ግሶች በቅርፃቸው የተለዩ ናቸው፡፡ ልዩነታቸው፣ ሁሉም በ/ተ-/ የሚጀምሩ መሆናቸው ነው፡፡ ባለፈው ክፍል እንዳየነው፣ /ተ-/ የተለያየ ትርጉም አላት፡፡ ከዚህ ላይ ግሉ የሁኔታ፣ ባለቤቱም የሁኔታው ተጠቂ መሆኑን ታመለክታለች፡፡ ባጭሩ የሁኔታ ግስ መስራች ነች፡፡ ወደ ሁዋላ እንመለስበታለን፡፡

የባህሪም ሆኑ የሁኔታ ግሶች መሙሊያ የላቸውም፡፡ ይሁን እንጅ፣ ከትርጉም አንፃር ሲታሰብ፣ መሙሊያቸው ባለቤቱ ሰማዊ ሀረግ ነው፡ ሰማለት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ የዚህን ስማዊ ሀረግ መዋቅራዊ ቦታ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ስር ያደርገዋል፤ መሙሊያ የሚገኘው በንዑስ ሀረግ ስር ነውና፡፡ በዚህ መሰረት፣ የባለቤቱ ቦታም ክፍት ይሆናል፡፡ ይህ በተለይ ከላይ በተራ ቁጥር (11) ስር የሚታዩት አረፍተ ነገሮች አይነተኛ ባህሪ ነው፡፡ የነዚህን ታህታይ አወቃቀር በ12(ሀ)፣ እንዲሁም ላዕላይ አቀማመጣቸውን በመዋቅር (ለ) እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

12




በመዋቅር 12(ሀ) ላይ በግልፅ እንደሚታየው፣ የባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (...) ነው፡፡ ካሳ ተጨናቂ መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ አስጨናቂው ማን ወይም ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ስለዚህም ቦታው ክፍት ነው፡፡ መዋቅር 12(ለ) ላዕላይ ነው፡፡ ካሳ የዚህ መዋቅር ባለቤት ሆኖ የሚታየው፣ በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ ከሚታይበት፣ ከመሙሊያው ቦታ ተነስቶ ክፍት ወደ ነበረው የባለቤት ቦታ ሲሄድና ተጨናቂ ባለቤት ሲሆን ነው፡፡

እስካሁን ያየናቸው ተራ ሀተታዊ አረፍተ ነገሮች ስለ ባለቤት፣ ምንነት፣ የትነት፣ ባህሪና ሁኔታ የሚያትቱ ናቸው፡፡ ግሶቻቸው በሙሉ ኢሳቢ ናቸው፡፡ መሙሊያ እንጅ ተሳቢ የላቸውም፡፡ አንዳንዶቹ በታህታይ መዋቅር ውስጥ ባለቤት የላቸውም፡፡ እንደነዚህ ያሉት መለያ ምልክት /ተ-/ የምትለዋ ምዕላድ ነች፡፡ ይችን የያዙ ግሶች በታህታይ መዋቅር ውስጥ መሙሊያ የነበረውን ስማዊ ሀረጋቸውን በላዕላይ መዋቅር ባለቤት አድርገው ይከሰታሉ፡፡ ይህም ከላይ በመዋቅር 12(ለ) እንደሚታየው ነው፡፡

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስለ ባለቤት ስማዊ ሀረግ ግብር የሚያትቱትን ተራ አረፍተ ነገሮች እንመረምራለን፡፡

## ገቢር አረፍተ ነገር

እነዚህ ድርጊትን የሚያመለክት ግሳዊ ሀረግ ያላቸው አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት የድርጊቱ ፈፃሚ ነው፡፡ ሁዋኝ ሳይሆን፣ አድራጊ ባለቤት ነው፡፡ ድርጊቱን የሚፈፅመውም በራሱ ወይም በሌላ አካል ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ለአብነት እንመልከት፡፡

የሚል እንቅስቃሴም አለ፡፡ ይኸውም በአንድ በተወሰነ ቦታ የሚፈፀም ነው፡፡ መነሻውም ሆነ መድረሻው አድራጊው፣ ማለትም ባለቤቱ የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡

(ሀ) ልጁ በር ላይ ቆመ 3
(ለ) አስቴር አልጋው ላይ ወደቀች
(ሐ) ዶሮዎቹ ቆጡ ላይ ሰፈሩ

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች እንድ አካል እንድ ድርጊት የሚፈፀምበትን ቦታ የሚገልፁ ናቸው፡፡ ድርጊቱ የሚፈፀምበት ቦታ በመስተዋድዳዊ ሀረግ የተገለፀው ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው አረፍተ ነገር፣ ልጆቹ የመቆምን ተግባር የሚፈፅሙት፣ በሩ ላይ ሲሆን፣ በሁለተኛው ደግሞ አስቴር የወደቀችው አልጋው ላይ ነው፡፡ ሁለቱም መስተዋድዳዊ ሀረጎች ሲሆኑ፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ በግሱ የተገለፀውን ተግባር የፈፀመበትን ቦታ ያመለክታሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በቀደምት ሲቃውንት ዘንድ የቦታ ተውሳከ ግስ በመባል እንደሚታወቁ ገልፀናል፡፡ ተውሳከ ግስነታቸው ግን የግብር እንጅ የቃል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የቃል ክፍላቸው፣ በክፍል ሁለት እንዳየነው፣ መስተዋድድ ነውና፡፡

እንድ ድርጊት በውጭ ሀይል ግፊት ወይም በራስ አነሳሽነት ሊፈፀም ይችላል፡፡ የሚፈፀመውም በራስ ላይ ወይም ከራስ ውጭ በሆነ ነገር ላይ ሲሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ከፍ ሲል የተጠቀሱት አረፍተ ነገሮች የሚያመለክቱት ባለቤቱ በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ እንድ ድርጊት ሲፈፅም ነው፡፡ የፈፀመውም ምናልባት በውጭ አካል ወይም ሁኔታ ግፊት ሊሆን ይችላል፡፡ ድርጊቱ በራሱ አነሳሽነትና ተሳታፊነት እንዲሁም በራሱ ላይ የሚፈፀም ሲሆን፣ ግሶቹ ለየት ያለ ቅርፅ ይኖራቸዋል፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ከመቀመጫው ተነሳ 4
(ለ) ልጆቹ ወንበር ላይ ተቀመጡ
(ሐ) አስቴር አልጋ ላይ ተኛች
(መ) አንበሳው ተንጠራራ

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ግሶች ከፍ ሲል ካየናቸው አረፍተ ነገሮች ግሶች የተለዩ ናቸው፡፡ ልዩነታቸውም ሁሉም በ/ተ-/ መጀመራቸው ነው፡፡ /ተ-/ ደግሞ በክፍል ሁለት እንደተገለፀው፣ ምዕላድ ነች፡፡ አንድ ድርጊት በራስ አነሳሽነትና በራስ ላይ የሚፈፀም መሆኑን ታመለክታለች፡፡ እስዋ ከሌለች ግሶቹ፣ ብሎም አረፍተ ነገሮቹ ተቀባይነታቸውን ያጣሉ፡፡ ስለዚህም፣

*ልጆቹ ወንበር ላይ ቀመጡ 5

ማለት አይቻልም፡፡ እንደዚህ የሚሉት ቋንቋዋውን ገና በመልመድ ላይ የሚገኙ ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ እንደ ቀደመ፣ ቀረበ፣ ወዘተ፣ ያሉ ግሶችን አካሄድ በመከተል፣ ቋንቋዋውን በመልመድ ላይ የሚገኙ ህፃናትም ቀመጡ ሲሉ ይችላሉ፡፡

የድርጊቱ መነሻ በመሰረቱ ድርጊቱን የሚፈፅመው ሰው ውስጣዊ ስሜት ወይም የሚገኝበት የአካባቢ ሁኔታ ሊሆን ይችላል፡፡ መነሻውም ሆነ መድረሻው ማለትም መፈፀሚያው፣ ሌላ አካል ሳይሆን፣ ራሱ ፈፃሚው ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉት <u>ውስጠ-ቀር</u> ግሶች ሊባሉ ይችላሉ፡፡ ድርጊቱ ስዚያው በባለቤቱ ውስጥ የሚቀር እንጅ፣ ወደ ሌላ አካል የማይተላለፍ መሆኑን ያሳያሉና፡፡ ከላይ በተራ ቁጥር (4) የተመለከቱት ምሳሌዎች በሙሉ ውስጠ-ቀር ድርጊትን ገላጮች ናቸው፡፡

አንድ ባለቤት ድርጊት ፈፃሚ ሳይሆን፣ ሌሎች የሚፈፅሙት ድርጊት ወይም የሚፈጥሩት ሁኔታ ተጎጅ ወይም ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡

(ሀ) አስቴር ሽልማት ተቀበለች 6
(ለ) ካሳ ንብረት ተረከበ

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>አስቴር</u> ሽልማት የመስጠት ተግባር ፈፃሚ ሳትሆን፣ የተግባሩ ተጠቃሚ ወይም ተቀባይ ነች፡፡ ሽልማት የመስጠቱ ድርጊት የተፈፀመው በሌላ ሰው ነው፡፡ እንደዚሁም በሁለተኛው ምሳሌ፣ <u>ካሳ</u> ንብረት የመረከብ ድርጊት ፈፃሚ ነው፡፡ አስረካቢው አሁንም ሌላ ሰው ነው፡፡ ያ ሰው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ ተረካቢው ካሳ ደግሞ የግሱ መሙሊያ መሆን አለበት፡፡ እንደነዚህ ያሉትን ግሶች <u>ውስጠ-ገብ</u> ልንላቸው እንችላለን፡፡ ከአረፍተ ነገሩ ባለቤት የሚወጣውን ሳይሆን፣ ወደ ባለቤቱ የሚመጣውን ወይም የሚገባውን ድርጊት ያመለክታሉና፡፡ ይህ ከሆነ፣ የአረፍተ ነገሮቹ ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው መሆን አለበት፡፡




7

በግልፅ እንደሚታየው፣ የባለቤቱ ቦታ ክፍት (...) ነው፡፡ በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ መሙሊያ ሆነው የሚታዩት <u>አስቴርና</u> <u>ካሳ</u> የሚሉት ስሞች ክፍት ወደሆነው ቦታ

የሚያደርገው ግን ዕምር፣ ማለትም ዕውቅ ሲሆን ነው፡፡ የሚከተሉትን አያነፃፀርን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ለወታደሮች <u>ገንዘብ</u> ሰጠ /ሰኧጥ-ኧ/ 9

(ለ) ካሳ ለወታደሮቹ <u>ገንዘቡን</u> ሰጣቸው /ሰኧጥ-ኧ-አችችኧው/

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ <u>ገንዘብ</u> የሚለው ርቱዕ ተሳቢ ዕምር ስም አይደለም፡፡ ስለዚህም የተሳቢ ምልክት የሆነችውን /-ን/ን አላስከተለም፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ ይኸው ስም ዕምር ስለሆነ፣ የተሳቢ ምልክትዋን አስከትሎአል፡፡ የዕምርነት ምዕላድዋ /-ኡ/ ነች፡፡ <u>ለወታደሮቹ</u> የሚለው ኢርቱዕ ተሳቢ በግሱ ላይ /-አችችኧው/ በሚለው የተሳቢ አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው፣ <u>ወታደሮቹ</u> የሚለው ሀረግ ዕምር በመሆኑ ነው፡፡ በምሳሌ (ሀ) ውስጥ ይኸው ሀረግ አልታመረም፣ ስለዚህም በግሱ ላይ በተሳቢ አፀፋ አልተጠቀሰም፡፡ በተሳቢ አፀፋ መጠቀስና የተሳቢ ምዕላድ የሆነችውን /-ን/ን ማስከተል ከዕምርነት ጋር የተቆራኙ ቅርፃዊ የተሳቢ ስማዊ ሀረግ ባህሪያት ናቸው፡፡

መዋቅራዊ የሆነው የነዚሁ ሀረጎች ባህሪ ደግሞ የርቱዑ ተሳቢ ቦታ በቀጥታ ከግሱ በፊት መሆኑ ነው፡፡ ይህንና ከሳቢ ግሳዊ ሀረጎች የሚዋቀሩ አረፍተ ነገሮችን አጠቃላይ አወቃቀር በሚከተለው ዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡

10



በግልፅ እንደሚታየው፣ ሰጣቸው የሚለው ሳቢ ግስ ገንዘቡን ከሚለው ለማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ የድርጊቱ ቀጥተኛ ተጠቃሽ ወይም ተጠቂ ስሙ ስለሆነ፣ ድርጊቱን ከሚገልፀው ግስ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡ ለለዚህም ከግሱ ቀድሞ ይገባል፡፡ በቦታው ካልተገኘ፣ ግሱ ብቻውን የተሙዋሳ መረጃ ስለ ድርጊቱ ሊሰጥ አይችልም፡፡ በአንፃሩ፣ ለወታደሮቹ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ገንዘቡ የሚለውን ስም ያህል፣ ከግሱ ጋር የጠበቀ ቁርኝት፣ ብሎም ቀረቤታ የለውም፡፡ ስለዚህም፣ ከግሱ ራቅ ብሎና ገንዘቡ የሚለውን ተሳቢ ቀድሞ ይገባል፡፡ መዋቅራዊ ግንኙነቱም በቀጥታ ከግሱ ጋር ሳይሆን፣ ገንዘቡን ሰጣቸው ከሚለው ንዑስ ሀረግ ጋር ነው፡፡ ከዚህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ የሚፈጥረው ሀረግም ገንዘቡን ሰጣቸው ከሚለው ንዑስ ሀረግ ትንሽ ሰፋ ያለ ሌላ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ነው፡፡ ይህም ለልጆቹ ገንዘቡን ሰጣቸው የሚለው ነው፡፡ ሁኔታው ሁለት ደረጃ ያለው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ እንዳለ ያሳያል፡፡ የመጀመሪያው፣ ከግሱና ከርቱዕ ተሳቢው የሚዋቀር ሲሆን፣ ሁለተኛው የነዚህ ውጤት ከሆነው ንዑስ ግሳዊ ሀረግና ከኢርቱዕ ተሳቢ የሚዋቀር ነው፡፡ የአወራረዱና የቅደም-ተከተሉን ልዩነት ያመጣው ሁለቱ ተሳቢዎች ከግሱ ጋር ያሳቸው የቁርኝት ደረጃ ነው፡፡ ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው፣ ኢርቱዕ ተሳቢ የርቱዕ ተሳቢን ያህል ለግሱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ምልክቱ አንድ አረፍተ ነገር ከኢርቱዕ ይልቅ ርቱዑ ተሳቢውን ሲያጣ፣ የተቀባይነቱ ደረጃ የሚቀንስ መሆኑ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች የተቀባይነት ደረጃ መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) ካሳ ለተማሪዎቹ ገንዘቡን ከፈለ 11
(ለ) ካሳ ገንዘቡን ከፈለ
(መ) ? ካሳ ለተማሪዎቹ ከፈለ

ምሳሌ (ሀ) ሁለቱንም ተሳቢዎች ይዞአል፡፡ ስለዚህም ተቀባይነቱ የተሙዋሳ ነው፡፡ ምሳሌ (ለ) ኢርቱዕ ተሳቢውን አልያዘም፡፡ ይሁን እንጅ፣ ተቀባይነቱ ብዙም አልተናጋም፡፡ ምሳሌ (መ) ርቱዕ ተሳቢውን አልያዘም፡፡ ተቀባይነቱ ግን አጠራጣሪ ነው፡፡ ምን ከፈለ? የሚል ጥያቄ የግድ ያስነሳል፡፡ ይህም ኢርቱዕ ተሳቢ የርቱዕ ተሳቢን ያህል ለግሱ ተፈላጊ አለመሆኑን ይጠቁማል፡፡

ከላይ የሚታየው የሁለቱ ተሳቢዎች ቅደም-ተከተላዊ አገባብ ሊቀየር ይችላል፡፡ ይህም የሚሆነው፣ ርቱዕ ተሳቢው መሰረታዊ ቦታውን ለቆ ኢርትዑን ተሳቢ እየቀደመ ሲገባ ነው፡፡ ይህ ሲሆን፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ካሳ ገንዘቡን ለተማሪዎቹ ከፈለ -አቸው 12

ይህ ላዕላይ መዋቅር ሲሆን፣ ርትዑው ተሳቢ ከሁለተኛው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ስር ወጥቶ ከአቢዩ ግሳዊ ሀረግ ጋር ይዋቀራል፡፡ ይህም የሚሆነው ለዚሁ ለማዊ ሀረግ ከኢርትዑ ተሳቢ የበለጠ አፅንዖት ለመስጠት ሲፈለግ ነው፡፡ የሁለቱም

ተሳቢዎች መሰረታዊ ቦታ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ስር ለመሆኑ ከአፀፋቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ይኸውም ሁለቱም በተራ የተሳቢ አፀፋ በግሱ አምድ ላይ መጠቀሳቸው ነው፡፡ ርቱዑ ተሳቢ /-ኡ/ በሚሰውና በግሀድ በማይታየው ምዕላድ ፣ ኢርቱዑ ደግሞ -አቸው በሚሰው የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ምዕላድ ተመልክቶአል፡፡ የሀረጉን እንቅስቃሴ የሚያሳየውን የቦታ ለውጥ በሚከተለው ዕፀ - መዋቅር እናሳያለን፡፡




13

ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ገንዘቡን የሚለው ርቱዑ ተሳቢ፣ በግሀ1 ስር፣ ከፈላቸው ከሚለው ሳቢ ግስ በፊት ከሚታየው ክፍት ቦታ (...) ተነስቶ፣ ኢርቱዑን ተሳቢ በማቋረጥ ከዋናው ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዳብሎ ገብቶአል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ከርቱዑ ተሳቢ የበለጠ አፅንዖት ሊያገኝ ችሎአል፡፡ ከዚህም በላይ፣ ባለቤቱን ሰማዊ ሀረግ አልፎ፣ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ሊዋቀር ይችላል፡፡ ይህን ሲያደርግ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[[ገንዘቡን]i [ካሳ[ለተማሪዎቹ [...]i ከፈላቸው]]] 14

ይዘቱም ሆነ በመዋቅራዊ ቅርፁ የተሙዋላ ከፍተኛ ግሳዊ ሀረግ ነው እንደማለት ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ አንድ አረፍተ ነገር ከባለቤት ስማዊ ሀረግና ከአቢይ ግሳዊ ሀረግ የሚቀናጅ አቢይ መዋቅር ነው፡፡ ስማዊ ሀረጉ የቅንጅቱ ርዕስ ሲሆን፣ ግሳዊ ሀረጉ የዚህ ርዕስ ሀተታ ነው፡፡ ከዚህ አባባል አንድ መዋቅር አረፍተ ነገር ለመባል የግድ ስማዊ ሀረግ ባለቤት እንደሚያስፈልገው እንረዳለን፡፡ እስካሁንም ያየነው ሁኔታ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ አንዳንድ መዋቅሮች በግሀድ የሚታይ ስማዊ ሀረግ ባለቤት ሳይኖራቸው፣ አረፍተ ነገር የሚሆኑበት ሁኔታ አለ፡፡ እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

(ሀ) እግዜርን ይፈሩአል 17
(ለ) ንጉስን ያከብሩአል
(ሐ) ምክርን ያዳምጡአል

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ግስ ሳቢ ወይም ኢሳቢ ሊሆኙ ይችላል፡፡ ከዚህ ላይ የሚታዩት በሙሉ ሳቢ ናቸው፡፡ ተሳቢም አላቸው፡፡ ተሳቢዎቹ ግን ዕምር አይደሉም፣ ስላልሆኑም በግሶቹ ላይ በአፀፋ አልተጠቀሉም፡፡ ይሁን እንጅ ለተሳቢነታቸው /-ን/ የምትለዋን የተሳቢ ምልክት አስከትለዋል፡፡ የ/-ን/ አገባብም ቀደም ሲል ስለ ተሳቢ ስማዊ ሀረጎች ስንወያይ ከገለፅነው የተለየ ነው፡፡ ያኔ /-ን/ ከዕምር ስሞች ጋር ቁርኝት እንዳላት ገልፀን ነበር፡፡ የአሁኑ አገባብዋ ይህን የሚቃረን ነው፡፡ ምክንያቱም ተሳቢዎቹ ዕምር አይደሉም፡፡

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች አስካሁን ካየናቸው ሌሎች አረፍተ ነገሮች የሚለዩዋቸው ሌሎችም ባህሪያት አሉዋቸው፡፡ መጀመሪያ ነገር፣ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ባለቤት በግሀድ የሚታይና በአንደበትም የሚነገር ሀረግ አይደለም፡፡ በአፀፋ መልክ ብቻ የሚከሰት ነው፡፡ ሲከሰትም /ይ-/ እና /-ኡ/ ሆኖ ነው፡፡ ለምሳሌ <u>ይፈሩአል</u> የሚለውን የምሳሌ (ሀ)ን ግስ ብንመለከት፣ ታህታይ ቅርፁ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

/ይ-ፍኧር-ኡ-ኣልል/ 18

/ይ-/ የሶስተኛ መደብ ምዕላድ እንደ ሆነች፣ በርባታው ከፍል አይተናል፡፡ /-ኡ-/ም የብዙ ቁጥር ምዕላድ እንደ ሆነ አይተናል፡፡ -ኣ<u>ልል</u> ጊዜን አመልካች የሆነ ረዳት ግስ ነው፡፡ መደበኛ በሆነው የምዕላዶች አገባብ፣ /-ኡ-/ የምትገኘውና መገኘትም ያለባት ረዳት ግሱን /-ኣልል/ን ተከትላ እንጅ፣ እዚህ ላይ እንደሚታየው፣ ቀድማ አይደለም፡፡ በመደበኛው አገባብ ስትገኝ፣ የግሱ አጠቃላይ ቅርፅ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

/ይ-ፍኧር-ኡ አልል-ኡ / [ ይፍኧርኣልልኡ] ይፈራሉ 19

በሁለቱ ግሶች መካከል ያለው ልዩነት በ/-ኡ-/ አገባብ ላይ ብቻ ነው፡፡ በዚህ የአገባብ ልዩነት ምክንያት፣ የሁለቱ ግሶች ባለቤት የተለያየ ነው፡፡ እንዴት እንደሚለያይ ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) እነሱ እግዜርን ይፈራሉ /ይ-ፍኧር-ኣልል-ኡ/ 20
(ለ) *እነሱ እግዜርን ይፈሩሐል /ይ-ፍኧር-ኡ-ኣልል/
(መ) ---- እግዜርን ይፈሩሐል /ይ-ፍኧር-ኡ-ኣልል/

ምሳሌ (ሀ) ተቀባይነት አለው፡፡ ግሱ መደበኛ የሆነ የሶስተኛ መደብና የብዙ ቁጥር ነው፡፡ ባለቤቱ በግሀድ የሚታይ የሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም ነው፡፡ ምሳሌ (ለ) ተቀባይነት የለውም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ <u>እነሱ</u> የሚለውን ተውላጠ ስም በግሀድ ማሳየቱ ነው፡፡ ተውላጠ ስሙን በግሀድ በማያሳይበት ጊዜ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አለው፡፡ ይህንንም ከምሳሌ (መ) መረዳት ይቻላል፡፡

ይህ አመለካከት ትክክል ከሆነ፣ ሁኔታው በሌሎች አረፍተ ነገሮችም በዚሁ መልክ መከሰት አለበት፡፡ ይህም ማለት፣ ተውላጠ ስሙ በግሀድ በሚታይበት ጊዜ አረፍተ ነገሮቹ ተቀባይነት ማጣት አለባቸው፡፡ ይህ ግን የሚሆን አይመስልም፣ ምክንያቱም በአፀፋ የተጠቀሰ ባለቤት በግሀድ ላይታይ፣ በዚህም ምክንያት አረፍተ ነገሩ ላይዛባ ይችላልና፡፡ የሚከተሉት የዚህ አስረጅ ምሳሌ ናቸው፡፡

(ሀ) እግዜርን ይፍሩ /ይ-ፍር-ኡ/ 21
(ለ) ንጉሱን ያክብሩ /ይ-እክብር-ኡ/

እነዚህ አረፍተ ነገሮች እንደ ቀዳሚዎቹ በግሀድ የሚታይ ባለቤት የላቸውም፡፡ በግሶቹ መነሻና መድረሻ ላይ ግን ባለቤትን የሚጠቁም አፀፋ አለ፡፡ በአፀፋው መሰረት ባለቤቱ አሁንም <u>እነሱ</u> የሚለው ተውላጠ ስም ነው፡፡ በግሀድ ሲከሰት ወይም ሳይከሰት ይችላል፤ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ሳያጣ፡፡ ስለዚህም፣

(ሀ) እነሱ እግዜርን ይፍሩ /ይ-ፍር-ኡ/ 22
(ለ) እነሱ ንጉስን ያክብሩ /ይ-አክብር-ኡ/

ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ከፍ ሲል ካቀረብነው አመለካከት ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ ከፍ ሲል ባየነው አመለካከት መሰረት፣ እነዚህ አረፍተ ነገሮች መዛባት ነበረባቸው፡፡ ተውላጠ ስሙ በግሀድ ይታያልና፡፡ ግን አልተዛቡም፡፡ ለምን?

በአማርኛ የሶሰተኛ መደብ ተውላጠ ስም ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው አይነት ሰዋዊና ዕምር ነገሮችን የሚወክል ተውላጠ ስም ሲሆን፣ ሁለተኛው አይነት ኢሰዋዊና ጥቅል ነገሮችን ወይም ሁኔታዎችን የሚወክል ነው፡፡ ሰዋዊ

የሆኑት እሱና እነሱ የሚሉ መደበኛ ቅርፆች አሉዋቸው። አፀፋዎቻቸውም እንደ ቅደም-ተከተላቸው /ይ-/ እና /ይ-ኡ/ ናቸው። ኢሰዋዊ የሆኑት ተውላጠ ስሞች መደበኛ ቅርፅ የላቸውም። ስለዚህም የሚታወቁት በግሱ ላይ በሚታየው አፀፋ ብቻ ነው። አፀፋው የሚታየው ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው በዋናው ግስ መነሻና መድረሻ ላይ ብቻ ነው። የሰዋዊ ተውላጠ ስሞች አፀፋ ግን በዋናው ግስ መነሻና መድረሻ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በረዳት ግሱ መድረሻ ላይም ነው። ይህም ከላይ በተራ ቁጥር (19) እና (20) እንደሚታየው ነው። ከአፀፋዎቹ የአቀማመጥ ልዩነት የተነሳ፣ ባለቤትን የሚመለከተው የግሶቹ መዋቅራዊ ባህሪ ሊለያይ ችሉአል። አንደኛው ግሀድ ባለቤት ሲፈቅድ ሌላኛው አይፈቅድም።

23




23(ሀ) የኢሰዋዊ መዋቅር ነው። ስለሆነም የባለቤቱ ቦታ ክፍት ነው። 23(ለ) የሰዋዊ መዋቅር ስለሆነ፣ የባለቤቱ ቦታ እነሱ በሚሰው ተወላጠ ስም ተሞልቶአል። በዚሁ መሰረት ግሶችን ሰዋዊና ኢሰዋዊ ብሉ መለየት ይቻላል። ሰዋዊ ግሶች ብቻ ባለቤት፣ ማለትም ርዕስ አላቸው። ሁለተኛም ሁተታውን የሚገልፁት ግሳዊ ሀረጎች በማንኛውም የጊዜ አይነት ሊነገሩ ይችላሉ። ኢሰዋዊ ግሶች ግን ሁል ጊዜ በኢሀላፊ ጊዜ ብቻ ይነግራሉ። ዋናው ነገር፣ ግሶች ባለ ባለቤትና ባለቤት-አልባ (በገሀድ የሚታይ ባለቤት የለላቸው) ተብለው በሁለት ሊከፈሉ የሚችሉ መሆናቸው ነው።

ማንኛውም ስዋዊ ግስ ኢስዋዊ አቻ አለው፡፡ ከኢስዋዊዎች መካከል አንዳንዶቹ /ተ-/ የሚለውን የተደራጊ ምዕላድ በመነሻቸው ላይ ያሳያሉ፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡

24

/ይ-ሰኽብር-ኡ/ /ይ-ሰኽብር-ኡ-አልል-/ /ይ-ት-ሰኽብብኽር-ኡ-አልል-/
/ይ-ግኽድል-ኡ/ /ይ-ግኽድል-ኡ-አልል-/ /ይ-ት-ግኽድድኽል-ኡ-አልል-/

በመሰረቱ /ት-/ የተገብሮ ግስ መስራች ምዕላድ ነች፡፡ ከተገብሮ ግስ የሚመሰረት አረፍተ ነገርም የተገብሮ አረፍተ ነግር ይባላል፡፡ እስካሁን ካየናቸው ገቢር አረፍተ ነገሮች በቅርፁ ይለያል፡፡ እንዴት እንደሚለይ ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## ተገብሮአዊ አረፍተ ነገር

እስካሁን ያየናቸው ሀተታዊ አረፍተ ነገሮች ሁነታዊ፣ ኑረታዊ፣ ልውጠታዊ፣ ባህሪያዊና ገቢራዊ ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ አራቱ በባለቤቱ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከልም በአዕምሮም ይሁን በአካል የሚፈፀምን ተግባር የሚያሳየው ገቢራዊ አረፍተ ነገር <u>ገባሪ</u>፣ ማለትም ድርጊት ፈፃሚ እንዳለውና፣ የድርጊቱን ተቀባይ የሚሆን <u>ተገባሪ</u> ስማዊ ሀረግም ሊኖረው እንደሚችል አሳይተናል፡፡ ገባሪው የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሲሆን፣ ተገባሪው የግስ ተሳቢ ነው፡፡ እስካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች በሙሉ ስለ ገባሪው ባህሪ፣ ሁነት፣ ኑረት፣ ወዘተ፡ የሚያትቱ ናቸው፡፡ ስለዚህም ገባሪ-ተኮር ልንላቸው እንችላለን፡፡

የነዚህ ተቃራኒ የሆኑት ስለ ተገባሪው የሚያትቱ ናቸው፡፡ ይህም የሚሆነው ተገባሪው ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሲሆን ነው፡፡ የዚህ አይነት አረፍተ ነገሮች ተገብሮአዊ ይባላሉ፡፡ ግሱም የተገብሮ ግስ ይባላል፡፡ በቅርፁም ከገቢር ግስ ይለያል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንምልከት፡፡

(ሀ) እስቴር ተሹማለች 1
(ለ) ጫካው ተመንጥሮአል
(መ) ቡናው ተወቅጦአል
(ለ) አገሩ ተወሮአል

የእነዚህ አረፍተ ነገሮች ባለቤት በሙሉ ተገባሪ ወይም ተደራጊዎች ናቸው፡፡ ገባሪው ማን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ የየአረፍተ ነገሩ ሀተታ የሚያተኩረው በተደራጊው ላይ ስለሆነ፣ አድራጊው ትኩረት ሊያገኝ እናም ሊጠቀስ፣ አይችልም፡፡ ባጭሩ አድራጊው ይዋጣል ወይም ከፍ ሲል እንዳየነው ኢስዋዊ ይሆናል፡፡

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም <u>ተሹማለች</u> የሚለው ግስ መሙሊያ ነው፡፡ ባለቤቱ ለለማይታወቅ ቦታው ክፍት (--) ነው፡፡ <u>አስቴር</u> የሚለው መሙሊያ ስም ክፍት ወደሆነው የባለቤት ቦታ በመሄድ የአረፍተ ነገሩ ተደራጊ ባለቤትና የሀተታው ርዕስ ይሆናል፡፡ የአካሄዱን ሁኔታ ከዚህ ቀጥለን በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡



4

ከዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለው የሚገባ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ማንኛውም እንቅስቃሴ የሚደረገው፣ በታሀታይ መዋቅር ውስጥ ከሚገኝ አንድ ቦታ፣ ክፍት ሆኖ ወደሚገኝ ሌላ ቦታ ነው፡፡ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም ባለቤት ሊሆን የቻለው በታሀታይ መዋቅሩ ውስጥ፣ የባለቤቱ ቦታ ባዶ ስለሆነለት ነው፡፡ ወደዚያ ክፍት ቦታ በመሄድ ባለቤት ሊሆን፣ እናም አፅንዖትን ሊያገኝ ችሎአል፡፡

ይህ እንግዲህ ሰዋዊ ባለቤት ባላቸው ገቢር አረፍተ ነገሮች የሚታየው የተገብሮ አረፍተ ነገር ሁኔታ ነው፡፡ ቀደም ሲል ደግሞ ባለቤታቸው ኢሰዋዊ የሆነ አረፍተ ነገሮች እንዳሉ ምሳሌ እየጠቀስን አሳይተን ነበር፡፡ የእነዚህ አይነት አረፍተ ነገሮች ተገብሮአዊ ስርዓት ምን እንደሚመስል በሚከተሉት ምሳሌዎች አማካኝነት እናስረዳለን፡፡

(ሀ) ንብረትን ይዘረፉአል /ይ-ት-ዝኧርርኧፍ-ኡ-አልል/ [6] 5
(ለ) ስንቅን ይነጠቁአል /ይ-ት-ንኧጥጥኧቅ-ኡ-አልል/

---

[6] ከዚህ ላይ የተገብሮዋ ምዕላድ ከእምዱ መነሻ ተናባቢ ድምፅ ጋር ሙሉ በሙሉ መመሳሰልዋን ልብ ይሉአል፡፡

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ተግብሮአዊ እንደሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሶአል፡፡ ለዚህም /-ት-/ የምትለውን ምዕላድ ማስቀደማቸው ምልክት ነው፡፡ የገቢሩ ግስ እንቀፅ ካልዓይ ነው፡፡ ለለሆነም የባለቤት አፀፋው /ይ-/ በእምዱ መነሻ ላይ ከተገብሮዋ ምዕላድ ቀድሞ፣ የብዙ ቁጥር ምዕላድ የሆነው /-ኡ/ እምዱን ተከትሎ ገብቶአል፡፡ የተገብሮው ግሱ ቅድመ-መድረሻ አግርም ጠብቆአል፡፡ በዚህም ምክንያት የእምዱ እንቀፅ ቀዳማይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ የቅድመ-መድረሻው እግር ጥብቀት ግን ከተገብሮአዊነቱ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ማንኛውም ካልዓይ እንቀፅ ተገብሮአዊ በሚሆንበት ጊዜ ቅድመ-መድረሻ እግሩን ያጠብቃል፡፡ ለዚሀ የምሳሌ 5(ሀ)ን ግስ ከገቢራዊ አቻው ጋር እያነፃፀርን ብናየው፣ ልዩነቱ ግልፅ ይሆናል፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ገቢር ፡ | ይዘርፉአል | /ይ- -ዝኧርፍ-ኡ-አል/ | 6 |
| ተገብሮ፡ | ይዘረፉአል | /ይ-ት-ዝኧርርኧፍ-ኡ-አል/ | |

ከምሳሌ 5(ለ)፣ /ይ-ት--ንኧጥጥኧቅ-/ የሚለው የተገብሮው ግለ እምድ ቅድመ-መድረሻ እግር ጥብቅ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

በምሳሌ (5) ውስጥ፣ <u>ንብረትን</u> እና <u>ሰንቅን</u> የሚሉት ስሞች የየግሶቹ መሙሊያ ናቸው፡፡ የየአረፍተ ነገሩ ባለቤት ቀደም ሲል እንደገለፅነው ኢሰዋዊ ነው፡፡ ለለዚህም ነጠላ ከሆነ፣ /ይ-/ በሚለው የሶስተኛ መደብ ምዕላድ ብቻ፣ ብዙ ከሆነ ደግሞ /-ኡ-/ በሚለው የብዙ ቁጥር ምዕላድ ጭምር ይጠቀሳል (ይታወቃል) እንጅ በግሀድ ፊፅሞ አይከሰትም፡፡ መዋቅራዊ ቦታው ግን ከላይ በተራ ቁጥር (3) በሚታየው ዕፀ-መዋቅር ውስጥ በሰረዝ የተመለከተው ነው፡፡ መሙሊያው ወደዚሀ ቦታ ሄዶ ባለቤት ለመሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም እዚሀ ቦታ ከተገኘ የሀተታው ርዕስ ስለሚሆን፣ ግሀድ መውጣት ይኖርበታል፡፡ ግሀድ ከወጣ ደግሞ እንድም ኢሰዋዊ መሆኑ ይቀራል፣ አለያም አረፍተ ነገሩ ይዛባል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| (ሀ) | በግ ይነጠቃል | /ይ-ት-ንኧጥጥኧቅ-አል/ | 7 |
| (ለ) | --- በጎችን ይነጠቁአል | /ይ-ት-ንኧጥጥኧቅ-ኡ-አል/ | |
| (መ) | *በጎች ይነጠቋል | /ይ-ት-ንኧጥጥኧቅ-ኡ-አል/ | |

ምሳሌ (ሀ) ሰዋዊ የተገብሮ አረፍተ ነገር መዋቅር ነው፡፡ ምሳሌ (ለ) ኢሰዋዊ የተገብሮ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የባለቤቱ ቦታ ክፍት (--) ነው፡፡ ምሳሌ (መ) <u>በጎች</u> የሚለው መሙሊያ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ሆኖ በግሀድ የሚታይበት አረፍተ ነገር ነው፡፡ ባለቤቱ ግሀድ በመውጣቱ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን አጥቶአል፡፡ ሳዕላይ አወቃቀሩን ግን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

8




ባጭሩ ኢሰዋዊ የሆነ የገቢርም ሆነ የተገብሮ አረፍተ ነገር ባለቤት በአፀፋ ይታወቃል እንጅ በግሀድ አይከሰትም፣ ስለዚህም በግልፅ አይታወቅም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ እንደነዚህ ያሉትን ባለቤታቸው በውል የማይታወቅ አረፍተ ነገሮችን ኢውሱን በማለት ባለቤታቸውን በግሀድ ከሚያሳዩ አረፍተ ነገሮች መለየት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣

ነጋዴዎቹ ሰንቃቸውን ተዘርፈዋል 9

በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ባለቤቱ <u>ነጋዴዎቹ</u> የሚለው ዕምር ሰማዊ ሀረግ እንደሆነ ከአገባቡም ሆነ ከአፀፋው መረዳት ይቻላል፡፡ <u>ሰንቅን ይዘርፉአል</u> በሚለው ኢሰዋዊ ገቢር አረፍተ ነገር ውስጥ ግን ዘራፊውን፣ እንደዚሁም <u>ሰንቅን ይዘረፉአል</u> በሚለው ተግብሮአዊ አቻው ውስጥ፣ ተዘራፊውን አካል በውል ማወቅ አይቻልም፡፡ ማንኛውንም ዘረፋን ሊያካሄድ የሚችል አካልና ማንኛውንም ሊዘረፍ የሚችልን ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል፡፡ ስለዚህም በይዘቱ ኢውሱን ነው፡፡

እስካሁን ካየነው ዝርዝር ሁኔታ ሁለት አይነት ገቢርና ሁለት አይነት የተገብሮ አረፍተ ነገሮች እንዳሉ ለመረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህም ሰዋዊና ኢሰዋዊ ወይም ውሱንና ኢውሱን ናቸው፡፡ ውሱኖቹ የታወቀ ገባሪ ባለቤት ሲኖራቸው፣ ኢውሱኖቹ ያልታወቀ፣ ያልተወሰነ ተገባሪ ባለቤት አላቸው፡፡ የየአረፍተ ነገሩ ሀተታ ትኩረትም በውሱኑ ባለቤት ወይም መሙሊያ ላይ ነው፡፡ በመሙሊያው ላይ የሚሆነው፣ በምሳሌ 7(ለ) እንደሚታየው፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ኢውሱን በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

## *መጠይቃዊ አረፍተ ነገር*

እስካሁን ያየነው የሀተታዊ አረፍተ ነገሮችን መዋቅራዊ ባህሪና ተግባር ነው፡፡ በመዋቅራዊ ባህሪያቸው ባለቤት ስማዊ ሀረግ እንዳላቸውና ይህም ባለቤት በመዋቅራዊ ቦታውና በአፀፋ እንደሚለይ፣ እንደ ግሳቸው ባህሪም መሰተዋድዳዊ ወይም ስማዊ ሀረግ መሙሊያ ሊኖራቸው እንደሚችልና እነዚህም በአገባባቸውና በአፀፋቸው አይነት ከባለቤት ሀረጎች እንደሚለዩ አይተናል፡፡ ባለቤታቸው በየግሱ ለሚጠቀሰው ሁኔታ ወይም ተግባር አድራጊ፣ ወይም ተደራጊ ወይም ሁዋኝ ሊሆን እንደሚችል ተገንዝበናል፡፡ ተግባራቸውን በሚመለከትም፣ ከለማቸው እንደምንረዳው፣ ሀተታዊ አረፍተ ነገሮች እታች ወይም ተራኪ ናቸው፡፡ የሚተርኩት ስለ ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ ባለቤት ስማዊ ሀረግን እንደ አረፍተ ነገር ርዕስ፣ ግሳዊ ሀረግን ስለዚህ ርዕስ እንደሚቀርብ ሀተታ ወይም ትረካ አድርገን ልንመለከተው እንደምንችል ቀደም አድርገን ገልፀናል፡፡

አንድ አረፍተ ነገር ግን የሚያትት ብቻ ሳይሆን፣ በታተተው ጉዳይ ላይ ጥያቄ የሚያነሳም ሊሆን ይችላል፡፡ ጥያቄው ስለ ባለቤቱ፣ ስለ መሙሊያው፣ ስለ አነላማሹ ወይም ስለ ድርጊቱ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚህ ያለ አገልግሎት ያለውን አረፍተ ነገር መጠይቃዊ አረፍተ ነገር እንለዋለን፡፡ መዋቅራዊ ባህሪውን ከዚህ ቀጥለን እንደተለመደው በቅደም-ተከተል እንመረምራለን፡፡

አንድ ሰው ጥያቄ የሚጠይቀው፣ አንድም የማያውቀውን ነገር ለማወቅ፣ አለያም የሚያውቀውን ነገር ለማረጋገጥ ነው፡፡ የማያውቀውን ነገር ለመጠየቅ፣ መጠይቅ ተውላጠ ስሞችን ይጠቀማል፡፡ የሚያውቀውን ነገር ለማረጋገጥ የማረጋገጫ ቃላትን ወይም <u>*ቅላፄን*</u> ይጠቀማል፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት[7]፡፡

(ሀ) ካሳ መቸ መጣ? 1
(ለ) ካሳ መጣ ወይ?
(መ) ካሳ መጣ?

የመጀመሪያው አረፍተ ነገር፣ ጠያቂው፣ ካሳ የመጣበትን ጊዜ እንዳላወቀ ያሳያል፡፡ ስለዚህም ጊዜውን ለማወቅ <u>መቸ</u> የሚል መጠይቅ ተውሳጠ ስም በመጠቀም፣ የጥያቄውን አረፍተ ነገር አዋቅሯል፡፡ የዚህ አይነት ጥያቄ ዛሬ፣ ትናንት፣ ወዘተ፣ የሚል መልስ ይፈልጋል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ደግሞ፣ ጠያቂው ካሳ እንደሚመጣ ያውቃል፡፡ በርግጥ መምጣቱን ወይም አለመምጣቱን ግን አያውቅም፡፡ ስለዚህም አረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ <u>ወይ</u> የምትለዋን <u>*ቃለ ጥያቄ*</u>

---

[7] በመጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት ስለሚጠየቁ ጥያቄዎች መዋቅራዊ ባህሪ ግርማ (1992)ን ይመልከቱ፡፡ መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹ እንደ መስተዓምር ሊወሰዱና ሊተነተኑ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩን ወደ ሁዋላ እናየዋለን፡፡

(ሀ) ካሳ መጣ እንዴ? 3
(ለ) አስቴር ምሳዋን በላች እንዴ?

እንደነዚህ ያሉ ጥያቄዎች አወን፣ ወይም እንዲያውም (የለም) በሚል መልስ ብቻ ሳያቆሙ ይችላሉ፡፡ ምነው? ለምን ጠየቅኸኝ? የሚል ሌላ ጥያቄ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ በተለይም ተጠያቂው፣ ጠያቂው ለጥያቄው መነሻ ያደረገውን አውደ ነገር ያልተገነዘበ እስከሆነ ድረስ፡፡ ለምሳሌ፣ በወር መጨረሻ ላይ፣ ባል እንደተለመደው፣ አንድ ጥቅል ነገር ይዞ ወደ ቤቱ ቢገባ፣ በሚስት በኩል ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ፣

(ሀ) ደሞዝ ወሰድክ ወይ? 4

ሳይሆን፣

(ለ) ደሞዝ ወሰድክ እንዴ?

የሚል ይሆናል፡፡ ጥቅል ይዞ መግባቱ፣ ገንዘብ የማግኘቱ ምልክት ነውና፣ ጥያቄው ይሁኑ በከፊልም ቢሆን የታወቀ ነገር ለማረጋገጥ የሚነሳ ነው፡፡ ነገር ግን ባል ደሞዝ እንደሚወስድ እየታወቀ፣ ምንም ነገር ሳያንጠለጥል ቢመጣ፣ ሚስት ልትጠይቅ የምትችለው ጥያቄ፣

(ሀ) ደሞዝ ወሰድክ ወይ? 5

ወይም

(ለ) ደሞዝ ወሰድክ?

የሚል እንጅ፣

(መ) ደሞዝ ወሰድክ እንዴ?

የሚል አይሆንም፡፡ እንዴ የሚለውን ቃለ-ጥያቄ መጠቀም ካለባት፣ ጥያቄውን አሉታዊ በማድረግ፣

ደሞዝ አልወሰድክም እንዴ? 6

ማለት ይኖርባታል፡፡ ከፍ ሲል ከጠቀስነው ቅላጼ በተጨማሪ አውደ ነገርም ለሚነሳው ጥያቄ አይነት አስተዋፅዖ ሊያደርግ እንደሚችል እንዴ እና ወይ ከሚሉት ቃለ-ጥያቄዎች አጠቃቀም መረዳት ይቻላል፡፡

በአንድ አረፍተ ነገር ስለ ተገለፀ ድርጊት ወይም ሁኔታ፣ ስለ ድርጊቱ ፈፃሚ፣ ስለ ማድረጊያው መሳሪያ ወይም ጊዜና ቦታ፣ ድርጊቱ ስለተፈፀመበት ምክንያት ወይም ዓላማ፣ ስላደራረጉ ሁኔታ ወይም ዘዴ፣ ወዘተ፣ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ እነዚህ ደግሞ የሚገለፁት በተለያዩ ሀረጎች ስለሆነ፣ ጥያቄው የሚነሳው በመሰረቱ በየሀረጎቹ ላይ ነው፡፡ ሀረጎቹ በአራት ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ እነሱም

አድራጊ፣ ተደራጊ፣ ገላጭ (አጎላማሽ) እና መስተዓምር ብለን ቀደም ሲል የገለፅናቸው የየሀረጉ ተዋቃሪዎች ናቸው፡፡ ሁሉም በግሱ ከሚገለፀው ድርጊት ወይም ሁነት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተቆራኙ ስለሆኑ፣ የዚሁ መግለጫ ከሆነው ግስ ጋር መዋቅራዊ ግንኙነት አላቸው፡፡ ግንኙነቱም ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የባለቤትነት፣ የመሙሊያነት፣ የአጎላማሽነትና የመስተዓምርነት ነው፡፡ ስለዚህም የሚነሳው ጥያቄ ከነዚህ በአንዱ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህን ከዚህ ቀጥለን በምሳሌ እያሰደገፍን እናስረዳለን፡፡ የሚከተለውን አረፍተ ነገር እንመልከት፡፡

[ካሳ [ከእናቱ ጋር [በተሲያት [ምሳውን በላ]]]] 7

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ሁለት ስማዊ ሀረጎችና ሁለት መሰተዋድዳዊ ሀረጎች አሉ፡፡ ስማዊ ሀረጎቹ <u>ካሳ</u> እና <u>ምሳውን</u> የሚሉት ሲሆኑ፣ ተግባራቸውም ባለቤትነትና ተሳቢነት ነው፡፡ መሰተዋድዳዊ ሀረጎቹ <u>ከእናቱ ጋር</u> እና <u>በተሲያት</u> የሚሉት ሲሆኑ፣ ተግባራቸው ገላጭነት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከተሳቢው ስማዊ ሀረግና ከገላጮቹ መስተዋድዳዊ ሀረጎች የተዋቀረውና ድርጊቱን የሚገልፀው ግሳዊ ሀረግ አለ፡፡ ይህም <u>ከእናቱ ጋር በተሲያት ምሳውን በላ</u> የሚለው መዋቅር ነው፡፡

ጥያቄ የሚነሳው እንግዲህ እነዚህን ሀረጎች በሚመለከት ስለሆነ፣ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) <u>ማን</u> ከእናቱ ጋር በተሲያት ምሳውን በላ? 8
(ለ) ካሳ ከእናቱ ጋር በተሲያት <u>ምን</u> በላ?

እነዚህ ጥያቄዎች ስማዊ ሀረጎቹን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹም የሚገኙት ስማዊ ሀረጎቹ በሚገቡበት፣ ማለትም በባለቤትና በተሳቢ ቦታ ላይ ነው፡፡

(ሀ) ካሳ <u>ከማን</u> ጋር በተሲያት ምሳውን በላ? 9
(ለ) ካሳ ከእናቱ ጋር <u>መቼ</u> ምሳውን በላ?

እነዚህ ጥያቄዎች ስማዊ ሀረግን ሳይሆን፣ መስተዋድዳዊ ሀረጎችን የሚመለከቱ ገላጭ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹም የሚገኙት <u>ከ</u> ከሚለው መስተዋድድ ጋር ነው፡፡ በመጨረሻም ራሱን ግሳዊ ሀረጉን የሚመለከት ጥያቄ እንደሚከተለው መጠየቅ ይቻላል፡፡

ካሳ ምን አደረገ? 10

ይህ ደግሞ የድርጊት ጥያቄ ነው፡፡ አድራጊን፣ ተደራጊን ወይም ገላጭን ሳይሆን፣ ድርጊቱን ራሱን ከነምናምኑ የሚመለከት ነው፡፡ የተጠየቀውም ምን በሚል መጠይቅ ተውላጠ ስምና አደረገ በሚል ግስ አማካኝነት ነው፡፡ አደረገ የሚለው ግስ በማንኛውም የድርጊት ግስ ምትክ ሊገባ ይችላል፡፡ ምን እና ማን የሚሉት ማንኛውንም ስም ተክተው ሊገቡ እንደሚችሉና በዚህም ምክንያት መጠይቅ ተውላጠ ስም እንደሚባሉ ሁሉ፣ አደረገ የሚለው ግስም መጠይቅ ተውላጠ ግስ ሊባል ይችላል፡፡ የማንኛውም የድርጊት ግስ ምትክ ነውና፡፡ የጥያቄዎቹን ሀረጎች መዋቅራዊ አቀማመጥ በሚከተለው ዕፀ - መዋቅር እናሳያለን፡፡

11




እንደ አደረገ ሁሉ፣ አለ የሚለው ግስም በመጠይቅ ግስነት ሊገባ ይችላል፡፡ የሚገባው ግን ድርጊትን ሳይሆን፣ ብለትን (የአንድን ነገር መባል) ለመጠየቅ ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

ካሳ አመጣለሁ አለ 12

ይህ አረፍተ ነገር የሚገልፀው አንድ ድርጊት ማድረግን ሳይሆን፣ አንድ ነገር ማለትን ነው፡፡ ስለዚህም ግሱን የማለት ግስ ልንለው እንችላለን፡፡ እንደነዚህ ባሉ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ግሳዊ ሀረግን የሚመለከት ጥያቄ በዚሁ ግስና ምን በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት መጠየቅ ይቻላል፡፡ ይኸውም፣

ካሳ ምን አለ 13

በማለት ነው።

ቀደም ሲል ስለ አረፍተ ነገሮች ስንወያይ፣ አንድ አረፍተ ነገር ድርጊትን ብቻ ሳይሆን፣ ሁነትንና ኑረትንም እንደሚያመለክት ገልፀን ነበር። በዚያም መሰረት እነዚህን የሚመለከቱ ጥያቄዎች እንደሚከተለው አድርጎ በሁነትና በኑረት ግሶች አማካኝነት ማንሳት ይቻላል።

(ሀ) ካሳ የት አለ? 14
(ለ) ካሳ ምን ሆነ?

የመጀመሪያው የኑረት ሲሆን፣ ሁለተኛው የሁነት ጥያቄ ነው። መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹም የገቡት ጥያቄውን ባለከተለው ተዋቃሪ ሀረግ ቦታ ላይ ነው።

እስካሁን ድረስ ያየናቸው መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ነጠላ ጥያቄ የሚጠይቁ ናቸው። ይህም ማለት፣ አረፍተ ነገሮቹ የሚጠይቁት ስለ አንድ ነገር ወይም ድርጊት ወይም ኑረት ወይም ሁነት ብቻ ነው። መጠይቅ ተውላጠ ስሞቹም አንዳንድ ብቻ ናቸው። ይህ አንዱ የጥያቄ አይነት ነው። ሌላው አይነት ድርብ ጥያቄዎችን የሚመለከት ነው። የሚከተሉት የዚህ ምሳሌ ናቸው።

(ሀ) ማን ምን አደረገ? 15
(ለ) ማን ከማን ጋር ምሳ በላ?
(መ) ማን ምን በላ?

የመጀመሪያው ምሳሌ ባለቤቱን ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረጉን፣ ማለትም አድራጊውንና ድርጊቱን የሚጠይቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ አድራጊውን ከነአጋሩ የሚጠይቅ ነው። የመጨረሻው አድራጊውንና ተደራጊውን የሚመለከት ነው። እንደነዚህ ላሉ ድርብ ጥያቄዎች የሚሰጠው መልስ ድርብ ነው። ስለዚህም የመጀመሪያው ጥያቄ መልስ፣

ካሳ እንጀራ በላ 16

የሚል አይነት ይሆናል። የሌሎቹም መልስ በዚሁ ሁኔታ የሚሰጥ ነው።

አንድ መጠይቅ አረፍተ ነገር ከድርብ አልፎ ድርብርብ ሲሆን ይችላል። ይህም በአንድ ጊዜ ከሁለት በላይ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎችን ሊመለከት ይችላል ማለት ነው። ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው።

ማን ከማን ጋር ምን አደረገ? 17

ይህ አረፍተ ነገር አድራጊውን፣ አዳራጊውንና ድርጊቱን የሚመለከቱ መጠይቆችን ይዞአል፡፡ አድራጊውን ማን፣ በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም፣ አዳራጊውን ከማን ጋር በሚል ገላጭ መጠይቅ መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ እንደዚሁም ድርጊቱን ምን አደረገ? በሚል ግሳዊ ሀረግ በመጠየቅ ነው፡፡ ለእንደዚህ አይነት ጥያቄ የሚሰጠው መልስም፣

ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ በላ 18

የሚል ይሆናል፡፡ አወቃቀሩ በተራ ቁጥር (16) የተገለፀው አይነት ነው፡፡ ርግጥ፤ እንደነዚህ ያሉ ድርብርብ ጥያቄዎች በአወቃቀር አንጅ በአጠቃቀም ላይ ላያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ አብዛኛው የቋንቋዋው ተጠቃሚ የሚያተኩረው አንድን ነገር ብቻ በመግለፅ ወይም በመጠየቅ ላይ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፤ የቋንቋዋው ጥናት በሚባለው ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በሚታሰበውና ሊባል በሚችለው ጭምር የሚያተኩር በመሆኑ፤ የጥናቱን ትንተና በአብዛኛው ከአጠቃቀም ያለፈ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በአጠቃቀም ላይ ብቻ የሚወሰን ከሆነ፣ ብዙ ጥያቄዎች ያለምላሽ ይቀራሉ፡፡ የብዙዎቹ ጥያቄዎች መልሰ ከሚባለው ሳይሆን፣ ከሚታሰበው፣ ማለትም አዕምሮአዊ ከሆነው የቋንቋዋ ችሎታ ላይ የሚገኝ ነው፡፡

ድርብም ሆነ ድርብርብ መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ መጠይቅ ሀረጎች መሰረታዊ ቅደም-ተከተላቸውን ሊያፋልሱ አይችሉም፡፡ ስለዚህም፣

(ሀ) ማን ምን በላ 19
(ለ) ማን ከማን ጋር ምን አደረገ?

እንጅ፣

(ሀ) ?ምን ማን በላ? 20
(ለ) ?ከማን ጋር ምን ማን አደረገ?

ማለት አይቻልም፡፡

ይህን የቅደም-ተከተል ገደብ ቀደም ሲል ከጠቀስነው ከሰዋዊነትና ከኢሰዋዊነት ባህሪ ጋር ማገናዘብ ይቻላል፡፡ ሰዋዊ የሆኑ ነገሮችን የሚገልፁ ሀረጎች፤ ኢሰዋዊ የሆኑ ነገሮችን ከሚገልፁ ሀረጎች የበለጠ አፅንዖትን ይፈልጋሉ፡፡ ይህን የሚያገኙት፤ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ሲገኙ እንደሆነ ገልፀናል፡፡ በዚህም ምክንያት ኢሰዋዊ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎች፤ ሰዋዊ የሆኑ መጠይቅ ሀረጎችን ቀድመው በላዕላይ መዋቅር ሲገቡ፤ አረፍተ ነገሩ ተቀባይነትን ያጣል፡፡ የምሳሌ (20)ን ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

21




<u>ምን</u> የሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም ክፍት ከሆነው (...) ታሀታይ ቦታው ወጥቶ፣ <u>ማን</u> የሚለውን ለዋዊ ባለቤት መጠይቅ ተውላጠ ስም በመቅደምና ከፍ ካለ ርከን ላይ በመቀመጡ፣ ውጤቱ ተቀባይነት የሌለው መጠይቃዊ አረፍተ ነገር ሊሆን ችሎአል፡፡

እንግዲህ ስለ መጠይቅ አረፍተ ነገር እስካሁን በዝርዝር ያቀረብነውን እንደሚከተለው ለማጠቃለል እንሞክር፡፡ መጠይቅ አረፍተ ነገር አንድ ነገርን ለማወቅ ወይም ለማረጋገጥ የሚነገር የአረፍተ ነገር አይነት ነው፡፡ መዋቅራዊ ባህሪው መጠይቅ ተውላጠ ስሞችን፣ መጠይቅ ምዕላዶችን ወይም ግሶችን በሚጠየቀው ሀረግ ቦታ ላይ ማስገባት ነው፡፡ ተውላጠ ስሞቹ ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ ወዘተ፣ ያሉት ሲሆኑ፣ ምዕላዶቹ ደግሞ <u>እንዴ</u> እና <u>ወይ</u> የሚሉት ናቸው፡፡ ግሶቹም <u>አደረገና</u> <u>አለ</u> ናቸው፡፡ የሚገልፁትም እንደ ቅደም-ተከተላቸው <u>ድርጊትን</u>ና <u>ብለትን</u> ነው፡፡ በመጠይቅ ተውላጠ ስሞች አማካኝነት የሚጠየቁት አድራጊ፣ ተደራጊ፣ ገላጭና መስተዓምር ናቸው፡፡ አድራጊ፣ ተደራጊና መስተዓምር ስማዊ ሀረግ የሆነ መልስ ይፈልጋሉ፡፡ ገላጭ ጥያቄዎች ስማዊ ወይም መስተዋድዳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ፡፡ የድርጊትና የሁነት ጥያቄዎች ግሳዊ ሀረግ ይፈልጋሉ፡፡ ባጠቃላይ ጥያቄዎች በመጠይቅ ተውላጠ ስም፣ በመጠይቅ ተውላጠ ግስ፣ በቃለ ጥያቄና በቅላፄ መልክ ይከሰታሉ፡፡

ጥያቄዎች ነጠላ፣ ድርብና ድርብርብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነጠላ ጥያቄዎች አንድ ነገር ወይም ድርጊት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ አንድ የመጠይቅ ተውላጥ ብቻ ይሻሉ፡፡ ድርብ መጠይቆች በአንድ ጊዜ ሁለት ሀረጎችን የሚጠይቁ ሲሆኑ፣

ድርብርብ የሚባሉት ደግሞ ከሁለት በላይ የሆኑ ሀረጎችን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ድርብም ሆኑ ድርብርብ መጠይቅ ሀረጎች መሰረታዊ ቅደም ተከተላቸውን አይለቁም፡፡ በዚህም የመጠይቅ አረፍተ ነገሮችን ጉዳይ ለጊዜው እልባት ሰጥተን ወደሚቀጥለው ርዕስ ጉዳይ እንሄዳለን፡፡ ለጊዜው የምንልበት ምክንያት በሌላ ቦታ በሌላ አይነት መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ስለምንገናኝ ነው፡፡

## *አሉታዊ አረፍተ ነገር*

አንድ አረፍተ ነገር፣ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የሚያትት ወይም የሚጠይቅ ብቻ ላይሆን ይችላል፡፡ የታተተውን የሚያልት (አሌ የሚል) ሊሆንም ይችላል፡፡ የሚያልተውም ቀደም ሲል በሀተታ አረፍተ ነገር የተገለፀን አንድ ሀሳብ ነው፡፡ እንደዚህ ያለ ተግባር ያለው አረፍተ ነገር አሉታዊ ይባላል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል የምናተኩረው በእሉ ላይ ነው፡፡ የሚከተለውን ለአብነት እንመልከት፡፡

[ካሳ [ከእናቱ ጋር [ምሳውን በላ]]] 1

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሁለት ስማዊ ሀረጎች፣ አንድ መስተዋድዳዊ ሀረግና አንድ ግሳዊ ሀረግ አሉ፡፡ የነዚህ ቅንጅት የሆነው አረፍተ ነገርም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ እንደ አንድ ሰፊ ሀረግ የሚቆጠር ነው፤ ለዚያውም ግሳዊ፡፡ የሀረጎቹ መዋቅራዊ ዝምድና በቅንፎቹ እንደተመለከተው ነው፡፡ መጀመሪያ ግሱና ምሳውን የሚለው ስማዊ ሀረግ [ምሳውን በላ] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ይመሰርታሉ፡፡ ይህ ሀረግ ምሳ የመብላትን ፅንሰ-ሀሳብ ይገልፃል፡፡ ይህ ንዑስ ሀረግ [ከእናቱ ጋር] ከሚለው አዳራጊ መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣ [ከእናቱ ጋር ምሳውን በላ] የሚለውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ ሀረጉም ከእናት ጋር ምሳ የመብላትን ሀሳብ ይገልፃል፡፡ በመጨረሻም ይህን አቢይ ግሳዊ ሀረግ ካሳ ከሚለው አድራጊ ስማዊ ሀረግ ጋር በማቀናጀት፣ [ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን በላ] የሚለውን ሰፊ መዋቅር እናገኛለን፡፡ ይህም የአረፍተ ነገሩ መዋቅር ነው፡፡ ሀሳባዊ ይዘቱ የካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ የመብላቱ ድርጊት ነው፡፡ ይህ አረፍተ ነገራዊ ሀሳብ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኙት ተዋቃሪ ሀረጎች ሀሳብ ድምር ውጤት ነው፡፡ የሀረጎቹ ሀሳብም እንደዚሁ በውስጣቸው የሚገኙ ንዑስ ሀረጎች ሀሳብ ድምር ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ አንድ አረፍተ ነገር የሚነገርበት ምክንያት እንድን ሙሉ ሀሳብ ለተነጋሪ ለማሳወቅ ወይም ለማስገንዘብ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ አረፍተ ነገሩ ሰዋሰዋዊ፣ ማለትም የመዋቅርን ህግ የጠበቀ፣ ሙሉ ሀሳብን ያዘለና ውነትን የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፤ ውነት እንፃራዊ

ቢሆንም፡፡ አንድ አረፍተ ነገር በቅርፁ የተሰተካከለ፣ በይዘቱም የተሙዋላ ሆኖ ሳለ፣ ውነትን ግን በከፊልም ሆነ በሙሉ ላያንፀባርቅ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፤ ከላይ የተጠቀሰው አረፍተ ነገር የዚህ አይነት ህፀፅ ካለበት፣ አድማጩ፣ ማለትም ተነጋሪው፤ ላይቀበለው ይችላል፡፡ ካልተቀበለው ደግሞ እንደሚከተለው አድርጎ <u>ሊያልተው</u> ይችሳል፡፡

ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ አልበላም 2

ይህ አረፍተ ነገር ከላይ ከተሰጠው አወንታዊ አቻው የሚለየው በግሱ ቅርፅ ነው፡፡ ግሱ /አል-/ የሚል መነሻና /-ም/ የሚል መድረሻ አለው፡፡ በዚህም ምክንያት አወንታዊ የነበረው አረፍተ ነገር ወደ አሉታዊነት ተለውጦአል፡፡ የአሉታዊነቱ መንለዔ /አል-/ የሚለው ምዕላድ ብቻ ነው፡፡ /-ም/ የተራ አሉታዊ አረፍተ ነገር ምልክት ወይም ሞይ ነች፡፡ ግንኙነትዋም ከተወሰነ ሀረግ ጋር ሳይሆን፣ ከአጠቃላዩ አረፍተ ነገራዊ መዋቅር ጋር ነው፡፡ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር፤ እንደ <u>ወይ</u> ወይም <u>እንዴ</u> ያለ ምዕላዳዊ ምልክት እንዳለው ቀደም ሲል አይተናል፡፡ ተራ አወንታዊ የሀተታ አረፍተ ነገር ለአወንታዊነቱ የተለየ ምዕላዳዊ ምልክት ወይም ሞይ የለውም፡፡ በዚህም ከሌሎቹ ይለያል፡፡ ከላይ የሚታየው አረፍተ ነገር በዕፀ-መዋቅር ሲታይ የሚከተሰውን ይመስላል፡፡

3




/-ም/ ሞይ ለመሆንዋ ምልክቱ፣ አረፍተ ነገሩ ከሌላ አይነት ሞይ ጋር በሚዋቀርበት ጊዜ አሰዋ በቦታዋ ላይ አለመገኘትዋ ነው፡፡ ሁለተኛም ከላይ እንደሚታየው /-ም/ ልትቀር ትችላለች፡፡ በመቅረትዋ ግን የአረፍተ ነገሩ አሉታዊነት አይቀየርም፡፡ ይህን ከሚከተለው ምሳሌ መረዳት ይቻላል፡፡

[አለቱር [ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳ እንዳልበላ (<u>እንደ</u> አል-በላ)] ታውቃለች] 4

6




በግልፅ እንደሚታየው፣ የዕሴቱ ምዕሳድ መዋቅራዊ ግንኙነት ከአረፍተ ነገሩ ጋር ነው፡፡ የዕሴቱን *መጠነ ስፋት* ከግሱ ጀምሮ፣ ወደ ላይ በመውጣት ደረጃ በደረጃ እያሰፋ፣ እስከ አረፍተ ነገሩ መዋቅር ድረስ መሄድ ይቻላል፡፡ ጠባቡ የዕሴት መጠን አልበላም በሚለው ግስ ሲወሰን፣ ከፍተኛው ደግሞ ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበላም እስከሚለው አረፍተ ነገር ድረስ ይሄዳል፡፡ ከዚህም የምንረዳው፣ የአንድን አሉታዊ አረፍተ ነገር ፍች ከንበታዊ ቅርፁ በቀላሉ ማግኘት የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ፍችው በማያሻማ ሁኔታ ሊታወቅ የሚችለው፣ አረፍተ ነገሩ የተነገረበት አውደ ነገር ሲታወቅ ነው፡፡ ይህ እስካልሆነ ድረስ፣ አረፍተ ነገሩ በውስጡ ያለውን የህረግ መጠን ያህል ፍችው የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህን የተለያየ አሉታዊ ፍች በሶስት መንገድ ማግኘት ይቻላል፡፡ አንደኛው ከፍ ሲል እንደተመለከተው፣ አይደለም በሚለው አሉታዊ የሁነት ግስ አማካኝነት እገሌ እንጅ፣ እገሌ አይደለም፤ በማለት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ እንዲታለት የተፈለገውን ሀረግ ከታሀታይ ቦታው እያነሱ፣ እሳቹ ምዕላድ ጋር እንዲዋቀር በማደረግ ነው፡፡

(ሀ) ከእናቱ ጋር ምሳውን [ካሳ አልበላም] 7
(ለ) ካሳ ምሳውን [ከእናቱ ጋር አልበላም]
(መ) ከእናቱ ጋር ካሳ [ምሳውን አልበላም]

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ ባለቤቱ ሰማዊ ሀረግ፣ መስተዋድዳዊ ሀረጉ እና ተሳቢው ስማዊ ሀረግ የዕሌቱ ምዕላድ ወዳለበት በመጠጋት ሲታለቱ ችለዋል፡፡ ሁኔታውን በዕፀ መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

8



በግልፅ እንደሚታየው፣ መስተዋድዳዊው ሀረግ በነጠብጣብ ከተመለከተው ታህታይ ቦታው፣ ማለትም ከግሳዊ ሀረጉ (ግሀ2) ውስጥ፣ ተነስቶ እላቹ ምዕላድ ወደሚገኝበት ወደ (እነ') በመሄድ ከምዕላዱ ጋር ተዋቅሮአል፡፡ በዚሁ አይነት ሌሎቹም ሀረጎች ከታህታይ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ምዕላዱ ክልል ሲጠጉ እልት ይሆናሉ፡፡ ግሱም እንደዚሁ ወደ እሌቱ ምዕላድ በመሄድ ይታለትና መጀመሪያ እል-በላ ይሆናል፡፡ ከዚያ በሁዋላ ደግሞ ይኸው ዕልት ግስ ወደ ዋይዋ ምዕላድ ይወጣና አልበላም ይሆናል፡፡ በዚህም ቦታውን ለቆ ከሄደው መስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር መዋቅራዊ ግንኙነት ይፈጥራል፡፡ ይህም ማለት፣ ሁሉቱም ከግሳዊ ሀረጉ ወጥተው በእነ" ጥላ ስር ከእላቹ ምዕላድ ጋር ይገናኛሉ ማለት ነው፡፡

ይህ እንግዲህ መዋቅራዊ የሆነው የእሌት ስርዓት ነው፡፡ ሌላው ንበታዊ ነው፡፡ ይህም ሊታለት የተፈለገውን ሀረግ ከሌሎቹ ለይቶ በኀላ ቅላጼ በመናገር ነው፡፡ ይህን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፡፡

(ሀ) ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበላም 9

(ለ) ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበላም

(ሐ) ካሳ ከእናቱ ጋር ምሳውን አልበላም

እነዚህ ያረፈባቸው ሀረጎች ደምቀው (ጎልተው) የሚነገሩት፣ እናም የሚታለቱት ናቸው፡፡

እስካሁን የተመለከትነው /እል-/ በሚለው የእሌት ምዕላድ አማካኝነት የሚገለፀውን እሌት ነው፡፡ እንዳየነውም ይህ ምዕላድ በግሀድ የሚታየው፣ በግሱ መነሻ ላይ ነው፡፡ ስለዚህም ግሳዊ የእሌት ምዕላድ ልንለው እንችላለን፡፡

ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ስማዊ እሌትን እንመስከታለን፡፡ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፡፡

(ሀ) ብዙ ህፃናት ያለረዳት (የ-እለ-ረዳት) ያድጋሉ 10
(ለ) ብዙ ሰዎች ያለትዳር (የ-እለ-ትዳር) ይኖራሉ

በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ፣ ያለረዳት እና ያለትዳር የሚሉት መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ መስተዋድዱ /የ/ ነው፡፡ /እለ-/ የሚለው የስማዊ ሀረግ የእሌት ምዕላድ ነው፡፡ መዋቅራዊ ግንኙቱ ከስማዊ ሀረጉ ጋር ነው፡፡ /የ/ መስተዋድድ ስመሆንዋ ማስረጃው /ከ/ በሚለው መስተዋድድ ያለምንም የትርጉም ለውጥ ልትተካ መቻልዋ ነው፡፡ ይኸውም /ከ-እለ-ረዳት/ በምንልበት ጊዜ ነው፡፡ ሁለተኛም ሀረጉ እወንታዊ ሲሆን፣ መስተዋድዱ በቦታው ይገኛል፡፡ ይህ ሲሆን 10(ሀ) የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ከፍ ሲል የተነሳውን የእሴቱን ምዕላድ የመሰረታዊ አገባብ ጥያቄ በሁለት መንገድ መመለስ ይቻላል፡፡ አንደኛው፣ በግሀድ እንደሚታየው፣ መዋቅሮችን ለማዊና ግሳዊ ብሎ በመለየት የእሴቱን አገባብም ከዚሁ ልዩነት ጋር ማያያዝ ነው፡፡ መዋቅሩ ለማዊ ሲሆን፣ በመነሻ፤ መዋቅሩ ግሳዊ ሲሆን፣ በመድረሻ ላይ ይገባል ብሎ፣ ልዩነቱን መግለፅ ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ የእሴቱ ምዕላድ ሁለት ታሀታይ አገባብ አለው እንደ ማለት ነው፡፡ ይሀም የአገባቡን ስርዓት አጠቃላይነት ያሳጣዋል፡፡ አንድ መዋቅር ሲገኝ የሚችለው በመሰረቱ በአንድ ታሀታይ ቦታ ብቻ ነው፡፡ ያን ታሀታይ ቦታ አንዳንድ ጊዜ በተለያየ ምክንያት ሊለቅና በሌላ ቦታ ገብቶ ሊታይ ይችላል፡፡

የእሴቱን ምዕላድ መሰረታዊ ቦታ ለመወሰን ሁለተኛው መንገድ፣ አጠቃላዩን የቋዋንቋዋውን የሀረግ አወቃቀር ስርዓት፣ ከመሪና ከተመሪ አቀማመጥ አኩዋያ ማየት ነው፡፡ ባለፈው ክፍል ስለ ሀረጎች ለንወያይ በሰፊት እንደ ተመለከትነው፣ ሀረጎቹ ቀኝ መሪ ናቸው፡፡ መሪያቸውን አንዳንድ ጊዜ በግራ የሚያስቀምጡት መስተዋድዳዊና መስተዓምራዊ ሀረጎች ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህም ቢሆኑ ይህንን የሚያደርጉት በንዑስ ሀረግ ደረጃ ብቻ ነው፡፡ በሌሎቹ ሀረጎች ውስጥ የመሪው ቦታ በሀረጉ መድረሻ ላይ ነው፡፡ አጠቃላይ ሁኔታው ይህ ከሆነ፣ የማንኛውም ሀረግ ታሀታይ አወቃቀር፣ መሪውን በቀኝ፣ ማለትም በመድረሻ፣ ላይ ያስቀምጣል፤ ብሎ ማጠቃለል እንደሚቻል ገልፀናል፡፡ በዚሁ መሰረት፣ በቀራ ቁጥር (12)ና (13) የሚታየውን የተስያየ የእሴት ምዕላድ አገባብ እንደሚከተለው አድርጎ በአንድ ላይ ማቅረብ ይቻላል፡፡

15




[የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ወደ ትምሀርት ቤት መሄድ]
[የእነዚያ ሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ]

እነዚህ በቅንፍ ውስጥ የሚታዩት መዋቅሮች፣ አረፍተ ነገራዊ ይዘት ያላቸው ስማዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ መሪዎቹ የተስመረባቸው ስሞች ናቸው፡፡ የሁለቱም ሀረጎች ታህታይ ቦታ ከእሴቱ ምዕላድና ከመስተዋድዱ በፊት ነው፡፡ በተራ ቁጥር 12(ለ) እና (13) የሚታየውን ላዕላይ ቅርፃቸውን የሚይዙት፣ ከታህታይ ቦታቸው እየተነሱ ወደ ምዕላዶቹ ቀኝ ጎን ሲሄዱ ነው፡፡ የሚሄዱበት ምክንያትም ለመታለት ነው፡፡ አካሄዳቸው እንደሚከተለው ነው፡፡ መጀመሪያ መሄድ የሚለው ስም ወደ አሉቱ ምዕላድ ወደ /አለ-/ ይሄድና አለ-መሄድ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ በተራው ወደ /የ-/ ይሄድና ከጎንዋ ሲለጠፍ የአለመሄድ ይሆናል፡፡ ሁለተኛ፣ እነዚያ የሚለው /አለ-/ ወደሚለው አላች ይሄድና አለ-እነዚያ ይሆናል፡፡ ከዚያ በሁዋላ ደግሞ አለእነዚያ የሚለው ወደ /የ-/ ይሄድና የ-አለእነዚያ ይሆናል፡፡ ከዚያ በሁዋላ የሀብታሞቹ ልጆቹ ርዳታ የሚለው ክፍል እንዳለ ይሄድና በቀኝ በኩል ይሰለፋል[8]፡፡

እስካሁን ያየነው የተራ እሴትን መዋቅራዊ ስርዓት ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን የድርብ እሴትን ስርዓት እንመለከታለን፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

ካሳ ያለገባስ (የ-አለ-ገባስ) ጠላ አይጠጣም (አል-ይ-ጠጣም) 16

ይህ ተራ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ተራ የሚያሰኘው አንድ ግስ፣ ብሎም ግሳዊ ሀረግ፣ ያለው መሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁለት የእሴት ሀረጎችን ስለያዘ የእሴት ደረጃው ድርብ ነው፡፡ የገባስ ጠላ የሚለው ስማዊ ሀረግ /አለ-/ በሚለው ስማዊ የእሴት ምዕላድ፣ ጠጣ የሚለው ግስ ደግሞ /አል-/ በሚለው ግሳዊ የእሴት ምዕላድ ታልተዋል፡፡ የአረፍተ ነገሩ ትርጉም፣

ካሳ ያለገባስ ጠላ ሌላ መጠጥ አይጠጣም 17

የሚል ነው፡፡ ሌላ መጠጥ የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ተሳቢነቱ ለእልቱ ግስ ነው፡፡ ያለገባስ ጠላ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ የዚህ ስማዊ ሀረግ አጎላማሽ ነው፡፡ የሁለቱን መዋቅራዊ ዝምድና እና የአረፍተ ነገሩን ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

[8] ዝርዝሩ ብዙ ነው፤ እንቅስቃሴውም በውነቱ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ለቀላል አቀራረብ ሲባል ግን በዚሁ እንወስነዋለን፡፡ ወደፊት በሌላ ፅሁፍ የተለየና የበለጠ አጥጋቢ የሚመስል ትንተና እናቀርባለን፡፡ ለአሁኑ ይህን ውነት ብለን እንቀበል፤ ነገ ውሸት ሊሆን እንደሚችል ተማምነን፡፡ ውነት አንፃራዊ ነውና፤ የዛሬ ውነት፣ የነገ ውሸት ነው፡፡




በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>የገብስ ጠላ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ /እስ-/ በሚለው ስማዊ
አላች ምዕላድ ታልቶአል፡፡ አልቱ ስማዊ ሀረግ /የ-/ ከሚለው መስተዋድድ ጋር
ተዋቅሮአል፡፡ ይህ አንደኛው እሴት ሲሆን፣ ሌላው፣ <u>ካሳ ያለ ገብስ ጠላ ይጠጣ</u>

የሚለው አረፍተ ነገር ነው። ይህም የታሉተው /አል-/ በሚለው ግሳዊ የዕሴት ምዕላድ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ኢውሱን ተውላጠ ስሞችን ከስማዊና ከግሳዊ የአሉት ምዕላዶች ጋር በመጠቀም የአሌቱን ደረጃ ድርብርብ ማድረግ ይቻላል። ኢውሱን ተውላጠ ስሞች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ማንም[9] | የትም | የማንም | አንድም | 19 |
| ምንም | መቼም | የምንም | | |

እነዚህ በሙሉ /-ም/ በሚለው ምዕላድ አማካኝነት ከየመጠይቁ ተውላጠ ስምና <u>አንድ</u> ከሚለው ኢውሱን ተውላጠ ስም የተመሰረቱ ናቸው። አገልግሎታቸው በመስተዓምርነት ነው። እነሱ የሚገቡበት አረፍተ ነገርም አሉታዊ ሊሆን ይችላል። ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል።

(ሀ) ማንም ለማንም ምንም አይሰጥም (አል-ይ-ስጥ-ም) 20
(ለ)* ማንም ለማንም ምንም ይሰጣል

የኢውሱን ተውላጠ ስሞቹ አገባብ በመስተዓምርነት ነው። የሚታመሩት ስማዊ ሀረጎች ማንነት ከአውደ ነገሩ ስለሚታወቅ፣ ሊገደፉ ይችላሉ። በሚገደፉበት ጊዜ አረፍተ ነገሮቹ ከላይ የሚታየውን ቅርፅ ይይዛሉ። በማይገደፉበት ጊዜ ደግሞ የአረፍተ ነገሮቹ ቅርፅ የሚከተለውን ይመስላል።

ማንም <u>ሰው</u> ለማንም <u>ሰው</u> ምንም <u>ነገር</u> አይሰጥም 21

ከምሳሌዎቹ የምንረዳው ሌላው ነገር፣ ግሳዊ ሀረጎቹ ከኢውሱኖቹ ተውላጠ ስሞች ጋር በአሉት ስምሙ መሆናቸው ነው። ይሁን እንጅ፣ ኢውሱኖቹ ተውላጠ ስሞች በተፈጥሮአቸው አልት አይደሉም። ስለዚህም፣

(ሀ) ካሳ <u>ማንንም</u> ያምናል 22
(ለ) ካሳ <u>ማንንም</u> አያምንም

---

[9] እነዚህ ኢውሱን ተውላጠ ስሞች አሻሚ ትርጉም አላቸው። ለምሳሌ፣ <u>ማንም</u> የሚለው በእንግሊዝኛው anyone ወይም no one የሚለውን ኢውሱን ተውላጠ ስም ሊተካ ይችላል። አልት ግስ የሚፈልገው no one በሚለው ትርጉሙ ሲገባ ነው። anyone በሚለው ትርጉሙ ከአወንታዊ ግስ ጋር ሊዋቀር ይችላል። ለምሳሌ፦

ማንም ሊመጣ <u>ይችላል</u>

ማለት ይቻላል። no one በሚለው ትርጉሙ ሲገባ፦

ማንም ሊመጣ <u>አይችልም</u>

ይሆናል። <u>እንድ</u> የሚለው ምዕላድ እንደ እህዝ የአንድን ነገር መጠን ያመለክታል። እንደ ኢውሱን መስተዓምር ደግሞ የአንድን ነገር ዕምር ወይም ዕውቅ አለመሆን ያመለክታል። ስለዚህም እሻሚ ምዕላድ ነው።

የዚህ አረፍተ ነገር ትርጉም ልጆቹ ተመልሰዋል የሚል ነው፡፡

ከፍ ሲል ኢውሉን ተውላጠ ሰሞች ከእሉት ግስ ጋር እንደሚዋቀሩ ገልፀን ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ቀረ ከሚለው እሉት ግስ ጋር አይዋቀሩም፡፡ የሚዋቀሩት አል-ቀረ ከሚለው ድርብ እሉት ግስ ጋር ነው፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

(ሀ) *ማንም ለምሳ ቀረ 28
(ለ) ማንም ለምሳ አልቀረም

የምሳሌ (ሀ) ተቀባይነት ማጣት የሚያሳየው፣ የኢውሉኖቹ ተውላጠ ሰሞች ስምሙነት በተፈጥሮው እሉት ከሆነ ግስ ጋር ሳይሆን፣ በ/አል-/ አማካኝነት ከታሉተ ግሰ ጋር እንደሆነ የሚያሳይ ይመስላል፡፡

እስካሁን የተመለከትነው ህገኛ ሊባል የሚችለውን የእሉት ስርዓት ነው፡፡ ከዚህ ለየት የሚለው የሁነትና የኑረት ግሶች ባህሪ ነው፡፡ ግሶቹ አሉትን የሚያሳዩት በ/አል-/ አማካኝነት ሳይሆን፣ ቅርፃቸውን በመለወጥ ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ኀበዝ ነው 29
(ለ) ካሳ ኀበዝ አይደለም
(መ) *ካሳ ኀበዝ አልነውም

ነው የሚለው የሁነት ግስ ነው፡፡ አሉታዊ ቅርፁ አይደለም እንጅ፣ አልነውም አይደለም፡፡ አልነውም የሚለው ቅርፅ ለምን ተቀባይነትን ሊያጣ ቻለ? ብሉ መጠየቅ ይቻላል፡፡ ወደ መልሱ ከመሄዳችን በፊት የኑረት ግሰን እንመልከት፡፡

(ሀ) ካሳ ቤት ውስጥ አለ 30
(ለ) ካሳ ቤት ውስጥ የለም
(መ) *ካሳ ቤት ውስጥ አል-አለ-ም

ነው የሚለው የሁነት ግስ ከድርጊትም ሆነ ከባህሪ ግሶች የተለየ ነው፡፡ የሚለየውም በቅርፁና ከዚህም ጋር በሚያያዘው በርባታ ደረጃው ነው፡፡ ቅርፁ /ነ-/ በሚለው አንድ ተናባቢ ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፡፡ በመሆኑም ከሶስት ተናባቢዎች ከሚመሰረቱ ሌሎች ግሶች ይለያል፡፡ ሁለተኛም /ነ-/ ምንም ትርጉም የለውም፡፡ ትርጉም የሚያገኘው እሱን ተከትለው ከሚገቡ የርባታ ምዕላዶች ብቻ ነው፡፡ እነዚህም ቢሆኑ፣ የተሳቢ አፀፋዎች ናቸው፤ የባለቤት አይደሉም፡፡ የተሳቢ አፀፋ የሚታየው በመሰረቱ በሳቢ ግስ ላይ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት /ነ-/ የርባታ ምዕላድ ለመሸከም ብቻ የሚገባ ትርጉም-የለሽ ቅርፅ ወይም ምዕላድ እንጅ፣ ግሰ አይደለም ለማለት ይቻላል፡፡ ምናልባትም የርባታ ምዕላዶቹ የተሳቢ አፀፋ የሆኑት ምዕላዶ መደበኛ ባለትርጉም ግሰ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡

የለም የሚለው እልት ግስ መሰረት አለ የሚለው የኑረት ግስ ነው፡፡ የአሌት ምዕላዱ የግዕዙ /ኢ-/ እንጅ የአማርኛው /አል-/ አይደለም የሚሉ አሉ፡፡ ስለዚህም ታህታይ ቅርፁ /ኢ-አለ-ም/ ሲሆን፣ /ኢ-/ ወደ /ይ-/ ትለወጥና፣ ቅርፁ /ይ-አለ-ም/ የሚል ይሆናል፡፡ ጉዳዩ በይነ-ልሳናዊ የሆነ ጠለቅ ያለ ጥናት የሚጠይቅ ስለሆነ፡ እዚህ ላይ የምንጨምረው የለም፡፡ በጥቅሉ የኑረትና የሁነት ግሶች ስርዓት ከሌሎቹ የተለየ ነው፡ ብለን እናልፈዋለን፡፡

## ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተቱት አረፍተ ነገሮች ሀተታን የሚያትቱ፣ ጥያቄን የሚጠይቁ ወይም ሀሳብን የሚያልቱ ሳይሆኑ፣ ትእዛዝን የሚሰጡ ናቸው፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ትዕዛዝ አንቀፅ በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ የትዕዛዝን በር የሚያሳዩ እንደማለት ነው፡፡ እኛ ግን ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ልንላቸው እንችላለን፡፡ ትዕዛዝን የሚያሳዩት አረፍተ ነገራዊ ቅርፅና ይዘት ያላቸው የመዋቅር አይነት ናቸውና፡፡ ይሁኑ እንጅ፣ ከሌሎቹ አረፍተ ነገሮች የሚለዩበት ባህሪያት ስላሉዋቸው፡ እነሱን ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመረምራለን፡፡

መዋቅራዊ ባህሪያቸው የተወሰነ፣ ማለትም የታመረ ባለቤት የሚፈልጉ መሆናቸው ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ባለቤታቸው ማንኛውም እምር ስማዊ ሀረግ ሳይሆን፣ በዋናነት የሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ብቻ ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ጠጅ አምጣ! 1
(ለ) ወጥ አውጪ!

የመጀመሪያው አረፍተ ነገር ባለቤት አንተ የሚለው ተውላጠ ስም ሲሆን፣ የሁለተኛው ደግሞ አንቺ የሚለው እንስታይ ተውላጠ ስም ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ማስረጃዎች አሉ፡፡ አንደኛውና ዋናው ሰዋሰዋዊ ሲሆን፣ ከዚሁ ላይ የሚመሰረተውና ሁለተኛው ማስረጃ ንግግራዊ ነው፡፡ ሰዋሰዋዊውን በሚመለከት፣ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች እንደሚከተለው ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡

(ሀ) አንተ ጠጅ አምጣ! 2
(ለ) አንቺ ወጥ አውጪ /አውጥ-ኢ/

ከላይ ያለባለቤት የሚታዩት አረፍተ ነገሮች እዚህ ላይ ከነባለቤታቸው ይታያሉ፡፡ ባለቤታቸውም ሁለተኛ መደብ መሆኑ በግሀድ ይታያል፡፡ በተጨማሪም በሁለተኛው ምሳሌ ግስ መድረሻ ላይ የምትገኘው /-ኢ/፣ በክፍል ሁለት ስለፆታ ስንወያይ እንደገለፅነው፣ የሁለተኛ መደብ እንስታይ ፆታ ምዕላድ ናት፡፡

እነዚህ እንግዲህ ሰዋሰዋዊ ማስረጃ ያልናቸው ሲሆኑ፣ ንግግራዊ ማስረጃ የምንለው ደግሞ እነዚህን አረፍተ ነገሮች በሚናገረውና በሚነገረው ሰው መካከል

ባለው ግንኙነት ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች አንድ ተናጋሪ ካጠገቡ ለሚገኝ አንድ ሌላ ሰው በትዕዛዛዊ ቅላጼ የሚነገሩ ናቸው፡፡ ካሁን በፊት እንደገለፅነው፣ ተናጋሪው አንደኛ መደብ ይባላል፤ ንግግር ጀማሪ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተነጋሪው ሁለተኛ መደብ ይባላል፤ የነገሩ መድረሻ ነው፡፡ ተናጋሪንና ተነጋሪን የሚታዘብ ሌላ ሰው ካለ፤ ያ ሰው ሶስተኛ መደብ እንደሚባል ቀደም ሲል ተገልፆአል፡፡ ከዚህ ንግግራዊ አውድ አኳዋያ ሲታይ፣ የትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ባለቤት ሁለተኛ መደብ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በአረፍተ ነገር ላይ በግሀድ የማይታየውም ለዚህ ነው፣ ዕውቅ ለለሆነ፡፡

የማይገደፈው በአፅንዖት ሲነገር ብቻ ነው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ተው! 3
(ለ) አንተ ተው!

የመጀመሪያው መደበኛ ትዕዛዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን መደበኛ ብቻ ሳይሆን፣ ማስጠንቀቂያም ጭምር ነው፡፡ 'ተው ይህ ነገር አያዋጣህም' የሚል አይነት ነው፡፡ ስለዚህም አስጠንቃቂ ትዕዛዝ ልንለው እንችላለን፡፡ ከዚህ ካለፈም አረፍተ ነገሩ እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፡፡

(አንተ) ተው ብየሃለሁ! 4

ይህ ትዕግስቱን የጨረሰ ሰው የሚናገረው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ከትዕዛዝ ደረጃ ያለፈ የዛቻ አነጋገር ነው፡፡

ሁኔታው ትዕዛዝ የተለያየ ተግባር፣ አይነትና ደረጃ እንዳለውና፣ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮችም በዚሁ ላይ የሚመሰረት የተለያየ ቅርፅ ሲኖራቸው እንደሚችሉ ያሳያል[10]፡፡ እሁንም የሚከተሉትን እናነፃፅር፡፡

(ሀ) ልብሱን እጠበ-ው /-ኡ/ 5
(ለ) ልብሱን እጠብ
(መ) ልብስ እጠብ

ከነዚህ ምሳሌዎች መካከል የሚታይ የቅርፅ ልዩነት አለ፡፡ የመጀመሪያው ምሳሌ ዕምር ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አለው፡፡ የዚሁ ሀረግ አፀፋ የሆነችው /-ኡ/ም በግሱ መድረሻ ላይ ትታያለች፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ግን አፀፋዋ አትታይም፡፡ በሶስተኛው ምሳሌ ደግሞ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ ዕምር አይደለም፡፡ ስላልሆነም በግሱ ላይ በአፀፋ አልተጠቀሰም፡፡ ከነዚህ የቅርፅ ልዩነቶች የመነጨ የሚመስል የትዕዛዝ ልዩነትም ያለ ይመስላል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው ምሳሌ ለስለስ ያለ ትዕዛዝን የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግን ከዚህ ከረር ያለ ትዕዛዝን

[10] በዚህ ጉዳይ ላይ ሀይሉ (1980)ን ይመልከቱ፡፡

የሚያመለክት ይመስላል፡፡ ሶስተኛው ከሁሉም የበለጠ የትዕዛዝ መንፈስ ያለበት ይመስላል፡፡ ከነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳው አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ዕምርነት የመደበኛ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ባህሪ ያለመሆኑን ነው፡፡ ዕምር ሰማዊ ሀረግ ያለበት ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር ከትዕዛዛዊነት ይልቅ ወደ ማሳሳቢያነት የሚያዘነብል ይመስላል፡፡

የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት፡፡

(ሀ) ብላ! 6
(ለ) በል ብላ!
(መ) በል ብላት!

አንድ ምግብ አልበላም እያለ የሚያስቸግርን ልጅ ብናስብ፣ የእነዚህን ምሳሌዎች አግባብነት በቀላሉ ልንረዳ እንችላለን፡፡ የመጀመሪያው ተራ ትዕዛዝ ነው፡፡ ሁለተኛው ወላጅ ከልጁ አጠገብ ቁሞ ከዛቻ ጋር የሚሰጠው ትዕዛዝ ሲሆን፣ ሶስተኛው ከዛቻ ያለፈ ሀይል የሚታይበት ትዕዛዝ ነው፡፡ ልጁ አንድም እየተመታ፣ አለያም ከተመታ በሁዋላ ምግቡን እያለቀሰ የሚበላበት ሁኔታ ነው፡፡ በሶስተኛው ምሳሌ መጨረሻ ላይ የምትታየው /-እት/ ይህን ሁኔታ የምታመለክት ምዕላድ ነች፡፡ በቅርፅዋ የሶስተኛ መደብ አንስታይ ፆታ፣ የተሳቢ አፀፋ ትመስላለች፡፡ ግን አይደለችም፡፡ ብትሆን ኖሮ፣ በሳቢ ግስ ላይ ብቻ ትገኝ ነበር፡፡ የሚከተለውን እንመልከት፡፡

(ሀ) በል ተኛት 7
(ለ) በል ሂዳት

<u>ተኛ</u> እና <u>ሂድ</u> የሚሉት ኢሳቢ ግሶች ስለሆኑ፣ የተሳቢ አፀፋ ሊይዙ አይችሉም፡፡ ስለዚህም ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው፣ /-እት/ በነዚህ ምሳሌዎች ውስጥ የተሳቢ አፀፋ ሳትሆን፣ የዱላ ቀረሽ ትዕዛዝ ምልክት ነች፡፡ የዛቻ ምዕላድ ልንላት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ልጅ አልታዘዝም ብሎ እየሮጠ ቢሄድ፣ ከአዛዡ በኩል፣

(ሀ) ቆይ ትመጣለህ! 8

ወይም

(ለ) ቆይ ትመጣታለህ! (ት-መጥ-እት-አለህ)

የሚል ዛቻ ይደርሰበታል፡፡ የመጀመሪያው ተራ ዛቻ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከዚያ የከፋ ነው፡፡ /-እት/ ም የምትገኘው በዚሁ በሁለተኛው ምሳሌ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ መደበኛ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገር የሚነገረው አዛዥ ወይም ገሳጭ በሆነ ቅላፄ ነው፡፡ በመደበኛ የንግግር ቅላፄ ከተነገረ፣ ትዕዛዛዊ መሆኑ ይቀርና ፈቃጅ፣ ጋባዥ ወይም ተለማማጭ ይሆናል፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ጠጣ 9
(ለ) በል ጠጣ
(ሐ) በል ጠጣት
(ሰ) ትጠጣት

ቅላፄአቸው ካልታወቀ በስተቀር፣ እንደነዚህ ያሉ አባባሎችን ሰዋሰዋዊ ቅርፅ በማየት ብቻ ትዕዛዛዊ ናቸው ብሎ ለመደምደም አይቻልም። ትዕዛዛዊ የሚሆኑት፣ ከላይ እንደተገለፀው፣ በትዕዛዛዊ ቅላፄ ሲነገሩ ብቻ ነው። ከዚያ ውጭ ፈቃድን፣ ግብዣን፣ ቁልምጫን፣ ወዘተ፣ ሊያመለክቱ ይችላሉ። ከዚህ አኳር ሲታይ፣ የመጀመሪያው ምሳሌ፣ 'ጠላ ልጠጣ?' ብሎ ለሚጠይቅ ልጅ የሚሰጥ ፈቃድ ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ደግሞ አልጠጣም እያለ ለሚግደረደር ተጋባዥ የሚነገር የግብዣ አነጋገር ሊሆን ይችላል። ሶስተኛው፣ 'ጠጣ እንጅ! ይቺ ደግሞ ምን አላት?' እያለ የሚጋብዝ ወይም የሚያባብል ነው። የመጨረሻውም ተጋባዥ በትዕዛዝ ሳይሆን፣ በፈቃደኛነት እንዲጠጣ የሚጠይቅ ነው። ቅርፁም የካልዓይ አንቀፅ ነው።

ሁኔታው አረፍተ ነገሮችን በሚታዩበት መልካቸው ብቻ ትዕዛዛዊ ናቸው፣ ለማለት እንደማይቻል ያስገነዝባል። ትዕዛዛዊነታቸው በውል የሚታወቀው፣ ሲታዩ ሳይሆን፣ ሲባሉና በጆሮ ሲሰሙ ብቻ ነው። ባጭሩ ትዕዛዛዊነት መዋቅራዊ ብቻ ሳይሆን፣ ስነ-ድምፀ ልሳናዊ ጭምር ነው።

እስካሁን ያየነው አንድ ሰው አንድን ሌላ ሰው ሊያዝ የሚጠቀምበትን የአረፍተ ነገር አይነት ነው። ትዕዛዙ አዛዥና ታዛዥ ፊት-ለፊት ሲገናኙ የሚሰጥ ነው። ከዚህ ለየት የሚለው ትዕዛዝ ደግሞ አዛዥ ትዕዛዙን ለታዛዡ ፊት-ለፊት ሳይሆን፣ በመልከተኛ፣ ማለትም በሶስተኛ ሰው በኩል የሚያስተላልፍበት ሁኔታ ነው። ይህም እንደሚከተለው ነው።

(ሀ) ልብሰ ትጠብ 10
(ለ) እንጨት ትሰበር
(ሐ) እንጀራ ትጋገር

እንደነዚህ ያሉት ኢርቱዕ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮች ሊባሉ ይችላሉ። አንድን ትዕዛዝ በቀጥታ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ የሚያስተላልፉ ናቸውና። ባለቤታቸውም ሁለተኛ መደብ ሳይሆን፣ ሶስተኛ ነው። ስለሆነም ከነባለቤታቸው እንደሚከተለው ሆነው ሊነገሩ ይቻላሉ።

(ሀ) አስቴር ልብሰ ትጠብ 11
(ለ) አያልነሽ እንጨት ትሰበር

እንደነዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ትዕዛዝን ብቻ ላይሆን፣ ፈቃድንም ሊያሳዩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ሰው 'አስቴር ወደ ትምህርት ቤት ትሂድ ወይ?' ተብሎ ቢጠየቅና፣

ትሂድ 12

ቢል፣ መልሱ የፈቃድ እንጅ፣ የትዕዛዝ አይሆንም። ይህም የሚያመለክተው፣ ቀደም ሲል እንደተነገረው፣ የትዕዛዛዊ አረፍተ ነሮችን የአሻሚነት ባህሪ ነው። ትዕዛዝን ወይም ፈቃድን ሊያመለክቱ ይችላሉ። ከሁለቱ የትኛውን እንደሚያመለክቱ በውል የሚታወቀው በሚነገሩበት ቅላፄ ብቻ ነው። የትዕዛዝ ቅላፄ ከፈቃድ፣ ከመጠይቅ፣ ከእሌት እንዲሁም ከሀተታ ቅላፄ የተለየ ነው[11]። እንደዚያም ሆኖ፣ መዋቅራዊ ቅርፁን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

13




በዚህ ክፍል ስንወያይ የቆየነው ስለ ተራ አረፍተ ነገሮች ያወቃቀር ስርዓትና ተግባር ነው። ተራ አረፍተ ነገሮች አንድ ግሳዊ ሀረግ ብቻ ያላቸው ናቸው። ተግባራቸው ሀተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ አሉታዊና ትዕዛዛዊ ነው። የአንዱ አወቃቀር ከሌላው የተለየ ባህሪ አለው። በሀተታዊ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሁነትን፣ የኑረትን፣ የገቢርና የተገብሮ አረፍተ ነገሮችን መዋቅራዊ ባህሪ አይተናል።

የገቢር አረፍተ ነገር ባለቤት አድራጊ ወይም ገባሪ እንደሆነና ተገባሪ ስማዊ ሀረግ ሊኖረው እንደሚችል ገልፀናል፡፡ የተገብሮ አረፍተ ነገሮች ግስ ሳቢ የሆነ አቻ ግስ እንዳለውና ባለቤቱም ተደራጊ ስማዊ ሀረግ እንደሆነ አይተናል፡፡ የተገብሮነት ምልክት የሆነችው ምዕላድም /ተ-/ እንደሆነችና አሰዋም በጥቅሉ *ማዕከላይ* ድርጊትን ከምታመለክተው ከሌላዋ /ተ-/ በአገባብዋ የተለየች እንደሆነች ገልፀናል፡፡ በጥቅሉ ግሶችን የድርጊትና የሁነት ብሎ በመከፈል፣ የድርጊቶቹን ደግሞ ገቢር፣ ማዕካላይና ተገብሮ ብሎ መለየት እንደሚቻል ተገንዝበናል፡፡ በመጠይቅ አረፍተ ነገር ውስጥ የተራን፣ የድርብንና የድርብርብ መጠይቅን መዋቅራዊ ሁኔታ ተመልከተናል፡፡ የመጠይቅ ምዕላዶች <u>እንዴና</u> <u>ወይ</u> እንደሆኑ፣ መጠይቅ ተውላጠ ስሞችም ለጥያቄ መነሻ በሚሆነው ሀረግ መስረታዊ ቦታ ላይ እንደሚገቡ አይተናል፡፡ ጥያቄዎቹ ተራ ድርብና ድርብርብ ሊሆኑ እንደሚችሉም ተገንዝበናል፡፡ አሉታዊ አረፍተ ነገሮችም /አል-/ እና /አለ-/ በሚሉት ምዕላዶች አማካኝነት እንደሚመሰረቱ አይተናል፡፡ በአይነታቸውም ተራ፣ ድርብና ድርብርብ አሌትን ሊያሳዩ እንደሚችሉ አይተናል፡፡ ትዕዛዛዊ አረፍተ ነገሮችን በሚመለከት በግስ ቅርፅ፣ በባለቤት ባህሪና በቅላፄ ሊለዩ እንደሚችሉ ተገንዝበናል፡፡ ከመዋቅር አልፈን እስከ ትርጉም ድረስ በመሄድ የተግባራቸውን አሻሚነትና ይህንንም አሻሚነት ለመፍታት ቅላፄ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልፀናል፡፡ በሁሉም አረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግ አፀፋውን በግሱ እምድ ላይ የግድ ማሳየት እንዳለበትና በታህታይ መዋቅር ውስጥም ከሁሉም ሀረጎች ቀድሞና ከፍ ብሎ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ እንደሚገኝ ገልፀናል፡፡ ተሳቢ ስማዊ ሀረግም ርቱዕ ወይም ኢርቱዕ ሊሆን እንደሚችልና በግሱ ላይም ከባለቤቱ አፀፋ ቀጥሎ በራሱ አፀፋ ሊጠቀስ እንደሚችል አይተናል፡፡ መስተዋድዳዊ ሀረጎችም እንደዚሁ በግሱ ላይ /ለ-/ ወይም /በ-/ በሚል መስተዋድድና በተሳቢ አፀፋ ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ተረድተናል፡፡ ግሉ ሊይዝ የሚችለው የባለቤትን፣ የርቱዕን እና የኢርቱዕን ወይም የመስተዋድድ ሀረግን አፀፋ ብቻ እንደሆነም ተግንዝበናል፡፡ በዚህም የተራ አረፍተ ነገሮችን ውይይት እንቋዋጫለን፡፡

## መልመጃ

1. የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ትንታኔ በዕፀ-መዋቅር ያመልከቱ፡፡

   (ሀ) ልጁ አስቴርን በጣም ተቀየማት፡፡
   (ለ) ልጁ ተገረፈ፡፡

[11] ዝርዝሩን ከዓለማየሁ (1988) ይመልከቱ

2. የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ተቀባይነት ሰምን አጠራጣሪ እንደሆነ ምክንያቱን ይግለፁ፡፡ ተቀባይነት እንዲያገኙ አድርገው ያዋቅሩአቸው፡፡

   (ሀ) ? እሾህ አስቱርን ወጋት፡፡
   (ለ) ? ገነት አስቱርን ወስደችባት

3. የሚከተለውን አረፍተ ነገር ተንትነው በዕፀ-መዋቅር ያሳዩ፡፡

   ልጆቹ ምሳ አልበሉም እንዴ?

4. "እንኩዋን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሰሀ" የሚለው አረፍተ ነገር ተግባር ምን እንደሆነ ይግለፁ፡፡ የዚህን አረፍተ ነገር ባለቤት ይግለፁ፡፡

5. የአንድን አረፍተ ነገር ባለቤት ያለጥርጠር ማወቅ የሚቻለው በሰነ-ምዕላዳዊ ቅርፅ ብቻ ነው፡፡ ምሳሌ እየሰጡ ያብራሩ፡፡

6. "ከዚህ ጥፉ!" የሚለው መዋቅር ተግባር ምንድን ነው፡፡ ባለቤቱ በምን ይታወቃል፡፡

7. የሚከተሉት መዋቅሮች ትርጉም አንድ አይነት ነው፡፡ ቅርፃቸው ለምን እንደተለያየ ያስረዱ፡፡

   (ሀ) የካሳ መፅሀፍ ንባብ
   (ሰ) ካሳ መፅሀፍ አነበበ
   (መ) ካሳ መፅሀፍ ማንበቡ

8. ልጆቹን ጉንፋን ያዛቸው የሚሰው ሁተታዊ አረፍተ ነገር ባሰቤት ማን ነው? እንዴት?

9. አይነተኛ የተገብሮ ምዕላድ መለያ ምንድን ነው?

10. ካሳን ደከመው በሚሰው አረፍተ ነገርና ካሳ ደከመ በሚሰው አረፍተ ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዱ፡፡

# ውስብስብ አረፍተ ነገር

## *ውስብስብ ሀተታዊ አረፍተ ነገር*

ባለፈው ክፍል ስለተራ አረፍተ ነገሮች አይነት፣ ሰርዓትና ተግባር ተወያይተናል፡፡ ተራ አረፍተ ነገሮች ከተራ ስማዊና ግሳዊ ሀረግ ይዋቀራሉ፡፡ ተራ ሀረጎች ደግሞ ከተራ መሪ፣ ከሀረጋዊ መሙሊያ፣ አጎላማሽና መስተዓምር ይዋቀራሉ፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን ቀደም ሲል ስለተለያዩ ሀረጎች ስንወያይ ተመልክተነዋል፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሳቢ ግስ ከመሙሊያ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግሳዊ ሀረጉን እንደሚፈጥር፣ ያ ንዑስ ሀረግ ደግሞ ከተለያዩ ገላጭ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ጋር ተቀናጅቶ አቢይ ሀረጉን እንደሚመሰርት፣ አቢይ ሀረጉም ከተለያዩ መስተዓምሮች ጋር በመዋቀር ዋናውን አቢይ ሀረግ እንደሚያዋቅር አይተናል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚፈጠር ሀረግ ተራ ሀረግ ሲባል፣ ከዚህ አይነት ሀረግ የሚፈጠር አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ተራ አረፍተ ነገር ይባላል፡፡ ተግባሩም ተራ ሀሳብን መግለፅ፣ መጠየቅ፣ ማለት (አሌ ማለት)፣ ወዘተ፣ ነው፡፡

አንድ አረፍተ ነገር ተራ ካልሆነ ውስብስብ ነው፡፡ እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር ደግሞ ከውስብስብ ሀረጎች የሚፈጠር ሰፊ መዋቅር ነው፡፡ ውስብስብ ሀረጎች በውስጣቸው ተራ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ አረፍተ ነገራዊ የሆነ መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ አላቸው፡፡ አረፍተ ነገራዊው መሙሊያ ወይም አጎላማሽ ከግሳዊ ወይም ከስማዊ ሀረግ ጋር ስለሚዋቀር፣ ከዚህ አይነት ግሳዊ ወይም ስማዊ ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ውስብስብ ይሆናል፡፡ ተግባሩም እንደዚያው፡፡

የዚህ አይነት ግሳዊና ስማዊ ሀረጎች ያሉዋቸውን አረፍተ ነገሮች ሰርዓት ከዚህ ቀጥለን አንድ በአንድ እንመረምራለን፡፡ ከዚያ በፊት ግን በሀረግ ውስጥ ስለሚገኙ አረፍተ ነገሮች አንድ ነገር ማንሳት አለብን፡፡ ይኸውም አረፍተ ነገሮቹ ግሳዊና ስማዊ ተብለው በሁለት የሚከፈሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ግሳዊ የሚባሉት ግሳዊ ሀረግ ያላቸው ሲሆኑ፣ ስማዊ የሚባሉት ደግሞ በግሳዊ ሀረግ ፋንታ ሰማዊ ሀረግ ያላቸው ናቸው፡፡ ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን፡፡

| | | |
|---|---|---|
| (ሀ) | አስቴር [በሩን ከፈተችው] (ከፈተ-ች-ው) | 1 |
| (ለ) | አስቴር [በሩን መክፈትዋ] (መክፈት-ኡ-ኣ) | |
| (መ) | የአስቴር [በሩን መክፈት] | |
| (ሰ) | --------- [በሩን መክፈት] | |

የመጀመሪያው ምሳሌ፣ ግሳዊ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ግሳዊ ሀረጉ በቅንፍ ውስጥ የሚታየው ሲሆን፣ የዚህ ሀረግ መሪ ደግሞ [ከፈተ-ች-ው] የሚለው ሳቢ ግስ ነው፡፡ ግሱ የባለቤቱንና የተሳቢውን አፀፋ ያሳያል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ውስጥ፣ [በሩን መክፈትዋ] የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ የሀረጉ መሪ [መክፈትዋ] የሚለው የድርጊት ስም ነው፡፡ እርዕስት እንደሚባል በምስረታው ንዑስ ክፍል ተገልፆአል፡፡ ይህም መሪ [-ዋ] < /ኡ-ኣ/ የምትለዋን ድርብ ምዕላድ አስከትሎአል፡፡ ይህች ምዕላድ በግሱ ላይ ከምትታየው የባለቤት አፀፋ፣ ማለትም ከ[-ች] < /-ት-ኢ/፣ ጋር በግብር አንድ ነች፡፡ ባለቤትን ትጠቁማለችና፡፡ በሁለቱ አፀፋዎች መካከል ያለው ልዩነት የቅርፅ ብቻ ነው፡፡ ይህም ልዩነት የመጣው አፀፋዎቹ ከተቀጠሉባቸው ቃላት ክፍል ልዩነት ነው፡፡ ቃላቱ ግሳዊ ሲሆኑ፣ አፀፋዋ [-ች] ትሆናለች፡፡ ቃላቱ ስማዊ ሲሆኑ፣ አፀፋዋ [-ዋ] ትሆናለች፡፡ ሁለተኛም ግሳዊ አረፍተ ነገር የባለቤትን ብቻ ሳይሆን፣ የተሳቢ አፀፋንም ሊያሳይ ይችላል፡፡ በአንፃሩ ስማዊ አረፍተ ነገር የተሳቢ አፀፋን አያሳይም፡፡ ከዚያም አልፎ ከምሳሌ (መ) እንደምንረዳው የባለቤት አፀፋንም ሳያሳይ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን፣ ባለቤቱ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ በመነሻው ላይ ያሳያል፤ አለያም በምሳሌ (ረ) እንደሚታየው በግሀድ ከመታየት ይታቀባል፡፡

በአጠቃላይ በአፀፋ የሚጠቀስ ሀረግ በግሀድ ላይከሰት ይችላል፡፡ ከአፀፋው ቅርፅ የየሀረጉን መደብ፣ ቁጥር ወይም ፆታ ለማወቅ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፣ ምሳሌ 1(ሀ) እና (ለ)ን እንደሚከተለው ለማለት ይቻላል፡፡

(ሀ) ----- [----- ከፈተችው] (ከፈተ-ች-ው) 2
(ለ) ----- [በሩን መክፈትዋ] (መክፈት-ዋ)

በምሳሌ (ሀ) የባለቤቱና የተሳቢው ሀረግ፣ በምሳሌ (ለ) የባለቤቱ ሀረግ ብቻ ተገድፈዋል፡፡ ስለ ስማዊና ግሳዊ አረፍተ ነገር ይህን ያህል ካልን፣ አሁን አረፍተ ነገሮቹ ወደሚገኙባቸው ሀረጎች እንመለስና መዋቅራዊ ባህሪያቸውን እንይ፡፡ ከስማዊ ሀረጎች እንጀምራለን፡፡

## ውስብስብ ስማዊ ሀረግ

ውስብስብ ስማዊ ሀረጎች በውስጣቸው መሙሊያ እና/ወይም አጎላማሽ አረፍተ ነገር አላቸው፡፡ የሁለቱንም ዓይነት አረፍተ ነገሮች አገባብ ከዚህ ቀጥለን በየተራ እንመለከታለን፡፡

### (ሀ) መሙሊያ አረፍተ ነገር

መሙሊያ አረፍተ ነገሮች የሚባሉት፣ በአንድ ስማዊ ሀረግ ውስጥ፣ ከመሪው ስም ጋር እየተዋቀሩ ንዑስ ስማዊ ሀረግ የሚመሰርቱና የመሪውን ስም ይዘትም ሙሉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ እነዚህም እንደሚከተሉት ያሉ ናቸው፡፡

[[የካሳ ቤት የመስራት] ዓላማ]　　　3

ይህ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ የሀረጉ መሪ [ዓላማ] የሚለው ስም ነው፡፡ ይህ መሪ [የካሳ ቤት የመስራት] ከሚለው መዋቅር ጋር ተቀናጅቶ [የካሳ ቤት የመስራት ዓላማ] የሚል ሰፊ ስማዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡

[የካሳ ቤት የመስራት] የሚለው መዋቅር ስማዊ አረፍተ ነገር ነው፡፡ አገባቡም ዓላማ ለሚለው መሪ ስም መሙሊያ ሆኖ ነው፡፡ ያለ መሙሊያው መሪው ስም ብቻ ሙሉ ሀሳብ አይሰጥም፡፡ የምን ዓላማ? የሚል አይቀሬ ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ጥያቄው እንዳይነሳ ከፈለግን፣ የዓላማውን ይዘት መግለፅ ይኖርብናል፡፡ ይዘቱ የሚገለፀው በአረፍተ ነገር ስለሆነ፣ አረፍተ ነገሩ የመሪው ስም መሙሊያ ነው፡፡ ከመሪው ጋር ያለው መዋቅራዊ ቅንጅት እንደሚከተለው ነው፡፡

4



በግልፅ እንደሚታየው፣ [የካሳ ቤት የመስራት] የሚለው ስማዊ አረፍተ ነገር ከንዑሱ ስማዊ ሀረግ (ስሀ1) አንጉዋ በመውረድ <u>ዓላማ</u> ከሚለው መሪ ስም ቀድሞ ገብቶአል፡፡ ይህ የመሙለያዎች አይነተኛ አገባብ ነው፡፡ ግንኙነታቸው በቀጥታ ከመሪው ስም ጋር ነው፡፡

መሙሊያው አረፍተ ነገር <u>የካሳ</u> ከሚለው ባለቤትና <u>ቤት መስራት</u> ከሚለው ስማዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው፡፡ <u>የካሳ</u> በሚለው ስም መነሻ ላይ የምትታየው /የ/ <u>ካሳ</u> የአረፍተ ነገሩ ባለቤት መሆኑን የምታመለክት ምዕላድ ነች፡፡ አፀፋ ግን አይደለችም፡፡ ያለእሰዋ ካሳ የሚሰው ስም ባለቤት መሆኑ አይታወቅም፡፡ ምክንያቱም <u>መስራት</u> በሚለው መሪ ስም ላይ ካሳን የሚጠቁም አፀፋ የለምና፡፡ በአፀፋ ያልተጠቀሰ የስማዊ አረፍተ ነገር ባለቤት፣ እንድም ከላይ እንደሚታየው /የ/ን ያስቀድማል፣ አለያም ከቦታው ይጠፋል፡፡ ከላይ የሚታየው ሁኔታ ባለቤቱ /የ/ን አስቀድሞ በግህድ ሲከስት የሚያሳይ ነው፡፡ /የ/ን ባለማስቀደሙ ከቦታው ሲጠፋ ደግሞ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[--- ቤት መስራት] 5

የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ በሰረዝ የተመለከተው ነው፡፡ <u>መስራት</u> የሚለው መሪ ላይ በአፀፋ ስላልተጠቀሰ፣ ማንነቱ አይታወቅም፡፡ ማንነቱ ስንል፣ መደቡ፣ ቁጥሩና ፆታው ማለታችን ነው፡፡

ሌላው ልንገነዘበው የሚገባ ነገር [ቤት የመስራት] በሚለው ሀረግ ውስጥ፣ <u>መስራት</u> በሚለው መሪ ስም መነሻ ላይ የምትታየውን /የ/ን ይመለከታል፡፡ ይህች /የ/ ስማዊ አረፍተ ነገሩ ነፃ ሳይሆን፣ ጥገኛ ሆኖ መግባቱን የምታመለክት ምዕላድ ነች፡፡ ጥገኝነቱም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ <u>ዓላማ</u> ለሚለው ለስማዊ ሀረጉ መሪ ነው፡፡ ስለዚህም ቀደም ሲል ካየናት ባለቤት አመልካች /የ/ በተግባርም ሆነ በአገባብ ትለያለች፡፡ ይህችኛዋ /የ/ ጥገኝነትን አመልካች ስትሆን፣ ያችኛዋ /የ/ ባለቤትነትን አመልካች ነች፡፡ ይህችኛዋ /የ/ በሳዕላይ መዋቅር ውስጥ፣ ከአረፍተ ነገሩ መሪ ስም ቀድማ ስትገባ፣ ያችኛዋ /የ/ ከአረፍተ ነገሩ ባለቤት ቀድማ ትገባለች፡፡ የዚችኛዋ /የ/ መስረታዊ አገባብ ጥገኛ ከሆነው አረፍተ ነገር ጋር ነው፡፡ ጥገኛው አረፍተ ነገር በሞይነት የገባ መሆኑን ስለምታመለክት <u>ምይ</u> ልንላት ችለናል፡፡ አረፍተ ነገሩንም ተሞይ ልንለው እንችላለን፡፡ መሙሊያው የጥገኛው አረፍተ ነገርና የሞይዋ ቅንጅት ሲሆን፣ አቀነጃጀቱንም እንደሚከተለው በዕፀ - መዋቅር እናሳያለን፡፡

6




ይሀ እንግዲህ የመመሲያው አረፍተ ነገር ታህታይ መዋቅር ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ ጥገኛ ሆኖ በመመሲያነት የገባ መሆኑን ከምታሳየው ከ/የ/ ጋር የተዋቀረ ስለሆነ፣ ይዘቱ ከመደበኛ፣ ማለትም ጥገኛ ካልሆነ፣ አረፍተ ነገር ይዘት የሰፋ ነው፡፡ ይህን ሰፊ መዋቅር (አነ') በሚል <u>ምህፃር</u> እናመለክታለን፡፡ እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር ሲተነተን፣ ከላይ እንደሚታየው፣ አረፍተ ነገር (አነ) እና ሞይ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ የሞዩ ቦታ በግልፅ እንደሚታየው ከመመሲያው አረፍተ ነገር በስተቀኝ ነው፡፡ /የ/ <u>መስራት</u> ከሚለው መሪ ስም ጋር የሚቀናጀው በላዕላይ መዋቅር፣ ማለትም በንግግር ደረጃ ነው፡፡ /የ/ ራስዋን ችላ መቆም የማትችል ምዕላድ ስለሆነች፣ ደጋፊ ያስፈልጋታል፡፡ ስለዚህም በላዕላይ መዋቅር ደረጃ፣ አጠገብዋ ከሚገኘው፣ መስራት ከሚለው መሪ ስም መነሻ ላይ ልትለጠፍ ችላለች፡፡ ይህን ስታደርግም መስራት የነበረው መሪ ስም ቅርፁን ለውጦ <u>የመስራት</u> ይሆናል፡፡ ካሁን በፊት፣ በእሉታዊ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ግሱ ወደ እሌቱ ምዕላድ ሲሄድ አይተን ነበር፡፡ የአሁኑም <u>መስራት</u> የሚሰው መሪ እካሄድ እንደዚያው አይነት መሆኑን እናስተውል፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም የሞይዋ ታህታይ በታ ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ስመሆኑ ማስረጃው ምንድን ነው? የሚል ነው፡፡ ለዚህ ሁለት ማስረጃዎች አሉ፡፡ አንደኛው ትውረታዊ ነው፡፡ ሞዮች የአረፍተ ነገር መሪ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ አንድ አረፍተ ነገር ጥገኛ መሆኑ የሚታወቀው በእነሱ አማካኝነት ነውና፡፡ አንድ መሪ ግሳዊ፣ ስማዊ፣ ቅፅላዊ፣ ወዘተ፣ መሆኑ የሚታወቀው፣ መሪው ግስ፣ ስም፣ ቅፅል፣ ወዘተ፣ ሲሆን እንደሆነ ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም ጥገኛ መሆኑ የሚታወቀው በጥገኝነት ምልክቱ ነው፡፡ ይህም ሞዩ ነው፡፡ ቀደም ሲል በየደረጃው ያየናቸው ሀረጎች፣ መሪያቸው የሚገኘው መሙሊያውን እየተከተለ በስተቀኝ በኩል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ሀረጎቹ በሙሉ ቀኝ መሪ ናቸው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት፣ በአረፍተ ነገር ደረጃም ቢሆን መሪው፣ ማለትም ሞዩ፣ የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ ሰስተቀኝ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ይህን በማለትም ቋንቋዋው በሀረግም ሆነ በአረፍተ ነገር ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የመሪ አገባብ እንዳለው ለማሳየት ይቻላል፡፡ ይኸውም ቋንቋዋው ቀኝ መሪ ነው፣ የሚል አጠቃላይ መግለጫ በመስጠት ነው፡፡

ሁለተኛው ማሰረጃ ትውረታዊ ብቻ ሳይሆን፣ ምክንያታዊ ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም እንደሚከተለው ያሉ ጥገኛ አረፍተ ነገሮች መኖር ነው፡፡

(ሀ) ካሳ ሰራ ይሰራ ዘንድ 7

(ለ) አስቴር ምሳዋን ትበላ ዘንድ

በቀደምት ሊቃውንት፣ እንደነዚህ ያሉ መዋቅሮች ዘንድ አንቀፅ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አንደኛ <u>ዘንድ</u> የሚለውን ቃል ማስከተላቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው እንዲፈፀምልን የምንሻውን ድርጊት የሚገልፁ መሆናቸው ነው፡፡ "....ይፈፀምልኝ ዘንድ በትህትና አመለከታለሁ፤" እንደምንለው ማለት ነው፡፡

ውስጣዊ ይዘታቸው፣ አረፍተ ነገራዊ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ ቅርፁ የመደበኛ ሳይሆን፣ የጥገኛ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ምልክቱ <u>ዘንድ</u> የሚለው ሞይ ነው፡፡ እሱም የሚገኘው ከአረፍተ ነገሩ በሰተቀኝ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት፣ በሌሎቹም ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሞዩ ቦታ እንደዚሁ በአረፍተ ነገሩ መድረሻ ላይ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡ ዘንድ እንደ /የ/ ጥገኛ ሳይሆን፣ ራሱን የቻለ ምዕላድ ነው፡፡ ስለሆነም ካጠገቡ ከሚገኘው ግሰ ወይም ስም ላይ መጠጋት አያስፈልገውም፡፡ እንደ /የ/ ያሉ ሞዮች የሚለጠፉበት ምክንያት አቅመ ቢስ ድሁር እናም ምርኩዝ ፈላጊ መሆናቸው ነው[1]፡፡

---

[1] በዚህ ጉዳይ ላይ ደምሴ (1977)ን ይመልከቱ፡፡ ምክንያቱ አቅመ-ቢስነት ላይሆን ይችላል፡፡ ወደ ውስብስብ ትውረት ስለሚወስደን ዝርዝር ውስጥ አንገባም፡፡

እንላማሽ፣ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከንዑሱ ሰማዊ ሀረግ ጋር ነው፡፡ ይህን እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡

3




ከዕፀ መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ ጥገኛው አረፍተ ነገር (አነ') የንዑሱ ሰማዊ ሀረግ ገላጭ ሆኖ ገብቶአል፡፡ አወራረዱ ከአቢዩ ሰማዊ ሀረግ ስሀ(2) እንጉዋ ላይ ነው፡፡ ይህ አይነተኛ የገላጭ ሀረጎች መዋቅራዊ ባህሪ ነው፡፡

አረፍተ ነገሩ (አነ) ከጥዩ ማስትም ከ(/የ/) ጋር ተዋቅሮ ስራውን ጥገኛ አረፍተ ነገር (አነ') መሰርቶአል፡፡ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ጥዩ በአረፍተ ነገሩ መድረሻ ላይ ይገኛል፡፡ አረፍተ ነገሩ ደግሞ፣ እንደ ማንኛውም ገላጭ

---

[3] በዚህ ምልክት (ᵢ) የሚጣቀሱ ሀረጎች አንድ አይነት ትርጉም ያላቸው ናቸው፡፡

አረፍተ ነገር፣ ከስማዊ ሀረግ ባለቤትና ከግሳዊ ሀረግ የተዋቀረ ነው። የግሳዊ ሀረጉ መሪ ሸጠ የሚለው ሳቢ ግስ ነው። ስለሆነም ተሳቢ ስማዊ ሀረግ አለው። ይሁን እንጅ፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም። ቦታው ግን በሰረዝ (--) የተመለከተው ነው። በግሱ መድረሻ ላይ ይህንኑ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ የሚጠቁም አፀፋ አለ። እሱም /-እ/ ነው። ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግን ያመለክታል። እንደዚህ ያለ ስማዊ ሀረግ ግን በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በግሀድ የለም። ስለዚህም ሸጠው የሚለው ግስ ተሳቢ ማነው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል።

ተሳቢው በግሀድ የማይታይ፣ ነገር ግን መደቡ፣ ቁጥሩና ፆታው የሚታወቅ ስማዊ ሀረግ ነው። ሊታወቅ የቻለውም በግሱ ላይ ከሚታየው /-እ/ ከሚለው አፀፋ ነው። ይህ አፀፋ በግሱ ላይ የግድ መታየት አለበት። ካልታየ የተሳቢው ስማዊ ሀረግ ይዘት ሊታወቅ አይችልም፣ እናም አረፍተ ነገሩ ተቀባይነት አይኖረውም። በሌላ አነጋገር፣

*[ካሳ የሸጠ] 4

ማለት አይቻልም።

ሌላው ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ፣ በአፀፋ የተጠቀሰ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ሁል ጊዜ በግሀድ አይታይም፣ ማለት ነው ወይ? የሚል ነው። በርግጥ እንደዚህ ያለ ሀረግ በግሀድ ሲታይም ላይታይም ይችላል። ወሳኙ ሀረጉ የሚገኝበት የመዋቅር አይነት ነው። መዋቅሩ ከፍ ሲል እንደሚታየው ያለ ጥገኛ አረፍተ ነገር ከሆነ፣ ሀረጉ በአፀፋ ይጠቆማል እንጅ፣ በግሀድ ሊታይ አይችልም። መዋቅሩ ቀደም ሲል እንዳየነው ያለ ስማዊ አረፍተ ነገር ወይም ከዚህ በታች እንደሚታየው ያለ መደበኛ (ጥገኛ ያልሆነ) ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ከሆነ፣ በግሀድ ሊታይ ይችላል። ስለዚህም በተሳቢ አፀፋ ላይጠቀስ ይችላል። የሚከተለውን እንመልከት።

ካሳ የብራና መፅሀፍ ሸጠ 5

እነሆ [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በግሀድ ይታያል። በግሱ ላይም እሱን የሚጠቁም አፀፋ የለም።

ከፍ ሲል በጥገኛ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኝ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በአፀፋ ሊጠቀስ እንጅ በግሀድ ሊከሰት እንደማይችል ገልፀናል። ከዚህም ላይ ለምን በግሀድ አይታይም? የሚል ጥያቄ አሁንም ይነሳ ይሆናል። ሀረጉ በግሀድ የማይታየው፣ በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛው ሀረጉ በአፀፋ በመጠቀሱና ከዚህም ይዘቱ የሚታወቅ በመሆኑ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ይኸው ሀረግ ከአረፍተ ነገሩ ጋር ከተዋቀረው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር በይዘት (ትርጉም) አንድ በመሆኑ ነው። ይህም ማለት፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግና [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ንዑስ ሀረግ የሚጠቁሙት አንድ ነገርን ነው። የማይታየው ተሳቢ ስማዊ ሀረግም [የብራና መፅሀፍ] የሚል ነው። ይህ ስማዊ ሀረግ በግሀድ ቢወጣ፣

*[[ካሳ የብራና መፅሀፍ የሸጠው] የብራና መፅሀፍ] 6

የሚል ይሆናል፡፡ [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ሀረግ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ በተሳቢነት፣ በስማዊ ሀረጉ ውስጥ ደግሞ በመሪነት ስለተከሰተ፣ ድግግሞሽን አስከትሎአል፡፡ ይህ አይነት ድግግሞሽም ከቋንቋዋ ባህሪ ጋር ይፃረራል፡፡ ቋንቋዋ አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽን ፈፅሞ አይፈቅድም፡፡ አዕምሮም እንደዚሁ፡፡ ለዚህ ነው፣ ሀረጉ ተቀባይነት የሌለው፡፡ ተቀባይነት እንዲኖረው፣ ከሁለቱ ተደጋጋሚ ስማዊ ሀረጎች አንደኛው የግድ በግሀድ እንዳይወጣ መታገድ ይኖርበታል፡፡ እንደዚህ የሚደረገው ደግሞ ማንኛውም ሳይሆን፣ በአፀፋ የሚጠቆመው ስማዊ ሀረግ ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ይዘቱ ከአፀፋው አይነት ይታወቃልና፡፡ [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ይዘት /-ኡ/ ከሚለው አፀፋ ስለሚታወቅ፣ በግሀድ እንዳይወጣ ታግዶአል፡፡

ተሳቢው ስማዊ ሀረግና [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ የትርጉም ብቻ ሳይሆን፣ የመዋቅርም ዝምድና አላቸው፡፡ ዝምድናውም ተሳቢውን ስማዊ ሀረግ የያዘው አረፍተ ነገር [የብራና መፅሀፍ] የሚለው ስማዊ ሀረግ አጎላማሽ ሆኖ መግባቱ ነው፡፡ በአጎላማሽነቱም [የብራና መፅሀፍ] የሚለውን ንዑስ ስማዊ ሀረግ በውስጡ ካለው ድብቅ ተሳቢ ጋር አዛምዶታል፡፡ የትኛው [የብራና መፅሀፍ] ብለን ብንጠይቅ፣ መልሱ [ካሳ የሸጠው] የሚል ይሆናል፡፡ ከዚህም ሁለቱን ስማዊ ሀረጎች የማዛመድ ተግባሩ የተነሳ፣ እንደ [ካሳ የሸጠው] ያለ መዋቅር አዛማጅ አረፍተ ነገር ይባላል፡፡

ይህ አይነቱ አረፍተ ነገር ቀደም ሲል ካየነው መሙሲያ አረፍተ ነገር የተለየ ነው፡፡ ልዩነቱ በሶስት ወገን ነው፡፡ በአንድ ወገን፣ ይኸኛው አረፍተ ነገር፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ግሳዊ ነው፡፡ በሌላ ወገን ደግሞ መዋቅራዊ ግንኙነቱ ከመሪው ስም ጋር ሳይሆን፣ ከንዑሱ ሀረግ ጋር ነው፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ በውስጡ ያለውን በአፀፋ ብቻ የተጠቆመ ድብቅ ስማዊ ሀረግ አብሮት ከተዋቀረው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር ስለሚያዛምድ፣ ገላጭና አዛማጅ ነው፤ መሙሊያ አይደለም፡፡

በአንድ አዛማጅ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘን ድብቅ ስማዊ ሀረግ ተዛማጅ እንለዋለን፡፡ የሚዛመደውም በአረፍተ ነገሩ ከሚጎላመሰው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ጋር ነው፡፡ ከላይ በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ፣ ተዛማጁ ስማዊ ሀረግ ተሳቢው ነው፡፡ ተዛማጅነት ግን የተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ የተለየ ባህሪ አይደለም፡፡ ባለቤት የሆነ ስማዊ ሀረግም ሊዛመድ ይችላል፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡

[--- አስቴርን የስደቡአት (/ስደብ-ኡ-አት/) ልጆች] 7

ይህም፣ ቀደም ሲል በተራ ቁጥር (1) እንዳየነው መዋቅር፣ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ መሪው <u>ልጆች</u> የሚለው ስም ሲሆን፣ አጎላማሹ፣

[--- አስቴርን የስደቡአት (/ሰደብ-ኡ-አት/)] 8

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ አረፍተ ነገሩ <u>አስቴርን የሰደቡአት</u> የሚል ግሳዊ ሀረግና በግሀድ የማይታይ ባለቤት ስማዊ ሀረግ አለው፡፡ ከግሱ ላይ ከሚታየው /-ኡ/ ከሚለው አፀፋ፣ ባለቤቱ ሶስተኛ መደብና የብዙ ቁጥር መሆኑን ለማወቅ ይቻላል፡፡ አዛማጁ አረፍተ ነገር ይህን ድብቅ ባለቤት ስማዊ ሀረግ <u>ልጆቹ</u> ከሚለው ከዋናው ስማዊ ሀረግ መሪ ስም ጋር አዛምዶታል፡፡ ስላዛመደውም ሀረጉ በግሀድ ከመታየት ታግዶአል፡፡ በግሀድ ቢታይ ኖሮ፣ መዋቅሩ [ልጆች አስቴርን የሰደቡአት (/ሰደብ-ኡ-አት/) ልጆች] የሚል ይሆን ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም አስፈላጊ ያልሆነ ድግግሞሽ ያሳያልና፡፡ የአዛማጁን አረፍተ ነገርና የስማዊ ሀረጉን መዋቅራዊ ተዛምዶ አሁንም በዕፀ መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

9




ከዕፀ-መዋቅሩ እንደሚታየው፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም፡፡ ቦታው በሰረዝ የተመለከተው ነው፡፡ ክፍት የሆነበት ምክንያት ሀረጉ /-ኡ/ በሚለው አፀፋ ስለተጠቀሰና <u>ልጆቹ</u> ከሚለው መሪ ስም ጋር

በትርጉም አንድ ሆኖ ስለተዛመደ ነው፡፡ ያዘግመዱም ሁኔታ ከፍ ሲልካየነው የተሳቢ ስማዊ ሀረግ አዘግመድ ጋር አንድ ነው፡፡

አስካሁን ያየነው የአንድ አዛግጅ እረፍተ ነገር ባለቤት ወይም ተሳቢ፣ በአረፍተ ነገሩ ከሚጎላመሰው ስማዊ ሀረግ ጋር የሚፈጥረውን መዋቅራዊ ዝምድና ነው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ የተዛማጅ መስተዋድዳዊ ሀረግን ሁኔታ እንመለከታለን፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡

[[ልጆቹ የሄዱበት] ሀገር] 10

ይህ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ መሪው ሀገር የሚለው ስም ነው፡፡ አጎላማሹ፣

[ልጆቹ የሄዱበት] 11

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የዚህን አረፍተ ነገር ግስ ስንመለከት፣ /-ኡ/ እና /-በት/ የሚሉትን ቅጣዮች እንዳስከተለ እንረዳለን፡፡ የመጀመሪያው ቅጣይ፣ ልጆቹ የሚለውን የብዙ ቁጥር ባለቤት የሚጠቁም፣ የብዙ ቁጥር አፀፋ ነው፡፡ ሁለተኛውስ? ሁለተኛው የሚጠቁመው አንድ በግሀድ የማይታይን መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው፡፡ ሀረጉ መስተዋድዳዊ ለመሆኑ ከግሱ ባህሪ ማወቅ ይቻላል፡፡ ሄደ የሚለው ግስ መድረሻ መስተዋድዳዊ ሀረግን በመሙሊያነት ይፈልጋል፡፡ የእንደዚህ አይነት መስተዋድዳዊ ሀረግ መሪም ወደ ነው፡፡ ሀረጉ በግሀድ የማይታይበት ምክንያት፣ የተዛመደው ሀረግ እሱ ራሱ በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግ በአፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ አፀፋውም /-በት/ ነው፡፡ ይህ አፀፋ ግን ተራ ሳይሆን ውስብስብ ነው፡፡ የ/በ/ እና የ/ት/ ቅንጅት ነው፡፡ /በ/ ወደ የሚለውን መስተዋድድ ሲወክል፣ /ት/ ከመስተዋድዱ ጋር የተዋቀረውን ስማዊ ሀረግ ትወክላለች፡፡ /-በት/ የሚለውን ውስብስብ የመስተዋድድ አፀፋ ልንለው እንችላለን፡፡ ውስብስብ ወይም ድርብ አፀፋዎችን ካሁን ቀደምም እንዳየን ያስታውሱ፡፡ ለምሳሌ፣ በስማዊ እረፍተ ነገር ውስጥ [-ዋ] የ/ኡ/ እና የ/ኣ/ ውሁድ፣ በግሳዊ እረፍተ ነገር ውስጥም [-ች] የ/-ት/ እና የ/-እ/ ውሁድ እንደሆነች አይተናል፡፡ ከዚህ ላይ የሚታየው /በት/ የሚለው አፀፋ አካሄድም እንደዚሁ ነው፡፡ የመዋቅሩን ተዛምዶ በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናመለክታለን፡፡

12




እነሆ፡ የግሱ መሙሊያ የሆነው መስተዋድዳዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (—) ነው፡፡ ክፍት የሆነበት ምክንያትም ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ሀገር ከሚለው ከስማዊ ሀረጉ መሪ ጋር በአረፍተ ነገሩ አማካኝነት ስለተዛመደና እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግም በአፀፋ ስለተጠቀሰ ነው፡፡ ሀገር የሚለው ስም፣ ሄዱ በሚለው ግስ ለተጠቀሰው ተግባር መድረሻ ነው፡፡ ልጆቹ ሄደው የሚደርሱበትን ቦታ ያመለክታልና፡፡ እንደዚህ ያለ ተግባር ያለው ሀረግ የሚዋቀረው፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ወደ ለሚለው መስተዋድድ መሙሊያ በመሆን ነው፡፡ ከዚህ ስንነሳ፣ በዕፀ መዋቅሩ ላይ ክፍት (-) የሆነው መስተዋድዳዊ ሀረግ ይዘት ወደ ሀገር የሚል ነው፡፡ ይህም የሚታወቀው /-በት/ ከሚለው ድርብ አፀፋ ነው፡፡ አፀፋው የሚያጣቅሰው ይህንኑ ሀረግ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፣ በሀረጉ ውስጥ ባለው መስተዋድድና በአፀፋው መስተዋድድ መካከል የቅርፅ ልዩነት አለ፡፡ በሀረጉ ውስጥ መስተዋድዱ ወደ የሚለው ሲሆን፣ በአፀፋው ላይ የሚታየው /-በ/ ሆኖ ነው፡፡

ሁኔታው በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ ለምሳሌ፣ ሀገር የሚለው መሪ ስም መድረሻ ሳይሆን፣ መነሻ ወይም መኖሪያ ቢሆን፣ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ

የሚጠቀሰው በተለየ ሳይሆን፣ በዚሁ /በ/ በሚለው አፀፋ ብቻ ነው። ልጆቹ የመጡበት፣ የደረሱበት፣ የሚኖሩበት፣ ወዘተ፣ ሀገር፤ ወይም ልጆቹ የበሉበት መሶብ፣ የጠጡበት ዋንጫ፣ ወዘተ፣ ብንል፣ የየሀረጉ መስተዋድድ ቅርፅ ይለያያል እንጅ፣ አፀፋው አይለወጥም። አፀፋው የተለየ የሚሆነው መስተዋድዳዊ ሀረጉ ለአንድ ድርጊት ተጠቃሚ መሆንን የሚያሳይ ሲሆን ነው። የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው።

አስቴር ለካሳ ገንዘብ ላከችለት 13

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣ ለካሳ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ በግሱ የተገለፀው ድርጊት ፈፃሚ ሳይሆን፣ ተጠቃሚ ነው። ስለዚህም በግሱ ላይ መስተዋድዳዊው ሀረግ /-ለት/ በሚል አፀፋ ተጠቅሶአል። ይህንኑ አረፍተ ነገር ወደ ስማዊ ሀረግ ብንለውጠው፣ በስማዊ ሀረጉ ውስጥ፣ መስተዋድዳዊው ሀረግ የሚጠቆመው በዚሁ /-ለት/ በሚለው አፀፋ ይሆናል። ይህም እንደሚከተለው ነው።

[[አስቴር ገንዘብ የላከች-ለት] ሰው] 14

ከላይ በሚታየው አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ የሚታየው፣ ለካሳ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ፣ በዚህ ስማዊ ሀረግ ውስጥ አይታይም። የማይታየውም ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ የተዛመደው ሀረግ እሱ ስለሆነና እንደ ማንኛውም ተዛማጅ ሀረግም በግሱ ላይ ብቻ በአፀፋ ስለተጠቀሰ ነው። አፀፋውም በግልፅ እንደሚታየው፣ /-ለት/ ነው። ባጭሩ፣ ስለ መስተዋድዳዊ ሀረግ የአፀፋ ስርዓት የሚከተለውን ማለት ይቻላል። ተጠቃሚነትን ከሚያሳይ መስተዋድዳዊ ሀረግ በስተቀር፣ ማንኛውም መስተዋድዳዊ ሀረግ በተዛማጅነት ሲገባ፣ የሚጠቀሰው /በ/ በሚለው መስተዋድድ ነው። በሌላ አነጋገር፣ /-በ/ እና /-ለ/ መስተዋድዳዊ አፀፋዎች ናቸው፣ /-በ/ ለማንኛውም መስተዋድድ፣ /-ለ/ ተጠቃሚን ለሚያሳይ መስተዋድድ ብቻ።

እስካሁን ድረስ ያየናቸው ተዛማጅ ሀረጎች በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ናቸው። የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ የግሱ ተሳቢ ወይም እንላማሽ የሆኑ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው። ከዚህ ቀጥለን ደግሞ በስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ስማዊ ሀረግ እንዴት እንደሚዛመድ እንመለከታለን። ለዚህ የሚከተለውን እንይ።

[[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-እት] ልጅ] 15

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣

[አስቴር ፀጉርዋን የሰራች-እት] 16

የሚለው ክፍል፣ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ባለቤቱ አስቴር የሚለው አንስታይ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ስለሆነም በግሱ ላይ /-ች/ በሚለው የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አንስታይ ፆታ ምዕላድ ተጠቁሞአል፡፡ የግሱ ተሳቢ ፀጉርዋን የሚለው ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ እሱም እንደዚሁ በግሱ ላይ /-አት/ በሚል አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ባለቤትም ሆነ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ በግሀድ በቦታቸው አሉ፣ ማለት ነው፡፡ ከዚህ ላይ ታዲያ፣ ልጅ ከሚለው መሪ ስም ጋር የተዛመደው ስማዊ ሀረግ የትኛው ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ የተዛመደው ስማዊ ሀረግ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ወይም የግሱ ተሳቢ ሊሆን አይችልም፡፡ እነዚሀ በግሀድ ይታያሉና፡፡ ስለዚህም ተዛማጁ ሀረግ ከነዚሀ ውጭ የሆነና በአፀፋም የተጠቆመ መሆን አለበት፡፡ ከባለቤትና ከተሳቢ አፀፋ ሌላ፣ በግሱ ላይ የሚታይ ምንም አፀፋ የለም፡፡ በተሳቢው ስማዊ ሀረግ መድረሻ ላይ ግን [-ዋ] </-ኡ-አ/ የምትል ድርብ አፀፋ አለች፡፡ ይህች አፀፋ የምትጠቁመው ገንዛቢ (ባለገንዘብ) ስማዊ ሀረግን ነው፡፡ የዚህ አይነት ስማዊ ሀረግ በተሳቢው ስማዊ ሀረግ ውስጥ በድብቅ አለ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አረፍተ ነገሩ ሲተረጎም፣

አስቴር ልጅትዋን ፀጉርዋን ሰራቻት 17

የሚል ይሆናል፡፡

የተዛመደውም ይህ ልጅትዋን የሚለው ገንዛቢ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ከዚህ ሀረግ ጋር የተገናዘበው ደግሞ ፀጉር የሚለው ተሳቢ ስማዊ ሀረግ መሪ ሲሆን፣ ሁለቱን ስሞች፣ ማለትም አስቴር እና ፀጉር የሚሉትን፣ የሚያገናዝበው (የሚያገናኘው) ምዕላድ /-ዋ/ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ልጅትዋን የሚለውን ስም ገንዛቢ፣ ፀጉርዋን የሚለውን ተገናዛቢ፣ እንዲሁም /-ዋ/ን አገናዛቢ የባለቤት አፀፋ ወይም ዘርፍ እንላታለን፡፡ አገናዛቢዋ ምዕላድ የገንዛቢው ሀረግ አፀፋ ነች፡፡ የምትታየውም በተገናዛቢው ስም መድረሻ ላይ ነው፡፡ የባለቤት አፀፋ በመሪ ግስ ላይ እንደሚታይ ሁሉ፣ የገንዛቢ አፀፋም በመሪ ስም ላይ ይታያል፣ ማለት ነው፡፡ ሲጠቃለል፣ አፀፋዎች የሚታዩት በመሪ ላይ ነው፣ ለማለት ይቻላል፡፡

ከላይ በሚታየው ምሳሌ ውስጥ፣ የተዛመደው ስማዊ ሀረግ ልጅትዋ የሚለው ገንዛቢ ስም ነው፡፡ ይህ ውነት ስመሆኑ ማስረጃው /-ዋ/ በሚለው ምዕላድ መጠቀሱና በግሀድ አለመታየቱ ነው፡፡ በአዛማጅ አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ አለመታየትና በአፀፋ መጠቀስ የተዛማጅ ስማዊ ሀረግ ምልክት ነው፣ ብለናል፡፡ ከዚህ አንፃር፣

[[አሰቴር ፀጉርዋን የሰራች-አት] ልጅ] 18

የሚለው ስማዊ ሀረግ ውስጣዊ ቅንጅት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

19




ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ የተሳቢው ስማዊ ሀረግ መሪ <u>ፀጉርዋን</u> የሚለው ተገናዛቢ ስም ነው። የዚህ ስም ገንዛቢ ስማዊ ሀረግ ደግሞ (ስሀᵢ)ነው። የተዛመደውም እሱው ነው። ስለተዛመደም ፀጉርዋን በሚለው መሪ ስም ላይ ስእፀፋ ተጠቅሶአል። ከአፀፋው ሶስተኛ መደብ፣ እንስታይ ፆታ፣ ነጠላ ቁጥርና ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል።

እስካሁን በዚህ ክፍል ውስጥ ያየነውን እንደሚከተለው እናጠቃልላለን፡፡ ለማየት የተነሳነው ውስብስብ ስማዊ ሀረጎችን ነው፡፡ ሀረጎቹ ውስብስብ የሆኑበት ምክንያት አረፍተ ነገራዊ ከሆኑ መሙሊያዎች ወይም ገላጮች ጋር ስለሚዋቀሩ ነው፡፡ መሙሊያዎቹ ስማዊ አረፍተ ነገሮች ሲሆኑ፣ ገላጮቹ አዛምጅ ግሳዊ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ አረፍተ ነገሮቹ የመሪው ስም መሙሊያ ወይም ገላጭ ሆነው በጥገኝነት መግባታቸውን የሚያመለክት /የ/ የሚል ምዕላድ አላቸው፡፡ ይህም ጥይ ያልነው አሀድ ነው፡፡ መዋቅራዊ ዝምድናው ከአረፍተ ነገሩ ጋር ሲሆን፣ አገባቡም አረፍተ ነገሩን ተከትሎ በስተቀኝ በኩል ነው፡፡

የስማዊ መሙሊያ አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ሲከሰት ወይም ላይከሰት ይችላል፡፡ የሚከሰተው፣ እንድም በመሪው ስም ላይ አፀፋው ሲታይ፣ አለያም /የ/ የምትለዋን ምዕላድ ሲያስቀድም ብቻ ነው፡፡

አዛማጅ አረፍተ ነገር ባለቤቱን፣ ወይም ተሳቢውን ወይም መስተዋድዳዊ ሀረጉን ከሚያነሳምሰው ስም ጋር ያዛምዳል፡፡ የሚዛመደው ስማዊ ሀረግ በግሀድ አይታይም፡፡ በአፀፋ ግን እንደተለመደው ይጠቀሳል፡፡ አፀፋው የሚታየው በግሱ ላይ ነው፡፡ ከአፀፋው አይነት በግሀድ የማይታየውን ተዛማጅ ስም ይዘት ማወቅ ይቻላል፡፡ ባለቤት ወይም ተሳቢ በሆነ ስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ገንዛቢ ስማዊ ሀረግም እንደዚሁ በአፀፋ ሊዛመድ ይችላል፡፡ ሲዛመድም በግሀድ አይከሰትም፡፡ እንደ ማንኛውም ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ አፀፋው በመሪው ላይ ስለሚታይ ይዘቱ ከዚያው ይታወቃል፡፡

ውስብስብ ስማዊ ሀረግ በባለቤትነት ወይም በተሳቢነት ወይም በገላጭነት ሊገባ ይችላል፡፡ እንደዚህ ያለ ውስብስብ ሀረግን የያዘ አረፍተ ነገርም ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ውስብስብ ይባላል፡፡ ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) [[የአስቴር ቤት የመስራት አላማ] [ከሸፈ] ] 20

(ለ) [እኔ [[የአስቴርን ቤት የመስራት አላማ] እደግፋለሁ] ]

የመጀመሪያው ምሳሌ [የአስቴር ቤት የመስራት አላማ] የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ባለቤት የሆነበትና <u>ከሸፈ</u> ከሚለው ግስ ጋር ውስብስብ አረፍተ ነገር ያዋቀረበት ነው፡፡ ሁለተኛው፣ ይኸው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ <u>እደግፋለሁ</u> ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ፣ ብሎም ተሳቢ ሆኖ የገባበት ውስብስብ አረፍተ ነገር ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉት በውስብስብ ስማዊ ሀረጎች ምክንያት ውስብስብ የሆኑ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ ውስጣዊ ቅንጅታቸውን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡




ከዚህ ቀጥለን ደግሞ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችንና በነሱ ምክንያት ውስብስብ የሚሆኑ አረፍተ ነገሮችን የአወቃቀር ስርዓት እንመለከታለን፡፡

## ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ

ባለፈው ክፍል ስለ ግሳዊ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ አንድ ግስ ከተራ ሀረጋዊ መሙሊያ፣ አጎላማሽ እና መስተዓምር ጋር እየተዋቀረ ተራ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርት ይችላል፡፡ ከዚህ አይነት ሀረግ የሚዋቀር አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ተራ ነው፡፡ ይህ ግን የሁሉም ግሶች ባህሪ አይደለም፡፡ አንዳንድ ግሶች ከተራ ሳይሆን፣ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ሊዋቀሩ ይችላሉ[4]፡፡ በዚህም መሰረት ግሶች

[4] ስለ መሙሊያ አረፍተ ነገሮች ደምሴ (1977)ን ይመልከቱ፡፡

ይለያያሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚፈጠረው መዋቅር ውስብስብ ወይም ተራ ግሳዊ ሀረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

[[ካሳ አስቴር ወደ ጎንደር እንደሄደች] [አውቆአል]] 1

በዚህ ምሳሌ ውስጥ፣

[አስቴር ወደ ጎንደር እንደ ሄደች] 2

የሚለው መዋቅር አረፍተ ነገራዊ ነው፡፡ አገባቡም <u>አውቆአል</u> ለሚለው ሳቢ ግስ መሙሊያ ሆኖ ነው፡፡ ግሱ ከዚህ አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር ሲቀናጅ የሚፈጥረው ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ እወቃቀር የሚከተለውን ይመስላል፡፡




3

ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ አስቴር ወደ ጎንደር እንደሄደች የሚለው አረፍተ ነገር አውቀአለ ለሚለው ላቢ ግስ መሙሊያ ሆኖ ገብቶአል፡፡ መሙሊያው አረፍተ ነገር እንደ የሚለው መስተዋድድና አስቴር ወደ ጎንደር ሄደች የሚለው አረፍተ ነገር ቅንጅት ነው፡፡ መስተዋድዱ፣ አረፍተ ነገሩ በንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ውስጥ፣ የግሱ መሙሊያ ሆኖ በጥገኝነት የገባ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ቀደም ሲል ስለ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ በመሙሊያነት ወይም በአጎላማሽነት የሚገባ አረፍተ ነገር /የ/ በሚል ምዕላድ እንደሚታወቅ ገልፀን ነበር፡፡ አሁንም በዚህ ምሳሌ ውስጥ የምናየው ሁኔታ ይኸው ነው፡፡ እንደ የሚለው መስተዋድድ፣

አስቴር ወደ ጎንደር ሄደች 4

የሚለው አረፍተ ነገር በጥይነት መግባቱን ያመለክታል፡፡ አገባቡም እንደ ማንኛውም የዚህ አይነት ምዕላድ፣ አረፍተ ነገሩን ተከትሎ ነው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ጥገኝነትን የሚያመለክቱ ምዕላዶች ጥይ እንደሚባሉ፣ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ በቀደምት ሊቃውንት ዘንድ ጥገኛ መስተፃምር ይባሉ እንደነበርም በክፍል ሁለት ስለ ቃላት ክፍል ስንወያይ ጠቅሰናል፡፡ መስተፃምር የሚያሰኛቸው ከአረፍተ ነገር ጋር መግባታቸው ብቻ ነው፡፡ በሌላው ባህሪያቸው ከመስተዋድድ እንደማይለዩ ገልፀናል፡፡

በስማዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ጥገኛ አረፍተ ነገር /የ/ በሚል ጥይ ሲታወቅ፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገኝ ተመሳሳይ አረፍተ ነገር ግን እንደ በሚል መስተዋድዳዊ ጥይ ይለያል፡፡ ሁኔታው ግን በዚህ ብቻ አያቆምም፡፡ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ አንዳንድ መሙሊያ አረፍተ ነገሮችም /የ/ በሚለው ጥይ ሊታወቁ ይችላሉ፡፡ የሚከተለው የዚህ ምሳሌ ነው፡፡

[[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደች] ይመስላል] 5

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣

[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደች] 6

የሚለው ጥገኛ አረፍተ ነገር ይመስላል የሚለው ግስ መሙሊያ ነው፡፡ ስለሆነም በግሱ ላይ /የ/ የምትለዋን ምዕላድ አስቀድሞአል፡፡ ይህችም ጥይ ምዕላድ ስትሆን፣ ታህታይ ቦታዋ ከአረፍተ ነገሩ በስተቀኝ ነው፡፡ ይህንንም ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡




7

የአረፍተ ነገሩን ውስጣዊ ቅንጅት ከፍ ብለን ያየነው ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ አንደግመውም፡፡ ከእሱ ይልቅ ይመስላል ስለሚለው ግስ መዋቅራዊ ባህሪ ጥቂት ገለፃ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ግስ ከአረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ጋር ንዑስ ግሳዊ ሀረጉን ይመሰርታል፡፡ እንደዚሁም ከገላጭ አረፍተ ነገር ጋር ሆኖ እቢይ ግሳዊ ሀረጉን ይመሰርታል፡፡ ይሁን እንጅ ባለቤት የለውም፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ፣ የባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ቦታ ክፍት (-) ይሆናል፡፡ በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ግን ቦታው አንድም ክፍት እንደሆነ ይቀራል፣ አለያም በመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ይሸፈናል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን አያነፃፀርን እንመልከት፡፡

(ሀ) [---[ልጆቹ [ስራ የሚሰሩ] ] ይመስላል] 8
(ለ) [ልጆቹ [---[ስራ የሚሰሩ] ] ይመስላሉ]

በምሳሌ (ሀ) [ስራ የሚሰሩ] የሚለው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ልጆቹ የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ይህን የሚሰሩ ከሚለው ግስ መድረሻ ላይ ከሚታየው /-ኡ/ ከሚለው የብዙ ቁጥር አፀፋ ማወቅ ይቻላል፡፡ ይመስላል የሚለው የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ፣ የባለቤት ቦታ በነጠብጣብ የተሸፈነው ነው፡፡ ከግሱ መነሻ ላይ /ይ-/ የሚል ምዕላድ ይታያል፡፡ ይህም ስስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነን ባለቤት ይጠቁማል፡፡ ይህም የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት መሆን አለበት፡፡ የታቃፊው አረፍተ ነገር ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት ልጆቹ የሚለው የብዙ ቁጥር ስም ነው፤

ብለናልና፡፡ ሁለተኛም <u>ይመስላል</u> የሚለው ግስ ባለቤት እንደሌለው ከፍ ሲል ገልፀናል፡፡

ይህ ውነት ከሆነ፣ /ይ-/ በሚለው ምዕላድ የሚጠቀሰው የእቃፌው አረፍተ ነገር ባለቤት ማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ አንድ ግስ በታህታይ መዋቅር ባለቤት የለውም ሲባል፣ ድርጊት ፈፃሚ ወይም ሁዋኝ ባለቤት አይኖረውም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅር፣ የእንደዚህ አይነት ግስ የባለቤት ቦታ ክፍት ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፡ ማንኛውም አረፍተ ነገር በላዕላይ መዋቅር የግድ ባለቤት ማግኘት አለበት፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም አረፍተ ነገር በይዘቱ ብቻ ሳይሆን፣ በቅርፁም የተሟላ መሆን ስላለበት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በታህታይ መዋቅር ውስጥ ባለቤት የሌለው አረፍተ ነገር ሙሉ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ሙሉ እንዲሆን ከፈለግን፣ አድራጊም ሆነ ሁዋኝ ያልሆነ፣ ግን በባለቤት ቦታ ሊገኝ የሚችል፣ የይስሙላ ባለቤት (ለስም ብቻ የገባ) በላዕላይ መዋቅር ማስገባት አለብን፡፡ ይህም የይስሙላ ባለቤት በሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር አፀፋ፣ ማለትም በ/ይ-/ ብቻ ይጠቀሳል፡፡ በግሀድ ግን አይወጣም፡፡ ቋንቋዋው የዚህ አይነት ግሀድ ባለቤት የለውምና፡፡

እንደ እንግሊዝኛ ባሉ የውጭ ቋንቋዎች፣ እንደዚህ ያለ የይስሙላ ባለቤት የሚሆን ተውላጠ ስም አለ፡፡ እሱም it ወይም there ነው፡፡ ይህ ተውላጠ ስም ደግሞ በአፀፋ አይጠቀስም፣ ምክንያቱም ቋንቋዋው የአፀፋ ምዕላድ የለውም፡፡ በሀገራችን ቋንቋዎች ደግሞ እንደነዚህ ያሉ የይስሙላ ባለቤቶች፣ እንደ it ወይም there በነፃ ተውላጠ ስም መልክ አይከሰቱም፡፡ የሚከሰቱት /ይ-/ በሚለው አፀፋ ምዕላድ ብቻ ነው፡፡ በአጭሩ፣ እንደ አማርኛ ባሉ የሀገራችን ቋንቋዎች it እና there መደበኛ ተውላጠ ስማዊ ቅርፅ የላቸውም፡፡ እንደ እንግሊዝኛ ባሉ የውጭ ቋንቋዎች ደግሞ፣ መደበኛ ቅርፅ አላቸው፣ በአፀፋ ግን አይጠቀሱም፡፡

በምሳሌ (ሀ) ውስጥ <u>ይመስላል</u> የነበረው ግስ፣ በምሳሌ (ለ) ውስጥ <u>ይመስላሉ</u> የሚል ሆኗል፡፡ የብዙ ቁጥር፣ የባለቤት ስማዊ ሀረግ አፀፋ የሆነውን /-ኡ/ን ያሳያል ማለት ነው፡፡ ይህም የእቃፌው አረፍተ ነገር ባለቤት <u>ልጆቹ</u> የሚለው የብዙ ቁጥር ስማዊ ሀረግ መሆኑን ያሳያል፡፡ <u>የሚበሩ</u> በሚለው ግስ መድረሻ ላይም ሀረጉ በዚሁ /-ኡ/ በሚለው አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ስለዚህም ባለቤትነቱ ለእቃፌውም <u>ለዕቅፉም</u> አረፍተ ነገር ነው፡፡ ለእቃፌው አረፍተ ነገር ባለቤት ለመሆን፣ በምሳሌ (ሀ) ከሚታይበት ታህታይ ቦታው ተነስቶ፣ ክፍት ወደሆነው ወደ እቃፌው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ መሄድ አለበት፡፡ በዚያ ሆኖ የእቃፌውም ሆነ የዕቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት ሊሆን ይችላል[5]፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው እንደ <u>ይመስላል</u> ያሉ ግሶች በመሰረቱ በባህሪያቸው ባለቤት-የለሽ በመሆናቸው ነው፡፡

ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ደግሞ እንመልከት፡፡

[5] ስለዚህ ጉዳይ ዝርዝር ሁኔታ ባየ (1988፣ 1994)ን ይመልከቱ፡፡

እንችላለን፡፡ ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ እንዴት እንደሚመሰርት በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡




በግልፅ እንደሚታየው፣ ገላጩ አረፍተ ነገር (እነ') ከንዑሱ ግሳዊ ሀረግ (ግሀ1) ጋር ተዋቅሮ አቢዩን ግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) መሰርቶአል፡፡ የአረፍተ ነገሩ አወራረድም ከዚሁ ሀረግ እንጉዋ ላይ ነው፡፡ ይህ የማንኛውም ገላጭ መዋቅር ባህሪ እንደሆነ በክፍል ሁለት ስለ ሀረግ ስንወያይ ተገንዝበናል፡፡ የአረፍተ ነገሩ ሞይ <u>እንደ</u> የሚለው ምዕላድ ሲሆን፣ እሱም እንደማንኛውም ሞይ አረፍተ ነገሩን ተከትሎ በስተቀኝ በኩል ገብቶአል፡፡

በሁለተኛው ምሳሌ (10ለ) ውስጥ ያለው መዋቅራዊ ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ <u>ተደሰተ</u> የሚለው ግስ ኢሳቢ ነው፡፡ ስለዚህም ተሳቢ የለውም፡፡ ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ የሚመሰርተው ብቻውን በመቆም ነው፡፡ ይህን ንዑስ ሀረግ የሚገልፀው፣

[አስቴር ወደ ትምህርት ቤት ስለሄደች] 13

የሚለው ገላጭ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የሚገልፀውም የደስታውን ምክንያት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገር የምክንያት ተውሳከ ግስ ይባላል፡፡ ከንዑሱ ሀረግ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ግንኙነት እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡

ከስዋሰው ህግጋት አንፃር ሲታይ፣ ይህ መዋቅር ተቀባይነት አለው፡፡ ከትርጉም አንፃር ግን ተቀባይነት የለውም፡፡ ምክንያቱም የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤትና ይፈልጋል በሚለው ግስ የሚመራው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት የሚጠቁሙት አንድን ሰው በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ ከመከሰት ይታቀባል፡፡ ማንነቱ ከእናቱ (ከአቃፊው) አረፍተ ነገር ባለቤት ይዘት ይታወቃል፡፡

[ወደ ጎንደር ለመሄድ] በሚለው ውስጥ የምትታየው /ለ/ መስተዋድዳዊ ሞይ ነች፡፡ አገባብዋም እንደማንኛውም ሞይ መሙሊያውን አረፍተ ነገር ተከትሎ ነው፡፡ የሁሉንም ስማዊ አረፍተ ነገሮችና የግሱን መዋቅራዊ ግንኙነት አጠቃለን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡




19

ይህ የኢውሱኑ መሙሊያ አረፍተ ነገርና፣ ይፈልጋል የሚለው ሳቢ ግስ መዋቅራዊ ግንኙነት ነው፡፡ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ አይታይም፡፡ ቦታው በሰረዝ የተመለከተው ነው፡፡ መሄድ የሚለው መሪ ስም የባለቤት አፀፋ በሚያሳይበት ጊዜ፣ ባለቤቱ በሰረዝ በተመለከተው ቦታው ላይ በግሀድ ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ ሞዩ አይታይም፡፡ የሚታየው የተሳቢ ምልክት የሆነው /-ን/ የሚለው ምዕላድ ነው፡፡ ይህ ምዕላድ ውሱን ከሆኑ ተሳቢ ሀረጎች ጋር ቁርኝት ስላለው፣ እሱ ይከሰትና ሞዩ ከቦታው ይጠፋል[7]፡፡ ይህም የሚሆነው በላዕላይ መዋቅር ነው፡፡ ቁዋንቁዋው ሁለቱ ምዕላዶች በላዕላይ መዋቅር ተከታትለው እንዲመጡ የሚፈቅድ አይመስልም[8]፡፡

ከሰማዊም ይሁን ከግሳዊ መሙሊያ አረፍተ ነገሮችና ከግስ የሚመሰረቱ ንዑስ ሀረጎች ከተለያዩ አጎላማሽ አረፍተ ነገሮች ጋር በመዋቀር አቢይ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡ ለዚህ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

]አስቴር ][ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] [[ካሳ መምጣቱን] ሰማች]]] 20

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ሰማች የሚለው ሳቢ ግስ፣ [ካሳ መምጣቱን] ከሚለው ስማዊ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ፣ [ካሳ መምጣቱን ሰማች] የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ መሙሊያው ስማዊ አረፍተ ነገር አፀፋ ስላለው ውሱን ነው፡፡ ስለዚህም ባለቤቱ ካሳ በግሀድ ሊከሰት ችሉአል፡፡ ይህ ንዑስ ግሳዊ ሀረግ ደግሞ በተራው፣

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] 21

ከሚለው ግሳዊ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ፣

---

[7] ከዚህ ላይ /-ን/ የተሳቢ ምዕላድ ሳይሆን፣ ሞይ መስተዋድድ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡ /-ን/ በመስተዋድድነት ሲገባ ቀደም ብለን አይተናል፡፡ እንደ ከሚለው ሞይ ጋር ተከታትሎ የማይመጣውም ለዚሁ ነው፡፡ የአንድን አረፍተ ነገር ጥገኛ መሆን ለማሳየት ሁለት ሞይ አያስፈልግም፡፡

[8] ይህ ገደብ በሌሎች ምዕላዶችም ይታያል፡፡ ለምሳሌ /የ/ የሚለው አገናዛቢ ምዕላድ ከማንኛውም መስተዋድድ በሁዋላ ሲገባ፣ በግሀድ አይታይም፡፡ ስለዚህም ለምሳሌ፡ የ-ካሳ ልጅ የሚለው አገናዛቢ ስማዊ ሀረግ፣ ]ለካሳ ልጅ]፣ [ወደ ካሳ ልጅ]፣ [እንደ ካሳ ልጅ]፣ ወዘተ፣ ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት ቀደምት ሊቃውንት ውስጠ-የ እና ግልፀ-የ የሚል አጠራር ነበራቸው፡፡ የካሳ ልጅ በሚለው መነሻ ላይ የሚታየው /የ/ ግልፀ-የ ሲሆን፣ ከየመስተዋድዱ ቀጥሎ የሚመጣውና በግሀድ የማይታየው /የ-/ ውስጠ-የ ነው፡፡

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደ ሄዱ ካሳ መምጣቱን ሰማች] 22

የሚለውን አቢይ ግሳዊ ሀረግ መሰርቶአል፡፡ [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ] የሚለው ገላጭ አረፍተ ነገር ነው፡፡ የሚገልፀው ንዑሱን ግሳዊ ሀረግ ነው፡፡ አገላለፁም ካሳ የመጣበትን ጊዜ በመጥቀስ ነው፡፡ ስለዚህም አረፍተ ነገራዊ የጊዜ ተውሳከ ግስ ልንለው እንችላለን፡፡ ከፍ ሲል እንደተጠቀሰው አረፍተ ነገሩ ግሳዊ ነው፡፡ ስማዊ አቻው፣

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው] 23

የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጅ አገባቡ አሁንም በገላጭነት ነው፡፡ ሲገባም ከላይ በተራ ቁጥር (20) የተገለፀው ምሳሌ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ከመሄዳቸው ካሳ መምጣቱን ሰማች] 24

በግልፅ እንደሚታየው፣ መሙሊያውም ሆነ ገላጩ አረፍተ ነገር ስማዊ ነው፡፡ ይሁን እንጅ፤ ሁለቱም ግሳዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን፣ መዋቅሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

(ሀ) [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ካሳ እንደመጣ ሰማች] 25
(ለ) ?[ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ ካሳ እንደመጣ ሰማች]

የምሳሌ (ለ) ተቀባይነት ትንሽ አጠራጣሪ ሊመስል ይችላል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የገላጩና የመሙሊያው አረፍተ ነገር ሞይ አንድ አይነት ቃል መሆኑ ነው፡፡ ከትርጉም አኩዋያ ሲታዩ፣ ልጆቹ እንደሄዱ እና ካሳ እንደመጣ ሰማች የሚሉት መዋቅሮች ሁለት ተከታታይ ድርጊቶችን ያመለክታሉ፡፡ ከምሳሌዎቹ ማንኛውም አይነት አረፍተ ነገር በመሙሊያነትም ሆነ በገላጭነት ሊገባ እንደሚችል መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፤ በአጠቃቀም ደረጃ፣ ገላጩ መዋቅር ግሳዊ ሆኖ መሙሊያው ስማዊ ቢሆን፣ አረፍተ ነገሩ የበለጠ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፡፡

የንዑስ ሀረጉን አወቃቀር በምሳሌ (22) አማካኝነት እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

26




እንደዚህ ያሉ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎች ቀደም ሲል እንዳየናቸው ካሉ ውስብስብ ስማዊ ሀረጎች ጋር ሲዋቀሩ በጣም ውስብስብ የሆነ አረፍተ ነገር ይፈጥራሉ፡፡ ስለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

[[አስቴርን የሰደበቻት ሴት] [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ [ካሳ መምጣቱን ሰማች]]] 27

የዚህ አረፍተ ነገር ባለቤት [አስቴርን የሰደበቻት ሴት] የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ግሳዊ ሀረጉ [ልጆቹ ወደ ትምህርት ቤት እንደሄዱ ካሳ መምጣቱን

ሰማች] የሚለው ክፍል ነው። የሁለቱን አወቃቀር እንደሚከተለው እናሳያለን። የግሳዊ ሀረግ ውስጣዊ መዋቅር ከላይ በተራ ቁጥር (26) በዝርዝር የሚታይ ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ በጥቅሉ ብቻ እናቀርበዋለን። ስማዊ ሀረጉን በዝርዝር እንመለከተዋለን።

28



በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ሶስት ጥገኛ አረፍተ ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም በባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ውስጥ፣ ሰደበቻት በሚለው ግስ የሚመራው ገላጭ፣ በግሳዊ ሀረጉ ውስጥ፣ ሄዱ በሚለው ግስ የሚመራ ገላጭና፣ መምጣቷን በሚለው ስም የሚመራው መሙሊያ አረፍተ ነገር ናቸው፡፡ አረፍተ ነገሩ ከዚህም የበለጠ ሊውስበሰብ ይችላል፡፡ ይህን ባደረገ ቁጥር እየረዘመ ስለሚሄድ፣ ለማስታወስ ያስቸግራል፡፡ ስለዚህም የእያንዳንዱ አረፍተ ነገር የውስብስብነት ደረጃ በተጠቃሚው የማስታዎስ ችሎታ ይወሰናል፡፡ ከስርዓት አንፃር ሲታይ ግን የማንኛውም አረፍተ ነገር መጠን ገደብ የለውም፡፡ ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

> ትናንት በግ የሸጠው ነጋዴ ያመጣውን የሰንጴ ዳቦ የሰረቀውን ልጅ የገረፈችው ሴት አለቴር የምትሸጠውን የገብስ ጠላ ጠጥቶ አልከፍልም በማለት እየዛተ የሄደውን ረዥም ልጅ የሰደበችው ነች፡፡ 29

ይህ ከ(12) ግላዊና ከአንድ ስማዊ ሀረግ በየደረጃው የተዋቀረ አንድ ውስብስብ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ከዚህም የበለጠ ሊረዝም ይችላል፡፡ ቢረዝምም መጠኑ ከአንድ አረፍተ ነገር አያልፍም፡፡ የሀረጎቹ መሪዎች የተሰመረባቸው ቃላት ናቸው፡፡ ዋናው አረፍተ ነገር ነች በሚለው ግስ መሪነት ከተመሰረተው ግሳዊ ሀረግና ሴት በሚለው ስም መሪነት ከተዋቀረው ስማዊ ሀረግ የተቀናጀ ነው፡፡ በተራ መልኩ ሲቀመጥ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[[.... ሴት] [.... ነች]] 30

ይህ እናት ወይም አቃፊ አረፍተ ነገር ሲሆን፣ በሌሎቹ በተሰመረባቸው ቃላት መሪነት በተመሰረቱት ሀረጎች አማካኝነት የተዋቀሩት አረፍተ ነገሮች በሙሉ ጥገኛ ወይም ዕቅፍ አረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡ አንዱ አረፍተ ነገር በሌላው አረፍተ ነገር ሀረግ ውስጥ እየገባ ጥገኛ ወይም ዕቅፍ የሚሆንበት ስርዓት ነው፡፡ ይህን በዚህ እንተውና ወደሌላ ጉዳይ እንሂድ፡፡ ከዚያ በፊት ግን በተራ ቁጥር (29) የተመከተውን አረፍተ ነገር ትንተና እንዲሞክሩት እንጋብዛለን፡፡

እስካሁን ያየናቸው ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎች በቃላዊ ግስ መሪነት የሚዋቀሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ በምዕላድ መሪነት የሚዋቀሩ ውስብስብ ግሳዊ ሀረጎችን ውስጣዊ ቅንጅት እንመለከታለን፡፡ ጉዳዩ በክፍል ሁለት፣ ስለ ቃላት ምስረታ ስንወያይ ካየነው ከአድራጊና ከአስደራጊ አዕማድ መዋቅራዊ ባህሪ ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ ያኔ አድራጊና አስደራጊ ምዕላዶች አንድ ግስ በሚፈልገው የመሙሊያ ሀረግ መጠን ላይ አስተዋፅዖ እንዳላቸው ገልፀን ነበር፡፡ ከዚያ አኳር፣ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፡፡

(ሀ) ቡና ፈላ 31
(ለ) አስቴር ቡና አፈላች
(መ) ካሳ አስቴርን ቡና አስፈላት

ፈላ የሚለው ኢሳቢ የድርጊት (ደራጊ) አምድ ነው። ኢሳቢ በመሆኑ መሙሊያ የለውም። ድርጊት ተቀባይ የሆነ ባለቤት ግን አለው። እሱም ቡና የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ኢሳቢ አምድ መነሻ ላይ /አ-/ የሚለውን ምዕላድ በመጨመር ኢሳቢና ደራጊ የነበረውን አምድ፣ ሳቢና አድራጊ ማድረግ ይቻላል። ሳቢ ግስ ደግሞ የግድ መሙሊያ ይፈልጋል። ስለዚህም አምዱ ቡና ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር በምሳሌ (ለ) እንደሚታየው ሆኖ ይዋቀራል። አስቴር የሚለው ስም ለዚሁ አድራጊ ግስ ባለቤት ሆኖ ይገባል። ከዚሁ ሳቢና አድራጊ አምድ መነሻ ላይ /አስ-/ የሚለው ምዕላድ ሲጨመር፣ አድራጊ የነበረው አምድ አስደራጊ ይሆናል። አስደራጊ አምድ ሁለት መሙሊያ የግድ ይፈልጋል። ስለዚህም አስቴር የሚለውን ሀረግ በሁለተኛ መሙሊያነት ይወስድና በዚህ ስም ፋንታ ባለቤት የሚሆን ሌላ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋል። በዚህም ምክንያት ካሳ የሚለውን ስም በባለቤትነት ይወስድና በምሳሌ (መ) እንደሚታየው ያለ ውስብስብ አረፍተ ነገር ይመሰርታል። የምሳሌ (መ) ትርጉምም፣

ካሳ አስቴርን ቡና እንድታፈላ (/ት-አፍኧላ/) አደረገ 32

የሚል ነው።

በዚህ ምሳሌ ውስጥ እንድታፈላ በሚለው ላይ /አስ-/ የሚል ምዕላድ የለም። በእሱ ፋንታ አደረገ የሚል ነፃ ግስ አለ። /አስ-/ እና ይህ ግስ አቻ ናቸው፣ ማለት ነው። ምክንያቱም በሁለቱ ምሳሌዎች፣ ማለትም በ31(መ) እና በዚህ ምሳሌ መካከል የትርጉም ልዩነት የለም። በሌላ አባባል፣ /አስ-/ የሚለው አስር ምዕላድና አደረገ የሚለው መደበኛ ግስ በግብር አንድ ናቸው። ሁለቱም አስደራጊ ናቸውና። የሚለያዩት በቅርፅ ብቻ ነው። ይኸውም አንደኛው አስር ሊሆን፣ ሌላኛው ሙሉ ግስ መሆኑና ከእሱ ጋር የሚዋቀረው አረፍተ ነገርም ሞይ ያለው መሆኑ ነው።

በአንፃሩ ካሳ አስቴርን ቡና አስፈላት፣ የሚለው ተራ አንጅ ውስብስብ አረፍተ ነገር ላይመስል ይችላል። ሞይ-አልባ መሆኑም ተራ ሊያሰኘው ይችላል። ዋናው መለኪያ ግን ሞይ አለሞኖሩ ሳይሆን፣ መዋቅሩን የሚመራው የግስ መጠንና አይነት ነው። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ መዋቅሩ የአንድ ደራጊና የአንድ አስደራጊ አምድ ቅንጅት ነው። ርግጥ፣ በላዕላይ መዋቅር ሁለቱ አምዶች አንድ አካል ስለሚሆኑና መዋቅሮቹም ስለሚዋሀዱ ተራ አረፍተ ነገር ሊመስሉ ይችላሉ[9]።

በዚሁ መንፈስ የምሳሌ 31(መ)ን ግሳዊ ሀረግ አቀነባበር በሚከተለው ዕፀ መዋቅር እናሳያለን።

---

[9] ርግጥ፣ የቃላዊውን ግስና የምዕላዳዊውን ግስ ግንኙነት በአዕማድ ምስረታው ላይ ማየታችን ግልፅ ነው። በዚህም መሰረት ምዕላዳዊ ግሶች መዋቅራዊ ቦታቸው ላይ ላይገኙ ይችላሉ። ለአቀራረብ ግልፅነት ሲባል ግን ከዚህ በታች በሚታየው መዋቅር (33) በቦታቸው ላይ እንዲታዩ ተደርጓል።

33



ከዕፀ-መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ /አስ-/ የሚለው አስደራጊ ምዕላዳዊ ግስ ነው። [አስቴር...አ-ች] የሚለው አረፍተ ነገራዊ መሙሊያ ነው። ሞይ የለውም፣ ስለዚህም ሞይ-የለሽ ንዑስ አረፍተ ነገር ልንለው እንችላለን። ሞይነቱ ለምዕላዳዊው ግስ ለ/አስ-/ ነው።

/አ-/ የሚለው አድራጊ ምዕላዳዊ ግስ ነው። እሱም [ቡና ፈላ] ከሚለው መሙሊያ አረፍተ ነገር ጋር ተዋቅሮ ንዑስ ግላዊ ሀረግ መስርቶአል። ይህም አረፍተ ነገር [አስቴር...አ-ች] እንደሚለው መሙሊያ አረፍተ ነገር ሞይ የለውም። ፈል- የሚለው ግስ ባለቤት ቡና የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ግሱ /አ-/ ከሚለው ምዕላዳዊ ግስ ጋር ሲዋሀድ፣ ቡና የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ የዚህ ውሁድ ግስ ተሳቢ ይሆናል። ውሁዱ ግስ ባለቤት ያስፈልገዋል። ስለዚህም አስቴር የሚለውን ስማዊ ሀረግ ባለቤት አድርጎ በመውሰድ [አስቴር ቡና አፈላች] የሚለውን አድራጊ አረፍተ ነገር ይመሰርታል። አፈላ የሚለው ውሁድ ግስ በተራው /አስ-/ ከሚለው ምዕላዳዊ ግስ ጋር ይዋሀድና /አስ-አ-ፈላ/ ይሆናል። /አስ-/ እና /አ-/ ተከታትለው ሲገኙ፣ /አ-/ ይገደፋል። ስለዚህም በላዕላይ መዋቅር ውስጥ ግሱ [አስፈላ] የሚል ይሆናል።

አስፈላ የሚለው አስደራጊ ግስ ተሳቢ ይፈልጋል። ስለዚህ አስቴር የሚለውን ባለቤት የነበረ ስማዊ ሀረግ እንደ ተሳቢ አድርጎ ይወስድና፣ እንደ ማንኛውም ግስ ባለቤት የሚሆን እንደ ካሳ ያለ ሌላ ስማዊ ሀረግ ይፈልጋል።

አደረገ የሚለው ተራ አድራጊ ግስ ነው። /አስ-/ በሚለው አስደራጊ ምዕላድ አማካኝነት ድርብ አድራጊ ሊሆን ይችላል። በዚህን ጊዜ ቅርፁ አስደረገ የሚል ይሆናል። የዚህ ድርብ አድራጊ ግስ መዋቅራዊ ይዘት እንደሚከተለው ነው።

ካሳ አስቴርን ቡና እንድታፈላ አስደረጋት 34

በዚህ ምሳሌ ውስጥ አራት ግሶች አሉ። እነሱም ፈላ ፣ አ- ፣ አደረገ እና አስ- ናቸው። ፈላ እና አደረገ መደበኛ ቃላዊ ግሶች ናቸው። አ- እና አስ- ምዕላዳዊ ግሶች ናቸው። ከምዕላድም አለር ምዕላድ ናቸው። በዚህም ቀደም ሲል ስለ ምስረታ ስንወያይ ካየናቸው ኀለር አምዶች ጋር ይመሳሰላሉ።

የአረፍተ ነገሩ ትርጉም፣ ካሳ በአንድ ሌላ ሰው አማካኝነት አስቴር ቡና እንዲፈላ እንድታደርግ አደረገ የሚል ነው። ከላይ እንደገለፅነው፣ አራት ግሶች ካሉ፣ አራት አረፍተ ነገሮች አሉ፣ ማለት ነው። እነዚህንም እንደሚከተለው እናሳያለን።

35


አነ
ስሀ
ግሀ
ስ
ግሀ1
ካሳ
አነ
ግ
አነ
አለ-(-አት)
ስሀ
ግሀ
ስ
ግሀ1
አነ
ግ
አነ
ሞይ
-ደረግ
ስሀ
ግሀ
ስ
አስቴር
ትሉ
ስሀ
ግ
ቡና
ፈላ

ይህ በታህታይ መዋቅር የሚታየው አቀነጃጀት ሲሆን፣ በላዕላይ መዋቅር ውስጥ፣ ፈላ የሚለው አምድ ት-አ- ከሚለው አድራጊ ምዕላድ ጋር ይገናኝና ት-አ-ፈላ ይሆናል። ይህም አንድ- ከሚለው ሞይ ጋር ተገናኝቶ አንድታፈላ ይሆናል። በዚህ ግስ መሪነት የተመሰረተው ግሳዊ ሀረግ ባለቤትም አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ -ደረገ በሚለው ደራጊ ግስ መሪነት የተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት፣ በግሀድ ያልተጠቀሰውና ቦታው በነጠብጣብ የተመለከተው ነው። ደረገ የሚለው አስር አምድ አስ- ከሚለው ምዕላድ ጋር ተገናኝቶ አስደረገ ይሆናል። /አስ-/ የሚለው ምዕላድ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ሲሆን፣ ካሳ ደግሞ የዚሁ አረፍተ ነገር ባለቤት ነው። ርግጥ፣ እንደ /አስ-/ ያለ ጥገኛ ምዕላድ እንዴት እንደ ግስ ሊቆጠር ይችላል? የሚል ጥያቄ ማንሳት ይቻላል። ዋናው መለኪያ፣ በቅርፁ አካባቢ ምክንያት የሚከሰተው መዋቅራዊ ለውጥ ነው። በ/አ-/ እና በ/አስ-/ ምክንያት፣ እንደ አስቴር ያለ፣ ባለቤት የነበረ ስማዊ ሀረግ ተሳቢ ይሆናል፣ ለባለቤትነት ደግሞ ሌላ ሀረግ አስፈልጎአል። ስለዚህም ካሳ ባለቤት ሆኖ ገብቶአል። አንድ ቅርፅ እንደዚህ ያለ መዋቅራዊ ለውጥ የሚያስከትል ከሆነ፣ ጥገኛም ይሁን ነፃ፣ መዋቅራዊ ቦታ ይሰጠዋል። ቦታውም ከላይ እንደሚታየው የግስ ነው።

ምሳሌ (34) አሻሚ ነው። አሻሚነቱ አስቴር በሚለው ስማዊ ሀረግ ሚና ላይ ነው። ሀረጉ አድራጊ ወይም ተደራጊ ባለቤት ሊሆን ይችላል። ዕፀ መዋቅር (35) የሚያሳየው፣ ሀረጉ አድራጊ ባለቤት ሆኖ ሲገባ ነው። ተደራጊ ባለቤት ሆኖ ሲገባ፣ የአረፍተ ነገሩ ትርጉም አስቴር ቡና እንዲፈላ እንድታደርግ ተደረገች የሚል ይሆናል። መዋቅሩም ተነብሮአዊ ነው። ዕፀ መዋቅራዊ ቅርፁ በተራ ቁጥር (35) ከሚታየው ጋር አንድ ነው። አደረገ የሚለው ግስ ተ-ደረገ የሚል የተደራጊ አምድ ቅርፅ ይይዛል። /አስ-/ ከሚለው አስደራጊ ምዕላድ ጋር ሲገናኝ፣ ግሱ /አስ-ተ-ድኧርርኧግ-/ የሚል ይሆናል። ቋንቋዋው የአስደራጊና የተደራጊ ምዕላድ ክትትሎሽን ስለማይፈቅድ፣ የተደራጊው ምዕላድ /-ተ-/ ይገደፋል። ይህ ሲሆን አስደረገ የሚለውን ላዕላይ ቅርፅ እናገኛለን። ይህ ቅርፅ ነው፣ አሻሚ የሆነው።

ሁኔታውን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የሚከተለውን ምሳሌ ደግሞ እንመልከት።

ካሳ አስቴርን አስደባት 36

ይህ አረፍተ ነገር አሻሚ ነው። ከትርጉም አንፃር፣ አስቴር ሰዳቢ ወይም ተሰዳቢ ባለቤት ልትሆን ትችላለች። ርግጥ፣ በቅርፅ ደረጃ አስቴር የሚለው ስም /-ን/ የሚለውን የተሳቢ ምዕላድ ስላስከተለ፣ ተሳቢ ብሎም ተደራጊ ስም ነው፣

ይባል ይሆናል። ከዚህ አኩዋያ ሲታሰብ፣ ዕፀ መዋቅራዊ ቅርፁ የሚከተለው ይመስላል።

37




ከዚህ ላይ ግሱ ሳቢ ስለሆነ፣ <u>አስቴር</u> የሚለውን ስም በተሳቢነት ይዞአል። ግሱ ተደራጊ ስለሆነና የባለቤቱ ቦታም ክፍት ስለሆነ፤ <u>አስቴር</u> የሚለው ስም ከተሳቢ ቦታው ተነስቶ ክፍት ወደሆነው የባለቤት ቦታ ይሄዳል። <u>ተሰደብ-</u> የሚለው ተደራጊ

ግስ /አስ-/ ከሚለው ምዕላድ ጋር ሲገናኝ /አስ-ተስደብ-አት/ ይሆናል፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ የአስደራጊው ምዕላድ /አስ-/ እና የተደራጊው (የተገብሮው) ምዕላድ /ተ-/ ሲከታተሉ፣ /ተ-/ ትገደፋለች፡፡ ባጭሩ የማንኛውም አስደራጊ አረፍተ ነገር ታህታይ ቅርፅ ገቢር ወይም ተገብሮ ሊሆን ይችላል፤ ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡ የአሻሚነቱም ምክንያት ይኸው ነው፡፡

በግልፅ እንደሚታየው፣ የሞዩ ቦታ ክፍት ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አረፍተ ነገሩ የ/አስ-/ መሙሊያ ሆኖ በሚገባበት ጊዜ ነው፡፡ አደረገ የሚለው መደበኛ (ነፃ) ግስ መሙሊያ ሆኖ ሲገባ፣ የሞዩ ቦታ አንድ[10] በሚለው ሞይ ይሸፈናል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ሲሆን ነው፡፡

[ካሳ [አስቴርን ሰው አንድትስድብ] አደረጋት] 38

ከዚህም ግሱ ቃላዊው አደረገ ሳይሆን፣ ምዕላዳዊው /አስ-/ በሚሆንበት ጊዜ፣ መሙሊያው አረፍተ ነገር ሞይ አይኖረውም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ቃላዊና ምዕላዳዊ ግሶችም በመሙሊያ አረፍተ ነገራቸው ይለያሉ፡፡ የምዕላዳዊ ግሶች መሙሊያ አረፍተ ነገር ሞይ የለውምና፡፡

በተሰጠው ምሳሌ ውስጥ አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ነው፡፡ ይሁን እንጅ የአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ተደራጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ይኸው አስቴር የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ፣ የዚሁ አቃፊ አረፍተ ነገር ባለቤት ይሆናል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

[አስቴር [--- ሰው አንድትስድብ] ተደረገች] 39

አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ መሰረታዊ (ታህታይ) ቦታ በነጠብጣብ የተሸፈነው ነው፡፡ ይህም የመሙሊያው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ ነው፡፡ ከዚህ ቦታ ተነስቶ ወደ አቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ቦታ በመውጣት [ሰው አንድትስድብ ተደረገች] ለሚለው ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ሊሆን ችሉአል፡፡ ይህ አረፍተ ነገር ቀደም ሲል፣ ይመስላል ለሚለው ግስ ባህሪ ስንወያይ ያስተዋልነውን ሊያስታውሰን ይገባል፡፡ ያኔ የአንድ አቅፍ አረፍተ ነገር ባለቤት

---

[10] ሞዩ አንድ የሚሆነው፣ የመሙሊያው አረፍተ ነገር ግስ የካልዓይ አንቀፅ ሲሆን ነው፡፡ ግሱ የቀዳማይ አንቀፅ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሞዩ እንደ ይሆናል፡፡ ምሳሌ፣

(ሀ) ካሳ ብርጭቆ እንደ ሰበረ ሰማሁ

(ለ) ካሳ ብርጭቆ እንዲሰብር (/እንደ-/ይ-ሰኧብር/) አዘዝኩ

የነበረ ስማዊ ሀረግ፣ የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤትም ሊሆን እንደሚችል አይተን ነበር፡፡ ከዚህ ላይ የምናየውም ይህንኑ ሁኔታ ነው፡፡

ሁኔታውን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እያነፃፀርን እንመልከት፡፡

(ሀ) [---[አስቴር ቡና እንድታፈላ] ይደረጋል (/ይ-ት-ድኧርርኧግ-ኣልል/)] 40
[ይድድኧርርኧግኣልል]

(ለ) [አስቴር]---ቡና እንዲታፈላ] ትደረጋለች (/ት-ት-ድኧርርኧግ-ኣልል-ኧች/)]
[ትእድድኧርርኧግኣልልኧች]

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ _ይደረጋል_ የሚለው የተገብሮ ግስ ባለቤት በግሀድ አይታይም፡፡ /ይ-/ ከሚለው አፀፋ ብቻ ሰስተኛ መደብ መሆኑን መለየት ይቻላል፡፡ በግሀድ የማይከሰተው፣ ባለቤቱ መደበኛ ተውላጠ ስም ሳይሆን፣ ቀደም ሲል የይስሙላ ባለቤት ያልነው፣ _it_ የሚለው ተውላጠ ስም በመሆኑ ነው፡፡ በአማርኛ፣ ይህ ተውላጠ ስም መደበኛ ቅርፅ እንደሌለውና ከላይ እንደሚታየው፣ በአፀፋ ብቻ እንደሚጠቀስ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ ባለቤት ሆኖ የሚገባውም እንደ _ይመስላል_ ላለ የሁኔታ ግስ እና እንደ _ይደረጋል_ (ይ-ት-ደረጋል) ላሉ ተደራጊ ግሶች ነው፡፡

እንደነዚህ ያሉ ግሶች መሰረታዊ ባህሪ አድራጊ ባለቤት አለመፈለግ እንደሆነ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ ስለዚህም በታህታይ መዋቅር ውስጥ፣ የነዚህ ግሶች ባለቤት ቦታ ክፍት (-) ይሆናል፡፡ በላዕላይ መዋቅር፣ አረፍተ ነገሮቹ ባለቤት የግድ ማግኘት አለባቸው፡፡ በቅርፃቸው ሙሉ ሆነው መገኘት አለባቸውና፡፡ ባለቤት ሊሆን የሚችለው ደግሞ አንድም የይስሙላው ተውላጠ ስም፣ ማለትም _it_ ፣ አለያም የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የሆነው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ የይስሙላው ተውላጠ ስም ባለቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ ምሳሌ 40(ሀ)ን እናገኛለን፡፡ የዚህ አረፍተ ነገር ግስም _ይደረጋል_ የሚል ነው፡፡ የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ 40(ለ)ን እናገኛለን፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ፣ ግሱ _ት-ደረጋለ-ች_ ይሆናል፡፡ ግሱ የሶስተኛ መደብ፣ አንስታይ ፆታ ምዕላድ የሆነችውን /ት-/ እና /-ች/ን ያሳያል፡፡ ከዚህም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት፣ በርግጥ _አስቴር_ የሚለው የሶስተኛ መደብና የአንስታይ ፆታ ስም መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ከዚህ ላይ መረዳት ያለብን ዋናው ጉዳይ፣ በተደራጊ አረፍተ ነገሮች ውስጥ፣ ተሳቢ ስማዊ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ ባለቤት ስማዊ ሀረግም ተደራጊ ባለቤት ሊሆን የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ባለፈው ንዑስ ክፍል ስለ ተራ ተደራጊ አረፍተ ነገሮች ስንወያይ፣ በታህታይ መዋቅር ተሳቢ የነበረ ስማዊ ሀረግ፣ በላዕላይ መዋቅር ባለቤት ሲሆን አይተናል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚታየው ግን በተራ

## ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ

እንደ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎች ሁሉ፣ ቅፅላዊ ሀረጎችም ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚወሳሰቡትም ከአረፍተ ነገሮች ጋር እየተቀናጁ አቢይ ሀረጋቸውን ሲመሰርቱ ነው፡፡ ዝርዝሩን ከዚህ ቀጥሰን እንመለከታለን፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንይ፡፡

(ሀ) ከአስቴር የበለጠ ወፍራም 1

(ለ) ከካሳ የባሰ አጭር

እነዚህ ቅፅላዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ ስለሆኑም እንደ ማንኛውም ቅፅል በስማዊ ሀረግ ውስጥ ከመሪው ስም እየቀደሙ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

[ከአስቴር የበለጠ ወፍራም] ሴት 2

በግልፅ እንደሚታየው፣ [ከእስቴር የበለጠ ወፍራም] የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ፣ <u>ሴት</u> የሚለውን ስም ቀድሞ በገላጭነት ገብቶአል፡፡ ይህ አይነተኛ የቅፅል አገባብ ነው፡፡ [ከአስቴር የበለጠ ወፍራም] የሚለው ቅፅላዊ ሀረግ መሪ [ወፍራም] የሚለው ቅፅል ነው፡፡

[ከአስቴር የበለጠ] 3

የሚለው ክፍል <u>ወፍራም</u> የሚለው ቅፅላዊ መሪ አሟላሽ ሲሆን፣ ተግባሩም ንፅፅርን ማሳየት ነው፡፡ ንፅፅሩ በአስቴርና በሴላ ባልተጠቀሰ ሰው መካከል ሲሆን፣ ማነፃፀሪያው ውፍረት ወይም ወፍራም መሆን ነው፡፡ [ወፍራም] የሚለው የሀረጉ መሪ <u>ወፈረ</u> የሚል ሁኔታን የሚገልፅ አቻ ግስ አለው፡፡ አንድ ሰው የሚያደርገውን ሳይሆን፣ የሚሆነውን የሚያመለክት ስለሆነ፣ የሁነት ግስ እንደሚባል ባለፈው ክፍል ገልፀናል፡፡ እንደዚህ ያሉ ግሶች በሙሉ መሙሊያ የላቸውም፡፡ አላቸው ከተባለ፣ መሙሊያ ሊሆን የሚችለው ራሱ ሁዋኙ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ስለዚህም ንዑስ ሀረጋቸውን የሚያዋቅሩት ብቻቸውን እንደ ምሰሶ እየቆሙ ነው፡፡ ከእነሱ ጋር አቻ ዝምድና ያላቸው ቅፅሎችም እንደዚሁ መሙሊያ ስለሌላቸው፣ ንዑስ ሀረጋቸውን የሚመሰርቱት ብቻቸውን ነው፡፡ አንድ ግስ መሙሊያ የሌለው ከሆነ፣ ከእሱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው ቅፅሎችና ስሞችም እንደዚሁ መሙሊያ አይኖራቸውም፡፡ መሙሊያ የመያዝ ወይም ያለመያዝ በአንድ ክፍል ብቻ የሚወሰን ባህሪ ሳይሆን ተዛማጅ ነው፡፡

በአቢይ ሀረግ ደረጃ [ወፍራም] የሚለው መሪ ቅፅል ከንፅፅራዊ አረፍተ ነገሮች ጋር ሊዋቀር ይችላል፡፡ የአወቃቀሩ ሁኔታ እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

4




ከመዋቅሩ እንደሚታየው፣ ንፅፅራዊ አረፍተ ነገር [ወፍራም] ከሚለው ንዑስ ቅፅላዊ ሀረግ ጋር በአጎላማሽነት ተዋቅሮአል፡፡ ጥገኝነቱን የምታመለክተው /የ/ ስትሆን፣ እስዋም እንደተለመደው አረፍተ ነገሩን ተከትላ በሞዩ ስር ትገኛለች፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ነገር ልብ ልንል ይገባል፡፡ ይኸውም በስማዊና በቅፅላዊ ሀረግ ውስጥ የሚገቡ የገላጭም ይሁን የመሙሊያ አረፍተ ነገር ሞይ አንድ

አይነት መሆኑን ነው፡፡ በሁለቱም ውስጥ ሞዩ /የ/ ሲሆን፣ አገባቡም ከላይ እንደተገለፀው አረፍተ ነገሩን እየተከተለ ነው፡፡ ይህ ሞይ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ ካየናቸው ጥገኛ አረፍተ ነገሮች ሞይ በከፊል የተለየ ነው፡፡ እንደምናስታውሰው፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ ያየናቸው የመሙሊያና የአጎላማሽ አረፍተ ነገር ሞዮች በአብዛኛው መስተዋድዶች (በጥንቱ አጠራር መስተፃምሮች) ናቸው፡፡ በአብዛኛው የምንልበት ምክንያት፣ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ <u>ይመስላል</u> የሚለው ግስ መሙሊያ አረፍተ ነገር /የ/ የሚል ሞይ ስላለው ነው፡፡

ስማዊ ሀረጎችና ቅፅላዊ ሀረጎች የሚመሳሰሉበት ሌላም ባህሪ አለ፡፡ ይኸውም የሁለቱም መሙሊያዎች ሊቀሩ የሚችሉ መሆናቸው ነው፡፡ በዚህም ባህሪያቸው ከግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ይለያሉ፡፡ ምክንያቱም የግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ሊቀር አይችልምና፡፡ ሊቀር የሚችለው አጎላማሹ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የማንኛውም አጎላማሽ ሀረግ ባህሪ ነው፡፡ የቅፅላዊና የስማዊ ሀረግ አጎላማሽ አረፍተ ነገር ምን ጊዜም ግሳዊ ነው፡፡ በዚህም ስማዊ ከሆነ አጎላማሽ አረፍተ ነገር ጋር ሲዋቀር ከሚችለው፣ ከግሳዊ ሀረግ ይለያሉ፡፡ ወደ ዕፀ-መዋቅሩ እንመለስ፡፡

የንፅፅራዊው አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ እንደማይታይ አንገነዘባለን፡፡ ቦታው ስነጠብጣብ የተሸፈነው ነው፡፡ በግሱ ላይ ግን /-ኧ-/ በሚለው አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ከዚህም ይዘቱ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይህ ባለቤት፣ ቅፅላዊው ሀረግ በመሙሊያነት ከገባበት ግሳዊ ሀረግ ባለቤት፣ ማለትም <u>ካሳ</u> ከሚለው ስም ጋር በትርጉም አንድ ነው፡፡ ተነፃፃሪው ስማዊ ሀረግም እሱው ነው፡፡ ይህን ከሚከተሉት ምሳሌዎች መረዳት ይቻላል፡፡

(ሀ) [[ካሳ] [[[--- ከአስቴር የበለጠ] ወፍራም] ነው]] 5
(ለ) [[እስቴር] [[[--- ከእኔ የበለጠች] ቀጭን] ነች]]

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ፣ <u>ነው</u> በሚለው ግስ መሪነት የተዋቀረው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት፣ <u>ካሳ</u> የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ [ከአስቴር የበለጠ] የሚለው ገሳጭ አረፍተ ነገር ባለቤትም እሱው ነው፡፡ በጥገኛው አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ ሊከሰት ያልቻለው በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንደኛው፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ በአፀፋ መጠቀሱ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ጋር በቅርፅም ሆነ በትርጉም አንድ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ባለቤት በግሀድ ቢታይ ኖሮ፣ አረፍተ ነገሩ፣

[ካሳ [[ካሳ ከአስቴር የበለጠ] ወፍራም] ነው] 6

የሚል ድግግሞሽ የሚታይበት መዋቅር ይሆን ነበር፡፡ ቀደም ሲል፣ ቁጥንቁጥ የማያስፈልግ ድግግሞሽን እንደማይፈቅድ ገልፀናል፡፡ ለዚህም ነው፣ የጥገኛው አረፍተ ነገር ባለቤት የሆነው ካሳ በግሀድ ሊከሰት ያልቻለው፡፡

በሁለተኛው ምሳሌ፣ ማለትም በ5(ሀ) ውስጥ የሚታየው ሁኔታም እንደዚሁ ነው፡፡ አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ የእቅፉም (ጥገኛው) ሆነ የእቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት ነው፡፡ በሁለቱም አረፍተ ነገሮች ግሶች ላይ [-ች] በሚል የባለቤት አፀፋ ተጠቅሶአል፡፡ ከፍ ሲል የጠቀስነው የድግግሞሽ ችግር እንዳይከሰት፣ በእቅፉ አረፍተ ነገር ውስጥ በግሀድ ከመከሰት ታቅቦአል፡፡ ከዚህም ሁኔታ የእቃፊና የእቅፍ አረፍተ ነገር ባለቤት አንድ ሲሆን፣ በግሀድ ከመከሰት የሚታቀበው የእቅፉ አረፍተ ነገር ባለቤት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

የንፅፅራዊ አረፍተ ነገር ግሶች የተወሰኑ ናቸው፡፡ የሚወሰኑትም በሚገልፁት የንፅፅር መጠን ነው፡፡ ንፅፅሩ እኩልነትን፣ በላጭነትን እና ተበላጭነትን ያሳያል፡፡ ግሶቹም እነዚህን ተግባራት የሚገልፁ ናቸው፡፡ በተራ አረፍተ ነገር ሲገለፅ፣ ንፅፅሩ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

(ሀ) ካሳ አስቴርን ያክላል 7
(ለ) ካሳ ከአስቴር ይበልጣል
(መ) ካሳ ከአስቴር ያንሳል

የመጀመሪያው ምሳሌ እኩልነትን፣ ሁለተኛው በላጭነትን፣ ሶስተኛው ደግሞ ተበላጭነትን ያሳያል፡፡ ግሶቹ ውሱን የሆኑት፣ ንፅፅሩ ውሱን በመሆኑ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳመለከትነው፣ እንደዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች፣ በእነዛፃሪነት ከቅፅላዊ ሀረግ ጋር ሲዋቀሩ፣ የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

(ሀ) አስቴርን የምታክል ወፍራም 8
(ለ) ከአስቴር የበለጠች ወፍራም
(መ) ከአስቴር ያነሰች ወፍራም

በግልፅ እንደሚታየው፣ ቅፅሎቹ ከንፅፅራዊ አረፍተ ነገሮች ጋር ተዋቅረው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ መስርተዋል፡፡ ቅንጅታዊ ስርዓታቸው በተራ ቁጥር (4) ላይ የተመለከተ ስለሆነ፣ ከዚህ ላይ አንደግመውም፡፡

ንፅፅራዊ መስተዋድዶቹ /ከ/ እና /-ን/ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው አበላላጭ ሲሆን፣ ሁለተኛው አደላዳይ፣ ማለትም እኩልነትን አመልካች ነው፡፡ ከዚሁ ተግባራቸው በመነሳት አበላላጭና አደላዳይ መስተዋድዶች ልንላቸው እንችላለን፡፡

አደላዳዩ አረፍተ ነገር፣ በተራ መስተዋድዳዊ ሀረግነት ሊከሰት ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ መስተዋድዱ እንደ ይሆናል፡፡ ስለዚህም አስቴርን የምታክል የሚለው አደላዳይ አረፍተ ነገር፣ እንደ አስቴር የሚል አደላዳይ መስተዋድዳዊ ሀረግ ይሆናል፡፡ ከቅፅሉ ጋር ሲገባም እንደ አስቴር ወፍራም የሚል ይሆናል፡፡ ከዚህ ላይ አስቴር የሚለውን ስም ተከትሎ የገባው /-ን/ መስተዋድድ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ መስተዋድድ በመሆኑ፣ እንደ የሚለው ሌላ መስተዋድድ ከስሙ ቀድሞ ሲገባ፣ /-ን/ ይጠፋል፡፡

የውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ ግንኙነት ከስማዊ ወይም ከግሳዊ ሀረግ ጋር ነው፡፡ ከስማዊ ሀረግ ጋር በገላጭነት፣ ከግሳዊ ሀረግ ጋር በመሙሊያነት እንደሚከተለው ይገባሉ፡፡

(ሀ) ካሳ [[ከአስቴር የበለጠች ወፍራም] ሚስት] አለችው 9

(ለ) ካሳ [[ከእኔ የበለጠ] ወፍራም] ነው

በመጀመሪያው ምሳሌ [ከአስቴር የበለጠች ወፍራም] የሚለው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ሚስት የሚለው ንዑስ ስማዊ ሀረግ ገላጭ ነው፡፡ ቅፅላዊ ሀረጉ ውስብስብ ስለሆነ፣ ስማዊ ሀረጉም ውስብስብ ሊሆን ችሉአል፡፡ ቅፅላዊ ሀረጉ ተራ ሲሆን፣ ባለፈው ክፍል ስለ ሀረግ ስንወያይ እንዳየነው፣ ስማዊ ሀረጉም እንደዚሁ ተራ ይሆናል፡፡ በዚህን ጊዜ፣

[ከአስቴር የበለጠች ወፍራም ሚስት] 10

የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ፣

[ወፍራም ሚስት] 11

የሚል ተራ ቅፅል ብቻ የሚገኝበት ስማዊ ሀረግ ይሆናል፡፡

በሁለተኛው ምሳሌ (9ለ) ውስጥ፣ [ከእኔ የበለጠ ወፍራም] የሚለው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ነው የሚለው የመሆን ግስ መሙሊያ ሆኖ ገብቶአል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ነው የሚለው ግስ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ሊመሰርት ችሉአል፡፡ ቅፅላዊ ሀረጉ ውስብስብ ባይሆን ኖሮ፣ ግሳዊ ሀረጉ ውስብስብ ላይሆን፣

[ወፍራም ነው] 12

የሚል ተራ ግሳዊ ሀረግ ይሆን ነበር፡፡

በተራ ቁጥር (10) ውስጥ የተመለከትነው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ ከስማዊ ሀረጉ ጋር ያለውን መዋቅራዊ ግንኙነት እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ - መዋቅር እናሳያለን፡፡

13




[11] በታህታይ መዋቅር፣ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ቀኝ መሪ መሆናቸውን ልናስታውስ ይገባል፡፡ መስተዋድዱ ድጋፍ ስለሚፈልግ ከመሙሊያው ስም መነሻ ላይ የሚቀጠለው በላዕላይ መዋቅር ነው፡፡ ተለጣፊነት የስው ብቻ ሳይሆን፣ የአቅመ ቢስ ምዕላዶችም ባህሪ ነው፡፡

እንደዚህ ካሉ ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረጎች የሚዋቀር አርፍተ ነገር ውስብስብ ነው፡፡ የውስብስብነቱ ደረጃ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ ስማዊ ሀረጉ ብቻ ውስብስብ የሆነበት አረፍተ ነገር፣ ስማዊና ግሳዊ ሀረጎቹ ውስብስብ ከሆኑበት አረፍተ ነገር ያነሰ ውስብስብ ነው፡፡ ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን እንመልከት፡፡

[ገነት[ካሳ ያገባት[ ሴት [ከእስቴር የበለጠች[ ወፍራም[እንደሆነች[ታውቃለች]]]]]] 14

በዚህ ምሳሌ ውስጥ አንድ ውስብስብ ባለቤት ስማዊ ሀረግ፣ አንድ ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ፣ እንዲሁም አንድ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ አለ፡፡ ሁሉም የሚገኙት <u>ታውቃለች</u> ለሚለው ግስ መሙሊያ ሆኖ በገባ አረፍተ ነገር ውስጥ ነው፡፡ ሀረጎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

(ሀ) ካሳ ያገባት ሴት 15
(ለ) ከእስቴር የበለጠች ወፍራም
(ሐ) ... እንደሆነች

<u>ካሳ ያገባት ሴት</u> የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ <u>ሆነች</u> በሚለው ግስ ለሚመራው ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው፡፡ <u>ከእስቴር የበለጠች ወፍራም</u> የሚለው ውስብስብ ቅፅላዊ ሀረግ ደግሞ የዚሁ <u>ሆነች</u> የሚለው ግስ መሙሊያ ነው፡፡ ግሱና መሙሊያው ተዋቅረው፤

ከእስቴር የበለጠች ወፈራም እንደሆነች 16

የሚለውን ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ መስርተዋል፡፡ <u>ካሳ ያገባት ሴት</u> የሚለው ውስብስብ ስማዊ ሀረግ፣ የዚህ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው፡፡ ሁለቱ ሲቀናጁ፤

ካሳ ያገባት ሴት ከእስቴር የበለጠች ወፈራም እንደሆነች 17

የሚለውን መሙሊያ አረፍተ ነገር እናገኛለን፡፡ መሙሊያነቱ <u>ታውቃለች</u> ለሚለው ግስ ነው፡፡ ግሱ ከዚህ መሙሊያ ጋር ሲዋቀር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ካሳ ያገባት ሴት ከእስቴር የበለጠች ወፈራም እንደሆነች ታውቃለች 18

<u>ገነት</u> የሚለው ስም የዚህ ውስብስብ ግሳዊ ሀረግ ባለቤት ነው፡፡ ሁለቱ ሲዋቀሩ፣ በተራ ቁጥር (14) የተመለከተውን ውስብስብ አረፍተ ነገር እናገኛለን፡፡ ከዚህ በላይ

ባየነው ትንታኔ መሰረት የዚህኑ አረፍተ ነገር አወቃቀር በዕፀ-መዋቅር ለማሳየት እንዲሞክሩ እያደፋፈርን ወደሚቀጥለው እንሄዳለን፡፡

## *ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረግ*

ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከመስተዋድዳዊ መሪና ከውስብስብ ስማዊ ሀረግ ይዋቀራሉ፡፡ ውስብስብ ስማዊ ሀረግ የሚባሉትን ቀደም ሲል አይተናቸዋል፡፡ ገላጭ አዛማጅ አረፍተ ነገር እና/ወይም ሞይ አረፍተ ነገር ያላቸው ናቸው፡፡ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

(ሀ) ትናንት ለመጣው ልጅ 1
(ለ) ስለ ካሳ ቤት የመስራት ዓላማ

እነዚህ ውስብስብ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡ መሪያቸው ለ እና ስለ የሚሉት መስተዋድዶች ናቸው፡፡ በተራ መስተዋድዳዊ ሀረግ መልክ ሲገኙ፣ እንደ ቅደም-ተከተላቸው፣ የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

(ሀ) ለልጅ 2
(ለ) ስለ ዓላማ

በምሳሌ 1(ሀ) ልጅ የሚለው መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ገላጭ አለው፡፡ ገላጩም ትናንት የመጣው የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ በምሳሌ (ለ)፣ ዓላማ በሚለው ስም መሪነት የተዋቀረው ስማዊ ሀረግም እንደዚሁ መሙሊያ ነው፡፡ መሙሊያነቱ ስለ ለሚለው መስተዋድድ ነው፡፡ መሙሊያው ስማዊ ሀረግም በውስጡ የራሱ መሙሊያ አረፍተ ነገር አለው፡፡ እሱም የካሳ ቤት የመስራት የሚለው መዋቅር ነው፡፡

የየሀረጎቹን ውስጣዊ አቀነባበር በዕፀ-መዋቅር እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡

3




ገላጩ እረፍተ ነገር አዛማጅ ነው፡፡ የተዛመደው ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ስለሆነም ቦታው በነጠብጣብ ተሸፍኖአል፡፡ የተዛመደ ሀረግ በግሀድ ሊከሰት አይችልምና፡፡ ይዘቱ በአዛማጁ ግስ ላይ ከሚታየው አፀፋና ከስማዊ ሀረጉ መሪ፣ ማለትም ልጅ ከሚለው ስም፣ ይታወቃል፡፡ አዛምጁ ሀረግ የተዋቀረው ከንዑሱ

[12] ቀደም ሲል እንደተገለፀውና መስተዋድዳዊ ሀረጎች ቀኝ መሪ ናቸው ብለን፣ ባጠቃለልነው መሰረት፣ ከዚህ ላይም መስተዋድዳዊው መሪ በስተቀኝ መገኘት እንዳለበት እናምናለን፡፡ ቢሆንም ለቀላል አቀራረብ ስንል መሪውን በግራ በኩል አስቀምጠነዋል፡፡

ስማዊ ሀረግ ጋር ሲሆን፣ የሚመሰርተውም አቢዩን ስማዊ ሀረግ፣ ማለትም (ስሀ2) ነው፡፡ ይህ አይነተኛ የገላጭ አረፍተ ነገር መዋቅራዊ ባህሪ ነው፡፡ ከንዑስ ሀረግ ጋር እየተዋቀሩ አቢይ ሀረግ ይመሰርታሉ፡፡

<u>ስሌ</u> የሚለውን መስተዋድድና የመሙሊያውን አረፍተ ነገር መዋቅራዊ አገባብ ከዚህ ቀጥለን በዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡

4



## *ውስብስብ መጠይቃዊ አረፍተ ነገር*

ባለፉት ሁለት ንዑስ ክፍሎች፣ ስለ ተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ተወያይተናል፡፡ ተራ አረፍተ ነገሮች ከተራ ሀረጎች፣ ውስብስብ አረፍተ ነገሮች ከውስብስብ ሀረጎች እንዴት እንደሚዋቀሩ በዝርዝር ለማየት ሞክረናል፡፡ በዚህ ንዑስ ክፍል ደግሞ ባለፈው ካየናቸው ለየት ያሉ ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን እንመረምራለን፡፡ ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት ግን ምናልባት ስለ አረፍተ ነገር ተግባር አንዳንድ ተጨማሪ ነጥቦችን እንደገና ማንሳቱና ግልፅ ማድረጉ ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ርግጥ ጉዳዩን ቀደም ሲልም በመጠኑ አንስተነዋል፡፡ መድገሙ ጉዳት የለውም፡፡

ማንኛውም አረፍተ ነገር የሙሉ ሀሳብ መግለጫ ነው፡፡ ቋንቋዎም በሀሳብ መግለጫነቱ ሙሉ ወይም ክፊል ሀሳብን የሚያስተላልፉ የቃላት፣ የሀረጎችና የአረፍተ ነገሮች ክምችት ነው፡፡ ያልተሙዋላ ሀሳብ በቃል ወይም በሀረግ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ሙሉ ሀሳብ ስለ አንድ ክስተት የሚሰነዘር ሀተታ ነው፡፡ ሀተታው ስለ ክስተቱ ድርጊት ወይም ባህሪ ወይም ሁነት ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ አረፍተ ነገር ሙሉ ሀሳብን የሚገልፀው ክስተቱንና በእሱ ላይ ሊሰጥ የሚገባውን ሀተታ አቀናጅቶ ሲይዝ ነው፡፡ ክስተቱን ወይም ሀተታውን ብቻ በመያዝ ሙሉ ሀሳብ ሊሰጥ አይችልም፡፡ ሀሳበ-ጎደሎ ይሆናል፡፡

ከዚህ ሁኔታ ሲታይ፣ ካሁን በፊት እንደተገለፀው፣ አንድ አረፍተ ነገር እንደ አንድ ድርሰት ሊቆጠር ይችላል፡፡ አንድ ድርሰት ርዕስና በእሱ ላይ የቀረበ <u>ድርሳን</u> ወይም ሀተታ እንደሚኖረው ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ክስተትና በእሱ ላይ የቀረበ ሀተታ ይኖረዋል፡፡ ክስተቱን እንደ ርዕስ፣ ሀተታውን እንደ ድርሳን፣ አረፍተ ነገሩን ደግሞ እንደ ድርሰት አድርጎ ማየት ይቻላል፡፡ አንድ ድርሰት የተሙዋላ ነው የሚባለው ርዕሱንና በዚያ ላይ ሊባል የሚገባውን ሁሉ፣ ከጥቅሉ እስከ ዝርዝሩ አካቶ ሲይዝ እንደሆነ ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም ሙሉ ነው የሚባለው፣ ክስተቱንና በእሱ ላይ ሊቀርብ የሚገባውን ሀተታ አቀናጅቶ ሲይዝ ብቻ ነው፡፡

አንድ ድርሰት የተለያየ ያደራረስ ዘዴ እንዳለው ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም የተለያየ ያወቃቀር ስርዓት አለው፡፡ ዘዴውን የሚወስነው የድርሰቱ ተግባር ነው፡፡ ድርሰቱ ተራ ሀሳብን የሚገልፅ ከሆነ፣ አደራረሱ ተራ ሊሆን ይችላል፡፡ አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ነው፡፡ ተራ ሀተታን የሚያስተላልፍ አረፍተ ነገር አወቃቀር ተራ ነው፡፡ በአንድ ግስ መሪነት ላይ ብቻ ይመሰረታል፡፡ ባለፈው ክፍል መጀመሪያ ላይ ያየናቸው አረፍተ ነገሮች የዚህ ምሳሌ ናቸው፡፡ አረፍተ ነገሩ አፅንዖትን የተላበሰና ጥልቅ ሀሳብን የሚያቀርብ ከሆነ፣ አወቃቀሩ ከተራው አረፍተ ነገር አወቃቀር ይለያል፡፡ ከዚህ አንፃር ለአብነት የሚከተለውን እንመልከት፡፡

አስቴር ብርጭቆውን ሰበረችው 1

ይህ ሙሉ ሀሳብን ያዘለ ተራ አረፍተ ነገር ነው። የሀሳቡ ርዕስ አስቴር የሚለው ስም ነው። ሀተታው ብርጭቆውን ሰበረችው የሚለው ክፍል ነው። ርዕሱና ሀተታው ድርሰቱን፣ ማለትም አረፍተ ነገሩን ፈጥረዋል። ከመዋቅር አኳዋያ፣ ርዕሱ አስቴር የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ ሀተታው ብርጭቆውን ሰበረችው የሚለው ግሳዊ ሀረግ ነው። የሁለቱ ቅንጅት ውጤት አረፍተ ነገሩ ነው። አረፍተ ነገሩ ብርጭቆውን ሰበረችው የሚለውን ግሳዊ ሀረግ ብቻ በመያዝ የተሟላ ሀሳብ ሊሰጥ አይችልም። ስለዚህም ብርጭቆውን ሰበረችው የሚለውን ሀረግ የሚሰማ ሰው፣ ብርጭቆውን የሰበረችው ማን ነች? ወይም ማን ነች ብርጭቆውን የሰበረችው? ብሎ በአፅንዖት መጠየቅና የጎደለውን ሀሳብ ማግኘት ይኖርበታል። ጥያቄው የርዕስ ጥያቄ ነው፤ የሀተታ አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ አስቴር የሚለውን ስም ብቻ ከተናጋሪው አንደበት ቢሰማ? አስቴር ምን ሆነች ወይም ምን አደረገች? ብሎ መጠየቁ የማይቀር ነው። ይኸኛው ጥያቄ የርዕስ አይደለም፤ የሀተታ ነው፤ ርዕሱ ተሰጥቶአልና። ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ አንድ አረፍተ ነገር ስለ አንድ ክስተት የሚያትት ብቻ ሳይሆን፣ የሚጠይቅም ሊሆን ይችላል። እንደዚህ ያለ አረፍተ ነገርም መጠይቃዊ አረፍተ ነገር እንደሚባል ባለፈው ክፍል ስለ ተራ አረፍተ ነገር ስንወያይ ገልፀናል።

ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ድርሰቱ ማለትም አረፍተ ነገሩ፣ የባለቤትና የአንቀፅ ቅንጅት ነው። ባለቤቱ አስቴር የሚለው ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ አንቀፁ ብርጭቆውን ሰበረችው የሚለው ግሳዊ ሀረግ ነው። ቅደም-ተከተል አገባባቸውን ስንመለከት፤ ባለቤቱ ቀድሞ፣ አንቀፁ እሱን ተከትሎ እንደገባ እንረዳለን። ከዚህ ላይ ታዲያ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይኸውም፣ ቅደም-ተከተሉ ለምን እንደዚህ ሆነ? የዚህ ግልባጭ ሊሆን አይችልም ነበር ወይ? የሚል ነው። ጥያቄው ስለ ተራ አረፍተ ነገሮች አወቃቀር ስንወያይ መነሳት ነበረበት። ያኔም ይነሳ አሁን፣ መልሳችን "አወን፣ ቅደም-ተከተሉ የዚህ ግልባጭ ሊሆን ይችል ነበር፤" የሚል ነው። ሊሆን ይችል ነበር፣ የምንልበት ምክንያት፣ በግሳዊው ሀረግ የሚጀምሩና በባለቤት የሚጨርሱ ወይም በባለቤት ጀምረው በተሳቢ ስማዊ ሀረግ የሚጨርሱ ቋንቋዎች በዓለም ላይ ስላሉ ነው። ሩቅ ሳንሄድ፣ እንደ ግዕዝ ያሉ የሴም ቋንቋዎችንና እንደ አኝዋክ ያሉ የአባያዊ ቋንቋዎችን ብንመለከት፤ በባለቤት ጀምረው በተሳቢ የሚጨርሱ መሆናቸውን እንረዳለን። ይህን ከሚከተለው የግዕዝ ምሳሌ መገንዘብ ይቻላል።

አነ አነብብ መጽሐፈ 2
እኔ አነባለሁ መጽሀፍን
እኔ መጽሀፍን አነባለሁ

የአማርኛ ስርዓትም እንደዚሁ በባለቤት ጀምሮ በተሳቢ የሚጨርስ ሊሆን ይችል ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ግዕዝ ያሉ ቋንቋዎች፣ እንደ አማርኛው ስርዓት በግስ ሊጨርሱ ይችሉ ነበር። ከትውረት አንፃር ሲታይ፣ የማንኛውም ቋንቋ የአረፍተ ነገር ስርዓት በግስ መጨረስ ወይም አለመጨረስ ነው፤ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል። ግሱ የአረፍተ ነገሩ ማሰሪያ ወይም መቋጫ ስለሆነ እሱ ከሚገኝበት ቦታ አንፃር፣ የአረፍተ ነገሩን ቅደም-ተከተላዊ ስርዓት ማወቅ ይቻላል።

ከዚህ አንፃር ቋንቋዎች ሁሉ ያላቸው ዕድል በግስ መጨረስ ወይም መጀመር ነው። ከዚያም አልፎ አንዳንድ የስነ-ልሳን ተዋሪዎች የቋንቋው ሁሉ ታህታይ አወቃቀር፣ <u>ባለቤት - ግስ - ተሳቢ</u> ነው፣ በማለት አጠንክረው ይከራከራሉ። ወደ ዝርዝሩ አንገባም።

ትውረቱ ይህ ሆኖ ሳለ፣ አንድ ቋንቋ አንዱን ወይም ሌላውን ስርዓት የሚከተልበት ራሱን የቻለ ምክንያት አለው። ምክንያቱ አገነዛዘብ (አመለካከት) ብሎም አገላለፅ ነው። ማንኛውም ሰው አካባቢውን የሚገነዘበው እየመረጠ ነው። ሁሉንም ሊገነዘብ አይችልም። ሲናገርም ሆነ ሲሰማ እየመረጠ ነው። ህይወት ራስዋ ምርጫ ነች። ስንመርጥ ነው የምንውለው።

ጫካ ውስጥ የገባ ሰው ጫካውን በጥቅል፣ አለያም እያንዳንዱን ዛፍ በተናጠል ይመለከታል። ከዚያም ስለ አጠቃላዩ ጫካ ወይም ስለ አንድ የተለየ ዛፍ የተገነዘበውን ይናገራል። ስለ አንድ ዛፍ የሚናገር ከሆነ፣ ንግግሩ በ<u>ዛፉ</u> አይነት ወይም <u>መጠን</u> ላይ ሊያተኩር ይችላል። በመጠኑ ላይ ካተከረ፣ <u>ትልቅ</u> ወይም <u>ትንሽ</u> ብሎ ገለፃውን በቅፅል ይጀምርና <u>ዛፍ</u> ብሎ በስም ይጨርሳል። አጠቃላይ ገለፃውም <u>ትልቅ ዛፍ</u> የሚል ስማዊ ሀረግ ይሆናል። ትኩረቱ በዛፉ ላይ ከሆነ፣ <u>ዛፍ</u> ብሎ፣ ገለፃውን በስሙ ይጀምርና፣ <u>ትልቅ</u> ብሎ በቅፅል ይጨርሳል። ይህም <u>ዛፍ ትልቅ</u> የሚል ስማዊ ሀረግ ይሆናል። የሌሎቹ ሀረጎች ቅደም-ተከተል ስርዓትም በዚሁ አገነዛዘብ ላይ የተመሰረተ ነው ለማለት ይቻላል።

በዚህ አይነት አትኩሮትን ያገኘ ነገር አትኩሮትን ካላገኘ ነገር ቀድሞ ከአንደበት ይወጣል፤ ቀድሞም ይደመጣል። በአረፍተ ነገር ደረጃ፣ ቀድሞ የሚወጣ ነገር ደግሞ ስማዊ ወይም ግሳዊ ሀረግ ነው። ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም። ሌሎቹ ሀረጎች በነዚህ ውስጥ በገላጭነት ወይም በመሙሊያነት ወይም በመስተዓምርነት የሚገኙ ናቸው። ርግጥ፣ የየራሳቸው የቅደም - ተከተል ስርዓት አላቸው። ይህም ቢሆን መሪያቸውን በመነሻ ወይም በመድረሻ የሚያስቀምጥ ነው። ከዚህ አንፃር የአማርኛ ሀረጎች መሪ መጨረሻ ላይ እንደሚገኝና በዚህም ምክንያት ቋንቋዋ ቀኝ መሪ እንደሆነ በክፍል ሁለት ስለ <u>*ሀገ-መዋቅር*</u> ስንወያይ ተመልክተናል።

አትኩሮት የሚያገኙ ነገሮችን የሚወስነው፣ ፍላጎት ነው። ፍላጎትን ለማሙዋላት ከፍተኛ አወንታዊ ወይም አሉታዊ አስተዋፅዖ ያላቸው ነገሮች ዋና

6




ከዕፀ-መዋቅሩ ለማየት እንደሚቻለው፣ የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት፣ <u>አስቴር የሰበረችው</u> በሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር የተጎላመሰው ስማዊ ሀረግ ነው። የዚህ

ሀረግ መሪ በግሀድ አይታይም፤ ድምፅ-የለሽ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ፣ ሀረጉን መሪ - አልባ ልንለው እንችላለን፡፡ ይህን ስንል ግን መጠንቀቅ አለብን፡፡ ምክንያቱም ሀረጉ ቅርፅ ሳይሆን፣ ይዘት ያለው መሪ አለውና፡፡ እሱም ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ የሆነ ስም ነው፡፡ ይህ ለመሆኑ ማስረጃው በአዛማጁም ሆነ በአቃፊው አረፍተ ነገር ግስ ላይ የሚታየው ው (/-ኡ/) የሚለው አፀፋ ነው፡፡ ይህ አፀፋ ካሁን በፊት ደጋግመን እንዳየነው፣ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር ተባዕታይ ፆታ ምዕላድ ነው፡፡ የሚጠቁመው በመጀመሪያ ደረጃ፣ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘውን ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በአቃፊው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ የባለቤቱን ስማዊ ሀረግ መሪ ስም ነው፡፡ <u>ምንድን</u> በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት የተጠየቀውም ይኸው መሪ ነው፡፡ በግሀድ ቢወጣ ኖሮ፣ አረፍተ ነገሩ የሚከተለውን ይመስል ነበር፡፡

አስቴር የሰበረችው <u>ነገር</u> ምንድን ነው? 7

<u>ነገር</u> የሚለው ምዕላድ፤ በግሀድ የማይታየው ኢስዋዊ የሆነ ስም ተውላጥ ነው፡፡

ከላይ በዕፀ-መዋቅሩ አማካኝነት የሚታየው ታህታይ መዋቅር አንዳንድ ጊዜ፣

ምንድን ነው አስቴር የሰበረችው (ነገር) ? 8

በሚል መልክ ሊከሰት ይችላል፡፡ በሁለቱ ላዕላይ መዋቅሮች መካከል የሚታየው ልዩነት የአፅንዖት ብሎም የቅርፅ ነው፡፡

<u>አሰቴር የሰበረችው ምንድን ነው</u>? የሚለው ጥያቄ የሚጀምረው <u>አስቴር የሰበረችው</u> በሚለው መሪ-አልባ ባለቤት ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ አፅንዖት ያገኘውም ይኸው ሀረግ ነው፡፡ <u>ምንድን ነው አስቴር የሰበረችው</u>? የሚሰው ደግሞ የሚጀምረው በግላዊ ሀረጉ ነው፡፡ በመሆኑም አፅንዖቱ ያረፈው በዚሁ ግሳዊ ሀረግ ላይ ነው፡፡ ከአፅንዖት መለያየት የተነሳ፣ አንድ መጠይቃዊ ታህታይ መዋቅር ወደ ሁለት የተለያዩ ላዕላይ መጠይቃዊ መዋቅሮች ሊለወጥ ችሉአል፡፡ የቋዋንቋዋው ውስጣዊ አቀነጃጀት በባለቤት ስማዊ ሀረግ ጀምሮ፣ በግሳዊ ሀረግ የሚጨርስ ስለሆነ፣ <u>ምንድን ነው አሰቴር የሰበረችው?</u> የሚለው ላዕላይ መዋቅር፣ ከላይ ከሚታየው ዕፀ-መዋቅር ላይ በ<u>ለዋጭ ህግ</u> አማካኝነት እንደሚከተለው ሆኖ የወጣ ነው፡፡


9
አነ
ግሀi
አነ
ግሀ1
ስሀ
ግሀi
ስሀ
ግ
ስሀ2
ስ
ነው
አነ
ስሀ1
ምንድን
አነ
ሞይ
ስ
ስሀ
ግሀ
የ
-
ስ
ግሀ1
አስቴር
ስሀ
ግ
ስ
ሰበረችው
-

በግልፅ እንደሚታየው፣ <u>ምንድን ነው?</u> የሚለው ግሳዊ ሀረግ ከመሰረታዊ ቦታው ተነስቶ፣ ከአረፍተ ነገሩ በመውጣት፣ የአረፍተ ነገሩ ርዕሰ ሆኖአል፡፡ የገባበት ቦታ፣ በዕፀ መዋቅሩ ውስጥ ከሚገኙት ቦታዎች ሁሉ ከፍተኛው ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ቦታ በአፅንዖት ለሚነገሩና ወይም የየአረፍተ ነገሩ ርዕሰ-ነገር የሆኑ ሀረጎች ማረፊያ ነው፡፡ ሀረጎችም እንደሰው ከፍተኛ ቦታ ይፈልጋሉ ማለት ነው፡፡ ቋዋንቋዋ ተናጋሪውን እንደሚመስል ቀደም ሲል ተናግረናል፡፡

በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ እንደሚታየው፣ <u>ምንድን ነው?</u> የሚለው ክፍል ግሳዊ ሀረግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ የአረፍተ ነገሩ ድርሳን (ሀተታ) ክፍል ነው፡፡ የአረፍተ ነገሩ ርዕሰ ባለቤቱ፣ ማለትም <u>አስቴር የሰበረችው</u>፣ የሚለው መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ በታህታይ መዋቅሩ ውስጥ፣ አፅንዖት ያገኘውም ይኸው ክፍል ነው፡፡ በመሆኑም፣ ከሁሉም ቀድሞ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ ሊገኝና ከአንደበትም ቀድሞ ሊወጣ ወይም ሊፃፍ ችሎአል፡፡ ግሳዊ ሀረጉን፣ ማለትም ሀተታውን፣ በአፅንዖት ሰመግለፅ ለንፈልግ፣ ከታህታይ ቦታው አውጥተን፣ አፅንዖት አግኝቶ የነበረውን፣ ባለቤቱን ስማዊ ሀረግ አሳልፈን፣ የዕፀ መዋቅሩን ከፍተኛ ቦታ እንዲይዝ ማድረግ አለብን፡፡ ይህን ለናደርግ፣ <u>አስቴር የሰበረችው ምንድን ነው?</u> ይል የነበረው መጠይቃዊ መዋቅር፣ <u>ምንድን ነው አስቴር የሰበረችው?</u> ወደሚል ለየት ያለ ላዕላይ መዋቅር ይለወጣል፡፡ በታህታይ መዋቅር አፅንዖት ያልነበረው ግሳዊ ሀረግ፣ በላዕላይ መዋቅሩ ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ ሊይዝና አፅንዖት ሊጎናፀፍ ችሎአል፡፡ ይህ ከመሆኑ፣ ማለትም ግሳዊ ሀረጉ ከመንቀሳቀሱ በፊት ከፍተኛውን ቦታ ይዞ የነበረው ባለቤት ስማዊ ሀረግ፣ በፊት የነበረውን አፅንዖት ቢያጣም፣ የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ከመሆን አይታገድም፡፡ አፅንዖት ያጣ ወይም በተራ አነጋገር ግርማ ሞገሰ የራቀው ተራ ባለቤት ብቻ ይሆናል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚከተለውን አይነት ላዕላይ መዋቅር ልናገኝ እንችላለን፡፡

አሰቴር ምንድን ነው የሰበረችው? 10

በዚህና <u>አስቴር የሰበረችው ምንድን ነው</u>? በሚለው ሀረግ መካከል ያለው ልዩነት፣ <u>ምንድን ነው</u>? የሚለው ያቃፌው አረፍተ ነገር ግሳዊ ሀረግ፣ ከታህታይ ቦታው ተነስቶ ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ መሄዱ እና እሱንም ተከትሎ የአዛማጁ አረፍተ ነገር ባለቤት እንደዚሁ ከመሰረታዊ ቦታው ተነስቶ አፅንዖት ሊያገኝ ወደሚችልበት ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ መሄዱ ነው፡፡ ዝርዝሩን እንደሚከተለው እናሳያለን፡፡


11
አነ'
ስሀ_k
አነ'
አስቴር
ግሀ_i
አነ
ምንድን ነው
ስሀ
ግሀ_i
አነ
ስሀ2
አነ
ሞይ_j
ስሀ1
ስሀ_k
ግሀ
የሰበረችው
ስ
....
ግሀ1
ስሀ
ግ_j
ስ
—
...

በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ተሳቢው ስማዊ ሀረግ ስለተዛመደ፣ ቦታው በሶስት ነጥብ ተሸፍኖአል፡፡ የተዛመደ ሀረግ በግሀድ እንደማይታይ ቀደም ሲል ገልፀናልና፡፡ የዚሁ የአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ ሰበረችው የሚለው ሲሆን፣ እሱም ከቦታው ተነስቶ ወደ ሞዱ ቦታ በመሄድ ከ/የ/ ጋር ተገናኝቶአል፡፡ ምንድን ነው? የሚለው ግሳዊ ሀረግ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ታሀታይ ቦታውን ለቆ ወደ አረፍተ ነገሩ መነሻ በመሄድ የተሻለ አፅንዖት ሊያገኝ ችሎአል፡፡ ይሁን እንጅ አስቴር የሚለው ባለቤት ስማዊ ሀረግም በዚሁ በአፅንዖት ምክንያት መሰረታዊ ቦታውን ለቆ፤ ምንድን ነው? የሚለውን ግሳዊ ሀረግ አቋዋርጦ በመሄድ፣ እሱም ከፍተኛውን የአፅንዖት ቦታ ሊይዝ ችሎአል፡፡ [illegible] እና [illegible] ሀረጎቹ የነበሩበትን መሰረታዊ ቦታና አሁን ያረፉበትን አፅንኦታዊ ቦታ ለማመልከት፤ እንዲሁም አፀፋዎችን ከየሀረጎቻቸው ጋር ለማጣቀስ የገቡ ምልክቶች ናቸው፡፡

ከፍ ሲል ያየነው ጥያቄ ምንድን? የሚል ነበር፡፡ ከዚህ ቀጥለን ደግሞ እነማን በሚለው መጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት የሚመሰረትን ውስብስብ ጥያቄ እንመለከታለን፡፡

አስቴርን የሰድብ-ኡ-አት (የሰደቡዋት) እነማን ናቸው? 12

ይህ አረፍተ ነገር አስቴርን የሰደቡአት የሚለው መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግና እነማን ናቸው? የሚለው ግሳዊ ሀረግ ቅንጅት ነው፡፡ አስቴርን የሰደቡአት የሚለው ስማዊ ሀረግ መሪ፣ ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ በግሀድ አይታይም፡፡ ይሁን እንጅ፣ ይዘቱን ሰደቡአት ከሚለው ግስ ላይ ከሚታየው የባለቤት አፀፋ፣ ማለትም ከ/-ኡ/፣ ማወቅ ይቻላል፡፡ ይህ አፀፋ የሶስተኛ መደብ፣ የብዙ ቁጥር የሆነ ባለቤትን ስለሚጠቁም፣ ከዚሁ በመነሳት ስማዊ ሀረጉን ከነመሪው እንደሚከተለው አድርገን በግሀድ ልናስቀምጠው እንችላለን፡፡

አስቴርን የሰደቡአት ልጆች 13

በዚህ ሀረግ ውስጥ፣ አስቴርን የሰደቡአት የሚለው ክፍል፣ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ተዛማጁ ስማዊ ሀረግ በአፀፋ ብቻ የተጠቀሰው፣ የብዙ ቁጥር ሀረግ ነው፡፡ አስቴርን የሰደቡአት እነማን ናቸው? በሚለው ውስጥ፣ አፅንዖቱ ያለው፣ በባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ላይ ነው፡፡ በአረፍተ ነገሩ መነሻ ላይ የሚገኘው እሱ ነውና፡፡ ግሳዊ ሀረጉ አፅንዖትን እንዲያገኝ ከፈለግን፣ ከታሀታይ ቦታው አንስተን፣ ከአቃፊው አረፍተ ነገር በማስወጣት፣ ከፍ ሲል ባየነው የርዕስ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ይኖርብናል፡፡ ይህን ስናደርግ ጥያቄው፣

እነማን ናቸው አስቴርን የሰደቡአት...? 14

የሚል ይሆናል፡፡ <u>የሰደቡአት</u> ከሚለው ግስ ቀጥሎ የሚታየው ነጠብጣብ የሚያመለክተው፣ <u>እነማን ናቸው</u>? የሚለው ግሳዊ ሀረግ የነበረበትን መሰረታዊ ቦታ ነው፡፡ ከዚህ ተነስቶ ነው፣ የአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ ሊሆን የቻለው፡፡ አካሄዱን አሁንም እንደሚከተለው በዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡

15



እስካሁን ያየናቸው ጥያቄዎች ተሳቢ ወይም ባለቤት ስማዊ ሀረግን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ መጠይቅ ተዋላጠ ስሞቹም ምን(ድን) እና (እነ)ማን የሚሉት ናቸው፡፡ ከዚህ ቀጥለን ተውሳከ ግሳዊ ጥያቄዎችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህም እንደሚከተሰው ያሉ ናቸው፡፡

አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው ለምንድን ነው? 16

ይህ ጥያቄ አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችበትን ምክንያት ወይም ዓላማ የሚጠይቅ ተውሳከ ግሳዊ መዋቅር ነው፡፡ የተጠየቀውም ለምንድን በሚለው መስተዋድዳዊ መጠይቅ ሀረግ ነው፡፡ ስዚህ አይነቱ ጥያቄ የሚሰጠው መልስም እንደዚሁ መስተዋድዳዊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡ ለጥያቄው የተሰጠው መልስ፣

አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው ለጨዋታ ነው 17

የሚል ቢሆን፣ ለምን የሚለው መስተዋድዳዊ ጥያቄ፡ ለጨዋታ በሚል መስተዋድዳዊ ሀረግ እንደተመለሰ እንረዳለን፡፡ መስተዋድዳዊ ሀረጎች ደግሞ፣ በሀረግ ክፍል በስሬው እንደተገለፀው፣ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ፣ አብዛኛውን ጊዜ በአጎላማሽነት፣ አንዳንድ ጊዜ በመሙሊያነት የሚገቡ መዋቅሮች ናቸው፡፡ ይህም እንደየግሱ ባህሪ የሚወሰን ነው፡፡ ከዚህ አኳዋያ ሲታይ፣ አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው ለጨዋታ ነው የሚለው ውስብስብ አረፍተ ነገር በተራ አረፍተ ነገር ቢነገር፣

አስቱር ለጨዋታ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች 18

የሚል ይሆናል፡፡ ለጨዋታ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች የሚለውን ንዑስ ግሳዊ ሀረግ አጎላምሶ እንደገባ በግልፅ ይታያል፡፡ ለምድን ነው? በሚል መልክ በአፅንዖት የተጠየቀውም ይኸው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው፡፡

አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው 19

የሚለው መሪ-አልባ የሆነ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ በውስጡ የተዛመደ ሀረግ አለ፡፡ ሀረጉም እንደማንኛውም ተዛማጅ ሀረግ ድምፅ-የለሽ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ይዘቱ የሄደችው ከሚለው ግስ መድረሻ ላይ ከሚታየው አፀፋ፣ ማለትም ከ ው (/-ኡ/) ይታወቃል፡፡ ሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ፆታ ነው፡፡ ከባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ጋርም በትርጉም አንድ ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የመጠይቁን አረፍተ ነገር ታህታይ መዋቅር እንደሚከተለው አድርገን እናሳያለን፡፡




ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም የአቃፊው አረፍተ ነገር ባለቤት የይስሙላው ተውላጠ ስም ሊሆን አይችልም ወይ? የሚል ነው፡፡ ጥያቄው

ተገቢ ነው፡፡ በርግጥም የአረፍተ ነገሩ ባለቤት ይህ ተውላጠ ስም ሲሆን ይችላል፡፡ ይህ ተውላጠ ስም ድምፅ-የለሽ መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡ ነ-ው በሚለው ግስ መድረሻ ላይ የሚታየው አፀፋ፣ ማለትም /-ኡ/ ይህንኑ ተውላጠ ስም ሊያመለክት ይችላል፡፡ በተጨማሪም ነው በሚለው ግስ ፋንታ ይ-ሆን የሚለውን የሁነት ግስ ብንጠቀም፣ ቀደም ሲል ያየነውን፣ /ይ-/ የሚለውን የድምፅ-የለሽ ተውላጠ ስም አፀፋ እናገኛለን፡፡ ይህ ውነት ከሆነ፣ አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው የሚለው መራ-አልባ ስማዊ ሀረግ፣ የግሳዊ ሀረግ አካል ነው፤ ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ሀረጉ ተውሳከ ግሳዊ ስም ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የአረፍተ ነገሩ ታህታይ መዋቅር የሚከተለውን መምሰል ይኖርበታል፡፡

21




በግልፅ እንደሚታየው፣ አስቴር ወደ ትምህርት ቤት የሄደችው የሚለው መራ-አልባ ስማዊ ሀረግ ከግሳዊ ሀረግ (ግሀ2) እንጉዋ ላይ ወርዶአል፡፡ ገላጭነቱ

iii (ሀ) አስቴር የሄደች-<u>በት</u> <u>ሀገር</u> የት ነው?
(ለ) አስቴር የሄደች-<u>ው</u> <u>ወዴት</u> ነው?

iv (ሀ) አስቴር የመጣች-<u>በት</u> <u>ሀገር</u> የት ነው?
(ለ) አስቴር የመጣች-<u>ው</u> <u>ከየት</u> ነው?

ከየጥንዱ ምሳሌ በግልፅ እንደሚታየውና ከፍ ሲልም እንደተገለፀው፣ ተዛማጁ መስተዋድዳዊ ሀረግ /-<u>በት</u>/ በሚለው አፀፋ በሚጠቀሰበት ጊዜ፣ ስማዊ ሀረጉ ከነመሪው ይከሰታል፡፡ በዚህን ጊዜም ጥያቄው በመጠይቅ ተውላጠ ስም አማካኝነት ይገለፃል፡፡ ተዛማጁ ሀረግ <u>ው</u> (<u>/-ኡ/</u>) በሚለው አፀፋ በሚጠቀሰበት ጊዜ፣ ስማዊ ሀረጉ ያለመሪ ይከሰታል፡፡ ጥያቄውም በመስተዋድድ ሀረግ አማካኝነት ይጠየቃል፡፡ ከዚህም የጥያቄውን አይነት የሚወስነው፣ የአፀፋው አይነት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ አፀፋው መስተዋድዳዊው /-በት/ ሲሆን፣ ጥያቄው ስማዊ ይሆናል፤ አፀፋው ስማዊው <u>ው</u> (/-ኡ/) ሲሆን፣ ጥያቄው መስተዋድዳዊ ይሆናል፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር ደግሞ፣ እንደ ምሳሌ 24(ለ) እና (መ) ያለ ተቀባይነት የሌለው አረፍተ ነገር ይከተላል፡፡

(ሀ) አስቴር የሄደችው ለምንድን ነው? 24
(ለ) *አስቴር የሄደችው ምንድን ነው?
(መ) አስቴር የሄደችበት ምክንያት ምንድን ነው?
(ሰ) *አስቴር የሄደችበት ምክንያት ለምንድን ነው?

ሁኔታው ተዛማጁ ሀረግ መስተዋድዳዊ ሲሆን፣ መሙሊያው ስማዊ ሀረግ እንደሚሆን፣ እንዲሁም ተዛማጁ ሀረግ ስማዊ ሲሆን፣ መሙሊያው መስተዋድዳዊ ሀረግ እንደሚሆን ያሳያል፡፡ ከዚህም ተዛማጅ መስታወድዳዊ ሀረግና መሙሊያ ስማዊ ሀረግ ተወራራሽ አገባብ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ፣ ይህ አይነት ተወራራሽነት የሚታየው ከላይ እንደሚታዩት ባሉ ኢሳቢ ግሳዊ ሀረጎች መሪነት በሚዋቀሩ መጠይቅ አረፍተ ነገሮች ውስጥ ነው፡፡ ግሳዊ ሀረጎቹ ሳቢ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ሁኔታው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

(ሀ) አስቴር የበላችው ለምንድን ነው? 25
(ለ) አስቴር የበላችው ምንድን ነው?

የመጀመሪያው መጠይቅ አረፍተ ነገር ገላጭ መሰተዋድዳዊ ሀረግን የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው መሙሊያ ሰማዊ ሀረግን የሚመለከት ነው፡፡ ሁለቱም ተቀባይነት አላቸው፡፡ ከዚህም የኢሳቢ ግሶች መጠይቅ መሰተዋድዳዊ መሆኑን፣ የሳቢ ግሶች ግን ገላጭ መሰተዋድዳዊ ሀረግ ብቻ ሳይሆን፣ መሙሊያ ሰማዊ ሀረግ እንደሚሆን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ልዩነት ከግሶቹ መዋቅራዊ ባህሪ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሳቢ ግሶች ብቻ ሰማዊ ሀረግ መሙሊያ ይፈልጋሉና፡፡

እሳካሁን ያየናቸው አረፍተ ነገሮች መጠይቅ ናቸው፡፡ ተራ ሳይሆኑ፣ ውስብስብ ናቸው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ጥያቄውን በአፅንዖት ለመጠየቅ የምንጠቀምበት አዛማጅ አረፍተ ነገር ራሱ ውስብሰበ መሆኑ ነው፡፡ ለውስብስብ መጠይቅ ሀረጎች ወይም ለእልት ሀተታዊ አረፍተ ነገሮች የሚሰጠው መልሰም እንደዚሁ ያለ አፅኖዖትን ለሰሚፈልግ ውስብስብ ነው፡፡ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

(ሀ) እሰቱርን የሰድብናት እኛ ነን 26
(ለ) ትናንት የመጣው ማን ነው?

እንደነዚህ ያሉ መጠይቅ አረፍተ ነገሮች በማንኛውም ሳይሆን፣ በተለየ አውደ-ነገር የሚነገሩ ናቸው፡፡ አውዱም በአፅንዖት የሚጠየቅ ጥያቄ ወይም በሀሰት የሚነገር ሀተታ ነው፡፡ ጥያቄው፣

አሰቴርን የሰደባት ማን ነው? 27

የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ሀተታው ደግሞ፣

ትናንት የመጣሁት እኔ ነኝ 28

የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚሀ አውድ ስንነሳ፣ 26(ሀ) ለ(27) የሚሰጥ መልሰ ነው፡፡ (28) ደግሞ ለ26(ለ) የሚሰጥ ተገቢ ምላሽ ሊሆን ይችላል፡፡

የእንደነዚሀ ያሉ አረፍተ ነገሮች መዋቅር ቀደም ሲል ካየናቸው ውሰብሰብ መጠይቃዊ አረፍተ ነገሮች መዋቅር ጋር አንድ ነው፡፡ አንድነቱን <u>አሰቴርን የሰደብናት እኛ ነን</u> በሚለው ምሳሌ አማካኝነት በሚከተለው ዕፀ-መዋቅር እናሳያለን፡፡

29




ከዕፀ-ዋቅሩ እንደሚታየው፣ <u>እስቴርን የሰደብናት</u> የሚለው ክፍል፣ አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው። አገባቡ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ መሪ-እልባ ስማዊ ሀረግን

በማጎላመስ ነው፡፡ ይህ ስማዊ ሀረግም ቀደም ሲል እንዳየናቸው ሌሎች ተመሳሳይ ሰማዊ ሀረጎች፣ መሪው በግሀድ አይታይም፡፡ ይሁን እንጅ፣ ይዘቱ መጀመሪያ ስደብ-ን ከሚለው ከአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ መድረሻ ላይ፣ ከዚያም ነ-ን ከሚለው ከአቃፊው አረፍተ ነገር የሁነት ግስ መድረሻ ላይ ከሚታየው የአንደኛ መደብ የብዙ ቁጥር የባለቤት አፀፋ፣ ማለትም ከ/-ን/፣ ይታወቃል፡፡ ይህ አፀፋ አንደኛ መደብ፣ ብዙ ቁጥር የሆነ ባለቤትን ይጠቁማልና፡፡ ከዚህም ነን በሚለው የሁነት ግስ ከሚመራው ግሳዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ አረፍተ ነገሩን የመሰረተው ባለቤት፣ ይህ መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም ስማዊ ሀረግ፣ የግሳዊ ሀረግ መሙሊያ ከሆነው እኛ ከሚሰው አሀድ ጋር በትርጉም አንድ ነው፡፡ ይህም ማለት መሪ-አልባው ስማዊ ሀረግና መሙሊያው ስማዊ ሀረግ የሚጠቁሙት ነገር አንድ ነው፡

በአዛማጁ አረፍተ ነገር ውስጥ የተዛመደው ክፍል ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ሀረግ በግሀድ አልተከሰተም፤ ሊከሰትም አይችልም፡፡ ማንኛውም የተዛመደ ሀረግ በአፀፋ ይጠቀሳል እንጅ፣ ግሀድ እንደማይወጣ ቀደም ሲል ገልፀናል፡፡ ስደብ-ን-አት በሚለው ግስ ላይ የሚታየው /-ን/ የሚለው አፀፋ ተግባር በግሀድ ሊወጣ ያልቻለውን ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ ማንነት መጠቆም ነው፡፡ የዚህ ተዛማጅ ስማዊ ሀረግ መሪ እንደ ተማሪዎች ያለ የብዙ ቁጥር የወል ስም ሊሆን ይችላል፡፡ ስሙ እኛ ከሚለው መስተዓምር ተውላጠ ስም ጋር ሲዋቀርና በግሀድ ሲከሰት የሚከተለውን ሊይመስል ይችላል፡፡

*[[እኛ ተማሪዎች] አስቴርን የሰደብ-ን-አት] 30

ይህ ስማዊ ሀረግ ተቀባይነት የለውም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የተዛመደው ባለቤት ስማዊ ሀረግ በግሀድ መከሰቱ ነው፡፡

በግልፅ እንደሚታየው ስደብ-ን-አት በሚለው ግስ አምድ መድረሻ ላይ የሚታየው /-ን/ የሚለው ምዕላድ የሚጠቁመው እኛ የሚለውን የስማዊ ሀረጉን ተውላጠ ስማዊ መሰተዓምር ነው፤ ተማሪዎች የሚለውን የሀረጉን መሪ ስም አይደለም፡፡

ከዚህ ስማዊ ሀረግ ጋር የተዋቀረውና እኛ ነን የሚለውን ግሳዊ ሀረግ በለዋጭ ህግ አማካኝነት ከመሰረታዊ (ታህታይ) ቦታው በማንሳት አፅንዖት ሊያገኝ ወደሚችልበት ቦታ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህ የአፅንዖት ቦታም ደጋግመን እንደገለፅነው፣ የአረፍተ ነገሩ ቅድመ-መነሻ ነው፡፡ ይህ ቦታ አፅንዖት ለማግኘት የሚንቀሳቀሱ ሀረጎች ማረፍያ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት እኛ ነን የሚለው ግሳዊ ሀረግ ወደዚህ ቦታ ሲመጣ፣ ከላይ በተራ ቁጥር (29) የተገለፀው ዕፀ-መዋቅር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

31




እነሆ፣ <u>እኛ ነን</u> የሚለው ግሳዊ ሀረግ በነጠብጣብ (...) ከተመለከተው ታሀታይ ቦታው ተነስቶ፣ የአረፍተ ነገሩን ባለቤት አቁዋርጦ፣ ከአረፍተ ነገሩ (አነ)

በመውጣትና ከእሱም ጋር በመዋቀር፣ (እኑ) የሚለውን መዋቅር ፈጥሮአል፡፡ ከዚህ መዋቅር ግራ ጎን በመግባትም ከፍተኛውን ስፍራ ሊይዝ፣ ብሉም የዕፀ-መዋቅሩ ቁንጮ ሊሆን ችሉአል፡፡

በተራ ቁጥር (28) የተመለከተውን ምሳሌ ደግሞ እንመልከት፡፡ ምሳሌው፣

ትናንት የመጣሁት እኔ ነኝ 32

የሚል ነው፡፡

በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ነ-ኝ የሚለው የሁነት ግስ ትናንት የመጣሁት ከሚለው መሪ-አልባ ስማዊ ሀረግ ጋር ተዋቅሮ፣

ትናንት የመጣሁት ነኝ 33

የሚለውን ግሳዊ ሀረግ መስርቶአል፡፡ ይህ ግሳዊ ሀረግ ደግሞ እኔ ከሚለው ስማዊ ሀረግ ጋር ተቀናጅቶ፣

እኔ ትናንት የመጣሁት ነኝ 34

የሚለውን አረፍተ ነገር አዋቅሮአል፡፡

ትናንት የመጣሁት 35

የሚለው አዛማጅ አረፍተ ነገር ነው፡፡ አገባቡም ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ መሪ-አልባ የሆነን ስማዊ ሀረግ በማጎላመስ ነው፡፡ የዚህ አዛማጅ አረፍተ ነገር ባለቤት በግሀድ አይታይም፡፡ ለዚሀም ምክንያቱ ግልፅ ነው፡፡ ተዛማጁ ሀረግ ራሱ ነው፡፡ የመጣሁት በሚለው ግስ ላይ /-ሁ/ የሚለው አፀፋ የሚያመለክተው ይህንኑ ተዛማጅ ባለቤት ሀረግ ነው፡፡ አንደኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ባለቤት ስማዊ ሀረግ ነው፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል፡፡ ይኸውም የመጣሁት በሚለው ግስ መድረሻ ላይ የምትታየው /-ት/ ምንን ታመለክታለች? የሚል ነው፡፡ በቅርፅዋ የተሳቢ አፀፋ ትመስላለች፡፡ መጣ የሚለው ግስ ግን ሳቢ አይደለም፡፡ ስለዚህም ከተሳቢ ስማዊ ሀረግ ጋር ሊዋቀር አይችልም፡፡ ባጭሩ በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ተሳቢ ሀረግ ሊኖር አይችልም፡፡ ከሌለ፣ ለለተሳቢ አፀፋ ማንሳት አይቻልም፡፡ "ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ" ይሆናልና፡፡

ታዲያ ምዕሳድዋ ምንድን ነኝ ባይ ነች? ምዕሳድዋ የተሳቢ አፀፋ ትምሰል እንጅ፣ በውንስ አይደለችም፡፡ በዚች ምዕላድ ወይም የእለዋ ተለዋጭ በሆነው በ/-እ/ አማካኝነት የሚገለፁ የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ተግባራት አሉ፡፡ ከእነሱም መካከል ዕምርነት፤ የሶስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ አገናዛቢነት፤ የሶስተኛ

ስማዊ ሀረግ አፀፋ ነች። በምሳሌ (መ) /-ት/ የተሳቢው አፀፋ ስትሆን፣ ከእስዋ ቀጥላ የገባችው /-ኡ/ ተውላጠ መሪ ነች። የሚከተለውን ደግሞ እንመልከት።

ትናንት የሰደብኩት (የሰደብ - ኩ - ት) ልጅ 39

በዚህ ምሳሌ ውስጥ የምትታየው /-ት/ የትኛዋ /-ት/ ነች? ተዛማጁን ስማዊ ሀረግ የምትጠቁመው? ተውላጠ መሪዋ? ወይስ መስተዓምርዋ /-ት/? መጀመሪያ /-ት/ የ/-ኡ/ ተለዋጭ መሆንዋን እንርሳ። /-ኡ/ ከሌላ /-ኡ/ በሁዋስ ስትገኝ ወደ /-ት/ ትለወጣለች።

ተውላጠ መሪዋ /-ት/ ልትሆን አትችልም፤ ምክንያቱም መሪው ስም ማለትም ልጅ በግሀድ ይታያልና። ከፍ ሲል እንደገለፅነው፣ ይህች ተውላጠ መሪ ምዕላድ የምትከሰተው የተዛመደው ስማዊ ሀረግ መሪ በግሀድ በማይታይበት ጊዜ ነው። ተውላጠ መሪዋ ካልሆነች፣ ልትሆን የምትችለው አንድም የተሳቢው ሀረግ አፀፋ፣ አለያም መስተዓምርዋ ት < /-ኡ/ ነው። መስተዓምርዋ ልትሆን አትችልም፤ ምክንያቱም መስተዓምርዋ ት ከሆነች፣ ተዛማጁ ስማዊ ሀረግ በአፀፋ አልተጠቀሰም ማለት ነው። በአፀፋ ያልተጠቀሰ ተዛማጅ ተሳቢ ሀረግን የያዘ ስማዊ ሀረግ ደግሞ ተቀባይነት የለውም። ስለዚህም፣

* ትናንት የሰደብኩ ልጅ 40

ማለት አይቻልም። ይህ ከሆነ፣ -ት የተዛማጁ ስማዊ ሀረግ ጠቃሽ መሆን አለባት። ርግጥ፣ ይህች ምዕላድ ቀደም ሲል እንደገለፅነው፣ ከተውላጠ መሪውና ከመስተዓምርዋ -ት ጋር በቅርፅ አንድ ነች። ስለዚህም ልንደናገር እንችላለን። ይሁን እንጅ፣ መስተዓምርዋ -ት ከተውላጠ መሪው ወይም ከተሳቢው አፀፋ ቀጥላ ትገባለች። ይህም በአንዳንድ የገጠር ቀበልኛ ነው፤ ለምሳሌ በወሎ። ይህ ሲሆን ሀረጉ፣

ትናንት የሰደብኩቱ (ሰደብ- ኩ - ት - ኡ) 41

የሚል ይሆናል።

ተውላጠ መሪዋ -ት የምትገኘው መሪ-አልባ በሆነ ስማዊ ሀረግ ውስጥ ነው ብለናል። ለዚህ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ትናንት የመጡት (መጥ - ኡ - ት) 42

በዚህ ሀረግ ውስጥ፣ የተዛመደው፣ ባለቤቱ ስማዊ ሀረግ ነው። በመሆኑም በግሀድ አይታይም፤ /-ኡ/ በሚለው አፀፋ ግን ተጠቅሶአል። ከዚህ አፀፋ ቀጥሎ የሚታየው ምዕላድ፣ ማለም -ት የሚጠቁመው አዛማጁ አረፍተ ነገር

የሚያጎላምሰውን ስማዊ ሀረግ መሪ ስም ነው፡፡ ስለዚህም የመሪው ተውላጥ ነው፡፡ ተውላጠ መሪ ያልነውም ስዚሁ ነው፡፡ ከሱ ቀጥሎ መስተዓምሩን /-ኡ/ በማስገባት፣

ትናንት የመጡቱ (መጥ- ኡ - ት -ኡ) 43

ማለት እንችላለን፣ ቢያንስ ከፍ ሲል በጠቀስነው ቀበልኛ፡፡

ከዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ይኸውም የመስተዓምሩን አገባብ የሚመለከት ነው፡፡ ስለ ስማዊ ሀረግ ስንወያይ፣ መስተዓምር የሚገኘው መሙሊያዎችንና አጎላማሾችን ቀድሞ በሀረግ መነሻ ላይ እንደሆነ ገልፀን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ከዚህ ላይ እንደሚታየው፣ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ መድረሻ ላይ እየገባ ይገኛል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በስማዊ ሀረጉ መነሻ፣ ሌላ ጊዜ በግሱ መድረሻ ላይ ሊገባ ይችላል ማለት ነው? ስዚህ መልሳችን "አወን ይችላል" የሚል ነው፡፡ በሀረጉ መነሻና በግሱ መድረሻ የሚገባው መስተዓምር ግን አይነቱ ለየቅል ነው፡፡ በሀረጉ መነሻ የሚገባው እንደ ይህ፣ ያ፣ ወዘተ፣ ያለ ነፃ መስተዓምር ሲሆን፣ በግሱ መድረሻ ላይ የሚገባው እንደ /-ኡ/ ወይም /-ኡ/-እ/ (ዋ) ያለ ጥገኛ መስተዓምር ነው[13]፡፡ ጥገኛ ስለሆነ፣ ቀድሞት ከሚገኘው መሪ ቃል ላይ ይጠጋል፡፡ መሪው ቃል ገላጭ ሀረግ ካለው፣ ከገላጩ መሪ ቃል ላይ ያርፋል፡፡ ሁኔታውን በሚከተሉት ምሳሌዎች እናሳያለን፡፡

(ሀ) ልጁ (ልጅ-ኡ) 44
(ለ) ትልቁ (ትልቅ-ኡ) ልጅ
(መ) ትናንት የመጣው (የመጥ-አ-ኡ) ትልቅ ልጅ

በመጀመሪያው ምሳሌ፣ መስተዓምሩ ልጅ የሚለውን ስም ተጠግቶ ገብቶአል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ ልጅ የሚለውን ስም አልፎ በገላጩ ቅፅል መድረሻ ላይ ይገኛል፡፡ በሶስተኛው ምሳሌ ደግሞ ቅፅሉንም አልፎ በአዛማጁ አረፍተ ነገር ግስ መድረሻ ላይ ገብቶአል፡፡ የመስተዓምሩ ታህታይ አገባብ ስማዊ ሀረጉን ተከትሎ ነው፤ ለማለት ይቻላል፡፡ ሀረጉ ገላጭ ሲኖረው ብቻ ወደ መጀመሪያው ገላጭ ይሸጋገራል ብሎ፣ ማጠቃለል ይቻላል፤ ለጊዜው፡፡

ስለ ሀረግ ስንወያይ መስተዓምር ስማዊ ሀረግን በመሙሊያነት እየያዘ መስተዓምራዊ ሀረግ እንደሚፈጥር ገልፀን ነበር፡፡ በዚያ አመለካከት መሰረት፣ በተራ ቁጥር (44) የተመለከቱት መዋቅሮች ስማዊ ሳይሆኑ፣ መስተዓምራዊ

[13] ጉዳዩ /ኡ-/ን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን እንደ /-ኧኛ/ ያሉትን ምዕላዶችም ይጨምራል፡፡ እነዚህም እንደ፡

ይኸኛው (ይኸ-ኧኛ-ኡ) ልጅ

ይህችኛዋ (ይኽ-ች-ኧኛ-ኡ-እ) ልጅ

ስንል ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታውን ወደፊት በሌላ ፅሁፍ እናሳያለን፡፡

ሀረጎች መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ከሆነ አወቃቀራቸውን እንደሚከተለው አድርገን በዕፀ መዋቅር እናሳያለን፡፡

45



በግልፅ እንደሚታየው፣ የመስተዓምራዊው ሀረግ መሪ /-ኦ/ ነው። እንደማንኛውም መሪ ቦታው በመሙሊያው ስማዊ ሀረግ ቀኝ ጎን ነው። ስማዊ ሀረጉ ገላጭ ሲኖረው፣ ከመጀመሪያው ገላጭ ጋር ይዋቀራል። ገላጭ ከሌለው ከመሪው ስም ላይ ይለጠፋል። እንዴት እንደሚለጠፍ ወደፊት በሰፊው እናሳያለን። ምናልባትም፣ የመስተዓምሩ ቦታ ከላይ እንደሚታየው በቀኝ በኩል ላይሆን ይችላል። ለጊዜው በዚህ እንተወው።

እንግዲህ በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ ስለ ውስብስብ አረፍተ ነገር በዝርዝር የተመለከትነውን እንደሚከተለው እናጠቃልና እንለያይ። ውይይታችን ያተኮረው በአፅንዖታዊ አረፍተ ነገሮች ላይ ነው። እነዚህም በአንድ በተለየ አውደ-ነገር ላይ በሚነሱ ጥያቄዎችና በመልሶቻቸው ላይ የሚያተኩሩ አረፍተ ነገሮች ናቸው። ተራ ሳይሆኑ፣ ውስብስብ ናቸው። ውስብስብ የሚሆኑበት ምክንያት በውስጣቸው አዛማጅ አረፍተ ነገር ስለሚይዙ ነው። የአዛማጁ አረፍተ ነገር መሪ በግሀድ ላይከስት ይችላል። በአፀፋ ግን ይጠቀሳል። ከዚህም ይዘቱ ይታወቃል። የአፀፋው ቅርፅ ከመስተዓምሩ /-ኦ/ ጋር አንድ ነው።

በእንደዚህ ያሉ አረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙ ስማዊ ወይም ግሳዊ ሀረጎች ከመሰረታዊ (ታህታይ) ቦታቸው እየተነሱ ከአረፍተ ነገሩ በመውጣት፣ ሌሎቹን የአረፍተ ነገር ክፍሎች እየቀደሙ ሊገቡ ይችላሉ። ይህን በማድረግም አፅንዖት ያገኛሉ። እንደነዚህ ያሉ ሀረጎች ተራ ሳይሆን፣ ዋና ሀሳብን ያዘሉ ናቸው። ስለዚህ የተለየ አቀራረብን፣ ማለትም የሀረግ አወቃቀርን ይጠይቃሉ። በዚህ ክፍልም ያየነው፣ ይህንኑ ከተራው ለየት ያለ የአወቃቀር ስርዓትን ነው።

በመጨረሻም፣ በዚህ መፅሀፍ፣ ከድምፅ ጀምረን፣ በቃላት ክፍሎች አድርገን፣ ሀረጎችንና አረፍተ ነገሮችን እየተመለከትን ከዚህ ደርሰናል። በጉዞአችን ላይ ለማየት የሞከርነውን ወደሁዋላ መለስ ብለን ብናስተውለው፣ ከአንድ ቤት ስራ ጋር ተመሳሳይ ነው። አንድ ቤት፣ መሰረት፣ ጣሪያና ግድግዳ ይኖረዋል። ያለመሰረቱ ግድግዳው፣ ያለግድግዳው ጣሪያው ፊፅሞ ሊታሰብ አይችልም። ሶስቱም በተናጠል ሳይሆን፣ በህብረት ተደጋግፈው ቤቱን ማቆም አለባቸው። ከዚያ በመለስ ያለው የመልክ ጉዳይ ነው።

አረፍተ ነገሮችን እንደቤት ልንቆጥራቸው እንችላለን። መሰረታቸው ድምፅ ነው። በዚህ ረገድ በክፍል አንድ የ30 ተናባቢና የ7 አናባቢ ድምፆችን አፈጣጠርና የአቀነጃጀት ስርዓት አይተናል። እነዚህ 37 ድምፆች ተናባቢ - አናባቢ - ተናባቢ በሚል ስርዓት ሲቀናጁ፣ ቀለምና ምዕላድ እንደሚፈጥሩ አይተናል። በየቀለሙና በየምዕላዱ ውስጥ፣ እንዲሁም በየድንበሩ ላይ በሚፈጠረው የድምፆች ንክኪ ምክንያት የሚከሰቱትን ልዩ ልዩ ድምፀ - ልሳናዊ ሂደቶችና ለውጦች ተመልክተናል። ለውጦቹ በአብዛኛው የመካነ እና/ወይም የባህርየ ንባብ ምስስሎሽ ናቸው።

በክፍል ሁለት የተመለከትነው በጥቅሉ የምዕላዶችንና፣ የቃላትን አይነትና የአፈጣጠር ስርዓት ነው፡፡ ቃላት እንደ ብሎኬት፣ ወይም እንደ ሸክላ አለያም እንደ ጠርብና ጨፈቃ ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ አፈጣጠራቸው ስነ-ድምፀ - ልሳዊና ስነ-ምዕላዳዊ ነው፡፡ ስነ-ምዕላዳዊ ስርዓታቸው በስር፣ በተለያየ አምድና ቅጣይ ምዕላዶች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በማንኛውም መንገድ የሚፈጠሩ ቃላት ልዩ ልዩ የርባታ ምዕላዶችን እያስከተሉ በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኙ ሀረጋትን መደብ፣ ቁጥር፣ ፆታ፣ ወሀተ፣ እንዲሁም የየግሱን የአንቀፅና የጊዜ አይነት እንዴት እንደሚያሳዩ ተገንዝበናል፡፡

በማንኛውም ሁኔታ የሚፈጠሩ ቃላት ርስበርስ ተያይዘውና ተደጋግፈው የሚፈጥሩዋቸው ሀረጎች እንደ ግድግዳ ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡ የሀረጎቹን አይነትና ይዘት ያየነው በክፍል ሶስት መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ ግድግዳውን ከሚፈጥሩት ሀረጎች መካከል ስማዊ ሀረጎችና ግሳዊ ሀረጎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ግንባር ለግንባር ተዋቅረው የቤቱን ጣሪያ የሚፈጥሩት እነሱ ናቸውና፡፡ ሌሎቹ ሀረጎች የእነዚሁ የሁለቱ አጎላማሾች ናቸው፡፡ ሀረጎቹ በቁዋንቁዋው የቃላት ክፍሎች አይነት ይወሰናሉ፡፡ ስድስት የቃላት ክፍሎችን አግኝተናል፡፡ በየክፍሎቹ ውስጥ በሚገኙ ቃላት አማካኝነት የሚፈጠሩ ስድስት አይነት ሀረጎችን አይተናል፡፡ እያንዳንዱ ሀረግ ከአንድ ቃላዊ መሪ፣ ከመሙሊያ፣ ከተለያዩ ገላጭ አጎላማሾችና መስተዓምሮች እንደሚመሰረት አይተናል፡፡ መሪው ቃል ሁል ጊዜ በስተቀኝ በኩል ይገኛል፡፡ በዚህም ቁዋንቁዋው ቀኝ መሪ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

አንድ ቤት ተራ ወይም ሰፊና ባለብዙ ፎቅ ሊሆን እንደሚችል ሁሉ፣ አንድ አረፍተ ነገርም እንደዚሁ ተራ ወይም ውስብስብ ሊሆን እንደሚችል አይተናል፡፡ ይህም የሚወሰነው በውስጡ በሚይዘው የሀረግ መጠን ነው፡፡ ብዙ ሀረግ የያዘ ውስብስብ ነው፡፡ ተግባሩም እንደዚሁ፡፡

ከመጀመሪያ አንስተን የቤቱን፣ ማለትም የአረፍተ ነገሩን መሰረተ ነገር የሆኑትን ድምፆች በመለየት፣ ከነዚሀ የሚፈጠሩትን ምዕላድና ቃላት፣ ማለትም ብሎኬቶችን በአይነት በአይነታቸው በመመደብ፣ ወደ ሁዋላም በእነሱ አማካኝነት የሚፈጠሩትን ሀረጎች በማያያዝና አንዱን ከሌላው በማዋቀር፣ የተለያዩ ቤቶችን፣ ማለትም አረፍተ ነገሮችን፣ ስንሰራ ቆይተናል፡፡ ቤቶች ለልዩ ልዩ ተግባር እንደሚውሉ ሁሉ፣ አረፍተ ነገሮችም እንደዚሁ ለልዩ ልዩ ተግባር ይውላሉ፡፡ ማተቻ፣ ማለቻ፣ መጠየቂያ፣ ማዘዣ፣ መቃወሚያ፣ ወሀተ፣ የሆነ ተግባር እንዳላቸው በሰፊው አይተናል፡፡ እንደ ተግባራቸው ልዩነት ቅርፃቸውም ይለያያል፡፡ የመመገቢያና የማብሰያ ቤት አንድ አይነት አይሆንምና፡፡ የማተቻና የማለቻ አረፍተ ነገሮችም እንደዚሁ አንድ አይነት አይሆኑም፣ እንዳልሆኑም በዝርዝር አይተናል፡፡

ወደፊት በሌላ ጊዜ እንገናኝ ይሆናል፡፡ እስከዚያው ግን ይህንኑ እየደጋገምን በማንበብ፣ ማንም ለራዩ ብሎ ሳያስተምረን፣ እኛም ለራዩ ብለን ሳንይዘው፣ ከእድሜ ዘመናችን እጅግ ውስን በሆነችው የልጅነት ጊዜአችን፤ ሳናውቀው ስላወቅነውና፣ በማወቅም ያለምንም ችግር፣ እድሜ ልክ ሳይስለቸንና ሳያልቅብን፤ በማንኛውም ጊዜና ቦታ፣ ለማንኛውም ጉዳይ፣ ከማንኛውም የእኛ ቢጤ ጋር ስለምንጠቀምበት ቋንቋ፣ ያለን ዕውቀት ምን እንደሆነና፤ መጠኑም ምን ያህል እንደሆነ? እንዴትስ እያደረግን እንደምንጠቀምበት እናሰላስል፡፡ በበኩሌ ባሰብኩትና ባሰላሰልኩት ቁጥር ግርም ይለኛል፡፡ ለየጥያቄው የማሰበው መልስም ዛሬ ቀኝ፤ ነገ ግራ እየሆነ ያስቸግረኛል፡፡ ለለዚህም ቀኝ ነው ያልኩት፤ ግራ ከመሆኑ በፊት ተሻምቼ የያዝኩትን በትንሹ አቅርቤአለሁ፡፡ ነገ እንደምለቀው ግን በጣም ርግጠኛ ነኝ፡፡ ሌላ ቀኝ ፍለጋ... ለዚያውም ከተገኘ፡፡

## መልመጃ

የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ታህታይ መዋቅር ያመልክቱ፡፡

1. እንደ ካሳ የተደሰተ ሰው እስካሁን አላየሁም፡፡
2. ማንንም እንዳላነጋገርኩ ለአስቴር ደብዳቤ ፃፍኩላት፡፡
3. ያች ትናንት በግ የገዛችው ሴት አስቴርን ሰደበቻት፡፡
4. ማን ነው ካሳ በግ ይገዛል ያለህ?
5. የአስቴር ቤት የመስራት አላማ ብዙ ሰው አስደስቶአል፡፡
6. ልጆቹ ቤት ለመስራት የፈለጉ ይመስላል፡፡
7. አንተ ልጅ ተው ብየሀለሁ፡፡
8. የት ነው አስቴር የሄደችው?
9. አቦ! ተው ክፉ አትናገር!
10. አቦ! የሚሰውን ምዕላድ የቃል ክፍልና ሰዋሰዋዊ ተግባር ይግለፁ፡፡

**መሙሊያ፣** አንድን ነገር በይዘቱ ሙሉ እንዲሆን የሚያደርግ ነገር፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ገደለ ብንል፣አረፍተ ነገሩ በጥቅል፣ ግሱ ደግሞ በተለይ የሚሰጠን ሀሳብ ሙሉ አይሆንም፡፡ ሙሉ የሚሆነው፣ እንደ አንበሳ ያለ ስማዊ ሀረግ ቀድሞት ሲገባና አረፍተ ነገሩም፣ ካሳ አንበሳ ገደለ የሚል ሲሆን ነው፡፡ ሙሉ የሚያደርገው አንበሳ የሚለው ስማዊ ሀረግ ስለሆነ፣ እንደዚህ ያለ ሀረግ መሙሊያ ይባላል፡፡ complement

**መላሽ፣** ወደሁዋላ፣ ማለትም ወደ ግራ የሚመልስ፣ አንድ ድምፅ ባህሪውን ቀድሞት ለሚገኝ ሌላ ድምፅ የሚያጋባበት የምስስሎሽ ሂደት፣ regressive

**መላምታዊ፣** በመላ፣ በግምት፣ ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ አመለካከት፣ hypothetical

**መሰራች፣** አንድን ቃል ከሌላ ቃል ላይ የሚፈጥር ወይም የሚመሰርት ምዕላድ፣ ለምሳሌ /-ኧት/ የሚለው ምዕላድ ብልጥ ከሚለው ቅዕል ላይ ብልጠት የሚል ስም ስለሚመሰርት መሰራች ምዕላድ ነው፡፡ derivational

**መስተዓምር፣** አንድን ነገር ከሌሎች ነገሮች ለይቶ የሚያሳይ ወይም የሚያሳውቅ ምዕላድ፣ specifier or determine

**መቼት፡** መቼ እና የት ከሚሉት ቃላት ላይ የተመሰረተ ቃል፡ አንድ ድርጊት የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ፡ setting

**መካነ-ፍጥረት፣** በአንደበት ውስጥ፣ አንድ ድምፅ የሚፈጠርበት ቦታ፣

**መዋቅር፣** ድምፅ ከድምፅ፣ ቃል ከቃል ወይም ከሀረግ፣ ወዘተ፣ ሲቀናጅ የሚፈጠረው ነገር፣ structure

**መዋዋጫ፡** ምግብ ከአፍ ወደሆድ የሚወርድበት ቱቦ፡ esophagus

**መጠነ-ስፋት፣** የአንድ ነገር ባህሪ የሚሸፍነው የሀረግ መጠን፣scope

**መጠነ-ወርድ፡** የአንድ ነገር የወርድ ርዝመት ወይም መጠን፣ linear size

**መጣኝ፣** የአንድን ነገር መጠን የሚያመለክት ቃል፣ ለምሳሌ ሁለት ተማሪዎች ስንል፣የተማሪቹን ስንትነት የሚጠቁመን ሁለት የሚለው አህዝ ነው፡፡ ስለዚህም መጣኝ መስተዓምር ነው፡፡ quantifier

**ማንቁርታዊ፣** ወደ ማንቁርት ድምፅነት የተለወጠ ወይም ማንቁርት ላይ የተፈጠረ ድምፅ፣glottalized

**ማለት፣** [ምእልልኧት] በአንድ ቦታ ወይም ወቅት መገኘት፣ አለሁ ማለት፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ርሳስ አለው ስንል፣ አለው የሚለው የማለት ግስ ነው፡፡ ነገሩ አከለ ብሎ ማከል ከተባለ፣ አለ ብሎም ማለት ሊባል እንደሚችል የሚያስረዳ ነው፡፡ verb to have

ማዕከል፣ የተለያዩ ነገሮችን አቅፎና ደግፎ የሚቆም፣ nucleus

ማዕከላይ፣ በባለቤት ስም ላይ የሚፈፀምን ድርጊት የሚያመለክቱ ግሶች፣ middle voice

ማዕቀፍ፣ እቅፎ የሚይዝና ከሌላ የሚለይ፣ frame

ምህፃር፣ ሙሉውን ቃል ወይም መዋቅር አሳጥሮ የሚያሳይ ምልክት፣ abbreviation

ምዕላድ፣ አንድ ትርጉም ያለውና አነስተኛ ወደሆነ ትርጉም አዘል አሀድ ሊከፈል የማይችል ቅርፅ፣ ለምሳሌ ቤት፣ morpheme

ምስስት፣ ተጎራባች ድምፆች ባህሪ የሚወራረሱበትና በዚህም ምክንያት የሚመሳሰሉበት ሂደት፣ assimilation

ምስረታ፣ አዳዲስ ቃላትን ከነባር ቃላት ላይ የመመስረት፣ የመፍጠር ሂደት፣ derivation

ምዝገባ ቃላት፣ ቃላትን በቅደም ተከተል ከነትርጉማቸው የመመዝገብና አጠቃቀማቸውንም የመግለፅ ተግባር፣ lexicography

ሞፈር ዘመት፣ ከመኖሪያ አካባቢ ርቆ የሚገኝ የእርሻ መሬት፣ far away farm

ሞይ፣ አንድ አረፍተ ነገር የአንድ መሪ ቃል መሙሊያ ሆኖ መግባቱን የሚያሳይ ምዕላድ፣ ለምሳሌ፣

ካሳ አስቴር እንደታመመች ሰምቶአል

በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ እንደ የሚለው ምዕላድ አስቴር ታመመች የሚለው አረፍተ ነገር ሰምቶአል ለሚለው ግስ መሙሊያ ሆኖ መግባቱን ያመለክታል። እንደዚህ ያለ ምዕላድ ሞይ ይባላል። complementizer

ሰበ-ነክ፣ ሰውን ብቻ ለይቶ የሚመለከት ባህሪ፣ human

ሰርን፣ ከአፍንጫ ቀዳዳ ጀምሮ እስከ እንጥል ድረስ ያለው ክፍት ቦታ፣ nasal cavity

ሰርጎት፣ በሁለት ነገሮች መካከል ጣልቃ የመግባት ሂደት፣ epenthesis

ሰረ-ገብ፣ ስር በሚመሰርቱ ተናባቢዎች መካከል የሚገባ፣ root internal

ሰርጎ-ገብ፣ በሁለት ነገሮች መካከል ፈልቅቆ የሚገባ፣ epenthetic

ሰርናዊ፣ አየር በሰርን በኩል አድርጎ ሲወጣ፣ አፍ ውስጥ የሚፈጠር ድምፅ፣ ለምሳሌ [ም] nasal

ሰርዓተ ቃላት፣ የቃላትን አጠቃላይ የርስበርስ ግንኙነት የሚገልፅ ህግ፣ lexical pattern or system

ሰምሙ፣ በባህሪ የሚጣጣም፣ የሚስማማ፣ matching

ስር፣ መስረት ወይም መነሻ፣ ለምሳሌ ከበደ ለሚለው ግስም ሆነ ከባድ ለሚለው ቅፅል መነሻ የሆነው /ክ-ብ-ድ-/ የሚለው

የሶስት ተናባቢዎች ቅንጅት ነው። እንደዚህ ያለ የተናባቢዎች ቅንጅት ስር ይባላል። root

ስነ-ልሳን፣ የቋንቋዎን ባህሪና አጠቃቀም የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ፣ linguistics

ስነ-ቃላት፣ የቃላትን የአፈጣጠር ስርዓት የሚመለከት የስነ-ልሳን ዘርፍ፣ morphology

ስነ-ድምፅ፣ የአንድን ቋንቋዎ ድምፆች የአፈጣጠርና የአቀነጃጀት ባህሪ የሚመለከት የስነ-ልሳን ዘርፍ፣ phonetics/phonology

ስነ-አዕምሮ፣ የሰውን ልጅ ባህሪና የአንጎልን ግንኙነት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ፣ psychology

ስነ-ዘዴ፣ የማስተማር ጥበብ፣ የምርምር አካሄድ፣ methodology

ሳቢ፣ የሚስብ፣ ተሳቢ ስማዊ ሀረግን በመሙሊያነት የሚፈልግ፣ transitive

ሰዋዊ፣ ሰውን የሚመለከት ተውላጠ ስም፣ ስምሳሌ አንተ፣ እኔ፣ ወዘተ፣ personal

ረቢ፣ ቅርፁን እየለዋወጠ ሲረባ፣ ሊበዛ የሚችል ቃል፣ productive

ርባታ፣ ቃላት የተለያዩ ሰዋሰዋዊ ባህሪያትን ለማሳየት ቅርፃቸውን በመጠኑ የሚለዋውጡበት ሂደት፣ inflection

ርዕስ፣ ለአረፍተ ነገርም ሆነ ለድርሰት መነሻ የሚሆን፣ በተለምዶ አርዕስት የምንለው ክፍል፣ topic

ርቱዕ፣ ከአንድ መሪ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ስማዊ ሀረግ፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ለአስቴር ገንዘብ ሰጣት በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ፣ ሰጣት ከሚለው ግስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው፣ ገንዘብ የሚለው ስማዊ ሀረግ ነው። ካሳ ከእጁ አውጥቶ የሚሰጠው ነገር እሱ ነውና። direct

ርግብግቢት ማንቁርት ውስጥ የሚገኙ ተርገብጋቢ ጡንቻዎች፣ vocal folds

ቀለም፣ የአንድ አናባቢ፣ ወይም የአንድ አናባቢና የተናባቢ(ዎች) ቅንጅት፣ syllable

ቀለማይ፣ የአንድ ቀለም ምሰሶ ሆኖ ሊገባ የሚችል ድምፅ፣ syllabic

ቀሪነት፣ በመዋቅር ውስጥ በቦታ ሳይገኙ የመቅረት ወይም የመገደፍ ችሎታ፣ optionality

ቀጣይ፣ ሲነበብ ትንፋሽ የማያስቆርጥ፣ continuant

ቀድሞ-ገብ፣ በቃል መነሻ ላይ ከተናባቢ ቀድሞ የሚገባ አናባቢ፣ prothetic

ቃለ-ጥያቄ፣ አንድ አረፍተ ነገር መጠይቃዊ መሆኑን የሚያመለክት ምዕላድ፣ question particle

ቅላጼ፣ የድምፅ ከፍታና ዝቅታ ማለት፣ intonation

| | |
|---|---|
| ተውላጥ፣ | ምትክ፣ እንድን ነገር ተክቶ የሚገባ፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳል ብለን፣ እንተስ? የሚል ጥያቄ ብናስከትል፣ እኔም እሄዳለሁ፣ የሚል መልስ ልናገኝ እንችላለን፡፡ እኔም በሚለው መልስ መድረሻ ላይ የምትታየው /-ም/፣ ወደ ትምህርት ቤት የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ምትክ ወይም ተውላጥ ነች፡፡ pro-form |
| ተውላጠ መሪ፣ | እንድን መሪ ቃል የሚተካ፣ የመሪ ምትክ፣ pro-head |
| ታህታይ መዋቅር፣ | በእንደበት የሚባል ሳይሆን፣ በአዕምሮ የሚታሰብ፣ የሚታወቅ መዋቅር፣ ለምሳሌ፣ ካሳ ተሰደበ ስንል፣ ካሳን የሰደበው ሰው እንዳለ ይሰማናል፡፡ አንድ ሰው ካሳን ሰድቦታል ማለታችን ነው፡፡ ግን ማን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ይህን ስሜት የሚይዝ መዋቅር ታህታይ ይባላል፡፡ ካሳ ተሰደበ የሚለው የዚህ ላዕላይ ወይም እንደበታዊ ቅርፅ ነው፡፡ deep structure |
| ትናጋዊነት፣ | አንድ የትናጋ ያልሆነ ድምፅ ወደ ትናጋ ድምፅነት የሚለወጥበት ሂደት፣ velarization |
| ትውረት፣ | theory |
| ትውፊት | ሳይፃፍ በቃል ብቻ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ህዝባዊ ባህል፣ folklore |
| ነባር፣ | የነበረ፣ የኖረ፣ base |
| ነቢበ-ነገር፣ | የሚነገር፣ ከእንደበት የሚወጣ ነገር፣ expression |
| ኑረት፣ | የመኖር፣ በአንድ ቦታ የመገኘት ሁኔታ፣ existence |
| ንበት፣ | አንድ ድምፅ የሚነበብበት ሁኔታ፣ pronunciation |
| ነዛሪ፣ | ማንቁርት ውስጥ የሚገኙት ተርገብጋቢ ጡንቻዎች ሲነዝሩ የሚፈጠር ድምፅ፣ voiced |
| ነጣይ፣ | አንድን ነገር ከሌሎች ነገሮች ነጥሎ፣ ማለትም ለይቶ፣ የሚያሳይ፣ singulative |
| ከፍናቢ፣ | ከፊል አናባቢ የሚለውን ሀረግ በማሳጠር የተፈጠረ አጭር ቃል፣ semi-vowel |
| ከፋች፣ | የቀለም መጀመሪያ ተናባቢ ድምፅ፣ onset |
| ከናፍራዊነት፣ | የከናፍር ያልሆነ ድምፅ ወደ ከናፍር ድምፅነት እንዲለወጥ የሚያደርግ ሂደት፣ labialization |
| ከበት፣ | ከንፈርን የመከበብ ሁኔታ፣ ለምሳሌ ሙሉ ስንል ከንፈራችን ክብ ይሆናል፣ rounding |
| አሀድ፣ | አንድ አካል፣ unit |

አለሳላሽ፣ — አንድ ነገር ለሰለሰና ረጋ ባለ ሁኔታ የሚፈፀም መሆኑን የሚያመለክት ቅርፅ ለምሳሌ፣ ከፈት፣ ለቀቅ፣ ወዘተ፣ attenuative

አላች፣ — የሚያልት፣ አሉ ወይም ሀሰት የሚል፣ negator

አምድ፣ — ቅጣይ ምዕላድ ሊያስከትል ወይም ሊያስቀድም የሚችል ቅርፅ፣ ለምሳሌ ውርደት የሚለውን ስም ብንመለከት፣ ውርድ ከሚለውና /-ኧት/ ከሚለው መስራች ምዕላድ የተፈጠረ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ውርድ የሚለው አምድ ሲሆን /-ኧት/ ቅጣይ ምዕላድ ነው፡፡ stem

አሰላሳይ፡ — የሚያሰላስል፡ የሚያስተውል፡ speculator, thinker

አሰተጋቢ፡ — ሞቅ - ደመቅ ብሎ የሚሰማ፡ ጎርናና፡ sonorant, sonorous

አሻቃቢ፣ — ከዝቅተኛ ወይም መሀከለኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሚወጣ ቅላፄ፣ rising intonation

አቃፊ፡ — አንድን አረፍተ ነገር አቅፎ በውስጡ የሚይዝ፡ matrix

አቆልቋዩ፣ — ከከፍተኛ ወይም መሀከለኛ ደረጃ ወደ ዝቅተኛ ደረጃ የሚወርድ ቅላፄ፣ falling intonation

አቆራኝ — ሁለት ነገሮችን የሚያያይዝ፡ የሚያቆራኝ፡ copular

አበላላጭ፣ — ሁለት ነገሮች የሚበላለጡ መሆናቸውን የሚገልፅ፣ ለምሳሌ፣ ከካሳ ይልቅ አስቴር ረዥም ነች፤ ስንል ይልቅ የሚለው አበላላጭ ምዕላድ ነው፡፡ comparative

አታች፣ — የሚያትት፣ ሀተታ የሚሰጥ፣ declarative

አንድምታ፣ — አንድ ነገር ሲነገር ወይም ሲፃፍ፣ በቀጥታ ሳይሆን፣ በተዘዋዋሪ የሚሰጠው ወይም ሊሰጥ የሚችለው ተጨማሪ ፍች ወይም መልዕክት፣ implication

አንጓዋ፣ — መለያያ ቦታ፣ መንታ መንገድ፣ አንድ መዋቅር ወደ ሁለት ወይም ወደ ሶስት ክፍሎች የሚከፈልበት ቦታ፣ node

አደላዳይ፣ — ሁለት ነገሮች እኩል መሆናቸውን የሚያሳይ ምዕላድ፣ ለምሳሌ ካሳ እንደ አባቱ ረዥም ነው፤ ስንል፣ ካሳ እና አባቱ እኩልረዥም መሆናቸውን እንገልፃለን፡፡ እንደ የሚለው አደላዳይ ምዕላድ ነው፡፡ positive or equative

አገናዛቢ፣ — ባለገንዘብን ወ/ይም ባለድርጊትን የሚያመለክት ምዕላድ፣ ለምሳሌ፣ካሳ ቤቱ ተቃጠለበት ወይም ካሳ መሄዱ ተሰማ ስንል፣በመጀመሪያው ምሳሌ፣ /-ኡ/ የሚለው ምዕላድ ካሳ የቤቱ ባለቤት መሆኑን ያሳያል፡፡ በሁለተኛው ምሳሌ

| | |
|---|---|
| | ደግሞ ይኸው /-ኡ/ ካሳ የመሄድ ተግባሪ ፈፃሚ ወይም ሂያጅ መሆኑን ያመለክታል፡፡ genitive |
| አጎላማሽ፣ | የሚያሳድግ፣ የሚያጎላምስ፣ ለምሳሌ ተውሳከ ግሶችና ቅፅሎች፣ modifier |
| አጎላባች | የሚያጎለብት፣ የሚያጎላ፣ augmentative |
| አጉዋዳኝ፣ | በጉዋድ፣ በጉዋድ የሚከፋፍል፣ someone and Co. |
| አይረቤ፣ | ቅጣይ እየጨመረ የማይረባ መሆን ቃል፣ unproductive |
| አውደ-ነገር፣ | አንድ አረፍተ ነገር የሚነገርበት ሁኔታ፣ context |
| አጠንካሪ፣ | አንድ ነገር በጠንከረ፣ በከረረ ሁኔታ የሚፈፀም መሆኑን የሚያመለክት፣ ለምሳሌ፣<br>ካሳ በሩን ክፍት አደረገው፣<br>ለንል፣ቤቱ በሀይልና በድንገት መከፈቱን እንገልፃለን፡፡ intensive |
| አዛማጅ፣ | የሚያዛምድ የሚያገናኝ፣ relative |
| አፀፋ፣ | አንድን ነገር የሚጠቅስ ወይም የሚያመለክት ምዕላድ፣ ለምሳሌ የባለቤት አፀፋ፣ reflexive |
| አፅንዖት፣ | በጉልህ፣ በጥንካሬ፣ የሚወጣ ወይም የሚነገር፣ emphatic, focused |
| ኢሀላፊ፣ | ያላለፈ ወይም ያልተፈፀመ ድርጊት፣ non-past |
| ኢሳቢ፣ | የማይስብ፣ ተሳቢ የማይፈልግ፣ intransitive |
| ኢሰዋዊ፣ | ሰው ነክ ያልሆነ፣ ለምሳሌ፣ ካሳ እንደተቀየመ ግልፅ ነው፤ ለንል፣ ግልፅ ነው የሚለው ግላዊ ሀረግ ባለቤት እሱ የሚለው ሰዋዊ ተውላጠ ስም ሳይሆን፣ it የሚለው ኢሰዋዊ ተውላጠ ስም ነው፡፡ በአማርኛ ይህ ተዋላጠ ስም ድምፅ የለውም፣ በአፀፋ ብቻ ይጠቀሳል፡፡ impersonal |
| ኢርቱዕ፣ | ቀጥተኛ ያልሆነ፣ indirect |
| ኢቀለማይ፣ | ብቻውን ቀለም ሊመሰርት የማይችል ድምፅ፣ ለምሳሌ ተናባቢ ድምፅ፣ non-syllabic |
| ኢነዛሪ፣ | የማይነዝር፣ ማንቁርት ውስጥ የሚገኙት ጅማቶች በማይርገበገቡበት ጊዜ የሚፈጠር ድምፅ፣ voiceless |
| ኢድምፀት፣ | አንድ ነዛሪ የሆነ ድምፅ ወደ ኢነዛሪ ድምፅነት የሚለወጥበት ሂደት፣ devoicing |
| እሰር፣ | ነፃ ያልሆነ፣ ብቻውን የማይቆም፣ ምሳሌ፣ ውፍር-፣ ድፍር-፣ ወዘተ፣ bound |
| እግድ፣ | አየር ታግዶ በአንድ ጊዜ ሲለቀቅ የሚፈጠር ድምፅ፣ stop / plosive |
| አሌት፣ | አሌ፣ ወይም ሀሰት የማለት ሂደት፣ negation |
| አልት፣ | ሀሰት የተባለ ነገር፣ negated |

| | |
|---|---|
| ድላንቃ፣ | በድድና በላንቃ መካከል የሚገኘውን ቦታ ለመሰየም፣ ድድ እና ላንቃ ከሚሉት ቃላት የተፈጠር አጭር ቃል፣ alveopalatal |
| ድምፅ-የለሽ፣ | ሊባል፣ በአንደበት ሲነገር የማይችል ምዕላድ፣ ለምሳሌ ካሳ ጠጅ መጠጣት ያዘወትራል፣ በሚለው ውስጥ፣ ጠጅ መጠጣት የሚለው ሀረግ ባለቤት፣ ድምፅ የለሽ ነው፡፡ በትርጉሙ ካሳ ከሚለው ስም ጋር አንድ ነው፡፡ ካሳ የሚለው ስም ግን ያዘወትራል የሚለው ግስ ባለቤት ነው፡፡ empty |
| ድምፀት፣ | ነዛሪ ድምፆች የሚፈጠሩበት ሂደት፣ voicing |
| ድርሳን፣ | ስለ አንድ ነገር የሚሰጥ አስተያየት፣ comment |
| ድህረ-ገብ፣ | በቃል መድረሻ ላይ ተናባቢን ተከትሎ የሚገባ አናባቢ፣ syncope |
| ድንጋሬ፣ | መደናገር፣ ግራ መጋባት፣ ድንጋጤ በሚለው ቃል አምሳያ የተፈጠረ፣ confusion |
| ዱካ፣ | አንድ ነገር ቦታውን ሲለቅ የሚተወው ምልክት፣ trace |
| የተፀውዖ ስም፣ | የአንድ ሰው የግል መጠሪያ የሆነ ቃል፣ proper noun |
| ጠቋሚ፣ | አንድን ነገር ከሚገኝበት ቦታ ወይም ጊዜ አኳያ ከሌሎች ለይቶ የሚያመለክት፣ deictic |
| ጥበበ-ነገር፣ | ዕውቀት፣ ስለማንኛውም ነገር ያለን ግንዛቤ፣ cognition |
| ጥብቅ፣ | ሲነበብ ምላሰን ጫን የማድረግ ባሀሪ ያለው ድምፅ፣ geminate |
| ጥመራ፣ | ቃል ከቃል እየተቀናጀ ጥምር ቃል የሚፈጥርበት ሂደት፣ compounding |
| ጥምር፣ | በጥመራ የሚፈጠር ቃል፣ ሀረግ ወይም አረፍተ ነገር፣ compound |
| ጥቋምነት፣ | የመጠቆም ወይም ተለይቶ የመታወቅ ሁኔታ፣ indexicality |
| ጨራሽ | የቀለም የመጨረሻ ተናባቢ ድምፅ፣ coda |
| ፅንሰ-ቃላት፣ | ገና ያልተወለደ፣ ያልተመሰረተ ቃል፣ potential word |
| ፍትግ፣ | የድምፅ መውጫ ቀዳዳ ሲጠብና አየር ሲፋተግ የሚፈጠር ድምፅ፣ fricative |
| ፍግድ፣ | እየተፋተገና እየታገደ የሚወጣ ድምፅ፣ ቃሉ ፍትግ እና እግድ ከሚሉት ቃላት ተቀናጅቶና ተጎርዶ የወጣ ነው፡፡ affricate |
| ፎኒም፣ | ትርጉም ለይ፣ ማለትም በሁለት ቃላት መካከል ለሚከሰት የትርጉም ልዩነት ምክንያት የሚሆን ድምፅ፣ phoneme |

# ዋቢ


መንግሥቱ ለማ፣ 1963፣ የአማርኛ ግጥም አይነቱ፣ ሥረቱ፣ ሥርዓቱ፣ *የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት፣* ቅፅ 1፣ ቁ. 1፣ (*133-149*)፡፡

በዕምነት ገብረ አምላክ፣ 1947፣ *የአንድ ቋንቋ አድገት - አማርኛ እንዴት እንደ ተስፋፋ፣* አዲስ አባባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ባየ ይማም፣ 1984፣ ስርዓተ ፅህፈት፣ *ውይይት፣* የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ማህበር መፅሄት፣ መጀመሪያ ቅፅ፣ (17-41)፡፡

ባየ ይማም፣ 1987፣ *የአማርኛ ሰዋሰው፣* አዲስ አበባ፣ የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ማተሚያ ቤት፡፡

ባየ ይማምና ቲም 89፣ 1989፣ ፊደል አንደገና፣ *የኢትዮጵያ የቋዋንቋዋና ሰነ ፅሁፍ መፅሄት፣* ቅፅ 7፣ (1-23)፡፡

ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወ.መ. 1959፣ *አማርኛ ቅኔ፣* አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ብላታ መርስዔ ህዘን ወልደ ቂርቆስ፣ 1948፣ *የአማርኛ ሰዋሰው፣*(4ኛ ዕትም) አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ፣ 2000፣ ምጣኔ በአማርኛ ስነ ግጥም፣ በተሾመ ይመር አበባው፣ "የአማርኛ ግጥም አይነቶች" *የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት፣* ቅፅ 33፣ ቁ. 1፣ (67-103)፡፡

ተክለ ማርያም ፋንታዬ፣ 1944፣ *ሆሄተ ጥበብ ዘሰነ ፅሁፍ፣* አዲስ አበባ፣ ትንሳዔ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፡፡

ተሾመ ይመር አበባው፣ 1997፣ የአማርኛ ግጥም አይነቶች፣ *የኢትዮጵያ ጥናት መፅሄት፣* ቅፅ 30፣ ቁ. 1፣ (89-118)፡፡

ደረጀ ገብሬ፣ 1975፣ ምት በስነ ግጥም ውስጥ፣ የኢትዮጵያ ቋዋንቋዎችና ስነ - ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ድማፅ፡፡

ጌታሁን አማረ፣1990፣ *የአማርኛ ሰዋሰው በቀላል አቀራረብ፣* አዲስ አበባ፡ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

Abraham Demoz. 1968. Amharic for Modern Use. *Journal of Ethiopian Studies*. 2:1, (15-30).

----------and Haylu Fulass. 1970. The Adjectival and the Näw Clauses in Amharic *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies*, II, (81-87). Addis Ababa, Haile Selassie I University.

Aday Abebe. 1987. The Role of the Ethiopian Revolution in the Development of Amharic Vocabulary. BA thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.

Afeworq G.J. 1905. *Grammatica della Lingua Amarica*. Rome.

Alemayehu Haile. 1987. An Autosegmental Approach to Amharic Intonation. PhD thesis, School of Oriental and African Studies, University of London.

---------.1988. Lexical Stress in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies*, 20, (19-43).

---------.1990 An Autosegmental Approach to Some Amharic Declarative and Interrogative Contours. *Proceedings of the First National Conference of Ethiopian Studies*, (449-460). Addis Ababa University.

---------1991. The Morphological Structure of the Imperative Stem in Amharic. *The Ethiopian Journal of Education*, XII:1, (62-76).

---------1995.Is Syllabic Weight Distinction Relevant for Amharic Stress? *Journal of Ethiopian Studies, XXVIII:2, (15-25)*

Appleyard, D. 1972. A- and As- verb forms in Amharic. *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, 35, (18-26).

Armbruster, C.H. 1908. *Initia Amharica, Part I, Grammar*. Cambridge: University Press.

Aster Taddese. 1981.The Syllable Structure of Amharic. BA Thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.

Ayele Bekerie. 1997. *Ethiopic፡ an African Writing System, its History and Principles*, Lawrenceville, NJ: The Red Sea Press.

Bach, E. 1970. Is Amharic an SOV Language? *Journal of Ethiopian Studies*, VIII, (9-20).

Baye Yimam. 1988(a). Towards a Definition of Nominal Specifiers in Amharic. In: Taddese Beyene, (ed), *Proceedings of the Eight International Conference of Ethiopian Studies*, (599-613). Addis Ababa University.

---------1990. Raising in Amharic. *Langue Orientale Ancienne de Philologie et de Linguistique*, 2:1, (231-256).

---------1994. Unaccusative Structures in Amharic. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1238-1253). New Jersey: Red Sea Press.

---------1996. Definiteness in Amharic Discourse. *Journal of African Languages and Linguistics*, 17, (47-83).

---------1997. The Verb to Have in Amharic. In: Fukui, K. et al, (eds.), *Ethiopia in Broader Perspective: Proceedings of the Thirteenth International Conference of Ethiopian Studies*, (619-638). Kyoyo, Japan.

---------1999(a). The Verb to Say in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies*, XXXII: 1, (1-50).

---------1999 (b) .Root Extension and Reduction in Amharic. *Ethiopian Journal of Language and Literature*, 9 , (56-88)

--------- 2004. Agreement Phenomena in Amharic. In Verena Böl et al. *Studia Aetiopica. In Honour of Siegbert Uhlig on the Occasion of his 65th birthday*, (319-337) Wiesbaden: Harrassowitz Verlag.

.......... 2006. The morphosyntactic properties of the form *bīčč* in Amharic. In: Siegberg Uhlig (ed.) *Proceedings of the 15th International conference of Ethiopian Studies.* (715-26) Wiesbaden: Harrassowitz Verlag

---------2006. The Interaction of Tense, Aspect, Agreement in Amharic Syntax. In: John Mugane et al (eds.), Selected Proceedings of the 35th Annual Conference of African Linguistics. Somerville, MA.: Cascadilla Proceedings Project, (193-202), www.lingref.com, document #1309

---------(in progress) The Structure of DP in Ethiopian Semitic: Amharic.

Bender, M.L. 1974. Amharic Verbal Types from Text to Lexicon. *Folia Orientalia,* 15 (23-46).

-------- et al. 1976. The Amharic Language. In : Bender et al (ed) *Language in Ethiopia.* London: Oxford University Press. (77-98)

--------- 1983. The Origin of Amharic. *Journal of the Institute of Language Studies.* Addis Ababa University, 1:1, (14-52).

Benneth, M.E. 1978. Stratificational Approach to Amharic Phonology. MA thesis, Michigan State University.

Beza Tesfaw. 1997. Causativization in Amharic. MA Thesis, School of Graduate Studies, Addis Ababa University.

Bliese, L. 1979. Constraints on Clitics in Amharic. *Folia Orientalia,* (113-142).

-------- 1988. A Discourse Analysis of Amharic Narratives. In: Taddese Beyene (ed) *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies,* (613-621), Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

Cohen, M. 1970 (2nd Edition). *Traite de Langue Amharic.* Paris: Institut d'Ethnolgie.

Cotterell, F.B. 1964. Amharic Word Classes. *Journal of Ethiopian Studies,* II:1, (11-33).

-------- 1966. The Amharic Primary Neutral Sentence. *Journal of Ethiopian Studies,* IV:2, (33-48).

-------- 1973. Control in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies,* 7:1, (75-106).

Cowley, R. 1969. A and B Verbal Stem Types in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies.* VII:1 (1-33)

---------. 1976. The Standardisation of Amharic Spelling. *Journal of Ethiopian Studies,* V:2, (1-18)

Dawkins, C.H. 1960. *The Fundamentals of Amharic.* Addis Ababa: Sudan Interior Mission.

Degif Petros Banksira. 2000. *Sound Mutations, the Morphophonology of Chaha.* Philadelphia/Amsterdam: John Benjamins Publishing Company.

Demissie Manahlot. 1977. Nominal Clauses in Amharic. PhD Dissertation, Georgetown University.

-------- 1988. On Amharic Performative Verbs. In:Taddese Beyene (ed) *Proceedings of the Eighth International conference of Ethiopian Studies* (623-629). Institute of Ethiopian Studies.

Demeke, G. Awigichew. 2000. The Structure of IP in Amharic. A paper presented at the 14th International Conference of Ethiopian Studies, Addis Ababa University

----------2001. N-Final Relative Clauses in Amharic. Studia Linguistica, vol.55 :2, (192-216)

----------2004. The Clause Structure of Ethiopian Semitic. PhD Dissertation, University of Tromso.

Ehret, Christopher. 1988. Social Transformation in the Early History of the Horn of Africa: Linguistic Clues to Development of the Period 500 B.C. to AD 500. In: Taddese Beyene (ed.) *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*.Vol. 1, (639-651), Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

Ferguson, C. 1976. The Ethiopian Language Area. In: Bender, et al, (eds.), *Language in Ethiopia.* Oxford University Press, (64-76).

Gasser, M. 1985. Amharic –m and –ss, Morphology, Theme and Assumed Knowledge. *Lingua.* 65:1/2, (56-106).

Getachew Haile. 1967. Demonstrative Pronouns in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies,* V, (9-12).

---------1971. The Suffix Pronouns in Amharic. *Papers in African Linguistics*, (101-111).

---------1972. The Copula naw in Amharic. *Proceedings of the Fourth international Conference of Ethiopian Studies,* (139-154). Rome,

---------1970. Archaic Amharic Forms. *Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies,* II, (61-80), Institute of Ethiopian Studies, Haile Selassie I University.

Getahun Amare. 1995. Baye Yimam: yamariñña säwasäw (Amharic Grammar), *Journal of Ethiopian Studies*, XXVIII:2, (51-60).

Girma Halefom. 1992. An Initial Wh-filter in Amharic. *Journal of Ethiopian Languages and Literature*, 2, (75-94).

--------- 1994. The Morphologically "Incomplete" Agreement Paradigms in Amharic. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1249-1260). New Jersey: Red Sea Press.

---------1994. The Syntax of Functional Categories: A Case Study of Amharic. PhD Dissertation, Montreal, Universite Du Quebec a Montreal.

Girmay Berhane. 1992. Word Formation in Amharic. *Journal of Ethiopian Languages and Literature*, 2, (50-74)

Goldenberg, G. 1964. On the Amharic Tense System. *Proceedings of the Second International Conference of Ethiopian Studies,* (47-49). Manchester.

--------- 1965. Studies in Amharic Syntax. *Journal of Ethiopian Studies*, III:1 (6-22).

Habte Mariam Marcos. 1973. Regional Variation in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies.* Vol. XI:1, (113-129)

Hartmann, J. 1980. *Amharishe Grammatik.* Wiesbaden: Franz Steiner Verlag.

Haylu Fulass. 1964. Derived Nominal Patterns in Amharic. PhD Thesis, UCLA.

-------- 1967. The Particle yä in Amharic. *Rassegna di studi etiopici*, 20, (103-119).

-------- 1968. Notes on the Verbal Noun and Possession Markers. *Journal of Ethiopian Studies*, 6:2, (71-76).

-------- 1972. A Pseudo-object Construction in Amharic. *Proceedings of the Fourth International Conference of Ethiopian Studies*, (115-125). Rome.

-------- 1972. Relative Clause in Amharic. *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, 35, (497-515).

-------- 1980. On Imperatives in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies*, XIV, (87-96).

-------- and Bender, M.L. 1978. *Amharic Verb Morphology*. East Lansing: Michigan State University, African Studies Center.

-------- Getachew Haile, and Roger Cowley. 1976. Dialect Variation in Amharic. In: Bender et al, (eds.), *Language in Ethiopia*. London: Oxford University Press, (90-99).

Hayward, R.J. (n.d.) The High Central Vowel in Amharic: New Approaches to an Old Problem. In: Fishman, J. (ed), *From Phonology to Society*, (301-325).

--------1991. A Propos Pattern of Lexicalization in the Ethiopian Language Area. *Afrikanstische Arbeitspapiere*.

Hebo, P. A. 1955. *Grammatica Amharica*. Asmara: Scuola Tipografica Francescana.

Hetzron, R. 1966. Pronominalization in Amharic. *Journal of Semitic Studies*, 2:1, (71-76).

--------1970. Towardss an Amharic Case Grammar. *Studies in African Linguistics*, 1:3, (304-354).

--------1972. Ethiopian Semitic: Studies in Classification. *Journal of Semitic Studies*, Monograph No 2., Manchester University.

Hodson, A. and C.H. Walker. 1922. *An Elementary and Practical Grammar of the Oromo Language*. London: Society for Promoting Christian Knowledge.

Hudson, G. 1972. Why Amharic is not a VOS Language. *Studies in African Linguistics*, 3.

--------1978. Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Prehistory. *Language Miscelanea*. Institute of Ethiopian Studies.

-------- 1981. Evidence of the Nominal Origin of the Perfect in Amharic. In: Segert, Stanislav, (ed). *Ethiopian Studies*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz.

-------- 1985. The Principled Grammar of Amharic Verb Stems. *Journal of African Languages and Linguistics*, 7:1, (39-58).

Isenberg, W.C. 1842. *Grammar of the Amharic Language*. London: Church Missionary Society.

Kapeliuk, O. 1969. Auxiliaires en amharique. *Proceedings of the Six international Conference of Semitic Studies*, 1-16. Jerusalem.

-------- 1978. Particles of Concatenation and Reference in Amharic. *Bulletin of the School of Oriental and African Studies*, 14, (272-282).

-------- 1980. Pseudo Questions in Amharic. *Proceedings of the Six International conference of Ethiopian Studies*, (337-341). Tel-Aviv.

--------1984. Semantic Analysis of Some Morphological Phenomena. In: Taddese Beyene (ed). *Proceedings of the Eighth International conference of Ethiopian Studies*, (697-703). Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.
-------- 1988 *Nominalization in Amharic*. Wiesbaden: Franz Steiner Verlag.
--------1994. The Evolution of ïrswo and ïrsaččäw as Sociolinguistic Variants. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1270-1281). New Jersey: Red Sea Press.
-------- 1994. *The Syntax of the Noun in Amharic*. Wiesbaden: Harrassowitz Verlag
Leslau, W. 1945. The Influence of Cushitic on the Semitic Languages of Ethiopia. A Problem of Substratum. *Word*, 5:1, (59-82).
-------- 1964. Toward a History of Amharic Vocabulary. *Journal of Ethiopian Studies*, II:2, (12-20).
-------- 1968. *An Amharic Conversation Book*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz
-------- 1995. *A Reference Grammar of Amharic*. Wiesbaden: Otto Harrassowitz
Levine, D. 1974. *Greater Ethiopia*. University of Chicago Press.
Lykowska, L. 1993. Sentence Schemata for Amharic. University of Warsaw.
Mantel-Niecko, J. 1971. Palatograms of Sounds of Amharic. *Africana Bulletin*, 15, (23-41).
Messelech Melkie. 1985. Interrogative Sentences in Amharic. BA Thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.
Meseret Teshome. 1985. The Verb Phrase in Amharic. BA Thesis, Department of Linguistics, Addis Ababa University.
Mullen, D.S. 1986. Issues in the Morphology and Phonology of Amharic: The Lexical Generation of Pronominal Clitics. PhD. Thesis, University of Ottawa.
Mulugeta Seyoum .2001. The Syllable Structure and Syllabification in Amharic. MPhil. Thesis, Norwegian University of Science and Technology.
Podolsky, B. 1977. Morphophonology of Amharic Verb. *Proceedings of the Fifth International Conference of Ethiopian Studies*, (91-96) Nice.
-------- 1980. The System of Verbal Stems in Amharic. *Proceedings of the Six International Conference of Ethiopian Studies*, (447-454). Tel Aviv.
-------- 1982. Some Problems in the Phonology and Morphology of Amharic. *Proceedings of the Seventh International Conference of Ethiopian Studies*, (17-18). Lund.
Polacek. Z. Functional Sentence Perspectives in Amharic, Preliminary Notes. In: Taddese Beyene, (ed). *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*, (567-572). Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.
-------- 1994. Several Notes on Amharic Syntactically – formed Adjectives. In: Harold Marcus, (ed), *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1282-1293). New Jersey: Red Sea Press.
Richter, R.1984. On the Enrichment and Expansion of the Amharic Scientific Vocabulary. In: Taddese Beyene, (ed). *Proceedings of the Eighth International Conference of*

*Ethiopian Studies,* (567-572). Institute of Ethiopian Studies, Addis Ababa University.

---------1994. Lexicographical Notes on Amharic.In: Harold Marcus, (ed). *New Trends in Ethiopian Studies: Papers From the 12th International Conference of Ethiopian Studies*, (1294-1301). New Jersey: Red Sea Press.

--------- 1997.Some Linguistic Peculiarities of Old Amharic Texts. In: Fukui, K. et al, (eds.). *Ethiopia in Broader Perspective: Proceedings of the Thirteenth International Conference of Ethiopian Studies,* (543-551). Kyoto, Japan.

Taddese Beyene. 1972. Aspects of the Verb in Amharic. PhD thesis, Georgetown University.

-------- 1980. Notes on Two Process Verbs in Amharic. *Journal of Ethiopian Studies,* 14, (123-129).

-------- 1989. Terms of Endearment in Amharic, Their Morphological Structures and Sociolinguistic Norms. *Journal of Ethiopian Studies,* XXII, (65-75).

Taddese Tamrat. 1972. *Church and State in Ethiopia 1270-1527.* London: Oxford University Press.

--------- 1988. Ethnic Interaction and Integration in Ethiopian History: The Case of Gafat, *Journal of Ethiopian Studies,* XXI, (121-144).

Takkele Taddese. 1992. Are t' and s' Variants of an Amharic Variable: A Sociolinguistic Analysis. *Journal of Ethiopian Languages and Literature*. No2, (103-121).

Titov, E. 1976. The Amharic Language. Moscow: NAUKA

Ullendorff, E. 1955. *The Semitic Languages of Ethiopia: a Comparative Phonology.* London: Tylor's Foreign Press.

Vassilevich, A. 1988. Colour Terms in Amharic. *Proceedings of the Ninth International Conference of Ethiopian Studies*, (142-148). Moscow

Voigt, R. 1980. The Amharic First Order Vowel. In: Serget, Stanislav (ed). *Ethiopian Studies: Dedicated to Wolf Leslau*, (142-148). Wiesbaden:

Wedekind, K. 1992. Which Form Predicts all Others Best? Variations on the Amharic Verb Theme. *Journal of Ethiopian Studies*, XXV, (73-92).

Zavdskaya, E. P. 1988. A Propos the Expression of Causation Category in the Amharic Language. *Proceedings of the Ninth international Conference of Ethiopian Studies,* (157-164). Moscow.